ሰርቫንቲስ

ዶን ኪሾት

ክፍል አንድ

በሚካኤል ደ ሰርቫንቲስ ሳቬንድራ
1547—1616

ከእስፓንኛ ወደ እንግሊዘኛ
ከሳሙኤል ፑትናም

ከእግሊዝኛ ወደ አማርኛ
አስፋው ተፈራ ወ/መስቀል

ግንቦት 1977

የመጽሐፉ ቴክኒክ ይዘት

—የኮፒመጠን 20 ሲሰሮ
—የቁመቱ መጠን 30 ሲ.ሜ.ር
—የፊደሉ መጠን ልክ 10 ኮር
—የቃላት ብዛት (ግ) 72,272
—የገጽመት ብዛት 10,000 ኮፒ

አሳታሚ ፤ አስፋው ተፈራ ወ/መስቀል

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ሴንትራል ማተሚያ ቤት
የሥራ ትዕዛዝ ቁ. 3586/1977
የታተመበት ፤ አዲስ አበባ
ግንቦት 1977

አ ር እ ስ ት

ገጽ

1. ለልዑል የቪሾር መስፍን የተጻፈ ደብዳቤ 5
2. የደራሲው የሕይወት ታሪክ 7
3. ምዕራፍ 1 ስለ ስመ ጥር ከበርቱ..... 16
4. ምዕራፍ 2 ብልሃተኛው ዶን ኪሾት 27
5. ምዕራፍ 3 ዶን ኪሾት የተካነ ፈረሰኛ..... 42
6. ምዕራፍ 4 ፈረሰኛችን ሆቴሉን ለቆ ከወጣ በኋላ በመንገዱ ላይ..... 54
7. ምዕራፍ 5 ፈረሰኛችን ላይ የደረሰው መውደቅ.. 66
8. ምዕራፍ 6 ቁስና ጠጉር ቆራጩ 75
9. ምዕራፍ 7 ጐበዙ ፈረሰኛችን..... 87
10. ምዕራፍ 8 ጀግናው ዶን ኪሾት ከሚያስፈሩት የነፋስ ወፍጮዎች ጋር ያደረገው 97
11. ምዕራፍ 9 የማንቻው ጀግናና ጐበዙ ቢስካሊያዊ የተሳለፉበት 112
12. ምዕራፍ 10 በዶን ኪሾትና በጋሻ ጃግሬው በሳንቾ ፓንቻ 121
13. ምዕራፍ 11 በዶን ኪሾትና በፍየል አርቢዎች የደረሰው ሁኔታ 130
14. ምዕራፍ 12 አንደኛው ፍየል አርቢ ከዶን ኪሾት ጋር 144
15. ምዕራፍ 13 የአረኖይቱ ማርቼላ ታሪክ 153
16. ምዕራፍ 14 የሚቹ አረኛ የጂሮስቶሞስ የብስጭት ግጥም 170

17. ምዕራፍ 15 ዶን ኪሾት እርሀራሄ ከሌላቸው ያንዳ
ሶች ጋር 191

18. ምዕራፍ 16 ብልሁ መኳንን ፈረሰኛው ዶን
ኪሾት እሱ የመስፍን ግንብ ብሎ ከሰ
የመው ሆቴል ውስጥ 204

19. ምዕራፍ 17 ቆፍጣናው ዶን ኪሾት 217

20. ምዕራፍ 18 በጌትየው በዶን ኪሾትና በጋሻ ጃግ
ሬው በሳንቾ ፓንቻ መካከል የተደረገ
ውን አስደሳች ንግግር 233

21. ምዕራፍ 19 ዶን ኪሾት ከጋሻ ጃግሬው ጋር
በጨለማ ሲጓዝ ካንድ ሬሳ ጋር ተገ
ናኝቶ ያከናወነው ግጥሚያ 252

22. ምዕራፍ 20 በስመ ጥሩነታቸው በመላው ዓለም
ላይ የገነኑት ዙዋሪ ፈረሰኞች 267

ለልዑል ጌታዬ የቪሾር መስፍን

የጂብራሌዎን ማርኪዝ ፣ የቤናልካዛርና የባናሬስ ካውንት ፣ የአልኮሰር አውራጃ ቪስ ካውንት ፣ የካፒላ—የኩሪዮል—የቡርጌሎስ ከተማዎች ጋታ ጌታ

ልዑል ጌታዬ ሆይ !

ብልህና አስተዋይ ልዑል እንደመሆንዎ መጠን ማናቸውንም ዓይነት ሥነ ጽሑፍ በቅን አስተያየት እየገመቱ ለመዘከርነት ለመቀበል እጅግ የሚወዱንና የሚፈቅዱ መሆንዎን አጣርቼ ስለማውቅ ፣ ይህን የብልህነትንና የጥሩ ስሜትን ጥበብ የሚገልጥ በተለይም እነዚያ በትውልዳቸው መሠረት ጨዋነት እየተመኩ ለተራ ጥቅም ዝቅ ብለው ማገልገልን ከታላቅ ውርደት የሚቆጥሩት ልበ ኩሩ ሰዎች የተከተሉትን የሕይወት ጉዳና የሚያብራራ ልብ ወለድ ድርሰት አዘጋጅቼ ለሕዝብ ለማበርከት በጋለ ትጋት ደክሜ ያጠናቀቅሁትን «የባለሞያው መኳንን የማንቻው ዶን ኪሾትን» የሕይወት ታሪክ በልዑልነትዎ ከፍተኛ ጠባቂነት ሥር ለማሳተም ቁርጥ ሀሳብ አደረግሁኝ ።

ይህን ያህል ተብሎ ለማይገመተው ለልዑልነትዎ ታላቅ ሰውነት የሚገባውን የላቀ ክበሬታ እየሰጠሁ ፣ የልዑልነትዎ መልካም ፈቃድ ሆኖ መጽሐፉን በጥቢታው ሥር እንዲቀበሉኝ እፈትዎ ተንበርክኬ ልመናዬን በፍጹም ትሕትና አቀርባለሁ ።

ይህም መጽሐፍ በልፁልነትዎ ጥላ ሥር የተጠበቀ እንደ ሆነ ምንም እንኳ በታላላቆቹ ጠቢባን ደራሲዎች ዘንድ የሚዘጋጁት ከፍተኛ ድርሰቶች ሁሉ የሚጐናጸፉትን ዓይነት እጅግ ብርቅና ድንቅ የሆኑትን የለዛ ማጌጫዎችና የመምህርነት ቃላት ያልተጐናጸፈ ደሀ መሆኑን ባውቅ የድንቁርናቸውን ወሰን ሳያክ ብሩ ጥሰው እያለፉ በሴሎቹ ድካም የተዘጋጀውን ድርሰት ለመን ቀፍና ለማኳስስ ሲሉ በከረረ ጥላቻና በታወረ አስተያየት እየ ወነጀሉ ሊያጠፉት ከሚነሱት ተንኰለኞች ሊድን ስለሚችል ፣ በዚሁ መጽሐፍ ላይ ጥፋት አይተናል በማለት በምቀኝነት መን

ፈስ እየዶለቱ አስመስለው ለማሳመን አንዳንድ ሐሳዊ መስካሪ ዎች የሚያቀርቡትን ሐሰተኛ ሰበብ በመቃወም ልዑልነትዎ እርግጠኛና ቁርጠኛ በሆነ ፍርድ ጋሻና ጠበቃ ሆነው ጠላቶቹን እንዲከላከሉለት በልዑልነትዎ ተማጥኜአለሁ ።

ስለዚህ የልዑልነትዎ ልበ ብሩህነትና አስተዋይነት የኔን መልካም ስሜት በቅን አስተያየት እንደሚገምተው ብርቱ እምነት ስላለኝ ይህችን አነስተኛ ስጦታ የማበረክተው በአነስተኛ ነቷ ቅር እንዳማይሰኙ ፍጹም እርግጠኛ ሆኜ ነው ።

የልዑልነትዎ ፍጹም ታማኝ አገልጋይ
ሚካኤል ዲ ሰርቫንቲስ ሳቬንድራ

መግቢያ

በደራሲው ሕይወት ዙሪያ የተገኘ አጭር ታሪክ

ሚካኤል ሰርቫንቲስ ሳቬንድራ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በጥቅምት ወር 1547 ዓ.ም. አልካላ ዲ ሔናሬስ ከሚባል አገር ሀብት ከሌላቸው ከምግባረ መልካም ቤተሰብ ወገን ተወለደ ። እርሱ እራሱ እንደተረከው ከልጅነቱ ዕድሜው ጀምሮ መንፈሱን ወደ ቅኔ ትምህርት ማዘንበሉን ብቻ ይገልጻል ፣ ከዚህ በስተቀር በጐልማሳነቱ ዘመን ያሳለፈውን ሁኔታ የሚገልጽ አንድም የታሪክ ምንጭ አልተገኘም ።

የመጀመሪያ ትምህርቱን በሳላማንካ ዩኒቨርሲቲ ካስመረቀ በኋላ ቀጥሎ በ1568 ዓ.ም. ወደ ግድሪድ ተዛውሮ ሲማር ከብፁዕ ካርዲናል አኳቪቫ ጋር ተዋወቀ ። ብፁዕነታቸውም የወጣቱን ብልህነትና ንቃት ተመልክተው ፍቅራቸውን አሳደሩበት ።

ሚካኤል ከብፁዕነታቸው ጋር መተዋወቁን ከታላቅ ዕድል ስለቆጠረው ምኞቱን ለመፈጸም ሲል በእልፍኝ አሽከርነት ደንብ አድሮላቸው ተከትሎአቸው ወደ ሮም ለመሄድ ቁርጥ አሳብ አደረገ ። ይህን የመሰለው የአገልግሎት ደንብ በንድ የቤተክህነት ወራሹ መንበር ዘንድ እንደማናቸውም ተራ አሽከርነት የሚቆጠር ሥራ አልነበረምና ሚካኤል ከብፁዕነታቸው ጋር በቆየበት ጊዜያት ማናቸውም መልካም አያያዝና ባለሟልነት አልተጓደለበትም ነበር ። ይልቁንም በዚያን ዘመን በእስፓኒያ አገር በአናኗራቸው እጅግ ተግደርዳሪ ከነበሩት የጨዋ ልጆች ዛሬ በዘመኑ መለወጥ የተነሳ የጥንት ክብራቸውን አጥተው ድህነት ከተጫናቸው ወገኖች የርምን ከተማ ጥንታዊ ታሪክና ውበት ለመጐብኘትና እንዲሁም የተፈጥሮ ስጦታቸውን በትምህርት ለማሻሻል ከሚመኙት ወጣቶች መካከል አንደኛው ሚካኤል ስለነበረ የጀመረውን ትምህርት አቋርጦ ወደ ሮም ለመሄድ በመነሳቱ ቅር አልተሰኘም ነበር ። ሮምም በሚገኝበት ጊዜ እንደተመለከተው ተሰፋው የተመሠረተበት የወደፊት ምኞቱ

የትንቢት ታላቅነቱን የሚያረጋግጥለት አለመሆኑን ከቀን ወደ ቀን እየተረዳው ስለሄደ ከዕለት ምኞት በስተቀር ዘላቂ የሆነ ሞያ ሊይዝ አለመቻሉን በመረዳት ብፀዕነታቸውን አንድ ዓመት ያህል ካለገላቸው በኋላ ተሰናብቶ ተለያቸው ።

በዚያን ዘመን በአውሮፓ አገር የነበረው የሰላም ሁኔታ የሚ ተማመንበት ባለመሆኑና በተለይም ደግሞ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ትልቅ ጦርነት እንደሚነሳ ታምኖ ሽብርና ግርግር በበረከተበት በእስፓኒያ ግዛት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ተፈላጊ የነበረውና በቀላሉም ሥራ ለማግኘት የሚችለው የጦር መሣሪያ ታጥቆ የሚንቦራደድ ጉልማሳ በመሆኑ በዘመኑ ብርቅ በነበረው በወታ ደርነት ፍቅር እየተነፋፉ የማናቸውም ወጣት ፍላጐት እንደሚ ያደላው ሁሉ ሚካኤልም መሣሪያ የመጨበጥን እድል ስለመ ረጠ በመንግሥቱ ጦር ሠራዊት ውስጥ ተመልምሎ በተራ ወታ ደርነት ተቀጠረ ።

በጥቅምት 7 ቀን 1570 ዓ.ም. የቱርክ መንግሥትና የክርስቲ ያን ነገሥታት ስለሃይማኖት ነጻነት ባደረጉት ጦርነት የመስ ቀል ምልክት የሚያደርጉት የክርስቲያን ሕብረት ወታደሮች በቱርክ ሠራዊት ላይ ያገኙትን ድል አድራጊነት ስናስታውስ በዚያን ጊዜ ሚካኤልም በሌምፓንቶ የመርከብ ተዋጊ ጦር ክፍል ተሰልፎ በታላቅ ጀግንነት እንደተዋጋ ትዝ ይለናል ። ውጊ ያው እንደተፋፋመ ወዲያውኑ ሚካኤል በወባ ተነድፎ በጠና ትኩሳት ስለታመመ ይህንኑ የሻምበል አዛዡ አይቶ ወደ መታከሚያ ክፍል ተዛውሮ ከሌሎች በሽተኞች ጋር እንዲታ ከም አጥብቆ መክሮት ነበር ። እርሱ ግን ተኝቶ መታከሙን ከሰ ንፍና ስለቆጠረው የሕመሙን ቀላልነት በማስረዳት እንዲህ ሲል ለአለቃው መለሰለት ይባላል ።

«ሻምበሌ ሆይ! በዚህ የጦር ሜዳ የተሠማራሁ ሕዝብ ለአ ናት አገሩና ለሃይማኖቱ ነጻነት ፥ እንዲሁም ለንጉሡ ክብር ሲል እራሱን መስዋዕት ለማድረግ በቆራጥነት መነፈስ ከንዱን እን ስቶ በሚራኩትበት ጊዜ እኔ ሳልሞት በብርድ ልብስ ተጠቅ ልዬ እዚህ ሥፍራ መገኘቴ የምመኘውን ክብር አያሰጠኝም ።

እንዲያውም ከጦርነቱ ፍጻሜ በኋላ ስለሚካኤል ሕይወት ታሪክ አንዳንድ ነገር በተጠየቀ ጊዜ የሚሰጠውን መልስ እኔው እራሴ በሕይወት ሳለሁ ሠርቼ መቆየት ይገባኛል» ብሎ ተናገረ ።

ጦርነቱ እያደር እየበረታ ስለሄደ ሚካኤል እንደምኞቱ በውጊያው ውስጥ ገብቶ በሰሰት አረር ተመትቶ እስኪቆስል ድረስ የተሰጠውን ቦታ ሳይለቅ ጠላቶቹን በሚያስደንቅ ጀግን ነት ለማጥቃት ችሏል ። አቆሳሰሉም ባንድ እርሳስ ከግራ ክንዱ ላይ ፥ በሁለት እርሳስ ከጡት ሥሩ በላይ ስለነበረ የደረቱ ቁስል በሕክምና ሲድን የክንዱ ቁስል እያመረቀዘ ጤና የሚነሳው መሆኑ በሐኪም ምርመራ ከተረጋገጠ በኋላ እንዲቆረጥ ስለተ ደረገ በዚሁ ጠንቅ የግራው ክንዱ ጉምድ ሆኖ ለመቅረት በቃ።

ይህ የተቆረጠው እጁ ስላላ ሆኖ ከዳነለት በኋላ በጦር ሜዳ ላይ ለፈጸመው የጀግንነት ሞያ አንዳች ውለታ ሳይደረግ ለት እንደገና በገዛ ፈቃዱ ወደ ቀድሞው ጦር ክፍሉ ተመልሶ አገልግሎቱን ቀጠለ ።

በ1575 ዓ.ም. ላይ ደግሞ ወደ ሌላ የጦር ግንባር ዘምቶ የሚያከራ ጀብዱ ሠርቷል ። ይህም ውጊያ እንደተፈጸመ ወዲ ያውኑ አገራቸው ለመግባት የሚፈልጉት ወታደሮች ሁሉ በተራ እየተጸፉ ፈቃድ እንዲያገኙ የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ ስላስታወቀ ፥ ሚካኤል የተወለደበትን አገር ለማየት አጥብቆ የሚናፍቅ ነበ ርና በአለቃው አሳሳቢነት በመጀመሪያው መርከብ ለመሳፈር ጠይቆ የቅድሚያ እድል ለማግኘት ቻለ ። ከዚያም በኋላ ለመነሻ በተ ወሰነው ቀን በቀጥታ ወደ ተወለደበት አገር በሚያደርሰው መር ከብ ተሣፍሮ በሚጓዝበት ጊዜ ባለመታደል በዚሁ መርከብ ላይ ድንገተኛ የባሕር ወንበዴ አደጋ ወደቀበት ። ይህም አደጋ ሊደ ርስ የቻለው ጥንት የአስፓኒያ መንግሥት ኃይል ደክሞ አረ ቦች በበረቱበት ዘመን ከአስፓኒያ አውራጃዎች አብዛኛውን ክፍል በኃይል ወረው ሕዝቡን አስገብረው አገሩን ይገዙ ከነበ ሩት የጥቁር አረቦች ወገን የሆነ አርናውቴ ማሚ የሚባል የባ ሕር ወንበዴ ተነስቶ በተሳላፊ መርከቦች ላይ አደጋ አየጣለ ተሳፋሪዎችን በመማረክና ሃብታቸውን በመዝረፍ አምዶ ይኖር

ነበርና ሚካኤልና ጓደኞቹ የተሳፈሩበት መርከብ እንዲጋጣሚ ከመንበዴው መርከብ ጋር ድንገተኛ ግጭት በመገናኘቱ የተለመ ደውን እደጋ ጥሎ ተሣፋሪዎችን በብርቱ በውጊያ አጣዳፋቸው ፤ እነዚያም በጦርነት የተንገላቱ ሰዎች ስለሆኑ ጠላቶቻቸውን በተ ኩስ ጉልበት ለማጥቃት ወይም ለመመከት የማይችሉ በመሆና ቸው ተስፋ በሌለው ሞናቸ ለጥቂት ጊዜ ከተከላከሉ በኋላ በመ ጨረሻው ተሸንፈው ከመርከባቸው ተማረኩ ። በፍጅቱ መካከል አብዛኞዎቹ ሰዎች ለመትረፍ ተስፋ በመቁረጥ ከመርከብ እየዘ ለሉ ወደ ባሕሩ ጠልቀው ቀሩ ። አንዳንዶቹ ደግሞ በጨበጣ ሲዋጉ ሕይወታቸውን ሠው ። ከሞት የተረፉት ግን እሻቸውን ስለሰጡ በሰንሰለት እየተቋራኙ ወደ አልጄር ግዛት ተሸግረው ለባርነት ተሸጡ ።

ያልታደለው ሚካኤል ከምርኮኞቹ አንዱ ስለነበረ በአረ መኔዎች እጅ ጉበቶ እምስት ዓመት ሙሉ በሞካኔ አገዛዝ ተጨ ቁኖ ሲንገላታ ኖረ ። ከዕለታት አንድ ቀን እነዚያን አብረው የተማረኩትን ጓደኞቹን በምክር አበራትቶ በርሱ መሪነት ለማ ሸፈትና በድንገት በሚያነሱት ሽብር እርዳታ በባርነት የሚሰ ቃዩትን ክርስቲያናቶች በሙሉ አንቀሳቅሶ በገዥዎቻቸው ላይ እን ዲያምጹ ለማድረግና ዘወትር ሁከት በማንሳት አሰልችተው ነጻ እንዲወጡ በማለት ወሰን በሌለው ቆራጥነት ሙከራ አደረገ ። ነገር ግን ከሐሳቡ ጋር የተባበሩት ጥቂት ሰዎች ሆነው ስለተ ገኙ ሙከራውን እንደምኞቱ ዳር ለማድረስ አልቀናውም ነበር ። እንዲያውም በክህደት መንፈስ የተመረዙ አንዳንድ ጓደኞቹ ይህን ከባድ የሽፍትነት አድማ እንዲሠሩ በምክር የሚያበረታታ ቸውና የሚመራቸው ሚካኤል መሆኑን ምስጢር አውጥተው በጠላቶቹ ፊት ስለአጋለጡት በዚህ ጥፋት ምክንያት እጁ ተይዞ ከወህኒ ቤት እንዲታሠር ተደረገ ። ሆኖም በጓደኞቹ ከሐዲነት ምክንያት የደረሰበት ይህ አሳዛኝ መሰናክል ስለነጻነቱ ፍቅር በልቡ የተሠረፀውን ጽኑ ተስፋ ለመደምሰስ የሚችል አልነበረ ምና እንደገና ትግሉን ለመቀጠል ሲል በማይታመን ድፍረት ከወህኒ ቤት ስብሮ ለማምለጥ ሲችል እነዚያን ከሐዲያን ጓደኞ ቹን እዚያው ተዋቸው ።

ውሎ አድሮ የማምለጡ ወሬ በተሰማ ጊዜ ይህ አስጊ የሆ ነው የሚካኤል ልበ ቆራጥነትና ድፍረት ሐሰን አጋ የሚባለ ውን ጨካኝ የአልጄር ባላባት ስለአሰጋው ሙከራው የሚናቅ አለመሆኑን በመገመት ከወህኒ ቤት ማምለጡን ሕዝቡ እንዲ ያውቅና ለፍለጋውም እንዲተጋ በማለት እጁን ይዞ ለሚያመጣ ለት ሰው ከፍ ያለ ሹመትና ሽልማት የሚሰጥ መሆኑን በአዋጅ አስነገረ ።

ይህ አዋጅ ከታወጀ በኋላ ስለሚካኤል መፈለግና መከበብ የየአውራጃው ኬላዎችና የየግዛቱ ወሰኖች በብርቱ እንዲጠበቁ ተደረገ ። ኮብላዩ ሚካኤል ምንም እንኳ ውስጡን በማያውቀው አገር ተደብቆ ማምለጥ ተአምር ከመሥራት የሚቆጠር መሆ ኑን ቢረዳውም የነጻነቱ ፍቅር እያጽናናው እጁን ለጠላቶቹ ከመ ስጠት ይልቅ በሚያመልጥበት መንገድ ላይ ሕይወቱ እንዲያ ልፍ መርጠ ሽሽቱን አጠነከረ ።

የአዋጁ ቃል በየባላገሩ ጆሮ በደረሰ ጊዜ ሹመትና ገንዘብ ለማግኘት የጓጉት ሰዎች ሁሉ ያለረፍት ፍለጋቸውን ስለአጠነ ከሩ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በብዙ ድካምና ብርበራ በጠቋሚ መሪ ነት ካንድ ባላገር ቤት ተገኘ ። ወዲያው እጁ ተያዘና ሕይወቱ እንደተከበረ ወደ ባላባቱ ችሎት ቀረበ ። ነገር ግን ይህን የሚያ ህል ጥፋት ሠርቶ ቢገኝም ዕድሉ አግዞት በጥብቅ እንዲታሠር ከመደረጉ በቀር በሞት እንዲቀጣ አልፈረዱበትም ነበር ።

ከዚህም በቀር እንደገና ተመልሶ አሥር ቤት ከገባ ወዲህ ለውጭ ሰዎች በሚነካው ስብከቱ አማካይነት የአልጄር ግዛት ዋና ከተማ ለእስፓኒያ መንግሥት ተገዥ እንዲሆን ለማድረግ ሲል በባርነት የሚሰቃዩትን ክርስቲያን ሕዝቦች በባላባቶቹ ላይ አስነሰቶ ለማዋጋት አቅዶ የክርስቲያን ሕብረት ጦር እንዲቋ ቋም በምስጢር ሲያሴር ተገኝቶ ነበር ። ይህንንም አድርጐ ቢያ ገኙትም ጠላቶቹ ስላልጨከኑበት ሕይወቱን ቆጥበውለታል ።

ዘወትር በሚካኤል ላይ የሚታየው ይህ ያለመገዛት ጠን ካራ መንፈስ በጣም እያሰጋ ስለሄደ አረመኔው የአልጄር ገዥ ይህን እጅ ጐራዳ ሰው ከመግደል ይልቅ በገንዘብ ገዝቶ እጅ

ማግባት የተሻለ መሆኑን ስለመረጠ የአምስት መቶ ወቄት ወርቅ ጌታ ነበርና ዋጋውን ለመጀመሪያ ጌታው ለእርናውቴ ማሚ እጅ በጅ ከፍሎ በባርነት ገዛው ።

ይህን የመሰለ የመከራ ቀንበር በሚካኤል ሜንቃ ላይ መው ደቁን የሰርቫንቲስ ቤተሰቦች ስለሰሙ እርሱን ከባርነት ነጻ ለማ ውጣት የሚከፈል የመጀ ገንዘብ መራር በሆነ ችግር ማጠራቀም ጀመሩ ። በዚያኑ ዘመን ሚካኤል ስለርሱና ስለክርስቲያን ወገ ኖቹ ነጻነት የሚያደርገው ትግል ዘወትር መሰናክል እያገኘው ተዳክሞ ነበርና በትግሉ መክሸፍ የተቆረቆሩት የእስፓኒያ ሕዝ ቦች እነዚያን በአልጄር ግዛት ውስጥ በባርነት የሚገዙትን ክር ስቲያናት በሚቻላቸው መንገድ ነጻ ለማውጣት የሚረዳቸውን ዘዴ ለመፈለግ ሲሉ ተሰብስበው ከተማከሩ በኋላ«የቅድስት ሥላሴ መነኰሳት ማኅበር» የተባለ አንድ ሚሲዮን በሕዝቡ መዋጮና ዕርዳታ አቋቋሙ ።

የሰርቫንቲስ ቤተሰቦች በተለይ ለወጀ ያጠራቀሙትን ገን ዘብ ለልጃቸው ነጻነት ዋጋ እንዲከፈል ለሚሲዮን አለቃ አስረ ከቡና ወዲያውኑ በግንቦት ወር 1580 ዓ. ም. ላይ ሚሲዮናው ያኖቹ አልጄር ግዛት ገብተው ስለባሪያ ነጻነት የሚደረገውን የመግባቢያ ውል መነጋገር ጀመሩ ። አረመኔው ሐሰን አጋ ግን የውሉን ሐሳብ ሲቀበል በተለይ ሚካኤልን ነጻ ለመልቀቅ የጠየ ቀው ገንዘብ የገዛበትን እጥፍ ስለሆነ እሱን ነጻ ለማውጣት ያጋጠመ ችግር የማይዘለቅ መስሎ ነበር ። ነገር ግን መቸም የማይቀር ዕዳ በመሆኑ አባ ጀል የሚባሉት የሚሲዮን አለቃ በጉዳዩ ከተጨነቁበት በኋላ ከግኅበሩ ስንቅ ላይ አምስት መቶ ወቄት ወርቅ ጨምረው ከብዙ ልመና ጋር አንድ ሺህ ወቄት ወርቅ ከፍለው ባላባቱን ለማስደሰት ቻሉ ።

እንዳጋጣሚ የዚያኑ ዕለት ሚካኤል ወደ ቱርክ አገር ተሻ ግሮ ለመሸጥ ከሌሎች ጋር በሰንሰለት ተቆራኝቶ ወደ ኩስታ ንቲኖፕል ለመጓዝ ተዘጋጅቶ ከወደቡ ላይ ከሚገኘው መርከብ ውስጥ ተግፍሮ ስለነበረ ዋጋው ከተከፈለ በኋላ ከሌሎቹ እሥ ረኞች መጨረሻ ወርዶ እጁ ለሚሲዮኑ አለቃ ተሰጠ ።

ከዚያ ወዲህ አገሩ ገብቶ ከቤተሰቦቹ ጋር ተቀላቅሎ ሲኖር የአሮጮች ዘመቻ በተደረገ ጊዜ እንደገና በሶስተኛው ክፍለ ጦር ውስጥ አባል ሆኖ እስከ 1583 ዓ. ም. ድረስ በወታደርነት አገ ልግሏል ። በ1584 ዓ. ም. ካቴሪና ፖላቼዎስ ኢ. ሳላዛር የምት ባል ትውልዱ ከጫዋ ወገን ሆኖ በአኗኗሯ እንደ ተራ ሰው ደህ የሆ ነች ልጅ አግብቶ ትዳር ከያዘ በኋላ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የወታ ደርነት ተግባሩን አቋርጦ መተዳደሪያውን በጽሕፈት ሥራ ላይ መሠረተ ።

ለመጀመሪያ ጊዜ «ጋላቴያ» (የመልካም አሰተዳደግ ምክር) ብሎ የሰየመውን የእረኞች የተረት መጽሐፍ ጻፈ ። ከሱም ቀጥሎ በሰው ልጅ ላይ የሚታየውን ጉልህ ስህተትና እንዲሁም ልማ ድን በመከተል የሚደርስበት የድንቁርና እምነት ሁሉ ለሥል ጣኔና ለአእምሮ እድገት ጠንቀኛ ደዌ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ፤ ከተፈጥሮ ስጦታ ፈልቀው የተዘጋጁ ፤ ብሩህ የሆነ የሐሳብ አገ ላለጥ ያላቸው አያሌ መጻሕፍት ጽፎ ነበር ። ነገር ግን በዘመኑ ቤተ መጻሕፍት ባለመጠበቃቸው የተነሳ ሁሉም በጊዜ ብዛት እየባከኑ ጠፍተዋል ።

ሚካኤል ሰርቫንቲስ በጽሕፈት ሥራ ተወስኖ ሲኖር ብዕሩ ማለት የጸሐፊነት ሞያው ኑሮውን የሚደግፍበት በቂ ጥቅም የማ ያፈራለት መሆኑን ስለተረዳው ይህን ሥራ ትቶ ሌላ የተሻለ ጥቅም የሚገኝበት ሥራ መፈለግ ግዴታ ሆነበት ። ስለዚህ ያለ ፈውን የወታደርነት አገልግሎቱን በማስታወስ የሥራ ጥያቄ ማመልከቻውን ለባለሥልጣኖቹ ቢያቀርብ ለጊዜው ሊሰጡት የቻሉት ሥራ በመርከብ ወደ ሲቪሊያ ለሚመላለሱት ለሕንድ ነጋዴዎች ወጭ ሸቀጥ ማቅረብና ገቢ የንግድ ዕቃ መቆጣጠር ነበር ። ይህም ሥራ ወዲያው በ1592 ዓ. ም. ግድም ስለቆመ ወደ ማዘጋጃ ቤት ተዛውሮ ። ከሕዝብ ጥቅም ገቢና ከሥራ ማኅ በር ቀረጥ በመቀበል ሥራ ተቀጥሮ ከቀድሞው ደረጃው ቁል ቁል ወርዶ ተገኘ ። ይህንንም ሥራ ለጥቂት ጊዜ ከሠራ በኋላ በብስጭት ምክንያት ትቶ ወደ እንዳሉሲያ ሄዶ ተቀመጠ ። እዚ ያም በነበረበት ሰሞን እጅግ የጣመና የተመሰገነ ልዩ ልዩ የተ ረትና የምሳሌ መጽሐፍ ጽፎ ለሕዝብ አበረከተ ።

በ1595 ና በ1603 ዓ. ም. መካከል በነበረው ዕድሜው አልፎ አልፎ ያጻረጣቸውን የድርሰት ጅምሮች ማናቸውም በዘመኑ የታወቁና ስማቸው የተጠራ ደራሲያን በብዙ ጥንቃቄና አገባብ ቢደክመበትም እንደባለቤቱ አሳክተው ለማጠናቀቅ አልሆነላቸውም ነበር ።

ስለደራሲው ሕይወት ታሪክ ለጊዜው ጫፍ ይዞ ለማውራት የሚቻለው እነዚያን ዓመታት በማንቻ ወረዳ ውስጥ ተቀምጦ ሳለ ኑሮውን በብዙ ችግርና መጉላላት ማሳለፉን ብቻ ነው ። እንዲሁም አርጋማሲላ ዴ አልባ በሚባለው በዚሁ አውራጃ ዋና ከተማ ውስጥ ጠላት በወንጀል ከሶ አሳስሮት ነበር ። ይህም የቆየ ቂም ለመበቀል በደባ ያሳሰሩት መሆኑ ታውቋል። ነገር ግን የእሥራቱ ምክንያት እያደር እንደተገለጠው ክብሩን የሚነካ ጥፋት ሆኖ አልተገኘም ።

«ዶን ኪሾት» ብሎ የሰየመውን ይህን አስደናቂ ጥውም የሆነ ልበ ወለድ ታሪክ መጻፍ የጀመረውና ሥራውንም በታላቅ ትጋት የቀጠለው በዚያን ጊዜ ወህኒ ቤት ታሥሮ ሳለ ምቹ የዕረፍትና የፀጥታ ጊዜ ስለአገኘ ነው ፤ እሱም እራሱ ስለዚህ ታሪክ መዋጣት ሲናገር «ይህን መጽሐፍ የወለደው ወህኒ ቤት ነው» ብሏል። የደራሲነት ችሎታውን መታወቂያ የሆነው የዚሁ መጽሐፍ የመጀመሪያ ጥራዝ በ1605 ዓ. ም. ላይ ታትሞ ለሕዝብ ታደለ።

የሚካኤል ሐሳብ የነበረውን በዚያን ዘመን የእስፓኒያ መኳንንት ዙሪያ ፈረሰኛ እየሆኑ አገር ለአገር እየዞሩ የሚያሳዩትን ከንቱነትና ወግ አጥባቂነት ፣ እንዲሁም ስለ ፈረሰኛነት ተጣባር ያላቸውን ታላቅ ትክታ በመንቀፍ ፣ በመንፈሳቸው የታተመውን ቅጥ የለሽ መራቀቅና የፈረሰኛነት ባለታሪክ የመሆን ምኞታቸውን በማኰሰስ አንድ በግጥም ቤት የተዘጋጀ አስታከ የሚነካ ድርሰት ለማውጣት ነበር ። ነገር ግን ለዚህ በታሪክ አገባብ ለተጻፈው ድርሰቱ የላቀ ግምት ስለተሰጠው የደራሲውን ስምና ዝና እስካለንበት ትውልድ ደረስ አቆይቶ ሕያው አድርጐ ታል ። መጽሐፉም በሕዝብ ስሜት ላይ ከልክ ያለፈ የደስታ ሽብር አስነስቶ ነበር ። ስለሆነም ደራሲውን ከከባድ የችግር ኑሮ ሊያወጣው ስላልቻለ ሕይወቱን በሙሉ በድህነት ውስጥ አሳለፈ ።

ከዚህ ሌላ ደግሞ በእስተያየት ርቀት ከመጀመሪያው መጽሐፍ ያላነሰ ሁለተኛ መጽሐፍ አሳትሞ ለማውጣት ሥራውን ጀምሮ ሳለ«ዴ አቤላንዳ» በሚባል የሐሰት ስም የሚጠራ አንድ ሸረኛ ጸሐፊ በሰርቫንቲስ ላይ በቅናት ተነሰቶ ዛቻና ነቀፌታ የመላበት መጽሐፍ በዚያው አርእስት አሰመስሎ ጽፎ አሳትሞ ለሕዝቡ ነዛው ። ሚካኤልም በዚህ በተሠራበት ተንኰል ስለተከፋና እጅግ ስለአዘነ ነገሩ እልህ አሳድሮበት ሁለተኛውን ጥራዝ ለማሳተም ተጣደፈና ወዲያው በ1615 ዓ. ም. መጀመሪያ ላይ ታትሞ እንዲወጣ አደረገ ።

እርሱ በሕዝቡ ዘንድ እንደፈላስፋና እንደ ንጹህ ክርስቲያን መገመቱን ያውቅ ነበርና ጊዜ ሞቱ መቃረቡን አስታውሶ ለመጪው ጊዜ ታሪኩ ተሰናድቶ ለማለፍ ሲል ጅምሩን አጠናቀቀና በቶሎ ለፍጻሜ አደረሰው ።

ኢድሮፒሲያ (በውስጥ አካል ውስጥ እንደ ውሀ ተቋጥሮ ደዌ የሚሆን በሽታ) ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ያሰቃየው ስለነበረ ። በዚሁ ጠንቅ በሚያዝያ 23 ቀን 1616 ዓ. ም. ማድሪድ ላይ አርፎ አስከሬኑ ኢዛቤላ የምትባለው ሴት ልጁ የምንኩስና ቆብ ከጫነችበት ገዳም ከሥላሰ ደናግላን ቤተ ክርስቲያን ጓሮ ተቀበረ። በ1633 ዓ. ም. እነዚህ ደናግል ወደ ሌላ ገዳም ሲዛወሩ የሚካኤል አጽም ከሌሎች ከብዙኃን ሙታኖች አጽም ጋር ተቀላቅሎ እንዳይላከር በማለት ልጅቱ ከዚያ መቃብር አስወጥታ ወደሌላ የመቃብር ቅጽር በክብር ሥፍራ አኖረችው ።

ሚካኤል ሰርቫንቲስ በሕይወቱ ላለ ያልታወቀ አልባሌ ሰው ሆኖ ይኖር ነበር ። ከሞተም በኋላ ካንድ መቶ ዓመት ይበልጥ ስሙ ተረስቶ ነበር ዛሬ ግን እውቀትና ሥልጣኔ እየተስፋፋ በሄደበት ዘመን የደራሲነቱ ሙያው በእስፓኒያ ብቻ ሳይሆን በድፍን ዓለም ስሙና ዝናው እየገነነ ስለሄደ እስከ ዛሬ ድረስ ታላቅ ክብር ሰጥቶት ለወገኖቹ መመኪያ አድርጐት ይኖራል።

ምዕራፍ 1

ስመ ጥር ከበርቴ የማንቻው ዶን ኪሾት ታሪክ

ስመ ጥር ዶን ኪሾት ማን እንደነበረና ምን እንደሠራ ይተረካል

በማንቻ ወረዳ ዋና ከተማ ባንደኛው መንደር (ለጊዜው የመንደሩን ትክክለኛ ስም ላስታውሰው አልቻልኩም) በጣም ረጅም ዘመን አልሆነውም ፣ አንድ የእስፓኒያ ከበርቴ ይኖር ነበር ። ይህም ከበርቴ ከነዚያ አሮጌውን ልማድ አጥብቀው ከሚከተሉትና ጣምራ ጦር በረጅም ዛቢያ ላይ ሰክተው ከሚይዙት የጥንት ክብ ጋሻ ከሚያነግቡት ፣ ከሲታ ፈረስ ላይ ተቀምጠው አዳኝ ውሻ ከሚያስከትሉት አንዱ ነበር ።

በወጥ ቤቱም ውስጥ ለምግብ ማብሰያና ማሰናጃ አንድ ድስት ነበረው ። በዚህም ድስት ውስጥ ከሙክት ሥጋ ይልቅ አብዛኛውን ጊዜ የጥጃ ብርንዶ ከድብላ ፍራፍሬ ጋር ተቀይጦ የሚቀቀልበት ነበር ። ቅቅሉም ከቀዘቀቀ በኋላ ተከትርና ልሞ ለእራት ይቀርብለታል ። ለዓርብ የጾም ምግብ ፣ ለቅዳሚት የምስር ሾርባ ፣ ለአሁድ የእርግብ ወጥ የዘወትር ምግቡ ስለሆነ ከዕለት ገቢው ሶስቱን እጅ የሚያወጣው ለማዕድ ቤቱ ጉዳይ ነበር። ከዚህ የሚተርፈውን ገንዘብ ግን በበዐላት ቀን የሚለብሰው ክምርጥ የሱፍ ጨርቅ የተሰፋ የክት ኩትና እንዲሁም ከጥሩ የሐር ጨርቅ የተሰፋ ሱሪ ፣ ከሱሪው ዓይነት ጨርቅ የተሠራ የቤት ለቤት ጫማ ከዚህ ሌላ ደግሞ በአዘቦቱና በሥራ ቀን የሚለበሰው የጨዋ ልብስ ከወፍራም መናኛ የሱፍ ጨርቅ የተሠራ የሸርክ ኩትና ሱሪ ለመግዣ ያወጣ ነበር ።

በቤቱም ውስጥ ቤተሰቦቹ ሆነው የሚያገለግሉት ሶስት ረዳቶች ነበሩት ። ከነዚህም አንደኛይቱ የቤቱ አስተዳዳሪ የሆነች ዕድሜዋ ከአርባ ዓመት የሚያልፋት አሮጊትና እንዲሁም ሁለተ

ተኛይቱ የወንድሙ ልጅ የሆነች ሃያ ዓመት ያልሞላት ልጃገረድ ፥ ሶስተኛው ደግሞ ዋናው ሥራው ፈረስ ለጓሚ ሆኖ የጓሮ አትክልት የሚኰተኩትና ሽንጉ የሚያጸዳ ፥ አንዳንዴም ወደገበያ የሚላላክ አሽከር ነበር ።

የኛው ከበርቴ ግን እድሜው የጠና ፥ ሰውነቱ የጠገገ ፥ የፊቱ ወዝ የተመጠጠ ፥ ቁመቱ የረዘመ ፥ በግምት ወደ አምሳ ዓመት የሚጠጋው ብርቱ ሽማግሌ ነበር ። በዚህም እድሜው ላይ አውሬ ማደን በጣም የሚወድ ስለነበረ ንቁህ ማላጅና የተመሰገነ አዳኝ ነበር ። ዘወትር ማለዳ እየተነሳ የአውሬ ሥጋ እያደነ ቅርብ ጐረቤቶቹን መጋበዝ ስላስለመደ ሁሉም በጣም ይወዱትና ያከብሩት ነበር ። የከበርቴው ዋና መተዳደሪያው ከርስቱ ላይ የሚገባለትን የሰብል ሽያጭ እያጠራቀመ ስለሆነ ይህንኑ ለኑሮው መተዳደሪያ በቁጠባ እያወጣ ርስቱን እያሳረሰ የሥጋ አውሬውን እያደነ ፥ በነፋሻ የገጠር ቤቱ ከቤተሰቦቹ ጋር በሰላ ምና በደስታ ይኖር ነበር ።

የዕለት ተግባሩን ሲፈጽም ውሎ የተለመደውን ዕረፍት በሚያደርግበት ሰዓት በእንግዳ ቤቱ ውስጥ በሥርዓት የተደረደሩትን ልዩ ልዩ የታሪክ መጻሕፍት በማንበብ ይወሰን ነበር። ከእነዚህም መጻሕፍት ውስጥ አብዛኛዎቹ በቀድሞ ዘመን ያሰሩትን ዙዋሪ ፈረሰኞች ሞያና ጀግንነት ለማወደስ ከየዘመኑ ደራሲያን የተጻፈ ስለሆነ ከሚያነባቸው መጻሕፍት ውስጥ በተለይ ስለ ፈረሰኞች ዜና የሚናገሩትን ይመርጥ ነበር ። ስለዚህ የዕረፍት ጊዜውን ሳይቆጥብ ቀንና ማታ ማለት ዓመቱን በሙሉ የፈረሰኞቹን ታሪክ የሚያንግሠውን መጽሐፍ እየመረጠ በታላቅ ትጋትና በማይሰለች ጣዕም በመመርመርና በማመንዠክ ውሎ ያድር ነበር ። አዘውትሮ ከማንበቡም የተነሣ የታሪኩ ፍቅር በልቡ ስለተመሰጠ ያንን የሚወደውን አደን ማቋረጥና የንብረቱንም አስተዳደር ችላ ማለት እያደር ይታይበት ጀመር። የታሪኩ ፍቅር በጊዜ ብዛት ስለተወሐደው በፈረሰኞቹ ተግባርና ሞያ ልቦናው ፈጽሞ ስመማረክ በቃ ።

እንዲያውም ይህ የዘወተረ ንባብ የወሬ ጉጉነት ስሜቱን እያጋለበት ስለሄደ የፈረሰኛነቱ ታሪክ ጠቀስ የሆኑትን መጻሕ

ፍት ለመግዣያ ገንዘብ ቢያንሰው ከርስቱ ዋጋ የሚያወጣውን መርጦ ብዙ የእርሻ መሬት ሸጠና የታሪኩን ተከታታይ ጥራዝና ሌላም ሊያገኝ የቻለውን ሁሉ በውድ ዋጋ እየገዛ በመጻሕፍት ቤቱ ውስጥ አከማች ። ከገዛቸውም መጻሕፍት መካከል በጣም ጥሩ መስሎ የታየው የስመጥሩው ፈልቺያኖ ዴ ሲልቫ ታሪክ የተጻፈበትን ነበር ። ምክንያቱም በዚህ መጻሕፍት ውስጥ የተገለጠው አስተያየት ጥልቅ ከመሆኑ የተነሣ የግጥሙ አሰባበር ፥ የቃላት አገባብና ያነጋገሩ ስውር ምሥጢርነት እጅግ የሚያስደንቅ ሆኖ ስለታየው ነው ። በተለይም በመጽሐፉ ውስጥ አልፎ አልፎ ተጽፎ የሚገኘውን የፍቅር ደብዳቤ የዛቻ ፉከራ፡ ባነበበ ጊዜ አድናቆቱ እየገነነ ይሄድ ነበር ። ተጽፎ የሚገኘውም ቃላት ቀጥሎ ያለው ነው ። ከሐሳባዊ በደለኛ የቀረበው ማስመሰያ ምክንያት ከኔው እውነተኛ ምክንያት ጋር ቢገናኝ እኔ የነበረኝን እውነትና ምክንያት በብርቱ መርህ፡ አመንምኖ ገደለው ። በዚህም አኳኋን ስለውበትሽ ያለኝን አድናቆት እንዳልገልጽ ምክንያቴን ጨቁኖ ብስጭት ላይ ጣለኝ» ።ወይም ደግሞ «ከፍ ያላችሁት ስማያት ሆይ ስለመለኮታዊነታችሁ መለኮት ነት በግርማ እንድትአጌጡ በከዋክብት የተከበባችሁ ሆናችኋል፡ እንዲሁም ለታላቅነታችሁ ዋጋና ውለታ ይሆን ዘንድ አክሊልና የጸጋ እረድኤት እንደሚገባችሁ ታውቋል» የሚል ነበር ።

ሚስኪኑ ፈረሰኛ በዚህ አነጋገር ልቡ ተነክቶ አእምሮውን ስለአጣ የምሥጢሩን ፍች ስነጣዋሮ ለመረዳት ሲል ሴሊቲን በሙሉ ሲያወጣና ሲያወርድ በሃሣብ እንደተወጠረ ያድር ነበር። ዳሩ ግን የዚህን እንቆቅልሽ ምሥጢር እንኳንስ እሱ ገና ግን በብ የጀመረው ቀርቶ ለዚሁ ሲል ፈላስፋው አሪስቶትል ከመ ቃብር ቢነሣም ሊፈታው የሚችል አልነበረም ።

ከዚህም በስተቀር በታሪኩ ላይ እንደሚነበበው ዶን ቤሊያኒጂ በግጥሚያ ላይ የሚሰጠውና የሚቀበለው ምት በጣም የልብ የሚያደርስ ሆኖ አላገኘውም ነበር ። ምክንያቱም በሕክምናቸው የጠነቱትን ወጌሻዎች የቴን ያህል ብለሃተኞች ቢሆንም እንኳ በተዋጊነቱ ብዛት አካላቱና ፊቱ ሁሉ በጎደኒሳና በጥብሳት ምልክት የተሸሞረሞረ ሳይሆን አይቀርም በማለት የሰውነቱን እት

ራት ባይነ ህሊናው ያስተውል ስለነበረ ነው ። ይህም ሆኖ ታሪኩን የጻፈው ደራሲ ህልቆ የሌለውን የግጥሚያ ሁኔታ በመዘርዘር ገና ማስረዳቱን የሚቀጥል መሆኑን ላንባቢያን ተስፋ ስጥቶ ለመጽሐፉ ዕልባት ያደረገበትን አኳኋን በመመልከት ልባዊ ምሥጋናውን ለደራሲው ከማቅረብ አይቆጠብም ነበር ። አንዳንዴም የታሪኩ መቀጠል የሚዘገይ እየመሰለው ከመቸኰል የተነሣ ብዙ ጊዜ ብዕሩን እያነሳ እርሱ እራሱ እየደረሰ በታላቅ ትክክልነት አሚልቶ ለመጨረስ ይቃጣው ነበር ። ይህንንም ለማድረግ እንደማያቅተው እራሱን ይተማመን ስለነበረ ሌሎች ከፍ ያሉና ሳያቋርጡ የሚደነቁ እንዳይጀምር ባያከላክሉት ኖሮ በር ግጥ ሲያደርገው እንደሚችልና እንደማይሳነውም የታወቀ ነበር ። ከመንደሩም ቄስ ጋር በተገናኙ ቁጥር (በሲንጓሳ ደብር የተካኑ ሊቅ ሰው ነበሩና ከመሐይምነት ደረጃ የሚሻል በጣም ዝቅ ያለ የፊደል መቁጠሪያ ትም/ቤት ስለሆነ በዚህ ጠባብ ደብር የተካነ ሊቅ ሲባል ማፌዣያ ነው ።) ከነዚህ በፈረሰኞች ታሪክ ላይ ስማቸው ከተጠቀሰው ከብሪታኒያው ፖልሜሪኖ፡ ወይም ከጋውላው አማዲስ ማነኛቸው በጀግንነት የላቁ ፈረሰኞች እንደነበሩ ለማበላለጥ በስፊው ይከራከሩ ነበር ። ዳሩ ግን የኔታ ኒኮላ የሚባለው የዚያው የመንደራቸው ጠጉር ቆራጭ ጣልቃ እየገባ«ማንም ቢሆን የፌቦን ፈረሰኛ የሚያህል አይገኝም» በማለት ፡ «ምናልባት ተወዳዳሪ ይፈለግለት ቢባል እንኳ አቻው ሊሆን የሚችለው የጋውላው አማዲስ ወንድም» ዶን ጋላውር ብቻ ነው ፡ ምክንያቱም ለማናቸውም አዶጋ የተሰናዳና በስሜቱም እንደ ወንድሙ የማይበገር ፡ ፍቅር አጥቅቶት የማይበሳጭና የማያለቅስ ፡ ቆራጥ ፈረሰኛ ስለሆነ በጀግንነት ረገድ ከፌቦ የማያንስ ብርቱ ታጋይ ነው» እያለ አስተያየቱን ይገልጥላቸው ነበር ።

በጠቅላላው አዲሱ ፈረሰኛችን በነዚህ ድርሰቶች ፍቅር ልቡ በጥልቅ ስለተማረከ ከዚያ ወዲህ ሌላ ጣልቃ ሃሣብ ሳይወጥን ከማታ አንስቶ እስከ ጧት ሙሉውን ሴሊትና እንዲሁም ከጧት አንስቶ እስከ ማታ ሙሉውን ቀን በቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ ተዘግቶ ያለፋታ ሲያነብ ውሎ ያነጋ ነበር ። አእምሮው እስኪደነዝዝና መንፈሱ እስኪዝል ድረስ የዕረፍት ጊዜውን ለን

ባብ ስላስገደደው ብዙ በማንበቡና የብዙ ጊዜ እንቅልፍ በማ
ጣቱ ምክንያት አንጐሉ ስለደረቀ ልቡን እንደመንሳት አድር
ጐት ስንበተና በመጨረሻው አሳበደው ።

አስተያየቱ ሁሉ በየድርሰቶቹ ገጽ ተጽፈው ባነበባቸው
ታሪኮች ታጨቀ ። ማመዛዘንና በትክክል መፍረድ እንዳይችል
አእምሮው ተናጋበት ። ዘወትር የሚታየው ሁሉ የአስማትና
የምትሐት ጥበብ ፣ ጠብ መጫር ፣ መፎካከርና መዛዛት ፣ ውጊያ
መግጠምና መቁሰል ፣ ጉራ መንዛት ፣ ፍቅር መወጠን ፣ በልብ
ኩራት ማሳደርና እንዲሁም እጅግ ብርቱና አደገኛ የሆኑትን
ተግባሮች ፈጽሞ ለመገኘት መጣጣር ፣ እነዚህንና ሌሳም ዝብ
ርቅርቅ ያሉ አታካችና ፍሬ ቢስ ሁኔታዎች ተዋህደውት ከቀ
ናው መንገድ እንዲወጣ አደረጉት ።

እነዚህም የቅዠት ትርኢቶችና ፈጠራዎች ሁሉ በደራ
ያን አሳቢነት የተጻፉና ስለጥንታውያን ፈረሰኞች ሞያ የሚና
ገሩ ልብ ወለድ ታሪኮች ከመሆናቸው በቀር እውነተኛ ድር
ጊቶች ስላልነበሩ ዶን ኪሾት በተመራመረው መጠን ይህ ተደ
ረገ ተብሎ የተወራው ታሪክ ሁሉ ንጹሕ እውነት መሆኑን
አምኖ ለመቀበል እስኪሸነፍ ድረስ በአእምሮው ውስጥ ስለጠ
ቀጠቀው በሱ ግምት በዓለም ላይ ከዚህ ይበልጥ እውነተኛ የሆነ
ታሪክ አለመኖሩን አረጋገጠ ። እሱም በበኩሉ ታሪኩን በመደ
ገፍና በማረም አስተያየቱን ሲሰጥ «ሰይድ ሩዋይ ዲያዝ የሚ
ባለው ጀግና ያለጥርጥር ምርጥ ፈረሰኛ ነበር ፣ ይሁን እንጂ ከባለ
አብረቅራቂው ሠይፍ ፈረሰኛ ጋር ሊወዳደር የሚችል አልነበ
ረም ፣ ይሽኛው ከሁለት ኃይለኞች ከሆኑ ሰማይ ጠቀስ ጀዊሣ
ዎች ጋር ተጋጥመው ባንድ የሠይፍ ስንዘራ ብቻ አካላቸውን
መሐል ለመሐል ስለተረከካቸው ጀግንነቱ ከፍ ያለ ብልጫ
አግኝቷል» ።

«ከሱ የሚበልጥ ጀግና ለማግኘት የተፈለገ እንደሆን ግን»
ቤርናርዶ ዲካርፒዮ የሚባለው»የሚያይል ነው ። ይህም ፈረሰኛ
በድፍረትና ፀቆራጥነት የተዳኘውን ሮናልዶ የሚባለውን ፈረ
ሰኛ ሮንሺስቫሌ ላይ ገድሎታል ። አገዳደሉም ጀዊሣው ኤር

ኩሌ የምድርን ልጅ አንቴዎን እግሩን ከመሬት አላቅቆ በእጁ
እንዳቴን አንቆ በገደለበት አኳኋን በዚሁ ብልሃት ተጠቅሞ
ነው ። ከዚህ በስተቀር ደግሞ ስለጀግናው ሞርጋንቴ የትህትና
ጠባይ ደራሲው የተናገረው ሁሉ እጅግ ከፍ ያለ ምሥጋና የሚ
ያሰጠው ነው ። ምክንያቱም እሱ ብቻ ከሌሎቹ በተፈጥሮ ጠባ
ያቸው ትእቢተኞችና ሰው ናቂዎች ከሆኑት ጀዊሣዎች በማይገ
ዥም አኳኋን አመለ ጌታና ሰው አክባሪ አኩሪ ትሁት ግብረገብ
ሰው ነበረ። እንዲሁም ከነዚህ ሁሉ በላይ በስመ ገናናነቱ ጉልቶ
የሚታየው ሪናልዶ ዴ. ሞንቴአልባኖ ነው ። በተለይም ከመኖሪያ
ግንቡ በወጣ ጊዜ ከፊቱ ያገኛቸውን ሰዎች ሁሉ በጐራዴ እየ
ጨፈጨፈ እንዶ ቅጠል እያራገፋቸው ጥሶ በማለፉና በታሪኩም
ላይ እንደሚተረከው ሁለመናው በወርቅ የተሠራውን የመሐ
መደን ሐውልት በሠረቀ ጊዜ ታምራዊ ድፍረት በማሳየቱ
እንደ ፀሐይ በምድር ላይ ሲያበራ የሚኖር ዝና ተቀዳጅቷል» ።
እያለ በመቀጠል ሲተች ቆየና ወደ ከሃዲው የሚጋንሳው ጋኖ
ታሪክ ላይ ስለደረሰ በሰውየው ጅላጅልነትና እንከፍነት ተናዶ
ከፊቱ ያገኘው መስሎት በእርግጫ ሊፈነቸረው እግሩን ሲሰነዝር
በመሳሳት አሮጊቷንና የወንድሙን ልጅ ሊደርባቸው ነበር ።

በዚህ መንፈስ ተነሳስሎ አንጐሉ ፈጽሞ ስለወደመ ያንድ
የለየለት ዕብድ አእምሮ እንኳ ይሠራዋል ተብሎ የሚያታሰበውን
የቅሌት ሥራ ለመሥራት ታጥቆ ተነሣ ። ዓላማውም የራሱን
ክብር ለሚሳደግም ሆነ ለዓለም ቤዛ ለመሆን ዙዋሪ ፈረሰኛ
ሆኖ ፣ የጦር መሣሪያ ይዞ በፈረስ ላይ ተቀምጦ ዓለምን እየዞረ
አጋጣሚውን መፈለግና እንዲሁም በታሪክ ላይ አንብቦ እንደ
ተረዳው ሁሉ ዙዋሪ ፈረሰኞች ለአደጋ በሚጋፈጡበት ዓይነ
ትና አኳኋን እሱም ለማናቸውም አደጋ አልፎ እየተጋፈጠ የሕ
ዝብን ሠላማዊ ኑሮ ለማናጋት ባንዳንድ ትምክህተኞች ጥጋብ
የሚፈጸሙትን የግፍ ሥራዎች ለመበቀል ፣ ለአደጋ በመከለልና
ከወደረኛው ጋር እየተዋጋ በአሸናፊነት የዘለቀ እንደሆነ ደካማ
ዎችን ለመርዳት ሲል ባደረገው ተጋድሎ ዘላለማዊ ክብርና
ምሥጋና ገብይቶ የማይሞት ስም ለማትረፍ ነበር ። የራሱን
ክብር ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ተግባሩ እንደሆነ ይቆጥ
ረው ነበር ።

ይህ ምስኪን ሰው ለክንዱ ብርታት ምሥጋና ይድረሰውና ይህን የወደፊት ተግባሩን አፈጻጸም በሚያሰላስልበት ጊዜ በትን ቢት ምኞቱ ዘውድ ጭኖ ቢያንስ ቢያንስ የትሬቢዞንዳ ንጉሠ ነገሥት መሆኑ እንደሕልም ይታየው ነበር ። በዚህ ከንቱ ተስፋ እየተገፋፋና ከተስፋውም ያገኘው ደስታ እያጠገበው ለተወራው የፈረሰኛነት ተግባር ብርቱ ፍቅር ስላደረበት ፍላጐቱን ወደ ፍጻሜ የሚያደርስበትን አቅድ ከሥራ ሊያውል ይጣደፍ ጀመር ።

ከሁሉ አስቀድሞ ለተግባሩ ማከናወኛ የሚገለገልባቸው በያይነቱ የጦር መሣሪያዎች ማግኘት አስፈላጊው መሆኑ ትዝ ስላለው የቅድሚያቶቹ ቅርስ የነበሩ ፣ ከብዙ መቶ ዓመታት ጀምሮ በቤቱ ባንዱ ጥግ ተረስተው የተቀመጡ የዛጉና የሻገቱ መሣሪያዎች መጠራረግ ጀመረ ።ዝገቱን እየፈቀፈቀ አስለቅቆ ቅባት ቀባብቶ የተቻለውን ያህል ካጸዳቸው በኋላ ባንዳኛው መሣሪያ ላይ በጣም ጠቃሚ የሆነው ወገን የሚጐድለው መሆኑን ተመለከተ ። ይህም አንድ መናኛ ተራ የእራስ ቆብ እንጂ ፊቱን በሙሉ የሚሸፍን ደንበኛ የራስ ቁር አልነበረም፣ ነገር ግን በጉድለቱ ተስፋ መቁረጥ የማይገባ መሆኑን በመረዳት በገዛ ብልሀቱ ፈጥሮ ወፈር ያለ የወረቀት ክርታስ በልኩ ከርክሞ በዚያ በጐደለው ቦታ እየሸጐጠ ጠጋነነውና ለጊዜው ደንበኛ የራስ ቁር አስመስሎ አበጀው ።

ነገር ግን በቅርብ ጊዜ በሚጀምረው የውጊያ ተግባሩ ላይ የሚገጥመውን የጐራዴ ምት ለመመከት የራስ ቁሩ በቂ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ለመፈተን ስለፈለገ ፣ እመሬት ላይ አስቀመጠና ጐራዴውን መዝዞ ሁለት ጊዜ መታው ። ዳሩ ግን ይህ የመጀ መሪያው ምት ብቻ ሳምንት ሙሉ የተደከመበትን ሥራ ባንድ አፍታ ሊበታትነው ቻለ ። የዚህ ራስ ቁር በቀላሉ መነካካት የሥራውን ግብዝነት ስለመስከረበት እንደገና አጠናክሮ ለመ ሥራትና ከማናቸውም አዲጋ የተረጋገጠ ለመሆን ሲል በክርታሱ ፈንታ ቀጭን የብረት ሾቦ ጣልቃ እያገባ አፍረግርጐ በጥንካ ሬውና ባሠራሩ ከመጀመሪያ የተሻለ አድርጐ ጠጋነነው ። ከዚህ በኋላ ሌላ ቁንጥና ማሳመር ሳያበዛ መናኛውን የራስ ቆብ ደንበኛ የራስ ቁር አድርጐ ለወጠው ።

ቀጥሎም ፈረሱን ለመጐብኘት ወደ ታሠረበት ጋጣ ፊጥኖ ሄደ ፣ ምንም እንኳ ይህ ያልታደለ ፈረስ ያረጀና የደከመ ፣ እጥንትና ጠጉር ብቻ የቀረው ከነጋዴ አጋሰስ ይበልጥ የተገ ጠበ ጌኛ ቢሆንም በርሱ የዕበደት አስተያየት የዓለምን ፈረ ሶች በተለይም የአስክንድርን ቡቄፋሉስና የስይድን ባቢዮካ በጮሌነት እንደሚበልጣቸው ይተማመንበት ነበርና በትምክ ህት ዓይን አንገቱን እየተመተመ ፣ ጋማውን እያሻሸ አባብሶት ተመለሰ ።

ፈረሱም ከዚህ ቀደም የመጠሪያ ስም ስላልነበረው ወደ ፊት የሚያወጣለትን ስም አራት ቀን ሙሉ ሲፈልግ ሰነበተ። ስም ለማውጣት ያስበበትም ዋናው ምክንያት አንድ ስመ ጥር ፈረሰኛ የሚቀመጥበት ፈረስ በዓለም ላይ የታወቀ ያለ ስም እንዲኖር አስፈላጊና የተገባ አለ መሆኑን ባነበበው ታሪክ ላይ ከተረዳው በኋላ ነው ። እንዲሁም ደግሞ ጌታው የቀድሞ ተግ ባሩን በሚለውጥበት ጊዜ የፈረሱም ሁኔታ አብሮ መለወጥ ከጥ ንት የቆየ የፈረሰኞች ልምድ ስለሆነ ጌታውና ፈረሱ በቅርብ ጊዜ አብረው ለሚጀምሩት ለዚህ እጅግ ከፍ ላለውና ለገነነው የፈረሰኛነት ተግባር መመኪያና መኩሪያ መሆኑን የሚያረጋግጥና እንዲሁም ያንድ ዙዋሪ ፈረሰኛ ሞገሳዊ ፈረስ ከመሆኑ በፊት ምን እንደነበረና አውን ደግሞ ወደ የትኛው ደረጃ ለመድረስ እንደተቃረበ የሚያስረዳ ጥሩ ስም ሳያወጣለት መቅረቱ የተገባ አለመሆኑን ስለተገነዘበው ነው ።

በዚህ አኳኋን በቅዠት መንፈሱ ሲያወጣና ሲያወርድ ፣ ሲመ ርጥና ፣ ሲለውጥ ሲያስረዝምና ሲያሳጥር ፣ ሰንብቶ በመጨረሻው «ሮዚናንቴ» የተባለውን ስም በመስጠት ተወሰነ ። ይህም ስም በራሱ ግምት እጅግ የላቀና የተበራራ ትርጉም ያለው መሆኑን እመነ ። ምክንያቱም «ሮዚኖ» የተባለው ፈረስ በዋንት ዘመን በመላው ዓለም በጋላቢነት ሞያው የተመሰገነ መሆኑን በታሪክ ላይ ተረድቶት ስለነበረ ባደረገው ምርጫ ቅር አልተሰኘበትም ነበር ።

ይህን መልካም ስም ለፈረሱ ከሰጠ በኋላ ለራሱ ደግሞ አንድ የሚያኰራ ስም መፈለግ ጀመረ ። ነገር ግን ለራሱ የሚ

ሆን ስም የመፈለጊያው ጊዜ ስምንት ቀን ፈጅቶበታል። እዚህም ላይ ብርቱ ማማረጥ ካደረገ በኋላ በመጨረሻው «ዶን ኪሾት» የተባለውን ስም አጸደቀ ። የስሙም ትርጓሜ «ዶን» ማለት በእስፓኒያ አገር ለምግባረ መልካም ወገኖች የሚሰጥ ተደራቢ የክብር ስም ነው ። «ኪሾት» ማለት ደግሞ በእስፓኒያ ቋንቋ የታፋን ወገን የሚሸፍን የብረት ልብስ ማለት ነው ።

ይህን እውነተኛ ታሪክ የጻፈው ደራሲ እንደሚለው ፈረሰኛው ከወላጆቹ የወረሰው የመጠሪያ ስሙ ያነሱ ሰዎች በመሳሳት እንደሚጠሩት ኪሻዳ የሚባለው ሳይሆን ትክክለኛው አጠራር ኪሻና የተባለው መሆኑን አረጋግጠዋል ። ስለዚህ የጹሮው ጀግና ፈረሰኛ አማዲስም በነጠላ አጠራር አማዲስ ተብሎ መጣራትን ባለመፍቀዱ የተነሳ የውልደት አገሩንና ያውራጃቸውን ስም ለማሳወቅ ሲል «የጋውላው አማዲስ» ተብሎ መሰየሙን አስታወሰና እሱም ጀግና ፈረሰኛ ለመሆን የተዘጋጀ ነበርና በስሙ ላይ ያነሩን ስም ደርቦ «የሚንቻው ዶን ኪሾት» ተባለ።

በዚህ አኳኋን ተደራቢ ስሙን ከአገሩ ስም በመውረሱና እንደዚሁም ታሪኩንና ጥንተ መሠረቱን ሳይለቅ ለብሒሩ የሚገባውን ክብር በመሰጠቱ ልቡ በደስታ መላ ።

ከፍ ብለን እንደተናገርነው የጦር መሣሪያዎቹን በሚቻለው መጠን በሥርዓት ወልውሎ አጸዳድቶ ፤ መናኛውን የራስ ቆብ በደህና የራስ ቁር አምሳያ ለውጦ ፤ ለፈረሱ ስም አወጣቶ ፤ እንዲሁም እራሱን በራሱ ሰይሞ ፣ በጦር መሣሪያና በስም ረገድ ጣጣውን ከጨረሰ በኋላ ሌላ የሚቀረው ነገር መኖር አለመኖሩን ለማጣራት ሲል ሃሣቡን መበርበር ጀመረ ።

ሃሣቡ የሚቀጥለውን ዋና ጉዳይ አስታወሰው ። ባገር የታወቀ ዙዋሪ ፈረሰኛ ሆኖ አንዲት የክንፈር ወዳጅ ሳይዝና የፍቅር ስሜት በልቡ ሳያሳድር መገኘት ቅጠልና ፍሬ እንደሌለው ዛፍ ፣ ነፋስ እንደሌለው አካል ፤ ከበድን የሚቆጠር ስለሆነበት ከዚህ ብርቱ ነቀፌታ ለመዳን ሲል አንዲት ለፍቅሩ የምትስማማ ሴት ፈልጎ ከርሷ ጋር የክንፈር ወዳጅነትን ከመመጠን በቀር ሌላ የሚጐድለው ነገር አለመኖሩን ካረጋገጠ በኋላ የሚቀጥለውን የሕልም ምኞት መመኘት ጀመረ ።

«ስለፈጸምሁት ስሕተትም ሆነ ፤ ወይም ስለመልካሙ አጋጣሚ ሁኔታዎችን ሳጤናቸው በጥንታውያን ፈረሰኞች ላይ ያጋጥም የነበረው ግጭት እኔንም ከአንድ ትምክህተኛ ኃይለኛ ጋር ያጋጥመኛ ይሆናል ። በዚያን ወቅት ከኃይለኛው ጋር በድፍረትና በቆራጥነት ውጊያ ገጥሜ ላሸንፍም እችል ይሆናል ወይም ትምክህተኛውን ተጋጥሜ ከሁለት ሥፍራ ልሰነጥቀውም እችል ይሆናል ። የምልከበት ሁኔኛ ሥፍራ ግጣቱ ትልቅ ጉድለት አይደለምን ? ስለዚህ ወደፊት ድል የማደርገውን ጀውሣ ከማ ፈቅራትና በልቤ ውስጥ ከምቀርጻት ወደ ማዓዛይቱ ወይዘሮ ዘንድ እንዲሄድ እልክዋለሁ ። ጀዊሣውም ትእዛዜን በመፈጸም ወይዘሮይቱ የምትኖርበትን አገር እየጠያየቀ ይሄድና ከፊቷ ቱን በርክክ ከተሰለመ በኋላ በትህትና አንደበትና በመሸቆጥቆጥ እን ዲህ ይላታል ።

«ክብርት ወልዕልት እመቤቴ ሆይ ! ባሪ እፊትዎ ለመቅረብ ሞነስ ያገኘሁት እኔ ባሪያዎ የማሊንድራኒያ ደቤት መስፍን ጀውሣው ካራኩሊያምብሮ ነኝ ። ነገር ግን ለጀግንነቱ ወደረኛ የሌለው ፈረሰኛ ከማንቻው ዶን ኪሾት ጋር አንድ ሳንድ ባደረግነው ግጥሚያ ድል ስለአደረገኝና ወደ ልዕልትነትዎ እን ድቀርብ ግዴታ ስላገባኝ እነሆ ትእዛዙን ለመፈጸም አገር አቋርጬ መጥቻለሁ ። ይህም የገባሁት ግዴታ በተለይ በኔ ላይ ለተፈጸመ የጀብዱ ሥራ እራሴ ምስክር ሆኜ እንድናገር ስለሆነ ልዕልትነትዎ ያሰኝዎትንና ያሻዎትን ሁሉ እንዲያዝዙኝ ትሁትና ፍጹም አገልጋይዎ ሆኜ ይህን የድል አድራጊነት ምሥራች ይገርልዎ መጥቼአለሁ» ብሎ ንግግሩን ጨረሰ ።

እዩ ጉድ..... የዋሁ ፈረሰኛችን ይህን የትንቢት ምኞት በሃሣቡ ተናግሮ ሲጨርስ ነገሩ አሁን ባሁን የደረሰ መስሎ ሰለታየው በዚያን ሰዓት በልቡ ያሰደረው ደስታ የሚለካ አልነበረም ። የባሰውን ደግሞ በደስታ የፈነጠዘው ለክንፈር ወዳጅነት ያጫትን ሴት ወይዘሮ በሐሣቡ መርጦ ካገኛት በኋላ ነው ። የመረጣትም ሴት እርሱ እራሱ በሚኖርበት መንደር የምትወለድ አንዲት የደሰ ደሰ ያላት ዓይናማ የባላገር ቆንጆ ነበረች ። እርሷም ከዚህ ቀደም ረው ያጫትና ያፈቀራት መሆኗን በልቦናዋ ተጠራጥራ ሰውነቷን ለመጠበቅና ነቃ ብላ ለመታየት ሳትኳኳልና

ሳታጌጥ ፤ ዶን ኪሾት በዚያው ባያት ሁኔታዋ መጠን በደም ግባቷ ብቻ ልቡ ደንግጠበት አንድ ሰሞን በጣም አፍቅሯት ስለነበረ ፤ በአጠገቡ ስታልፍና ስታገድም ባያት ቁጥር ዓይኑ አብሮ ይንከራተት ነበር ። አሁን ግን ይህን የከንፈር ወዳጅ የሚፈልግለትን አጋጣሚ ምክንያት ስለአገኘ ልቡ ሳያወላው ልና ሌላ ምርጫ ለማድረግ ሳያመነታ በቀጥታ እሷኑ በማፍቀር ተወሰነ ።

ይህችም ሴት የመጀመሪያው ስሟ «አልዶንሳ ሎሬንዞ» ትባል ነበር ። ዳሩ ግን የሱ እጮኛና የልቡ እመቤት እንድትሆን ከመረጣት ወዲህ በወትሮው ስሟ መጠራቷ እንዲቀር ስለ ፈቀደ ለራሱ ከቀድሞው ስሟ ጋር እጅግ የሚይራራቅ ሆኖ ከዚህ ቀደም ሌላ ሴት ያልተጠራችበትና የልዕልትነትንም ጠባይ የሚ ሰጥ ስም ፈልጐ «የቶቦሶይቱ ዱልቺኒያ» ብሎ ሰየማት ። ይህን ንም ስም የሰጠበት ምክንያት ልጅቱ የቶቦሶ ተወላጅ በመሆኗ እሷም የአገሯን ስም ደርባ እንድትጠራበት በመፍቀዱ ነው ። ስምነቱም የላቀ ምሳሌና ትርጉም ያለው ፥ ለአጠራርም ደስ የሚያሰኝ ምርጥ ስም ስለመሰለው ከዚህ የተሻለ ስም ፈልጐ ለመለወጥ ሌላ ምርጫ ለማድረግ አልሞከረም ።

ም ዕ ራ ፍ 2

ብልሃተኛው ዶን ኪሾት ለመጀመሪያው ጊዜ ለዙረት ከትውልድ አገሩ እንደወጣ ይተረካል ።

እንግዲህ እነዚህን የፈረሰኛነት ተግባር ማከናወኛ መሣሪ ያዎች አጠናቅቆ ከጨረሰ በኋላ እቅዱን በገቢር ላይ ለማዋል ከመጣዳፍ በስተቀር ጣልቃ ገብ የሆነ ጊዜ አባካኝና አሳናፊ ሃሳብ እንዲደቀንበት አልፈቀደም ነበር ። ምክንያቱም በዳኝ ነቱ እየፈረደ ጉድለትን ለማቃናትና ጥፋተኛንም ለመበ ቀል የተዘጋጀባቸው ተግባሮች ብዙዎች ስለሆኑ ፤ በእሱ መዘ ግየት የተነሣ ኃይለኞችና ሃብታሞች የግፍ ሥራቸውን ለመ ፈጸም ምቹ ጊዜ እግኝተው ያሰኛቸውን በደል ለማድረግ መቻ ላቸውና በዓለም ላይ የሚያመጡት ጉዳትና እንባ ከባድ መሆኑ እየታየው ነው ። ይህም አሳሳቢ ምክንያት ከመቸውም ይበልጥ መንፈሱን ስላነቃቃው የዙረት ጉዞውን ለመጀመር ልቡ ክፉኛ ቸኮሳ ።

አዲሱ ፈረሰኛ የሞቀ ትዳሩንና ሞላ ንብረቱን እንዳለ ትቶ ፅድሜውን በዙረት ለመጨረስ የቆረጠበት ዋናው መነሻ ዓለማው በዚች በምንኖርበት ዓለም አያሌ የግፍ ሥራዎች በየዋሆችና በደካሞችን ላይ ሳያቋርጡ የሚፈጸሙ መሆናቸውንና እንዲሁም ኃያሉን ኃይለኛው አዝሎት ሁለቱንም ደርቦ የሚሸከም ያው እሳረኛው ይህ መሆኑን ስለሚያውቅ ፤ ግፈኞችን በመቅጣት የፍርድ አድልዎን በማስተካከል ፥ ጥጋበኛን በማብረድ ፤ የተበ ደለውን በማስካስ ፤ ዕዳን በማከፋፈል ፥ የተጐዳን በመርዳት እነዚህንና ሌሎችንም እነዚህን የመሳሰሉትን የዳኝነት ተግባ ሮች እየፈጸመ የተቻለውን ያህል ግፍን ለማቃለልና ሰላምን ለመመሥረት የህሊና ቃል ኪዳን ስለገባ ነው ። ለዚህም የበጐ

አድራጮት አገልግሎቱ ዋጋ በሕይወቱ እስካለ ድረስ ምድራዊ ክብር የሚወርስና ከሞተም በኋላ ሀያው ስም የሚያተርፍ መሆኑን አረጋግጦ ነበር ። በዚህ መሠረት ሃጣብ ላይ ብርቱ እምነት ካሳደረ በኋላ ይህንኑ ሃጣቡን ለማንም ሳያካፍልና የጉዞውንም ምሥጢር ለወዳጆቹ ሳይገልጥ ማለዳ ጕሕ ሲቀድ ከምኝታው ተነስቶ የነሐስ ጥሩራውን ከእግሩ እስከ ራሱ አጥልቆ ፥ ያንን አውተፍትፎ የሠራውን የራስ ቁር ጭንቅላቱ ላይ ደፍቶ ፥ ጋሻውንና ጦሩን ይዞ ፥ ጕራዴውን ታጥቆ ፤ ከተሰናዳ በኋላ ቤተሰቦቹ ከእንቅልፋቸው እስመንቃታቸውንና መንደሩም ጭር ማለቱን ሰልሶ ሲያበቃ ሮንዚንናቱ ላይ ተቀመጠና በመስኩ አካያ ባንዲት ስርቆሽ በር በኩል ወጥቶ ወደ አውራው መን ገድ ገባ (ወራቱም ሐምሌ ሙቀቱ የሚወብቅበት ወቅት ነበር) ።

በዚህን ጊዜ በጠቅላላው ያቀደው ሃጣብ አንዳች እንቅፋት ሳያደናቅፈው ገና ከውጥኑ ጀምሮ ይህን ወደመሰለው አስደሳች ነጥብ ላይ ስላደረሰውና እጅግ ለተከበረውም ምኞት መልካም አዘላለቅ አስተማማኝ ምልክት ስላሳየው ፤ በዚያን ጊዜ የተሰማውን ታላቅ ደስታ የሚገልጥ የብርሃን ፈገግታ በፊቱ ላይ ሲያበራ ይታይ ነበር ። ይሁን እንጂ በዚህ ደስታ እየፈነደቀ ጥቂት ምዕራፍ መንገድ ሄዶ ካንዲት ገላጣ ሜዳ ላይ ሲደርስ አንድ ብርቱ የጥርጣሬ መንፈስ በድንገት ወረረው ። ይህም የጥርጣሬ መንፈስ ያልነው በብዙ ችግርና ብዙ ቀን በፈጀ ድካም ኣዘጋጅቶ ያቀደውን ሃጣብ የሚያፋልስና በእቅዱም ውስጥ አንዳች ጉድለት መኖሩን የሚያስታውስ ነበር ። እንዲያውም ይህን የጀመረውን የዙረት ተግባር አቋርጦ ወደ አገሩ እንዲመለስና የቀድሞ ተግባሩን እንዲቀጥል የሚገፋፋው ነበር ።

ሃጣቡም የደፈረሰበት ምክንያት በጥንት ልማድ ወደ ፈረሰኛነት ተግባር የሚሠማራ ማናቸውም ሰው በፈረሰኛነቱ ሞያው የላቀ ሆኖ ስመ ጥር ለመባል እንዲበቃ አስቀድሞ የፈረሰኛነት መብቱን የሚያጸና የክህነት ቡራኬ መቀበል የሚገባው መሆኑ ትዝ ስላለው ነው ። ዶን ኪሾት ግን ገና ከቤቱ የወጣ አዲስ ጀማሪ ከመሆኑ በቀር ከዚህ በፊት ለዚህ ተግባር የሚሰጠውን ፈተና አልፎ ክህነት አለመቀበሉን ፥ ስለፈረሰኛነትም ተግባር

ተመራር በተደነገገው ሕግ ውስጥ እንደ ተጻፈው ክህነት ያልተቀበለው ፈረሰኛ ከዚያ ከተቀበለው ፈረሰኛ ጋር ተፎካክሮ ሕጋዊ ውጊያ ለመግጠም የማይችልና የማይፈቀድለት መሆኑን እንዲሁም ደግሞ ፈተናውን አልፎ ክህነት የተቀበለ ፈረሰኛ ቢሆንም እንኳ ከወደረኛው ጋር የሕጋዊ ውጊያ ግጥሚያ አድርጐ በአሸናፊነቱ ምርኮና ሰለባ አስኪያገኝ ድረስ በጋሻው ሰጉድ ላይ የጀግንነት መለያ ምልክት ሳያደርግ ልሙጥ ጋሻ ብቻ መያዝ የሚገባው መሆኑን ፥ በጦር መሣሪያ ረገድ አውን እንደታጠቀው ያለ አሮጌና ደነዝ መሣሪያ ሳይሆን አዲስና ሰለ ታም መሣሪያ እንዲታጠቅ አስፈላጊ መሆኑን ፥ ደንቡ አጥብቆ ስለሚያዝዝ ይህን ሁሉ ሳያጣራና ጉድለቱን ሳያስተካክል፥ ፈተናውን ሳያልፍ ፥ ክህነት ሳይቀበል ፥ በችኩልነት ተንደርድሮ የጀመረው የዙረት ጉዞ ከንቱ መሆኑን ሲመለከት ስሞኑን የለቆበት ድርጅትና ሲጠበብበት የከረመው እቅድ ሁሉ ዋጋ አልባ ሆኖ መቅረቱን በመገንዘብ ብስጭት አደረበት ። ስለሆነም ለዚህ ዕብደት ያበቃው አስተያየት ማናቸውንም ዓይነት የተዛባ ነገር በመሰለው መንገድ እያቃና ለመለወጥ የሚያስችል ብር ታት ሰጥቶት ስለነበረ በእነበባቸው መጻሕፍት ውስጥ እንደ አጠናው ሌሎች ብዙዎች ሰዎች ሲያደርጉት የነበረውን ምሳሌ በመከተል ፥ መጀመሪያ ከሚገናኘው የፈረሰኛ ክህነት ሰጭ ዘንድ ቀርቦ የፈረሰኝነት መብቱን የሚያጸና ክህነት ለመቀበል ወሰነ። ስለጦር መሣሪያዎቹ አዲስነትና ስለታምነት ደግሞ ጥቂት የረፍት ጊዜ እንዳገኘ ወዲያውኑ ከመስታወት በበለጠ አኳኋን እንዲያንጸባርቅ አድርጐ ለመወልወልና ለመሳል መቻሉን አረጋገጠ ። በዚህ አይዘህ ባይ አስተያየት ብስጭቱን ካሰወገደ በኋላ የመንገድ አቅጣጫ የመምረጡን ፈቃድ ለፈረሱ ተወሰትና ፈረሱ ወደ አመራበት አካያ ጉዞውን ቀጠለ ። እንዲህም ማድረጉ እርሱ እንደሚያምነው የአጋጣሚ አፈላለጉ ዘዴ በዚህ ሁኔታ መፈጸም ይገባዋል ስለሚል ነው ።

አዲሱና ትንታጉ ፈረሰኛችን ጉዞውን ወደፊት በሚቀጥልበት ጊዜ እንዲህ እያለ ብቻውን ይነጋገር ነበር ። «ማን ያውቃል? ምናልባት አንድ ቀን በስመ ጥሩነቱ የሚዘነው የጀግንነት ተግባሬ እውነተኛው ታሪክ ተጽፎ በሚገልጥበት ዘመን፥

የሕይወት ታሪኬን ለመጻፍ የታደለው አዋቂው ደራሲ በዚህ በመጀመሪያው አስደሳች የዙረት አወጣጡ ላይ ሲደርስ ያካባቢውን መልክና ሁኔታ በመዘርዘር ቀጥሎ ያለውን ቃል ሳያክል ልበት አይቀርም ። አጸዶችና ተክሎች ጫፍ ላይ ብቅ ብሎ የሚ ያማምሩትን ወርቅማ ጨረሮችን በሠፊውና በተንጣለለችው ምድር ላይ ገና መፈንጠቁ ነበር ፣ እንዲሁም ደግሞ በልዩ ልዩ ቀለማት ተሸላልመው ያሬጡት አዕዋፎች ጣፋጭ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ለዛ በጎመላ ዘፈን እየዘመሩ የቀናተኛ ባሏን ምቹ የጫጉላ አልጋ ለቅቃ በማንቻው ሰገነት መስኰት በኩል ዘልቃ ለሙታን ፍጥረታት ለመታየት የምትወጣውን ጀምበር እያመ ሰገኑ የምስራች ሰላምታቸውን ገና ማለማታቸው ነበር ። በዚ ያን ጊዜ የማንቻው ነበልባል ፈረሰኛው ዶን ኪሾት በሳባ ፍራ ሽና መከዳ ላይ የመንደላቀቅን ምኞት ንቆ በፎሌው ሮንዚናንቴ ላይ ቁብ ብሎ ጥንታዊውንና ስመ ጥሩውን የሞንቲዮልን ገጠር አቋርጦ ጉዞውን ጀመረ» የሚል ነበር ። እውነትም አቋርጦ ያለ ፈው በዚሁ መንገድ ነው ።

ቀጥሎም እንዲህ አለ ፣ «በነሐስ ላይ ተቀርጾ በእብነ በረድ ላይታንጸ ፣ በሰሌዳ ላይ ተሰሎ የዘለዓለም መታሰቢያ ሆኖ መኖር የሚገባው የስመ ጥሩው ዝናዬ ታሪክ የሚገለጥባቸው ዘመናትና የትውልድ ዕድሜ የታደሉና በትፍስሕት የተመሉ ናቸው ። ለዚህ አስደናቂ ለሚሆነው ተግባሬ ታሪክ ጸሐፊ እንድትሆን የምትመረ ጠው ማንኛህም ጠቢብ አስማተኛ ሆይ ፣ በጉዞዬና በመንገዴ ሁሉ የማይለየኝን የታማኙንና የባዳሙን ጓደኛዬን የሮንዚናን ቴንም ታሪክ ከመጻፍ እንዳትረሳ በጥብቅ አደራ እያልኩ እለ ምንሃለሁ ። ከዚህም በማከታተል በርግጥ ያፈቀረ ይመስል እን ዲህ ይል ጀመር ። «ልዕልት ድልቼና ሆይ ፣ የዚህ የአስረኛው ልብ እመቤት ሆይ ፣ በውበትሽ ፊት እንዳልቀርብ ጠንካራ እግድ ስላደረግሽብኝና መጥቼም እንድገናኝሽ ስላዘዝሽኝ ባልተጣራው ትእዛዝሽ ምክንያት የሚደርገው ቅሙ ስለጠፋኝ በጣም በድለ ሽኛልና ይህን እጅግ የሚያፈቅርሽን ዜጋሽ የሆነውን ልብ ለማስ ስታወስ የናፍቆት ትዝታሽን እንድትአዘነብይ እለምንሻለሁ» ካለ በኋላ ይህን ከመሳሰለው አነጋገር ጋር በመቀላቀል ከዚያ ካነበባቸው መጻሕፍት ላይ ያጠናውን አነጋገሮች ምሳሌ እየ

ተከተለ ይዘላብድ ጀመር ። ይህም ሲሆን ይህን ጉዳይ እያሰላሰለ በዝግታ እርምጃ ሲያዘግም ፀሐይዋ ደግሞ በፍጥነት ወደ ተሲያቱ እየተጠጋች ትሄድ ነበረ ። የፀሐይዋ የግለት ኃይል የተረፈውን አንጐሉን ለማቅለጥ ያህል የሚበቃ ነበር ።

ይህን የመጀመሪያውን ቀን በሙሉ አንዳች ለወሬ የሚ በቃ ነገር ሳያጋጥመው ሲጓዝ ዋለ ። ነገር ግን የውሎውን ሁኔታ ሲመለከት እንደተመኘው ሁሉ በቶሎ ካንድ ሰው ጋር ተጋጥሞ የኃይለኛ ክንዱን ብርቱነት የሚሞክርበት ጊዜ የዘገየ ስለመሰ ለው ትእግሥት አጥቶ ለምኞት ተስፋ ወደመቁረጥ ያዘነብል ጀመር ። ስለዚህም ጉዳይ አንዳንድ ደራሲያን መሠረት አድ ርገው እንደሚከራከሩት የመጀመሪያውን ግጥሚያ ያደረገው ቋጡዬርቶ ላፒቼ» ከሚባለው ሥፍራ ላይ ነው ይላሉ ። ሌሎች ደግሞ ይህን በማስተባበል የመጀመሪያው ግጥሚያ ሆኖ የተመ ዘገበው ከነፋስ ወፍጮዎች ጋር ያደረገው ነው ይላሉ ፣ ይሁን እንጂ እኔ ለመወሰን የቻልኩትና በማንቻም የታሪክ ዝክረ መዝ ገብ ውስጥ ተጽፎ ያገኘሁት የመጀመሪያው ዕለት ቀኑን በሞላ በፈረሱ ላይ ተቀምጦ ሲንጠራወዝ መዋሉንና ከመሸም በኋላ እሱና ሮንዚናንቴ በረሃብ ጠውልገው ተዳክመው ግማሽ እሬሣ ዎች ሆነው አንዳች ነገር ሳያደርጉ መጨለሙን ብቻ ነው ። ስለዚህ ጨለማው ፈጽሞ ከመደንገሩ በፊት ማደሪያና ምግብ ለማግኘት የሚችሉበት አንድ የመስፍን ግንብ ወይም የፍየል አርቢዎች ጐጆ ይታይ እንደሆን በማለት የቀበሌውን ዙሪያ እያ ሻገረ ሲመለከት ቆየና ከመንገዱ ጥቂት እልፍ እንዳለ ወዲያ ውኑ አንድ የመንገደኛ ሆቴል ተከሰተለት ፣ ይህንንም መልካም ዕድል ማግኘቱ ወደ ምሕረት ምድረክ የሚያደርሰውን ሳይሆን በቀጥታ ወደ ሰላም አልፍኝ የሚያጋባውን መሪ ኰከብ እንዳ ገኘ ያህል ቆጠረው ። ከዚህ በኋላ ፈረሱን ጐታግቶ የተቻለውን ያህል እርምጃውን አፋጠነና ከጨለመ ወዲያ ወደዚህ ሆቴል ለመድረስ ቻለ ።

በዚህም ሆቴል ውስጥ እንዳጋጣሚ ሁለት የባላገር ኮረዳ ዎች ከስብሳብ ጥግ ቆመው እርስ በርሳቸው ሲጫወቱ አያቸው ። እነዚህም ኮረዳዎች በዚሁ ሆቴል ከሠፈሩት ነጋዴዎች ጋር

ወደሲቪሊያ ለመንዝ የነዚያን መነሳት የሚጠባበቁ ገበያተኞች ነበሩ ። ዙዋሪው ፈረሰኛችን ግን የሚያስበውና የሚያየው የሚያልመው ነገር ሁሉ በርግጥ የተደረገ እውነትና ትክክል ስለሚመስለውና እንዲሁም ባነበባቸው ልብ ወለድ ድርሰቶች ውስጥ የተመለከታቸው ሁኔታዎች ሁሉ በዓለም ሥዴዳ ላይ ተስለው የሚገኙ ፣ መድረስም ያለባቸው ጉዳዮች መሆናቸውን ስላረጋገጠ ፣ ሆቴሉን ከማየቱ ወዲያውኑ ልዩ ልዩ ምሳሌና መልክ ይሰጠው ጀመር ። ይኸውም ሆቴልነቱ ቀርቶ ባለአራት መናፈሻ ሰገነት ከነአብራቅራቂው የብር ጉልላቱና እንዲሁም ባለአንድ ታጣፊ የብረት ድልድይ ከሥሩም የውሃ መፍሰሻ ሠፌ ቦይ ፣ ከምድረ ግቢውም በተክልና በአበባ የተሸለመ የመናፈሻ ትፍስሕት ክበብ ፣ በጠቅላላው ደራሲያን ሰዓሊያን የመሳፍ ንት መኖሪያ ግንብና ግቢ እቅድና አኳኋኑን ዘርዝረው እን ደሚነድፉት ሁሉ አብሮ ሲገኝ የሚገባውን ማናቸውንም ዓይ ነት ተቀጥላ አካል ጨማምሮ በመስጠት እንደመሰለው አድ ርጐ ለዋወጠው ። መቸም አንዴ ይህን የመንገደኞችን ሆቴል በመስፍን ግንብ መስሎታልና ወደሱም እየቀረበ ሄዶ ጥቂት ርቀት ላይ ሲደርስ የሮንዚናንቴን ልጓም ገታና ከግንቡ ሰገነት ላይ ዘብ የሚቆመው እንግዳ ተጠባባቂ ድንክ ብቅ ብሎ አንድ ዙዋሪ ፈረሰኛ ወደ ግንቡ መምጣቱን በቱልቱላ ንፍ እስኪያበ ስር ድረስ ቆሞ ይጠብቅ ጀመር ። ነገር ግን ይህ የራሱ ቅዠት የፈጠረው ድንክ በዚህ ሥፍራ ፈጽሞ የሌለ በመሆኑ ሺህ ዓመት እንኳ ተገትሮ ሽቅብ ቢያንጋጥጥ ብቅ የማይልለት በመሆኑና እን ዲሁም ሮንዚናንቴ በፊናው ወደጋጣው ገብቶ ከሸክሙና ከድ ካሙ ለማረፍ ቸኩሎ እየተቅበጠበጠ አንገቱን ከፍና ዝቅ እያ ደረገ ፣ ልጓሙን እንዲለቅለት ስለታገሰው በዚህ አኳኋን ሲያ ዳምጥ ቆይቶ በመጨረሻው ትእግሥቱን ጨርሶ ፣ የፈረሰኛነትም ሕግ ሳይከበር በመቅረቱ ቅር እንዳለው ልጓሙን ለዚያ ለቅብ ጥብጡ ፈረስ ለቀቀለትና ወደ ሆቴሉ አዘገመ ። ወደ ሆቴሉም እየተቃረበ ሲሄድ ፊት ለፊት ከሚያያቸው ከነዚያ ከሁለቱ ኰረ ዳዎች ጋር ዓይን ለዓይን ተጋጠመ ። እነሱም ከመድረኩ በስ ተጉን ባለው ስብሳብ ቆመው ዶን ኪሾትን ገና ካመጣጡ ጀም ረው መልኩንና ሁኔታውን መለየት አቅቷቸው አትኩረው ይመ

ለከቱት ነበር ። ምንም እንኳ እነዚህ ሴቶች የመንገድ ድካም ያንገላታቸው የባላገር ወንዲሳዎች መሆናቸው ባይሰወር እሱ በበኩሉ በዕብደት አስተያየት እንደገመታቸው በተከበረው የመስፍን ግንብ ውስጥ በድሎት ተንቀባረው የሚኖሩና በዚ ያን ሰዓት እንደወጉ በአማረው ትፍሥሕት ክበብ ውስጥ ለመና ፈስ ወጥተው የተገኙ ሁለት ሞንዳላ ደንገጡሮች ፣ ወይም ሁለት የተዋቡ ወይዛዝርት መስለው ስለታዩ ለክብራቸው የሚገባውን ሰላምታ ለማቅረብ ወደነሱ እየለጠቀ በሚሄድበት ጊዜ የፈረስ አቀማመጡና ትክለ ሰውነቱ ፣ የደርባባነቱ ለዛ በወይዛዝርቱ ፊት ሞገስና ግምት እንዲያሰጠው በማለት በተቻለው መጠን ድካ ሙን ሁሉ አስወግዶ በግድርድርነት ተሸታተረ ።

በዚህን ጊዜ በግርግም ማብያው አውድማ ውስጥ የነ በረው የሆቴሉ የአሳማ እረኛ (እንዲህ ተብሎ መጠራት ባይገ ባውም ለማኳሰስ ሳይሆን እውነተኛው ስሙ ይኸው ነው) እን ደተለመደው አሳማዎቹን ሰብስቦ ለማብላት ሲል ቱልቱላውን ነፋላቸው ። አሳማዎቹም የጥሪ ምልክት መሆኑን ለምደውታ ልና እየተንጋጉ በግርግማቸው ዳር ተኰለኰሉ ። ዶን ኪሾትም ሲፈልገው የነበረው ድንክ የሱን መምጣት ለግቢው ሰዎች ለማሰማት ሲል መለከት የነፋ ስለመሰለው በደስታ ፈገግ እን ዳለ ወደሆቴሉና ወደ ኮረዳዎቹ ተጠጋ ። እነሱም ይህ ከዚህ ቀደም አይተውት የማያውቁት ሰው ከአግር ጣት እስከ ጠጉር ድረስ በነሐስ ጥሩራ ተጠርዞ የቆረፈደ ጋሻና አሮጌ ጦር ይዞ እፊታቸው ተገትሮ ባዩት ጊዜ እጅግ ስለተደናገጡ ወደ ሆቴሉ ለመግባት እገነገኑ ። ዶን ኪሾትም መፍራታቸውንና መሸሻቸ ውን አወቀና ፊቱን የሸፈነበትን የክርታስ መከለያ ገልጦ ፣ ትቢያ የለበሰውንና የከሳውን መልኩን እያሳየ በመልካም ትህትናና በተለሳለሰ አንደበት እንዲህ አላቸው ።

«ወዲያልኝ ፤ የተከበራችሁ ወይዛዝርት ሆይ ! ስለየትኛው ምክ ንያት ፈርታችሁ እንደምትሸሹኝ ባለማወቄ ተጨንቄአለሁ ። ይህ በኔ ላይ የምትመለከቱት የፈረሰኝነት አለባበስና ሁኔታ ለዓ ለም መድኃኒት መሆኔን ከማስረዳቱ በስተቀር የወንበዴነት መልክ የሌለበት መሆኑ ግልጥ ነው ። እንዲሁም ተግባሬ ለሆነው ለፈ

ረሰኛነት ግዳጅ አፈጻጸም ባለኝ ኃላፊነት መሠረት ለተጠቁት ጠበቃ ነኝ እንጂ ማንንም ቢሆን ያለአግባብ ለመበደልና ለማስቀየም የመጣሁ አይደለሁም ። እንኳንስ እናንተን ሁኔታችሁ እንደሚመስክረው ወይዛዝርት ልጃገረዶችን ይቅርና ተራ ሴቶች ሆናችሁ ባገኛችሁም ቅሉ በናንተ ላይ አንዳች ጉዳት እንዳይ ደርስባችሁ ከመጠበቅና ከማገልገል በስተቀር በበኩሌ ቅር የም ትሰኙበትንና የምታፍሩበትን ነገር እንዳላደርግ በመሐላና በግዝት የተቀበልኩት የፈረሰኛነት ክህነት አይፈቅድልኝም አላቸው ።

ኮረዳዎቹ ግን ከዚያ ከተረገመው የፊት ሽፋን ውስጥ ጨርሶ ያልተለጠውን አስቂ መልክ ለማየት ቸኩለው ባይና ቸው ከመፈለግና አትኩረው ከመመልከት በስተቀር እርሱ ከልቡ የሚናገረውን ቋንቋ አላዳመጡትም ነበር ። በዚህ ንግግሩ መካከል «ወይዛዝርት ልጃገረዶች» የሚለው ቃል ከሴ ቶቹ ተግባር ጋር የተራራቀ ስያሜ በመሆኑ ያሸፈባቸው ስለ መሰላቸው ነገሩ አስደንቋቸው ልባቸው እስኪፈርስ ድረስ ይስ ቁበት ጀመር ። ሳቃቸውም እየባሰ ከልክ አልፎ ስላንከተከታ ቸው ዶን ኪሾት በመሳቃቸው ተቀየመና እንዲህ ሲል ገሠግ ቸው ።

«የሰውን ልክ አመዛዝኖ ማወቅና ከዚያም በኋላ ለክብሩና ለማዕረጉ የሚገባውን አቀባበል መስጠት ፣ በወይዘሮናም ወግ መሽኩርመም ፣ መንዘባነን ፣ ዓይናፋር መሆን ፣ ይህ ሁሉ የልጃ ገረዶች ሞያ ነው ። ነገር ግን አሁን እናንተ እንዳደረጋችሁት በማይበቃ ምክንያት እንደቂል መሳቅና ማሽካካት በውነቱ ከብልግናና ከሃይን አወጣነት ወይም ከስድ አደግነት የሚያስ ቆጥር የሚታዘቡት የተዋረደ ጠባይ ነው ። ይህንንም ከባድ ንግ ግር በፊታችሁ መናገሬ በሚገባው መንገድ እናንተን ለመም ከር እንጂ ለማሳፈር ወይም ለማስቀየም በመጥፎ መንፈስ ተነ ስቼ አይደለም ። እንዲያውም አፍራሻውን ለዚህ ቅፌታ ላሳደ ረብኝ አጉል አቀባበላችሁ ከኔ ወገን መልካም ብድር ለመመ ለስ ስለምፈቅድ ለደረጃችሁ የሚገባውን ከበሬታ ሳልቀንስ በቅን ልቦና ላሰደስታችሁና ላገለግላችሁ የተዘጋጀሁ መሆኔን አሁንም ደጋግሜ እገልጽላችኋለሁ ።

ብትቀበሉት ከታላቅ ካሣ ስለምቆጥረው ይሆን ሐሣቤን እንዳት ነቅፉት በትህትና እለምናችኋለሁ» አላቸው ።

ይህ ዘይቤው ያልታወቀ የፈረሰኛው አነጋገር ኮረዳዎቹ በሕይወታቸው ውስጥ ሰምተውት የማያውቁት የአግብዎ ፈሊጥ ስለሆነባቸውና እንዲሁም የተራቀቀ አነጋገር የማይገባቸው ፣ ፊደል ያልቆጠሩ መሐይማን ስለነበሩ ፣ ከዚህም በስተቀር ለመ ቀለጃ የተሠራ የሚመስለውን ከሲታ መልኩን ከአነጋገሩ ጋር ሲያስተያዩት ይበልጥ የሚያስደንቃቸው ሆኖ ስላገኙት ፣ ያ ሁሉ ምክሩና ተግሣፁ ሳቃቸውን አባሰባቸው እንጂ እንዲጨምቱ አልረዳቸውም ነበር ። ይህም ከመጠን ያለፈ አሳሳቃቸው በቋፍ የተያዘውን የዶን ኪሾትን ቁጣ ስላነሳሳለው ልክ በዚያኑ ሰዓት ድርምቢታሙና ቦርጫሙ ፤ በጣምም የረጋው ሆቴልኛ በመካ ከላቸው ደርሶ ዶን ኪሾትን በትህትና እየቆላመጠ ተቀብሎ ለእንግድነት ባይጋብዘው ኖሮ የሳቁና የአታከራው ፍጻሜ ወደ መጥፎ ነጥብ አዘንብሎ ነበር ። ሆቴልኛውም አጠገባቸው እን ደደረሰ በመጀመሪያ አስተያየቱ ዶን ኪሾትን ሲመለከተው ከሲታ መልኩና የተዘበራረቀ ትጥቁ፡ የያዘው መሣሪያ ጥርቃ ሞነት ፤ የጋሻው ቆርፋዳነት ፤ የጦሩና የኰራይው ዝገት ፡ የጥ ሩራው ዝባዝንኪነት ፡ እንድነት ተደምሮ የሚያሰጠው ትርጉም የነሆለለ ዕብድ ወይም የጀለ ጤነኛ መሆኑን የሚያሳምን ስለነ በረ እሱም እንደኮረዳዎቹ በፈረሰኛው ቅጥ የለሽ አኳኋን ተገ ርሞ በሳቅ ሊፈነዳ ምንም ያህል አልቀረውም ነበር ። ነገር ግን ያንን ውጥንቅጥ መሣሪያ ታጥቆ በንዴት ሲንጐራደድ በማየቱ እውነተኛ ፍርሐት ስለተሰማው በተቻለ መጠን ከቁጣው ለማ ብረድ ሲል የፈረሰኛነት አቋቋሙንና የጀግንነት ባሕሪውን እያ ሞጋገስ ካገረመው በኋላ አከታተለና እንዲህ ሲል ጠየቀው ።

«የተከበሩት ፈረሰኛ ሆይ ፡ ክቡርነትዎ ከሰማይ እንደወ ረዱ መልአክ በድንገት እዚህ የተገኙበት ምክንያት ጊዜውና ልማዳችን እንደሚነግረን እሆቴላችን ለማደር የመጡ ስለሚ መስለን የእርስዎም ፍላጐት ይኸው እንደሆነ ከመኝታ አልጋ በስተቀር ሌላውን መስተንግዶ እንድንአዘጋጅልዎ ያሰኝዎትን መርጠው ለያዘዙን ይችላሉ ። የመኝታ አልጋ ግን በሆቴላ

ችን ጨርሶ የሌለ በመሆኑ ልናገኝልዎ ባለመቻላችን እናዝና ለን» አለው ።

ዶን ኪሾትም ይህ «ከምሽጉ ገዥ» ሆቴለኛውንና ሆቴሉን እንዲህ ብሎ ሰይሞአቸዋልና የቀረበለት የከበሬታና የትህትና አቀባበል በጣም ስላስደሰተው እንዲህ ሲል በጉራ አነጋገር መለሰለት ።

«እጅግ የተከበሩ የግንቡ ገዥ ሆይ! ድንገተኛ ለሆነው እን ግድነቴ አቀባበል እስከዚህ ድረስ ተጨንቀው ስላስቡልኝ ከልብ አመሰግንዎታለሁ ። ዳሩ ግን የፈረሰኛነት ተግባሬ ማናቸውንም ዓይነት ድሎት የማይጠይቅ ስለሆነ ምኞት ያለው መስተንግዶ እንዲያደርጉልኝ አላሳሰብዎትም ። ምክንያቱም የፈረሰኛነት ምኞቴና ጌጤ ይህ የታጠቅሁት መሣሪያዬ ስለሆነና እረፍቴም የዘወትር ውጊያና አደጋን ማሳደድ ስለሆነ ነው» አለው ።

ሆቴለኛው ግን «የግንቡ መስፍን (ካስቲላኖ) ብሎ ሲጠራው በሰማው ጊዜ በሌላ አጠራር ተረጉመውና » ይህ ሰው ካስቴ ላኖ ማለቱ የካስቴሌያ የጨዋ ልጅ መሰየው ይሆናል ሲል አሰበ ። እሱ ግን ልቦናው እንደሚያውቀው ያንዳሉሲያ አገር ተወላጅ ነበር ፤ እንዲያውም በተለይ ከአንዳሉሲያ ውስጥ ከቅ ዱስ ሎካር አውራጃ ባላገሮች የሚወለድ ሌብነታቸው እን ደካኩ ከሆኑት መካከል አንዱ ነበርና በበኩሉ እንዲህ ሲል መልሱን ሰጠው ። ክቡርነትዎ በመረጡት ዓይነት መኝታውን በሚጐረብጥ ኮረት ላይ እናነጥፍልዎታለን ፤ እንቅልፍዎም ዘወትር መንቃት ይሆናል ። ስለዚህ በሆቴላችን ውስጥ አንድ ሌሊት ብቻ ሳይሆን ያመቱን ለሊቶች በሙሉ እንቅልፍና ጸጥታ የሚነሳ ጫጫታ ስላለ ዓመቱን በሙሉ እንደነቁ ለመገኘት የሚ ያስችልዎ ምክንያት መኖሩን አረጋግጠው ከፈረስዎ ላይ ለመ ውረድ ይችላሉ» አለው ።

ይህን ተናግሮ ሲያበቃ ወዲያውኑ እርካቢን ሊይዝለት አጉ ነበሰ ። ዶን ኪሾትም ቀኑን በሙሉ አንዲት ጉርሻ ምግብ እንኳ ሳይቀምስ ጠሙን እንደዋለ ነበረና ብዙ ችግርና ድካም እንደተጫጫነው ከፈረሱ ላይ ወርዶ ወደሆቴሉ ገባ ። ገብቶም

እንደተቀመጠ ወዲያውኑ የፈረሱን ድካም አስታወሰና ሆቴለ ኛውን ጠርቶ እንዲህ ሲል አዘዘው ።

«ይህ ፈረስ ከዓለም ፈረሶች ይበልጥ የከበረና ጥሬ በመመ ገብ ተቀማጥሎ ያደገ ስለሆነ የሚያስፈልገውን መልካም አያያ ዝና ጥንቃቄ ያድርጉለት» አለው ። ሆቴለኛውም የፈረሱን ሁኔታ ሲመለከተው ዶን ኪሾት እንደሚለው ሆኖ ስላላገኘውና እንዲ ያውም አኩሌታውን ያህል እንኳ ስላልገመተው ከመጋጀነት የተሻለ አስተያየት አልሰጠውም ነበር ። ሆኖም ማኳሰሱን ሳያ በዛ ወደጋጣ ነድቶ ቦታ ካስያዘው በኋላ እንግዳው የሚሰጠውን ትእዛዝ ለማስማት ተመለሰ ። በዚህም ጊዜ ዶን ኪሾት ከኮረዳ ዎቹ ጋር ታርቆ የወዳጅነት ጭውውት ማድረስ ጀምሮ ነበር። እነሱም ቅድም በመሳቃቸው አስቀይመውት ለነበረው ካሣ ይሆን ዘንድ ፈረሰኛው ትጥቁን በሚፈታበት ጊዜ መሣሪያውን እየተቀበሉ በማስቀመጥ ይረዱት ነበር ። መጀመሪያ በትከሻ ውና በደረቱ ላይ ያለውን የብረት ልብስ ካወለቁለት በኋላ የራስ ቁሩን ደግሞ ሊያወልቁለት ሞከሩ ። ዳሩ ግን ከጭንቅላቱ እስከ አገጩ ድረስ ያጠለቀው ቅጥልጥል የራስ ቁር እንደማይወልቅ አድርጐ ባረንጓዴ ጥብጣብ ተብትቦ አሥሮት ስለነበረ ፥ የአን ገት ጌውም ጸጠሮ የጠበቀ በመሆኑ ፤ በሰንጢ ካልቆረጡት በስተቀር በፍጹም ለመፍታት የማይችሉት ስለሆነ እሱም እን ዲቆርጡበት ስላልፈቀደ ፤ በዚህ አኳኋን የራስ ቁሩን እንዳደረገ ሙሉን ሌሊት ታይቶ የማይታወቅ የአስቂኝነት መልክ እየጋበዘ በሆቴሉ የሠፈሩትን እንግዶች ሲያስቅቃቸው አደረ ። እነዚያ መሣሪያውን በመቀበልና ትጥቁን በመፍታት ሲረዱት የነበሩት ሁለት ኮረዳዎች የዶን ኪሾት አጫዋችነት በጣም ስላስደሰታቸው ካጠገቡ አልራቁም ነበርና ዶን ኪሾት በቀዣባሪነቱ እንደገመ ታቸው በዚህ የመስፍን ግንብ ውስጥ በመጀመሪያ የክብር ደረጃ ላይ የሚገኙ እመቤታትና ወይዛዝራት መሆናቸውን በማመን ልብ በሚነካ ዜማ እያንጐራጐረ ቀጥሎ ያለውን ግጥም ያሰማ ቸው ጀመር ።

በክብር አወዳድረው እንደ ዶን ኪሾት ፥
ወይዛዝርት በሥርዓት እያግለገሉት ፥

ምን ጊዜም አልታየ ሌላ ፈረሰኛ
እንዲህ የታደለ ተዋጊ ጦረኛ ።
ገና ከመውጣቱ ተነሰቶ ካገሩ ፣
ወይዛዝርት ለሱ በትጋት ሲያሰቡ ፣
ደንገጡሮች ደግሞ ሮንዚናን መገቡ ።

ይሀን ግጥም ካሰማ በኋላ እንዲህ ሲል ማስረዳቱን ቀጠለ «እመቤቶቹ ሆይ ! በሰማችሁት ግጥም ውስጥ«ሮንዚናን» ያል ኩት «ሮንዚናንቴ» የሚባለውን የፈረሴን ስም ነው ፣ »የማን ቻው ዶን ኪሾት» ማለት ደግሞ የኔ ስም ነው ። ምንም እንኳ እዚህ ተገኝቼ ለናንተ ጥቅምና አገልግሎት የሚሆን የተከበረ ተግባር በምፈጽምበት ጊዜ በመላ ማንነቴ እስክታውቁት ድረስ እኔ ተሸቀዳድሜ ልገልጥላችሁ ባልፈቅድም ፣ ላንቼሎቶ የሚባለው ጀግና ፈረሰኛ እጅግ የሚያኩራ ሞያ በመፈጸሙ የሱን ዝና ለማሞገስ ሲባል በተለይ የወጣውን ይሀን ጥንታዊ ግጥም ማሰማት አሁን ለምንገኝበት የደስታ ሰዓት የሚስማማ ሆኖ ስላገኘሁት ካሰብኩት ጊዜ በፊት ስሜንና ተግባሬን ልታ ውቁት ችላችኋል ። ይህም ግጥም በኛው ዘመን የወጣና የሰማው ሕዝብ ሁሉ ዳር እስከ ዳር የተደነቀበት ምርጥ ቃል ስለሆነ ምናልባት ከኔ በፊት በሌላ ሰው እንደበት ሲነገር ሳትሰሙት የቀራችሁ አይመስለኝም ። ይህም ቢሆን ለተከበራችሁት እመ ቤቶቹ አገልግሎቴን እንዳበረክትና የምታዘዝበትን የምፈጽም በት ጊዜ የሚያርስ ስለሆነ በዚያን ጊዜ የክንዴ አብነት ለና ንተ አገልግሎት የማውለውን ታዳጊነቴን ብሩህ እንደሚያደ ርገው አምናለሁ» አላቸው ።

ኮረዳዎቹ ግን ይህን የመሰለውን ቄንጠኛ አነጋገር መስ ማት ያልለመዱ ፍጹም መሐይማን ከመሆናቸው የተነሳ የግ ጥሙም ሆነ የሐተታው ምሥጢርና ትርጉም የሚገባቸው አል ነበሩም ። ስለዚህ ለግጥሙም ሆነ ለሐተታው የሚገባውን አድ ናቆትና ግምት በመስጠት አንዳች መልስ ሊመልሱለት ሳይችሉ እርስ በርሳቸው እየተጠቃቀሱ በሳቅ ታፍነው በዝምታ ሲያ ዳምጡት ከቆዩ በኋላ በመጨረሻው እራቱን ለመብላት ይፈቅድ እንደሆነ ጠየቁት ። ዶን ኪሾትም ጨዋታው ባያዘነጋው ኖሮ

ሪው ክፉኛ እየሞረመረው ነበርና «የምትሰጡኝን ግናችሁ ገና ምግብ በደስታ እበላለሁ ፣ ምክንያቱም ስሕተት አይሆ ልብኝ እንጂ የተግባሬ አፈጻጸም እንዲቃና ምግብ በጣም የሚ ያስፈልገኝ ነው » አላቸው ።

እንዳጋጣሚ ደግሞ ቀኑ ዓርብ ስለነበረ በየሆቴሎቹ የሚ ዘጋጀው ምግብ እንደ አገሩ አጠራር ለየቅልነት አንዱ ሥፍራ የአሣ ድርቆሽ ፣ ሌላው ዘንድ የአሣ እንፍርፍር ወይም የአሣ ወጥ እየተባለ ስሙ ይለዋወጣል እንጂ የሚሠራው በዚያው ጨአሣ ቋንጣ ብቻ ነበረና ስለዚህ ሌላ ዓይነት ዓሣ ስለሌላቸው የትንንሽ ዓሣ ቋንጣ እንፍርፍር ይፈቅዱ እንደሆነ ጠየቁት ። እሱም የቀኑ ረሐብ ምግብ እንዲያማርጥ የማይፈቅድለት ስለ ሆነ እንዲህ ሲል መለሰላቸው ።

«እነዚህ የዓሣ ቋንጣ እንፍርፍሮች በርከት ያሉ ከሆኑ ያንድ ሙሉ ምግብ ያህል አጥጋቢነት ሳይኖራቸው አይቀርም፣ ምክንያቱም ጠንካራውን የፈረሰኛነት ተግባር የሚያከናውን ሰው ሁሉ የኑሮ ምኞት ስለሌለው ጦሙን ከማደር የሚያድነ ውን ምግብ ካገኘ ዕድሉን አመስግኖ መብላት አለበት ። ለምሳሌ ያህር ብር ምንዛሪ ቢሰጡኝ ወይም ድፍኑን አሥር ብር ቢሰጡኝ ለኔ ጠቃሚነቱ እኩል ነው ። ደግሞም እነዚህ የትንንሽ ዓሣ ቋንጣ እንፍርፍሮች እንደ ጥጃ ሥጋ ቢሆኑ ኖሮ ከወይፈን ሥጋ የሚሻሉ የፍየል ግልገል ሥጋ ቢሆኑ ኖሮ ከሙኩት ፍየል የሚሻሉ ይሆኑ ነበር ማለት ነው ። የሆነ ሆኖ በቶሎ አቅርቡ ልኝ ምክንያቱም የመንገድ ድካምና የጦር መሣሪያ ሸክም በባዶ ሆድ የማቻል አይደለም» አላቸው ።

ከዚህ በኋላ ከሆቴሉ በራፍ አልፍ አደርገው ነፋሻ ሥፍራ ላይ ገበታ አስናዱለት ። ቀጥሎም ሆቴሉኛው በደንብ ያልራሰና አጉል ሆኖ የበሰለ ያንድ ሰው ድርሻ የሣላ ቋንጣ እንፍርፍርና እንደዚሁም እንደያዘው መሣሪያ የሻገተና የጠቆረ አንድ ከራራ ዳቦ አቀረበለት ። ዶን ኪሾትም ይህን አሸርባሸር ምግብ ላይነት መብላት ጀመረ ። ነገር ግን አበላሉን ለሚመለከተው ሰው በጣም የሚያስቅ ነበር ። ምክንያቱም የራስ ቁሩን ለማውለቅ ባለመቻሉ እራሱ ላይ እንዳደረገ የፊት መከለያውን ብቻ ወደ

ላይ ገልጦት ስለነበረ አገሙን የሚሸፍነው ታትካላ ብረት ወደ ፊት አሞጥሙጦ ምግቡን ወዳፉ ለማድረስ እንቅፋት ሆኖ ስላ ስቸገረው ሌላ ሰው በብልሃት እዲያጕርሰው አስፈልጕ አንደኛ ይቱ ኮረዳ እንድታጕርሰው ስለተደረገ ነው ።

ኮረዳይቱም ሳቂታ ስለሆነች ሣቋ እንዳያመልጣትና እን ደገና እንዳይጣሱ በመስጋት በተቻላት መጠን ተጠንቅቃ ምግ ቡን ተቀብላ ማጕረስ ጀመረች ። በተለይ ደግሞ የመጠጥ አሰ ጣጡ ዘዴ የባሰ ችግር ሆኖ ስለተገኘ ሦቱለኛው አንድ ሽን በቆ ፈልጕ መካከሉን ነድሎ አንዱን ጫፍ በአፍ ውስጥ ሽጕሮ በሁለተኛው ጫፍ በኩል የወይን ጠጅ እየተንቆረቆረለት እን ዲጠጣ ባያደርግ ኖሮ የቀረበለትን መጠጥ ሳይጠጣው እንደሚ መለስ የታወቀ ነበር ።

ይህ ሁሉ ሲሆን የራስ ቁሩ ጥብጣብ አያቆረጥበት እንጂ ፈረሰኛው በአመጋገብ ላይ የደረሰበትን ችግር ሁሉ ሳይማረር ታግሶ ነበር ። ምክንያቱም ሥራው ግብዝ መሆኑን ልቦናው ስለ ሚያውቅ ጥብጣቡ የተቆረጠ እንደሆነ ለማግሥቱ ጕዞው እንደነ በረ አድርጕ ለማሠር የሚያስችግረው ከመሆኑም በላይ ምናል ባት ደግሞ ከራሱ ላይ አውርዶ ቢያስቀምጠውና ድንገት አን ዳች ነገር ቢወድቅበት እንደሚጠረመስ ስለሠጋ ነው ።

ፈረሰኛው ምግቡን በሚበላበት ጊዜ የሦቱሉ አሳማ ሠናጊ ከየአንግዶቹ ገንዘብ የመለመን ልምድ ነበረውና ወደ ሦቱሉ መጥቶ ዋሽንቱን መዘዘና የእረኞችን ስልት እየነፋ ማሰማት ጀመረ ። ዶን ኪሾትም ይህን የዋሽንት ንፍ በመስማቱ እጅግ ደስ ስላለው ይህ ያረፈበት ቤት በጣም የተከበረና ስመ ጥር የሆነ የመስፍን ግንብ መሆኑን ከቀድሞው ይበልጥ እያመነ ሄደ ። እንዲሁም ደግሞ በተለይ የእሱን እንግድነት ለማክበር ሲባል ልዩ የሙዚቃ ድርጅት ተሠናድቶ መዚቀኞቹ በየተራቸው እየ ተጠሩ ስልታቸውን በማሰማት ከፍ ያለ ግብዣ የተደረገለት መሆኑን በሙሉ ልብ ለማመን በቃ ። የግብዣውንም ታላቅነት ሲያመዛዝነው ለእራቱ የተሰጠው ከአሳ ቋንጣ እንፍርፍር የተ ሠራ መሆኑ ቀርቶ በተለይ ከትኩስ አሳ የተሠራ የጨዋ ምግብ መሆኑንና የጠቆረውን ዳቦ ስለብስኩት ፥ ኮረዳዎቹን ስለወይ

ዛርት ፥ ሦቱለኛውን ስለ ግንቡ መስፍን እየተረጕመ የምግቡን ጥራትና ዓይነት ፥ የሰዎቹንም ክብርና መልክ በዕብደት አስተ ያየቱ እንደመሰለው አድርጕ ለየወጣቸው ።

ይህን የመሰለ የበለጸገ ግብዣና ሌላውም የክብር አቀባ በል ሁሉ ለዙዋሪ ፈረሰኞች ተግባር ማበረታቻና ግዳቢያ እን ዲሆን መሳፍንቱ ሁሉ በቅንዓት የሚጠብቁት ወግና ልማድ መሆኑን በማስብ ፥ እሱም ይህንኑ በድፍን ዓለም የታወቀው ጉና እንዲሁም ድፍረትንና ቆራጥነትን የሚጠይቅ ተግባር መርመ ሯያዙ ለዕድሉ ከፍተኛነት ኩራትና ትምክህት በልቡ እሳ ደረ ። ዳሩ ግን የፈረሰኛነት ክህነት ከመቀበሉ በፊት ከግናኛ ውም ወደረኛ ጋር የጦር ግጥሚያ ለማድረግ ሕጉ የማይፈት ድለት መሆኑንና እንዲሁም እስካሁን ድረስ ይህን እስኸይ የክህነት ቡራኬ ሳይቀበል ወረጋውን የሚገኝ ፈረሰኛ መሆኑን እያሰበ የሕሊና ዕረፍት ማጣቱ ባይከነክነው ኖሮ ይህ የመጀ መሪያው ቀን ብዙ ቁም ነገርና ከፍ ያለ ጥቅም ያለበት ጉዳይ እንደተፈጸመበት እንጂ በከንቱ የባከነ አለመሆኑን ተረድቶት ነበር ።

ምዕራፍ 3

ዶን ኪሾት የተካነ ፈረሰኛ ለመሆን የቻለበት

የለበጣ ዘዴ ይተረካል ።

ዶን ኪሾት እስከ ዛሬ ድረስ የተካነ ፈረሰኛ አለመሆኑ በጣም እየከነከነው ያንን ፍርፋሪና ሙጣጭ የጓሮ ምግብ በች ካላ በልቶ ከጨረሰ በኋላ ሆቴለኛውን ጠርቶ ወደፈረሶች ጋጣ ገብተው በሩን ዘግተው ቆይታ አደረጉ ። ወዲያውም ዶን ኪሾት ከሆቴለኛው ጫማ ላይ ተደፋና እንዲህ ሲል ልመናውን ማቅ ረብ ጀመረ ።

«ጀግናው ፈረሰኛ ሆይ ፣ (ሆቴለኛውን) በተለመደው ሠፊ ቸርነትዎ ሊያደርጉልኝ የሚችሉትንና የሚመሰገኑበትን ፣ ከሰው ልጅነትዎ በጐ ፈቃደኛነት የሚመነጨውን ፣ የክህነት ቡራኬ ካልሰጡኝ በስተቀር ከዚህ ከወደቅሁበት ጫማዎ ላይ አልነሳም ። ይህም የምጠይቀው ቡራኬ የሚገባኝ መሆኑን የሰው ልጅ ፍርዳዊ አስተያየት እንደሚያጸድቀው አይጠራጠሩ» አለው ።

ሆቴለኛው ግን ይህ እንግዳ ሰው በዚህ አኳኋን ጫማው ላይ ተደፍቶ ይህን መላው ያልታወቀ ልመናውን ሲያቀርብለት በመስማቱ ምን እንደሚለውና ምንስ እንደሚያደርግለት ግራ ገብቶት ስለተጨነቀ ከጫማው ላይ እንዲነሳለት ብቻ ይለማመጠው ጀመር ። ያኛው ግን የጠየቀውን የክህነት ቡራኬ የሚሰጠው ለመሆኑ ቃል ኪዳን ካልገባለት በስተቀር የማይነሳ ችክ ስለሆነ በማናቸውም መንገድ ቶሎ ለመገላገል ሲል የጠየቀውን ውሉ የሚፈጽምለት መሆኑን አረጋገጠለት ። ዶን ኪሾትም ይህን ተሰፋ ተመርኩዞ ተነሳና እንዲህ ሲል ፍላጐቱን ፣ በዝርዝር ማስረዳት ጀመረ ።

«ከፀጋዊነትዎ ዘንድ በሙሉ ተስፋ የጠበቅሁትን የክህነት ቡራኬ እንድቀበል ከልብ ስለፈቀዱልኝ እጅግ ከፍ ያለ ውለታ ዋለውብኛል ። ስለዚህ እኔ ይገባኛል ስል የጠየቅሁትንና በቸርነትዎም አጸድቀው የፈቀዱልኝን ይህን ፀጋዊ ስጦታ ስተበል ነገ ጠዋት የተካንሁ ፈረሰኛ ለመሆን የሚያበቃኝ ስለሆነ ዛሬ ሌሊት በዚህ በግንብዎ ሰገነት ላይ ወጥቼ የክህነት ፈተናዬን ዋዜማ እጀምራለሁ ። በማግሥቱም ቅድም እንደአልኩት በተግባራዊ ግዴታ መወረት በአራቱ የዓለም ማእዘናት እየተዘዋወርኩ አጋጣሚዬን በመፈለግ እርዳታ ለሚያሻቸው ተረጅዎችና አቅም ለሌላቸው ደካሞች ጥቅምና ድጋፍ የሚሆን አገልግሎት ለማበርከት ያደረብኝ ብርቱ ፍላጐት ይፈጸማል ። ይህ የፈረሰኛነት ግዴታና የዘመሪ ፈረሰኞችም ተግባር በሰብአዊ አገልግሎት ውስጥ የላቀ ሞያ እንደመሆኑ መጠን እኔም የዚሁ ክፍል ባልደረባ ለመሆን ይህንኑ መርጬ ተግባሬ አድርጌ በመያዜ በእጅጉ እኩራበታለሁ» ብሎ ንግግሩን ጨረሰ ።

ዶን ኪሾት ይህን ሐተታ በሚናገርበት ጊዜ ሆቴለኛው እዝግሚያውን በእርጋታ ያስተውል ነበርና መቸም አስቀድሞን እንደተናገርነው ሆቴለኛው ማሽንክ ተኩላ በመሆኑ ከመጀመሪያው ግንኙነታቸው ጀምሮ የእንግዳውን አእምሮ ደካማነት ተጠራጥሮ ለማበድ አንድ ዓርብ የቀረው መሆኑን ተረድቶት ነበርና በሃሳቡ አገላለጥ ብርሃን እንደተመለከተው እብድነቴን ሙሉ በሙሉ ለማረጋገጥ ከቻለ በኋላ በጀርባው ጥቂት እንዲሳቅበት ለማድረግና በሆቴሉም የሠፈሩት እንግዶች የጊዜ ማሳለፊያ ጨዋታ እንዲጋበዙ በማለት ከፈረሰኞች ተግባር ጋር እግባብ ያለውን እንዳንድ ነገር በመቀላቀል የማሾፊያ ንግግሩን አሰናድቶ የተዘበራረቀውን የዶን ኪሾት መንፈስ የባሰ ለማነሳሳል ሲል የፈረሰኛነት ክህነት ቡራኬ መፈለጉና መጠየቁም ፍጹም ትክክለኛ መሆኑንና እንዲሁም አቋቋሙ እንደሚመሰረረና እሱም አምሳያው ሆኖ እንደሚታየው በዚህ እጅግ ከፍተኛ በሆነው ተግባር ደረጃ ላይ ለማገኙት ዘዋሪ ፈረሰኞች ሁሉ ይህን ዓይነት የክህነት ዝግጅት እንዲኖራቸው ተገቢና ሕጋዊ መሆኑን አሰረዳው ። አከታትሎም የራሱን ያለፈ ሕይወት ታሪኩን በመዘርዘር እንዲህ እያለ ዶን ኪሾትን ይሰብከው ጀመር ።

«እኔም እራሴ» ሲል ንግግሩን ቀጠለና» በጐልማሳነት እድሜዬ በልዩ ልዩ የዓለም ክፍሎች ወዲያና ወዲህ እየተዘዋ ወርኩ አጋጣሚዬን በመፈለግ ይህን የተከበረ ተግባር አከናው ኛለሁ ። በዚያን ጊዜ በማላጋ አራዳ ውስጥ ፣ በሪያራን ደሴት፣ በሲቪሊያ አደባባይ ፣ በሲጐቪያ ገበያ ፣ በሻሴንሳ የዘይት መቸ ርቸሪያ ፣ በግራናዳ አካባቢ ፣ በሳንሎካር መደብር ፣ በጐርዶሻ የባዝራ ተራ ፣ በቶሌዶ ያሮጌ ጨርቃ ጨርቅ ተራ ፣ በነዚህና በሌሎችም የገዲቃባ መገበያያ ሥፍራዎች ሁሉ ወንብጂበታ ለሁ ። ይህንንም ሳደርግ አያሌ አምባጓሮ እያስነሳሁ በማበጥ ሴቶችን እያማገጥሁና እያባለግሁ የዋሆችን እያጭበረበርኩ ፣ ባደረግሁት የውምብድና ሞያዬ በድፍን እስፓኒያ ፍርድ ቤቶች ስሜን ለማስጠራት እስከበቃሁበት ጊዜ ድረስ የእግሮቹ ፈጣን ነት ፣ የእጆቹ አሰልጣጠንነት ተወዳዳሪ የሌለው አድናቆት አትርፌ ውልኝ ነበር ። ከዚያ ወዲህ ግን እጅግ በሚያሰለችና በሚያን ገፈግፍ ምክንያት ይህን ሁሉ ተግባሬን ያለ ውዴታዬ እርግፍ አድርጌ ትቼ በዚህ የራሴ ንብረት በሆነው ግንብ ውስጥ ለመ ኖር ቆርጪ መጣሁ ። አኗኗሬም በራሴ ጥረትና ግረት ፣ እንዲ ሁም የተግባር ወዳጆቼ በሆኑት ሥውር እርዳታ ፣ በተለይም ደግሞ በየጊዜው በዚህ መንገድ ሲተላለፉ ጉራ የሚሉትን ዘዋሪ ፈረሰኞች በማናቸውም ዓይነትና ደረጃ ላይ የሚገኙም ቢሆኑ ሳልመርጥና ሳላበላልጥ ትክክል በሆነ አስተያየት እየተ ቀበልኩ በማስተናግድበት ጊዜ እነሱ ደግሞ ወሮታዬን በኪሣ ቸው የያዙትን ገንዘብ ከኔ ጋር ተካፍለው ለመብላት የሚወዱ ትን ሁሉ በተለይ ተሸቆጥቁጬ እያስተናበርኩና በለጋስነታቸ ውም የሚሰጡኝን ችሮታ ሳልንቅና ሳላቃልል አመስግኜ እየተ ቀልኩ ነው «ካለ በኋላ ንግግሩን በመቀጠል» በግንቡ አናት ላይ ሊኖር የሚገባው የፈተና ዋዜማ ማድረጊያው ሰገነት ስለአረጀብኝ እዲስ ለማሠራት አስቤ አፍርሼዋለሁ ። ስለዚህ የዋዜማው አስፈላጊነት የማይቀር ጉዳይ በመሆኑ በማናቸውም ገላጣ ሥፍራ ላይ ሊደረግ ይቻላል» በማለት ፣ ለዛሬ ሌሊት በዚሁ በግንቡ ግቢ ውስጥ ባለው መስክ ላይ ዋዜማውን ለመ ጀመር መቻሉንና በማሥቱም ደግሞ የጊዜው አጋጣሚ የፈ ቀደ የሆነ እንደሆነ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅና ለሌላም ፈረሰኛ ባልተደረገለት አኳኋን የክህነት ቡራኬ መስጫው አዲስ

ሥን ሥርዓት የሚፈጸምለት መሆኑን አረጋገጠለት ። ከዚህም አስከትሎ በገንዘብ ረገድ እንዴት እንደሆነ ዶን ኪሾትን ጠየ ቀው ።

ዶን ኪሾትም ከዚህ ቀደም ባንበባቸው የፈረሰኛነት ታሪክ መጻሕፍት ውስጥ ገንዘብ በኪሱ ይዞ የሚሄድ ዙዋሪ ፈረሰኛ መኖሩን ስላልተረዳ በዚህ ምክንያት እንዴት ቤሳ እንኳ የሌለው መሆኑን ገለጠለት ። ሦቴለኛው ግን «እጅግ ተሳስተሃል» ሲል መለሰለትና ቀጥሎ ያለውን ማስረዳት ጀመረ ።

«ምንም እንኳ ይህን የመሳሰለው ጉዳይ በታሪክ ውስጥ ተጽፎ ባይገኝ ፣ ገንዘብ ለሰው ልጅ መግደርደሪያ ካስፈላጊነት በላይ ሆኖ የተመረጠ መሣሪያ መሆኑ ተረጋግጦ የታወቀ ነው ። ምናልባትም በታሪክ ጸሐፊዎች አስተያየት ይህን አስፈላጊነቱ እጅግ ግልጥ ሆኖ የሚታየውን የገንዘብ ጠቃሚነት ወሰን ሰዎች እንዲያውቁት ለማድረግ ልዩ ማስገንዘቢያ ለመጻፍ ያል ፈቀዱበት ምክንያት እንኳንስ ዙዋሪ ፈረሰኛ ቀርቶ ተራ መን ገደኛም ቢሆን ለስንቁ የሚሆን ገንዘብ ሳይቋጥር ባዶ እጁን ከቤቱ የሚወጣ ሰው አለመኖሩን አሳምረው ስለሚያውቁት ነው ። ከዚህም በስተቀር ገንዘብ ለያንዳንዱ ሰው ራስ ማስቻያ ጠቃሚነቱ ተፈትኖ እስከዛሬ የዘለቀውንና የግል ግዴታው የሆ ነውን ጉዳይ ይዘነጋዋል በማለት የማይገባ ማስጠንቀቂያ ቢሰው ከፍ ያለ ነቀፈታ የሚደርስባቸው መሆኑን ስለአመኑበት ነው ። ስለዚህ ዙዋሪ ፈረሰኞች ሁሉ በጉዞአቸው ላይ የሚያጋጥማቸ ውን ችግር የሚያስወግዱበት የስንቅ ገንዘብና ንጹሕ ሸሚዝ ሳይዙ ይጓዛሉ ብሎ ማመን በጣም ወደ መታለል የሚያደርስ እምነት ነው ። ይህን በማሰብ ዙዋሪ ፈረሰኞች ሁሉ እያሌ የታ ሪክ መጻሕፍት እንደሚመስክሩላቸው በማናቸውም ጊዜ የሚ ተማመኑበት በደንብ የታጨቀ የገንዘብ ቦርሳና እንዲሁም የግ ፈራረቂያ ንጹሕ ሸሚዝ ፣ ለቁስል ማከሚያ የሚሆን በያይኑ መድኃኒት ያለበት ኩሮጆ ይዘው እንደሚጓዙ እርግጠኛ መሆን ይችላሉ ። ምክንያቱም ፣ በዙሪታቸው ላይ ለሚደርስባቸው አደጋ ምናልባት አንድ አዋቂ አስማተኛ ወዳጅ ያላቸው ፈረሰኞች ሆነው ይህኑ የደረሰባቸውን አደጋ በጥንቆላው አይቶ በደመና ላይ ተንሳፍፈው አየሩን አቋርጠው ለእርዳታ የሚደርሱላት

አንዲት ልጃገረድ ወይም አንድ ድንክ ባንደ ብልቃጥ የተሞላ ልዩ ውሃ አስይዞ ከላከላቸውና ከዚህም ወሃ ጥቂት ጉንጨት እንደጠጡ ወዲያውኑ ቁስላቸው ድኖ ወይም ስብራታቸው ተጠ ግኖ ፈጽሞ እንዳልነበረና ምንም እንዳልነካቸው ሆኖ እንዲሽ ርላቸው ካላደረገ በስተቀር ጅው ያለ በረሃ በሚያቋርጡበት ጊዜ ወይም ሰው በሌለበት ገጠር ላይ ከጠላት ጋር በድን ገት ግጭት ተሞክተው በሚቆስሉበት ጊዜ የሚያክማቸው ሰው ስለማያገኙ የደረሰባቸው አደጋ ጸንቶ ለሞት አሳልፎ የሚሰጣ ቸው ስለሚሆን ነው ። ይህም ቢሆን ጥንታዊ ዘዋሪ ፈረሰኛ ሁሉ ዘወትር በብልህ ሰው የምክር እርዳታ ላይ ሙሉ እምነት ማድ ረግ የማይበቃ መሆኑን ስለሚያውቁ ጋሻ ጃግሬዎቻቸው በቂ የስንቅ ገንዘብና ሌላም አስፈላጊ የሆነውን መድኃኒት ለምሳሌ እንደመታከሚያ ሻሽ ፣ እንደቅባት ያለ መሰናዶ አስይዘው እን ዲከተሏቸው ማድረግ ዋና ጥንቃቄ መሆኑን አልዘነጉትም ። ምና ልባት እንኳ ጋሻ ጃግሬ የሌላቸው ጠልጣላ ፈረሰኞች ቢሆኑ ይህም አጋጥሞ የማያውቅ ብርቅ ነገር ነው ። ይህን የተዘረዘ ረውን የመንገድ መሰናዶ ሁሉ ባንድ በማይታይ ቦርሳ ውስጥ ከትተው በፈረሳቸው ውደሳ ላይ አመቻችተው እንደ ውድ እቃና እንደ ከበረ ጌጣጌጥ አስመስለው እነርሱ እራሳቸው ይይ ዙታል ። በዚህ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በተለምዶ ዙዋሪ ፈረሰኞች የመንገድ ሳጥን መያዝ የማይፈቀድላቸው ስለሆነ ነው እያለ ለወደፊቱ ገንዘብና መለመጫ ልብስ ሳይዝ ፣ ጋሻ ጃግሬም ሳያስከትል ፣ በዚህ አኳኋን ጉዞውን እንዳይጀምርና ይህንንም ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ወደፊት በሚደርስበት ሁኔታ አስገንዛቢነት ይህን ምክር ሳይፈጽም ቢቀር ኖሮ እጅግ አድ ርጐ የሚያዐጽት ጉዳት ይደርስበት እንደነበረ በማስረዳት አጥ ብቆ መክረው ። እንዲያውም ከጥቂት ጊዜ በኋላ በሚቀበለው የክህነት ቡራኬ ምክንያት በትእዛዙ ሥር የሚገኝ ደቀ መዝ ሙሩ ስለሆነ መምከር ብቻ ሳይሆን ይህን የተባለውን ሁሉ ሳያ ጓድል ተጠንቅቆ እንዲፈጽም በቀጥታ ሊያዝዘው የሚችል መሆ ኑን አስታወቀው ።

ዶን ኪሾትም የተመከረውን ሁሉ አንዳች ነገር ሳያጓድል በትክክል የሚፈጽም መሆኑን የመላ ቃሉን ከሰጠ በኋላ ወዲ

ያው ወደ ውጭ ወጥቶ ከሆቴሉ አቅራቢያ በሚገኘው መስክ ላይ የፈተና ዋዜማውን ልምምድ ለመጀመር ዝግጅቱን አሰናዳ ። አስቀድሞ መሣሪያዎቹን በፍጥነት ሰበሰበና ከወሃው ጉድጓድ አጠገብ በሚገኘው የድንጋይ ገንዳ ላይ አስደግፎ አስቀመጠ ። ቀጥሎም ጋሻውን አነገበውና ፣ ጦሩን ጨበጠና በኩሩነት መን ፈስ በገንዳው አኳያ ወዲያና ወዲህ ይንጐራደድ ጀመር ። ይህ ነንም ንቅናቄ በሚያደርግበት ጊዜ ቀኑ ወደ መሸቱ እየተቃ ረበ ሄደ ። ሆቴልኛው እዚያው ደጅ ቆሞ የአዲሱን እንግዳ ልውጥ ሁኔታ ከተመለከተ በኋላ በአኳኋኑ እጅግ እንደተገረመ ወደ ሆቴሉ ገባና የሰውዬውን ወፈፍተኛነትና ሌላውን የእብደት ጠባይ፡ እንዲሁም ነገ የተካነ ፈረሰኛ ለመሆን ዛሬ ሌሊት በመስኩ ላይ ለማድረግ እንዲፈቀድለት የጠየቀውን የፈተና ዋዜማ ፣ የክህነቱ ቡራኬ የሚፈጸምበትን የለበጣ ዘዴ ጭምር በሆቴሉ ለነበሩት ሰዎች ሁሉ አወራላቸው ። ሰዎቹም ይህን የመሰለ ያል ተለመደ የእብደት ጠባይ በመስማታቸው በነገሩ እጅግ ስለተ ደነቁ ወደሰውዬው ቀርበው ጉዳን ለማየት ቸኩለው እየተጋፉ ከሆቴሉ ወጡና ሁኔታውን ይመለከቱ ጀመር ። እሱም በዚያን ጊዜ በተጀነነ መንፈስ እየተንጐራደደ ፣ እንዲሁም ደግሞ አንድ እፍታ ቆም ብሎ ጦሩን እየተመረኩዘ ፣ ፊቱን አኩስትሮ ረዘም ላለ ጊዜ መሣሪያዎቹን አትኩሮ ሲመለከት ያዩት ነበር ። ይህም ሲሆን ቀኑ ፈጽሞ ጨለመ ። ይሁን እንጂ በዚያን ጊዜ የጫጫ ችው ደማቅ ጨረቃ ከፀሐይ ጋር የሚወዳደር ብርሃን ስለነበ ራት በዚያን ሰዓትም ቢሆን አዲሱ ፈረሰኛ የሚያደርገውን ንቅ ናቄ ሁሉ ተመልካቾቹ ያለችግር ለማየት ችለው ነበር ። ሁኔ ታው በዚህ አኳኋን እንደቀጠለ በመከለሱ በሆቴሉ ውስጥ ከመ ፈራት ነጋዴዎች ያንደኛው ጐረዶማ በመስኩ ላይ ይገቡ የነበ ሩትን እጋስሶች ውሃ ለማጠጣት አስበና እየነዳ ወደ ጉድጓዱ አመራ ። ከብቶቹንም እንደልቡ ለማጠጣት የሚያመቸው ከሁሉ በፊት ከገንዳው ላይ የተደገፉትን መሣሪያዎች አንስቶ ሌላ ሥፍራ በማስቀመጥ ስለሆነ ሥራ ፈቱ ይህንኑ ለማድረግ ወደ መሣሪያዎቹ መጠጋቱን ዶን ኪሾት በተመለከተ ጊዜ እንዲህ ሲል ጮኾ አስጠነቀቀው ።

«አንተ ደፋሩ ፈረሰኛ ሆይ! ማንም ብትሆን ወዮልህ ፤ አመጣጥህ እንደሚያሳምነኝ ምንጊዜም ጉራዬውን ከወገቡ ላይ ፈትቶ የማያውቀውን የመራዡን ፈረሰኛ መሣሪያ ለመንካት የመጣህ ስለሚመስል የምታደርገው ድርጊት አደገኛ መዘዝ የሚያስከትልብህ መሆኑን አይተህ ተጠንቀቅ ። ስለ ክልፍልፍነትህ ቅጣት ነፍስህን ለመክፈል የማትፈቅድ እንደሆንክ መሣሪያዎቹን ከሥፍራው እንዳታንቀሳቅሳቸው» አለው ።

ሥራ ፈቱ ግን ይህን ደህና ማስጠንቀቂያ ከቁም ነገር ቆጥሮ አላከበረውም ነበር ። ዳሩ ግን ማስጠንቀቂያውን ሳይንት ቢያከብረው ኖሮ ይህ ከበሬታ ለጤናው የሚጠቅመው አብነት ይሆ ነው ነበር ። እንዲያውም ማስጠንቀቂያውን አመናጭቆ የመ ሣሪዎቹን ማንነቻ እየጨበጠ አሽቀንጥሮ ይወረውራቸው ጀመር ። ዶን ኪሾትም በዚህ አኳኋን ተንቆ ክብሩ በመደፈሩ በንዴት ስለጠፈ ዓይናቹን ወደሰማይ አቅንቶ ሃሳቡን ወደ እመቤቱ ዱል ቺኒያ መለሰና ሁኔታው ያስረዳው ይህንኑ ስለሆነ ነው እንዲህ አለ ።

«እመቤቴ ሆይ! ይህ ባንቺ ውቃቢ የተማጠነው ደረት አውን በሚጋፈጠው ግጥሚያ ላይ የሚያስፈልገውን እርዳታሽን እን ዳትነፍገው ይለምንሻል ። በዚህ በመጀመሪያ የመፈጣፈጥ አደጋ ላይ ሲገኝ የመንፈስ እገዛሽና ጥበቃሽ እንዳይጓደልበት ይማ ጠንሻል» ብሎ ተለማመነ ።

ይህንና ሌላም ይህን የመሳሰለውን ሐተታ በሚናገርበት ጊዜ ጋሻውን አስወስዶ ነበርና ጦሩን ብቻ በሁለት እጁ ጨብጦ እየተንደረደረ በብርቱ አወራወር የጦርያማውን ጭንቅላት ተር ትሮ ጣለው ። ያኛውም ከፋኛ ተጉድቶ ደም አስከርቶ እስ ኪወድቅ ድረስ ተጉዳ ። የዚህን ዓይነት አመታት ሁለተኛ ጊዜ ደግሞት ቢሆን ኖሮ ጉሪደማው ሐኪም እያሻውም ነበር ማለት ነው ።

ይህን አደጋ ከጣለ በኋላ መሣሪያዎቹን ከወደቁበት ለቅሞ እዚያው እንበሩበት ሥፍራ መልሶ አስቀመጠና በቀድሞው ሠላ ማዊነቱ መንጉራደዱን ቀጠለ ። ይህን የደረሰውን አደጋ ያልሰማ

ሁለተኛው ጉርደማ ደግሞ ወደ ጎንዳው መጣ ምክንያቱም የመጀ መሪያው ጉርደማ ሕሊናውን በመሳቱ የርዳታ ድምጽ ለማሰ ማት ባለመቻሉ ነው ። የሱም አመጣጥ እንደ ጓደኛው አጋሰ ችን ውሃ ለማጠጣት ስለነበረ ጎንዳውን ነፃ ለማድረግ መሣሪያ ዎቹን በሚያነሳበት ጊዜ ዶን ኪሾት አንዳች የማስጠንቀቂያ ቃል ሳይናገርና አንዳችም የመንፈስ እርዳታ ሳይጠይቅ ጋሻውን ነጥቆ እንደገና እቦታው አስቀመጠና ጦሩን አንስቶ ሁለተኛውን ጉር ደማ አናቱ ላይ መታው ። ምንም እንኳ በንዴቱ ብዛት ባይገ ነጣጥለው አራት ቦታ ላይ ፈንክቶታል ። በዚህን ጊዜ ጩኸት ስለበረከተ በሆቴሉ የነበሩት ሰዎችና ሆቴለኛውም ጭምር ሰምተው ለእርዳታ እየተሯሯጡ ደረሱ ። የባሰውን ደግሞ ሆቴ ለኛው ይህን የመሰለ አደጋ በምድረ ግቢው ውስጥ ተፈጽሞ በማየቱ ክፉኛ ደነገጠ ። ዶን ኪሾትም ይህን ግርግር ሲመል ከት የበለጠ ጥንቃቄ ማድረግ ስላስፈለገው ጋሻውን አንስቶ አነገበና የጉራዴውን መከድ ጨበጠና አንፈራጥጦ ቁሞ እን ዲህ አለ ።

«የውበት ንግሥት ሆይ! ለሚመታው ልቤ ኃይል ሰጪና አዳኙሪ የሆንሽው እመቤቴ ሆይ! እጅግ አስጨናቂና አደገኛ የሆነ ግጥሚያ ለሚጠባበቀው ለዚህ ባሪያሽ ለሆነው ፈረሰኛ የእርዳታ ፊትሽን መለስ አድርገሽ ብርታት በሚሰጡት ዓይና ችሽ ልትጐበኝው የሚገባሽ ጊዜው አሁን ነው»።

በዚህ አነጋገር በሱ ግምት ውስጣዊ ኃይሉን በጣም የሚያ በረታ የጥንካሬና የግለት መንፈስ እንደተወረወበት ስላመነ ሌላው ቀርቶ በዓለም ላይ ያሉት ጉሪደማዎች ሁሉ ተሰብስ በው ቢሠሩበት እንኳ አንዲት እርምጃ ወደ ኋላው እንደማያ ፈገፍግ በልቡናው አረጋገጠ ። የቁስለኞቹም ጓደኞች የደረሰውን አደጋ በተመለከቱ ጊዜ ጥቂት እራቅ ብለው ተሠልፈው በሩምታ የኮረት ነጐድጓድ ያወርዱበት ጀመር ። እርሱም በበኩሉ ፀተ ቻለው መጠን በጋሻው እየተከላከለ የሚወረወርበትን ኮረት ይመ ልስ ነበር ። ይህም ሲሆን መሣሪያዎቹ እንዳይጋለጡበት ከገን ዳው ጐን አንዲት ስንዝር አልራቀም ነበር ። ሆቴለኛው ደግሞ ጠቡ እንዳይጋጋል በብርቱ ስለሠጋ በኮረት ወርዋሪዎቹ ላይ

እየጮኸ ሰውዬው እንጉሉ የተናወጸ እብድ መሆኑን አበክሮ የነገራቸው መሆኑንና ሁላቸውንም ቢገድላቸው እብድ በመሆኑ ምክንያት በፍርድ ነጻ የሚወጣ ሰው መሆኑን እያስረዳ እንዲ ተውት ይለፈልፍ ነበር። ዶን ኪሾትም ደግሞ ከመጀመሪያው ጊዜ ይበልጥ እየጮኸ ባላጋራዎቹን ከሐዲዎችና ፈሪዎች እያለ በመጥራት ፥ እንዲሁም የግንቡን መስፍን ጭምር ዙዋሪ ፈረስ ኞች በዚህ አኳኋን እንዲደፈሩና እንዲቀየሙ የሚፈቀድ ከሆነ እሱም እራሱ ወረተኛና አሳዳጊ የበደለው ወራዳ ፈረሰኛ መሆ ኑን እያማ ይለፈልፍ ነበር። ቀጥሎምዉይህ አምባገሮ የተነሳው የፈረሰኛነት ክህነት ከተቀበልሁ በኋላ ቢሆን ኖሮ የመላዋይነ ቱን ልክ አስገንዝበው ነበር ፥ እናንተን ደጀቦችን ጋንዲያዎችን ውሾችን ግን በፍጹም ከቁጥር አላገባችሁምና ኮረታችሁን ወር ውሩብኝ ፥ ተጠጉኝ ፥ ኑ ወደፊት ፥ የቻለችሁትን ጉዳት ሁሉ አድርጉብኝ ፥ ከዚህ ከተዋረደው ድርፍታችሁ የምትአመር ቱትን መራራ ፍሬ አቀምሳችኋለሁ» እያለ የዛቻ ድንፋቱን አሰ ማቸው።

ይህንንም የሚናገረው ባመረረ ቁጣና በቁርጠኛ ወኔ ስለ ነበረ እውነትም በባላገሮቹ ልብ የፍራቻ ስሜት እንዲፈጠ ርባቸው ለማድረግ ሳይችል አልቀረም። እነሱም ባንድ በኩል በዛቻው ፍርሐትና በሌላም በኩል ደግሞ በሆቴሉኛው ምክርና ልመና ረገብ ካሉ በኋላ ኮረት መወርወራቸውን አቋርጠው ቆሙ። በዚህን ጊዜ ዶን ኪሾት ጠበኞቹ መዳኘታቸውን ስለተረዳው ወደፊት ተጠግተው ቁስለኞቻቸውን እንዲያነሱ ፈቀደላቸውና ወዲያውኑ በዚያው በተለመደው ልውጥነቱ የቁጣ መንፈሱን አረጋግቶ የጀመረውን የፈተና ዋዜማ ሥርዓት ለመፈጸም ሄደ።

ሆቴሉኛው ግን የእንግዳውን አምባገሮኛነትና ወፈፍተኛነት እጅግም ስላልወደደው ሌላ አደጋ ከማምጣቱ በፊት ቶሎ እን ዲሸኘለት አስበና ያንን ገደቢስ የሆነውን የፈረሰኛነት ክህ ነት አጣድፎ ሊሰጠው ቁርጥ ሐሳብ አደረገና ሲፈራ ሲቸር በቀ ስታ እየተራመደ ተጠግቶ ይቅርታ እንዲያደርግለት ከጠየቀ በኋላ ፥ እነዚህ ባለጌ ጠባይ ያላቸው ገልቱ ሰዎች በድብቅ ሾል ከው መጥተው ባንሱት ጠብ ምክንያት በደረሰው ሁኔታ እጅግ

አድርጉ ማዘኑን ሲገልጥ ገልቱዎቹም ስለአጉል ድፍረታቸው የሚገባቸውን ቅጣት የተቀበሉ መሆናቸውን አረጋጠለት። እንዲሁም ቅድም ያስረዳውን እንደገና በመድገም ፥ በግንቡ እናት ላይ ሊኖር የሚገባው ሰገነት መፍረሱንና ለፈተናውም ዋዜማ የሚጐድል ልምምድ ቢኖር እንኳ ባሁኑ አጋጣሚ የተ ደረገው የመከላከል ውጊያ እንደ ደንበኛ የፈተና ዋዜማ የሚ ቆጠር በመሆኑ የቀረ ነገር ይኖራል በማለት ሌላ መቀጠል አለ ማስፈለጉን አስገነዘበው። ቀጥሎም ለክህነቱ ቡራኬ አደጋም የሚጠየቀው ሥነ ሥርዓትና የተዋጊነት ችሎታ ማስመስከሪያ እርሱ እራሱ አጣርቶ በሚያውቀው የፈረሰኛነት ሕግ ላይ ተጽፎ እንደሚገኘው በጉራዴ ደንደስና ስለት በኩል የሚከናወነውን አመካከትና አመታት ጠንቅቆ ማጥናትና ቅልጥፍናንም ማሳ የት ስለሆነ ይህን የመሰለው የፈተና ዋዜማ በመስክም ላይ ቢሆን ሊደረግ የሚቻል ነው። ይህም ባይሆን ቅሉ ለፈተናው ዋዜማ መለማመጃ የተወሰነው ጊዜ ሁለት ሰዓት ሆኖ ሳል ከዚህ አልፎ ከአራት ሰዓት ይበልጥ ስለቆየ ከበቂነት በላይ ሆኗል እያለ በሰፊው አስረዳው።

ዶን ኪሾት ይህን የተባለውን ሁሉ በሙሉ ልቡ አምኖ ከተቀበለ በኋላ ትእዛዙን ለመፈጸም የተዘጋጀ መሆኑን ሲገልጥ የሚጠብቀው የክህነት ቡራኬ ሥነ ሥርዓት በተቻለ ፍጥነት እንዲፈጸምለት አደራ ጭምር ልመናውን አቀረበ። ይህንንም ሲል ክህነት የተቀበለ ፈረሰኛ ከሆነ በኋላ እነዚያ ጠበኞቹ ጸጋ መኛ ጠብ አንስተው የሚገቧጩት ቢሆን ከዚያ ሊያዘጋው ከሚችለው መስፍንና መስፍኑም በአማላጅነቱ ከሚያስተምራ ቸው ሰዎች በስተቀር በዚህ ግንብ ውስጥ ነፍስ ያለውን ፍጥ ረት ሁሉ የማይተው መሆኑን በቁርጠኛ ዛቻ አስታወቀ።

የግንቡ መስፍን በዚህ አኳኋን የተነገረውን የዛቻ ማስጠ ንቀቂያ በእርጋታ ሰምቶ ወደ ሆቴሉ ተመለሰና ለጐረምሶቹ ገፈራና ገብስ ሰጪተ ማስታወሻ የጻፈበትን የሂሳብ ደብተር ይዞ፥ እንዲሁም ደግሞ አንድ ጉማጅ ጢፍ ላንድ ልጅ አስይዞ ፥ ሁሉ ቱም ኮረዶች ለአቋቋሚነት እንዲረዱት አስከትሎ ሙሽ ዶን ኪሾት ወደሚገኝበት ሥፍራ ሄዶ ፥ አጠገቡም እንደደረሰ

ዶን ኪሾትን እንዲንበረከክ ትእዛዝ ሰጥቶ ካስበረከከው በኋላ በደብተሩ ላይ የሥርዓተ ቡራኬ ጸሎት የሚያነብ ቄስ ይመስል በቀስታ እያሎረመረመ አንድ ገጽ ያህል እንደገለበጠ በቀኝ መዳፉ የዶን ኪሾትን ማጅራት ጫን አድርጎ ተመተመው ። ቀጥሎም ድግምት እንደሚደግም ደብተራ ማጉረምረሙን ሳያቋርጥ ያንኑ የዶን ኪሾትን ጉራዴ መዘዘና በጠፍጣፋው ወገን ጀርባውን ከረር አድርጎ ጠበጠበው ። ይህን የለበጣ ሥርዓተ ቡራኬ ከፈጸመ በኋላ ከኮረዳዎቹ አንዷን ጠርቶ ጉራዴውን እንድትስስታጥቀው አዘዛት ፥ ኮረዳይቱም በታላቅ ትሕትና በበዛ መሽቆጥቆጥ ተጠግታ ጉራዴውን በሁለት እጅዋ ተቀብላ አስታጠቀችው ። ይህ ሁሉ ሲሆን በያንዳንዱ የክህነት ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም ላይ የነበረው የግብዝነት ሁኔታ ሲታይ በዙሪያው አሰፍስፈው የሚመለከቱትን ሰዎች ሁሉ በሳቅ ሊያፈነዳቸው የሚበቃ ነበረ ።ዳሩ ግን አዲሱ ፈረሰኛ ቀደም ብሎ ባነሳው አምባጓሮ አማካይነት ኃይለኛነቱን ለማሳየት በመቻሉ እጅግ ተፈርቶ ስለነበረ በዚህ ምክንያት በያንዳንዳቸው ላይ ያደረውን የመሳቅ ፍላጐት ጥርሳቸውን ነክሰው እንዲውጡት ግዴታ ሆኖባቸው ነበር ። ብልሂቱ ኮረዳም ጉራዴውን በምታ ስታጥቅበት ጊዜ ፈረሰኛውን እንዲህ ብላ መረቀችው ።

«ክቡርነትዎ እጅግ የታደሉ ፈረሰኛ ነዎት ፤ በሚውሉበትም የጦር ሜዳ ቀኙ የእርስዎ ይሁን» አለችው ።

ዶን ኪሾትም በዚህ ምረቃዋ በጣም ደስ ስላለው ስለው ለታዋ ለወደፊቱ በክንዱ ብርታት ተዋግቶ በሚያገኘው የድል አድራጊነት ክብር ተካፋይ እንድትሆን በማሰብ ከዛሬ ጀምሮ ወደፊት የባለውለተኛነት ግዴታው ለማን እንደሆነ ለማወቅ ሲል ስሟን እንድትነግረው ጠየቃት ፥ እሷም በፍጹም ትሕትና ስሟ«ቶሎዛ» መሆኑንና እንዲሁም ያንድ የቶሌዶ ሰው የሆነ ጫማ ሠሬ ልጅ መሆንዋን ነገረችው ። ከዚህም በስተቀር ይሽው አባቷ ሳንቶ ቢያናያ ከሚባለው ሰው ሱቅ ውስጥ የሚሠራ ስለ ሆነ በማናቸውም ቦታ ቢያገኘው እንደ ጌታው አድርጐ የሚያገለግለውና የሚያከብረው መሆኑን አስረዳችው ። ዶን ኪሾትም መለሰና ከዛሬ እንስታ ወደፊት ለሱ ፍቅር ስትል የእመቤትን ክብር ደርባ «እመቤት ሆይ ቶሎዛ» ተብላ እንድትጠራ ለመናት ። እሷም ከዚህ ቀን እንስታ «እመቤት ሆይ ቶሎዛ» ብለው ካልጠሯት ለማንም ቢሆን ሳትመልስ ቃሏን ስጠችው። ሁለተኛይቱ ኮረዳ ደግሞ የፈረሱን መኩርኩሪያ ብረት ከሜጣው ተረከዝ ላይ ስታስርለት ነበረችና ለእሷም የባለጉራዴይቱን ዓይነት ጥያቄ አደረገላት እሷም ስሟ «ሞሊኔራ ሙኛያ» መሆኗንና አባቷም የአንቴኳራ ሰው የሆነ ሐቀኛ ባለወፍጮ መሆኑን ነገረችው ። ዶን ኪሾት እሷም እንደጓደኛዋ እመቤትነትን ደርባ «እመቤት ሆይ ሙኛያ» እየተባለች እንድትጠራ ሲሾማት ሌላም አነልግሎትና ክፃ በረከት ወደፊት እንደሚሰጣት አረጋገጠላት ።

ዶን ኪሾት በዚህ አኳኋን ይህን አዲስ ወጥ የሆነውን የክህነት ቡራኬ አፈጻጸም ሥነ ሥርዓት በታላቅ ፍጥነትና በግል ቢያ አጣድፎ ከፈጸመ በኋላ ፈረሱ ላይ ወጥቶ አጋጣሚውን ለመፈለግ የሚሄድበት ጊዜ ገና ሺህ ዓመት የሚያቆየው እየ መሰለው የመቸኰሉ ብዛት ያቅበጠበጠው ጀመር ። ሆኖም ሮጌ ዚናንቴን ጭኖ ለመነሳት ከተሰናዳ በኋላ የግንቡ መስፍን ስለ ሰጠው የፈረሰኛነት ክህነት ምስጋናውን በማቅረብ አቅፎ ስሞ በሚሰነባበትበት ጊዜ የተናገራቸው የምስጋና ቃላት እጅግ የመ ዘበራረቃቸው ብዛት በዝርዝር ተጽፈው ለመገለጥ የሚያስቸግሩ ነበሩ ።

ሆቴሰኛውም የመዘዘኛውን እንግዳ ሐተታ በትእግሥት ሲያዳምጥ ቆይቶ በመጨረሻው አክትሞ ከሆቴሉ መውጣቱን ከተመለከተ በኋላ ምንም ቃሉ አጠርና ኰስተር ያለ ቢሆን የቁልምጫው መዘበራረቅ ከዚያኛው ባላነሰ አነጋገር ለስንብ ብቱ ለውጥ ሰጥቶ የሆቴሉንም ሂሣብ እንዲከፍለው ሳይጠይቅ ድንገት ረፍዶበት እንዳይመለስ በመሥጋት ብቻ በጥሞና ዝሩ ፍቶ ሽኝቶት ተመለሰ ፥ ያኛውም ጉዞውን ቀጠለ ።

ምዕራፍ 4

ፈረሰኛችን ሦቴሱን ለቀ ከወጣ በኋላ በመንገዱ ላይ የደረሰበት ሁኔታ ይተረካል ።

ዶን ኪሾት ከሦቴሱ ሲወጣ ጀምበር ሥራዋን መፈንጠቅ ጀምራ ነበር ፡ እሱም የተካነ ፈረሰኛ በመሆኑ በደስታ ፈንድቆ ስለነበረ የደስታው ብዛት ከሱ ተርፎ በፈረሱ መጣብርና አንፋር ፡ እንዲሁም በየጠፍሮቹ ዘለበት ላይ ሲያናጥር ይታይ ነበር ። ዳሩ ግን ሦቴለኛው ለመንገዱ ጉዳይ የሚያስፈልገው መሆኑን በጥብቅ እያስረዳ የዘረዘረለትን ሥንቃሥንቅና በተለይም ገንዘብና ልብስ ሳይዝ ባሁኑ ሁኔታ እንዳይሄድ አስጠንቅቆ የመከረውን አስታወሰና ወደ ቤቱ ተመልሶ ማንኛው ንም ጉዳይ ለማጠናቀቅና አንድ ጋሻ ጃግሬም ፈልጐ ለማስከ ተል ሀሳቡን ቆረጠ ። ስለ ጋሻ ጃግሬ ማግኘትም ያደረገው ምርጫ ያገሩ ሰው የሆነ ወዲህም ቅርብ ጐረቤቱ የሆነ ፡ በታታ ሽነቱና በመከራ ቻይነቱ የታወቀ የልጆች አባት ፡ ለዙዋሪ ፈረ ሰኛ ጋሻ ጃግሬነት በጣም የሚስማማ ጠባይ ያለው አንድ ባላ ገር መኖሩን አስታወሰና እሱኑ በቀላሉ ደልሎ እንዲያገለግለው ለመውሰድ አቀደ ። በዚህ ውሳኔ ፈረሱን አዞረና ወደ አገሩ አቅ ጣጫ አመራ ። ፈረሱም የጋጣው ጠረን የሸተተው ይመስል ከዚህ ቀደም ያላሳየውን ንቃት ፈጥሮ በሶምሶማ እርምጃ ሲሠ ግር በኩቴው መራቱን የማይነካ ይመስል ነበር ።

በዚህ ሀሳብ ተወጥሮ ጥቂት ምዕራፍ መንገድ እንደተጓዘ ወዲያውኑ ከመንገዱ በስተቀኙ በኩል ጥቅጥቅ ካለው ጫካ ውስጥ ባንድ አኳያ በጸዐር እንደተጨነቀ ሰው የሚጠሩት ድምጽ ወጥቶ እጅየው ጥልቅ አለ ። ይህንንም ድምጽ በመስ ማቱ እንዲህ ሲል ስሜቱን ገለጠ ።

«የበጐ ሙከራዬን አፍላ ፍሬ ለመልቀምና የተግባሬንም የተቀደሰ ዕዳ ለመክፈል እንዲህ በቅርብ ቀኑን ለሰጠኝ አም ላክ ክብርና ምስጋና ይድረሰው ። ይህ የምሰማው ጩኸት ያንድ ወይም ያንዲት የኔን እርዳታና ዳኝነት የሚጠይቅ የተጠቂ ሰው ድምጽ ነው» አለ ።

ይህንንም ካለ በኋላ ፈረሱን አዙሮ ጩኸት የሚመጣ መስሎ ወደተሰማው አቅጣጫ ገሠገሠ ። ወደ ጫካው መካከል ገብቶ ጥቂት እልፍ እንዳለ ወዲያውኑ ባንድ የብርብራ ግንድ ላይ እንዲት የፈረስ ባዝራ ታሥራ ፡ በሌላው ግንድ ላይ ደግሞ ዕድሜው አሥራ አምስት ዓመት የሚሆነው ፡ ከወገቡ በላይ የተ ራቆተ አንድ ልጅ የፊጥኝ ታሥሮ አየ ። የሚጮኸውም ይኸው ልጅ ኖሮአል ። እሱም ያላንዳች ምክንያት አልነበረም ፡ አንድ ወደልና ወፍራም የሆነ ባላገር በሙሉ ኃይሉ እየተንጠራራ በጠፍር አለንጋ እያከታተለ ይገርፈው ስለነበረ ነው ።

በያንዳንዱም ግርፋት ላይ አንድ ጊዜ ስድብ ፡ አንድ ጊዜ ምክር እየቀላቀለ «አፍህን ዝጋና አይንህን ክፈት» ይለው ነበር።

ልጁ ደግሞ «ጌታዬ ሆይ ዳግመኛ አይለምደኝም እጠ ነቀቃለሁ ፡ በእውነት ስም መሐላ ይሁንብኝ ፡ ከእንግዲህ ወዲያ አላደርገውምና ይማሩኝ ፡ ይቅርታ ያድርጉልኝ ፡ ከዛሬ ጀምሮ ወደፊት በጉቹን በበለጠ ጥንቃቄ የምጠብቅ ለመሆኔ ቃል ገብ ቻልዎታለሁ» ፡ እያለ በማሳዘን ይወተውት ነበር ። ዶን ኪሾት አጠገባቸው ደርሶ ይህንን ድርጊት በተመለከተ ጊዜ በቁጣ እን ደጋለ ሰውነቱ እየተንዘፈዘፈ በኃይል ቃል ባላገሩን እንዲህ አለው ።

"ልበ ደንዳናው ፈረሰኛ ሆይ ! በገዛ አቅሙ እራሱን ለመ ከላከል በማይችል ደካማ ላይ ቁጣን በማከረር አስከዚህ ድረስ ግስጨነቅ በጠቅላላው አነጋገር ምክንያት የማይገኘለት ግፍ ስለሆነ ፡ ጦርህን አንስተህ ሶቂ ፈረስህ ላይ ውጣና እንደአጋጣሚ ደግሞ እውነትም ይህ ባላገር እዚያው ባዝራይቱ ከታሠረችበት ግንድ ላይ የተደገፈ ጦር ነበረው ። ከኔ ጋር ውጊያ ገጥመን ይዘ የአሁኑ አደራረግህ የፈሪ በትር መሆኑን ላረጋግጥልህ» አለው።

ባላገሩም ይህ ጥርቃሞ መግሪያ የተሸከመ አስደንጋጭ የጭራቅ መልክ ሳያስበው ድንገት አጠገቡ ደረሰ ፥ ጦሩን እፊቱ ላይ ደግኖ ሲዝትበት ባየው ጊዜ እዚያው እቆመበት ቦታ የሞተ ሰው ይመስል በድንጋጤ ክው ብሎ ከመፍዘዙ በሰተቀር ለመ ጀመሪያው ጊዜ መልስ የሚሰጥበትን ድፍረት አላገኘም ነበር ። ድንጋጤው ጥቂት አልፎለት ነፍሱ ከተመለሰ በኋላ እየተርበ ተበተ በመለማመጥ እንዲህ ሲል መለሰለት ።

«የተከበሩ ፈረሰኛ ሆይ ! ይህ አውን የምቀጣው ልጅ በዚህ ቀበሌ አካባቢ የግረባቸውን የበግ መንጋዎች እንዲጠብቅልኝ በደ መወዝ የቀጠርኩት አሽከሬ ነው ። ዳሩ ግን ልጁ በጣም ግጋጣ በመሆኑ ምክንያት ለጥበቃ ተግባሩ ሳይተጋ እየቀረ በየቀኑ እን ዳንድ በግ እያሰረቀብኝ እናድዶኛል ፥ አውን ምክንያት አግኝቼ የቀጣሁት በጭካኔ መንፈስ ተገፋፍቼ ሳይሆን ከግጋጣነቱና ከች ላባይነቱ እንዲታረም በማሰብ ነው ። እሱ እንደሚለው ግን ደመ ወዙን ለማስቀረት በተንኰል መንፈስ ላጠቃው የተነሳሁ አለ መሆኑን ለክቡርነትዎ እያረጋገጥሁ ልጁ በተፈጥሮው ቀላማጅና «ውሸታም» መሆኑንም በእግዚአብሔር ስምና በሕሊናዬ ክብር ምዬ እባልጥልዎታለሁ» አለው ።

«አንተ ፈርጣጭ የቤት አይጥ «ውሸታም» ብለህ የምትናገ ረው በኔ ፊት ነውን አንተ ቡከን ባላገር» ፥ ሲል «ዶን ኪሾት» በቁጣ ገሠፀውና ዛቻውን በመቀጠል «በዚች ብርሃኒን በም ትሰጠን ፀሐይ መሐላ ይውንብኝ በዚህ በያዝኩት ጦር ሆድ ሀን መሐል ለመሐል ወግቼ ልጥልህ አሰኝቶኛል ። በል አውን አንዳች መልስ ሳትሰጠኝ ልጄን ፈትተህ ደመወዙን እጅ በእጅ ከፍለህ ነጻ እንድትለቀው ። አለበለዚያ ግን በቸርነቱ የሚጠብ ቀን ጌታ አይለመነኝ ከዚህ ሥፍራ ሳትንቀሳቀስ እንዳልነበርክ አድርጌ እጨርስሃለሁ አለው ።

ባላገሩም ለጥ ብሎ እጅ ከነሳ በኋላ አንዳች ቃል ሳይተ ነፍስ እንደታዘዘው ልጁን ከአሥራቱ ፈትቶ ለቀቀው ። ዶን ኪሾትም ልጁን ጠርቶ አጠገቡ አስጠጋውና ጌታው ምን ያህል ገንዘብ ሊከፍለው እንደሚገባው ጠየቀው ልጁም በወር ሰባት ብር ሂሳብ ተቀጥሮ ዘጠኝ ወር ሙሉ ያለደመወዝ ግብል

ገሉን አመለከተ ። ዶን ኪሾት ሂሣቡን አስልቶ ድርሻው ሰልሳ ስድስት ብር መሆኑን ካስተማመነ በኋላ ባላገሩ ነፍሱን የሚ ወዳት እንደሆነ ደመወዙን አሁኑኑ በሱ ፊት እንዲከፍለው አዘ ዘው ። ባላገሩ ግን አውን እግረ መንገዱን በሚገኝበት ውኃታ ቅድም በግለውም መሐላ መሠረት (በውነቱ እስካሁን ድረስ በፍ ጹም አልግለም ነበር ።) ይህ ዕዳ እንደሚደርስበት አውቆ ገንዘብ በኪሱ ይዞ ያልመጣ መሆኑን በማስረዳት ምንም እንኳ ብዙ ባይሆን በልጁ ደመወዝ ኢያሰበ ያወጣው የሶስት ጥንድ ጫማ ዋጋና እንዲሁም ታሞ በነበረበት ጊዜ ለሁለት ዋግምት የከፈ ለለት አንድ ብር በቅናሽ እንዲታሰብለት አመለከተ ።

«ሂሣቡ ትክክል ሊሆን የሚችል ነው» ሲል ዶን ኪሾት ሲበይን ቀጥሎ ያለውን ማነጣጠሪያ ማስረጃ ሰጠ ። የጫማውና የዋግምቱ ዋጋ ያለምክንያት ለፈጸምክበት ግርፋት ካሣው ሆኖ ይቀርለታል እንጂ በደመወዙ ሊታሰብ አይገባም ። በመንጋ ጠባቂነት ተቀጥሮ ደን ለደን ሲራወጥ ለጋራጣ መከላከያ እንዲሆነው ገዝተህ የሰጠኸውን ጫማ አድርጐ ሲረግጥበት ሰንብቶ ቢጨርሰው ፥ አንተ ደግሞ ቀድሞ ለስላሳ የነበረውን ጀርባውን በግርፋት እየበጣህ ገጥበህ ጨርሰህበታል ። ልጁ ታሞ በነበረበት ጊዜ ወጌሻው እንዲድንለት አስቦ ደሙን በዋግምት ቢቀዳው ፥ አንተ ደግሞ በጤንነቱ ላለ ደሙን በከንቱ አፍስ ሰህ ሕመም ላይ ጥለኸዋል ። ስለዚህ በዚህ አኳኋን ስጦታውና በደሉ ሲመዛዘን የሚቻቻል ሂሣብ ነው እንጂ ከልጁ ደመወዝ ላይ ሊቀነስበት የሚገባው ዕዳ አለመኖሩ ግልጥ ነው» አለው፡

ባላገሩም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ «የተከበሩ ፈረሰኛ ሆይ ! ብይንዎ የበጀ በመሆኑ ምንም ሳልከራከር ተቀብዬዋለሁ ። ዳሩ ግን አውን ታላቅ ችግር የሆነብኝ ይህን ዕዳ እንደምጠየቅ አውቄ ከቤቱ ገንዘብ ይዤ አለመምጣቴ ስለሆነ አንድርያ ተከትሎኝ እቤቴ ድረስ ይምጣና ደመወዙን በብር ላይ ብር ጨምሬ አጠፈታ አድርጌ እከፍለዋለሁ» አለ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን አንድሬያ ተጠንቅቆ ያዳምጥ ነበርና አብሮ እቤት የመሄድን አሳብ በሰማ ጊዜ« እሳቸውን ተከትዬ የምሄደው ስቃይ ለመቀበል ነውን? ይህን በፍጹም አላደርገውም ። እንዳያ

ውም በሃሳቤ ውስጥ አላገባውም ። ምክንያቱም ብቻችንን ቀር ተን ዓይን ላይን ከተፋጠጥን በኋላ ዳግመኛ እጃቸው ያገቡኝ እንደሆነ እንደ ቅዱስ ባርቶሎሚዎስ በሕይወቴ ሳለሁ ቆዳዬን እየገፈፉ እንደሚዘለዝሉኝ እርግጠኛ ነኝ» ሲል አሰታወቀ ።

ዶን ኪሾትም መለሰ «የለም ይህን አያደርገውምና አይ ዞህ አትፍራ ። እኔ አሁን የጠበቀ ትእዛዝ እሰጠዋለሁ ። እሱም ትእዛዜን እንዲያከብር በተቀበለው የፈረሰኛነት ክህነት ከማ ለልኝ በኋላ በዚህ አመኔታ አለቀዋለሁ ። መሐላውን አክብር ደመወዝህን ሳይከፍልህ ቢቀር ግን እኔ ኃላፊ ሆኜ አከፍለሃ ለሁ» አለው ።

«አዬ ጌታዬ ሆይ ! በዚህ አነጋገርዎ ምን ማለትዎ እንደሆነ አልገባኝም ሲል ልጁ ያስጠነቅቅ ጀመር» እኒህ የኔ ጌታ ከማ ብርና ሥራ በሰተቀር ስለፈረሰኛነት ክህነት የሚያውቁት አን ዳች ነገር የለም ። እንዲሁም ማንኛቸውንም ዓይነት የፈረሰኛ ክህነት አልተቀበሉም ። ስማቸውም ዮሐንስ ጐኔላ የሚባሉ የኩ ይንታናር ባለፀጋ ስለሆኑ በመሐላ ብቻ ቃላቸውን የሚጠብቁ መስሎዎት አጋልጠውኝ እንዳይሄዱ ተማጥኜብዎታለሁ» አለው።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል መለሰ ! ይህስ ቢሆን ታዲያ ምን አለበት ፡ መቸም እያንዳንዱ ሰው ለምግባሩ የባህር ልጅ ስለሆነ የኩይንታናር ባለፀጋም ቢሆኑ ከጐኔላ ዘሮች ውስጥ ፈረሰኞች ሲወጡበት ይችላሉ» አለው።

«ይህ ክብርነትዎ ያሉት እውነት ሊሆን ይችላል» አለ አንድሬያ» ዳሩ ግን ላቤን ያንጠፈጠፍኩበትን የድካሜን ዋጋ ሲከለክሉኝ እኒህ የኔ ጌታ ለየትኛው ምግባራቸው የባህር ልጅ የሆኑ ይመስልዎታል» ።

ባላገሩም «ውድ አንድሬያ ሆይ ! ገንዘብህን የምክለክልህ አይምስልህ ፡ ይህንስ በፍጹም አላደርገውም ። ይልቁንስ ለኔ ስትል እባክህን አብረን ወደ ቤታችን እንሂድ ። እዚያም ከደረሰን በኋላ ቅድም እንደነገርኩህ አንዱን ብር እጥፍ አድርጌ ከነወለዱ በርከት ያለ ብር በሽቶ አርከፍክፈ የምሰጥህ መሆኔን በዓለም ላይ በሚገኙት የፈረሰኛነት ክህነታት ስም እምልልሃለሁ» አለው ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ አለ «ሰለ ሽቶው ማርከፍከፍ አሥሰ ግንሃለሁ ። ይሁን እንጂ ነባ ገንዘቡን ብቻ ከከፈልከው ደስ ይል ኛል ። ስለዚህ መሐላህን አጽንተህ ግዴታህን እንድትፈጽም አሁንም ደግሜ አስጠነቅቅሃለሁ ። ምናልባት መሐላህን ባለ ማክበር የልጁን ደመወዝ ባትከፍለው ግን ተመልሼ መጥቼ ፈልጌ ሳልቀጣህ የቀረሁ እንደሆነ አንተ የማልከው መሐላ በኔ ላይ ይድረስብኝ ። ይህም ሆኖ ከኔ ተደብቀህ ለማምለጥ ከእንሽላ ሊት ይበልጥ ብትሰወርም እንኳ ከገባህበት ገብቼ እንደአተር ፈልፍዬ ላወጣህ እንደምችል አረጋግጥልሃለሁ ። ከዚህም በስ ተቀር ግዴታህን ሳታወዛ ለመፈጸም ይበልጥ እንድትሠጋበት ይህንን ማስጠንቀቂያና ትእዛዝ የሚሰጥህ ግን መሆኑን ለማወቅ የምትሻ እንደሆነ እኔ ጀግናው የማንቻው ዶን ኪሾት የምባ ለው ማናቸውንም ዓይነት ግፍ የምቀበል ፡ ግፈኞችን የምቀጣ ጠማማዎችን ሁሉ የማቃና መሆኔን አውቀህ የማልከው መሐላና የገባኸው ቃል ኪዳን እንዳይዘነጋህ በልቦናህ ቀርፀህ ያዘው ። እንግዲህ በርታ ደህና ሰንብት» ብሎት ፈረሱን አዞረ ።

ይህን ከተናገረ በኋላ ሮንዜናንቴን ኮረኮረና ባጭር ጊዜ ውስጥ እርቆ ሄደ ። ገበሬውም ባይኑ ሲሸኘው ነበርና ጫካውን አቋርጦ መጨረሱንና ሳይን መራቁን ከተመለከተ በኋላ ወደ አሽከሩ ተመልሶ «ልጄ ሆይ ፡ ይህ ግፈኞችን የሚቀጣ ፈረሰኛ እንዳዘዘኝ የሚገባህን ደመወዝ እንድከፍልህ ወዲህ ናልኝ» አለው።

«እርግጥ ነው» አለ ። እንድሬያ ለሁሉም ነገር የተጋላ ጨን ነትን በማግኘት እንደገና ሺህ ዓመት ጨምሮ ያኑረውና የዚህን የምስጉን ፈረሰኛ ትእዛዝ ቢፈጽሙ በጣም ጥሩ ይሆንልዎታል። ትእዛዙን ባለመፈጸም ሳይከፍሉኝ ቢቀሩ ግን መቸም ዓለም ዋሾ መሆኑ ቢታወቅም ተመልሶ መጥቶ የተናገረውን ቃል እን ደሚፈጽም ተስፋ አደርጋለሁ» አለው ።

ባላገሩም መለሰ» እርግጥ ነው እኔም ያልኩት ይኸንኑ ነበር ነገር ግን አንተን እጥብቄ ስለምወድህ ደመወዝህን ለማሳደግ እንዲረዳኝ ዕዳዬን ለማብዛት እፈቅዳለሁ» አለው ። ይህን እየተናገረ አዘንግቶ ተጠጋውና ክንዱን አፈፍ አድርጉ በዚያው በቅድመ ግንድ ላይ የፊጥኝ ካሠረው በኋላ ከፊተኛው በባሰ

ሁኔታ በጠጫና በእርግጫ አልፍቶት ግማሽ ራሳ አድርጐ ለቀ ቀው ።

በሚመታበትም ጊዜ እንዲህ እያለ ያቮፍበት ነበር ።ጌታው እንድሬያ በል እንግዲህ ዳኛህን ጥራውና አሁን እዚህ መጥቶ ከእጇ ሲያስጥልህ እንየው ፣ ያ ጥቃትን የሚበቀለው ጌታህ አሁን ይድረስልህ ፣ በል እኮ ጥራው ፣ ይህን ጥቃት እንዲበቀ ልልህ እንዲያውም የሚበቃህን ያህል ጨርሼ የሰጠሁህ አል መሰለኝምና ቅድም አንተው እንደፈራኸውና እንዳልከው ከነ ሕይወትህ ቆዳህን ብገፈው አልጠላም ። እያለ የልቡን አድርሶ ንዴቱን ካበረደ በኋላ ፈትቶ ለቀቀውና ልጁ ዳኛውን ፈልጐ ይግባኙን እንዲያሰማ ፈቅዶ አሰናበተው ።

አንድሬያም ከመጀመሪያው ይበልጥ ተደብድቦ ፊቱ እንደ ነበዘ እልክ ይዞት በንዴት ራሱን እየነጨ ጀግናውን የማንቻው ዶን ኪሾት በዱካ ተከታትሎ ፈልጐ ለማግኘትና የተፈጸመበትን የግፍ ድርብ በዝርዝር አሰረድቶ ጌታውን ሰባት እጥፍ ቅጣት ለማስቀጣት እየማለ በሩጫ ተፈተለከ ። በዚህ አኳኋን ልጁ እያለቀሰ ሲሔድ ጌታው ደግሞ ቆሞ እየሳቀበት እዚያው ቀረ ።

ጀግናው ዶን ኪሾት ሳይቸገረው ገብቶ ጌታና አሽከርን ሆድ ለሆድ አባብሶ እዚያው እጫካው ውስጥ ትታቸው በመሄዱ ጥቃ ትን የተበቀለ ስለመሰለው ለዙዋሪ ፈረሰኛነት ተግባሩ መልካም አፈጻጸም ገና ከአሁኑ ዕድል አጋጥሞት ይህን የመሰለ አሰደ ሳችና አኩሪ የሆነ ፍርድ በመስጠቱ በዳኝነቱ ላከናወነው ሞያ እጅግ ደስ እንዳለው በቀስታ ድምጽ ብቻውን እየተነጋገረ ጉዞ ውን ወደ መንደሩ አቅጣጫ ቀጠለ ። የሚለውም እንዲህ ነበር ፡

«ከቆንጆዎቹ ሁሉ በላይ ቆንጆ የሆንሽው የቶቦዞይቱ ዱል ቺኔያ ሆይ ! የማንቻው ዶን ኪሾትን የመሰለ ተፈሪና አሸቀጥቋጭ ፈረሰኛ በፈቃድሽ ሥር አዳሪና ተገዢ ዜጋሽ እንዲሆን ዕጣ ስለ ደረሰሽ ዛሬ በምድር ላይ ከሚኖሩት ሴቶች ይበልጥ በዕድልሽ ለመኩራትና ዕድለኛም ተብለሽ መጠራት ይገባሻል ። ይኸው ፈረሰኛሽ የጀግንነቱ ዝና በመላው ዓለም የተንዛውን ያህል ትና ንት የፈረሰኝነትን ክህነት ተቀብሎ ገና ከንዱን ማፍታታት ሲጀ ምር እነሆ ዛሬ አንዱን ለጋ ወጣት አንድ ጨካኝ ባላገር ያለን ዳች ምክንያት ሲገርፈው ደርሶ አሰንጋውን ከእጁ ላይ መንጭቆ ሞሎ አሰቃቂ የአረመኔነት መንፈስ የሚይሠራውንና የግፈኛም ዕብሪት አድርጐት የማያውቀውን እጅግ ከፍ ያለ ጥቃትና እጅግ ከፍ ያለ የሕግ አፍራሽነት አመጽ ደመሰሰልሽ» ብሎ የብቻ ንግ ግሩን ጨረሰ ።

ይህን እየቀባጠረ ጉዞውን በመቀጠል ላይ ሳለ መንገዱ በአ ራት መንታ በተከፈለበት ነጥብ ላይ ደረሰ ። በዚህን ጊዜም ይህን የመሰለ ስብጥር መንገድ ጥንታዊ ዙዋሪ ፈረሰኞችን ሲያጋ ጥማቸው የትኛውን መንገድ መምረጥ እንደሚገባቸው ለማወቅ ቆመው ያሰላሰሉ እንደነበረ ትዝ አለውና አሱም የጥንቶቹን ምሳሌ በመከተል ጥቂት ቆም ብሎ በማሰረጥ በጥልቅ ካሰበበት በኋላ በመጨረሻው ልጓሙን በሮንዚናንቴ አንገት ላይ ለቀቀለ ትና መንገድ የመምረጡን ፈቃድ ለፈረሱ ተወለት ። ፈረሱም በእ ንስሳ አእምሮው ውስጥ የተቀረጸውን የመጀመሪያውን ምርጫ በማጽደቅ ያንኑ ወደጋጣው የሚወስደውን መንገድ መርጠ ተጓዘ። ፈረሰኛውም በፈረሱ እርምጃ እየተመራ ሁለት ምዕራፍ የሚሆን መንገድ ከተጓዘ በኋላ ከፊት ለፊቱ በርከት ያሉ ሰዎች ወደርሱ ሲመጡ በሩቁ አያቸው ።

የነዚህም ሰዎች ሁኔታ ቆይቶ እንደታወቀው ከሙርቻ ገበያ ሐርና ድር እየገዙ የሚያተርፉ የቶሌዶ ነጋዴዎች ስለሆኑ የዕለቱ ገበያ እንዳያመልጣቸው ወደ ሙርቺያ የሚሄዱ ነበሩ።ብዛታቸውም ስድስት ሰዎች ሆነው አራቱ በፈረስ የተቀመጡ ባላቤቶችና ሁለቱ ደግሞ በእግር የሚከተሉ ጐርደማዎች ናቸው ። ዶን ኪሾት ሰዎቹን ለይቶ ከተመለከታቸው በኋላ ወዲያውኑ ሴላ አዲስ ግጥሚያ እንደቀረበለት ተረዳ ። መቸም በዚያ በአነበበው የፈሰኝነት ልበ ወለድ ታሪክ ላይ ያጠናውን ዝባንዝንኬ ሁሉ እውነተኛ ነገር አድርጐ ያመነበት ስለሆነ ልክ በዚያን ጊዜ በሀሳቡ ውስጥ ሲፈ ነጩ ከነበሩት ከብዙዎቹ ምሳሌዎች አንደኛውን በመከተል ይህ ነኑ ለመፈጸም የሚችልበት ደህና አጋጣሚ እንደተገኘለት እርግ ጠኛ ሆኖ ተሠናዳ ። ስለዚህም በኩሩነትና በወኔያምነት መንፈስ ሰውነቱን አንቅቶ ፣ እርካቡን አመቻችቶ ተቆናጠጠና ጦሩን ዘቅ ዝቆ ይዞ ፣ ጋሻውን ወደ ደረቱ ለጥፎ እነዚያ ዙዋሪ ፈረሰኞች

(መቼም በዚሁ ሁኔታ መድቦአቸዋልና) እስኪጠዮት ድረስ እውራው መንገድ መካከል ቆሞ ይጠብቃቸው ጀመር ።

ነጋዴዎቹም ወደፊት እየተቃረቡ መጥተው ለመተያየትና ለመደማመጥ በሚችሉበት ነጥብ ላይ እንደደረሱ ዶን ኪሾት ድምጹን ከፍ አድርጎ በተጀነነ አነጋገር እንዲህ አላቸው ።

«ዘንፋላዋን እመቤቴን የማንቻይቴን ንግሥት ነገሥታት ወደር የለሽ የቶቦዞይቴን ዱልቺኒያን በቁንጅና የምትበልጥ ሴት በመላው ዓለም ላይ ያልተፈጠረችና ያልታየች መሆኗን አረጋግጣችሁ ሁላችሁም ባንድ ቃል እስክትናዘዙ ድረስ አንድ እርምጃ እንኳ ወደፊት ላትራመዱ እዚያው አላችሁበት ቦታ ቀጥ ብላችሁ እንድትቆሙ» አላቸው ።

ነጋዴዎቹም ይህን ግራቢስ አነጋገርና እንዲሁም የተናጋሪውን ማስፈራሪያ መልክ በማየታቸው ተደንቀው ለማጣራት ሲሉ ቆሙ ። ነገር ግን ለጥቂት ጊዜ አስተውለው እንደተመለከቱት በመልኩና በአነጋገሩ አስረጂነት እንደገባቸው ካንድ የለየለት ዕብድ ጋር መዳረቅ መሆኑን ለመገንዘብ ቻሉ ። ይሁን እንጂ ይህ የተጠየቁት የቁንጅና ማረጋገጫ ኑዛዜ ዓላማው ምን እንደሆነ ለማወቅ ስለፈለጉ ከመካከላቸው አንደኛው ቀልደኛና በጣም አፈጮሌው ቢጤ ተሽ ቀዳደመና በሁሉም ስም እንዲህ ሲል ፈረሰኛውን ጠየቀው ።

«ክቡር ፈረሰኛ ሆይ ! ይህችን ስሟን የጠቀሱልንን መልካም ሴት እኛ ስለማናውቃት እርስዎ እንደሚሉት ሁሉ ቁንጅናዋ እስከዚህ ድረስ የሚያስደንቅ ተአምር ከሆነ ለኑዛዜ ከመገደዳችን በፊት እውነቱን ለመመስከር እንድንችል መልኳን ቢያሳዩን ደስ ይለናል» አለ ።

«ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል መለሰለት ፡» እኔ መልኳን ካሳየኋችሁማ ብሩህና ግልጥ የሆነውን እውነት በመመስከራችሁ ዋጋ ችሁ ምን ሊሆን ይችላል ፣ መናዘዝና መመስከር የሚገባቸው መልኳን በጭራሽ ሳታይዋት በህላዊ ብቻ ቁንጅናዋን እያነነናችሁ ማመን ፣ ማድነቅና ማረጋገጥ መግልና መወራረድ ነው» ይህን ካላደረጋችሁ ግን እምቢተኞችና ሰው ናቂዎች መሆናችሁን መግለጣችሁ ስለሆነ ሁላችሁንም የውጊያ ግጥሚያ ጋብዤአች

ኋለሁ ። የፈረሰኛነትን የግጥሚያ ሕግ የምትመርጡ እንደሆናችሁ አንድ ባንድ ተራ ገብታችሁ ወደፊት ተጠጉኝ ፣ ይሀን የማትመርጡ ከሆናችሁ ግን እንደቢጤዎቻችሁ መጥፎ ልማድ ችሁም ተነባብራችሁ ግጠሙኝ ፣ በኔ በኩል ስላለው መስናዶ እመቤቴ የምትሰጠኝን የመንፈስ ዕርዳታና ኃይል በመተማመን አንድ እራሴን ቆሜ እጠብቃችኋለሁ» አላቸው ።

ነጋዴውም መለሰ» ክቡር ፈረሰኛ ሆይ ፣ ክቡርነትዎ ለምን ጠይቀው ትክክለኛ ማስረጃ አሰጣጥ በኔና በሌሎችም መኳንንትና ልዑላን ስም ሆኜ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ልመና አቅርብልዎታለሁ ። እኛ ምን ጊዜም ያላየነውን ቁንጅናና ያልሰማነውን ዝና ባሁኑ አጠያየቅ ብቻ ዕውነት ነው ስንል በማድነቅ መስክረን ነፍሳችንን ለማስኰነንና የሕሊናችንንም ሽክም ለማክበድ እንፈቅድም ። ይህንንም ብናደርግ እስካሁን ድረስ የተደነቁትን የአልካሪያንና የኤስትራማዱራን ንግሥታትና ልዕልታት ቁንጅና በእጅጉ ግቃለል ስለሚሆንብን አንዳች ማወዳደሪያ የሚሆን ማስረጃ ሳንጨብጥ ለይስሙላ ብለን ለመመስከር በፍጹም አንችልም ። ስለዚህ የክቡርነትዎ መልካም ፈቃድ ሆኖ የዚህችን ሴት መልክ የሚያሳይ እንዲት ቁራጭ ፍቶ ግራፍ እንኳ እንዳልዎት ቢሰሙን እናመሰግንዎታለን ፣ መቼም እንደሚባለው ከድር ወደ ድመር የሚደርስ ስለሆነ የፎቶግራፍዋ ማነስ የስንዴ ቅንጣት ያህል ትንሽም ቢሆን እንኳ ለምስክርነታችን መነሻ መሠረትነት የሚያገለግለን በመሆኑ እሱን ማግኘታችን ለሕሊናችን ደስታና እረፍት ይሰጠናል ። ክቡርነትዎም የልብዎ ምኞት ተሟልቶ በመረጃ መሠ ለመደሰት ይችላሉ ። እንዲያውም የግል ሃሳባችንን ስንገልጽልዎ ዘወትር ወደሴትዬይቱ ቁንጅና ወገን በማድላት ምንም እንኳ ሊሆን እንደሚችለው በፎቶግራፍዋ ላይ አንድ ዓይኗ ሽሙራራ ሆኖ ሁለተኛው ደግሞ እየሞጨመጨ የድኅ ብጥብጥና የጣዝማ ወለላ የሚያዝ ቢሆን ፣ በፊታም ላይ ለምጥ ቢኖርባት መልኳም ገርጥቶ ቢያስቀይም ፣ ክቡርነትዎን ለማስደሰት ስንል የሚጐድላትን ሁሉ እየጨመርን የእንከኗን ወገን ሸፋፍነን ቁንጅ ኖን ለማመስገን ቅር አይለንም »አለው ።

ይህን ንግግር ሲሰማ ዶን ኪሾት በንዴት ተቃጥሎ እንዲህ ሲል ጮኸባቸው» እናንተ ችጋራም ውሾች ፣ የኔ እመቤት

ዓይናቿ ፤እንደ አጥቢያ ኮከብ በሩቅ ያበራል እንጂ እናንት ከተናገራችሁት ውስጥ አንዳችም እንከን የለባትም ከዓይናቿም ውስጥ ምንም አያሸጉም ፥ቢያሸጉም እንኳ የዝባድ እጽርና የናርዶስ ሽቶ ነው ፥ይሽውም እጅግ ምርጥና ንጥር የሆነው ዓይነት ነው። ሸውራራም ጠንጋራም ጐባጣም አይደለችም ፥ዳሩ ግን እንደሸ ንበቆ መለሎ ነች ። የእመቤቴን አስደናቂ ውበት በማኳሰስ እስ ከዚህ ድረስ በድፍረት ስተናገራችሁት ስድብ ካሳዋን በውድ ዋጋ እንደምትከፍሏት እወቁ» አላቸው ።

ይህን መልስ ከተናገረ በኋላ በንዴት እንደጋለ ፊረሱን አስ ነሳና ጦሩን ዘቅዝቆ ወደ አሽሚጣጩ ነጋዴ ጋለበ ። የሰውዬው ዕድል አዛዞ ሮንዚናንቴ በግማሽ መንገድ ላይ ተደናቅፎ ባይወ ድቅ ኖሮ ባፈጮሌው ነጋዴ ላይ ለሕይወቱ የሚያሠጋ አደጋ ሳይ ደርስበት አይቀርም ነበር ። ሮንዚናንቴ ወድቆ ሲንከባለል ጌታ ውንም እንደተሸከመ ነበርና መሬት ለመሬት እየጐተተ ጥቂት አንገላታው ። ሆኖም ዶን ኪሾት በዚያ በታጠቀው አሮጌ መሣ ሪያና እንዲሁም በጦሩ በጋሻው በመኰርኩሪያው በእራስ ቁሩ በብረት ልብስ ክባድ እንደታወከ ከወደቀበት ሥፍራ ለመነሳት ብዙ ጊዜ ታግሎ ሳይሆንለት ቀረ ። ለመነሳትም እየታገለ በሚፈ ራገጥበት ጊዜ እንዲህ እያለ በነጋዴዎቹ ላይ ይዝትባቸው ነበር።

«አትሽሹ ቱሪናፋዎች ፥ አትሽሹ መድረሻ ቢሶች ፥ ቆማችሁ ጠብቁኝ ፥ አሁን መሬት ላይ ተዘርግቼ የምታዩት በፈረሴ ስሕተት ነው እንጂ በኔ ደካማነት አይምሰላችሁ ፥ ወንዶች ከሆናችሁ ላንድ ሰው መሸሽ አይገባችሁም» አላቸው ።

በዚህን ጊዜ ከነጋዴዎቹ ሌሎዎች አንደኛው ሞኛሞንና ግልፍተኛ የሆነው ጐረደማ ይህን የመሰለ ዛቻና ስድብ በመስ ማቱ ተናድዶ መልሱን በጐድኑ ላይ ካልሰጠው በስተቀር ለመታ ገስ ስላልቻለ ወዲያውኑ ከነጋዴዎቹ ተነጥሎ ወደ ዶን ኪሾት ገሠገሠና ጦሩን ነጥቆ ዛቢያውን ከሠባበረ በኋላ ባንዳኛው የዛ ቢያ ጐማጅ ከለበሰው ጥሩራ ጋር ደርቦ እየጀለጠ በሙቀጫ ውስጥ እንደገባ ስንዴ ደህና አድርጐ ይፈትገው ጀመር ። ይህን ንም ሁኔታ የሚመለከቱት ጌቶቹም በቃህ አትምታው ተወውና ተመለስ» እያሉ ይከለክሉት ነበር ፥ ጐርደማው ግን መምታቱ

ተሞት ስለነበረ የልቡን አድርሶ እስኪጠግብ ድረስ አልተወም ነበር ። በመጨረሻውም የዛቢያዎቹን ስብርባሪዎች ሊታትሞ ባል ታደለው ፈረሰኛ ጀርባ ላይ ሰነጣጥሮ ጣለው ። ይህም ሲሆን በዶን ኪሾት ላይ ይህ ሁሉ የዱላ በረዶ እየወረደበት አፉን አልዘጋም ነበርና የመናደዱ ብዛት ሰማይና ምድርን እየተራገመ በሱ አስተያ የት መንበዴዎች የሚላቸውን ነጋዴዎች ከፉኛ ይዝትባቸው ነበር ። ጐርደማው በመሠንዘር ብዛት ከንዱ ዝሎ ስለደከመው ትቶት ወደ ጌቶቹ ሄደ ። ከዚህ በኋላ ሁሉም ተከታትለው በሚንዙበት ጊዜ የዚህን ያልታደለ ተደብዳቢ ታሪክ ለጉዞአቸው ቀን ደህና የመ ጨዋወቻ አርእስት እንዲሆናቸው ወሬውን ይዘውት መንገዳቸውን ቀጠሉ ።

ዶን ኪሾት ብቻውን መቅረቱን በተመለከተ ጊዜ አሁንም ደግሞ ለመነሳት ተፍጨረጨረ ፥ዳሩ ግን ቅድም በጣም ሳይጐዳ ለመነሳት ሞክሮ ያቃተው አሁን ይበልጥ ተደቁሶ ፥ ሰውነቱ ተለ ያይቶ ፥ ግማሽ እሬሳ ሆኖ ሳለ በፍጹም ለመነሳት የማይችል መሆኑ የታወቀ ስለሆነ እሱም ይህንኑ በመረዳት ተመልሶ መተኛት ግዴታ ሆነበት ። ሆኖም በዚህ አደጋ ምክንያት የደረሰበት ጉዳት እንደ መልካም የዕድል አጋጣሚ መስሎ ታይቶት ነበር ፥ምክንያ ቱም በርሱ ግምት ይህን የመሳሰለው አደጋ ሁሉ ከብዙ ዘመን ጀምሮ የፈረሰኛነትን ተግባር በሚያከናውኑበት በጥንታዊ ዘዋሪ ፈረሰኞች ላይ ሲደርስ የኖረና የተለመደ በመሆኑ ፥ አደጋውም ሊደርስ የቻለው በፈረሱ መደናቀፍ ምክንያት በመሆኑ ይህ ሁሉ ውኔታ በፈረሰኛነት ተግባር ውስጥ ከውርደት ይልቅ ክብር የሚ ያሰጥ መሆኑን ስለአመነበት ነው ።

የሆነ ሆኖ ከወደቀበት ሥፍራ ብቻውን ለመነሳት ተስፋ የሌ ለውና በፍጹም የማይቻል መሆኑን ስለአረጋገጠ በዚያን ሰዓት ዙሪያው በወደቀበት አካባን እመሬት ላይ እንደ ተዘረረ ቆየ ።

ምዕራፍ አምስት

በፈረሰኛችን ላይ የደረሰው የመውደቅና የመደብደብ አደጋ ታሪክ የሚቀጥልበት ።

ዶን ኪሾት በአወዳደቁ አጉልነትና ከዚያም በኋላ በተጨመረበት ድብደባ ሕዋሳቱ ክፉኛ ተለያይቶ ስለነበረ እራሱን ችሎ ለመነሳት በፍጹም እንዳቃተው ተረድቶ በአደጋው ምክንያት የተሰማውን ብስጭት የሚያስረሳ አንዳች አፅናኝ ሀሳብ እንዲፈልቅለት ወደ ተለመደው መድኃኒቱ አዘነበለ ። ይህም መድኃኒቱ ያልነው በመጽሐፉ ውስጥ ካነበበው ከብዙ ታሪክ መካከል ከዚህ ከደረሰበት አደጋ ጋር ተመሳሳይነት ያለውን አንቀጽ ጠቅሶ እሱን በቃሉ እያነበበ መፅናናት ነበር ። እብደቱም ከሌሎች ከብዙዎቹ ታሪኮች መካከል በተለይ ካርሎቶ የሚባለው ጀግና በተራራ ጫፍ አቁስሎ ጥሎት የነበረውን የዚያን የባልዶቪኖንና የማንቶቫውን ማርኬዝ ታሪክ አስታወሰው ። ይህም ታሪክ ለሕማናቶች በልጅነት እድሜያቸው እየተተረከላቸው ያጠኑትና ጐልማሶች ያልረሱት ፣ የዱሮዎቹም ሽማግሌዎች እውነተኛቱን አምነው አክብረው የኖሩት ነው ። ዳሩ ግን ይህ ታሪክ በእውነተኛነቱ መሐመድ ካሳየው ተአምር የሚበልጥ አይደለም ይባላል ።

ይህ አፈ ታሪክ በዚያን ሰዓት ከደረሰበት አደጋ ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ሆኖ ስለአገኘው ታላቅ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን በሚገልጥ ሁኔታ ማንባሩን ወደመሬት ደፍቶ ያ የደኑ ቆሳይ ፈረሰኛ በጦር ቆስሎ ወድቆ በነበረበት ጊዜ የተናገረውን የመጽናኛ ቃል በቀሰስተኛ ድምጽ እንዲህ እያለ ማንጐራጐር ጀመረ ። የቃሉም ጥቅስ ቀጥሎ ያለው ነው ።

«ወዬት ነሽ እመቤቴ ስሚኝ ፣
«ስለአደጋዬ ያላዘንሽው አንቺ ጨካኝ ፣

«መጐዳቴን አታውቂምን በውነሽ ፣
ወይስ ቃል የማታከብሪ አባይ ነሽ»

በዚህ አኳኋን እያንጐራጐረ እስከ ሁለት የሚጥም ጥቅሶች ድረስ በመቀጠል ፣

«ክቡር የማንቶቫው መስፍን ጀግናው ወንድ ፣
አጐቴ ጌታዬ የኔ ሥጋ ዘመድ ።»

ብሎ ከመጨረሱ ወዲያውኑ እንደ እድል አጋጣሚ አንድ ያገሩ ሰውና ወዲህም ቅርብ ጐረቤቱ የሆነ ገበሬ አንድ ጆንያ ስንዴ አስፈጭቶ ወደ ቤቱ ለመመለስ እንደተጣደፈ አህያውን እየነዳ በዚሁ ዶን ኪሾት በወደቀበት መንገድ ለማለፍ በሚመጣበት ጊዜ ይህ ለጊዜው የማያውቀው ሰው እመንገድ መካከል ወድቆ በመሬረ ሀዘን ሲያንጐራጉር ስለአገኘው በሰብዓዊ እርህራሄ ተገፋፍቶ ተጠጋውና መጀመሪያ ማን መሆኑን ፣ ምንስ አጣችቶት እንደሚያቃስት ጠየቀው ። ዶን ኪሾትም ዓይኑን ቀና አድርጐ ገበሬውን ከማየቱ ወዲያው ያላንዳች ጥርጣሬ ቅድም በሃሳቡ ታይቶት የታሪኩን ጥቅስ ሲያነበው የነበረው የማንቶቫው መስፍን በአካል አጠገቡ ቆሞ «ምንሆነሃል» ብሎ የጠየቀው ስለመሰለው የታሪኩን ጥቅስ እያከታተለ በመቀጠል በእንጉርጉሮ ምስጢር ለጥያቄው መልስ በሚሰጥበት ጊዜ የአደጋውን ምክንያት በመግለጥና እንዲሁም ባልዶቪኖ የሚባለው ፈረሰኛ እጮኛው ከነበረችው ከንጉሡ ልጅ ጋር ያደረገውን ጽኑ ፍቅር እስከነ ምክንያቱ በመዘርዘር በዚያው ባልዶቪኖ በተናገረው ግጥም ውስጥ ያለውን ጥቅስ በሙሉ ቀድቶ ልነበረው አስረዳው ። ገበሬውም ዶን ኪሾት የዘባረቀለትን መላ የሌለው መልስ በመስማቱ በጣም ስለተገረመ መልኩን አጣርቶ ለማየት ሲል በዱላ ተመትቶ የተሠባበረውን የራስ ቁር አውልቆ ፣ ትቢያ የወረሰውን ፊቱን ጠራርጐ ቢመለከተው ያ የአጎሩ ክቡርቴ መሆኑን ስለአወቀ በደንበኛው ስሙ ጠርቶ እንዲህ አለው ።

« ጌታው ኪሾት ሆይ ፤ (ቀድሞ ከነአንጐሉ ሳለ አንዱ ምናውቀው መሆን የሚገባው ስሙ ይህ ነበርና) ኧረ ለመሆኑ ዛሪህ ሁኔታ አንካክቶ የጣለዎት ማነው? ብሎ ጠየቀው ።

ዶን ኪሾት ግን ለጥያቄዎቹ ሁሉ የሚሰጠው መልስ ያንኑ በመጽሐፍ ውስጥ ተጽፎ የሚገኘውን ጥቅስ ብቻ እንጂ ትክክለኛውን መልስ ሊሰጠው አልቻለም ነበር። ስለዚህ ደጉ ገበሬ ግራ ስለገባው ምናልባት ልቡን የሚነሳው አቆሳሰል ቆስሎ ይሆናል በማለት ተጠራጥሮ ይህንኑ ለማረጋገጥ ሲል የተቻለውን ያህል ታግሎ የነሐስ ጥሩራውንና የትከሻ ልባዱን አውልቆ እያገላበጠ ሰውነቱን በዳብሰው ከሰንበር በስተቀር ለሕይወቱ የሚያሰጋ ቁስልና የደም ምልክት አላገኘበትም ነበር። ሆኖም በጉረቤትነቱ የሚገባውን ግዴታ ለመፈጸም ሲል በብዙ ደክሞ አቅፎ ከመሬት አነሳውና ዶቂት ከተጫነች አህያ ላይ አመቻችቶ አስቀመጠው። በፈረሱ ላይ ሊያስቀምጠው ያልፈቀደበትም ምክንያት ከፈረሱ ይልቅ አህያይቱ የረጋችና እርምጃዋም የማይጠው መሆኑን ስለገመተ ነው።

ቀጥሎም የተበታተነውን መሣሪያና የጦሩንም ስብርባሪ ከየወደቀበት ሊቃቅሞ በሮንዚናንቴ ቀዳማ ላይ ካሠረ በኋላ ፈረሱን በዛቡ አህያይቱን በሎከዋ እየሳበ በዶን ኪሾት መቀባገር በጣም እንዳዘነና እንደተከዘ ያንን ስፍራ ለቅቆ ወደ አገሩ አቅጣጫ ጉዞውን ቀጠለ። ዶን ኪሾትም በበኩሉ የተመታው በትር ከፉኛ ጉድቶት ሰውነቱ ተገሸላልጦ ስለነበረ በአህያው ላይ እንደልቡ ለመቀመጥ ባለመቻሉ የተነሳ ያደረበት ብስጭትና ንዴት በጣም እያስቃሰተው የሚተነፍሰው ኃይለኛ እስትንፋስ ሰማዩን ሽቅብ የሚነፋው ይመስል ነበር። እዚህም ላይ ገበሬው አላስችልህ ብሎት እስከዚህ ድረስ እያግጠ የሚያቃስተበትን ምክንያት መጠየቅ አሰፈላጊ መስሎ ስለታየው ሕመሙ ምን እንደሆነ እንዲነግረው ዳግመኛ ጠየቀው። መቸም ዶን ኪሾትን የለከፈው ሰይጣን አለቀቀውም ነበርና በፈረሰኞች የታሪክ መጽሐፍ ውስጥ ከተጻፉት ተረቶች መካከል አሁን ከሚገኝበት ያደጋ ሁኔታ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ሁኔታዎች ስለአስታወሰው ቅድም ያቋረጠውን እንደገና በመቀጠል የባልዶቪኖን ታሪክ ዘለሰና የአንቴኳራው ግንብ መስፍን ዶን ድሪጌዝ ዴና ቫዬዝ የሚባለው የጥቁሩን ዓረብ ልዑል አቢን ዳራዬዝን ማርክ ወደ ግንቡ ወሰኒ ቤት ወስዶ በግዞት ያሠረውን ታሪክ ደቀነለት። ስለዚህ ገበሬው «ምን ሆነሃል፣ ምንስ ይሰማሃል» ብሎ

ላቀረበለት ጥያቄ የሰጠው መልስ በዚያን ጊዜ አሰሪኛው የዓረብ ልዑል ለዶን ሮድሪጌዝ ዴ ናርቫዬዝ የተናገረውን ታልፍ የዘረዘረውን ሐተታ ጠቅሶ ታሪኩ ተጽፎ በሚተረክበት «ዲያና ዴ ቴባለው በጊዮርጊስ ሞንትማየር ድርሰት ላይ ያነበበውን ታል ሳይገድፍና ሳያሳሳት ያንኑ እየከለሰ ማስረዳት ነበር። ይህም ጀግና የተጠቀመበት ከገበሬው ጥያቄ ጋር የተጣረሰው ዝል በዳና ፍሬ ከርስኪ የሆነ መልስ ገበሬው በሰማው ጊዜ መገረሱ ስለተሳከረበት በውነቱ ከዲያብሎስ ጋር እንጂ ከሰው ጋር የሚነጋገር አልመሰለውም። በዚህ አኳኋን ገበሬው ይህ ጉረቤቱ በፍጹም እንጉሉ የተናወጸ መሆኑን አረጋግጦ ካመነ ቁኣላ ሳይመሽበት በጊዜ ወደ መንደር ገብቶ ከበርቴውን ለቤተሰቦቹ ለማስረከብና ከዚህም ጅሮውን እየኩረኩረ ካሰለቸው የቅኔ ዝብዝብ ለመገላገል ሲል እርምጃውን ያፋጥን ጀመር። ዶን ኪሾትም ዝልበዳውን ከጨረሰ በኋላ እንደገና ዝርዝሩን ይግስረዳት ገበሬውን እንዲህ አለው።

«ከቡር ዶን ሮድሪጌዝ ዴ ናርቫዬዝ ሆይ፣ (ገበሬውን) ቅድም ሰሚን የጠራኋት ውቢቷ ጃሪፋ በአሁኑ አጋጣሚ ዘንፋላይቱ የቶቦሶይቱ ዱልቺኔያ መሆኗ ነው። በዚህ ዓለም ላይ ታይቱው ያለፉትን፣ አሁንም የሚታዩትንና ወደፊትም ሊታዩ የሚጠበቁትን እጅግ ስመጥር የሆኑትን የፈረሰኛነት ተግባሮች በሚያስደንቅ አኳኋን የፈጸምኩትና ገናም የምፈጽመው የዱልቺኔያን ክብር ከሴሎቹ ሴቶች ለማስበለጥ ስል ነው።»

«ወይኔ ያልታደልኩት» ሲል ገበሬው መለሰ። እስቲ ከቡርነትዎ ዓይንዎን ይከፈቱና ደህና አድርገው ይመልከቱኝ እኔ የሚያውቁኝ ጉረቤትዎ ጴጥሮስ አሎንሶ ነኝ እንጂ ዶን ሮድሪጌዝ ዴ ናርቫዬዝ ወይም የማንቶቫው መስፍን አይደለሁ ሥ፡ እርስዎም በመንደራችን የታወቁት ደኅ ከበርቴ ጌታው ዶን ኪሾት ነዎት እንጂ ቁስለኛው ባልዶቪኖ ወይም ዓረብ አቢን ዳራዬዝ አይደሉም» አለው።

«እኔ እራሴ እኔ መሆኔን ከኔ ይበልጥ አውቆ የሚነግረኝን ሎ አልፈለግሁም» ሲል ዶን ኪሾት ክርክሩን ጀመረ፣ ንግግሩን ቋተጠል» ከዚህም በስተቀር ደግሞ እንዚህን የጠራኋቸውን

ሰዎች በመሆን ብቻ ላልወሰን ከነሱም በልጬ አሥራ ሁለቱን የፈረሳይ ፈረሰኞች ፡ ዘጠኙን የዓለም ስመጥር ተዋጊዎች ለመ ሆን የምችል ነኝ ። ይህንንም ስል እነዚህ ታላላቅ ሰዎች ሁሉም እንድነት ሆነው የፈጸሙትንና በተለይም ደግሞ እያንዳንዳቸው የሠሩት ሞያና ጀብዱ ተደምሮ እኔ ብቻዬን ሆኜ ከፈጸምኩት ጀብዱ ጋር ቢመዛዘን ውጤቱ ኩበትና ድንጋይ እንደሚሆን አይ ጠረጠርም» ሲል ንግግሩን አቆመ ።

ገበሬውና ዶን ኪሾት በዚህ ንትርክና በሴላም ይህን በመ ሳሰሉው አርእስት እየተጨቃጨቁ ሲጓዙ ውለው ጀምበር ጠልቃ ጨለማው ለዓይን መያዝ ሲጀምር ወደ መንደራቸው ድምበር ተቃ ረቡ ። ገበሬውም ይህ በእነሩ የታወቀው ጨዋ ከበርቴ በዚህ ሁኔታ ተጉሳቁሎ እንደሠናጋ በአሀያ ላይተጭና ወደ ቤቱ ሲመ ለስ የሚያዩት ሰዎች ሁሉ መሰቂያና መተረቻ እንዳያደርጉት በማ ሰብ ጨለማው አስቲደነጉር ድረስ ከመንገድ ጐራ ብሎ ቆየ ። ሰዓቱ የተመቸ መሆኑንም ካየ በኋላ አጋሰሶቹን ከነጭነታቸው እየነዳ ጉዘውን ቀጥሎ ወደ መንደሩ ገባ ። ከዚያም ወደ ዶን ኪሾት ቤት በራፍ ሲደርስ ከቤት ውስጥ በጣም የደመቀ ጫጫ ታና ሁካታ ሰማ ። በቤት ውስጥ ያሉትንም ሰዎች በድምጻቸው እንደለያቸው ለዶን ኪሾት ጥብቅ ወዳጆች የሆኑት የደብሩ ቄስና የመንደሩ ጠጉር ቆራጭ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ቻለ ። ባልቴቲም ድምጿን ከፍ አድርጋ እንዲህ እያለች ታማርር ነበር።

«በጌታዬ ላይ የደረሰው ይህ አደጋ ምን ይመስልዎታል? አባ ጴጥሮስ ፔሬስ(የቄሱ ስም ይህ ነበርና)» አሳቸውም ሆኑ ፈረሳቸው ፡ ጋሻቸውም ሆነ ጦራቸው ፡ መሣሪያቸው ሁሉ ጭም ጭምታቸው ከጠፋ እነሆ ስድስት ቀን ስለሆናቸው የደረሱበት ቦታ አልታወቀም ወሬያቸውንም ብናስጠይቅ አየናቸው የሚሰን ሰው አላገኘንም ። ከቶ ምን ይበጀን ይሆን? ወይኔ ያልታደልኩት፡ ሁላችንም ለሞት የተፈጠርን መሆናችን እውነት የሆነውን ያህል እሳቸው እዚህ በነበሩበት ጊዜ ሰሞኑን ሥራ ፈትተው እነዚያን የተረገሙ የፈረሰኛነት መጻሕፍት ከጠዋት እስከ ማታ ሲነብ ንዙ ከስነበቱ በኋላ ሕሊናቸው ተናውጠ አገር ጥለው ለመኳብ ለል እንደበቁ ያለጥርጥር አምናለሁ ። ዛሬ ትዝ ብሎኝ እንደማ ቴታውሰው ያለወትሮአቸው ብዙ ጊዜ ብቻቸውን ሲነጋገሩ ድን ጉት አፈትልኳቸው ምስጢራቸውን እንደሰማሁት ዙዋሪ ፈረሰኛ ሆነው ዓለምን እየዞሩ አጋጣሚያቸውን ለመፈለግ ይመኙ እንደ ነበረ አረጋግጣለሁ ። አየ አለመታደል ፡ አየ የአምላክ ቁጣ ፡ የዛሬውን አያድርግባቸውና በድፍን ማንቻ ውስጥ ለሕዝብ ያስደነ ቀውን አስተዋይ አእምሮአቸውን ስማናወጥ የበቁት እነዚህ የተ ረገሙ መሕጻፍት ስለሆኑ ዲያብሎስና ባርናባስ ጠራርገው ይዘ ዋቸው በሄዱ» እያለች ከራኛ ስትንቀለቀል በሩቅ ትሰማ ነበር። ያጐቱ ልጅ ደግሞ ከአሮጊቷ ተቀበለችና ይህንኑ ዓይነት ማግ ረር ማለማት ጀመረች ። እንዲያውም እፏ ብሳ የመግረሱዋን ጣእም ይበልጥ የሚያንገሸግሽ በማድረግ እንዲህ ስትል ነበር ።

«የኔታ ኒኮላ እንዲያውቁት ልገልጥልዎ የፈለግሁት (የጠጉር ቆራጩ ስም ይህ ነበርና) ብዙ ጊዜ በእጐቴ ላይ ያርስባቸው እንዳየሁት በቤተመሕፍታቸው ውስጥ ብቻቸውን ዘግተው ሁለት ቀንና ሁለት ሌሊት እረፍት ሳያደርጉ እነዚህን ገጾ ቢስ መጻሕ ፍት በማንበብ ተወስነው እንደነበረ የማስታውስ መሆኔን ነው ። አንዳንዴም የያዙትን መጽሐፍ እጥፈው ይወረውሩና ጐራዴያ ቸውን መዝዘው የክፍሱን ግድግዳና መዓዘን እየመቱና እየወጉ ይሰነጣጥቁት ነበር ። በመሰንዘር ብዛት ከንዳቸው ዝሎ ሲደክ ማቸው በሐሳባቸው ግምት ግድንግድ የሆኑ አራት ጠብደል ጀዊ ሳዎች የገደሉ መስሎአቸው ይፎክራሉ ። ከድካማቸው ብዛት የተ ነሳ በሰውነታቸው ላይ የሚንቆረቆረው ነጭ ላብ በውጊያው ላይ ቆስለው የሚፈስባቸው ደም ነው ይላሉ ። ከዚህም በኋላ አንድ ግብረጀ ሙሉ ቀዝቃዛ ወሀ እንዳመጣላቸው ያዘዙኝና ባንድ ትንፋሽ ጅው አድርገው ይጠጡታል ። ይህንንም አድርገው ሰው ነታቸውን ካወቁ በኋላ ወሀው ተአምራዊ አብነት ያለው ጠበልና የላከላቸውም አቃቢ ወዳጃቸው የሆነው ታላቁ ጥበቡኛ ሺፎ የሚ ባለው መሆኑን አምነው ይናገራሉ ። ይህ ሁሉ ሲሆን ባንድ ጥግ ከለላ ይገ እመለከታቸው ስለነበር አጐቴ የሚያደርጉትን የእብ ደት ሥራ ሁሉ በጊዜያቱ እንድታውቁት አስጠንቅቄአችሁ አሁን ከደረሱበት ነጥብ ላይ ከመድረሳቸው በፊት የሚፈፀሱበትን መድ ኃኒት እንድትፈልጉላቸው ሳላያርግ በመቅረቱ ጥሩቱ ሙሉ በሙሉ የኔ መሆኑ ይሰማኛል ። ይህን ያየሁትን የእብደት ዋዜማ ችላ

ሳልል አበክሬ ነግሬአችሁ ቢሆን ናሮ በአብዶታቸው እንዳይቀ ጥሉ ለማቋረጥ የሚረዳውን ብልሀት በመፈለግ በተለይ እነዚህን ውጉዛን መጻሕፍትና እነዚያንም እርኩማን ዶራስያን ጭምር እሳት ውስጥ ትጨምሩአቸው ነበር ። በእርግጥም እንደመሰቀል ደመራ መቃጠል የሚገባቸው አያሌ መጻሕፍት አሉዋቸው» አለች ።

ቂሱም በርጋታ ሲያዳምጧት ቆይተው ነበርና እሷ. ይህን ተናግራ እንዳበቃች እንዲህ ሲሉ የራሳቸውን አስተያየት ገለጡ ላት ።» ልጄ ሆይ ፣ መጠንቀቅ ፊት እንደነበረ አንቺም አውቀሽ ዋል ። ይሁን እንጂ» ያለፈ ወሀ አይፈጭም» እንደሚባለው ተረት ባለፈው ጉድለት መጻጸትን ትተን ለመጪው የሚበጀውን መድ ኃኒት ብንፈልግለት የተሻለ ነው ። እኔም ስለነዚህ መጻሕፍት መቃጠል ያንቺኑ ዓይነት ሃሳብ በልቤ አሳድሬ ነበር ። እንዲያ ውም ምን አለ በይኝ የዛፉን ሌሊት በሰላም አንግቶልን የነገ ሰዎች ይበለን እንጂ የነዚህን መጻሕፍት ቅጣት ለመወሰን ደን በኛ ችሎት አስችሎን እየመረመርን ጥፋተኞችን በእሳት የመቃ ጠል ፍርድ ሳንፈርድባቸው የነገውን ቀን አናሳልፈውም ። ይህነ ንም በማድረጋችን ወዳጆችንን ከእብዶቱ አድነን እንዲሁም ደግሞ ወደፊት እነዚህን መጻሕፍት አግኝቶ ለማንበብ አጋ ጣሚ ፈቅዶለት በማንበብ ያልታደለው ወዳጃችን የደረሰበትን ዓይነት በሽታ ሊደርስበት የሚችለውን ሁለተኛውን ሰው እናስ ጥለዋለን ። ላሁኑ ግን የሚያዛልቀን ብልሀት በየአገሩ ሰው ልክን ወሬውን ማጠያየቅና አድራሻውን ስናውቀው ሒደን አባብለን ማምጣት ብቻ ነው» አሉ ።

እነዚህ ንግግሮች ሁሉ ውጭ ቆመው ለሚያዳምጡት ለገበ ሬውና ለዶን ኪሾት ጉልተው ይሰሙ ስለነበር ገበሬው የጉረቤ ቱን በሽታ መነሻ ካወቀው በኋላ እንዲህ ሲል ሮኽ ተጣራ ።

«ቤቶች ፣ ክፈቱልኝ ፣ ጌታው ባልዶቬናና የማንቶቫው መስ ፍን በብርቱ ቆስለው ተመልሰው እደጅ ቆመዋል ። እንዲሁም የአንቴካራው ግንብ መስፍን ጀግናው ዶን ሮድሪገዝ ዴ ናርቫ ዬዝ የዓረቡን ልውል አቢንዳራዬዝን አሥረው አምጥተውታልና ፈጥናችሁ ተቀበሉን» አላቸው ።

በዚህ ጥሪ ተደናግጠው እቤት ውስጥ የነበሩት ሰዎች በሩን ከፍተው ግር ብለው ወጡ የመጡትንም እንግዶች በተመለከቱ

ጊዜ ለቤቶቹ ጌታና አጉት ፣ ለውሮች ደግሞ ወዳጃቸው መሆ ኑን አወቁ እሱም አቅሙ የማይችል በመሆኑ እራሱን ችሎ ከአ ሀያይቱ ላይ አልወረደም ነበርና ተቀባዮቹ ዙሪያውን ከብበው አቅፈውና ደግፈው አወረዱት ። ከወረደም በኋላ እንዲህ አላቸው

«ተውኝ እባክችሁ ግርግር አታብዙብኝ ፣ በፈረሴ መደናቱፍ ምክንያት ወድቄ በብርቱ ቆስያለሁና በቶሎ ወደ አልጋዬ ወስዳ ችሁ አስተኙኝ ። ቢቻልም በሽታዬን መርምራ እንድትፈውሰኝ ዑርጋንዳን ጥሩልኝ ።

በዚህ አነጋገሩ ላይ አሮጊቷ እንዲህ ስትል በመገረም መል ሰችለት ። «አከሀደከ ሰይጣን ፣ አያችሁልኝ አዝማሚያቸውን ፣ ይበሉ ወደቤት ይግቡ ጌታዬ ፣ አይዞት ፣ ይበርቱ ምንም አይሆኑ ፣ ይህችን የሚሏትን ኢቶት ወላፊንዳን ባንጠራልዎትም ለማከሙና ለማስታመሙ እኛው እንበቃለን«ካለች በኋላ» ለዚህ እብደት ያበቋቸው እነዚህ አሳሳች መልዕክት ያዘሉ መጻሕፍት ስለሆኑ አውንም እርግማኔን ሺህ ጊዜ እየደጋገምኩ የሚያጠፋቸውን መዓት እንዲያወርድባቸው እረግማቸዋለሁ» ስትል ምርር ብላ ተናገረች ። ከዚህም በኋላ እየደጋገሙ አልጋው ላይ አውጥተው አጋደሙትና ልብሱን አውልቀው ገላውን እየዳበሱ ቁስሉን ይፈልጉለት ጀመር ። ዳሩ ግን እንዳች የሚያሰጋ ምልክት ሳያ ገኙበት ቀሩ እሱም በሰውነቱ ላይ ቁስል የሚፈልጉ መሆናቸ ውን አውቆ እንዲህ ሲል አሰረዳቸው ።

«ሕመሜ የውስጥ ድቁሳትና ወለምታ ነው እንጂ የላይ ቁስል አይደለም ። ይህም የሆነበት ምክንያት በምድር ላይ ታይ ተው ከማይታወቁ ፣ እጅግ ኃይለኛ ከሆኑ ፣ ከአሥር ጀግኖቻች ጋር እንዱ ብቻዬን ውጊያ ገጥሜ ፣ ሁሉንም አሸንፈዎቸው ሲሸሹ እነሱን ለማባረር ፈረሴን አስነስቼ በፍጥነት ስጋልብ ፣ እመንገድ መሐል የተጐሰቶ ቋጥኝ አጠገብ ደረስኩና ያንን ዘሎ እንዲሻ ገር ፈረሴን እስገደድኩት ፣ በዚህን ጊዜ እመር ብሎ ለመዘለል ሽቅብ ሲነሳ ባለመታደል ተደናቅፎ ሮኋሊት ስለወደቅን ከኩርቻ ላይ ተፈናጥሬ ከድንጋዩ ጋር ተላጋውና እንደምታየኝ ለጉዳት ቢታው ጸኅለ በኋላ ንግግሩን በመቀጠል» ምንም እንኳ እነዚህ ጀዊግዎች ፈርታው ለመሸሽ የተገደዱት እኔን እጅራን ቢሆን እው

ነተኛውን ለመናገር እነሱን የመሰለ ኃይለኛ ጦረኛ ከፀሐይ በታች በፍጹም አላየሁም ። ምናልባትም አይቻለሁ የሚለኝ ሰው ቢኖር ዋሾነቱን አስተባብልዋለሁ» አላቸው ።

ይህን ሁሉ ጉራ ሲዘከዝክ መምህሩ በጥንቃቄ ሲያዳመጡት ነበርና እንደጨረሰ ተቀብለው እንዲህ ሲሉ መደነቃቸውን ገለጡ «ወዲያልኝ፣ ወዲያ!፡ አይጣል እኮ ነው የሚሻለው ።» ስሙኝ ወዳጄ ግድየልዎትም አይቸኩሉ ፣ እነዚያ ያመለጡት ኃይለኛ ጃዊነዎች የተደበቁበትን ሥፍራ እናውቀዋለንና ሲነጋ አጥምደን ይዘን በመ ስኩ ላይ እናዝፍናቸዋለን ፣ ካሉ በኋላ ወደ ባልቴቷ መለሰ ብለው» ይህ የያዝኩት መሰቀል ግዘት ይውንብኝ ነገ ከመምሸቱ በፊት እነዚህን መጻሕፍት ሳላቃጥላቸው ብቀር በእውነቱ ጴጥሮስ ተብዬ አልጠራም» ብለው ዛቱ ።

ቄሱም ተናግረው እንዳበቁ ሌሎች ዶን ኪሾትን የከበቡት ሰዎች በእብደቱ እየተገረሙ ስለደረሰበት አደጋ ብዙ ጥያቄ አቅ ርበውለት ነበር ። እሱ ግን በዚያን ሰዓት እጅግ አስፈላጊው የነበ ረው ከወሬ ይልቅ ምግብ ሰጥተውት በልቶ መተኛት ስለነበረ ይህንኑ እንዲያደርጉለት ከመለመኑ በስተቀር ለጥያቄያቸው እንዳች መልስ ሊሰጣቸው አልፈቀደም ነበር ። እነሱም ይህንኑ ፍላ ጐቱን አውቀው የውጪዎቹ ምሀረቱን ይላክለት እያሉ ተሰነባ ብተው ወደ እየቤታቸው ለመሔድ ተነሱ ። ከዚህም በኋላ ቄሱ ገበሬውን ጠቀሱትና በተለይ ቆይታ አድርገው ዶን ኪሾትን ለማ ግኘትና ወደቤቱም ለማምጣት እንደምን አድርጐ እንደሆነለት እንዲያስረዳቸው በሰፊው ይመረምሩት ጀመር ። ገበሬውም ምንም ሳይደብቃቸው ዶን ኪሾትን መንገድ ዳር ወድቆ ባገኘው ጊዜ ምንሆነህል ብሎ ላቀረበለት ጥያቄ የሰጠውን የተዘበራረቀ መልስና ከዚያም ወዲህ በእሀያው ላይ ጭኖ ወደቤት ሲያመጣው መንገድ ለመንገድ ያጐረፈውን የእብደት ንግግር ሁሉ ዘርዝሮ አስረዳቸው ቄሱም ይህን አሳዛኝ ሁኔታ በመስማታቸው ተከዘው ቅድም እን ደተነገረቱት በማግሥቱ ጧት በቁርጥ ውሳኔ ሊያደርጉት ያቀዱ ትን ሀሳብ ያለማወላወል እንዲገፋበት የባሰውን አስጨከናቸው ይኸውም የልብ ወዳጃቸውን የመንደሩን ጠጉር ቆራጭ የኔታ ኒኮላን ጠርተው ማለዳ ወደ ዶን ኪሾት ቤት ሔደው መጻሕፍቱን እየበዘበዙ ጠንቀኛ የሆኑትን በእሳት ማቃጠል ነበር ።

ምዕራፍ 6

ቄሱና ጠጉር ቆራጩ በብልሁ ከበርቴ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ያደረጉት አስገራሚ የሆነ ጠቅላላ የመጻሕፍት ብዝበዛ ሁኔታ ይተረካል ፣

ቄሱና ጠጉር ቆራጩ ማለዳ ተነስተው ወደ ዶን ኪሾት ቤት ሲመጡ እሱ ገና ተኝቶ ነበርና ከመንቃቱ በፊት ቄሱ እን ዚያ ይህን ሁሉ ጉዳት ያስከተሉት መጻሕፍት የሚገኙበትን ክፍል ቁልፉን እንድትሰጣቸው ልጅቷን ጠየቋት ። እፅ ም ደስ እን ዳላት ካስቀመጠችበት ሥፍራ አንስታ ለቄሱ አስረከበቻቸውና በሩን ከፍታው ሁሉም ተከታትለው አሮጊቷም ጭምር ወደ ክፍሉ ገቡ ።በክፍሉም ውስጥ ከመቶ የሚበልጡ በጣም ጥሩ ሆነው የተጠረዙ ትልልቅና ትንንሽ መጻሕፍት በየመልካቸው ተደርድረው አገኙ ። አሮጊቷ እነዚህን መጻሕፍት እንዳየች ወዲያውኑ ፈጥና ከክፍሉ ወጣችና ከጥቂት ሰዓት በኋላ ባንድ ብርሴ ሙሉ የጠበል ውሀና እንዲሁም የመርጫ ሙሬ ይዛ ተመልሳ ለቄሱ ስትሰጥ እንዲህ አለች ።

«መምር ሆይ ፣ ይህን ይቀበሉኝ እና በነዚህ አስፈሪና አስጸ ንጋጭ በሆኑት መጻሕፍት ውስጥ የተደበቁትን ጥበቦች ለማጥ ፋት ክፍሎቹን በሙሉ ይርጩልኝ ። አውን በእሳት አቃጥለን ከዚህ ዓለም ልናጠፋቸው ያደረግነውን ቁርጥ ሃሳብ ሲያውቁ ቂማቸውን ለመበቀል ሲሉ በልታዊ አደጋ ሳይጥሉብን አይቀሩ ምና አስቀድመን ብናስደነግጣቸው የተሻለ ነው»

ቄሱም አሮጊቷ የገለጠችላቸውን ሃሳብ በሰሙ ጊዜ በየጥህ ነታ ሰቁና ከነዚህ መጻሕፍት መካከል ምናልባት መቃጠል የማይገባቸው አንዳንድ ሳይኖርባቸው አይቀርም በማለት ጸሐፍ

ቹን እየመረመሩ ለመለየት እንዲመቻቸው ጠጉር ቆራጩ አንድ ባንድ እያነሳ እንዲያቀብላቸው ነገሩት ።

ልጅቷም ይህን ምክራቸውን በሰማች ጊዜ በበኩሏ እንዲህ ስትል ሃሳቧን ሰጠች ። «አባ ሆይ ፥ የለም አይሆንም ፥ ሁሉም ኩልኩሎች በደለኞች ስለሆኑ አንዳቸውም ተመርጠው መቅረት አይገባቸውም ። የሚሻለው በመስኩቱ በኩል እየወረወርን እግቢው መስክ ላይ መጣል እሳት ለኩሰን ማቃጠል ነው ። ወይም ደግሞ እየተሸከምን አውጥተን ከግቢው ራት ወዳለ ሥፍራ ከምረን ማጋየት ነው ። ይህም ሲሆን ጢሱ ወደቤት ተመልሶ ሊያፍነን አይችልም» አለች ።

አሮጊቷም ይህንኑ ሃሳብ ደጋፊ ስለሆች ሁለቱም ሴቶች እነዚህን ንፁሃን መጻሕፍት ያለአበሳቸው ለማውደም ያደረባቸው ፍላጐት እጅግ ከፍ ያለ ነበር ። ቄሱ ግን አርአስታቸውን እንኳን ከማንበባቸው በፊት ኩልኩሎች እንዲቃጠሉ በቀረባላቸው የፍርድ ሃሳብ ለመስማማት አልፈቀዱም ነበርና በዚያው በቀድሞው ውሳኔያቸው ፀኑ ። ለመጀመሪያ ጊዜ የኔታ ኒኮላ የሰጣቸው መጽሐፍ «አራቱ የጋውላው አማዲስ» መጻሕፍት ነበሩ ።

«ወይ አጋጣሚ» አሉ ቄሱ» አያችሁልኝ ሆን ብሎ እሱው ሲወጣ ሲያወሩ እንደሰማሁት በእስፓኚያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው የፈረሰኛነት ልብ ወለድ ድርሰት ይህ ነው ይባላል ፥ የቀሩት ሁሉ ጽንሰታቸውንና መሠረታቸውን ያገኙት ከዚሁ ድርሰት ላይ ነው ። ስለዚህ ይህን የመሰለ የጥሩት ጉራ ለሆነው ጉማ ዋና መሥራች እንደመሆኑ መጠን ያለአንዳች ይቅርታ የመቃጠል ፍርዱን መቀበል ይገበዋል ።

«አይሆንም መምሩ» አለ ጠጉር ቆራጩ እኔ እንደሰማሁት ካሁን ቀደም ከተጻፉት ከዚህ ዓይነት መጻሕፍት ውስጥ በተለይ ብልጫ ያለው ነው ስለሚባል ከሚመስሉት መጻሕፍት ዓይነተኛውና አንዱ በመሆኑ ምክንያት ልናተርፈው ይገባናል» ።

«ይህም እውነትህን» ነው ፤ አሉ ቄሱ «በዚህ ምክንያት ለጊዜው ምሕረት አድርገንለታል ። እስቲ ደግሞ እኮኑ ያለውን እንየው»

ጠጉር ቆራጩ እነበበና «የጋውላው አማዲስ የበሀር ልጅ የኤስፕላንዲያን ጉብዝና» የሚል ነው አላቸው ።

«አይ ሂሂ» አሉ ቄሱ «መች ይሆንና ያባቴን ደግነት ልጅ አይወርስም ። በይ እንቺ እህቴዋ ተቀበይኝና ያንን መስኮት ከፍተሽ ወርውረሽ እመስኩ ላይ ጣይው ። በማቃጠያውም ሥፍራ ላይ የመግነጃውን እንጨት መረብረብ ጀመሩ» ብለው ትእዛዝ ሰጡ። አሮጊቷም በደስታ እንደፈነደቁች በሩጫ ወጣችና እሳቱን እቶ ጣጠሰች ። ወዲያውኑ ጉበዙ ኤስፕላንዲያንም ወደ መስኩ በረረና የተዛተበትን የእሳት ቅጣት ለመቀበል በተቀደሰው ትእግሥቱ እርፎ ይጠብቅ ጀመር ።

«በል ቀጥል» አሉ ቄሱ ፥

ጠጉር ቆራጩም «ይህኛው ደግሞ» ሲል ግስረዳቱን ቀጠለ «የግሪኩ አማዲስ» ነው በዚህ መደዳ ያሉት ሁሉ እና እንደሚ መስለኝ የዚያው የአማዲስ ዝርያዎች ናቸው ።

«እንግዲያውስ ሁሉን አውርዳቸውና ወደ መስኩ ይወሰዱ» ሲሉ ቄሱ መለሱ» የንግሥት ፒንቲክኔስትራና» የእረኛው ጻሪ ኔሎም» ታሪክ ከነደራሲው መውድስና ከነ ሰይጣናዊ ሐተታው ጭምር በእሳት ይኮማተር ሌላው ቀርቶ የወለዱኝ አባቴ እንኳ በዙዋሪ ፈረሰኛነት መልክ እራቴ መጥተው ባያቸው እንድነት ቀላቅዬ ለማቃጠል እንደማልመለስ እወራረዳለሁ አሉ ።

«የእኔም ሃሳብ ይኸው ነው» አለ ጠጉር ቆራጩ ።

«እኔም እንዲሁ ነኝ» አለች ልጅቷ ።

ባልቴቷም «ሃሳባችሁ አንድ ከሆነ ወዲህ አቀብሉኝና ከሌሎቹ ጋር ወደ መስኩ ልውሰዳቸው ስላለች ጠጉር ቆራጩ ሰብሰቦ ካሰ ታቀፋት በኋላ መስላሉን መውጣትና መውረድ ጊዜ እንዳይፈጅባት በመስኩቱ በኩል እያምዘገዘገች ወደ መስኩ ትጥል ጀመር።

ቄሱ ከመደርደሪያው ላይ አንዱን አነሱና «ይህኛው አሳዝጅ ደግሞ ምን ይባላል» ሲሉ ጠጉር ቆራጩን ጠየቁት ።

«ይህኛው» ሲል መለሰ ጠጉር ቆራጩ» የላውራው ዶን አልቫንቴ» የሚባለው ነው ።

«የዚህ መጽሐፍ ደራሲ» ሲሉ ቄሱ በማስረዳት» የአበበች ክበብ» የሚለውን መጽሐፍ የደረስ ነው ። በውነቱ ከሁለቱ መጻ ሕፍት የትኛው እውነተኛ እንደሆነ ወይም ደግሞ በተሻለ አነጋገር በሀለተኛነቱ እነስ የሚለው የትኛው እንደሆነ ለማወቅ አልቻልኩም ። ይሁን እንጂ አረጋግጭ ለመናገር የምችለው በአሳሳችነትና በአጭበርባሪነት ጥፋት ወደ መስኩ መሄድ የሚ ገባው መሆኑን ብቻ ነው» አሉ ።

«ይህ አሁን የሚመጣው ደግሞ» አለ ጠጉር ቆራጩ የኢርካኒየው ፍሎሪስማርቲ» የሚባለው ነው ።

እስቲ ወዲህ በለው ፣ ጌታው አቶ ፍሎሪስ የሚባለው ይህ ነው ደግ ፣ ደግ ፣ የቀኖበረ ጠባዩ ደረቅና ችኮ የሆነው ዓመሉ ሌላ አቀባበል አያስጠውምና ንቪ እቴዋ! ከዚህና ከዚያኛው ጋር ወደ መስኩ ሽኻው»

እሷም መምህር ሆይ ፣ ጉሽ አበጁ እንዴት ልቤን አራሱኝ ብላ ተቀበለችና ደስ እንዳላት ትእዛዛቸውን ፈጸመች ።

«ይህ ፈረሰኛው ፕላቲር» የሚባለው ነው» አለ ጠጉር ቆራጩ ።

«የዱሮ መጽሐፍ ነው» በማለት ንግግራቸውን ቀጠሉ ቄሱ ፣ ዳሩ ግን ምሕረት የሚያሰጠው አንዳች በጉ ነገር አሳገኘሁበትም ስለዚህ እሱም ያለክርክር ይሂድና ከሌሎች ጋር ጓደኝነት ይግ ጠም» ብለው ስለወሰኑ ፍርዱን ለመቀበል ሔደ ። ደግሞ ሌላ መጽሐፍ ተገልጦ በታየ ጊዜ » የመስቀሉ ፈረሰኛ የሚለ ውን እርዕስት ይዞ አገኙት ።

ይህን የመሰለ የተቀደሰ ስም በመያዙ ምክንያት በጅላጅል ነቱ ሊፈረድበት ከሚገባው ቅጣት ሊድን በተገባው ነበር ፣ ዳሩ ግን «ከጀርባው ክፋትን ያዘለ ሁሉ አለ» የተባለውን ተረት መዘንጋት ስለማይገባ እሱም ወደ አሳቱ እንዲላክ ተደረገ ።

ጠጉር ቆራጩ ሌላ መጽሐፍ አነሳና« ይህ የፈረሰኛነት ሙስ ተዋት» የሚባለው ነው አሳቸው ።

ይህን ጌታ ! ዱርም እውቀዋለሁ «አሉ ቄሱ» ከዚህ መጽ ሐፍ ላይ የምንቱአልባኖው ሪናልዶ የሚባለው ከካኮ ይበልጥ መንታፊ ሌቦች ከሆኑ ወዳጆቹና ጓደኞቹ ጋር ፣ እንዲሁም አስራ ሁለቱ መማክርትና እውነተኛው ታሪክ ጸሐፊ ቱርፒኖ ጭምር ይገኙበታል ። በኔ አስተያየት ግን ከዘለዓለም ግዞት የበለጠ ሌላ ቅጣት ልፈርድባቸው አልታየኝም ። ምክንያቱም ስመ ጥሩው ግቱ ፖስ ቦያርዶ ለፈለሰፈው ኪነ ጥበብ ዕርዳታቸውን በከፊል የሰጡ ናቸው ። እንዲሁም ክርስቲያኑ ባለቅኔ ሌዶቪክ አርዮስቶ የሚ ባለው የቅኔውን ቀመር የቀዳው ከዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ነው ። ይህም ቢሆን የራሱ ባለሆነ በባዕድ ቋንቋ ሲናገር ያገኘውት እን ደሆነ አንዳችም ክብር አልሰጠውም ። ዳሩ ግን የራሱን ቋንቋ የሚናገር ሆኖ ካገኘውት ቆቤን አውልቄ መሳለም ይገባኛል» አሉት ።

«እኔ የማነበው ጽሑፍ በኢጣሊያንኛ ቋንቋ የተጻፈ ስለሆነ ፍችው ምን እንደሆነ አልገባኝም» አለ ጠጉር ቆራጩ ።

«ባይገባህ ይሻላል» ሲሉ መለሱለት ቄሱ» ጌታው ዶን ኪሮቲም እክሲሜኔስ ይህን መጽሐፍ ወደ አስፓንኛ አምጥቶ ካስ ቲሊያዊ ባያደርገው ኖሮ በጣም እናመሰግነው ነበር ። ምክንያቱም ይግባለባበጥ ብዛት ቀድሞ የነበረውን ለዛና ጣዕም በጣም ስለቀነሰ ቤት ነው። በግጥም የተጻፉትን ያንድ አገር ድርሰቶች ወደ ቋንቋቸው ልመተርጎም የሚሞክሩት ሰዎች ሁሉ የሚያተርፉት ይህንኑ ዓይ ነት ጉድለት ነው ። በብዙ ጥንቃቄና በብዙ መጠበብ ቢደክሙ ቱትም እነዚህን ድርሰቶች ጥንት ከመሠረታቸው ወደነበራቸው ፍጹምነት ምን ጊዜም ሊያደርሳቸው አይችልም ። ስለዚህ በጠ ቅላላ አነጋገር የኔ አስተያየት ይህን መጽሐፍና ሌሎችንም በነ ዚህ በፈረንሳይ ትችቶች አካባቢ የሚገኙትን ሁሉ ወደፊት ምን ልናደርጋቸው እንደሚገባን በጥልቅ ምርምር አጥንተን አስፈላ ጊውን ውሳኔ አስከንሰጣቸው ድረስ ለጊዜው ባንድ ማዕዘን ጥገ ተከማችተው እንዲቀመጡ ማድረግ ነው ። ይሽውም «የካርፐዮ ፊርናርድ» የሚለው መጽሐፍና (ከዚሁ መከከል ሳይገኝ አይቀ

ርም) ሌላው ደግሞ«ርንቺሰቫሌ» የሚባለውን አርዕስት የያዘው ጭምር በእጁ የገቡ እንደሆነ ወዲያውኑ በቀጥታ ወደ ባልቴቷ እጅ ተጋብተው ከዚያም ያለ ይቅርታ ወደ እሳቱ መሔድ አለ ባቸው» አሉት ።

ጠጉር ቆራጩም በዚህ በቂሱ አስተያየት ሙሉ በሙሉ ተስማምቶ ፍርዱ አድልዎ ሰሌለበት ትክክለኛ መሆኑን አረጋ ግጦ ተቀበለ ። ምክንያቱም ቄሱ እጅግ ደግና ንጹህ የሆነ ዓለማ ያላቸውና እውነትንም አጥብቀው የሚወዱ ፣ የዓለምን ወርቅ በሞላ ሰብስበው ቢያስታቅፋቸው እንኳ እውነትን ከመናገር በስተቀር ሃሰት ከአንደበታቸው የማይወጣ ፣ በጎንዘብ የማይደለሉ መሆናቸውን አጣርቶ ስለሚያውቅ ነው ።

ቀጥሎም እንደኛውን መጽሐፍ ገለጠና ሲያነብ «የወይራው ፒልግሪና» የሚባለውን አርእስት አየ ። ከሱም ጋር አብሮ ያነሳው የሁለተኛው መጽሐፍ አርዕስት«የእንግሊዙ ፖልግሪና» የሚ ባል ነበር ። ቄሱ ተቀብለው ከተመለከቱት በኋላ እንዲህ አሉ ።

«ይህ ባለወይራው አመዱ እንኳ ተርፎ እንዳይቀር በቶሎ ይገነጣጠልና ይቃጠል ። ይህኛው የእንግሊዙ ባለዘንባባ ደግሞ እንደብርቅ ነገር ተቅዋሮ በጥንቃቄ እየተጠበቀ በክብር ቦታ ይቀመጥ ። እንዲያውም ትልቁ እስክንድር በዳሪዮስ ዕቃ ቤት ውስጥ ያገኘው የምርኮ ንዋይና ዋንጫዊ መዝገብ የተቀመጠበ ትንና በኋላም የአሚርን ድርሰት የኖረበትን የሚመስል ሣጥን ይሠራለት ። ወዳጄ ጠጉር ቆራጭ ሆይ ፣ ይህ መጽሐፍ ለሁለት ምክንያት ክብርና ማዕረግ አለው ። የመጀመሪያው እራሱ መጽ ሐፉ በውስጡ እጅግ ክፍ ያለ በጉነት የሚገኝበት ነው ። ሁለ ተኛው ደግሞ ብልሁ የፖርቱጋል ንጉሥ የጻፈው በመሆኑ ስመ ጥሩነትን የገበየ ነው ። በመጽሐፉ የተጠናቀቁት ድርጊቶች በሚ ራንርዳ ግንብ ውስጥ የተፈጸሙት ሁኔታዎች ሁሉ ይገኙበታል ። እነሱም በጣም ጥሩዎችና ታላቅ የፍልስፍና አስተያየት የተመ ላባቸው ናቸው ። የድርጊቶቹም እውነተኛነት ብሩህችና ሞገሳዊ ዎች ናቸው ። ስለነሱ ውዳሴ የሚናገረውን ማናቸውንም ሰው በልበ ሙሉነት እንዲናገር የሚያኩራና የሚያስመካ ስሜት ያሳድ ርብታል ። ስለዚህ የኔታ ኒኮላ ያንተ አስተያየት ሌላ ካልሆነ በስ

ተቀር የኔ አስተያየት ይህን መጽሐፍና እንዲሁም «የጋውላው እግዲስ» የሚለውን አስቀርተን የተረፉትን ሁሉ ሌላ ጋጪእት ሳናበዛባቸው ወደ እሳቱ እንዲጨመሩ ማድረግ ብቻ ነው ።

«አይሆንም መምህር ሆይ» አለ ጠጉር ቆራጭ ፣ ይህኛው ስመ ጥሩው ዶን ቤሊያኒጂ» የሚባለው ስለሆነ ብናተርፈው እመ ጻለሁ ።

«የዚህ መጽሐፍ» አሉ ቄሱ» ሁልተኛውና ሶስተኛው አራ ተኛው ክፍል እትም ጥቂት ግራዎ ጠጥቶ የበዛው መራራ ሐሞት እንዲቀነስ በተቅማጥ እንዲወጣለት ማድረግ ያስፈልገዋል ። ከዚ ያም በኋላ «የፋግንግንብ» ድርጊቶች የሚጠቅሰውን ክፍልና ሌላ ውንም አልፎ አልፎ ያለውን አንጃ ግራንጃ ሁሉ እየመረጥን ካመ ጣን በኋላ በግዙት ማስቀመጥና የሚሻሻልበት ብልሃት እንዳለ በግሻሻል አለበለዚያም ምሕረት ወይም ቅጣት እንወስንባቸው እንደሆነ ጊዜ ሰናገኝ ሁኔታቸው ያመረመራል። እስከዚያው ድረስ ግን የኔታ ኒኮላ እንተው ውሰደውና እቤትህ አስቀምጣቸው ። ዳሩ ግን አያራሀን ለማንም ቢሆን እንዳታስነብበው» አሉት።

«ደግ ነው» አለ ጠጉር ቆራጩ፡

ከዚህ በኋላ ቄሱ አርእስት በማንበብ ደክሞ ሳይጨምሩ አሮጊቷን ጠሩዋትና ትልልቆቹን መጻሕፍት እያመጣች አመ ስኩ ላይ እንድትከምራቸው አዘዙዋት ። አሮጊቷም ቀድሞውኑ መጻሕፍቱን የማቃጠል ታላቅ ፍላጐት ያደረባት ስለሆነች ይህ ትዕዛዝ ላንዲት ደንቆሮ የተሰጠ አልነበረምና እሷም ፈዝዛ አል ቀመችም ነበር ። ስለዚህ ሰባትና ስምንቱን ያህል መጻሕፍታት ወዘ ንዲ ታቀፈችና በመስኩቱ በኩል እየወረወረች ትጥለው ጀመር። እንደገና ተመልሳ በርከት አድርጋ ሰብስባ ስታነሳ አንዱ አመለ ጭትና ከጠጉር ቆራጭ እግር ስር ወደቀ ። እሱም አንስቶ ቢመለ ከተው አርዕስቱ «የስመ ጥሩው ፈረሰኛ ቲራንቴ ነጩ » የሚለ ውን አየ ።

«አምላኬ ድረስልኝ» ሲሉ ጮኹ ቄሱ» ቲራንቴ ነጩም እዘፀት ወዲህ በለው ጠጉር ቆራጭ ሆይ ፣ ወዲህ ስጠኝ እሳክሥ

በውነቱ የደስታ ንዋይና የሚያፈነጥዝ ማዕድን እንዳገኘሁ ያህል አቆጥረዋለሁ። በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ጀግናው ፈረሰኛ የሞንቴ አልባኖው ዶን ኪሬይላይሰንና ወንድሙ የሞንቴ አልባኖ ቶማስ፥ ፈረሰኛው ፎንሴካ ፥ ጕበዙ ቲራንቴ ከአላኖ ጋር ያደረገው የሥይፍ ውጊያ ፥ «የሕይወቴ ሠናይ» የምትባለዋ ሴት ቀልደኛነትና የጋለሞታይቱ ሪፖዛታ ፍቅርና ብልጠት ፤ ኢፖሊቶ የሚባለውን ጋሻ ጃግሬዋን ያፈቀረችው ንግሥት ታሪክ ፥ በሠፊው ተዘርዝሮ ይገኝበታል ።

የምወድህ ጠጉር ቆራጭ ሆይ ፥ በውነቱ ይህ መጽሐፍ በዘ ይቤውና በአቀማመሩ በዓለም ላይ ከተጻፉት መጻሕፍት ሁሉ የበለጠ ነው ሊባል ይገባዋል ። እዚህ ላይ የሚገኙት ፈረሰኞች ሁሉ አልጋቸው ላይ እንዳሉ እንደተኙ የሞቱ ናቸው ። እንዲሁም ይህን በመሰለው መጽሐፍ ውስጥ ተጽፎ የማይገኘውን አያሌ በጐ ነገር ያደረጉና ከመሞታቸው በፊት ደንበኛውን ሥርዓተ ኑዛዜ የፈጸሙ ናቸው ። ይህም ሆኖ የመጽሐፉ ደራሲ የማያሰፈልጉትን ብዙ የተዘበራረቁ ሐተታዎች በመጨመሩ የተረፈውን ሕይወቱን በወህኒ ቤት እንዲጨርሰው ሊያሥሩት የሚበቃ ነበር። በል እስቲ እቤትህ ወስደህ እንብበውና አሁን የነገርኩህ ሁሉ እውነት መሆን አለመሆኑን እዚያው ላይ ታገኘዋለህ» አሉት ።

«ድንቅ ነው» አለ ጠጉር ቆራጩ» እነዚህን ያስቀረናቸውን ትንንሽ መጻሕፍት ደግሞ ምን እናድርጋቸው ? »

«እነዚህ» አሉ ቄሱ» የሚጥም ድርሰታት ናቸው እንጂ የፈረሰኛን ታሪክ የሚናገሩ አይደሉም «ካሉ በኋላ አንደኛውን ገልጠው ሲመለከቱት ደራሲው ጊዮርጊስ ሞንትማዮር የጻፈውን» ዲያና» የሚለውን እርዕስት አዩና ሁሉም ይህንኑ ዓይነት መሆ ናቸውን በመገመት እንዲህ አሉ ።

እነዚህ መጻሕፍት እንደሌሎቹ መቃጠል የሚገባቸው አይ ደሉም ፥ ምክንያቱም የፈረሰኝነት ጠቀሰ የሆኑት መጻሕፍት ያስከተሉትን ዓይነት ጉዳት ያላመጡና የማያመጡ ስለሆኑ ነው። እነዚህ ሰውን የሚጐዳና ቁም ነገር ያለባቸው መጻሕፍት በመሆናቸው ምክንያት አጥፊውን ከንጹህ ሳንሰይ ሁሉንም ኩልኩሎች ብናቃጥላቸው የሕሊና ፍርድ አይደለም» አሉት ።

«አየ መምህሩ» አለች ልጅቷ ፤ ይልቁንስ እንደሌሎቹ ቢያቃ ጥሉዋቸው የተሻለ ነው። ምክንያቱም የተከበሩት አጐቴ ከፈረሰኝ ነት ዕብደታቸው የዳኑ እንደሆነ እነዚህን የተረፉትን የቅኔ ድር ሰቶች ማንበባቸው የማይቀር ነገር ስለሆነ ምናልባት ነሺጥ ያደ ርጋቸውና ሁሉንም እርግፍ አደርገው ትተው ወደ መንጋ እረኛ ነት ገብተው ጫካ ለጫካ ሜዳ ለሜዳ እየተዘዋወሩ ዋሽንት እየ ነፉና እየዘፈኑ የሰው መሳቂያና መሳለቂያ ሆነው ይቀራሉ ። ወይም ደግሞ ግጥም በመልመዳቸው የተነሳ ላሊበላ ስለሚሆኑ ሰዎች እንደሚሉት ላሊበላነት የማይዳንና የሚጋባ በሽታ በመ ሆኑ የባሰ ጉዳት ላይ ወደቁ ማለት ነው ።

« ይህች ልጅ የተናገረችው እውነቷን ነው» አሉ ቄሱ» ይህንንም የሚያስናክል እንቅፋት ከወዳጃችን እግር ስር ብናስ ወግደው የሚከፋ ሃሳብ አይደለም ። ስለዚህ መቃጠሉ ሞንቴማ የር ከጻፈው ከዲያና ይጀመር ። ዳሩ ግን የኔ ሃሳብ በሞላ ይቃ ጠል ለማለት ሳይሆን የባለውቃቢይቱን «ፊሊቺታ» ድርጊትና «የደግምት ውሀ» የሚለውን እንዲሁም ረጅም የሆኑት ግጥሞቹ ሁሉ ከመካከሉ እየተቀደዱ ወጥተው ይቃጠሉ ። በስምና ወርቅ አግባብ የተገጠሙት ግን ለመጽሐፉ ክብርና ሞገስ የሚሰጡ በመሆናቸው እንዳሉ ይቀመጡ» ብለው ወሰኑ ።

«ይኸኛው ደግሞ» አለ ጠጉር ቆራጩ» አርዕስቱ ዲያና» ሆኖ በውስጡ ዳግማዊው ሳልማቲኖ» የተባለው ክፍል አለበት። እንዲሁም ደግሞ «ጂል ፖሎ» የሚባለው ደራሲ የጻፈው የዚህ ዓይነት አርዕስት ሴላ መጽሐፍ አለ» አላቸው ።

«ይህ» ዳግማዊው ሳልማቲኖ ያልነው ክፍል ድርሰት» ሲሉ መለሱ ቄሱ» የመስክ ፍርድ የተፈረደባቸው ጥፋተኞችን ቁጥር እንዲያበዛ እዚያው ሔዶ ዓይኻነት ይግጠም ፥ ያኛው ጂል ፖሎ የጻፈው ግን እራሷ አፖሎ እንደሆነ ያህል ተቆጥሮ ይቀመጥ ። በል ቶሎ ቀጥልና ሴላ ምዘዝ ሳይመሽብን እንጨርስ» አሉ ።

«ይህ ደግሞ» አለ ጠጉር ቆራጩ ሁለተኛውን ገለጠና «አሠርቱ የፍቅር ዕድል መጻሕፍት» የሚባለው የሳርዶው ባለ ቅኔ አንቶኒዮ ዲሎፍራሶ ያዘጋጀው ነው» አላቸው ።

«በተቀበልኩት ቅዱስ ክህነት ይሁንብኝ» ሲሉ ቄሱ ተደ ነቁ ። «የቅኔው አምላክ አፖሎ ፣ አፖሎ ከሆነ ጀምሮ ፣ ዜማ ከተ ፈጠረ ጀምሮ ፣ ባለቅኔ መቀኘት ከጀመረ ጀምሮ ፣ ይሆን የመሰለ የመንፈሳዊና የመደነቂያ ስሜት የያዘ መጽሐፍ ምንጊዜም ተከ ውኖ አያውቅም ። ከብጤዎቹ የበለጠና እስከ ዛሬ በይፋ ከወጡት ከዚህ ዓይነት መጻሕፍት ውስጥ ሞክሼ የሌለው ነው ። ይሆን መጽሐፍ ያላነበበ ሰው ጣዕምና ለዛ ያለው መጽሐፍ ምንጊዜም አላነበብኩም ለማለት ይችላል ። ወዳጄ ሆይ ወዲህ ስጠኝ ይህን መጽሐፍ ማግኘቴን የፊሬንሲን ጥንግ ድርብ መጐናጸፊያ እንዳ ገኘሁ ያህል እቆጥረዋለሁ ካሉ በኋላ ይሆን መጽሐፍ ተቀብለው በታላቅ ደስታ እያንቆራጠጡ ለብቻው ለይተው አስቀመጡት ። ጠጉር ቆራጩም እንዲህ ሲል ቀጠለ ።

«የነዚህኛዎቹ ደግሞ» የኢቤሪያው እረኛ» የሔናሪስ ሐመ ልግል» የቅናት ማሞኘያ» የሚባሉት ናቸው ።

«እነዚህን» አሉ ቄሱ» ለባልቲቷ አይምሬ ከንድ ከማሳቀፍ በስተቀር ከዚህ የተሻለ የምናደርግላቸው ነገር የለም ፣ ምክንያ ቱ ምንድርነው ብለህ አትጠይቀኝ ፣ አለበለዚያ ምንጊዜም ፈት ሽን ለመጨረስ አንችልም ።

«እነሆ ይኸው» የፊሊዬው እረኛ» አለ ጠጉር ቆራጩ ።

«የለም እረኛስ አይደለም» አሉ ቄሱ» ማህበራዊና ግብረ ገብ ፣ በዕውቀት የተካላ ሰው ነው ፣ ስለዚህ ለተግባሩ እንደሚ ገባው እንደብርቱ ጌጥ ደህና ሥፍራ አኑረው አሉት ።

«ይህኛው ትልቁ ጥራዝ ደግሞ» ሲል ጠጉር ቆራጩ ቀጠለ «የልዩ ልዩ ቅኔዎች ወርቅ የሚለው አርዕስት ነው?»

«አነስተኛ ቢሆን ኖሮ ጥሩ ነበር» አሉ ቄሱ» ሆኖም ከብዙ ዎቹ ታላላቅ ዘይቤዎች መካከል ጣልቃ የገቡትን አንዳንድ ልማ ዳዊ ግሶች ከውሰጡ ጠራርጐ ማውጣት ወይም እንዳለ ማቃጠል ከሁለት አንዱን ማማረጥ አለብን ። ዳሩ ግን ደራሲው ወዳጄ ስለሆነና ሌላም ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸው ጥሩ ጥሩ መጻሕፍት የጻፈ ስለሆነ ምህረት አድርገን ብናስቀምጠው አልጠላም» አሉ ቄሱ።

“ይህኛው” ሲል ቀጠለ ጠጉር ቆራጩ “የሎፒዝ ግልዶ ናዶ አስተዋጽኦ ግጥም” ይላል ።

“የዚህም መጽሐፍ ደራሲ” ሲሉ መለሱ ቄሱ “ታላቅ ወዳጄ ነው ። እሱ የጻፋቸው ጥቅሶች ምንም እንኳ ታላቶቹ ረዘም ያሉ ቢሆኑ የስሙት ሁሉ በጣም ይደነቃሉ ። ጥቅሶችንም በቂ ንጥ እያራቀቀ በሚያሰግበት ጊዜ የድምጹ አሰባበርና የንግግሩ ግግር የሚያፈዝ ነው ። ሆኖም ጥሩ ነገር ሁሉ ዘወትር መጠ ያኑ ስለሆነ ለጊዜው ከነዚህ ከምርጦቹ ጋር ተቀላቅሎ ይቀ ሙ” አስቲ ያኛውን እጐኑ ያለውን አሳዩኝ ።

“የሚካኤል ሰርቫንቴስ ጋላቲያ” ነው አሉ ጠጉር ቆራጩ

“ይህ ሰርቫንቴስ ያልከው ከብዙ ዓመታት ጀምሮ በጣም ታላቅ ወዳጄ ነው ፤ እኔ እንደማውቀው ስጦታው ከባለ ቅኔነት ይልቅ ወደ ዕድለቢስነት ያደላል ። የሚጽፈው መጽሐፍ ሁሉ እጅግመሩ ሳይ በጣም ጥሩ ነበር ። ዳሩ ግን እንዳንድ ፍሬ ነገር ልመወጠን ይሞክርና ምንጊዜም አላክቶ ሳይጨርሰው በጅምር ይተወዋል ። የሆነ ሆኖ ይህ ደራሲ ወደፊት አሳትማለሁ ሲል ያስታወቀውን ሁለተኛውን ክፍል ጨርሶ እስኪያወጣ ድረስ መጠባበቅ ያስፈልጋል ። ግን ያውቃል! ምናልባት አርሞና አሻሽሎ ሊያወጣው የቻለ እንደሆነ አውን የነፈግነውን ምህረት በዚያን ጊዜ ሊያገኝ ይችል ይሆናል ። ስለዚህ የሚታተመውን መጠባበቅችን ክልቀረ ለጊዜው እቤትህ መስደህ በሰንዱቅ ውስጥ ዝጋበትና ይቀመጥ ፤ አሉ ቄሱ ።

“እሺ መልካም ፈቃዴ ነው” አለ ጠጉር ቆራጩ” እነሆ ደግሞ አብረው የተጠረዙ ሶስት መጻሕፍት” የኢርሲላው ዶን አልፎንስ የጻፈው “አራውከና” ዮሐንስ ፋኖ የሚባለው የኮር ዶቫ ጐተራ ጠባቂ የጻፈው “ አውስትሪያዳ ” የ ቫንሌንሳው ፊለቅኔ ክሪስቶፎር ቪሉዮዝ የጻፈው “ ሞንሴራቶ” ናቸው ። ”

“እነዚህ ሶስቱ መጻሕፍት” አሉ ቄሱ “ስለ ጀብዱ ተግ ባር በእስፓኒኛ ቋንቋ በግጥም የተጻፉትን ሁሉ የሚበልጡ ናቸው ። እነርሱም የውጭ አገር ስመ ጥሩ ደራሲያን ከጻፍዋቸው

መጻሕፍት ጋር ሲወዳደሩ ይችላሉ ። ስለዚህ የእስፓኒያ ሕዝብ የሚከራባቸው እጅግ ክቡር የሆኑ የቅኔ ሀብቶች ብመሆናቸው በጥንቃቄ ልናስቀምጣቸው ይገባናል ።

በዚህ አኳኋን ሲመረመሩ ቆይተው በመጨረሻው ጠንር ቆራጩ ስለሰለቸው የቀሩትን ገና ያልተመረመሩትን በክፌል በእውር ጭፍን ወደ እሳቱ እንዲጣሉ ቄሱ ትእዛዝ ሰጡ ። ባል ቴድና ልጅቷ እየተረዳዱ ጠራርገው ወደ መስኩ ወሰዱና በተሩፋመው ነበልባል ላይ በገለጡት ጊዜ ሽቅብ የቦለቀው ጢስ ባንድ አፍታ መስኩን ሸፍኖት ጊዜውን ቀንና ሌሊት የተደባለቀ አስመ ሰለው ። መጻሕፍቱ ከመደርደሪያው ላይ ሲጠራረጉ ጠንር ቆራጩ አንዱን አስቀርቶ ነበርና ገልመ ሲመለከተው አርዕስቱ "የእጂሊካ ለቅሶ" የሚለውን አየና ለቄሱ ሰጣቸው ።

ቄሱም የአርዕስቱን ስም በተመለከቱ ጊዜ "ወይኔ ጉድ ሆኜ ነበር ፤ ይህን የመሰለው ውድ መጽሐፍ በስህተት ተቃጥሎ ቢሆን ኖሮ የመጸጸቴ ብዛት ከእንጂሊካ ይልቅ የማለቅሰው እኔ ነበርኩ ። ምክንያቱም ይህን መጽሐፍ የጻፈው ዶራሲ በእስፓኒያ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ስማቸው ከታወቀው ታላላቅ ባለ ቅኔዎች አንዱ ነው ። ከዚህም በስተቀር "አቪዲዮ" የተባለውን የሥነ ፍጥረት ምስጢራት በመተርጎሙ ታላቅ ምስጋናና አድናቆት የተሰጠው ነው ። ሲሉ መጽሐፉን በብብታቸው ይዘው ከክፍሉ ወጡ ።

ምዕራፍ 7

ጕበዙ ፈረሰኛችን የማንቻው ዶን ኪሾት ዳግመኛ ለዙረት ከሰገሩ እንደወጣ ይተረካል ።

ይህ የመጻሕፍቱ መቃጠል ፍርድ በሚፈጸምበት ጊዜ ቄሱና ጠንር ቆራጩ በቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ የመጨረሻውን ምርመራ አድርገው ለመውጣት በመጣደፍ ላይ ሳሉ ዶን ኪሾት ከእንቅልፉ ነቅቶ ኖሮ እንዲህ እያለ ሲጮህ ተሰማ ።

«ኑ ወዲህ ፤ ወዲህ ኑልኝ ፤ ጀግና ፈረሰኞች የተባላችሁት ሁሉ የክንዳችሁን ኃያልነት ማሳየት የሚገባችሁ ቦታው እዚህ ግጥሚያ ላይ ነው። የግቢ እውደልዳይ ፈረሰኞች የበለጠ ጀብዱ ለመሥራት የሚችሉት ጉራ በሚነዛበት በጕማስ ሜዳ ላይ ብቻ ነውና ተጠጉ ወዲህ —፤ እዚህም ላይ ቢሆን፡ መመከት አለባችሁ"።

ይህ የፉከራ ጩኸት እንደተሰማ ወዲያውኑ ሰዎቹ ሁሉ ለእርዳታ እየተሯሯጡ ወደ ዶን ኪሾት መኝታ ቤት ስለገቡ በዚህ ምክንያት የቀሩትም መጻሕፍት ምርመራ ሥራ መቋረጥ ግዴታ ሆኖ «ካሮሊያ» ና «የእስፓኒያው አንበሳ» የሚባሉትም መጻሕፍት ሞምር ሳይታዩና ሳይሰሙ ወደ እቶኑ መጣል የማ ይቀር ዕዳ ሆነባቸው ። እነዚህም መጻሕፍት «የአቢሳውን ዶን ሉዊጂ» የጻፋቸው የንጉሠ ነገሥቱን የጀግንነት ሙያ የሚ ናገሩ ስለሆኑ ያለጥርጥር ከቀሩት መጻሕፍት ጋር ተቀላቅለው የሚገኙ መሆናቸው የታወቀ ነበር ። ምናልባትም ቄሱ አይተዋ ቸው ቢሆን ኖሮ ይህን የመሰለ ብርቱ ቅጣት እንዲፈጸምባቸው አያደርጉም ነበር ።

በመኝታ የተጀበሩት ሁሉ ወደ ዶን ኪሾት መኝታ ቤት በደረሱ ጊዜ በፍጹም ተኝቶ እንዳልነቃ ሁሉ ተነስቶ ቆሞ ጩኸ

ቱንና መዘባረቁን ሳያቋርጥ በግራና በቀኙ በኩል ያለውን ግድግዳ በጉራዴ እየገመሰ ይፎክር ነበር። ሰዎቹም እዘንግተው ከወዳ ኋላው ያዙትና ጉራዴውን ከእጁ አስለቅተው በግድ ታግለው አልጋው ላይ አስተኙት። ጥቂት አርፎ ዕብዶቱ ከበረዶለት በኋላ ፊቱን ወደ ቁሱ መልሶ በሚነጋገርበት ጊዜ እንዲህ አላቸው ።

ብዑዕ ሊቀ ጳጳስ ቱርፒኖ ሆይ ፤ (ቁሱን) እኛ ዙዋሪዎቹ ፈረሰኞች በሰሳቱ የግጥሚያ ውድድሮች ላይ አሸናፊነት አግኝ ተን ሳለ ፤ እነዚያ አስራ ሁለቱ ዓቢይ መግከርቶች ብለን የምንጠራቸው ዳሞች የዚህን ጉግስ አሸናፊነት ለግቢ ፈረሰኞች መልቀቃቸው በውነቱ በእድሳቂነት የሚያስገምታቸው ታላቅ እፍረት ነው ።

«ዝም ይበሉ ወዳጄ ሆይ» ሲሉ መለሱለት ቁሱ «በእም ላከ እርዳታ ዛሬ ያጡትን አሸናፊነት ነገ እንዲያገኙት ዕድልዎ ይሰምርልዎት ይሆናል ። ላውኑ ግን ይበልጥ ማሰብ ያለብዎ ስለ ጤናዎ በጉጉት ብቻ ነው ። ምንም እንኳ በጦርነቱ ላይ በብርቱ የቆሰሉ ባይሆን ፈጽመው የተዳከሙ ሳይሆኑ አይቀሩም» አሉት ።

«መቁሰልስ አልቆሰልክም» አለ ዶን ኪሾት «ዳሩ ግን ሰውነቴ መደቋሱና መባዘቱ እርግጥ ነው ፤ ምክንያቱም ያ ዲቃላው ኦርላንዶ በወይራ ግንጣይ ሊሞት አድርሶ ስለደበደ በኝ ነው ። ይሽንንም ያደረገው የሱን ጀግንነት ለማራከስ የምች ለው እኔ ብቻ መሆኔን በማወቁ ቅናት ስለደረሰበት ነው ። ይህም ቢሆን ቅሱ ከዚህ ከአልጋዬ ላይ በጉ ሆኜ ልነሳ እንጂ ምንም እንኳ በአስማቱ ኃይል ቢመነ ብድሬን በውድ ዋጋ ሳልመልስ ብቀር በእውነት የሞንቱ አልባኖው ሪኖልዶ አይደለሁም ። ለጊዜው ግን እባክችሁን የሚበላ ነገር ስጡኝና ልተኛ ፤ ለማገ ሚያ ከሁሉ ይበልጥ የሚያስግለኝ ምግብ ብቻ ነው ። ከዚያ በኋላ ላለው ጉዳይ ጠላቴን ለመበቀል እኔው ራሴ እቢቃለሁ» አላቸው ።

ካሳግያቹም ይህንኑ የጠየቀውን ምግብ አቅርበውለት በልቶ ከጨታ በኋላ ወዲያውኑ እንቅልፍ ወሰደው ። የንበሩትም ሰዎች ሁሉ በዚህ እብደቱ እያዘኑና እየተገረሙ ወደ ቤታቸው ሔዱ ።

አሮጊቷ ግን ሌሊቱን ሳታርፍ በመስኩ ላይ የተራረፉትንና በቤተ መጻሕፍቱም ውስጥ በየጥጉ ተሸጉጠው የቀሩትን መጽ ሐፍት ሁሉ እንዲሁም ቁሱና ጠንር ቆራጩ መርጠው ለዘ ለዓለም ሊያኖሩዋቸው በማሰብ ያስቀሩዋቸውን ጭምር የመርግ ሪዎቹ ምሀረትና የመጻሕፍቱም ዕጣ ሊያስጥላቸው ሳይችል ተቃጥለው እስኪያልቁ ድረስ እየቆሰቆሰች አነደደቻቸው ። ስለዚህ የነዚህ ምርጥ መጻሕፍት ከሌሎች ጋር አንድነት መታ ጠል ። ለእንዱ የመጣ ለሌላው ይተርፋል ።» የሚባለው ተረት እንደደረሰባቸው ያስረዳል ።

በማግሥቱ ከበርቴው በጎ ማደሩን ለመጠየቅ ቁሱና ጠንር ቆራጩ መጥተው ሳለ የተመረጡትም መጻሕፍት በሞላ መታ ጠላቸውን በማወቃቸው ክፉኛ ስለአዘኑ አሮጊቷም ተጨምራ እንዳበደች ያህል ቆጠሩዋት ። ሆኖም የሚብሰው ጉዳይ መዳኔ ቸው ጤንነቱን የሚያጎናፅፉትን ዘዴ መፈለግ ስለነበረ ሁለቱ ሰዎች እየተማከሩ ከእብደቱ ለማዳን የሚቻልበትን ብልሐት ያጠኑ ጀመር ። ለማዳኛ እንደሚረዳ የተማመኑበትም መድኃኒት ወደ ቤተ መጻሕፍቱ የሚገባውን በር በሙሉ አሸገብተው ግስ ደፈን ስለሆነ ምናልባት ዕብደቱ የመነጨበት ሥፍራ ለዘውትር ሲያጣው ተስፋ ይቆርጥና እያደር እየረሳው ሲሄድ ሊድን ይች ላል በማለት ፤ ከዚህም በስተቀር ድኖ ተነስቶ ወደ ቤተ መጒ ፍቱ ለመሔድ በሚፈልግበት ጊዜ በሩን ማግኘት አቅቶት ቢጠ ይቅ አንድ አስማተኛ ድንገት መጥቶ ክፍሉን ከነመጻሕፍቱ በምትሐት ጠራርጦ ይዞት ሄደ ተብሎ ይነገረዋል በሚል ግታ ለያ ሃሳብ ከተስማሙ በኋላ ወዲያውኑ ግንበኛ ጠርተው በሩን የመድፈኑን ሥራ እጅ በእጅ ኑጣድፈው ጨረሱት ።

ይህ በሆነ በሁለተኛው ቀን ዶን ኪሾት ለመጀመሪያ ጊዜ ክሕመሙ በጉ ሆኖ ከአልጋው ላይ ለመነሳት ከቻለ በኋላ እግ ሩን ለማፍታታት ቤት ለቤት መንከላወስ ጀመረ ። ምን ጊዜም በልቡ ውስጥ የተቀረፁት እነዚያ የፈረሰኛነት መጻሕፍት በመሆናቸው መጀመሪያ ትዝ ያለው ጉብኝት ወደመጻሕፍት ቤቱ መግባትና መጻሕፍቶቹን ማንበብ ነበርና ይህንኑ ለማድረግ ክፍሉ ወደሚገኝበት ሄደ ፤ ዳሩ ግን ለዙሪት ከቤቱ ሲወጣ ክፍ

ሉን ከተወበት ሥፍራ ስላጣው በቤቱ ውስጥ ወዲያና ወዲህ እየተመላለሰ በሚፈልግበት ጊዜ ለወትሮው በሩን በሚያንኳኳበት ነዋብ ላይ ደረሰና የመደናገሩ ብዛት እንዳች ቃል ሳይናገር እንደእውር ግድግዳውን በእጁ ይዳብስ ጀመር ። በዚህ አኳኋን ሽቅብና ቁልቁል ሲንዠባረር ከቆየ በኋላ በመጨረሻው የሚና ገረው ቅጡ ስለጠፋው ባልቴቷን ጠርቶ መጻሕፍቱ ያሉበት ክፍል በሩ በወዴት በኩል እንደሆነ እንድትለሳየው ጠየቃት ። ባልቴቷም ልትሰጠው የሚገባውን መልስ በደንብ አስጠንተዋት ነበርና እንደዚህ ብላ አስረዳችው ።

"ክቡርነትዎ የምን ክፍልና የምን መጻሕፍት ነው የሚፈ ልጉት እዚህ ቤት ውስጥ እንደሆነ ክፍልም ሆነ መጻሕፍት በፍጹም የለም ። ምክንያቱም ትላንትና ሌሊት ዲያብሎስ እራሱ በገሐድ እዚህ መጥቶ ማናቸውንም ነገር ጠራርጎ ይዞት ሄዷል" አለችው ።

ልጅቷም በባልቴቷ አነጋገር የልቧ ስለደረሰ ቀበል አደረገ ችና «ክፍሎቹንና መጻሕፍቱን የወሰደው ዲያብሎስ አልነበ ረም ፤ ዳሩ ግን እርስዎ በሄዱ በማግሥቱ ሌሊቱን አንድ ሥልታዊ ተዋጊ በፈረስ ላይ ተቀምጦ በደመና ላይ እየጋለበ መጣና እዚህ ሲደርስ ወርዶ ክፍሉን በምትሐት ሰንጥቆ ገባ ። እዚያም ውስጥ ገብቶ ምን ዓይነት ድግምት እንዳደረገ አላወቅሁም ። ጥቂት እንደ ቆየ ቤቱን በሙሉ ጭስ አድርጐት በአልጋው በኩል አቋርጦ ከመቅጽበት እየበረረ ወደ አየር ጠለቀ ። ያደረገውንም ነገር ለማየት ቸኩለን ብንሄድ ክፍሉንም ሆነ መጻሕፍቱን ካሉበት ሥፍራ አጣናቸው ። እኔና አቃቢቷ ይህና አድርገን የምናስታውሰው ያ የጃጀ አስተማኛ ልክ በርሮ በወጣበት ሰዓት ድምጹን ከፍ አድርጎ እየጮኸ ከዚህ ክፍልና ከነዚህ መጻሕፍት ባለቤት ጋር ሥውር ጠላትነት ስላለው ቆይቶ የሚገልጥና እያደር የሚ ያንገበግበ ከባድ ጉዳት አድርጐ መሄዱንና ስሙም ጥበበኛው "ሙኛቶኔ" የሚባል መሆኑን ተናገረ ።

አይደለም ተሳስተሻል "ፍሬስቶኒ" ብሎሽ ይሆናል" ሲል ዶን ኪሾት አጣራ ።

«እንጂ እንግዲህ" ስትል መለሰች አቃቢቷ «ሰሙን ፍሬ ስቶኒ ይበል ወይም "ትሬስኪ" የትኛው እንደሆነ ልብ አላደረ ግነውም ፤ ይሁን እንጂ የስሙ መጨረሻ ፊደል በ«ቶኒ» የሚያ ልቅ መሆኑን በውል አስታውሳለሁ" አለችው ።

"ነው ፤ ነው ፤ እሱው ነው" አለ ዶን ኪሾት « ታላቁ ጠላቴ ፍሬስቶኒ መሆኑን ገና አሁን አወቅሁት ። እስከዚህም ድረስ የተጣመድንበትም ምክንያት በጊዜ ብዛት አንድ ቀን የሱ አማኝና ገባሩ ከሆነው ፈረሰኛ ጋር አንድ ላንድ ግጥሚያ አድርገን አስማተኛው በማናቸውም መተቱ ሊያስጥለው ሳይችል በቀጥታ የማሸንፈው መሆኔን በጥንቆላውና በአስማት ጥበቡ ታይቶት በማወቁ ነው ። ስለዚህ ይህ ውርደትና አፍረት እንደ ሚደርስብኝ በማወቁ ዘወትር እየተከታተለ ይህን የመሰለ የሚያበሽቅ ተንኮል እየሠራ ይፈታተነኛል ። ይህም ቢሆን ቅሉ የዓለም አስማተኞች ተሰብስበው ቢዶልቱ አንዱ ከአምላክ የታዘዘውንና የተቆረጠውን ነሲብ ከማቡ ለማዛባት ወይም ለማስ ቀረት የማይችሉ መሆናቸውን እኔ ላረጋግጥላቸው እችላለሁ» አላቸው ።

ልጅቷም እንዲህ ስትል መለሰች ፤ «ይህ እንደሚሆን ማን ይጠ ራጠራል ፤ የአምላክ ኃይልና ፈቃድ ከሁሉ የሚበልጥ አይደለም? ከቡር አጐቴ ልጅ ነች ብለው ሳይንቁ ምክሬን ይሰሙኝ እንደሆነ አርፈው ይቀመጡ ። ይህን ከመሳሰለው ጭቅጭቅና እልክ ውስጥ እንዲገቡ ከቶ የሚያስገድድዎት ማነው? በገዛ እጅዎ ጠላት ከሚያ ፈሩ ይልቅ በሰላም እቤትዎ ቢቀመጡ አይሻልዎትምን? ከስንዴ የበ ለጠ የዳቦ እህል ለመፈለግ ወይም ደግሞ የወርቅ እንቁላል የም ትጥል ዶሮ አገኛለሁ በማለት አገር ለአገር መንከራተትዎን ትተው እዚሁ እርስዎ ላይ ሆነው ተፈጥሮ ባርኩ የሰጥዎትን ሃብት እየበሉ ከኛ ጋር ቢያሰቱ የበለጠ እድል አይሆንምን? ይህንንም የምልዎት ብዙዎቹ ሰዎች የሌሎችን እራስ ለመላጨት ፎክረው ሄደው እነ ሱው እራሳቸውን ተላጭተው የሚመለሱ መሆናቸውን ሳላነሳው ነው» አለች ።

«አዬ ጉድ! የኔ ልጅ ፤ በዚህ አነጋገርሽ ምንኛ ተሳስተሻል አለ ዶን ኪሾት» እንኳንስ እኔን ደፍረው እራሴን ሊላጩኝ

ይቅርና የጠራን አንዲቷን ዘለላ ለመንካት ያሰቡትን ሁሉ አስቀድሚ ሪዛቸውንና እራሳቸውን ለመላጪት የምችል መሆኔን አለማወቅሽ ነው እንጂ ብታውቀው ኖሮ ምላስሽን በነከስሺው ነበር ።

ልጅታም ሆነች አሮጊቷ ዶን ኪሾት ይህን መልስ በሚሰጥበት ጊዜ ፊቱ ባንዴ መለወጡን ስላዩ እብዶቱ እንዳያገረሽበት ፈርተው ዝም ከማለት በስተቀር ምንም መልስ አልመለሱ ለትም ። ከዚያ ወዲህ ለአስራ አምስት ቀን እድሚ ከቤቱ ሳይ ወጣ የቀድሞውንም ወፈፍታ የሚጀምር ለመሆኑ አንዳች ምል ክት ሳያሳይ በሰላምና በፀጥታ አርፎ ሰነበተ ። በዚህም በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ አንዳንዴ ብቅ እያሉ የሚጐበኙት ወዳጆቹ ከቁሱና ከጸጉር ቆራጩ ጋር ረጅም ወግ አንስተው ይጫወቱ ነበር ፤ በጨዋታው መካከል በዓለም ላይ ፍጹም ሰላም ለመመ ስረት ቢፈልግ ከማናቸውም ጉዳይ ይበልጥ የዙዋሪ ፈረሰኞች መኖር በማም ማስፈለጉንና የዙዋሪ ፈረሰኞችንም ሕግ እንደገና ታድሶ እንዲቋቋም ማድረግ እጅግ የሚያሳስብ ጉዳይ መሆኑን እያ ስረዳ ጠቃሚነቱን ያስገነዝባቸው ነበር ። ቄሱም ይህን የሚያቀር ብላቸውን ከንቱ ክርክር ለመቀበልም ሆነ ላለመቀበል የተከተሉት ዘዴ አንዳንድ ጊዜ እያቃለሱ በማስተባበል ፤ አንዳንድ ጊዜም ደግሞ ያመኑት መስለው እውነተኛነቱን በመደገፍ ማዳመጥ ነበር ፤ እንዲህም ያደረጉበት ምክንያት ይህን በመሰለ የመልስ አሰጣጥ ዘዴ ካልሆነ በስተቀር በድርቅና መንገድ የናቁበት እንደሆነ በንግግራቸው ምን ጊዜም ተጣጥመው ለመግባባት እንደ ማይችሉና ከነአካቴውም እንደሚቀያየሙ ስለእወቁት ነው ። በዚህ አኳኋን ሲሟገቱና ሲነታረኩ ውለው ሲሰላቹ ወደየቤታ ቸው ይሄዱ ነበር ።

ከዚያ ወዲህ በተደረገለት መልካም አቀባበል እያደር ሰው ነቱ እየተጠናከረ ሰለሄደና ቀስ በቀስም ልቡ ለዙሪት ስለተነሳሳ መጀመሪያ ወጥቶ በነበረበት ጊዜ ከሆቴለኛው የተመከረውን የጋሻ ጃግሬ ማስከተል አስፈላጊነት አስታወሰና ሰሞኑን ለመና ፈስና እግሩን ለመፍታት እያመካኘ ወደ መንደር ብቅ እያለ በጉረቤቱ የሚኖር አንድ ጢሰኛ ባላገር በድብቅ እያሰጠራ

በተሰፋ እያባበለ አብሮት እንዲሔድ ይለብከው ጀመር ። ይህም ባላገር በተላላነቱ በመንደሩ ሰዎች የታወቀ ልበ ጉጉ ቂላቂል ብጤ ስለነበረ (መቼም የድሆች ሁሉ ምኞት ይሞገት ዓይነት ስለሆነ ነው) ከዚህም በስተቀር በዱባው ውስጥ ሙዳ ጨው የሚያንሰው አልሚ በመሆኑ በቀላል ተሰፋ የሚያለል መሐይም ነው እንጂ ነገር አዙሮ የሚመለከት አስተዋይ ሰው አልነበረም ፤ ስለዚህ በብዙ ማባበልና በብዙ ተሰፋ ስለእሺነፈው ያልታደለው ባላገር በጋሻ ጃግሬነት አድሮ አሱን ተከትሎት ለመሄድ ተስማማ ።

ዶን ኪሾት ባላገሩን ለማስከብለል በሚሰብክበት ጊዜ ይህ የሚሔድበት መልካም ዕድል እንዳያመልጠው በውዴታ ፈቃዱ ሊከተለው የሚገባው መሆኑን ለማስረዳት ካደረገው ከፊ ዙው የስብከት ንግግሩ መካከል የባላገሩን ልብ ጠልቆ ለመንካት የበቃው ተሰፋ የዙዋሪ ፈረሰኛነት ተግባሩን ለማከናወን ከእገር ወደ አገር እየተዘዋወረ አደጋን በሚያሳድድበት ጊዜ በዕድሉ እርዳታ በቅጽበት አንዲት ደሴት ሊያገኝ የሚችልበት ውጊያ የሚያጋጥመው መሆኑንና በዚያን ጊዜ ያለአንዳች ምክንያት እሱን አገረ ገዢ አድርጐ በደሴቱ ላይ የሚሾመው መሆኑን ካረጋገጠለት ወዲህ ነው ።

ይህ ሳንቾ ፓንቻ የሚባለው ባላገር (ስሙ ይህ ነበርና) በዚህና በሌላም ይህን በመሳሰለ ከንቱ ተሰፋ ተሸንፎ ምንም ሳያቅማማ ሚስቱንና ልጆቹን ትቶ ለጉረቤቱ ለዶን ኪሾት በጋሻ ጃግሬነት አድሮ አብሮት እየዞረ ለመማሰን በጓጎ ፈቃዱ ቆርጦ ተነሳ ። ዶን ኪሽትም በማም ይፈልገው የነበረውን ጋሻ ጃግሬ ካገኘ በኋላ በተሰይ ደግሞ ለስንቁ የሚሆን ገንዘብ መፈለግ ጀመረ ። ይህንንም ገንዘብ ለማግኘት ደህና ዋጋ የሚያ ወጣ አንዳንድ ዕቃ በመሸጥም ሆነ በመለወጥ ሁሉንም በርካቼ እየወረወረ ጥቂት ጠቀም ያለ ገንዘብ ለማጠራቀም ቻለ ። እን ዲሁም ደግሞ አንድ ወዳጁ ዘንድ አንድ ከብ ጋሻ ተዋሰ ። የተሰበረውንም የራስ ቁር የተቻለውን ያህል ለባብዶ ከጠነ በኋላ ሳንቾን ጠርቶ ለጉዞው በተወሰነው ቀንና ሰዓት ዝግጁ ሆኖ ለመገኘት እንዲችልና ለመንገዳቸውም አስፈላጊ የሚሆ ውን ሥንቅ ለማሰናዳት ጊዜ እንዲያገኝ ፤ የውዴላውንም ቦርሳ

በደንብ ጠቅጥቆ እንዲይዝ በማስጠንቀቅ እሱ ለመነሳት ያሰበ በትን ቀንና ሰዓት ቀደም አድርጐ አስታወቀው። ጋሻ ጃግሬውም ምንም ባላገር ቢሆን የመንገድ ችግር የሚገባው ሰው ስለሆነ የውዬላውን ቦርሳ ጠቅጥቆ ለመያዝ ምን ጊዜም የማይረሳው ጉዳይ መሆኑን ለጌታው አረጋገጠለት። እንዲሁም ደግሞ በእ ግሩ ረጅም መንገድ መሄድ የማይሆንለት ዳተኛ በመሆኑ ምክን ያት እንዲት አመለ ደግና ብርቱ የሆነች አህያ ስላለችው እሷን ጭኖ ለመጓዝ ማሰቡን ገለጠለት። ዶን ኪሾት ግን ይህን የቀረ በለትን የአህያ መጫን ሃሳብ መቀበል ሁኔታው ውርደትን የሚያስከትል መስሎ በመታየቱ ቅሬታ ስላሳደረበት ከሽሙጥ ለመዳን ሲል ከጥንታዊ ዙዋሪ ፈረሰኞች መካከል በአህያ የተቀ መጠ ጋሻ ጃግሬ የሚያስከትሉ ፈረሰኞች መኖር አለመኖራቸውን ለማጣራት ለጥቂት ጊዜ መልስ ሳይሰጠው እንደተከዘ ሲያስላ ስል ቆየ። ሆኖም ትዝ የሚለው አንድም ፈረሰኛ እንኳ ስላጣ ወደፊት ከሚገናኘው ካንድ ጥጋበኛ ፈረሰኛ ጋር ውጊያ ገጥሞ ካሸነፈው በኋላ ፈረሱን ማርኮ አንድ የተከበረ መጋባ ለጋሻ ጃግሬው በመስጠት ሁኔታውን ለማሻሻል የሚችል መሆኑን በማሰብ ለጊዜው አህያይቱን ጭኖ እንዲከተለው ፈቀደለት። ከዚህም በስተቀር የማፈራረቂያ ሸሚዝና እንዲሁም ሆቴለኛው በሰጠው ምክር ላይ የተዘረዘሩትን አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ አዘ ጋጀ። ይህን መሰናዶ ካጠናቀቀ በኋላ ልክ ለመነሻ በተቃጠሩ በት ዕለት ሁሉቱም ዝግጁ ሆነው ሳንቾ ከሚስቱና ከልጆቹ ሳይ ሰናበት ፤ ዶን ኪሾትም ከወንድሙ ልጅና ከአሮጊቷ ሳይሰና በት ሁለቱ ብቻ በጠበቀ ምስጢር ተስማምተው ለማንም ሳይታዩ በመንፈቀ ሌሊት ከመንደራቸው ወጥተው በማስጋሴ ተጓዙ። ማልዶ የተነሳ ፈላጊ እንኳ ተከታትሎ ቢፈልጋቸው ሊያ ያቸውና ሊደርስባቸው እንደማይችል በአፈጣጠናቸው የተማ መኑ እርግጠኞች ነበሩ። ብዙ መንገድ እርቀው ከሄዱ በኋላ የመያዝ ሥጋታቸውን ለማስወገድ ወደ ኋላቸው እየተገላመጡ አይተው ማንም ያልተከተላቸው መሆኑን አረጋግጠው ሲያውቁ ተዝናንተው በዝግታ ይጓዙ ጀመር።

ሳንቾ ፓንቻ ውዬላውን ቀርቅቦ ኮሮጆውን አዝሎ እርኩ ቱን አንግቶ ባሕታዊ ይመስል በአህያው ላይ ተንዘራፍጦ ጌታው

ተስፋ በሰጠው ደሴት ላይ በቶሎ ተሾሞ ለመታየት እንደቋመጠ ይሄድ ነበር። ዶን ኪሾትም ይሔድ የነበረው በመጀመሪያ ጊዜ ካገሩ ሲወጣ የሄደበትን ያንኑ አቅጣጫና ያንኑ መንገድ ይዞ ነው። ይሽውም የምንቲዮልን ሜዳ አቋርጠ የሚወስደው መንገድ መሆኑ ነው። ይሁን እንጂ አካሄዱ እንደመጀመሪያው ጊዜ የተ ጣደፈ አልነበረም ፤ ምክንያቱም የተነሳው በሌሊት ስለሆነ በዚ ያን ሰዓት በደረሰበት ምዕራፍ በሜዳው ላይ የነበረው የማለዳ ፀሐይ ጨረር ግንባር የማይወጋና እጅግም የማያውክ በመሆኑ ነው። በዚህ አካኋን ጭር ባለው መንገድ ጥቂት ከተጓዙ በኋላ ሳንቾ ፓንቻ በመካከሉ ወግ አነሳና እንዲህ ሲል ጌታውን አሳሰበው።

«ክቡር ጌታዬ ዙዋሪው ፈረሰኛ ሆይ ፤ ያቺን ተስፋ የሰጡኝን ደሴት እንዳይረሱብኝ አደራ ብየዎታለሁ ፤ ይህች ደሴት የቱን ያህል ሰፊ ምድር ብትሆንም እንኳ ደህና አድርጌ ልገዛት እንደ ምችል አይጠራጠሩኝ አለው።

«ወዳጄ ሳንቾ» ሲል መለሰለት ፤ ዶን ኪሾት» ጥንታዊ ዙዋሪ ፈረሰኞች ሁሉ ድል አድርገው ባስገበሩት አውራጃ ግዛት ላይ ወይም በቁርጥራጭ ደሴቶች ላይ ጋሻጃግሬዎቻቸውን አገረ ገዢዎች አድርገው መሾም በጣም የተከበረ ልማዳቸው መሆ ኑን ማወቅ ይገባሃል። እኔም እንደዚሁ ወደፊት ስሜን ለማስጠ ራት የተነሳሁ በመሆኔ ምክንያት ይህን የመሰለ እጅግ የተመሰ ገነ ልማድ ተረስቶና ወድቆ እንዳይቀር በብርቱ ለመጠበቅ የቆ ረጥሁ ነኝ ፤ እንዲያውም ከፍ አድርጌ በመጠበቅ ብቻ ሳልመ ሰን ከዱሮው ልማድ በማብለጥ እልፍ ሳደርገው አስቤበታለሁ። ምክንያቱም የጥንቶቹ ዙዋሪ ፈረሰኞች አብዛኛውን ጊዜ ምናል ባትም ከነአካቴው ጋሻጃግሬዎቻቸው እስኪያረጁ ድረስ በደጅ ጥናት አቆይተው ጉልበታቸው ደክሞ ማገልገል ሲሳናቸውና የመከራውን ቀንና የጭንቁን ሌሊት ችለው ማሳለፍ ሲያቅታ ቸው በዚያን ጊዜ ብቻ ለመጦሪያቸው ይሆን ዘንድ የገባር ገዢ ነት ወይም ግሩ ቢል የጉልት ገዢነት ማዕረግ ይሰጧቸዋል። ይሽውም ወጣም ወረደ ባንድ ቀበሌ ወይም ባንድ ወረዳ ግዛት የተወሰነ ነው። እኔንና አንተን ግን እግዚአብሔር በሕይወት ያቆየን እንጂ ከዛሬ አንስቶ እስከ ሰድስት ቀን ድረስ ያለ ጥር

ጥር ሊያጋጥመኝ እንደሚችለው ያንድ መንግሥት ግዛትና በር ከት ያሉ የቅኝ ግዛቶች በተደራቢነት ያሉት አገር ድል ለማድ ረድ እችል ይሆናል ። በዚያን ጊዜም እንተን አማርው አንደኛውን የወደድኸውን ልስጥህ የምችልበት ሥልጣን ይኖረኛል ። ይህም ምናልባት ሊደርስ የማይችል አስቸጋሪ ነገር አይምስልህ ። ምክንያቱም ለዙፋሪ ፈረሰኞች ዕድል የሚያጋጥሙት ነገሮች ሁሉ በፍጹም ያላታሰቡና ታይተው የማይታወቁ ስለሆኑ ከዚህ ተስፋ ከሰጡህ የደሴት ገዢነት ማዕረግ ይበልጥ ሴሳም ከፍ ያለ ሰመታ እንድታገኝ ለማድረግ በቀላሉ የምችል ነኝ'' አለው ።

«እንዲህማ ከሆነልኝ» አለ ሳንቾ ፓንቻ» አውን ከቡርን ትም ከተናገሩዋቸው ተአምራቶች ውስጥ አንደኛው (በእግዚአ ብሔር ፈቃድ ተፈጽመው እኔ ንጉሥ ለመሆን የበቃሁ እንደ ሆነ የኔይቱ ሚስት ጀይኒና ጉቴዶሬዝ ቢያንስ ቢያንስ እቴጌ ትሆናለች ፤ ልጆቼም ያለጥርጥር ልዑላን አልጋ ወራሾች ይሆናሉ ማለት ነዋ!

«ይሀን ማን ይጠራጠረዋል» ሲል መለሰለት ዶን ኪሾት»

«እኔ ግን አንጀ እጠራጠራለሁ አለ ፤ ሳንቾ ፓንቻ» ምክ ንያቱም እኔ እንደማምነው ጊዜው ፈቅዶ ወቅቱ ይሁን ብሎ የንግሥና ዘውድ ከሰማይ ወደ መሬት ቢያዘንም ለጃይኒና ጉቴዶሬዝ ጭንቅላት የሚሆን አንደማይገኝ እርግጠኛ ነኝ ። ወይዘሮነትን ከአገኙት ግን ሳይሰማማት አይቀርም ። ይህንንም ምናልባት ልዩ አጋጣሚ ፈቅዶላት ሁኔታው የተቃና እንደሆነ ብቻ ነው» አለው ።

«ሳንቾ ሆይ » አለ ዶን ኪሾት «ማናቸውንም ነገር ለሚ ዛን አስተካክል ኃይሉ ተውለት ፤ ቢሆንም የቀረው ቢቀር ከአገረ ገዢነት ያነስ ሹመት በማግኘት ተደስተህ ለወደፊት የምትደር ስበትን ምኞት ባጭር አትቅጪው ።

«ይህንንስ ያደርገዋል ብለው አይጠራጠሩ» አለ ሳንቾ» ግናቸውንም ዓይነት በእጁ-የሚሞላውንና ልጪብጠውም የምችለ ውን ሁሉ የሚሠጠኝ ከቡርንትዎን የመለ ቸርና ኃያል ጌታ እያ ለኝ እድሌን ዝት ላለ ነገር አላጪውም ። እንዲያውም ካሁኑ ጀምሮ የሚታየኝ ሁሉ በተንቀባረረ ጌትነት መኖር ብቻ ነው» አለው ።

ምዕራፍ 8

ጀግናው ዶን ኪሾት ከሚያስፈሩት የነፋስ ወፍጮዎች ጋር ያደረገው የተብራራ የጕብዝና ግጥሚያና ሌሎችም የማይረሱ አስደሳች የጀግንነት ሞያዎች ይተረካሉ ፤

በዚህ የሹመት ጉዳይ ላይ እየተነጋገሩ ሲጓዙ በስተፊታ ቸው በተንጣለለ ሜዳ ላይ በተርታ የተተከሉ ሠላሳ ወይም አርባ ያህል የሚሆኑ የነፋስ ወፍጮዎች ቆመው ታዩዋቸው ። ዶን ኪሾት እነዚህን ወፍጮዎች አሻግሮ ከማየቱ ወዲያውኑ ለጋሻ ጃግሬው እንደዚሁ አለው ።

«ወዳጄ ሳንቾ ፤ ዕድላችን እኛ ከተመኘነው ይበልጥ ጉዳ ያችንን ወደ መልካም ፍጻሜ ሲመራው ተመልከት ። ቅድም የተመኘነው ምኞት ገና ከጧቱ ሳለ እነሆ ይኸውልህ እውነት ለመሆን ሲጣደፍ ። ወዳጄ ሳንቾ ደህና አድርገህ ተመልከት ፤ እኒያውልህ ከሚጸው ባሻገር ሠላሳ ወይም ጥቂት በርከት ያሉ ሰማይ ጠቀስ ጀውግዎች ተሰልፈውልሀል ። እኔም ከነሱ ጋር ግጥሚያ አድርጌ ሁሉንም በመደዳ ለመግደል የተዘጋጀሁ ስለ ሆንኩ ከነሱ በምንገፍፈው የምርኮ ዕቃ ካሁኑ አንስተን መክበር እንጀምራለን ። ከዚህም በስተቀር እነዚህን የመሰሉትን መጥፎ የአንክርዳዱ ዘሮች ከንፁሆች መካከል እየለዩ ከዓለም ላይ ማጥ ፋት ደንበኛ የተዋጊነት ተግባርና ለትክክለኛነትም የተቀደሰ አገልግሎት እንደማበርከት የሚቆጠር ነው» አለ ።

«የምን ጀውግዎች ነው የሚሉኝ ፤ የትኞቹ ናቸው ሲል ጠየቀ ሳንቾ ፤

«እንዚያን ከንደ ረጃጅሞች ነዋ» ሲል መለሰለት ዶን ኪሾት» አይታይህም የያንዳንዳቸው ክንድ ወጋግራ ይመስል ተንቀዋሎ ሲያስፈራ»

«ይልቁንስ ደህና አድርገው ይጠንቀቁ» አለ ሳንቾ "እዚያ ማዶ ቆመው የሚታዩት የነፋስ ወፍጮዎች ናቸው እንጂ ጃውሳዎች አይደሉም ። ክንድ የመሰልዎትም ክንፋቸው ስለሆነ እሱን ነፋስ ሲያዞረው ነው ወፍጮው የሚፈጨው» አለው ።

«እኔ ምን እንደሆኑ አውቄአቸዋለሁ» ሲል መለሰለት ዶን ኪሾት» አንተ ግን የግጥሚያ ጉዳይ የማይገባህ ደነዝ ስለሆንክ ልትገነዘበው አትችልም ። ወዳጄ ሆይ ፤ እነዚያ ለአንተ ወፍጮ መስለው የታዩህ ለኔ ደግሞ ጃውሳዎች ሆነው ታይተውኛል ። እኔ ወደነሱ ሄጄ እኩያዎቼ ካልሆኑት ከነዚህ አረመኔዎች ጋር ኃይለኛ ውጊያ ስገጥም ለማየት ፈርተህ እንደሆነ ራቅ ብለህ ቁምና "አቤቱ ሰውረኝ» እያልክ ጸልይ እንጂ እኔን እንደ ሕፃን ልጅ አታታለኝ» አለው ።

ይህን ከተናገረ በኋላ ሳንቾ በስተኋላው እየጮኸ የነፋስ ወፍጮ ነው እንጂ ጃውሳዎች አይደሉም እያለ የሚናገረውን ለማዳመጥ ሳይሞክር ፤ ሮንዚናቴን ኩረኩሪና ሽምጥ እየጋለበ ሄደ ። መቸም ጃውሳዎች መሆናቸውን በፍጹም አምኗልና አጠገባቸው ከደረሰም ወዲህ በጉልህ ስህተቱ ሳይነቃ ጋሻ ጃግሬው ጉሮሮው እስኪደርቅ እየጮኸ መላልሶ በማስረዳት የሚለፈልፈውን ለመስማት ሳይፈልግ እንዲህ እያለ በታላቅ ድምጽ ይዝት ባቸው ጀመር ።

«አትፈርጥጡ እርብድብድና ፈሪ የሆናችሁ ፍጥረቶች ፤ አትሸሹ እናንት ድርቢታሞች ፤ ሊገጥማችሁ የመጣው አንድ ጠልጣላ ፈረሰኛ ብቻውን ነው»

እንዳጋጣሚ ደግሞ ልክ በዚያን ሰዓት ነፋሱ ጥቂት በር ከት ብሎ ስለነፈሰ እነኛ ትልልቅ ክንፎች መዞር ጀመሩ ። ይህንንም ዶን ኪሾት በተመለከተ ጊዜ እንዲህ አለ ፤

"መች እንላቀቅና ፤ ሌላው ቀርቶ ጃውላው በሪያፊዎ ካለው መቶ ክንድ የበለጠ ኖሮአችሁ ብታርገበግቡት እንኳ ዋጋችሁን መቀበላችሁ የማይቀር ነው ፤ ካለ በኋላ ይህን ብርቱ ጦርነት አሸንፎ በሕይወት ለመመለስ እንዲያበቃው የመንፈስ እርዳታዋን እንድትሰጠው የእመቤቴን የዱልቺኒያን ውቃቢ በሙሉ ልብ ተማጠነና በጋሻው ራሱን ሸፈነና ጦሩን ዘትዝቶ ሮንዚናንቴን በሙሉ ፍጥነቱ እያስጋለበ በፊት ለፊቱ ካለው ከመጀመሪያው ወፍጮ ጋር ተገናኝቶ አንደኛውን ክንፉን በጦሩ በሳው ። ዳሩ ግን በዚያን ሰዓት ነፋሱ ከመጀመሪያው የበለጠ ፍጥነት ጨምሮ ክንፉን በኃይል ስላሽረው ጦሩን ከእጁ ላይ ነጥቆ እንከትክት አደረገበት ። እንዲሁም ደግሞ መላፊት ፈረሱንና ፈረሰኛውን ጠለፈና አምዘግዝጎ ከረበታቸው ። ዶን ኪሾት በጣም እንደተጐዳ ወድቆ መሬት ለመሬት ይንከባለል ጀመር ። ሳንቾ ፖንቻም ይህን አደጋ እንዳየ ወዲያውኑ አህያይቱን በሙሉ ፍጥነቷ አስነስቶ እያስጋለበ ጌታውን ለመርዳት ሮጠ ። ደርሶ ጌታው በፍጹም ለመንቀሳቀስ የማይችል ጥምልምል ሆኖ አገኘው ። ምክንያቱም ከሮንዚናንቴ ጋር አንድነት የተቀበለው ብትር ከባድ ስለነበረ ነው ።

"አቤት! አቤት! አይጣል እኮ ነው" ሲል ተገረመ ። ሳንቾ "እረ ለመሆኑ የነፋስ ወፍጮ መሆናቸውን እያስረዳሁ የሚያደርጉትን አይተው ይጠንቀቁ ብዬ አልነገርኩዎትም ? እውነተኛውን ነገር በመካድ ይህን የመሰለ አደገኛ ስህተት በራስዎ ውስጥ አግብተው እስከዚህ ድረስ መቅለል ይገባዎት ኖሮአልን? ወየው ጉድ!" እያለ ያማርር ጀመር ።

"እባክህን ዝም በለኝ ወዳጄ ሳንቾ" ሲል መለሰለት ዶን ኪሾት" "የጦርነት ጉዳዮች ከሌሎቹ ከማናቸውም ዓይነት ጉዳዮች በተለየ አኳኋን ያላቋረጠ መለዋወጥ እንዲያደርስባቸው ዘወትር የተጋለጡ ስለሆኑ ምን ጊዜም እንዳሰብከውና እንደተመኘኸው ሆኖ የሚፈጸምልህ ነገር አታግኝም ። እኔም እራሴ እንደማስበው በጦርነት ጉዳይ ላይ ይህን የመሰለ መለዋወጥ ሊያደርስ እንደሚችል አምናለሁ ። ይህንንም የምለው ያ ፍሬስቶኔ የሚባለው መጻሕፍትንና ክፍሉን የሰረቀብኝ አስማተኛው ጠላቴ በነዚህ ጃውሳዎች ላይ ማግኘት የምችለውን የድል አድራጊነት ክብር ለማሳጣት ሲል ወደ ነፋስ ወፍጮነት የለወጣቸው መሆኑን ስለማውቀው ነው ። ይህ አስማተኛ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በጠላትነት መርዞ ይዞኛል ። ዳሩ ግን በመጨረሻው ላይ የማታ ማታ በዚህ የተንኮል ጥበቡ እየተመካ ከአመኖኛ

መቅጫው ጐራዴዬ ጋር የሚያደርገው ፉክክር የማያዛልቀው መሆኑን ላረጋግጥልህ እችላለሁ ።”

“ጥሪትዎ ሁሉ እንዳሰቡት ይሁንልዎ” ሲል መለሰ ሳንቾ ንግግሩን በመቀጠል “በዚህ አያያዛችን የምንሬመድ ከሆነ የደሴት ገዢነት ሹመት ማግኘቴ ቀርቶ የጥንቱን ጠሰኝነቴንም እንኳ አጥቼው እንደምቀር አምናለሁ” አለው ።

ከዚህ በኋላ ደጋግፎ አነሳውና ሮንዚናንቴ ላይ እንዲወጣ አገዘው ። ፈረሱም በበኩሉ በመውደቁ ምክንያት ጀርባው ተጎሽልጦ እግሩም ተመትቶ ያንከስ ነበር ። ይህም ሆኖ በዚህ አጋጣሚ ላይ የደረሰባቸውን ሁኔታ ለንግግራቸው አርዕስት አድርገው እየተጨዋወቱ “የፑዬርቶ ላፒቼ” ን ኰረኰንች መንገድ ይዘው ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። ይህንም መንገድ የመረጠበት ምክንያት ዶን ኪሾት እንደሚለው ይህ ሥፍራ ሰው የሚያዘወትረው የሕዝብ መተላለፊያ ኬላ ስለሆነ ብዙና ልዩ ልዩ ዓይነት አጋጣሚዎች ሳይገኙበት አይቀርም የሚል እምነት ስለነበረው ነው ። ይህም ቢሆን ከነፋስ ወፍጮዎች ጋር ባደረገው ግጥሚያ ላይ የጦሩ ዛቢያ ተሰባብሮ ስለቱ ብቻ በመቅረቱ ክፉኛ አዝኖ ስለነበረ ይህንኑ ለጋሻ ጃግሬው በማዋየት እንዲህ አለው ።

«በመጽሐፌ ላይ ያነበብኩትን እንደማስታውሰው» ዲዬጐ ፔሬዝ ዴ ቫርጋስ” የሚባል የእስፓኚያው ኑፍስ ባለ ፈረሰኛ በአንድ ብርቱ ጦርነት ላይ ገጥሞ ከጠላቱ ጋር በሚዋጋበት ጊዜ ሠይፉ ስለተጐረደበት ወዲያውኑ የወይራ ቅርንጫፍ ይሁን ወይም እራሱን ግንዱን ይሁን እንጂ ገነጠለና በዚህ የእንጨት መጣሪያ ጦርነቱን ቀጥሎ በዚያኑ ቀን ብዙዎችን አረቦች እየሰባበረ ስለረፈረፋቸው የፈረሰ ስሙ “አባ ስበር” ተብሎ ተሰየመ ። ከዚያን ቀን አንስቶ እሱም ሆነ የሱ ትውልዶች «አባ ስበር ቫርጋስ» እየተባሉ ይጠሩ ጀመር ። ይህንን ምሳሌ የጠቀስኩልህ እኔም የሱን አርአያ ለመከተል ስለምፈቅድ መጀመሪያ የማገኘውን የወይራ ወይም የክትክታ ዛፍ ያፈቀደው ዓይነት ይሁን ወይም ያንኑ ቫርጋስ የገነጠለውን የመሰለ ብርቱ ቅርንጫፍ ገንጥዬ በሱ እየተዋጋሁ ከፍ ያለ የጀብዱ ሙያ ለመፈጸም አስቤአለሁ ። አንተም አቦታው ላይ ተገኝተህ ይህን ለዓመል

እንኳ ለማመን የሚያስቸግረውን ከፍተኛ የጀብዱ ሥራ ስፈጽም አይተህ ሳላዩት ሰዎች ለመመስከር በመብቃትህ የዕድልህን ቃላችነት ለማመስገን ትችላለህ” አለው ።

«የጊዜው መፍቀድ ይጨመርበት» ሲል መለሰለት ሳንቾ “መቼም እርስዎ የሚሉትን ሁሉ መቀበል ግዴታዬ ስለሆነ እሁን የተናገሩትን አምንዎታለሁ ። ለጊዜው ግን ከአሁኑ ውድቀትዎ ባገኙት ጉዳት የተነሳ ባንድ ጉንዎ የተንጋደዱ ስለሚመስለኝ በኮርቻው ላይ ጥቂት ቀጥ ብለው ቢቀመጡ የተሻለ ነው” አለው ።

«እውነትህን ነው» አለው ዶን ኪሾት «ጉዳቱ በጣም ሳይሰማኝ አልቀረም ፤ ይሁን እንጂ በሕመሜ ለማማረርና የማልችልበት ምክንያት ዙዋሪ ፈረሰኞች ሁሉ ማናቸውም ዓይነት አደጋ ደርሶባቸው ቢቆስሉና ቢፈነከቱ ጥርሳቸውን ነክሰው ከመቻል በስተቀር ማቃሰትና ማማረር የማይፈቀድላቸው በመሆኑ ነው ። ሌላው ቀርቶ ሆድቃቸው እንኳ ቢዘረገፍ መደንገጥና ማጣጣር ነውራቸው ነው ።

«አለ ሳንቾ ነገሩ እንደዚህ ከሆነማ አፈን ዘግቼ ዝም ከማለት በስተቀር ምንም የምመልሰው መልስ የለኝም ። እንደኔ ግን አንዳች አደጋ ደርሶ ሕመሙ በተሰማ ጊዜ ቢያቃስቱ ደስታዬ መሆኑን እኔና አምላክ ብቻ እናውቀዋለን። በኔ በራሴ በኩል ከሆነ ግን ሕመሙ ከተሰማኝ ለትንፍሿ ቁስል ቢሆን እንኳ ማቃሰቴ የማይቀር መሆኑን ላረጋግጥልዎ እወዳለሁ ። ምናልባት ይህን የመሰለው ማቃሰት ክልክልነቱ ከዙዋሪ ፈረሰኞች ወሰን አልፎ ወደ ጋሻ ጃግሬዎችም የሚንጠራራ እንደሆነ ይህን የአረመኔ ልማድ ልታገሰው የማልችል መሆኔን ካሁኑ ጀምሬ አስጠነቅቅዎታለሁ» አለው።

ዶን ኪሾትም በጋሻ ጃግሬው አነጋገርና የዋህነት ሳይሰቅ ለግለፍ ባለመቻሉ ሳቀበትና የፈረሰኛነት ሕግ ካንዱ ሰው የሚጠይቀው የመጨረሻውን ጠንካራነት መሆኑን ካስረዳው በኋላ እሱ ግን ሕመም ቢሰማውም ባይሰማውም ባሰኘውና ባሰፈለገው ጊዜ ለማቃሰትና ለመንፈራፈር መቻሉን አረጋገጠለት ። ይህንንም

ያለው እስከ ዛሬ ድረስ በፈረሰኛነት ሕግ ውስጥ ጋሻ ጃግሬዎች እንዳያቃስቱ የሚከለክል አንድም አንቀጽ አለማንበቡን መሠረት አድርጐ ነው ። ይሁን እንጂ በሰውነቱ ላይ የደረሰበትን ጉዳት መቻል አቅቶት በሕገ ወጥነት ሲያቃስት የተሰማ ጋሻ ጃግሬ ከጌታው የለመደው ይሆናል ተብሎ በሐሜት የሚያስጐሽመው መሆኑን ሳያስጠነቅቀው ለማለፍ አልፈለገም ነበር ። ንግግራቸው እዚህ ላይ እንዳለቀ ሳንቾ ቀጠለና የምላ ሰዓት መድረሱን ለጌታው አስታወቀ ። ዶን ኪሾት ግን ባሁኑ ሰዓት ምግብ ያላስ ኘው መሆኑን በመግለጽ እሱ እንዳሰኘውና እንደመሰለው እንዲ በላ ፈቀደለት ። ሳንቾም ይህን ፈቃድ ካገኘ በኋላ ሴላ ጥያቄና መግደርደር ሳያበዛ ፤ የተቻለውን ያህል ተደላድሎ አህያው ላይ ተቀመጠና ከኮርጀው ውስጥ የከተተውን ዳቦና ደረቅ አይብ እውጥቶ እየገመጠ ከጌታው ኋላ ይሄድ ጀመር ፤ እየቆየም ስርቅ ሲይዘው እርኩቱን ወደ አፉ ያዘነብልና የማላጋን ወይን ቀምቃሚ በሚያስቀና አጠጣጥ እየመጠጠ ይጐነጭ ነበር ፤ በዚህ አኳኋን እስታትሎ እየጠጣ በሚጓዝበት ጊዜ ጌታው የሰጠውን ታላቁን የደሴት ገዢነት ተስፋ እንኳ እስከ መርሳት ደርሶ ነበር ። የቱን ያህል አደገኛም ቢሆን ከቤት ወጥቶ ጫካ ለጫካ ፤ ገጠር ለገጠር እየተዘዋወረ አጋጣሚን መፈለግ ፈጽሞ ድካም የሌለበትና እንዲያውም እውነተኛው ረፍትና ምኞት የሚገኝበት ጉዞ መስሎ ታይቶት ነበር ።

ጌታና አሽከር ምንም አዲስ ነገር ሳያጋጥማቸው ብዙ ምዕራፍ መንገድ ከተጓዙ በኋላ ጊዜው ስለጨለመ ከፊት ለፊታቸው በርከት ያሉ ዛፎች ወደሚገኙበት ጫካ ውስጥ ገብተው ለማደር ወሰኑ ። ዶን ኪሾትም ያንን የቫርጋስን ታሪክ ጠቅሶ የተናገረውን አስታወሰና አንድ በሮር ፋንታ የሚያገለግለው ደረቅ ጨረቃ ገንጥሎ ከዚያ ከተሰበረው ላይ ያወለቀውን የጦር ስለት አዋደደበት ። የዚያን ዕለት ሌሊት ፈረሰኞችንን እንቅልፍ በፍጹም አልያዘውም ነበር ፤ ምክንያቱም በዚያ በመጽሐፍ ላይ ካነበበው ውኔታ ጋር ለመተካከል ፈልጐ እመቤቱን ዱል ቺኒያን በልቦናው እያሰበ ትዝታዋን ባይኑ ላይ መቅረጽ ስለተገባው ነው ። ይህም አደራረግ አያሌ ዙዋሪ ፈረሰኞች ሲያደርጉት እንደ ነበረው ኃሳባቸውን በቀዋታ በእመቤታቸው ትዝታ ላይ አሳር

ፈው በየጫካውና በየበረሃው በሚዘዋወሩበት ጊዜ ብዙውን ሌሊት እንቅልፍ ሳይወስዳቸው ዓይናቸውን እንዳፈጠጡ ያነጉ እንደነበር ተጽፎ የሚገኝ በመሆኑ ነው ። ሳንቾ ፖንቻ ግን ሌሊቱን ያህ ለፈው በዚሁ አኳኋን አልነበረም ፤ ምክንያቱም ቅድም እንደተነገረው ያንን ከርሱን በውሀና በጐመን ሳይሆን በትኩስ ሥጋቅሞልቶት ስለነበር ለመጋደም ከመቻኮሉ በስተቀር የጌታውን ትካዜና ትዝታ ለመካፈል ባለማሰቡ ነው ። ስለዚህ እስቀደሞ አህያ ይቱን ከግንድ ላይ አሠረና ቅጠል መልምሎ መኝታውን እነጠፈና ጌታውን በትክዜ እንደተጨበጠ ጉልቶት እልፎ ተነሄሰ ። ገና ጐኑን ከማሳረፋም ወዲያውኑ የወሰደው እንቅልፍ ሳንድ ሳምንት የሚበቃው ነበር ። ሆኖም ነግቶ እስኪረፍድ ድረስ አልተንቀሳቀሰም ነበርና ጌታው ተናዶ እየረገጠ ጠርቶ ባይቀሰ ቅሰው ኖሮ በፊቱ ላይ የሚያንፀባርቀው የማለዳ ጮራና የአዲሱን ቀን መውጣት በምስጋና ለማብሰር ከዛፍ ወደዛፍ እየበረሩ በዶ ስታ የሚንጫጩት አዕዋፎች ዜማ እንኳ ሊያነቃው የሚችል አልነበረም ። በጉትጐታ ብዛት ባንና እንደተነሳ ወዲያውኑ የአራስ ጌውን እርኩት ዳበስና ቢጠው ከትላንትናው ይዘታው በጣም ጐድሎ ሲንቦጫቦጭ ስለሰማ ይህን ታላቅ ጉድለት በቶሎ ለመ ሙላት የሚቻልበት ዘዴ በቅርብ ሥፍራ እንደማይገኝ ተረድቶ ልቡ በፀፀት እስኪነደፍ አዘነ ።

ዶን ኪሾት ግን እስካሁንም ድረስ አልበላም ነበር ፤ ምክ ያቱም ቅድም እንደተናገርነው ጣዕም ያለው ትዝታ እየተመገበ ልቡ ጠግቦ ስለአደረ ነው ። ስለዚህ እንደወትሮው ልማዱ ገና ዱሮ ታጥቆ ለመነሳት ዝግጁ ሆኖ ነበር ። ሳንቾም ከነቃ በኋላ ከመነሳት አልዘገየም ነበር ። ሁለቱም ከብቶቻቸውን ጭነው ከጫካው ከወጡ በኋላ ወደ ፔዬርቶ ላፒቼ መንገድ ተመልሰው ጉዞአቸውን ጀመሩ ። ከቀትር በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ግድም ከፊት ለፊ ታቸው በርከት ያሉ መንገደኞች ወደነሱ ሲመጡ አዩ ።

ዶን ኪሾት ሰዎቹን ከማየቱ ወዲያውኑ እንዲህ አለ ። «ወዳጄ ሳንቾ እዚህ ሥፍራ ላይ በነዚያ አጋጣሚ በምንላቸው ውስጥ እጃችንን እስከ ክንዳችን ድረስ ለመንከር እንደምንችል አረጋግጠልሃለሁ ። ዳሩ ግን አውን አጥብቄ የማስጠነቅቅህ አንድ

ብርቱ ጉዳይ አለ ፤ ይኸውም በዚህ ዓለም ላይ ታይቶ በማይታ ወቅ ታላቅ አደጋ ውስጥ ተጋፍጨ ብታየኝም የገጠምኳቸው ጠላቶቼ ዝቅተኞችና ወረበሎች ካልሆኑ በስተቀር እኔን አግዝህ ለው ብለህ ጕራይህን መዘዘህ ለእርዳታ እንዳትመጣ ነው ። ጠላቶቼ መደያዎች ሆነው ከተገኙ ግን አሳምረህ ልትአግዘኝ ትችላለህ ፤ ጠላቶቼ ፈረሰኞች የሆኑ እንደሆነ በፈረሰኛነት ሕግ መሠረት አንተ የተካንህ ፈረሰኛ ከመሆንህ በፊት በማናቸውም ምክንያት ረዳት ለመሆን አልፈቅድልህም» አለው ።

«እዚህ ላይስ ግዴልዎትም ሥጋትዎን ጨርስው ሊያስወ ግዱት ይችላሉ» ሲል መለሰ ሳንቾ «እርስዎም ባይነግሩኝ ኖሮ ይህ ትእዛዝዎ በበለጠ ጥንቃቄ የሚፈጸም ነበር ። እንደሚያውቁት በተፈጥሮዬ የረጋሁ ደመ ቀዝቃዛና ሰላማዊ ሰው ስለሆንኩ ለጠብና ለአምባ ጓሮ ዋና ጠላቴ ነኝ ። ጠብና ጭቅ ጭቅ የተነሳ በትን ሥፍራ በሩቁ ከመሸሽ በስተቀር እግሬን አድርሼ አላው ቅም ። ስለዚህ በሰው ዳፋ እንድገባ ሰይጣን እየገፋፋ ቢያስተ ኝም እንኳ ተፈጥሮዬ እንደሚገታኝ አምናለሁ ። ዳሩ ግን እውነ ቱን ለመናገር ከሆነ በቀጥታ በራሴ ላይ የሚመጣውን አደጋ ለመከላከል ባለኝ ኃላፊነት መሠረት ከህነት አልተቀበልኩም በማለት አጕንብሼ ለመደብደብ ስለማልችል ይህን የፈረሰኛነት ሕግዎን ከቁም ነገር የማላገባው መሆኔን ላረጋግጥልዎ እወዳ ለሁ ። ምክንያቱም መለከታዊም ሆነ ሰብዓዊ ሕጐች እያንዳንዱ ፍጡር የሚያጠቃውን ጠላት እንዲከላከል የፈቀድለት መሆኑ የማይካድ ስለሆነ ይህን የመከላከል ተግባሬን ሳልፈጽም ለመቅ ረት በውነቱ ከበረዶ የተፈጠርኩ መሆን የሚገባኝ ነው» አለው።

«ይህንስ አሌ አልልህም» አለ ዶን ኪሾት «የሆነው ሆኖ ከፈረሰኞች ጋር በምዋጋበት ጊዜ እኔን ለመርዳት የሚያድርብ ህን የተፈጥሮ ቁጣህን እንድትአበርደው አሁንም ደጋግሜ አስጠነቅቅሃለሁ» አለው ።

«በፍጹም አይጠራጠሩ» አለ ሳንቾ ይህን «ትእዛዝዎን» ሰንበትን አክብር «እንደተባለው የአሪት ቃል አክብሬ እጠብ ቀዋለሁ» ሲል አረጋገጠለት ።

በዚህ ጉዳይ እየተነጋገሩ ወደፊት ሲራመዱ ሁለት የቤኔ ዲክት ገዳም መነኮሳት በሁለት ግመሎች ላይ ተቀምጠው ብቅ አሉ ። ግመሎቹ ያልናቸውም የተቀመጡባቸው በቅሎዎች ትንንሾች ስላልነበሩ ነው ። መነኮሳቱ ትልቅ የመንገድ መነ ጥር አድርገው የፀሐይ ጃንጥላም ይዘው ነበር ። ከነሱም በስተኋላ ለጥቀው የሚመጡት በፈረስ ላይ የተቀመጡ አራት ወይም አምስት የሚሆኑ ሰዎችና ሁለት እግረኛ ጕሪደማዎች ያጀቡት አንድ ሠረገላ ነበር ። ቀጥሎም እንደታወቀው በሠረገላ ውስጥ የነበረችው አንዲት የቢስካሊያ ሴት ወይዘሮ ባልዋ ከፍ ያለ ሹመት ተቀብሎ ወደ ሕንድ አገር ለመሔድ ሲቢልያ ይገኝ ስለነበር እሱን ለመሰናበት የምትሔድ ነበረች ፤ መነኮሳቱ ግን መንገዳቸው አንድ ይሁን እንጂ ከሴትዮይቱ ጋር አውቀት አልነበራቸውም ። ሆኖም ዶን ኪሾት እንዳያቸው ወዲያውኑ ለጋሻ ጃግሬው እንዲህ አለው ።

«ወይም እኔ ተሳስቼ ይሆናል ፤ ወይም ደግሞ ይህ የዛሬው የውጊያ ድግስ ምን ጊዜም ያልታየ እጅግ ስመ ገናና የጀግ ኖች መራኮቻ ግጥሚያ መሆን አለበት ። ምክንያቱም እነዚያ ወደኛ ሲጠጉ የምናያቸው ሁለት ጥቋቁር ጥቅልሎች በዚያ ሠረገላ ውስጥ አንዲት የተጠለፈች ልዕልት በመተት አደንግ ዘው የሚወስዱ አስማተኞች መሆን አለባቸው ። እንዲያውም ያለ ጥርጥር እነሱው ስለሆኑ ባለኝ ሙሉ ችሎታ ይህን ጥቃት መበቀል አለብኝ» አለው ።

«ይህ የአሁኑ አጋጣሚ ከነፋስ ወፍጮዎች ይልቅ የባሰ አሳፋሪ ሊሆን ነው» አለ ሳንቾ «እባክዎን ጌታዬ ይጠንቀቁ ፤ እነዚያ ወደኛ የሚመጡት ሁለቱ ሰዎች በአሰባበሳቸው እንደ ሚታየው የገዳም መነኮሳት መሆናቸው የማያሳስት ነው ። ሠረገላውም የሌሎች መንደገኞች ሳይሆን አይቀርምና አሁን በተናገሩት ላይ እርግጠኛ ከመሆንዎ በፊት አጣርተው ቢመለ ከቱ የተሻለ ነው ። የሚያደርጉትንም ነገር በሚገባ ይመርምሩት ። እስከዚህ ድረስ እያጭበረበረ የሚያታልልዎት ዲያብሎስ ሳይሆን አይቀርምኛ እንዲያው በከንቱ ልብዎን ከፍተውለት መፈንጫ አያድርጉት» አለው ።

«ሳንቾ» አለ ዶን ኪሾት «እኔ ከብዙ ጊዜ ጀምሬ እንደ ነገርኩህ አንተ ስለአጋጣሚ ጉዳይ ምንም የማይገባህ ደደብ መሆንክን ገልጬ አስረድቼህ ነበር ። አውንም ደግሞ እውነተኛው እንተ ሃሰተኛው እኔ መሆን አለመሆናችንን በወሬ ሳይሆን በሥራ ገልጨ አሳይሃለሁ» አለው ።

ይህን ተናግሮ ሲያበቃ ወደፊት ተራመደና መነኮሳቱ ለማለፍ በሚመጡበት መንገድ መካከል ገብቶ ተደነቀረ ። መነኮሳቱ እየተቃረቡ መሞተው የሱን ድምጽ ለመስማት በሚችሉበት ሥፍራ ላይ የደረሱ ሲመስለው እንዲህ እያለ ይጮህ ጀመር ።

"እናንት አጋንንት የሠፈረባችሁ ፣ እርኩስ መናፍስት ያደረባችሁ አስማተኞች ፣ በዚህ ወገባላ ውስጥ አፍናችሁ በእስረኛነት የምትአንከራትቷቸውን ልዕልታት አሁን በፍጥነት ነፃ እንድትለቋቸው አዝዤአችኋለሁ ። አለበለዚያ ግን ለመጥፎ ተግባራችሁ የተዘጋጀላችሁን የሞት ቅጣት ለመቀበል ተሠናዱ" አላቸው ።

መነኮሳቱም በድንጋጤ የከብቶቻቸውን ልጓም ጉትተው ቆሙና በዶን ኪሾት መልክና አነጋገር እንደተገረሙ እንዲህ ሲሉ መለሱለት ።

"የተከበሩ ፈረሰኛ ሆይ ፣ እኛ የቅዱስ ቤኔዲክት ገዳም መነኮሳት ነን እንጂ ክቡርነትዎ እንደሚሉት አጋንንት የሠፈረብን ወይም እርኩስ መናፍስት ያደረብን አስማተኞች አይደለንም ፣ የስላም መንገዳችንን ይዘን ወደ ጉዳያችን የምንሄድ ከመሆናችን በስተቀር በሰረገላው ውስጥ የታሠሩና የታፈኑ ልዕልታት መኖር አለመኖራቸውን በጭራሽ አናውቅም ።" አሉት ።

"የማስመሰያ ምክንያትና የተኳለ የመቅለስለስ ንግግር ምን ጊዜም አታልሎኝ አያውቅም" አለ ዶን ኪሾት" እኔ እንደሆንኩ ማን እንደሆናችሁ አሳምሬ አውቃችኋለሁ ። አናንተ እምነተቢስ ውሾች ፣ አንዳች ማምለጫ ዘዴ የላችሁምና ነፍሳችሁን ለማሰንበት የምትመርጡ እንደሆነ ይልቁንስ ያዘዝኳችሁን በቶሎ ፈጽሙ ፣ አለበለዚያ ግን ያልኳችሁን ማድረጌ ነው" አላቸው ።

ከዚህ ሌላ መልስ እስኪሰጡት ሳይጠብቅ ርጉዚናንቱን ኩሪኩሪና ጦሩን አዘቅዝቆ ይህ ነው በማይባል ፍጥነትና ድንፋታ ወደ አንደኛው መነኩሴ ተወረወረ ። መነኩሴው አመጣጡን አይተው ከመ—ቅጽበት ዘለው ወርደው እቢቅሎይቱ ሆድ ስር ባይገቡ ኖሮ ምንም እንኳ በቀጥታ ባይገድሳቸው ክፉኛ አቁሰሎ ከኮርቻቸው ላይ ገልብጦ እንደሚያወርዳቸው የተረጋገጠ ነበር ። ሁለተኛው መነኩሴ ደግሞ ለጓደኛቸው የተደረገላቸውን የክብር አቀባበል በተመለከቱ ጊዜ የበቅሎአቸውን ወገብ በሁለት ጭናቸው አጠበቁና ብማይገታ ሽሽት በሚዳው ላይ እንደነፋስ ተፈተለኩ ።

ሳንቾም እመሬት ላይ የወደቁትን መነኩሴ ተመለከተና ከአህያው ላይ ወርዶ እየሮጠ ደርሶ እላያቸው ላይ ከተከመረ በኋላ ሠናፊላቸውን መግፈፍ ጀመረ ። በዚህን ጊዜ ካንዲት ምንጭ ውሀ ለመጠጣት ወደ ኋላ ቀርተው የነበሩት ሁለት የመነኮሳት አሽከሮች ደርሰው ሳንቾ የሚያደርገውን አይተው በምን ምክንያት እንደሚገፋቸው ጠየቁት ። ሳንቾም በበኩሉ ጌታው ዶን ኪሾት በደንበኛ ውጊያ ላይ ጠላቱን ስለአሸነፈ የምርኮውን ዕቃ በሕጉ መሠረት መውሰድ ያለበት እሱ መሆኑን አስረዳቸው ። እነዚያ ተማሪዎች ግን የውጊያና የምርኮ ታሪክ የማያውቁ ስለሆኑ ሳንቾ የሰጣቸው መልስ የወሮበልነት መንፈስ ያለበት ማላገጫ ስለመሰላቸው ፣ እንዳጋጣሚ ደግሞ ዶን ኪሾት ከባለ ሰረገላዎቹ ሰዎች ጋር ለመነጋገር ወደዚያ ሄዱ ስለነበረ ብቻውን አግኝተው በላዩ ላይ ወደቁበትና ማንቁርቱን እንቀው ወደ መሬት ከጣሉት በኋላ እያነሳበጡ በእርግጫና በጡጫ አልፍተው ፣ እሪዙን በሙሉ ነጭተው ያለ ትንፋሽና ያለ ስሜት እመሬት ላይ ዘርግተውት ሔዱ ። የወደቁትም መነኩሴ በድን ጋጤ ፌታቸው አመድ እንደመሰለ በተማሪዎቹ እርዳታ ተነስተው እበቅሎአቸው ላይ ወጥተው እንደፈሩና እንደተንቀጠቀጡ ጓደኞቻው መጠነኛ ርቀት ላይ ቆመው የረብሻው ፍጻሜ ምን እንደሆነ እየተመለከቱ ይጠብቋቸው ነበርና ወደዚያው አቅጣጫ ገሥግሠው ተገናኙ ። ከዚህ በኋላ ሁለቱም መነኮሳት የረብሻውን መጨረሻ ለማየት ጠልተው ዲያብሎስ በተረከባቸው ስር የነባቸው ይመስል አሥሬ እያማተቡና ፀሎት እያደረሱ ጉዞአ

ቸውን ቀጠሉ ። ዶን ኪሾትም ቅድም እንደተባለው ከሠረገላው ውስጥ ካለችው ወይዘሮ ጋር ንግግር ጀምሮ ስለነበረ እንዲህ እያለ ይነዘንዛት ነበር ።

"ልዕልት አመቤቱ ሆይ ፤ ከእንግዲህ ወዲህ የተዋበው ልዕልናዎ ለውነትዎን እንዳሰኝዎት ሊያዙትና ሊያዝናኑት መቻልዎን አረጋግጥልዎታለሁ ። የጠላፊዎችን ትምክሕትና ኩራት በዚህ በኃይለኛው ክንዴ ብርታት ተሰባብሮ እነሆ ይኸው እመ ፌት ላይ ወድቋል ። የአስማተኛውም ጥበብ እንደጪስ በኖል እንደበረዶም ሟምቷል ፤ የነፃ አውጭውንም ስም ለማወቅ እንዳይ ችሩ "የማንቻው ዶን ኪሾት" እጋጣሚውን የሚፈልግ ዙዋሪ ፈረሰኛ ወደር የሌላት የውቢቷ የቶቦዞይቱ ዱልቺኒያ ባሪያ" መሆኔን ስገልጽልዎ ከኔ ለተቀበሉት በጐ አገልግሎት ወሮታ እንዲሆነኝ ሌላ ዋጋ እንዲከፍሉኝ አላሰቸግርኩዎትም ። ዳሩ ግን ከታላቅ ወሮታ የምቆጥረው መንገድዎ ወደ ቶቦዞ አቅጣጫ አጥፈው በኔ ስም እመቤቱ ፊት ቀርበው ልዕልትነትዎን ነፃ ለማ ውጣት ያደረግሁትን ብርቱ የጀግንነት ተጋድሎ በዝርዝር እንዲ ነግሩልኝ ብቻ ነው" ሲል መልሱን በመጠበቅ ንግግሩን አቆመ ።

ሠረገላውን ከሚያጅቡት መካከል አንደኛው የቢስኪሊያ ተወላጅ የሆነ ጋሻ ጃግሬ ይህን ሁሉ ንግግሩን ተጠንቅቆ ያዳ ምጥ ነበርና ዶን ኪሾት መንገዳቸውን ወደፊት እንዳይቀጥሉ የሚከለክልና እንዲያውም የቸኮሉበትን ጉዳይ ትተው በፍጥነት ወደ ቶቦዞ እንዲሄዱ የሚያዝዛቸው መሆኑን ከተረዳ በኋላ ወደሱ ተጠግቶ ባንድ እጁ የዶን ኪሾትን ጦር ጨበጠና ባልተጣራ የአስፓኚያና የካስቲሊያ ቅልቅል ቋንቋ እንዲህ ሲል ሰደበው ።

"ወግድ ከዚህ ፤ ሂድ ወደገደል መጨረሻህ የማያምር ወግ አራቂ ፈረሰኛ ፤ ልቀቅ ሠረገላውን እምቢ ካልህ አምላክ አይማ ረኝ እኔ የቢስካሊይቱ ልጅ እገድልሃለሁ" አለው ።

ዶን ኪሾትም የቢስካሊያው ንግግር ደህና አድርጐ ሰሰን ባው በተጀነነና በንቀት አነጋገር እንዲህ ሲል መለሰለት"

"አንተ አቶክቷኪ ገልቱ ፍጥረት ፤ ፈረሰኛ አለመሆንህ በጀህ እንጂ ፈረሰኛ ብትሆን ኖሮ ላሁኑ የድፍረትና የብልግና አነጋገርህ የሚገባህን ቅጣት እስጥህ ነበር" አለው ።

"እኔ እንዳንተው ፈረሰኛ ነኝ" ሲል መለሰለት ቢስካሊ ያው "አምላክ ይመስክርብኝ አንተ ቀጣፊ ዋሾ ነህ ፤ በል እስቲ ወንድ ከሆንክ ጦርህን ጣልና ጐራዴህን ምዘዝ ፤ የሰገመን እንገትህን ቆርጬ ስዋለው ታያለህ ፤ እኔ የቢስካሊይቱ ልጅ እመሬት ላይ ስቀር እንተ ዲያብሎስ እንዲቀበልህ ወደ ባህር እወረውርሃለሁ ፤ ሐሰት ነው ብትል ና ላሳይህ" አለው ።

"እንግዲህ እስቲ ጉብዝናህን እንየው" ሲል በንቀት መለ ሰለት ዶን ኪሾት ። ይህን ተናግሮ ሲያበቃ ጦሩን ወደመሬት ጣለና ጐራዴውን ጨብጦ ጋሻውን አነባበና ቢስካሊያውን ለመግ ደል ቁርጥ አሳብ አድርጐ ተንደረደረበት ። ቢስካሊያውም በዚህ አኳኋን በቁጣ ግሎ ሲመጣበት በተመለከተው ጊዜ ከበቅሎ ላይ ዘልሎ ለመውረድ ፈልጐ ነበር ፤ ምክንያቱም በቅሎይቱ የተውሶ ስለሆነች አመሷን ስላልተማመነው ነው ። ዳሩ ግን ያኛው ሰላማ ደፈው በቅሎይቱ ላይ እንደሆነ ጐራዴውን ከመዎዘዝ በስተቀር ለመውረድና ለመዘጋጀት ፋታ አላገኘም ። እንደ ዕድል ደግሞ ቢስካሊያው ከሠረገላው አጠገብ አልራቀም ነበርና እጁን ሰድዶ አንድ መከላ ጐትቶ እንደጋሻ እንዲያገለግለው ያዘ ፤ ከዚህ በኋላ ምንም ያህል ሳይዘገዩ መሠረተ ደንበኞች ይመስል ለመተራረድ ተፋጥጠው ተሰለፉ ። ሌሎቹም አሽቢዎች ገላግለው ጠቡን ለማብረድ ሞክረው ነበር ። ዳሩ ግን ቢስካሊያው ክፉኛ አምርሮ ስለነበር በዚያ በጐልዳፋ ቋንቋው እየሰፈሰፈ ውጊያውን እናስ ጨርስህም ብለው ያሰናከሉት እንደሆነ ገላጋዮችንና እመቤቲ ቱንም የሚገድላቸው መሆኑን በዛቻ አስጠነቀቃቸው ። የሰረገላውም ባለቤት ይህን ረብሻ በማየቷ በፍርሐት ስለተሸበረች ነጂውን ጠቅሳ ከዚህ ስፍራ ራቅ አድርጐ እንዲያቆም ካዘዘችው በኋላ በሩቁ ሆና ከደንገጡሮቿ ጋር ይህን አስደንጋጭ ውጊያ ትመል ከት ጀመር ። በዚህን ጊዜ ቢስካሊያው ጐራዴውን ወንዝር በዶን ኪሾት ትከሻ ላይ አሳረፈበት ፤ የተሰነዘረውም ጐራዴ የጋሻ ውን ከንፈር አግኝቶ እሱኑ ብቻ ጠርቦ ኃይሉ ባይበርድ ኖር

የዶን ኪሾትን ትክሻ እስከመቀነቻው ድረስ ሊሰነጥቀው ይችል ነበር ።

ዶን ኪሾትም የዚህ የብርቱ ሰንዘራ ምት ክባዱ ዘልቆ ትክሻውን ክፉኛ ስለተሰማው እንዲህ ሲል በኃይል እየጮኸ ተማጠነ ።

"የነፍሴ እመቤት ዱልቺኒያ ሆይ ፣ የቁንጅና አበባ ሆይ ፣ የክብርሽን ታላቅነት ይበልጥ ለማግነንና ፍላጐትሽን ለማስደሰት የሚዋጋውን ፈረሰኛሽን ከዚህ ከጐምዛዛው መጋፈጥ ላይ አሸና ፊነትን እንዲያገኝ እርዳታሽን ላኪለት" ካለ በኋላ ይህን ቃል መናገሩ ፣ ጐራዴውን አጥብቆ መጨበጡ ፣ ጋሻውን በደንብ መመ ከቱ ፣ በቢስካሊያ ላይ መወርወሩ ይህ ሁሉ ባንዲት ደቂቃ ውስጥ የተከናወነ ሥራ ነበር ። ምክንያቱም የቢስካሊያውን ዕድል ባንድ የጐራዴ ምት ብቻ አጠቃልሎ ለመጨረስ ቁርጥ ሃሳብ ስላደረገ ነው ።

ቢስካሊያውም ባላጋራው ከመጀመሪያው በተለየ ድፍረትና ቆራጥነት እሳት ጐርሶ ሲመጣበት ባየው ጊዜ በዚህ ቁጠኛ መንፈሱ ጉብዝናውን ስላወቀለት እሱም ይህንኑ ያህል ጉብዝና ለማሳየት ደሙን አስቆጥቶ በመከዳው ጭንቅላቱን ሸፍኖ ጠበቀው ። ይህም ሲሆን ያኛ በቅሎ ይህን የመሰለ የውጊያ ንቅ ናቂ ማድረግ አጋጣሚት የማታውቅ በመሆኗና ይህም የነሱ ልፊያ አድክሟት ታክታ ስለ ነበረ ወዲያም ሆነ ወዲህ ሊያነ ቃንቃት ሞክሮ ስለአቃተው እዚያው እንደተገተረች ቀረች ። ስለዚህ ከፍ ብሎን እንደተናገርነው ዶን ኪሾት ጐራዴውን ከጫፉ ቀና አድርጐ ቀበጡን ቢስካሊያዊ ከሁለት ሥፍራ ለመ ሰንጠቅ እንደተዘጋጀ ሲወረውር ፣ ቢስካሊያው ደግሞ በበኩሉ ጐራዴውን አቅንቶ በትራሱ ደህና አድርጐ መክቶ ይጠብቀው ነበር ፣ እቦታው ላይ የሚገኙት ሰዎች ሁሉ በፍርሃት እየተንቀ ጠቀጡ ሁለቱ ተዋጊዎች የተዛዛቱበት ይህ ብርቱ የጐራዴ ስንዘራ ምን ዓይነት ውጤት ለመስጠት እንደሚችል ለማወቅ በችኩላ ይጠባበቁ ነበር ።

ዛቻው እዚህ ነጥብ ላይ ደርሶ ሳለ የዚህ ታሪክ ደራሲ ለተንኮሉ ከዚህ በላይ ከተተረከው ሁኔታ በስተቀር የዶን ኪሽ

ትን የተዋጊነት ሙያ ፍጻሜውን የሚናገር ሌላ ታሪክ አላገኘ ሁም በማለት አመካኝቶ የውጊያውን ውጤት ለመግለጥ እስመ ቻሉን እስታውቆ እንደዚሁ ተንጠልጥሎ መቅረቱን ብቻ ጽፎ አል ፣ ይህን ታሪክ ከአረብኛ ወደ እስፓንኛ የተረጐመ ሁለተኛው ደራሲ ደግሞ ይህን የመሰለ የሚያጓጓ ታሪክ በዝምታ ጨለማ ውስጥ ተቀብሮ ሊቀር የሚገባው አይደለም በማለትና እንዲሁም የማንቻ ታሪክ አዘጋጅዎች በቤተ መዘክራቸው ውስጥ በየግስ ታወሻቸው ላይ የዚህን የስመ ጥር ፈረሰኛ ታሪክ የሚጠቅሱ አን ዳንድ ማስረጃዎች ሳያስቀምጡ ምንም ቢሆን በችላ ባይነት አይተውት በማለፍ በዚህ አኳኋን የታሪኩ ፍጻሜ መቋረጡን ለማመን አልፈለገም ነበርና በዚህ አስተያየት ተጽናንቶ ተስፋ መቁረጡን ትቶ በትጋት በመፈለግ ብዛት የታሪኩን መጨረሻ አግኝቶ በሚቀጥለው ምዕራፍ ላይ እንደሚተርከው አድርጐ ለመጻፍ በመቻሉ ደስታው ከልክ ያለፈ ሆኗል ።

ምዕራፍ 9

የማንቻው ጀግናና ጉበዙ ቢስካሊያዊ የተሳለፉበት አስደናቂው የውጊያ ሁኔታ የሚተረክበት ፍጻሜ የሚስተበት ።

በዚህ ታሪክ በመጀመሪያው ክፍል ላይ ጀግናው ቢስካሊ ያዊና ስመ ጥር ዶን ኪሾት ጉራዲያቸውን መዝዘው ጫፉን ሽቅብ አቅንተው ሁለት ኃይለኛ ስንዝራ ለማውረድ እንደተፋጠጡ ትተናቸው ነበር ። ይሁን እንጂ በዚህ ስንዝራ ሙሉ ለሙሉ ተማትተው ቢሆን ኖሮ አካላቸውን ከላይ እስከታች ተሰናጥቀው እንደሩማን ፍሬ መተርከካቸው የማይቀር ነበር ብንል አጉል ግምት አይሆንብንም ። ዳሩ ግን ይህን በመሰለው አፋላሚ ነጥብ ላይ ደርሰው ግንባር ለግንባር እየተያዩ በሚገኙበት ጊዜ ደራሲው አጽርጦ የተወው የታሪኩ ረቂቅ ወዴት እንደሚገኝ ሳይናገር በጣም ጠቃሚና አንኒ የሆነውን ክፍል ሳይቀጥል መቅረቱን ብቻ ተናግሮ በማለፉ በውነቱ እጅግ የሚያንገበግብ ስሜት ሳይፈጥር አልቀረም ነበር ።

ስለዚህ ጉዳይ በተለይ በጣም የሚያበሳጨው ሁኔታ ይህ አስካሁን ድረስ የተነበበው ጥቂቱ ክፍለ ታሪክ ላንባቢው ያስገኘውን ደስታ እንደገና ያንን ተጽርጦ የቀረውን አብዛኛውን ክፍለ ታሪክ ከተጣለበት ሥፍራ ፈልጐና ተመራምሮ አግኝቶ ፍጻሜውን ለማወቅ የሚያደርገው ከፍ ያለ ድካም ሲታሰብ ደስታውን ወደ ሃዘን ለመለወጥ ምክንያት መሆኑ ነው ። እኔም እንደማስበው ተጽርጦ የቀረው ታሪክ በጣም አስደሳቹ ክፍል መሆን እንዳለበት አምናለሁ ። የሆነ ሆኖ ሌሎቹ ዘዋሪ ፈረሰኞች እንኳ ከነዚያ ሰዎች ሁሉ «በለስ ፈላጊዎች» ከሚልዋቸው ውስጥ አንዳንዶቹ ታሪካቸውን ዕለት በዕለት እየተከታተለ የሚጽፍ

ላቸው ደራሲ ምን ጊዜም እንዳላጡ ስለማውቅ በተለይም ደግሞ ይህን ለመሰለ ስመ ጥር ጀግና ፈረሰኛ አስደናቂ የጀብዱ ተግባሩን እግር በእግር እየተከታተለ የሚጽፍለት አንድ ታሪክ ጸሐፊ አልነበረም ለማለት ከቶ የማይታመን ከማናቸውም መልካም ወግና ልማድ ውጭ የሆነ ነገር መስሎ ስለታየኝ ታሪኩ ሳይጻፍለት ቀር ቷል ብዬ ለማመን አልቻልኩም ። ምክንያቱም አንዳንዶቹ ፈረሰኞች በተለምዶ አንድ ወይም ሁለት ታሪክ ጸሐፊ ያላቸው ስለ ሆኑ እነዚህ ጸሐፊዎች የውጊያ ተግባራቸውን ዋና አርዕስት ብቻ በመተረክ ሳይወስኑ እንስተኛውን ሃሳባቸውንና በጣም ጥቃቅንና ጥብቅ ምስጢር የሆነውን ስሜታቸውን ጭምር በመ ዘርዘር እንደሚተርኩላቸው ስለማውቅ ነው ። የዙዋሪ ፈረሰኞች ታሪክ የነፕላቲሮና የሴሎችም ታሳላቆች ጭምር በዚህ አካኋን እየተለቀመ አስቀድሞ ሲጠናቀቅላቸው ይህን የመሰለው ጉበዝ ፈረሰኛ ደግሞ ከሌሎቹ አንሶ እስከዚህ ድረስ የታሪክ ደሀና ዕድለ ቢስ ሊሆን መቻሉን እጠራጠራለሁ ። ስለዚህ ይህን የመሰለው ታላቅ የጀግንነት ታሪክ ተልከስከሶ እንካሳና ጉደኛ ሆኖ ቀርቷል ብዬ በማመን አጉራጠናኝ ለማለት ስላታተኝ ጥፋቱን ማናቸውንም ነገር በሚውጠውና በሚያወድመው በጊዜ መጥፎነት ላይ መሳከክ ግዴታ ሆነብኝ ። ይህንንም ያደረ ግሁት ተጽርጦ የቀረውን ታሪክ ጊዜ ደብቆት ወይም ድራቹን አጥፍቶት ይሆናል በማለት ገምቼ ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ መጻሕፍቱ ውስጥ ከዘመናዊዎቹ መካከል «የቅናት ማሞኝያ» የሔናሬስ ሐመልማል « የሔርሬስ አረኞች» የሚባሉት ስለተገኙበት የሱም ታሪክ ዘመናዊ መሆን እንደአለበት ግልጥ ነው ። ታሪኩ ተጽፎ ባይገኝም ቅሉ የእኩ ሽማግሌዎችና በአቅራቢያውም የሚኖሩት ጐረቤቶቹ በታላቸው አጥንተው ሳያስታውሱት አይቀሩም በማለት አሰብኩ ። ይህም ሃሳብ ስሜቴን ቀስቅሶ የስመ ጥርውን አስፓኛል የማንቻው ዶን ኪሾትን ሕይወትና ሞት ፤ ግብረ ተአምራት በውነትና በትክክል አጣርቼ ለማወቅ የበረታ ፍላጐት አሳደረብኝ ። ይህ ለማንቻዎቹ የፈረሰኛነት ተግባር ማህበር ደልጋሙሴ ፤ መብራትና መስታወት የሆነውን ጀግናና እንዲሁም በክፍለ ዘመናችን ይህን የሞተውን ማህበር አስነስቶ ለአቆመውና የመጀመሪያውን መሥ

ረት የተከለውን ይህን በመሰለ አስተካክ ጊዜ ውስጥ ጠማማ ምችን ለማቅናት የሙት ሚስቶችን ለመርዳት ልጃገረዶችን ለመ ጠበቅ ቀዳማዊ ሆኖ የተነሳው እሱ ብቻ በመሆኑ ታሪኩ በዚህ አካኋን ተረሳስቶ የሚቀር አልነበረም ። እነዚህም ወይዘ ዝርት በፊተኛው ዘመን በኮርቻ ፈረስ ላይ ተቀምጠው አስ ንጋ ይዘው ከነድንግሳቸው ከተራራ ወደ ተራራ ከሜዳ ወደ ሜዳ ሲንሸራሸሩ በሚውሉበት ጊዜ አንዳንድ ሽረኛ ሰው ወይም መገሪያ የያዘ ባላገር ወይም ደግሞ ግድንግድ ጀዋዛ ድንገት ጠልፎ ክብራቸውን ይገስፋቸው ነበር ።

በድሮ ዘመን ከተወለዱ ጀምረው በፍርሃት እየተሳሳቁ አንዲት ሴሊት እንኳ እቤታቸው ገብተው ሳይተኙ እንደወለዱ ዋቸው እናቶቻቸው ሆነው በስማንያ ዓመታቸው ከነድንግላቸው መሬት ውስጥ የሚገቡ ሴቶች ነበሩ ።

ስለዚህ በዚህና በሌላም በብዙ ምክንያቶች የኛው ትን ታጉ ዶን ኪሾት መታሰብና ዘለዓለም መመስገን የሚገባው ሆኖ እናገኘዋለን ። ይህም ሲሆን ለኔም ለራሴ ይሆን እጅግ ናፋቂ የሆነውን ታሪክ ፍጻሜ ፈልጌ ላልሰሙት ለማሰማት ላደረግሁት ድካምና ትጋት የሚገባው ምስጋና እንዳይነፈገኝ አሳስባለሁ ።

የሆነ ሆኖ የታሪኩን ፍጻሜ ለማግኘት ቸሩ አምላክ ወይም አጋጣሚው ምክንያት ወይም ዕድሉ አግዞኝ ባላገኘው ኖሮ ወደፊት ታሪኩን በጥንቃቄ የሚያነበው ሰው እንደሚገነዘበው መላውን ዓለም ላንድ ሰዓት ያህል የሚያስቅ መደሰቻ ነገር አጥቶ ቀረ ለማለት የሚቻል ነበር ፤ እነሆ እንግዲህ የታሪኩን ፍጻሜ ለማግኘት የቻልኩት ከዚህ ቀጥዬ በማስረዳው አካኋን ነው ።

ከዕለታት አንድ ቀን በቶሌዶ ከተማ አልካና በሚባለው አደባባይ ሳለሁ አንድ ልጅ ላንድ የሀር ነጋዴ አሮጌ የተጻፈ ባቸው ደብተሮችና አሮጌ የእጅ ጽሕፈት ያለባቸው ክታቦች ለመሸጥ ሲያስማማ አየሁት ፤ መቸም እኔ መጽሐፍ ማንበብ በጣም የምወድ ሰው በመሆኔ የተነሳ በመንገድ ላይ ወድቀው የማናኛቸውን ብጥስጣሽ ወረቀቶች እንኳ አንስቼ ሳላነብ

አላልፍም ነበርና በዚህ ዝንባሌዬ ተገፋፍቼ ከልጁ ከንድ ላይ አንዱን ደብተር አንስቼ ብመለከተው ፊደሉ በዓረብኛ ትርጉ የተጻፈ ሆኖ አገኘሁት ። የዓረብኛው ፊደል መሆኑን በአጣጣሉ ልለየው እንጂ ንባቡን ስለማላውቅ በዚያው በአለሁበት ዙሪያ ምናልባት አንድ የተጠመቀ ዓረብ አግኝቼ ያነብልኛል በማለት በዓይኔ እፈልግ ጀመር ። የዚህንም ቋንቋ ተርጓሚ በዚህ አገር ውስጥ ማግኘት የሚያስችገር ነገር አልሆነብኝም ነበር ፤ ምክን ያቱም ሌላው ቀርቶ በኔ መሳሳት ምክንያት ጽሕፈቱ የጥንታ ዊው ዕብራይስጥ ቋንቋ ሆኖ ቢገኝም ኖሮ የዚህንም ቋንቋ ትር ጓሚ ወዲያውኑ ሳገኘው እንደምችል እርግጠኛ ነበርኩ ።

ስለዚህ ይህንኑ የምፈልገውን ትርጓሜ አግኝቼ ሃሳቤን ገለጥኩለት ዮ የእጅ ጽሑፍ ያሰበትን ክታብ ሰጠሁት ።

እሱም ገልጦ በውስጡ ከተጻፈው አንዳንድ ታሳት ካነበበ በኋላ ከት ብሎ ይስቅ ጀመር ። በዚህን ጊዜ በምን ምክንያት እንደሳቀ ብጠይቀው በክታቡ ባንደኛው ገጽ ላይ የተጻፈውን ቃል አይቶ መሳቁን ነገረኝ ።

እኔም ንባቡን ተርጉሞ እንዲነግረኝ ለመንኩት ። እሱ ግን መሳቁን ሳያቆም እንዲህ አለኝ ።

''ቅድም እንዳልኩት በዚህ ገጽ ላይ ተጽፎ የሚነበበው ቃል ትርጉም በዚህ ታሪክ ላይ ብዙ ጊዜ እየተደጋገመች የተነሳ ችው ይህች የቶበዘይቱ ዱልቺኒያ የምትባልዋ ሴት የአሳማ ሥጋ በመቀመምና በመሰነግ ረገድ በማንቻ ውስጥ ካሉት ሴቶች ይበልጥ ባለሞያና እጅ በረከታም ነች ይሏታል'' የሚል ነው ሲል ተረጉመልኝ ።

''የቶበዘይቱ ዱልቺኒያ'' የሚለውን ስም ባነሳብኝ ጊዜ በጣም ስለገረመኝ ይህ ክታብ የዶን ኪሾትን ሙሉ ታሪክ የያዘ መሆኑን ለመገመት ቻልኩ ።

በዚህም ሃሳብ እንደተቻኮልኩ አርዕስቱን እንዲያነብልኝ እንደገና ለመንኩት ። እሱም ዓረቢኛውን ወደ ካስቴሊያ እየተረ ጐመ አርዕስቱ ቀጥሎ ያለውን መሆኑን አስማኝ ፤ ይኸውም


"ከዓረቡ ታሪክ ጸሐፊ ከሲዲ አህመድ ቤኒንጌል የተጻፈ የማን ቻው ዶን ኪሾት ታሪክ የሚል ነበር ። የዚህ መጽሐፍ አርዕስት ተነቦልኝ በተረዳሁት ጊዜ የተሰማኝን ደስታ ለመደበቅ ታላቅ የመንፈስ ኃይል እንዲኖረኝ የሚያስፈልግ ነበር ። እንግዲህ ይህ ታሪክ እንዳያመልጠኝ በጣም ሠግቼ ነበረና ከሐር ነጋዴው ላይ አፋርሼ ልጁ የተሸከማቸውን ደብተሮች በሙሉ በብር አላድ ገዝቼ ወሰድሁ ። ልጁ ብልጥ ቢሆንና ፍላጐቴንም ቢያውቀው ኖሮ መጐምጀቴን በራቴ ላይ ዓይቶ ዋጋውን ከስድስት ብር በላይ ሊነጫኝ ይችል ነበር ። ወዲያውኑ ከዓረቡ ጋር ተያይዘን እራቅ ብለን ሔድንና ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ደጅ ሰላም ገባን ። እዚያም ተቀምጠን በምንነጋገርበት ጊዜ የዶን ኪሾትን ታሪክ የሚጠቅሱትን ጽሑፎች ሁሉ እንዳች ትርፍ ቃል ሳይጨምርና ሳይቀንስ ወደ ካስቲሊያ ቋንቋ እንዲተረጐምልኝ ለመንኩት ። ለድካሙም ዋጋ የጠየቀኝን ሂሳብ ልከፍለው ቃል ገባሁለት ። እሱ ግን የድካሙን ዋጋ እምሳ ንዋር ዘቢብና ሁለት ድርብ ስንዴ ከሰጠሁት የሚበቃው መሆኑንና እንዲሁም ትርጉሙን ቀላል በሆነ አገባብ በትክክልና በሐቀኛነት የሚተረጉምልኝ መሆኑን ቃል ገባልኝ ። እኔ ግን ሥራውን ለማጣደፍና ይህም መልካም አጋጣሚ እንዳያመልጠኝ በማለት ዓረቡን ወደቤቱ ይዤው ሔድ ኩና ካንድ ወር ተኩል ጥቂት በለጥ በሚል ጊዜ ውስጥ ትርጉሙን በሙሉ አጠናቆ ጨረሰልኝ ። ይኸውም ትርጉም እንዳለ በሙሉ በሚከተለው ሁናቴ የሚተረከው ነው ።

በመጀመሪያው ደብተር ላይ ዶን ኪሾት ከቢስካሊያው ጋር የተጋተረው የውጊያ አሰላለፍ በሚገባ ተስሎ እውነተኛውን መልኩን እንደያዘ ይታይ ነበር ። ሁለቱም ተዋጊዎች በታሪኩ ላይ ሁኔታቸው በተነገረው ዓይነትና አኳኋን የመሰለፊያ ቦታቸውን እንደያዙ ጐራዴያቸውን እንዳቀኑ ፤ ዶን ኪሾት በጋሻው እንደተሸፈነ ፤ ቢስካሊያው በትራሱ እንደተከለለ ፤ የበቅሎዬቱም አቋቋም በደንብ እንደተነገረው ሁሉ ከዚያው ከቦታዋ ሳትነቃነቅ ተገትራ የተውሶ ከብት መሆኗን ባንድ ቀላድ ርቀት ላይ ቆሞ ለሚያያት ሰው በጉልህ የምትአስታውቅ ሆና ትግኛ ነበር ። ከቢስ ካሲያው ስዕል ግርጌ "ዶን ሳንቾ ዳስፔሲያ" የሚል ጽሑፍ ይነበባል ። ይህም ያለ ጥርጥር የሱው ስም መሆን አለበት ።

በሮንዜናንቴ እግር ስር ደግሞ "ዶን ኪሾት" የሚል ጽሑፍ ይነበባል ።

የሮንዜናንቴም አቋቋም ቁመቱ እንደተንተዋለለ ፤ አዋንቱ እን ደቆመ እንደቀጠነና እንደከሣ እንደጐበጠና እንደጠመለገ ወትሮ መልኩ ግሩም ሆኖ የተሳለ በመሆኑ ይኸው ስዕሉ "ሮንዜ ናንቴ" የተባለውን ስም በምን ያህል ትክክለኛነትና ሥዩምነት እንደተሰጡት በግልጥ የሚመሰክርለት ነበር ። ከሮንዜናንቴ በስተጐን ደግሞ ሳንቾ ፖንቻ አህያውን በሎኮዋ እንደያዛት ተስሎ ይገኛል በግርጌውም "ሳንቾ ቻያንኬ" የሚል ጽሑፍ ይነበባል ። እንዲህም የተባለበት ምክንያት በስዕሉ ላይ እንደሚታየው ምናልባት ከራቱ ቦርጭ የገፋና ቁመናው ጽሑር ሆኖ የእግሩ አንገ ስለረዘመ ይመስላል። ስለዚህ ቻንቻ ወይም ቺያንኬ እየተባለ በታ ሪኩ ጐዳና ውስጥ ብዙ ጊዜ ይጠራበታል ። ከዚህም በስተቀር ሌሎ ችም ጥቃቅን ዝርዝር ሁኔታዎች በስዕሉ ላይ ይገኛሉ ። ዳሩ ግን ቁም ነገርነታቸው ያነሰ ስለሆነ ለዚህ ለዕውነተኛው ታሪክ ምስክር ነት ቢጨምሩም ቢቀሩም የማይጠቅሙና የማያስፈልጉ በመሆናቸ ው እዚህ ላይ አልተዘረዘሩም ። ይሁን እንጂ በታሪክ ዝግጅት ውስጥ የሚታከለው ድርጊቶች ወይም ሁኔታዎች ሁሉ እውነተኞች ከሆኑ ማናቸውም ዓይነት ዝርዝር ቢሆን መጥፎ ነው ተብሎ ሊናቅ የሚገባው አልነበረም ።

ይህ ሁኔታ እውነተኛ መሆኑን በመጠራጠር አንዳች ነቀ ፊታ ለማድረግ ቢሞክር ነቀፌታው ክብደት ሊያገኝ የሚችለው ታሪኩን የጻፈው የዓረብ ሰው መሆኑ ሲታሰብና እነዚህም የዓረብ ሰዎች መዋሸት የታወቀ አመላቸው በመሆኑ ሲገመት ብቻ ነው። ይሁን እንጂ ብዙ ምቀኛ ጠላት ስለማይጠፋ የዶን ኪሾትን የጀግንነት ሞያ ከማጋነን ይልቅ በመጠኑ ለክተው ያሳነሱበት መሆኑን ለሚረዳው ሰው ይህንኑ የተተረከውን ጥቂቱን አምኖ መቀበል ይቻላል ። ለኔም አስተያየት ትክክለኛ መስሎ የታየኝ በእርግጥ ይኸው ግምት ነው ። ምክንያቱም ይህን የመሰለውን ጀግና ፈረሰኛ ለማመስገን የሚዘጋጀውን ታሪክ አፋጥኖ ለመጻፍ በብዕር ላይ ክንፍ ማቀበል በሚያስፈልግበትና በሚገባበት ዘመ ላው ግጥሚያ ጊዜ ሁኔታውን አጀርጮ በዝምታ ለማሳለፍ የተደ



ረገው ሙከራ ሲታይ ደራሲው ሆነ ብሎ ያደረገው ተንኮል መሆኑን ያሰምናል ። ይህም በውነቱ አጉል ሃሳብና መጥፎ አድራጐት እንደሆነ ለማንም የተሠወረ አልነበረም ። ምክንያቱም ታሪክ ጸሐፊን ሲባሉ በሙሉ ትክክለኞች ሐቀኞች እውነተኞች የማ ያዳሉ መሆን ስለሚገባቸው ይህን ከመሳሰለው ግምት ውስጥ እንዳይገቡ አጥብቀው መሸሽና መጠንቀቅ ስላለባቸው ነው ። ጥቅም ፈላጊነትም ሆነ ወይም ፍርሃት ወይም ቂመኛነት ወይም ለወዳጅ ማድላት ከእውነት መስመር ሊያወጣቸው አይችልም ።

እውነት የታሪክ እናት ስለሆነች የጊዜ ተወዳዳሪ ፤ የድር ጊት መዝገብ ፤ የኃላፊው ምስክር የአሁኑ ምሳሌና ማስጠንቀቂያ የመጪው መምህርና መካር ለመባል የምትችል ናት ። ስለዚህ በእውነት መሠረት ላይ ያልተገነባ ታሪክ ሁሉ በቀላሉ ዋጋ አልባ ሆኖ ስለሚወድቅ በበኩሴ በዚህ ታሪክ ውስጥ ይበልጥ ጠቃሚ ሆኖ የሚፈለገው ሁሉ እንደሚገኝበት አውቃለሁ ። ምናልባት ደግሞ በጥልቅ ማስተዋል ተመራምራችሁ ፍሬ ነገር ያለው ድርጊት ያጣችሁበት እንደሆነ እኔ በበኩሴ ጉድለቱን የማየው ከታሪኩ መካንነት ይልቅ በዚያ በውሻው ደራሲ ላይ ነው ። እንግዲህ እስከዚህ ድረስ ካሰረዳሁ በኋላ የሁለተኛው ክፍል ታሪክ መስመሩን በመከተል የተዘጋጀው ትርጉም ቀጥሎ እንዳለው ሆኖ መነበቡን እገልጣለሁ ።

ሁለቱ ጀግናዎችና ሳታናዎች ደፋር ተዋጊዎች የሾለና የተ ሳለ ጐራዴያቸውን መዝዘው ጫፉን ወደላይ አቅንተው እየሰበቁ ሲዳንቱ ላያቸው ተመልካች ሰማይና ምድርን ገሃነም አሳትን ጭምር ለማደበላለቅ ቆርጠው የተነሱ ይመስሉ ነበር ። መቸም የተያያዙት እልክና ቁጭት ከመጠን በላይ ያለፈ በመሆኑ መጀ መሪያ ጐራዴውን ወንዝሮ ምቱን ያሳረፈው ቁጠኛው ቢስካ ሊያዊ ነበርና በበዛ ኃይልና ንዴት ዶን ኪሾትን አብስሎ መታው ። ምቱንም በሚያዋርድበት ጊዜ ጐራዴው ለጥቂት አዳልጦት በጨረፍታ ባይስት ኖሮ ይህ ምት ብቻውን ለዚህም ለተጋጋለው ውጊያና ለፈረሰኞችም ያጋጣሚ ፈላጊነት ዙረት የማያዳግም ፍጻሜ ለመስጠት የሚበቃ ነበር ። ዳሩ ግን ዕድሉ ለሌላ እጅግ ከፍ ላለ ተግባር ተቆጥቦ እንዲቆይ በመፈቀዱ

ምክንያት በኃይል የተሠነዘረው የወደረኛው ጐራዴ ዓላማውን እንዲስት አደረገው ። ይህም ሆኖ ምንም እንኳ ምቱ ክዣራ ትከሻው ላይ ቢያርፍ በዚያ ወገን የሚገኘውን ነገር በሙሉ ጠርቦ የራስ ቁሩን አብዛኛውን ክፍል ሸርፎ ፣ የጀርውንም እኩሌታ ቆርጦ ከመጣሉ በስተቀር ከዚህ የከበዱ ሌላ ጉዳት አላደረገም ነበር ። ማናቸውም ጥራቢና ቁርጥራጭ ሁሉ እየተፈ ናጠረ በሚያስደነግጥ አሰባበር ተንካክቶ መሬት ላይ ወደቀ ። ፈረሰኛውም በጣም ለመጐዳት በቃ ።

"የጀግኖች ያለህ ፤ እንግዲህ አውን የማንኛቸው ጀግና በዚህ አካኋን ተጠቅቶ ጉዳት ደርሶበት ሲታይ በልቡ ውስጥ የገባውን አንገብጋቢ ትኩስ ንዴት በሚገባ አብራርቶ ለአንባቢ ለመተረክ የሚችል ማን ይገኛ ይመስላችኋል ? በውነቱ በሱብሳቢ ቃል የንዴቱ ወሰን ከልክ አልፎ እንደ እቶን የጋለ ነበር ብሎ መናገር ብቻ በቂ ይሆናል ። ስለዚህ በዚህ ንዴቱ ሲታው እየተ ናነቀው ከኮርቻው ላይ ተነስቶ እርካቡን ተረግሞ ቆመ ፤ ጐራ ዴውን በሁለት እጁ ጨብጦ ፤ አንድ ኃይለኛ ምት ሠንዝር በቢስካሊያው ላይ ሙሉ በሙሉ ቢያሳርፍበት ትራሱን ደርቦ መሐል አናቱን ተረከከው ። ይህኛውም ምንም እንኳ የትራሱ ከለላ ከሞት ቢያስጥለው ያረፈበት ምት ከባድነቱ ተራራ የተና ደበት ያህል ዘልቆ ተሰምቶት ነበርና በአፉና በአፍንጫው በጀሮውም ጭምር ትኩስ ደም እየተፋ ከበቅሎይቱ ላይ ለመው ደቅ ይዝለፈለፍ ጀመር ። ሆኖም የበቅሎይቱን አንገት በሁለት እጁ አቅፎ ባይጠመጠምባት ኖሮ በቀጥታ መውደቁ የማይጠረ ጠር ነበር ። ይህንንም በሚያደርግበት ጊዜ እግሮቹ ከእርካቡ ውስጥ ስለወጡበትና እጆቹም ዝለው ስለላሉበት በቅሎይቱ በአስደንጋጩ በትር ደንብራ በእርሻው መካከል ስለ ፈረጠጠች ጭነቷን ሶስትና አራት ለሚሆን ጊዜ ካጋደለች በኋላ ወዲያውኑ ጌታዋን እንደያዘች ወድቃ ተንከባለለች ።

ዶን ኪሾት በልበ ሙሉነት አስተያየት ቆሞ ተሸናፊውን ሲመለከት ነበርና መውደቁን ባየ ጊዜ ከፈረሱ ላይ ዘልሎ ወርዶ በፍጥነት ከተጠጋው በኋላ የጦሩን ጫፍ ዓይኑ ላይ ደግሮ እንዲማረክ አለበለዚያ ግን አንገቱን የሚቆርጠው መሆኑን አስ

ታወቀው ። ቢስካሊያው ግን በዚያን ሰዓት ክፉኛ ተጐድቶ በመፍዘዙ የተነሳ ግማሽ ቃል እንኳ ለመናገር የሚችል አልነበረም ። ዶን ኪሾት ደግሞ ከእብደቱ በላይ ንዴት ተጨምሮ ልቡን ሰውሮት ነበርና እስካሁን ድረስ ከሰረገላው ውስጥ ሳይ ወጡ በድንጋጤ እየራዱ ውጊያውን ይመለከቱ የነበሩት ሴቶች በሩጫ ደርሰው የጋሻ ጃግሬአቸውን ነፍስ እንዲተርፍላቸው በታ ላቅ ልመናና መለማመጥ ምሕረት ባይጠይቁለት ኖሮ የቢስካ ሊያዊው ፍጻሜ አደገኛ ሊሆንበት ነበር ። መቸም ቢሆን ዶን ኪሾት በወይዛዝርታት የሚጨክን ልበ ደረቅ ሰው አልነበረምና በተጀነነ ጕልማሳነት እንዲህ ሲል መለሰላቸው ።

''እርግጥ ነው ፤ የተዋባችሁ ወይዛዝርት ሆይ ፤ ልመናችሁን ለመቀበል በጣም ደስ ይለኛል ። ዳሩ ግን ምሕረት ከመስጠቱ በፊት ከናንተ ዘንድ የምጠይቀው ግዴታና ውለታ ይህ በገዛ ጥጋቡ ተሸንፎ የወደቀው ቀበጥ ፈረሰኛ በቀጥታ ወደ ቶቦዞ ሄዶ በኔ ስም ወደር የሌሽ እመቤቱ ዱልቺኒያ ፊት ቀርቦ እፅ. ያስኛትን እንድታደርግበት እሱም የታዘዘውን እንዲፈጽም የምታደርጉ የሆነ እንደሆነ ነው አላቸው ።

የሚንቀጠቀጡትና የተጨነቁት ሴቶች ግን ዶን ኪሾት የተናገረው ምን እንደሆነ አጣርተው ሳይሰሙና ነገሩ ሳይገባ ቸው ፤ ይህቺም ዱልቺኒያ የምትባለው ሴት ማን እንደሆነች ሳይጠ ይቁና ሳይረዱ በደፈናው ጋሻ ጃግሬው የታዘዘውን ሁሉ እንዲ ፈጽም ከዶን ኪሾት የተጣለበትን ግዴታና ውለታ ላያጓድሉ ለመፈጸም ቃል ገቡለት ።

ዶን ኪሾት የምነት ቃላቸውን ከተቀበለ በኋላ እንደኩራ እንዲህ አላቸው ፤ ምንም እንኳ ይህ ክልፍልፍ ፈረሰኛ ምሕረት ማግኘት የማይገባው ቢሆን ይህን የታመነ ቃላችሁን በማክበር የደገኃችሁን ጦር አንስቼ ነፍሱን ምሬላችኋለሁ አላቸውና ከቢስ ኪሊያው አጠገብ ተነሰቶ ወይዛዝርታትን ተሰናብቶ ተለየ ። እነዚያም ቁስለኛቸውን አንስተው በሰረገላው ላይ ከጫኑ በኋላ ጉዞአቸውን ቀጠሉ ።

ም ዕ ራ ፍ 10

በዶን ኪሾትና በጋሻ ጃግሬው በሳንቾ ፖንቻ መካከል የተደረገው አጫዋች ንግግር ይተረካል ።

ምንም እንኳ የመኮሳት አሽከሮች ሳንቾ ፖንቻን ክፉኛ ደብድበው ቢጥሉት ለጥቂት ጊዜ እንደወደቀ ቆይቶ ነፍስ ከዘራ በኋላ ተነስቶ ቆሞ ይሆን ጌታው የተጋጠመውን የመጀመ ሪያውን ኃይለኛ ውጊያ እንዲያሸንፍና አንድ ደሴት አግኝቶ ከዚህ ቀደም በሰጠው ተስፋ መሠረት እሱን ለደሴቷ ገዢ አድ ርጐ ለመሾም እንዲያበቃው በልቦናው እግዚአብሔርን እየለመነ ይመለከት ነበር ።

የውጊያው ክስክስ አልቆ ጌታው ሮንዜናንቴ ላይ ለመው ጣት በሚሠናዳበት ጊዜ ሳንቾ እርካቡን ሲይዝለት ፈጥኖ ተጠጋውና ያኖው ፈረሱ ላይ ከመውጣቱ በፊት አጠገቡ ደርሶ ተንበርክኩ እጆቼን ከሳመ በኋላ የሚቀጥለውን ተናገረ ።

''የኔ ጌታ ዶን ኪሾት ሆይ ፤ እንግዲህ አሁን መልካም ፈቃ ድዎ ይሁንና በዚህ ጉምዛዛ ፤ በሆነው ውጊያ ላይ ድል አድርገው ያገኙዋትን ደሴት ግዛቷን ይስጡኝ ። የቱን ያህል ሰፊና ታላቅ አገር ብትሆንም እንኳ በዓለም ላይ የሚገኙት የደሴቶች ገዢዎች እንደሚገዙዋት አድርጌ ወይም አስበልጬ በትክክል ለመግዛት ችሎታና ብርታት ስለሚሰማኝ ችሎታዬን በመጠራጠር መስጠቱ ቅር እንዳይልዎት'' አለው ።

''የኔ ወዳጅ ሳንቾ ሆይ ፤ ሲል መለሰለት ዶን ኪሾት ''ይህ አሁን ያየኸው አጋጣሚና ሌላውም እሱን የመሳሰለው ሁሉ ተራ የመንገድ ግጭት ይባላል እንጂ አንተ እንደገመትከው

ደሴት የሚገኝበት ጦርነት አይደለም ። ከዚህ ዓይነት ግጭት የሚገኘው ትርፍ ጭንቅላትን አስፈንክቶ አንደኛውን ጆሮ አስ ቆርጦ እየበሸቁ ወደ ቤት መመለስ ብቻ መሆኑን ማወቅ ይገ ባሃል ። ስለዚህ አሁን ለጠየቅኸኝ ጉዳይ መፈጸም እስክ ጥቂት ቀን እንድትታገስኝ አደራ እልሀለሁ ። ምን ጊዜም ቢሆን ሌሎ ችም አጋጣሚዎች እንደምናገኝ የተረጋገጠ ስለሆነ በዚያን ጊዜ የደሴት ገዢ በማድረግ ብቻ ሳይሆን ከሱም እጅግ ወደላቀ ማዕረግ ላደርስህና ብዙም ነገር ላደርግልህ እንደምችል እመ ነኝ" አለው ።

ሳንቾም ለዚህ ለተቀበለው ተስፋ ጥልቅ ምስጋናውን አቀረ በና እንደገና የጌታውን እጅና የለበሰውን ጥራሬ ከተሳለመ በኋላ እንዳተለመደው ሮንዜናንቴ ላይ እንዲወጣ አገዘው ። እሱም ተራውን አህያው ላይ ተቀመጠና ጌታውን ለመከተል ዝግጁ ሆኖ ተሰናዳ ። ዶን ኪሾትም በሠረገላው ውስጥ የተቀመጡትን መንገደኞች ሳይሰናበትና አንዳችም ጥያቄ ሳያደርግላቸው በፈጠነ ሰምሰማ እቅቡ ወዳለው ጫካ አመራ ። ሳንቾም ባህያው ኩስክ—ስታ ተከትሎት ነበር ። ነገር ግን ሮንዜናቴ በቀለጠፈ እርምጃ የሚሄድ ርስለነበረ ሳንቾ ከጌታው ተነጥሎ ወደኋላ መቅረቱን አየና ጌታው ቆሞ እንዲጠብቀው ጮሆ መናገር ግዴታ ሆነበት ። ዶን ኪሾትም ጥሪውን ሰምቶ የሮንዜናንቴን ልጓም ስቦ ቆመና ስነፉ ጋሻጃግሬ እስኪደርስበት ድረስ ጠበ ቀው ። ያም ከደረሰ በኋላ እንዲህ አለው ።

"ጌታዬ ሆይ ፣ ቅድም በውጊያው ላይ የፈነከቱት ወደረ ኛዎ በብርቱ ቆስሎ አይቸዋለሁ መቸም የአደጋውን ወሬ ለመ ንደሩ ጐረምሶች መናገሩ የማይቀር ስለሆነ ጐረምሳዎቹ በዱካ ችን ተከታትለው መጥተው እንደሚይዙን የማይጠረጠር ነው ። ከተያዝንም በኋላ ከምንደበደበው ዱላ ይበልጥ በወንጀለኛነት ተይዘን የምንታሰር ስለሆነ ከወህኒ ቤት ሰብረን ለማምለጥ ከመቻላችን በፊት የደም ላብ ማንጠፍጠፍ እንደሚኖርብን አምናለሁ ። ስለዚህ የተከበሩት ጌታዬ ምክሬን ሳይንቁ ቢያዳም ጡኝ አውራ መንገድ ይዘን ከምንንቀሪፈፍ ይልቅ ወደ ቀኞችን እጥፍ ብለን ወደ አንድ ቤተ ክርስቲያን ወይም ወደ ገዳም

ንብተን ብንሰወር ከሚያሰጋን መያዝ የምናመልጥ ይመስለኛል አለ ።

"እባክህ አትቃዥ ዝም በል" አለ ዶን ኪሾት "ለመሆኑ አንድ ዙዋሪ ፈረሰኛ የፈቀደውን ያህል አመጽ ቢሠራና ነፍስ ቢገድል እጁ ተይዞ ፍርድ ቤት ይቀርባል ሲባል ወሬ ሰምተህ ወይንስ ታሪክ አንብበህ ታውቃለህ ? ።

"ሳንቾም መለሰ" እኔ ስለ ነፍስ መግደልና ስለ አመጽ መሥራት አንዳች ነገር ለማወቅ አልፈለግም ፤ ምክንያቱም በሕ ይወቴ ውስጥ ይህን የመሰለ ወንጀል ሰርቼ ተከስሼና ተቀጥቼ ስለማላውቅ ነው ። ባንዳንድ ጠብ ምክንያት እርስ በርሳቸው የሚግቱ ሰዎች በአገሬው ዘበኛ እየተያዙ መታሠራቸውን ብቻ አረጋግጣለሁ ። በተለይ ስለሌላው የአመጽ ሥራ ግን እኔን የሚያገባኝ ነገር የለም" አለ ።

ዶን ኪሾትም መለሰ "ወዳጄ ሆይ ፤ አይዞህ ይህን ያህል አትፍራ ፤ አትርበድበድ ፤ እኔ እንደሆንኩ እንኳንስ ከመንደር ዘበኞች እጅ ይቅርና ከአይሁዳውያን እጅ ቢሆን መንጥቄ ላወ ጣህ የምችል ነኝ ። እረ እንዲያው ለመሆኑ በል እስቲ ንገረኝ ፤ በምድር ገጽ ላይ በጀግንነት የሚበልጠኝ ፈረሰኛ አይተህ ታው ቃለህን ? ለመጋጠም የቆራጥነት ድፍረት ያለው ፤ ለሞያ የበለጠ ትባት ያለው ፤ ለመምታት የፈጠነ ቅልጥፍና ያለው ፤ ባላንጣውን አሸንፎ ለመጣል የበለጠ ብልሀትና ብርታት ያለው ወይም ሊኖረው የሚችል ሌላ ፈረሰኛ አለ ሲባል በታሪክ ላይ አንብበህ ታውቃለህን ? "

"እውነቴን ለመናገር " አለ ሳንቾ "ጽሕፈትም ሆነ ንባብ ስለማላውቅ ከቶ ታሪክ የሚባል ነገር አላነበብኩም ። ዳሩ ግን በሕይወቴ ውስጥ በጀግንነቴ ከርስዎ ለሚበልጥ ጌታ አድራና አገልግዬም እንደማላውቅ ልወራረድ እችላለሁ ። ላስገኝዉ የምፈልገው ይህ ከልበ ደንዳናነት የመጣው ጀግንነትዎና ዕውር ድፍረትዎ የበረታ አደጋ ላይ እንዳይጥልዎት ብቻ ነው ። እስከዚያው ድረስ የጆሮዎ ቁስል ብዙ ደም እየፈሰሰው ነውና

ቢታከሙት የተሻለ ይመስለኛል ። ከቦርሳዬም ውስጥ ጨርቅና ነጭ ቅባት ስላለ ለመታከሙ በጣም ይረዳዎታል" አለ ።

ዶን ኪሾትም መለሰ "የፊዩሮብራዙዬን" ዕፀ ፈውስ ቀምሜ በብልቃጥ ሞልቼ መያዘን እስቀድሜ ባስታውሰው ኖሮ ይህ የምትለኝ መድኃኒት ሁሉ ከንቱ በሆነ ነበር ። ምክንያቱም ዕፀ ፈውሱ ብርቱ አብነት ስላለው የሱ አንዱ ጠብታ ብቻ መድኃኒቱንና ለሕክምናም የምናጠፋውን ጊዜ ያስቆጥበን ነበር" አለው ።

ሳንቾም እንዲህ ሲል ጠየቀ "የምን ዓይነት ዕፀ ፈውስና የምን ብልቃጥ ነው የሚያወሩኝ ፣ እሱስ ለምን የሚበጅ ዕፅ ነው ? አለ ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል አስረዳው "ይህን ዕፀ ፈውስ የያዘ ሰው ለሞት መደንገጥና በመቁሰልም ምክንያት እሞታለሁ ብሎ መሸበር አይገባውም ። አቀማመሙን እንኳ በቃሌ አስታውሰዋለሁ ። ስለዚህ ይህን ዕፅ በልኩ ቀምሜ በብልቃጥ ሞልቼ ላንተ ካስረከብኩ በኋላ ካንድ ፈረሰኛ ጋር ውጊያ ገጥሜ በምዋጋበት ጊዜ ዘውትር ሊደርስ እንደሚችለው ሁሉ ወደረኛዬ በጕራዴ ወገቤን ከሁለት ላይ ጕርዶ ጥሎኝ ስታይ በቶሎ ፈጥነህ መሬት ላይ የወደቀውን ጉራጅ እንስተህ ደሙ ሳይረጋ ወስደህ ኩርቻ ላይ ተቀምጦ ከቀረው ጉማጅ ጋር ከቦታው እንዳይዛነፍ በጥንቃቄ አላክከህ ከማዋደድ በቀር ሌላ ድካም የለብህም ። ይህ ንንም ከፈጸምክ በኋላ ከዚያ ከያዝከው ዕፀ ፈውስ ከሁለት ጉንጭት የማይበልጥ ታጠጣኛለህ ። ይህ እንደሆነ ወዲያውኑ ከባህር ወጥቶ በትኩሱ እንደተመለሰ አሣ ድኜ ስፈነጭ ታየኛለህ" አለው ።

"እንዲህማ ከሆነ" አለ ሳንቾ "እኔ ስለረጅሙና ስለ መልካሙ አገልግሎቴ ዋጋ ተሰፋ ያደረጉልኝ የደሴቷን ገዢነት ጅማት ከዛሬ ጀምሮ ትቼ የዚህን የተአምራዊ መጠጥ አቀማመጥ ብቻ እንዲያስተምሩኝ ከመለመን በቀር ሌላ ውለታ እንዲውሉልኝ ዳግመኛ አላስቸግርዎትም ። ምክንያቱም በማናቸውም ሥሩራና ጊዜ ልሸጠው ካሰብኩት በትርምሮ ቤት እንኳ አንዲን

ጠብታ በሁለት ብር ሂሳብ ለመቸብቸብ እንደምችል አምናለሁ ። ስለዚህ የተረፈውን ሕይወቴን በረፍትና በጌትነት ለማሳለፍ ከሱ ሽያጭ ከማገኘው ጥቅም ይበልጥ የምጠይቀው ሌላ ነገር የለኝም ። ለመሆኑ አቀማመሙ ብዙ ገንዘብ ይፈጃል መሆን አለመሆኑን አስቀድሞ ማጣራት ያሻል" አለ ።

ዶን ኪሾትም መለሰ ፣ "ከሶስት ብር ባነሰ ገንዘብ ሶስት ኪሎ የሚወጣውን ዕፀ ፈውስ ለመቀመም ትችላለህ" አለው ።

ሳንቾ እንዲህ ሲል አመለከተ "የተደረገለትን በማመስገን እንግዲያውስ ዕፁን ከመቀመምና እኔንም ከማስተማር በቀር ሌላ ምን ይጠብቃሉ" አለው ።

"እረ ዝም በል ሳንቾ ገና ምን አይተሃ" አለ ዶን ኪሾት" ብዙ ምስጢር ላስተምርህና እንዲሁም ዋጋህን በጣም ከፍ አድርጌ ልከፍልህ አስቤአለሁና አትቸኩል ። ይልቁንስ አሁን የጀርዬ ቁስል እየቆጠቆጠኝ ከማልፈልገው ይበልጥ አሞኛልና እንደ እውቀትህ አድርገህ አክመኝ" አለው ።

ሳንቾ ከቦርሳው ውስጥ ጨርቅና ቅባት ማውጣት ጀመረ ። ነገር ግን ዶን ኪሾት በዚያን ጊዜ የራስ ቁሩን መጠርመስ አይቶ የንዬቱ ብዛት በአንድ አፍታ እንደ እብድ አደረገው ። ወዲያውኑ የጕራዬውን እጀታ ጨበጠና ዓይኖቹን ወደ ሰማይ አንጋጥጦ እንዲህ ሲል ማለ ። "ሁሉን በሚችል በፈጣሪ አም ላክና አራቱ ቅዱሳን በጻፉት ወንጌል ባለው ቃል መሐላ ይሁንብኝ ፣ ይህን ጉዳት ያደረገብኝ ሰው ፈልጌ አግኝቼ ስለ እራስ ቁሩ መጠርመስ ሙሉ በቀል እስክበቀለው ድረስ የማንቾቫው ማርኪዝ የወንድሙን ልጅ የባልደቤኖን ሞት ለመበቀል ምሎ በነበረ ጊዜ መሐላውን እስኪፈጽም ድረስ የኖረውን ዓይነት ኑሮ እኔም እኖራለሁ ። ይኸም መሐላ በተሰናዳ ገበታ ላይ ቀርቦ ላይበላ ፣ ከገዛ ሚስቴ ጋር በግብረ ሥጋ ላይገናኝ ፣ ሌላም ከዚህ የባሰ ነገር እንዳያደርግ የሚመስነው ስለነበረ ምንም እንኳ ሁሉን በሙሉ ላስታውሰው ባልችል በበኩሌ በመሐላዬ ምክንያት ከዚህ ይበልጥ የሚያሳቅቅ ችግር ቢደርስብኝም ተግሪሬ ላልተው በመሐላዬ እጸናለሁ" አለ ።



በታከሙት የተሻለ ይመስለኛል ። ከቦርሳዬም ውስጥ ጨርቅና ነጭ ቅባት ስላለ ለመታከሙ በጣም ይረዳዎታል" አለ ።

ዶን ኪሾትም መለሰ "የፊዩሮብራዙን" ዕፀ ፈውስ ቀምሜ በብልቃጥ ሞልቼ መያዝን አስቀድሜ ባስታውሰው ኖሮ ይህ የምትለኝ መድኃኒት ሁሉ ከንቱ በሆነ ነበር ። ምክንያቱም ዕፀ ፈውሱ ብርቱ አብነት ስላለው የሱ አንዱ ጠብታ ብቻ መድኃኒቱንና ለሕክምናም የምናጠፋውን ጊዜ ያስቀጥበን ነበር" አለው ።

ሳንቾም እንዲህ ሲል ጠየቀ "የምን ዓይነት ዕፀ ፈውስና የምን ብልቃጥ ነው የሚያወሩኝ ፣ እሱስ ለምን የሚበጅ ዕፅ ነው ? አለ ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል አስረዳው "ይህን ዕፀ ፈውስ የያዘ ሰው ሰሞት መደንገጥና በመቁሰልም ምክንያት እሞታለሁ ብሎ መሸበር አይገባውም ። አቀማመሙን እንኳ በቃሌ አስታውሰዋለሁ ። ስለዚህ ይህን ዕፅ በልኩ ቀምሜ በብልቃጥ ሞልቼ ላንተ ካስረከብኩ በኋላ ካንድ ፈረሰኛ ጋር ውጊያ ገጥሜ በምዋጋበት ጊዜ ዘወትር ሊደርስ እንደሚችለው ሁሉ ወደረኛዬ በጦራዬ ወገቤን ከሁለት ላይ ጉርዶ ጥሎኝ ስታይ በቶሎ ፈጥነህ መሬት ላይ የወደቀውን ጉራጅ አንስተህ ደሙ ሳይረጋ ወስደህ ኩርቻ ላይ ተቀምጠ ከቀረው ጉማጅ ጋር ከቦታው እንዳይዛነፍ በጥንቃቄ አላክከህ ከማዋዶድ በቀር ሌላ ደካም የለብህም ። ይህ ንንም ከፈጸምክ በኋላ ከዚያ ከያዝከው ዕፀ ፈውስ ከሁለት ጉንጭት የማይበልጥ ታጠጣኛለህ ። ይህ እንደሆነ ወዲያውኑ ከባህር ወጥቶ በትኩሱ እንደተመለሰ አሣ ድኜ ስፈነጭ ታየኛለህ" አለው ።

"እንዲህማ ከሆነ" አለ ሳንቾ "እኔ ስለረጅሙና ስለ መልካሙ አገልግሎቱ ዋጋ ተስፋ ያደረጉልኝ የደሴቷን ገዢነት ሹመት ከዛሬ ጀምሮ ትቼ የዚህን የተአምራዊ መጠጥ አቀማመጥ ብቻ እንዲያስተምሩኝ ከመለመን በቀር ሌላ ውለታ እንዲውሉልኝ ዳግመኛ አላስችግርዎትም ። ምክንያቱም በማናቸውም ሥፍራና ጊዜ ልሸጠው ካሰብኩት በችርቻሮ ቤት እንኳ አንዱን ጠብታ በሁለት ብር ሂሳብ ለመቸብቸብ እንደምችል አምናለሁ ። ስለዚህ የተረፈውን ሕይወቴን በረፍትና በጌትነት ለማሳለፍ ከሱ ሽያጭ ከማገኘው ጥቅም ይበልጥ የምጠይቀው ሌላ ነገር የለኝም ። ለመሆኑ አቀማመሙ ብዙ ገንዘብ ይፈጃል መሆን አለመሆኑን አስቀድሞ ማጣራት ያሻል" አለ ።

ዶን ኪሾትም መለሰ ፣ "ከሶስት ብር ባነሰ ገንዘብ ሶስት ኪሎ የሚወጣውን ዕፀ ፈውስ ለመቀመም ትችላለህ" አለው ።

ሳንቾ እንዲህ ሲል አመለከተ "የተደረገለትን በማመስገን እንግዲያውስ ዕፁን ከመቀመምና እኔንም ከማስተማር በቀር ሌላ ምን ይጠብቃሉ" አለው ።

"እረ ዝም በል ሳንቾ ገና ምን አይተህ" አለ ዶን ኪሾት" ብዙ ምስጢር ላስተምርህና እንዲውም ዋጋህን በጣም ከፍ አድርጌ ልከፍልህ አስቤአለሁና አትቸኩል ። ይልቁንስ አውን የጀሮዬ ቁስል እየቆጠቆጠኝ ከማልፈልገው ይበልጥ አሞኛልና እንደ እውቀትህ አድርገህ አክመኝ" አለው ።

ሳንቾ ከቦርሳው ውስጥ ጨርቅና ቅባት ማውጣት ጀመረ ። ነገር ግን ዶን ኪሾት በዚያን ጊዜ የራስ ቁሩን መጠርመስ አይቶ የንዴቱ ብዛት በአንድ አፍታ እንደ እብድ አደረገው ። ወዲያውኑ የጦራዬውን እጀታ ጨበጠና ዓይኖቹን ወደ ሰማይ አንጋጥጦ እንዲህ ሲል ማለ ። "ሁሉን በሚችል በፈጣሪ አም ላክና አራቱ ቅዱሳን በጻፉት ወንጌል ባለው ቃል መሐላ ይሁንብኝ ፣ ይህን ጉዳት ያደረገብኝ ሰው ፈልጌ አግኝቼ ስለ አራስ ቁሩ መጠርመስ ሙሉ በቀል እስክበቀለው ድረስ የማንኾቸው ማርኪዝ የወንድሙን ልጅ የባልደቤናን ሞት ለመበቀል ምሎበነበረ ጊዜ መሐላውን እስኪፈጽም ድረስ የናረውን ዓይነት ኑሮ እኔም እኖራለሁ ። ይሽም መሐላ በተሰናዳ ገበታ ላይ ቀርቦ ላይበላ ፣ ከገዛ ሚስቱ ጋር በግብረ ሥጋ ላይገናኝ ፣ ሌላም ከዚህ የባሰ ነገር እንዳያደርግ የሚወሰነው ስለነበረ ምንም እንኳ ሁሉን በሙሉ ላስታውሰው ባልችል በበኩሌ በመሐላዬ ምክንያት ከዚህ ይበልጥ የሚያሳቅቅ ችግር ቢደርስብኝም ተማርሬ ላልተው በመሐላዬ እጸናለሁ" አለ ።

ይህን መሐላ በሰማ ጊዜ ሳንቾ እንዲህ ሲል አስጠነቀቀ ። ''ጌታዬ ሆይ ፤ ይህ ነገር አላማረኝምና ኋላ አይሆንም በነገሩ ተመላልሰው ያስቡበት ። በደንብኛ ግጥሚያ ላይ የተዋጉት ፈረሰኛ በኃይልዎ ተሸንፎ ከጫማዎ ሥር ወድቆ ሳለ ወደ ወይዘሮ የቶባይዝቱ ዱልቺኒያ ዘንድ እንዲሄዱ የስጡትን ትእዛዝ ተቀብሎ አክብሮ ከሄደ የሚገባውን ተግባር ፈጽሟልና እንደገና አዲስ ወንጀል ሠርቶ ካልተገኘ በቀር ለዚህ ሳሁኑ የራስ ቁር መሰበር ኃላፊ ሆኖ ሌላ ቅጣት መቀበል አይገባውም'' ሲል አስረዳው ።

ዶን ኪሾትም መለሰ ''እዚህ ላይ ደግ ብለሀል ፤ እውነት ህን ነው ፤ ከሰውዬው ጋር የሚገባውን ውል ተነጋግሬን እንደ ጨረስን ገና አሁን ትዝ አለኝ ። ስለዚህ እሱን ለመበቀል ያደረግሁትን መሐላ ሰርዠዋለሁ ። ዳሩ ግን መሐላው እዚያው እንዳለ ሆኖ ይህንን የራስ ቁር የሚመስል ሌላ አዲስ የራስ ቁር ለመ ተካት ካንድ ፈረሰኛ ጋር ተዋግቼ ማርኬ በእጄ እስካገባ ድረስ ያንኑ ያልኩትን ዓይነት ኑሮ እንደምኖር መሐላውን አድ ሼአለሁ ። ንግግሩን በመቀጠል ''ይህንም ስል አጉል ምኞት የተመኘሁ አይምሰልህ ፤ እንዲያውም ምሳሌ አድርጌ የምከተለው ድርጊት አለ ፤ ምክንያቱም ይህን የመሰለ አጋጣሚ 'በምብራኖ' የራስ ቁር ላይ እንደደረሰው ሁሉ ለማንም ሊደርስ ይችላል ። ይህም ''ሳክሪፖንቴ' የሚባለውን ብርቱ እንዲጐዳ አድርጐታል'' አለ ።

ሳንቾም እንዲህ ሲል መለሰለት'' አባክዎን ይህን የማይረባ መሐላዎን ለዲያቢሎስ ይተውለት'' በጨናም ላይ ብርቱ ጉስቁልና የሚያመጣና ሕሊናዎ ጨርሶ ማመዛዘን እንዳይችል የሚያደርግ ጠንቅኛ ሙከራ ስለሆነ ይህን የመሰለ ሥራ እንዲሠሩ በበኩሌ አልመክርዎትም ።

''እስቲ ይበሉ ምናልባት አሁን በቅርቡ እራሱ ላይ የራስ ቁር የደፋ አንድ ሰው አግኝተው የሚጋጠሙ ቢሆን ምን ሊያደርጉት ይችላሉ ? በስንት ችግርና በስንት መከራ ውስጥ ነው ያለነው ከሞቀው ቤታችን ወጥተን መጠለያ በሌለበት ገጠር ውስጥ በደረስንበትና ባገኘንበት ሥፍራ ወድቀን ከነልብሳችን እየተኛ

ንና ሌላም ከዚህ የሚበልጥ ፍዳ ደርሶብን ሰውነታችን በረሀብ ተጐድቶ እንደዚህ ጠውልገን ሳለ ግጥሚያውን ማሸነፍ ያቃተ እንደሆነ መሐላው በገባ እጁ መፍረሱ አይደለምን ? የዚያን ያበደ ሽማግሌ የማንቶሻውን ማርኪዝ መሐላ ማምጣትዎ አውን ላስንበት ሁኔታ ይስማማል ብለው ነውን ? ለመሆኑ እይመለከቱ ምን እስካሁን ድረስ ስንንዝ በመንገዳችን ላይ የተገናኘናቸው ሰዎች ሁሉ አጋሰስ የሚነዱ ጐረደማዎችና ባለጋሪዎች ብቻ አይደሉምን ? እነሱም እንኳንስ በራሳቸው ላይ የራስ ቁር ሊያ ደርጉ ይቅርና በሕይወታቸው ውስጥ ስሙንም ሰምተውት የማ ያውቁ ሰዎች ከመሆናቸው በቀር መሣሪያ የያዙ ሰዎች ሲያልፉ እንዳላጋጠመን አይረዱትምን አለው ? ።

''ተሳሳትህ'' አለው ዶን ኪሾት ''ውቢቷ አንጀሊካን ለመጥለፍ ወደ አላባርካ ከሚሄዱት ሰዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ መሣሪያ የታጠቁ ወረኞች ስለሆኑ በዚህ በመንታው መንገድ ለማለፍ ሲመጡ እነሱን ለማግኘት ሁለት ሰዓት እንኳ አይፈጅ ብንም ።

ሳንቾም መለሰ ''እንግዲያውስ ከኔ ወገን በቃኝ እርስዎ እንዳሉት ይሁን ፤ ጉዳያችን አደጋን ሳያስከትል እንዲፈጸም ባምላክ ቸርነት ላይ ተስፋ እናድርግ ፤ እኔም ብዙ ፈተና የተቀ በልኩበት የደሴቷ መገኛ ጊዜ በቶሎ እንዲደርስልኝ በምኞቴ እጸናለሁ ። ከዚያም በኋላ አምላክ የፈቀደውና ይሁን ያለው ይሆ ናል'' አለው ።

''ውድ ሳንቾ'' አለ ዶን ኪሾት አሳዳመጥኽኝም እንጂ ለዚህ ጉዳይ እንዳች ሃሳብ አይግባህ ብዬ ብዙ ጊዜ ደጋግሜ ነግሬህ ነበር ። ደሴቶች የማይገኙም ቢሆን እንኳ የዴንማርክ ፤ ወይም የሰብራዲላ ግዛቶች አሉልህ ፤ እነሱም የእግሮችህ ጫማዎች ናቸው ። እነዚህ አገሮች በረጋ መሬት ላይ የሚገኙና ሥራቸው የጠበቀ ስለሆነ እነሱን ለመግዛት በመቻልህ ይበልጥ ደስተኛ መሆን ይገባሃል ። ሆኖም ስለዚህ ጉዳይ ጊዜው ሲደርስ በሰፊው የምንነጋገርበት ስለሆነ ላሁኑ ከነዚህ ቦርሳዎችህ ውስጥ የሚበላ ነገር እንዳለ አውጣና ያገኘነውን ከተቃመስን በኋላ ለዛሬ ግደ ሪያና እንዲሁም ያገን የነገርኩህን ዕፀ ፈውስ ለመቀመም የም

ንችልበት የመስፍን ግንብ ለመፈለግ እናዝግም ። በውነቱ ይህ የጀርዬ ቁስል በጣም የሚቆጠቁጠኝ መሆኑን አረጋግጥልሃለሁ ።

ሳንቾም እንዲህ አለ ፤ "እርስዎን ለመሰለ ጀግና ፈረሰኛ የሚገባ የጨዋ ምግብ አይደለም እንጂ ለመኖሩስ አንድ ራስ ሽንኩር ትና ጥቂት ደረቅ ዓይብ ፤ አንድ ቁራሽ ዳቦ ይበቃለሁ" አለው።

ዶን ኪሾትም መለሰ "እየ ጉድ እንዴት ሞኝ ነህ ውድ ሳንቾ ፤ ዙዋሪ ፈረሰኞች ሁሉ ሳይመገቡ አንድ ወር ጾማቸውን መክረምና ቢመገቡም ደግሞ ያገኙትን ሳይመርጡ መብላት ክብራቸው መሆኑን አታውቅምን ? እኔ ያነበብኩትን ያህል እን ተም ብዙ ታሪክ ያነበብህ ሰው ብትሆን ኖሮ ስለዚህ ጉዳይ አንዳች ጥርጣሬ አይገባህም ነበር ። ምንም እንኳ ያነበብኳቸው መጻሕፍት ብዙዎች ቢሆኑ በተለይ ለክብራቸው ሲባል አን ዳንድ ጊዜ በሚዘጋጅላቸው ታላቅ ግብዣ ላይ እየተገኙ ከሚመ ገቡት ምግብ በቀር በአዘቦቱ ቀን ዙዋሪ ፈረሰኞች የሚመገቡትን ምግብ ዓይነቱን የሚያስረዳኝ ታሪክ አላጋጠመኝም ። ቢሆንም የጊዜያቸውን አብዛኛውን ክፍል በሱባዔ እንደሚያሳልፉት የታ ወቀ ነው ። እነሱም እንደኛው ሥጋ የለበሱ ሰዎች በመሆናቸው መቸም እህል ሳይቀምሱና የተፈጥሮ ፍላጐታቸውን ሳይፈጽሙ ለመኖር አይችሉምና በዙዋሪነታቸው የተነሳ ወጥ ቤት ሳያስከ ትሉ የዕድሜያቸውን አብዛኛውን ደንና በረሃ በሆኑ ሥፍራዎች በመ ዘዋወር በሚያሳልፉበት ጊዜ የታወቀው መናኛ ምግባቸው በአሁኑ ሰዓት እንተ እንዳቀረብህልኝ ያለ ተራ ምግብ መሆኑን ማወቅ ይገባሃል ። ስለዚህ ወዳጄ ሳንቾ እኔ ለማልከፋበትና ለማሳፍር በት ነገር እስከዚህ ድረስ መጨነቅ አይገባህም ። ዓለምን ከሕጉ ለማናወጥ ፤ ዙዋሪ ፈረሰኞችንም ከተለመደው ኑሮአቸውና ባሕ ላቸው ለማፈረት አትሞክር ። ማናቸውም ነገር የነበረበትን ጠባይ ሳይለውጥ መቀጠል እንዳለበት እወቅና በአዕምሮህ ቀርፀህ አኑረው " አለው ።

ሳንቾም እንዲህ አለ "ስለሞኝነቴ ይቅርታ ያድርጉልኝ ፤ ባለፈው ጊዜ እንደነገርኩዎ ጽሕፈትና ንባብ የማላውቅ ደደብ መሐይምን መሆኔ እስከ ዛሬ ድረስ ስለፈረሰኞች ያመጋገብ ሕግ የማውቀው አንዳች ነገር አልነበረም ። ነገር ግን አሁን ነገሩ ስለተ

ገለጸልኝ ከእንግዲህ ወዲህ ለርስዎ ፈረሰኛ ለሆኑት የሚስማማ ልዩ ልዩ ዓይነት የደረቅ ፍራፍሬ ፤ ኩቸሮና እርጋፊ እይዛለሁ ። ለኔ ደግ ሞ ፈረሰኛ ላልሆንኩት የሚበጅ ደምና ላባ ሊኖረው የሚችል ሲሳ ይነት ያለው የተሻለ ምግብ በቦርሳዬ ውስጥ አስቀምጣለሁ ፤ አለ ።

ዶን ኪሾትም መለሰ "አይደለም ይህን አድርግ ማለቱ አይ ምሰልህ ፤ ዙዋሪ ፈረሰኞች ከዚህ ከደረቀ ፍራሀና ከቸሮህ በቀር ሌላ ምግብ ከመመገብ ይወሰናሉ አላልኩህም ፤ ነገር ግን የተገ ኘውን መናኛ ምግብ ዓይነተኛው የችግር ቀን ስንቃቸው ሆኖ ከሱም ጋር እኔም እራሴ የማውቀው በየሜዳውና በየጫካው የሚገኘውን ፍሬና ቅጠላቅጠል እየለቀሙ በመመገብ ሕይወታ ቸውን ያንቀሳቅሱታል ማለቴ እንጂ ነው" አለው ።

ሳንቾም እንዲህ ሲል መለሰ ፤ "በአሁኑ ሰዓት ይህን የዱር ቅጠላቅጠል ተበይነት ማወቅማ በጣም ጠቃሚና ጥሩ ነገር ነው ። ምክንያቱም ለወደፊቱ በዚህ አረማመዳችን የቀጠልን እንደሆነ ካንድ ቀን አንድ ቀን ለሚያጋጥመን ችግር አስፈላጊያችን ሆኖ መገኘቱ የማይቀር ይመስለኛል" አለ ።

ይህን ከተባባሉ በኋላ ከቦርሳው ውስጥ አለኝ ያለውን ምግብ አወጣና ሁለቱም በሰላምና በመልካም ጓደኛነት መብላት ጀመሩ ። ጊዜው ሳይጨልምባቸው ማደሪያ ቦታ ለመፈለግ ተጣድፈው ነበርና ያንን የኰሰሰና እርጋፊ ምግባቸውን በችኰላ በልተው ከጨረሱ በኋላ ከብቶቻቸው ላይ ወጥተው ከመጨለሙ በፊት ሰው ወደሚገኝበት መንደር ለመድረስ በቶሎ ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። ዳሩ ግን ጥቂት ተጉዘው የፍየል አርቢዎች ጓጆ ከሚገኝበት ሥፍራ ሲደርሱ ጀምበሯ ስለጠለቀች ወደተመኙት ገደማ ለመ ድረስ የነበራቸው ተስፋ ከጀምበሯ ጋር አብሮ ስለጠለቀ ከዚያው ከሚገኝበት ቀበሌ ለማደር ቁርጥ ኃሳብ አደረጉ ። ይህም ሲሆን ሳንቾ ወደ መንደር ለመድረስ ሳይችል በመቅረቱ በጣም ከፍቶት ነበር ። ጌታው ግን ፍቅር የያዛቸው ፈረሰኞች እንደሚያደርጉት ሁሉ እሱም ይህን የዛሬውን ሌሊት ባልተሸፈነው ሰማይ ሥር ዛፍ ተደግፎ ለማንጋት በመቻሉ ደስ ብሎት ነበር ። ምክንያቱም ይህን የመሰለ ሁኔታ ባጋጠመው ቁጥር ለዙዋሪ ፈረሰኛነቱ ፍቱንነት ምስክር የሚሆን ማስረጃ ለማጠራቀም የሚያስችለው ስለሚመስለው ነው ።

ምዕራፍ 11

በዶን ኪሾትና በፍየል አርቢዎች መካከል የደረሰው ሁኔታ ይተረካል ፤

ፍየል አርቢዎቹ ሁለቱን መንገደኞች በደስታ ተቀብለው በጐጆአቸው እንዲያደሩ ስለጋበዙዋቸው ወዲያውኑ ሳንቾ ሮንዚ ናንቴንና አህያውን አራግፎ የተቻለውን ያህል አጥብቆ ከግ ንድ ላይ ከአሰራቸው በኋላ ፤ በትልቅ ምንቸት ሞልቶ እሳት ላይ ተጥዶ እየተፍለከለከ ሲገነፍል የነበረው የፍየል ሙክት ጮማ ሥጋ መረቁ ስለሸተተው በረሀብና በጉጮጅት እየተሳበ ወደዚ ያው ይሄድ ጀመር ። ምንም እንኳን ከምንቸት ወደከርስ ለመጋ ባት የደረሰ መሆኑ አለመሆኑን ቀርቦ ለማየት በጣም ቢቋምጥ ለጊዜው አላደረገውም ነበር ። ምክንያቱም ልክ በዚያኑ ሰዓት ፍየሎቹ የተጣደውን ምንቸት ከእሳቱ ላይ አውርደው እመሬት ላይ ቁርበት አንጥፈው ማዕዳቸውን በፍጥነት ሰርተው ቅቅሉን ከዘረገፉ በኋላ ፤ ሁለቱ እንግዶቻቸው ቀርበው እንዲጋበዙላቸው ግልጥ በሆነ የለጋሥነት ልብ ስለለመኑዋቸው ነው ።

በዚያን ሰዓት ከጐጆው ውስጥ የነበሩት ስድስቱም ሰዎች ዶን ኪሾትን ካንዲት ባርጩማ ላይ እንዲቀመጥ ግብዝ በሆነ ማቆላመጥ ለምነው አስቀመጡትና እነሱ ደግሞ ዙሩያውን አኩልኩለው በየድብዳባቸው ላይ ተቀመጡ ። ሳንቾ ግን በእጁ የያዘውን ወይን ጠጅ የተሞላ ዋንጫ ለጌታው ለማቀበል ቆሞ ይጠባበቅ ስለነበረ ፤ ጌታው ቀና ብሎ አይቶት እንዲህ አለው ።

''ሳንቾ ሆይ'' ለምን ፈዝዘህ ትቆማለህ ? የዙዋሪ ፈረሰኛነት ተግባር ምን ያህል ደግነት በውስጡ እንዳለ አታውቅምን ? ወይስ ደግሞ ፈረሰኞች ሲባሉ በየትኛውም ሥፍራ በደረሱ ጊዜ የተገ

ናኙዋቸው ሰዎች ሁሉ በአክብሮትና በመልካም ግምት እንደ ሚጨነቁላቸው አታውቅምን ? ስለዚህ አንተም የዚህ ዕድል ተካ ፋይ ስለሆንክ ከነዚህ ከደጉች ባላገሮች መካከል ገብተህ ከኔ ጐን መቀመጥ ይገባሃል ። እኔ የተፈጥሮ ጌታህና አለቃህ ስለሆ ንኩ አንተም ከኔ ጋር አንድ አካልና አምሳል መሆን አለብህ ። ምግብህንም እኔ ከምበላበት ማዕድ ላይ እየቆረስህ እንድትበላ ። መጠጥህንም በኔው ጽዋ እየሞላህ እንድትጠጣ ፈቅጄልሃለሁ ። ዙዋሪ ፈረሰኛነት ማለት ሁሉን ነገር የሚያስተካክል ያው ራሱ ፍቅር ስለሆነ በፍጹም አትስቀቅ'' አለው ።

ሳንቾም እንዲህ አለ ፤ ''ስለ መልካሙ ሃሳብዎ በጣም አመሰ ግንዎታለሁ ። ዳሩ ግን በዐኩሌ ለጌታዬ የማስረዳው አንድ ነገር አለኝ ፤ ይኸውም በራበኝ ሰዓት የደረሰ ምግብ ካገኘሁ እንዲሁ እንደሚያዩኝ ሆኜ ቆሜ ብበላም ተሰግምቶ ይዋጥልኛል ፤ በተረፈ ግን ካንድ ንጉሥ ጐን ተቀምጬ ከመብላት ይልቅ ለብቻዬ ገለል ብዬ ቆሜ መብላት እጅግ አድርጌ እመርጣለሁ ። እንዲያውም እውነቴን ለመናገር ከሆነ የበዛ ልመናና ቁልምጫ ሳይደረግልኝና እኔም ሳልግደረደር ፤ ያበላል ወግና ስርዓት እንድጠብቅ ሳልገደድ ምግቡ ሽንኩርትና ዳቦም ቢሆን እንኳ ባንድ ጥግ ብቻዬን ሆኜ ከለላ ይገፎ ያለታዛቢ እንደልቤ ብበላ ደስ ይለኛል እጠግባለ ሁም ። ከዚህ ሌላ ደግሞ ባንድ አንድ የድግስ ቤት በሚሰናዳው የማዕረግ ገበታ ላይ እንደሚደረገው የግሪክ ዶሮ ጥብስና ሴላም የክቡራን ምጥን ምግብ በያይነቱ ተደርድሮ ተጋባዦቹ በፀጥታ በሚበሉበት ጊዜ በዝግታ ማላመጥ ፤ በለዘብታ መዋጥ ፤ በቀስታ መጠማት ፤ በየደቂቃው አፍን መጥረግ ፤ ቢያስፈልግም አለማን ጠስና አለማሳሳት ፤ ከዚህም በስተቀር ለብቻና ነፃ ሲሆኑ ግድ ረግ የሚቻለውን ጐላ ያለ የእስትንፋስ ድምጽ አለማሰማት ፤ ይህ ሁሉ አጥብቆ ክልክል በሆነበት ሥፍራ ቀርቤ ከምበላ ጠሜን ውዬ ማደርን እመርጣለሁ ። ስለዚህ ለተወዳጁ ጌታዬ ጋሻጃግሬ በመሆኔ ምክንያት ባገኘሁት ዕድል ለዙዋሪ ፈረሰኛ ነት አባልና ቤተሰብ እንድሆን ሊሰጡኝ የፈለጉትን ይህን ታላቅ ክብር ለኔ ሲሉ መልካም ፈቃድዎ ሆኖ በሌላ ይበልጥ በሚመ ቅመኝ ነገር እንዲለውጡልኝ እለምንዎታለሁ ። ይህ የሰውኛ ከበሬታ ምንጊዜም የማልወደውና የማይመጥነኝ ስለሆነ ጌታዬን

ደስ ለማሰኘት ብቻ ከኔ ወገን እንደተቀበልኩት ያህል ይቁጠሩትና ይዝለሉት አለው ።

"ይህም ባይሆን አለ ዶን ኪሾት ፣" በጠባዩ ትዑት የሆነ ሰው ዘወትር የሚመስገን ስለሆነ ፈቃድ ፈጻሚ ሆነህ በተሰጠህ ሥፍራ መቀመጥ አለብህ" አለውና እጁን ጉትቶ አጠገቡ እንዲ ቀመጥ አስገደደው ።

ፍየል አርቢዎቹም ስለ ጋሻ ጃግሬነትና ስለ ዙዋሪ ፈረሰ ኛነት ሕግ አንዳች ነገር የማይገባቸው ባላገሮች ስለሆኑ እነዚህ እንግዶች የሚያወሩት ዘይቤኛ ንግግር ምን እንደሆነ ምሥጢሩ ሊገለጥላቸው አልቻለም ነበርና እየበሉ ዝም ከማለትና አንዳን ድዬም ደግሞ እንግዶቻቸውን እየተመለከቱ አንጀት በሚያርስ አበላልና አራብን በሚከላ አጉራረስ ቡጢ የሚያክል የጉመን ቅቅል እያነሱ ከመዋጥ በቀር ሌላ የሚያደርጉት ነገር አልነበ ረም ።

የቅቅሉ ሥጋ እንዳለቀ ወዲያውኑ እዚያው እቁርበቱ ላይ አንድ ክምር ፍሬ ዘረገፉ ። ባጠገቡም እንደናራ የደረቀ የከብ እኩሌታ አይብ አስቀመጡበት ። ይህ ሁሉ በሚሆንበት ጊዜ ዋንጫው ብቻ አልቦዘነም ነበር ፤ ምክንያቱም እንደ ጉድንድ ውሃ መቅጃ ባልዲ አንዴ ሙሉውን አንዴ ባዶውን እየሆነ ያለማቋረጥ እየተፈራረቀ ለየሰዎቹ ለመዳረስ ይዘዋወር ስለነበረ ነው ። በዚያን ሰዓት ሙሉ ሆነው ከሚታዩት ሁለት እርኮቶች ውስጥ አንደኛው እርኮት በአንድ አፍታ ተጨልጦ ባዶውን ቀረ ። ዶን ኪሾት የተራበ ሆዱን ሞልቶ እንደጠገበ ከደረቁ ፍሬ አንድ እፍኝ ዘግኖ ይዞ ለጥቂት ጊዜ በጥንቃቄ ካስተዋለ በኋላ ቀጥሎ ያለውን ረጅም ሐተታ መናገር ጀመረ ።

"ዕድለኛው ክፍለ ዘመን ሆይ ፤ የታደላችሁት ዓመታት ሆይ ፤ የጥንታዊ ሰዎች የወርቅ ዕድሜ ብለው የሰየሟችሁ በዚህ በዛሬው በብረት ዕድሚያችን ውስጥ የተወደደውን ወርቅን ለማንሳት ፈልገው አይደለም ። በዚያ በዕድለኛው ዘመን ያለአንዳች ድካ ምና ችግር ወርቅ በቀላሉ የሚገኝ ዋጋው ያነሰ ማዕድን ነበ ርና ። በዚያን ዘመን በሚኖሩት ሰዎች ዘንድ "የኔ ፤ ያንተ የሚባሉት ሁለት የመተዛዘኑ ቃላት አይታወቁም ነበር ። በነዚያ የተባረኩ ዘመናት ማናቸውም ነገር የጋራና የዋጅራት ነበር ። ማናቸውም የዱሮ ሰው የዕለት ምግቡን ለማግኘት በሳሩና ጣፋጩ ፍሬ ከተንዠረገገበት ከወፍራሙ የሾላ ዛፍ ሳይ የፈለገ ውን ያህል ፍሬ በነፃነት አውርዶ ከመሬት የረገፈውንም ለቅሞ ከመብላት በቀር ከቶ ሌላ ድካም አልነበረበትም ። ኩለል ያሉት ምንጮችና ወንዞች ፤ በሚያስደንቅ ሲሳይ የሞሉትን ፤ በጥራትና በንጽሕና የነጠሩትን ውሀዎቻቸውን ለተጠማው ፍጥረት በነፃ እየሰጡ ያረኩት ነበር ። ትጉሆችና ታታሪ የሆኑት ንቦች በየዋሻ ቸው ጉራና በየግንዱ ፉካ ውስጥ የጎበረት መንግሥታቸውን አቋቁመው ሌትና ቀን ሳያርፉ እየሠሩ የመልካም ሞያቸውን ፍሬ ጣፋጭን የማር ወለላ ለፈለገው ሰው ይናኙት ነበር ።

ከሰማይ የሚወርደውን ውርጭና ዝናብ ለመከላከል ሲባል በቋሚ ግንዲላ ተዋቅሮ ለሚሠራው የመጠለያ ጉጅ ክዳን ይሆን ዘንድ የጫካው ዛፎችና ሰንበሌጦች ሁሉ ንጽሕና ግልጥ የሆነ ትህትና ለመሥራት ሲሉ ሰፊና ቀላል የሆነውን ቅርፊታቸውን ለማንም ለመስጠት በገዛ ፈቃዳቸው ተራቁተው ይገኙ ነበር ። በዚያን ጊዜ ሁሉም ሰላም ፤ ሁሉም ተወዳጅ ፤ ሁሉም ተፋቃሪ ነበር ። የዚያ የጐባጣው ሞፈር ሹል ማረሻ እንኳ የጥንታዊት እናታችንን እርሀሩኅ ማኅፀን ለመቅደድና ውስጡን ገልብጦ ምስ ጢሯን ፈልፍሎ ለማውጣ አልሆነለትም ነበር ፤ ምድራችን ማን እንዳሰገደዳትና ማን እንዳዘዛት ሳይታወቅ ኃብታምና ፍሬያማ በሆነው አፈሩዋ ውስጥ በየትኛው ሥፍራ የምታበቅለውን ሬድ ኤት በዚያን ዘመን በላይዋ ሰፍረው የሚኖሩትን ልጆቿን መግባ ለማሳደግ ፤ ለማጥገብና ለማጐልመስ በረከቷን ከመስጠት አልነ ፈገችም ነበር ።

በዚያን ዘመን እነዚያ ቦራቂዎችና ግድ የለሾች የሆኑት የዘላን ልጃገረዶች እንደዛሬው መሸሞንሞንና መሸገን ሳያሻ ቸው ፤ ቁንድላቸውን ሳይሸርቡና ፤ ፀጉራቸውን ሳይጐነጉኑ ፤ እንዲሁም ጨዋነት ዘወትር እንዲያበቅለት የሚያዘውን ገላ በጨዋ ደንብ ለመደበቅ ብቻ ከሚያስፈልጋቸው የገመና መሸፈኛ ጨርቅ በቀር ሌላ ቁንጠኛና ቱር ያለ ቀሚስ ሳይለብሱ

ለሐሜታ ሳይሰጉና ሳይገላመጡ ከቋሚ ወደ ቋሚ ካፋፍ ወደ አፋፍ እየዘለሉ በየሜዳው እየተሯሯጡ በደስታ ሲፈነድቁና ሲቦርቁ ይውሉ ነበር ። የሚለብሱትም ልብስ በዛሬው ዘመን እንደሚለበሰው ያለ ይበልጥ የከበረ ከደማስ ከፋይ ጨርቅ ተሰርቶ በዝምዝምና በጥልፍ ያጌጠ ፤ ከጥሩ የሐር ድርና ማግ በውቅ የተሠራ ፤ ስፌት በልዩ ልዩ ዓይነት አቅድና እቅድ ተዘጋጅቶ አስቸጋሪና አስደናቂ በሆነ ጥበብ የተሰፋ ፤ በላዩም አረን ጓያ ቅጠልና አረግግ ጥለት አበባና ፈርጥ የተጠለፈበት ፤ የዛሬዎቹ የቤተ መንግሥት እመቤቶችና ወይዛዝርት ለብሰው የሚታዩትን የመሰለ እጅግ ብርቅና ድንቅ ሆኖ በአዲስ ፈጠራ የተዋጣ ፤ ለተመልካች የሚያስቀናና እጅግ የሚያስጐመጅ ቀሚስና አልባሳት ለብሰው ተሸልመው እንደሚጀነኑት ያለ ዘመናይ ልብስ አልነበረም ።

በዚያን ዘመን የነፍሰን ፍቅራዊ ስሜት ለመግለጥ ፤ በዛሬው ዘመን እንደሚደረገው ሁሉ ፤ ይበልጥ ተሰሚነት እንዲኖረው ለማድረግ፤ በንግግር ዘይቤ መካንና የማሽኮርመምንም ፈሊጥ ማወቅ ሳያሻ ፤ የመንፈስን ዝንባሌና ያስተያየትን ጥልቅ ዓላማ በሚያፈቅሩት ልብ ውስጥ ለመቅረጽ በቀላሉ ይቻል ነበር ። እንዲሁም የተሩቃሪዎቹ መዋደድ ዘወትር እየፈካና እያበበ ፍላጐታቸውን ለማስተሳሰር እንዲችል ቅንነት በተመላ የልብ ንጽህና ይከተኩት ነበር ። በዚያን ጊዜ ክኅደትና ማታለል ክፋትና ተንኮል መመቀኛኘት እንደዛሬው ከእውነትና ከሐቅ ጋር አልተዳቀሉም ነበር ። ፍርድም እንደዛሬው ዘመን በወገን ደጋፊነት ፤ በዘመድ አጋርነት ፤ በጥቅም ፈላጊነት ፤ ሳይታጠርና በአድላዊነት ሳይወረር ፤ መታወክና መሰደድ ሳይደርስበት ፤ ሚዛኑ ሳይዛነፍ ለሁሉም እኩልነትን እያካፈለ በማይወላውለው መንበሩ ላይ ፀንቶ ይኖር ነበር ። በዚያን ጊዜ የሚፈረድበት ሰውና የሚፈረድለት ጉዳይ እጅግም ስለሌለ የፍርድ ሕጋዊነትና የማመዛዘን ችሎታ በዳኞች አስተያየት ውስጥ ገና አልገባም ነበር ። ስለዚህ ቅድም እንደተናገርኩት ልጃገረዶችና ክብራቸው ባልታሰበ ሕውከትና ድፍረት ጉዳት ይደርስብናል ብለው ሳይፈሩና ሳይሰቀጠጡ ብቻቸውን የትም ለመሄድ ይችሉ ነበር ።

ምናልባት ስንኳ በገዛ ፈቃዳቸው ተዳርተው የመደፈር አደጋ ቢወድቅባቸው ስህተቱ የማን እንደሆነ ለማጣራት ሳያስፈልግ ድርጊቱ ተሸፋፍኖ ሊቀር ይችል ነበር ። ዛሬ ግን በዚህ በማስጠሎው ዘመናችን ውስጥ ወደሴት ገዳም ገብተው ቢደበቁና ቢጠበቁ ስንኳ ምንም ቢሆን ተሰውሮ ለማምለጥ አርግጠኛ ሊሆን አይችልም ። ምክንያቱም አንዳንድ ያልሰከነለት ጥጋበኛ ጐረምሳ ባንዳንድ ስርቆሽ በር በኩል ወይም በዘያው በአየሩ ውስጥ ሾልኮ ለመግባት ስለሚችል ተሸሽጉ መኖርንም ከጉዳት የማያስተርል ስደት አድርጐታል ። ስለዚህ በጊዜ ብዛት ሀሴትና ተንኮል እየበዛ ሄዶ ሴቶችና አቅመ ቢሶች እንዳይጠየቁ ለመከላከልና ለደካሞችም ጥበቃ ሲባል የዙዋሪ ፈረሰኛነት አገልግሎት እንዲመሠረት ተደረገ ። የዚህም አገልግሎት መቋቋም ዋናው ዓላማ ስንኩሎችን ለመጠበቅ ፤ የሙት ሚስቶችንና ልጆችን ለማጽናናት ፤ ሌሎችንም እርዳታ የሚፈልጉትን ሁሉ ለመርዳት ስለሆነ ፤ የዚህ አገልግሎት ኃላፊነት የተጫነበት ሰው ሁሉ ይህን ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ ለሚደርስበት አደጋ ግንባሩን ሳያጥፍ አልፎ መጋፈጥ ግዴታው ነው ።

"ስለዚህ እናንት ወንድሞቼ ፍየል አርቢዎች ሆይ ፤ እኔ የዚህ ታላቅ አገልግሎት ባልደረባ ስለሆንኩ በዛሬው ቀን ለኔና ለጋሻ ጃግሬዬ ላደረጋችሁልን መልካም አቀባበል የማያልቅ ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ ። ምንም እንኳ የተፈጥሮ ሕግ እንደ ሚያዝዘው በሕይወት ያሉት ሰዎች ሁሉ ዙዋሪ ፈረሰኞችን መቀበልና ማስተናገድ ግዴታቸው ሲሆን እናንተም ይህንኑ ግዴታ ባታወቁትም ሳትዘነጉና ሳታጓድሉ በቅን ልቦና ተቀብላችሁ ስለካደማችሁኝ እኔም በሚቻለኝ ሁሉ ውለታችሁን ለመመለስ ሕሊናዬ ብድረኛ ያደርገኛል" ሲል ንግግሩን አቆመ ።

ይህን ረጅም ንግግር (በውነቱ ሊያሳጥረው ይችል ነበር) ፈረሰኞችን የተረተረበት ምክንያት እነዚያ የዘገናቸው ደረቅ ፍሬዎች የወርቁን ዘመን ስላስታወሱት ብቻ ነበር ። ይህን ከንቱ ሐተታ ለፍየል አርቢዎች ለማሰማት ሲል መዘላበድ ቢያሰኘውም ከነርሱ በኩል አንዳች ቃል ሳይመልሱለት ንግግሩን በመገረም ፈዝዘው ከማዳመጥ በስተቀር ሰልችተው አላቋረጡትም

ነበር ። ሳንቾም ፍሬዎችን እየጠረጠረ አንዳንዱም እንዲቀዘቅዝ ከዛፍ ጥላ ሥር የተደገፈውን ሁለተኛውን እርኩት የወይን ጠጅ እያነሳ ይጐበኘው ነበር ። ሁሉም እራታቸውን በልተው ከጨረሱበት ጊዜ ይልቅ ብዙ ጊዜ የፈጀው የዶን ኪሾት ንግግር ስለነበረ ይህ እንዳለቀ ወዲያውኑ አንደኛው ፍየል አርቢ አነሳና እንዲህ ሲል ሀሳቡን ገለጸላቸው ።

"የተከበሩት ፈረሰኛ ሆይ ፤ በሙሉ ልባችንና በወዳጅነት መንፈስ ተቀብለን ያስተናገድነው ለመሆናችን ይበልጥ እርግጠኛ ሆነው ሊያመሰግኑን እንዲችሉ አሁን በቅርብ እዚህ የሚመጣውን ጓደኛችንን እንዲዘፍን ለምንን እንዲያሜውትም እናደርጋለን ። ይህም ጓደኛችን ብርቱ ፍቅር ያደረበትና በጣምም ብልህ የሆነ ወጣት ነው ። ማንበብና መጻፍም ያውቃል ። እንዲሁም ከሚገመተው ይበልጥ ከራር መሎታት ይችላል" አለ ።

ፍየል አርቢው ይህን ተናግሮ እንደጨረሰ ወዲያውኑ ከወደ ውጭ የክራር ድምጽ ኮሰማ ምንም ያህል ሳይቆይ ደግሞ ከራር መቺው በግምት ሀያ ሁለት ዓመት ዕድሜ ያለው ተክለ መልካም ወጣት ብቅ ሲል ታየ ። አጠገባቸውም እንደደረሰ ጓደኞቹ እራቱን በልቶ እንደሆነ ጠየቁት ። እሱም እምን በልቼአለሁ ስላአላቸው ያ ቅድም አዘፍነዋለሁ ሲል ለዶን ኪሾት ቃል የገባው ሰውዬ ጓደኛውን እንዲህ ሲል ለመነው ።

"ውድ አንቶኒዮ ሆይ ፤ እንግዲህ እንደወትሮህ አንድ ጥሩ ዜማ ከክራርህ ጋር አሳልተህ ልትዘፍንልን ትፈቅድ የለምን ? ይህ የተከበረ ጌታ እንግዳችን በተራራና በሜካም ውስጥ የሙዚቃን ቃና የሚያውቁ ሰዎች መኖራቸውን ቢያውቅልን ደስታችን ሰለ ሆነ የቱን ያህል አዋቂ መሆንክን ቅድም ነግረነው መጥተህ እስኪያይህ ድረስ ችኩሎ ነበርና ይህ ቃላችን እውነት መሆኑን ለመመስከር ከራርህን አየመታህ ዘፈንህን እንድትአሰማን አለ ምንሃለሁ ። እባክህን ተቀመጥና በተለይ በዚህ በአገራችን ውስጥ የሰሙትን ሰዎች ሁሉ እጅግ አድርጐ ያስደነቃቸውን አጉትህ ቁሉ ያወጡልህን የፍቅርህን ታሪክ የሚያስረዳውን ግጥም በዘፈን አሰማን" አለው ።

ወጣቱም እንዲህ ሲል መለሰ ፤ "እሺ መልካም ፈቃዱ ነው" ካለ በኋላ ከዚህ ይበልጥ ተለማመጡኝ ሳይል ካንዲት የጎራር ጉቶ ላይ እግሩን አጣምሮ ተቀመጠና ከራሩን መቃኘት ጀመረ ። ስልቱን በማዋሀድ ጥቂት ከቆየ በኋላ ባማረ መልካም ድምጽ የሚቀጥለውን ግጥም ማሰማት ጀመረ ።

የወጣቱ ፍየል አርቢ የፍቅር ግጥም

"ምንም ባትነግሪኝ ምስጢሮሽን ገልጠሽ
የልብ ዲዳ ቋንቋ በሆነው ባይንሽ
ልብሽ ማዘንበሉን አወቅሁት በርግጥ
ታድያለሁና ወትሮ አንቺን ስመርጥ ።
የተረዱት ፍቅር ከፍቶ አይከፋምና
የኛ መነፋፈቅ አምሮ ከተቃና
እምነቴ ብርቱ ነው ፍቅርሽ እንዲጠና ።

ባማረው መልክሽ ላይ ስሜትሽን አንብቤ
ዕድልሽ ከዕድሌ ልብሽም ከልቤ
ተቆራኝቶ አንድነት አብሮ የሚኖር
መሆኑን አውቂ ላንቺ ሳማክር
ሀሳቤ እንደገባሽ ላውቀው ስለቻልኩኝ
ምስጢር ላካፍልሽ ምስጢረኛሽ ሆንኩኝ ።
ዕውነት ነው ዘወትር በመደጋገም
እንዲገባኝ አርገሽ ስትነግሪኝ ግጥም
ነፍስሽ ብረት ሆኖ ልብሽም ድንጋይ
ፍቅር ለማያጠብቅ እጉል ወላዋይ
መፍትሔ የሌለው መርዝ የምታበይ
ወይም በጭካኔሽ ቀስፈሽ የምትገይ
መሆንሽን አወቅሁት አፍዛዥ አታላይ ።
ይህንን ዘንግቼ ባነኝ ፈተና
ይቅርታ ብጠይቅ ባቀርብም ልመና
ጨክነሽ በእምቢታ ባሳየሽኝ ኩራት
በግሳጼሽና በጥላቻሽ ምሬት
ጨቁነሽ ብትይገርኝ ረግጠሽ ከመሬት

የወጣቱ ፍየል አርቢ የፍቅር ግጥም ይቀጥላል ፤

"እንተቼን ደፍቼ አቀርቅሬ ሳለሁ
በተስፋዬ ጥናት የቀሚስሽን ዘርፍ አየሁ ።
በጥላቻሽ ምክንያት ያልቀረጠው ልቤ
ወይም በማፍቀርሽ ያልሞላው ሀሳቤ
ቀንም ሆነ ሌሊት ጭንቁን ሳያሻሽል
በተስፋ ፍቅርሽን ሲመገብ ያመሻል ፤
እንግዲህ ጉዳቴን ማወቅ ይገባሻል ።
አንቺ እንደገለጥሽው አይተሽ በጥሞና
የፍቅር ጠባዩ ቢሆን ትህትና
አንቺን የሚያስደስት እኔን የሚያጽናና
ለጉዳቱ ካሣ ሊሆን የሚገባው
መስሎም የሚታየኝ ባሳቤም የገባው
ይቅርታን ለማግኘት ባለኝ ፍላጐቴ
የኔን ትሕትና ላንቺ በመስጠቴ
ከኔ እንዳልጐደለ ፍጹም ነው እምነቴ
መልካም አገልግሎት ልብን ማግራት ቢችል
የሠራሁት ሁሉ ደክሜ ላንቺ ስል
ምክንያቶቼን ሁሉ በዕውነት ለማስከበር
ምስክርነቱ በቂ ይሆነኝ ነበር ።
ካንድ ጊዜ ይበልጥ ልብ አርገሽ አይተሽኝ
እንደሆን ምናልባት ሳልፍም አማኝተሽኝ
የሰንበቱን ልብሴን ለብሼ በሠርክ
ቱር ብዬ ነበር አንቺን ልማርክ ።
ፍቅርና ቱርታ መንገዳቸው እንድ
መሆኑን አውቄ ወደ አንቺ ስሔድ
ዘወትር በፊትሽ ጸድቼ እንድታይ
እጣጣር ነበረ ምንም ብደሽይ ።
ምን ጊዜም ላንቺ ስል ያደረግሁትን ቅብጠት
ልነግርሽ አልፈቅድም እንዳይሆንሽ ፀፀት ።

የወጣቱ ፍየል አርቢ የፍቅር ግጥም ይቀጥላል ፤)

"የዚያን ሌሊት ዘፈን የዜማውን ቃና
አላስታውስሽም ይቅር ይረሳና

እንዲያው ለነገሩ ሳነሳው በተለይ
በመጀመሪያው ወቅት በዶሮ ጩኸት ላይ
ሕሊናሽ ሲሸበር መንፈስሽ ሲሰቃይ
በዜማ ያጽናናሁሽ እኔ አልነበርኩም ወይ ።
ለውበትሽና ለቁንጅናሽ ዜና
የተቀኘሁትን የግጥም ምስጋና
ከኖ አላነሳውም እንግዲህ ዳግመኛ
ምንም እውነት ቢሆን የግጥሙ አማርኛ
ከወሰን አለፈ በጣም ተቀናጣ
በልክ አልሆን አለ መውደዱ ቅጥ አጣ
ለሁሉም መላ አለው የሚያዋጣ ብልሀት
ሲሆን የተሳካ ሳይሆንም በመርሳት
ፍቅር አዲስ ሆኖ በሱ አልተጀመረ
ምነዋ አራጀው እስከዚህ ሠከረ
ካልሆነ በስተቀር ፍቅራቸው የጋራ
ድካሙ ከንቱ ነው ጭንቁም አያባራ
ይህን በመስለ አግብኦና ስሞታ
ስሜን እያነሱ ፍየል ሲያልቡ ማታ
ያላግጡብኛል ብዙ ወጣት ሴቶች
አበዛው እያሉ ምነው የማይሰለች ።
አንድ ቀን እንግዲህ ሳሞግስ አንቺን
ቱሬዛ ቤሮካል እይታኝ ብቻዬን
እንዲህ ብላ አሰችኝ በእውነት አስተካክላ
የሴትን ጭካኔ ክፋት አስተውላ፤
"እናንት ወጣት ወንዶች ፍቅር ሲይዛችሁ
"መልእክ መስላ በአካል የምትታያችሁ
"እታላይ ከሐዲ ሴት ጦጣ መሆኗን
አለማወቃችሁ የብልጠት ጠባይዋን

የወጣቱ ፍየል አርቢ የፍቅር ግጥም ይቀጥላል ፤

"ታላዝናላችሁ ስትሆኑ የዋኃን ።
"ፍቅር የሩቅ እሳት የተሳለ ሠይፍ
"የራቀውን ሲምር የቅርቡን ሲጠልፍ

"ተፈርቶ ይኖራል በጠባዩ ታውቆ
"ማንም አይደፍረውም እንደዋዛ ንቆ
"ካልያዘው በስተቀር በጣም ተጠንቅቆ
"ሰውሶ ይጥላል ከመሬት ደባልቆ

"ነገር ግን እናንተ በተለይ ወንዶቹ
"እየመሰላችሁ የማይጐዳ ምቹ
"በመዳራት ብዛት ትጠጉና በውል
"በትኩስ መፋቀር ስሜታችሁ ሲግል
"በሴት ሳቅና ቀልድ ልባችሁ ሲደለል
"ፍጻሜው ለቅሶ ነው የኋለኛው ዕድል ።

"የሴት መግዛነት የመሳብ ችሎታ
"ንፅይል እየጨመረ አቅሙ እንዲበረታ
"አለው ብዙ ምስጢር የቅመም ጠብታ
"ለማይነቃ ድልል ቶሎ የማይፈታ

"በጌጦቿ ብዛት በአልማዟ በወርቋ
"በለበጣ ወጉሯ በፈገግታ ሳቋ
"በሚጠቅሰው ዓይኗ በሽቶዋ ማዓዛ
"ባንጋገር ቅቤ በከንፈሯ ለዛ
"በሀሰት ውበቷ ከተሸነፋችሁ
"በዋዛ ሽንገላ ከተማረካችሁ
"አይጠረጠርም ወጥመዷ መግባታችሁ

"በመኳኳል ብዛት በጌጥ በመሸለም
"ፊትን በመወልወል በቅባት በቀለም
"እንደመስክ አበባ ፈክቶ እንዲለመልም
"በቀን እንዲያሳሳ በሌት እንዲታለም
"ልብን እንዲማርክ መንፈስን እንዲስብ
"ሆን ብሎ ታስቦ በረቀቀ ጥበብ

<u>የወጣቱ ፍየል አርቢ የፍቅር ግጥም ይቀጥላል</u>

"የተሰራው ውበት እንኳን ሰዎችን
"ሊያፈዘው ይችላል እራሱን ፍቅርን
ብላ ብትመክረኝ የልቧን እውጥታ
እኔም መለስኩላት ወዲያው በቀጥታ

ውሸታም ነሽ አልኳት በሰው ፍቅር ገብታ
መሠረት የሌለው ምክር በመስጠታ ።
እሷም በዚህ መልሴ በጣም ተቆጥታ
ተቀይማኝ ሔደች ከኔ ተለይታ ።
ለሰጠችኝ ምክር ቆጥራ እንደወዳጅ
ምስጋና እንደማቅረብ እንደመንሳት እጅ
ባጉል አነጋገር ጠልቆ በሚፋጅ
መልሱን ከስድብ ጋር መስጠቴም ባይበጅ
ይህንኑ ስሞታ ለወንድሟ ልጅ
ሔዳ ነግራው ኖሮ አግኝታው ከደጅ
አጋር ሆኖ ለሷ መጥቶ ቢዝትብኝ
ጠብ ፈላጊነቱን መቅጣት ግድ ሆነብኝ

ባንቺ የተነሳ ከአብሮ አደጌ ጋር
ጨክኜ ስጣላው ይሉኝታ ሳልፈራ
መንደር እስቲሸበር ወገን እስቲራዳ
ገላጋይ ሰልችቶት ብዙ ሰው ሲጐዳ
ምን እንዳደረገኝ ምን እንዳደረግሁት
መቸም አይተሸዋል ጉድ እንደሠራሁት

እኔ አንችን ማፍቀሬ ወረት አይምሰልሽ
ሆን ብዬ ፈልጌ የማሽኮረምምሽ
አጥምደሽ ሳበቃ በረቀቀ ሥንኰል
የሚያሳዝንሽን እምነቴን በማጉደል
ልሠራሽ አይደለም ሰው ያልሠራው በደል
እመኚኝ ከልብሽ እንደሌለኝ በቀል
አንቺንና እኔን የሚያራርቅ ገደል
በፍቅር ተከቦ ጸንቶ እንዲደለደል

<u>የወጣቱ ፍየል አርቢ የፍቅር ግጥም ይቀጥላል ፤</u>

"በዕውነት ይገባኛል ስሜቴን መቀበል ።
አንቺ ስግተሽበት የጠረጠርሽውን
ይክደኛል ብለሽ የምታወሪውን
ከቶ አልመኘውም ይህንን ለማድረግ
ስሜቴ ንጹህ ነው ፍጹም የሆነ ደግ ።

የፍቅር ማሠሪያ የቃል ኪዳን ጽላት
ውሉ የማይፈታ እስካሉ በሕይወት
ቅድስት ቤተክርስቲያን አንድ ገመድ አላት
ከሐር ፈትል ከርሮ የተገመደላት
በዚህ ሽምቅቆ ውስጥ አንገትሽን ካገባሽ
እኔም የኔን አንገት ሳገባው ታያለሽ ።

የዚህም ምሳሌ ሲገለጥ በይፋ
ቅዱስ ጋብቻ ነው የደስታ ተስፋ ።
ይህ ካልሆነ በቀር መሃላዬ ይድረስ
ይበልጥ ለከበረው ለጻድቁ ቅዱስ
ጋብቻ ለማግኘት ካልቻለ የኔ እጣ
ሰምንኩስና እንጂ ላላማዊ ጣጣ
ከዚህ ተራራ ውስጥ ከእንግዲህ ላልወጣ ።

እዚህ ላይ ሲደርስ ፍየል አርቢው ዘፈኑንና ግጥሙን አሰ ምቶ ጨረሰ ። ዶን ኪሾትም ወጣቱ ሌላ ግጥም እንዳለው ጨምሮ እንዲያሰማቸው በሁሉም ሰም ለምኖት ነበር ። ወጣቱ ግን ለጊ ዜው በቃሉ ያጠናው ይህንኑ ብቻ መሆኑን ገለጠለትና ምናል ባት የተጻፈ ድርሰት እንዳለ እፈልጋለሁ ብሎ ለመነሳት ሲል ሳንቾ በንግግራቸው መካከል ጣልጋ ገባ ።

መቸም ሳንቾ ፖንቻ ዘፈን ከመስማት ይልቅ በጸጥታ መተ ኛትን እጅግ የሚመርጥ ሰው በመሆኑ የፍየል አርቢውን ግጥም ከቁምነገር አልቆጠረውም ነበርና እንዲህ ሲል ጌታውን መከረ ።

"እንግዲህ ጌታዬ ለዛሬ ሌሊት የሚተኙበትን ሥፍራ ካሁኑ መፈለግ አለብዎት ። እነዚህ ትሑታን ሰዎች ስለእንግድ ነታችን ያደረጉልን አቀባበል ከአቅማቸው ጋር ሲተያይ እጅግ የበዛ መሆኑን የሚገልጥልን ነው ። እነሱም ቀኑን በሙሉ በጣም በሚያደክም የእርኖነት ሥራ ላይ ሲራወጡ የሚውሉ ስለሆኑ አሁን ደግሞ በእረፍታቸው ጊዜ ለኛ ምችትና መንቀባረር ሲሉ ሌሊቱን በሙሉ እንደ ሠርገኛ ሲዘፍኑ ለማንጋት የሚችሉ አይ መስለኝምና እንደኔ ቢሆን ባያስቸግሩአቸው የተሻለ ነው ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል መለሰለት ፤ "ይገባኛል ሳንቾ አውቄብሃለሁ ፤ ቅድም ያለ መጽረጥ ስታደርገው የነበረው የኪር ኮት ጉብኝትህ ሙዚቃና ዘፈን ከመስማት ይልቅ ተኝቶ የማ ንኩራፋት ፍላጐት በላይህ ላይ እንደጫነብህ ይሰማኛል" አለው ።

ሳንቾም መለሰ ፤ "አምላክ ይክበር ይመስገን ፤ በሰዓቱ መተ ኛትን ማን ይጠላዋል ፤ እንደኔ ግምት የማይግደረደር ሁሉ በተ ፈጥሮው እረፍትንና እንቅልፍን እንደሚወድ አምናለሁ ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል አረጋገለጠት ፤ "ይህንንስ እኔም አሴ አልልህምና ላንተው እንዳሰኘህ ለጐንህ ተመቻችና እንቅልፍ ህን ለጥ ። እኔ ግን የኔን የመሰለ ተግባር ያላቸው ሰዎች ሁሉ አብዛኛውን ጊዜ ከመተኛት ይልቅ ነቅተው መገኘት ለታላቅ ክብር የሚያደርሳቸው ነገር ስለሆነ አንተን መስዬና ምክርህን ተከትዬ መተኛት አይገባኝም ። የሆነው ሆኖ ሳንቾ ሆይ ከመተ ኛትህ በፊት አስቀድመህ ይህን የጀርዬን ቁስል ብታከመኝ እወዳለሁ ። ምክንያቱም ከማልፈልገው ይበልጥ እየቆጠቆጠ ጤና ነስቶኛል" አለው ።

ሳንቾም እሺ ብሎ ትዕዛዙን ተቀበለና የማከሚያ ቅባትና ሻሽ ለማምጣት ተነሳ ። ዳሩ ግን ከፍዬል አርቢዎቹ አንዱ ወደ ዶን ኪሾት ተጠግቶ የጀርውን ቁስል ተመለከተና እንዲህ አለው "አይዘት አይስጉ እኔ የማውቀው አንድ ፍቱን የሆነ መድኃኒት ስለአለኝ በሱ አክሜ ብቶሎ እንዲድኑ አደርጋለሁ" ካለ በኋላ ወደ ውጭ ወጣ ብሎ በዚያ በአቅራቢያው መስክ ላይ በብዛት ከሚገኙት የቆላ ቅጠሎች በየዓይነቱ ቆረጠና እንክ ከጨው ጋር ሰውሶ ከቁስሉ ላይ ደመደመለት ። ቀጥሎም ከእን ግዲህ ወዲያ ሌላ ሕክምናና መድኃኒት ማድረግ ይህኛውን የሚያረክሰው መሆኑን አስጠንቅቆ የሱን መድኃኒት ፍቱንነት አረጋገጠለት ።

ምዕራፍ 12

አንደኛው ፍየል አርቢ ከዶን ኪሾት ጋር ለነበሩት ጓደኞቹ ያስማቸው ወሬ ይተረካል ።

የቤት ጉዳይ ለመገብየት ከገጠር ወደ ከተማ ሄዶ የነበረ አንድ ጉልማሳ በዚያን ለዓት መጣና ፍየል አርቢዎቹን እንዲህ አላቸው ።

"ጉበዝ ዛሬ በቀበሌያችን የደረሰውን ሁኔታ ሰምታችኋልን ?" ከመካከላቸው አንደኛው እንዲህ ሲል መለሰለት' "እን ደምታውቀው እኛ ሰሞኑን ወደ ከተማ አልመጣንም እንደምን አድርገን ለመስማት እንችላለን"

ጉልማሳውም "ዛሬ ጠዋት" ሲል ማሰረዳት ጀመረ ፤ አንደ ምታውቁት ሁሉ ያስሙ በአገር የተጠራው ጂሮኦሰቶሞስ የሚ ባለው ወጣት ከተማሪነት ወዶ እረኛነት ተለውጦ ስለነበረ ሰዎች እንደሚንሾካሾኩት ያቺን ማርቼላ የተባለችውን በዚህ በአካባቢ ያችን የእረኛ ልብስ እየለበሰች ስትሄድ የምትታየውን የሐብታ ሙን የኮሲየልሞን ልጅ ወዶ በሷው ፍቅር የተነሳ ዛሬ ጧት በገዛ እጁ ታንቆ ሞተ እየተባለ ይወራል" አለ ።

"ለማርቼላ ሲል ሞተ" አለ አንደኛው ። "እምን ለሷው ሲል ነው የሞተው" በማለት ፍየል አርቢው ንግግሩን ቀጠለ ። "በእስዋው ፍቅር ምክንያት ከመሞቱም ይልቅ የአገሩን ሕዝብ ሁሉ በጣም ያስገረመው ድርጊት በጻፈው የኑዛዜ ወረቀት ላይ የሱሬር ወንዝ ከሚመነጭበት ከጽጥኙ ጥግ በሚገኘው ሞንጫ ሥፍራ ላይ እንደ አንድ እንሰሳ በድን እንዲቀብሩት መፍቀዱ ነው ። እንደሚወራው ለመጀመሪያ ጊዜ ማርቼላን ያያትና ያፈ

ቀራት ልክ እዚሁ ሥፍራ ላይ ነው ይባላል ። ከዚህም በቀር ልላ ብዙ የኑዛዜ ቃል በርዝር ጽፏል አሉ ። የመንደሩ ቄሶች ግን ሟቹ የተናዘዘውን ቃል መፈጸም የማይገባ ነው መንፈሱ ሁሉ የሳረመኔነት ስሜት ያለው ስለሆነ እሱ በብስጭት ምክንያት ተስፋ ቆርጦ ይሆን የመሰለ አጉል ኑዛዜ ቢናዘዝም እኛ ይውን ብለን ግጽደቅ አይገባንም በማለት የኑዛዜውን ባለአደራ ተታ ውመውታል ። ዳሩ ግን ያ ከሱ ጋር የእረኛ ልብስ ለብሶ ይሄድ የነበረው አምብሮጂዎ የሚባለው የነፍስ ባልንጀራው በጣም ይወደው ነበርና ሟቹ ወዳጁ የተናዘዘውን ቃል እንዲት ነጥ እንኳን ሳያጓድል እሱ እንዳዘዘው አድርጐ በትክክል ለመፈጸም የቆረጠ መሆኑን ስላስታወቀ በዚህ የተነሣ የመንደሩ ሰዎች ሁሉ ጉድ ነው እያሉ በነገሩ ታምሰዋል ።

"ይሁን እንጂ የመጨረሻው ውሳኔ እንደታወቀው የተ ብሩ ሥነ ሥርዓት አምሮጂዩና ሴሎችም እረኞች ጓደኞች እንደ ተሰማ መበት ሆኖ ይፈጸማል ስለተባለ ነገ በዚያው በተባለው ሥፍራ በታላቅ ክብር ሊቀብሩት አስከሬኑን ይዘው ይመጣሉ ማለትን ሰምቻለሁ ። እኔ እንደማምነው ይህ ነገር በውነቱ መታ የት የሚገባው አስደናቂ ነገር ስለሆነ ምናልባት ነገ ጠዋት ወደ ከተማ የሚያስኬደኝ ምክንያት ያላጋጠመኝ እንደሆነ ለዚው ስል ሥራዬን ፈትቼ ሄጀ ይህንን ድርጊት ለማየት እፈቅዳለሁ" አለ ።

ፍየል አርቢዎችም እንዲህ ሲሉ አውካኩ "ማን ይቀራል ብለህ ታስባለህ ፤ ሁላችንም ሄደን ለማየት የምንፈቅድ ስለሆነ ከመካከላችን አንድ ሰው እዚህ ቀርቶ ፍየሎችን እንዲአግድ 'እጣ እንጣጣል' አሉ ። አንደኛው አነሳና እንዲህ አላቸው "ጴጥሮስ ደግ ብለህ ነበር ፤ ዳሩ ግን እጣ በመጣጣል ጊዜ ከምት አባክኑና ከምትቸገሩ እናንተ ሄዳችሁ እዩ ፤ እኔ ግን በገዛ ፈቃዴ ቀርቼ ፍየሎቹን አግዳለሁ ፤ ይህንንም ማለቴ ለናንተ ምቾት ስል ወይም ለመፈው ሳልጓጓ ቀርቼ ሳይሆን ፤ በቀደም ዕለት ፍየሎቹን ከጉብታው ላይ ቁልቁል እየነዳሁ ስሮጥ ጫማዬን መሐል ለመሐል በሱቶ የወጣው ጋሬጣ ክፉኛ ስላቆሰለኝ አንደኛው አግሬ እያነከሰ በጭራሽ አሳስኬድህ ስላለኝ ነው" አላቸው ።

ጴጥሮስም እንዲህ ሲል መለሰ ፤ "የሚያስቀርህ ምክንያት ይህ የንጉርኽን ቢሆንም ቅሉ መቅረትህን ለኛው ምችት ስትል እንዳደረግኽው ያህል ቆጥረን እናመሰግንሃለን" አለው ።

ዶን ኪሾት ወደነሱ ተጠጋና ሚቹና እረኛይቱ ማን እንደ ነበሩ እንዲነግሩት በተለይ ጴጥሮስን ጠየቀው ። ጴጥሮስም እን ዲህ ሲል መለሰለት ፤ "እኔ የማውቀው ይህ ማቹ ጉልማሳ እዚያ ማዶ በሚታዩት ኩረብታዎች አቅራቢያ ባለው መንደር የሚኖር ያንድ ጨዋ ከበርቴ ልጅ መሆኑንና ልጁም ብዙ ጊዜ በስላማንካ ከፍተኛ ትምህርት ቤት ሲማር ቆይቶ አዋቂና ብልህ የሚያሰኝ የማዕረግ ስም ይዞ ወደአገሩ መመለሱን ብቻ ነው ። እንደሰማሁት የከዋክብትን ቆጠራና እንዲሁም እዚያ ሰማይ ላይ ፀሐይና ጨረቃ የሚሠሩትን ምስጢር ጠንቅቆ ያውቃል ይላሉ ። እኔም በበኩሌ እንደማስታውሰው የፀሐይንና የጨረቃን መሳሳም እያየ ሁኔታቸውን በትክክል ሰማስረዳት መቻሉ ባገሩ ሰዎች እየተ ወራ ሲያንቅለት አሰማለሁ" አለው ።

"ወዳጄ ሆይ" አለ ዶን ኪሾት ፤ "የፀሐይ መጨለም ፤ ሲሉ ሰምተህ ይሆናል እንጂ የፀሐይ መሳሳም አይባልም" አለው ። ጴጥሮስም ይህን ትንሽ እርማት አላስተዋለም ነበርና እንዲህ ሲል ንግግሩን ቀጠለ ፤ "ከዚህም በስተቀር አዝመራ የሚሆንበት ወቅትና የዝናም ጉርፍ የሚቅለጠለጥበትን ጊዜ እየለየ ትንቢቶ ይናገራል አሉ ። ዶን ኪሾትም መልሶ "ዶፍ የሚጥለቀለቅበትን ማለትህ ይሆን" አለው ።

ጴጥሮስም መለሰ "መቅለጥለጥ ወይም መጥለቅለቅ ምንም ያህል አይራራቅም ፤ ስለዚህ እኔ የምለው ለአባቱና ለዘመዶቹ ሁሉ ዘንድሮ ገብስ ዝሩ ፤ ለክርሞ ገብስን ትታችሁ ምሥር ዝሩ ፤ በሶስተኛው ዓመት የወይራ ዛፍ ስለሚያፈራ ዘይት በጣም ይብረክታል ፤ በተከታዩ ዓመት ግን አንድም ጠብታ ዝናም አታገኙም እያለ የሚሰጣቸውን ምክር እየተቀበሉ ስለሚሠሩ በሱ ረዳትነት ዛሬ በጣም ሀብታሞች ሆነዋል" አለ ።

"ይህ ዕውቀት" አለ ዶን ኪሾት "አስትሮሎጂ ይባላል ።"

ጴጥሮስም መለሰ እኔ በውነቱ ምን እንደሚባል አላው ቅም ። ዳሩ ግን ወጣቱ ተማሪ ይሆን ሁሉና ሴላም ብዙ ነገር የሚያውቅ መሆኑን አውቃለሁ ። ስለዚህ ከሰላማንካ እንደተመ ለስ እጅግም ወራት ሳያልፈው አንድ ቀን በድንገት የደብተራ ነት ሰናፈሉን አውልቆ ጣለና እንደአገሩ ሰዎች የእረኛ ደበሎውን አጥልቆ ቆመጥ ዱላውን አንምዶ ብቅ አለ ። ከርሱም ጋር የትም ህርት ቤት ጓደኛውና የነፍስ ባልንጀራው የሆነው አምብሮጂዎ የሚባለው ወጣት የእረኛ ልብሱን ለብሶ ተከተለው ። እዚህ ላይ ሳልነግራችሁ የዘለልኩት አንድ ነገር አለ ፤ ይህ ጂሮስቶምስ ከሴላው ዕውቀቱ በላይ የዘፈን ግጥም በመግጠምና የዜማን ስልት በማውጣት በጣም የተመሰገነ ችሎታ ያለው መሆኑን ነው ። ስልደት ሴሊት የሚሆን የውዳሴ መዝሙርና እንዲሁም "የክብር መወድስ እያወጣ የአገሩ ወጣቶችና ልጆች እያጠኑ ይዘምሩ ነበር ። ዜማውንና መወድሱን የሰሙትም ሊቃውንት ሁሉ በጣም ጥሩም ነው እያሉ ያጋንኑለት ነበር" ።

"ምን እንደገፋፋቸውና ምን እንደነካቸው ሳይታወቅ እነ ዚህ ሁለቱ ባልንጀራሞች የተመረቁበትን ማዕረጋቸውን ጥለው ፤ ደንበኛ ልብሳቸውን አውልቀው ፤ የእረኛ ልብስ ለብሰው ፤ መታየ ታቸው የአገሩን ሰዎች በጣም ስለአስገረመ ይህን የመሰለ ድንገ ተኛ መለወጥ እንዲያደርጉ ያስገደዳቸው ምክንያት ከቶ ምን እን ደሆነ ም ስጠሩ አልገባቸው ብሎ ብዙ ጊዜ ተቸግረውበት ኖሩ ። የጂሮስቶምስም አባት በዚያኑ ሰሞን ሞቶ ነበርና ልጁ እንደ ደንቡ ያባቱን የደለበ ሀብት ፤ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ፤ ቁጥሩ በርክት ያለ የትልትና የትንሽ ከብቶች መንጋ ፤ እንዲሁም ብዙ ጥሬ ገንዘብ ጭምር ወርሶ ለዚህ ሁሉ ሀብት ተቀናቃኝና ባላንጣ የሌለው ፍጹም ባለቤት ሆነ ።

እንደእውነቱ ልጁ ለተራ ሰዎች መልካም ጓደኛና ለፍ ጡር አዛኝ ፤ እሩኅሩኅ ፤ ተወዳጅ ጠባይ ያለው ስለሆነ የወረሰው ሀብት እንዲባረክለት የማይመርቀው ሰው አልነበረም ። ከዚህ በቀር ሎጋንቴና ውበቱ የሚያፈዝ ነበር ። እነዚህ ባልንጀራሞች ይህን መለወጥ ያደረጉበት ምክንያት ምስጢሩ ቆይቶ እንደተገ ለጸው ያኛኑ ቅድም ጓደኞችን ስሟን የጠራትን በፍቅሯ ጠንቅ

ለመሞት ያበቃችውን ማርቼላ የምትባለውን እረኛ ወዶ እሷኑ በሚከተልበት ጊዜ በነዚህ ውድማና ደገላ በሆኑት የፍየል መንጋ መሰማሪያ ጥሻዎች ውስጥ እንደልብ ለመዘዋወር እንዲመቸው መሆኑ ሊታወቅ ተችሏል። ይህችም ሴት ማን እንደሆነች ብታውቋት የሚጠቅማችሁ ስለሆነ ታሪኳን ከሥር ጀምሬ ልነግራችሁ እፈቅዳለሁ። ምናልባት፤ እንዲያውም ያለ ምናልባት ወደፊት እንደ በትራርክ በዕድሜ ብታረጁ እንኳ በሕይወታችሁ ውስጥ ይህን የመሰለ አስደናቂ ታሪክ ለመስማት እንደማችችሉ እርግጠኛ ነኝ።

ዶን ኪሾትም ፍየል አርቢው በንግግሩ እየተንተባተበ ቃል ሲዘነጥል ሰምቶ አላስችል ስላለው እንደ ፓትሪያርክ ለማለት ፈልገህ ነውን? አለው።

ፍየል አርቢውም መለሰ "እኛ በትራርክ ማለት ከጀመርን ጊዜው የቆየ ስለሆነ ውድ ጌታዬ በያንዳንዱ ንግግር ላይ ያለፍ ጆታም እያቋረጡ ለማረም ከፈለጉ ታሪኩ ምንጊዜም ሊያልቅ አይችልም ማለት ነው" አለው።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል መለሰ "ወዳጄ ሆይ በማረሚ ይቅርታ አድርግልኝ፤ በበትራርክና በፓትሪያርክ መካከል ልዩ ነት መኖሩን ላስረዳህ ፈልጌ ነው እንጂ ያቋረጥኩህ ለክፋት አይደለም። ከዚህ በቀር ሌላው ንግግርህ ሁሉ ለዛ ያለው ስለሆነ እንከን አላገኘሁበትም። ነገር ግን በትራርኮቹ ከፓትሪያርክ ይበ ልጥ እንደሚያረጁ የታወቀ ነው። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ አላርምህምና በል ታሪክህን ቀጥል" አለው።

"ውድ ጌታዬ ሆይ፤ ምን ነበር ያልኩት" "ስለማርቼላ የሕይወት ታሪክ" ሲል ፍየል አርቢው ማስታወስ ጀመረ። በዚህ በቀበሌአችን ውስጥ በከበርቴነቱ ከጂሮሶስቶምስ አባት የሚበልጥ ጉሊዬልም የሚባል አንድ ሀብታም ገበሬ ነበር። እግዚአብሔር ከዚህ ሁሉ ሀብቱ በላይ አንድ ሴት ልጅ ሰጥቶት ስለነበረ እናቷ ሕፃኗን እንደተገላገለች ወዲያውኑ በመሊደ ምክንያት ሞተችበት። ይህችም እናት በዚህ በአካባቢያችን ካሉት ሴቶች በታማኝነቷና በሐቀኝነቷ ዋክቪ የሌላት ልበ ቅን ሴት ነበረች። ያ እንደ ፀሐይ የሚያምረውና እንደጨረቃ የሚያስደስተው ገጿ አውንም በፊቱ ድቅን እያለ ይታየኛል። ከዚህም በቀር በጣም ታታሪና እሩሀሩህ፤ የድሆች እናት ስለነበረች በዚህ የበጉ አድራጊነት ምግባሯ ፀድቃ በዚህን ስዓት ያለጥርጥር በቀ ጥታ መንግሥተ ሰማያት ገብታ እንደምትገኝ አምናለሁ"።

"እንዲህ ያለችው ትጉህና ባለሞያ ሴት ባፍላ ዕድሜዋ ላይ ሕፃን ልጅ ትታ በመቀጨቷ ለባልዋ የመረረ ሐዘን ስለሆ ነበት በዚሁ ምክንያት እሱም ታመመና ምንም ያህል ሳይቆይ ተከታትሏት ለመሞት ቢቃ ።ማርቼላም ገና ለጋ ሳለች ወላጆቿ ስላለ ቁባት ለዚያ ሁሉ ሀብት ወራሽ ሆና እዚሁ አገራችን ይህና ትዳር ያለው ቁስ አጐቷ ሞግዚት ሆና ያሳድጋት ጀመር። ሕፃኗም የናትዋን መልክ እየያዘች በጣም ውብ እየሆነች ታድግ ጀመር። ምንም እንኳ እናቷ ቆንጆ ብትሆን ልጅቷ በቁንጅና እንደምት በልጣት ይገመት ነበርና እውነትም እያደገች ሄዳ ዕድሜዋ ከ14 ወደ 15 ዓመት መካከል ሲደርስ አፍላ ቁንጅናዋ እንደተባለው አስደናቂ ሆነ። ያያት ሰው ሁሉ ግንም ቢሆን እንደዚህ አቆን ጅቶ ለፈጠራት አምላክ ምስጋናውን ሳያቀርብ አያልፍም ነበር። ብዙዎቹም ሰዎች ልባቸው እስኪጠፋ ድረስ በውበቷ እየተማረኩ ያፈቅሩዋት ጀመር።

"አጐቷ ይህን ሁኔታ በማወቁ በጣም እየጠበቀና ከዓይን እየሰወረ በድብቅ ማስቀመጥ ግዴታ ሆነበት። ይሁን እንጂ የውበቷ ዝና ጥበቃውን ዋሶ ወደውጭ ሰለወጣና በያለበት ስለ ተዳረሰ፤ ለውበቷም ሆነ ለሀብቷ እየጓጉ የአገሩ ባለፀጋዎች ብቻ ሳይሆኑ ከሩቅ አገርም ያሉት ታላላቅ ሰዎችና መኳንንት ለማጫት እየተሽቀዳደሙ አጐቷን ዳርልን እያሉ በጥያቄና በልመና ልጆች ገበሬዎችም ጭምር ብዛታቸው የቱን ያህል እንደነ በረ ብነግራችሁ በውነቱ ትደነቃላችሁ። ከነዚህም ጉልማሶች አንዱ ቅድም እንደተባለው ይህ ያልታደለው ቂቹ ነበር። ስለ ሱም ለሞች እንደሚያወሩት ከማፍቀርም አልፎ ያመልከባት ነበር ይላሉ። ምንም እንኳ ማርቼላ ይህን የመሰለ ያጃቢዎች ቁራኛና ዓይነ ገብነት ሳይለያት ሰድ የሆነ ኑሮ መኖር ብትጀ ምርም ክብሯንና ጨዋነቷን የሚያሳግ አንዳች አጠራጣሪ ግምት

አልተጣለበትም ። ይልቁንም ከብሯንና ጨዋነቷን በመጠበቅ ረገድ የነበራት ንቃትና ጥንቃቄ እጅግ የታፈረ ስለሆነ ዙሪያዋን ከብበው ያሰፍራቻ ከሚያጅቧት ወጣቶች መካከል ፍላጐቷን የሚያስደስትበት ቅንጣት ተስፋና ቀረቤታ ሰጥታኛለች በማለት ሊመካ የቻለና ወደፊትም የሚችል አንድም ሰው አልተገኘም ። መቸም ቢሆን እረኞቹ በማጀብም ሆነ በመከተል በማነጋገርም ሆነ በማሽኮርመም አልተለዩዋትም ነበርና ምንም በትህትናና በቁልምጫ ቢያንከባክቧትም ፣ አንዳንዶቹም ደግሞ ከልባቸው ማፍቀራቸውን ገልጸው ቢጋብቻ በኩል ቢጠይቋት ከቧ ወገን ድንጋይ ወርውሮ እንደመምታት በሚቆጠር መልስ ፊት እየነሳች ታግልላቸው ነበር ። ስለዚህ ይህን በመሰለው የጨመተ መንፈስ የምታደርገው ነገር ሁሉ የፈጠረው ሁኔታ በዚህ በቀበሌያችን ውስጥ የመቅሰፍት በሽታ እንደገባ ያህል የሚያስፈራ ሆኗል ። ምክንያቱም የትህትና ዘይቤዋንና የንግግሯን ጥልቅዊነት ፣ የውበቷን ፀዳል በቅርብ ሆነው ያይዋትንና የሰሟትን ሁሉ ልባቸውን እየማረከ በፍቅሯ ውጥመድ ውስጥ ሲያገባቸው ባንድ በኩል ደግሞ ፊት ነጪነቷና አግላይነቷ ተስፋ በሚያስቆርጥ ብስጭት ላይ እየጣላቸው ስለሚታመሙ ለጤና ማጣታቸውም በሽታና መድኃኒት እሷው ብቻ ስለሆነች ነው ። ስለዚህ ምን እንደሚሏት ምንስ እንደሚያደርጓት ግራ እየገባቸው ጨካኝና ፍቅር የማይገባት አረመኔ ነች እያሉ ጠባዩዋን በሚያከፋ ስያሜ እያጠቋ ሲሯሯ ይሰማሉ ። ከቡርነትዎ ሰጥቷት ቀን እዚህ ቢሰነብቱ ኖሮ እነዚህ ተራራዎችና ሸንተረሮች ያጀቢዎቿን አፍቃሪዎችና የተገፈዎቹን ወጣቶች የመረረ እርግማንና ጩኸት ሲያስተጋቡ ይሰሙ ነበር ። ከዚህ እምብዛም በማይርቅ ሥፍራ ላይ በርከት ያሉ ረጃጅም የዝግባና የጥድ ዛፎች ያሉበት ጫካ ይገኛል ። በነዚህም ዛፎች በለሰለሰው ቅርፊታቸው ላይ የማርቼላ ስም ያልተቀረጸበት ግንድ አይገኝም ። አንዳንድ ጊዜም ስሟ በተቀረጸበት ቅርፊት ከራስጌው በኩል የአክሊል ቅርጽ ይገኝበታል ፤ የዚህም ምሳሌ በአፍቃሪው ስሜት እንደሚተረጐመው ማርቼላ ከአዳም ልጆች ሁሉ በቁንጅናዋ በልጣ የተደነቀች በመሆኗ አክሊል መድፋት ይገባታል ለማለት የፈለገ ይመስላል ።"

"ካንዱ ቦታ አንዱ እረኛ ሲቅበጠበጥ ይገኛል ። አልፍ ሲል ደግሞ ሌላው እረኛ እየተንጐራደደ ሲያፏጭ ይሰማል ። በዚያ በኩል የፍቅር ዘፈን ሲዘፍን ይሰማል ። በዚህ በኩል የብስጭት እንጉርጉሮና የጭንቅ ማቃሰት ያደነቁራል ። አንዳንዱ አፍታሪ ቀኑን በሙሉ በወደቀ ግንድ ላይ ወይም መሬጥ ድንጋይ ላይ ተቀምጦ በንባ የራሱትን ዓይናቹን ሳይከድን አንጥቲን ደፍቶ ባሳብና በትካዜ እንደተዋጠ ያድርና ከዚያው ሥፍራ ሳይነቃነቅ የማለዳ ፀሐይ እንደ ተኩራመቱ ታግኝቶአት ልጓሙ ደግሞ ለጭንቱቱ ፋታና እረፍት ሳይሰጥ በሚያንበጨጭው የዜጋ ፀሐይ እየተንቃቃ ቢጋለው መሬት ላይ በደረቱ ተደፍቶ ልጁ ሳይኖቹ ሰማያት ለቅሶውን ሲያሰማ ይውላል ። ለዚህም ሆነ ለዚያኛው ለነዚህም ሆነ ለነዚያ ውቢቷ ማርቼላ ቂንጠኛ ወሬ ዝባኔ ልቧን የሰጠች እየመሰለች አሸቢዎቿን እያፋጀች ታተራምሳ ሳቸዋለች እንጂ አንዱን ለይታ አላፈቀረችም ነበር ።

እኛም ይህን ቅጥ የለሽ ሁኔታዋን የምናውቀው ሰዎች ሁሉ ይህ የማርቼላ ኩራትና መጀነን እንደምን ሆኖ እንደሚያልቅና ይህን የመሰለውንስ ኃይለኛ ጠባይዋን ለመዳኘት ስጦታ የሚኖረውና ይህን የመሰለውንም የተሟላ ውበት የራሱ አድርጉ ቀልቡን ለማሳረፍ የሚችለው ዕድለኛ ማን እንደሆነ ለማወት በናፍቆት እንጠባበቃለን ። መቸም ይህ የተረክሁላችሁ ሁሉ ንጹሕ እውነት ስለሆነ እንዲሁም ስለ ጂሮሶስቶምስ አሟሟት የተነገረው ሁኔታ ቅድም ጓደኞችን ያጫወተን ወሬ እርግጠኛ እንደሚሆን አምናለሁ ። ስለዚህ የቀብሩ ሥነ ሥርዓት መታየት የሚገባው ነውና ከቡርነትዎም እንዳይቀሩ አጥብቄ እመክርዎ ታለሁ ። ምክንያቱም ጂሮሶስቶምስ ብዙ ዘመድና ወገን ያለው ባለፀጋ ስለሆነ ለለቅሶ የሚሰበሰበው ሰው እጅግ የበዛ እንደ ሚሆን አይጠረጠርም ። የሚቀበርበትም ሥፍራ ርቀቱ ከዚህ እንስቶ ግሩ ቢል ከሁለት መረባ አይበልጥም" አለና ታሪኩን ጨረሰ ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ አለ "በውነቱ በጣም ይገርማል ፤ እኔም ሄጂ ለማየት ፈቃዴ ነው ፤ ሆኖም ይህን የመሰለ ጠቃሚ ወሬ በማሰማት ላደረጉልኝ ደስታ አመሰግንዎታለሁ" አለው ።

ፍየል አርቢውም ፣ ''ምንም አይደል'' ሲል መለሰና ንግግሩን በመቀጠል የግርቼላ አፍቃሪዎች የሆኑት ወጣቶች ሁሉ በመጨረሻው እንዴት እንደሆኑ ላውቀው አልቻልኩም ። ጸሩ ግን ነገ ጥዋት ወደ ለቅሶው ስንሄድ በመንገዳችን ላይ እንዳንድ እረኞች ሳያጋጥሙን አይቀርምና የተረፈውን ወሬ ከነሱ ጠይቀን እንደምንረዳው ተስፋ አለኝ ። እስከዚያው ድረስ ግን ክቡርነትዎ እቤት ገብተው ተሸፋፍነው ቢተኙ መልካም ነው ። ምክንያቱም በተደረገልዎ መድኃኒት ምንም እንኳ የሚያስፈራዎ ነገር ባይኖር እውርጭ ላይ መተኛት የጀርውን ቁስል የሚያብሰው ሊሆን ይችላል'' አለ ።

ሳንቾ ፓንቻ ግን የፍየል አርቢው ወሬ ስለመነቸከበት ከቁም ነገር አላገባውም ነበርና እሱም በበኩሉ ወደ ኢጥሮስ ጐጆ ገብቶ እንዲተኛ ጌታውን ይጐተጉተው ጀመር ። ከዚህ በኋላ ዶን ኪሾት ምክራቸውን ተቀበለና ወደ ጐጆው ገብቶ አስነዋር ተኛ ። ይሁን እንጂ እንቅልፍ አልወሰደውም ነበርና እሱም የተረፈውን ሌሊት እንደግርቼላ አፍቃሪዎች ሆኖ የልቡን እመቤት ወይዘሮ ዱልቺኒያን እያስታወሰ ሲያስባት አደረ ። ሳንቾ ግን በጓደኞቹ በሮንዚናንቴና በአህያው መካከል ገብቶ ከተመቻቸ በኋላ እንደተገፋ አፍቃሪ ሳይሆን በርግጫ እንደለፋ ሰው ሆኖ እንቅልፉን ይለጥጥ ጀመር ።

ምዕራፍ 13

የአረኛይቱ ግርቼላ ታሪክ ፍጻሜና ሌላም የደረሰ ሁኔታ ይተረካል ።

በፀሐይ መውጫ ሰዓትት ላይ የማለዳ ጀንበር ጮራዋን መፈንጠቅ እንደጀመረች ወዲያውኑ ከስድስቱ ፍየል አርቢዎች አምስቱ ከእንቅልፋቸው ነቅተው ዶን ኪሾትን ከቀሰቀሱት በኋላ የጀሮዕስቶሞስን አስደናቂ የቀብር ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም አብረው ሄደው ለማየት ትናንት ባደረጉት ቀጠሮ ዛሬም ሃሳቡን አልለወጠ እንደሆነ ጠየቁት ። ዶን ኪሾትም ከዚህ የተሻለ ነገር ቢፈልግም ሊያገኝ የሚችል አልነበረምና በቱሉ ከመኝታው ተነስቶ '' አዎ በደስታ እከተሳችኋለሁ'' አላቸውና ወዲያውኑ ሳንቾን ጠርቶ ከብቶቹን እንዲጭን አዘዘው። ሳንቾም በተለመደው ቀልጣፋነቱ ሮንዚናንቴንና አህያውን በትጽበት ጭኖ ካቀረበ በኋላ ከብት ያለው በከብቱ ፣ እግረኛ በሚሉ ሁሉም እየተጣደፉ ጉዞአቸውን ጀመሩ ። ገና ግማሽ መረባ እንኳ ሳይርቁ ካንድ ቀጣና መንገድ መንትያ ላይ ጥቋቁር ደበሉ የለበሱና እንዲሁም በእራሳቸው ላይ ያክርማ አንፋሮና የአበባ አክሊል የጠመጠሙ እያንዳንዳቸውም ወፍራም የከተከታ ዱላ የያዙ ስድስት እረኞች መደነሱ ሊመጡ በሩቁ አዩዋቸው ። ከነሱም ለጥቀው ሁለት አጀከሮች ያስከተሉ ለመንገዳቸውም በሚገባ የተሰናዱ — በፈረስ የተቀመጡ ሁለት መኳንንት ለጥቀው ነበር ። በተገናኙም ጊዜ የተለመደውን የትህትና ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ አካሄዳቸው ወዴት እንደሆነ ተጠያየቁ ፤ የሁሉም ዱካ መደታሪክኛው ለቅሶ መሆኑን ስለአወቁት መደዚያ የሚወስደውን መንገድ ይዘው አንድነት ተከታትለው ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። በፈረስ ከተቀመጡት አንደኛው አነሳና ጓደኛውን እንዲህ አሉ ።

''ወንድም ቪባልዶ ሆይ ፤ ይህን አስደናቂ የቀብር ሥነ ሥርዓት ለማየት በጊዜ ሳንደርስ ቀርተን ቢያመልጠን ኖሮ በውነቱ

ሲፀፅተን እንደሚኖር አምናለሁ ። እነዚያ ሰዎች እንዳጫወቱን ለሞቱ ምክንያት የሆነችው የእረኛይቱ ታሪክና የሟቹ ልውጥ ሁኔታ በርግጥ አስደናቂ ነገር ሳይሆን አይቀርም ።''

ቪባልዶም መለሰ ''ይህንስ እኔም አምናለሁ ፤ ድርጊቱን ለማዬት በጣም ከመናፈቄ የተነሳ እቦታው ልመድረስ አንድ ቀን ብቻ ሳይሆን አራት ቀኖች እንኳ ባጠፋ ቅር አይለኝም ነበር'' አለው ።

ዶን ኪሾት አነሳና ስለማርቼላና ስለኧሮሶስቶሞስ ታሪክ ምን ሲባል እንደሰሙ እንዲነግሩት ጠየቃቸው ።

መንገደኛውም ''የዚያኑ ዕለት ጠዋት የዛሬዎቹን የመሰሉ እረኞች አግኝቶ ፤ የሐዘን ልብስ ለብሰው በማየቱ ተሰቅጥጦ ፤ በዚህ አካኋን የለበሱበትን ምክንያት እንዲገልጡለት ጠይቋቸው ስለነበረ ፤ አንደኛው ባለደበሎ የማርቼላን ቅኖ የሌለሽ ባህርይና እንደዚሁም ወዶር የሌለውን የውበቷን ዝና ዘርዝሮ ካሰረዳን በኋላ በዚች ልጅ ፍቅር የተለከፉት እያሌ ጉልማሶች ዱካዋን እየተከታተሉ ሲያጅቧት እንደነበርና በመጨረሻውም አውን የቀ ብሩን ሥነ ሥርዓት ለማየት የሚሄዱበትን የኧሮሶስቶሞስን አሟሟት ታሪክ ነገረን'' ሲል መለሰለት ። ይህም የተጠየቀው መንገደኛ ካነጋገሩ ቀልጣፋነት የተነሳ ቅድም ጴጥሮስ ሲናገር ብዙ ጊዜ የፈጀበትን ታሪክ ባንድ ሰብሳቢ ቃል ለዶን ኪሾት አስረዳው ። የዚህ ንግግር አርእስት አልቆ ሌላ ጨዋታ ከለወጡ በኋላ ያ ቪባልዶ የሚባለው ሰው አነሳና በአማን አገርና በሰላ ማዊ ሕዝብ መካከል በዚህ አካኋን የወር መገሪያ ታጥቆ ለመ ሄድ ያሰጋው ምክንያት ምን እንደሆነ ዶን ኪሾትን ጠየቀው ። ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል መለሰለት ''የተግባሬ ግዴታ ከዚህ በተለየ አካኋን ጀሌ ሆኜ እንድሄድ አይፈቅድልኝም አይገባኝም ። ሽርሽርና እረፍት ፣ መዝናናትና መንደላቀቅ የተፈጠሩት ለአውደል ዳዮችና ለሴት አጀቢዎች ብቻ ነው እንጂ ለዘዋሪ ፈረሰኞች አይደለም ። እንዲያውም የዘወተረ ድካምና ያላቋረጠ ንቃት ፣ መገሪያን መታጠቅና በሹም መጠቀምን ማወቅ ፣ ጥንቱንም የተፈጠረው ለነዚያ መላው ዓለም ዙዋሪ ፈረሰኞች እያለ በግጋ

ነን ለሚጠራቸው አሳረኞች ነው ። ምንም እንኳ በአስተያየት ከሌሎቹ ፈረሰኞች ያነስኩና ገና ከደረጃው ያልደረስኩ ብመስል እኔም የነሱው ባልደረባና የተግባራቸው ተከታይ በመሆኔ ግዴ ታቸውን ማክበር አለብኝ'' አለው ።

መንገደኞቹም ይህን አነጋገሩን ሲሰሙ ሁሉም ስውቱው ጤና የጐደለው እብድ መሆኑን ስለገመቱ ጥርጣሬውን ይበ ልጥ ለማጣራትና ባነጋገሩም ትርጉም ይበልጥ እርግጠኞች ለመሆን ፤ እንዲሁም የእብደቱስ መንፈስ ምን ዓይነት እንደሆነ ለመስለል ሲሉ ቪባልዶ አነሳና ዙዋሪ ፈረሰኛ ማለቱ ምን ማለት ፈልጐ እንደሆነ ጠየቀው ።

ዶን ኪሾትም በመደነቅ እንዲህ ሲል መለሰ ''እንግዲያውስ እርስዎ እስከ ዛሬ ድረስ የንጉሥ አርቱርን የጀግንነት ገድል የተጻፈበትን ስመ ጥርን የእንግሊዝ የታሪክ መዝገብ አላነ በቡም ለማለት እደፍራለሁ ፤ እኛ እንኳ በካስቲሊያዊ ቋንቋችን ''ንጉሥ አርቱ'' እንለዋለን ። እጅግ ጥንታዊነት ያለው በመላዋ ታላቋ ብሪታኒያ የታወቀው የታሪክ ባሕር መዝገብ እንደሚና ገረው ይህ ንጉሥ እስካሁን ድረስ አልሞተም ፤ ዳሩ ግን በምትሐት ኃይል ተሠውሮ ባልታወቀ ሥፍራ ይኖራል ይባላል ። እሱም በቁራ መልክ ተለውጦ በሕይወቱ ስለሚገኝ በጊዜ ብዛት ወደ ስውነቱ ተመልሶ ዘውዱንና ሉሉን ፤ በትረ መንግሥቱን ተተ ብሎ ንግሥናውን ይቀጥላል የሚባል ንግርት ስለአለና ፤ ይህም በብርቱ የታመነ በመሆኑ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የእንግሊዝ ተወላጅ ለሆኑ ሁሉ ቁራ ገደል ተብሎ ሲወራ ኩቱ ተሰምቶ አይታወቅም ። ስመ ጥሩው ''የክብ ጠረጴዛ'' ፈረሰኞች ሕግ የተመሰረተውና ሥርዓተ መሐላው የተፈጸመው በዚህ በጀግ ናው ንጉሥ ዘመነ መንግሥት መሆኑ በመላው ዓለም የታወቀ ነው ። በዚያን ጊዜም ስለነበረው ሁኔታ በትክክል እንደሚተረ ከው የባሕሩ ላንቺ ሎቶ የሚባለው ጉበዝ ከንግሥት ጂኔቬራ ጋር የወጠነውን የፍቅር ሁኔታ ያስታውሳል ። ይህችም ንግሥት ''የቺንታኞና እመቤት'' ተብላ በመጠራት ስሟን አስነስታለች ። በተፈጥሮ ምግባሩዋ የተጣሉትን ሰዎች አስታራቂና ምስጢር ጠባቂ በመሆኗም ከፍ ያለ ግምት ያገኘች ስለሆነች እሷ የመጣ

ችው በአገራችን በእስፔን ውስጥ ዘመትር እየተከለሰ የሚዘፈ
ነው ቀጥሎ ያለው የማይረሳ ግጥም እንዲህ ይላል ።

"ድል ነስቶ ሲመለስ ከእንግሊዝ አገር ፤
ሴቶች በእልልታ ከፍ ባለ ክብር ፤
እየተቀበሉ የሠገዱለት ፤
ወይዛዝርት ሁሉ ያገለገሉት ።
ምን ጊዜም አልነበር በምድር ላይ ከቶ ፤
ጐበዝ ደፋር ጀግና እንዳላንቺሎቶ" ።

ይህንና ሌላም እዚህ ላይ ያልተጻፈውን ግጥም እጅግ በሚያስደ
ስት ዜማ እየዘፈነች ላንቺሎቶን ስለጠንካራው የጀብዱ ምያውና
ስለ ፍቅራዊነቱ ታሞግሰው ነበር ። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ይህ
የፈረስኞች ሕግ እያደር እየተሰፋፋና እየተዘረጋ በብዙ ልዩ ልዩ
የዓለም ክፍሎች ተዳረሰ ። በየአገሩ ከተነሱትም ዘዋሪ ፈረሰኞች
ውስጥ ከዚህ ቀጥሎ ስማቸው የተጠቀሰው ፈረሰኞች መታወስ
ይገባቸዋል ። ጐበዙ የጋውላው አማዲስ ከነልጆቹና እስከነ የልጅ
ልጆቹ እስከ አምስተኛው ትውልድ ድረስ ስመጥሩነቱ እንደ
ተወራረሰ ዘልቋል ። ጀግናው የኢርካኒያው ፊልቺማርቴና ምን
ጊዜም በበቂነት ያልተመሰገነው ቲራንቴ ነጩ ፤ የሁሉም መደ
ምደሚያ የማይሸነፈው ቆፍጣናው የግሪኩ ዶን ቤሊያኒጀስ
የነዚህ የጐበዝ አውራዎች ታሪክ በዘመናችን የተሰማና የታወቀ
ነው ለማለት እንችላለን ። ስለዚህ አሁን ሰርሰም ለወንድሜ ለማስ
ረዳት የምፈቅደው ዙዋሪ ፈረሰኛ ማለት በነዚህ እሳይ በጠቀስ
ኳቸው ጀግኖች ሲከናወን የኖረ ድፍረትንና ቆራጥነትን ፤ መከራ
ቻይነትን የሚጠይቅ ጠንካራ ተግባር መሆኑን ነው ።

ቅድም እንደተናገርኩት ምንም እንኳ እኔ እስከዛሬ ድረስ
እድለቢስነት ባይለየኝና ባይቀናኝም ተግባሬ እንዲሆን መርጬ
የያዝኩት ይህንኑ አሁን የማከናውነውን የፈረሰኛነት ተግባር
ስለሆነ ፤ በዚህ ምክንያት ተገፋፍቼ በነዚህ በረሀዎችና ውድማ
በሆኑት ቀበሌዎች አጋጣሚዬን ለመፈለግ እየተዘዋወርኩ ደካ
ማዎችን ለማገዝና እርዳታም የሚፈልጉትን ለመርዳት ክንዴንና
መሳ ስውነቴን ኃይለኛ ለሆነው አደጋ እያጋፈጥኩ በእድሌ ላይ

እንዲደርስ የታዘዘውን ሳልማረርና ሳልበሳጭ ለመቀበል በቂር
ጠኛ ልብ የተዘጋጀሁ ሁኜ በመገኘቴ ለዚህ ግዴታ መልካም
አፈጻጸም የጦር መሣሪያ መያዝ የሚገባኝ ሆነ ።

በዚህ በዶን ኪሾት ንግግርና አስተያየት ብርሃን መንገደኞቹ
በሙሉ ያላንዳች መጠራጠር እብድነቱን ለማመን ስለቻሉ በመ
ጀመሪያ ጊዜ ተገናኝተው ሁኔታውን የሚመለከቱት ሰዎች
እንደሚሆኑት ሁሉ እነሱም ግራ ገብቷቸው ቆይተው በመጨረ
ሻው የእብደቱን ዓይነት ከተረዱት በኋላ ባነጋገሩና ባኳኋኑ
እጅግ ተደነቁበት ።

ቪባልዶ የሚባለውም ሰው በተፈጥሮው ብልጥና ቀልደኛ
ስለነበረ ወደ መቃብሩ ሥፍራ ለመድረስ ጥቂት ይቀረዋል የተ
ባለውን መንገድ እስኪጨርሱ ድረስ አሜዋች ወሬ አግኝተው
የሚሰማቸውን ድካም ለማቃለል በማሰብ ዶን ኪሾት ያንን
የተዘበራረቀ ታሪኩን ድውር እንዲተረትር በማለት እንዲህ ሲል
ቆስቋሰ አነሳሳው ።

"የተከበሩ ዘዋሪ ፈረሰኛ ሆይ እንደሚመስለኝ ይህ መር
ጠው የያዙት ተግባር ያፈጻጸሙ ሕግ በምድር ገጽ ላይ ከሚገ
ኙት ጥብቅ ሕግጋቶችና ግዳጆች ይበልጥ የጠበቀ ይመስለኛል ።
በበኩሌ እንደማውቀው የቼርቶዚን ገዳም ሕግጋት እንኳ እስከ
ዚህ ድረስ የሚጠብቅ አይመስለኝም ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል መለሰ ፤ "ከነሱም ሕግጋት ይበ
ልጥ የጠበቀና የከረረ ሲሆን ይችላል ፤ እንዲሁም ደግሞ ይህ
ተግባር ለዓለም ሰላም አጠባበቅ አስፈላጊነቱና ጠቃሚነቱ እጅግ
ከፍ ያለ መሆኑን ለመጠራጠር አልቃጣም ። እውነቱን ለመናገር
ከሆነ ከሻምበል አዛዥ የተቀበለውን ትእዛዝ በሚገባ የፈጸመ
ወታደር ከዚያው ከአዛዥ የሚያንስ አይደለም ። ይህንንም የምል
በት ምክንያት ፤ የገዳም መነኮሳት በረጋ ሰላምና በአረፍት
ሥፍራ ተቀምጠው አምላክ ምሕረቱን በምድር ላይ እንዲያወ
ርድላቸው በጸምና በጸሎት ሲለምኑ እነሱ በጸሎትና በጾም
ለምነው የሚያስገኙትን ምሕረትና ሰላም እኛ ወታደሮችና ዘዋሪ
ፈረሰኞች ደግሞ በክንዶቻችን ኃይልና በጐራዴያችን ስለት

ሜፍ ጠይቀን ስለምናገኘው ነው ። ይህንንም ስናደርግ ለማናቸውም ችግር ዕርዳታና መጠለያ አግኝተን ሳይሆን በጠራው ስማይ ሥር ሁነን ፤ የበጋውን ነዲድ ፀሐይና የክረምቱን አንሰፍሳፊ ውርጭና ብርድ ታግሰን ነው ። ስለዚህ እኛ ዙዋሪ ፈረሰኞች በምድር ላይ የምንገኝ የአምላክ ሚኒስትሮችና መሣሪያዎች ስለ ሆንን ፍርዱን ለዓለም የሚያከፋፍለው በኛ በእንደራሴዎቹ አማካይነት ነው'' ።

''መቸም የጦርነት ጉዳይና እንዲሁም እሱን የሚጠቅሱትና የሚመለከቱት ጉዳዮች ሁሉ ያለድካምና ያለችግር ፤ ያለላብ ማንጠ ፍጠፍ የሚፈጸሙ ስላይደሉ አምላክ ደካማዎችን እንዲረዳላቸው በማለት በጸጥታ ሥፍራንና በረፍት ላይ ተቀምጠው ከሚለም ኑት ባሕታውያን ይልቅ የበለጠ ድካምና ፍዳ የሚደርስባቸው የዙዋሪ ፈረሰኛነትን ተግባር በሚያከናውኑት ከርታታ ፈረሰ ኞች ላይ መሆኑ ለማንም ቢሆን የተሰወረ አይደለም'' ።

''የዙዋሪ ፈረሰኛነት ተግባር እንደመነኮሳቱ ተግባር ምኞት ያለበት ነው ብዬ ለመናገር አልደፍርም ። እንዲያውም ትዝም አይለኝም ። እኔ አረጋግጬ ለመናገር የምችለው እኔ ራሴ የምሰቃይበትን ብቻ ስለሆነ የፈረሰኛነት ተግባር ያለጥርጥር አድካሚ አማቃቂ ፤ አማሳኝ አሣሪኛ ፤ ለረሀብና ለውኃ ጥም የተ ጋለጠ ፤ ቡቱቷም እድፋም መሆኑን ሳስረዳችሁ የምኞቱን ወገን ማመዛዘንና የማናችን ጉስቁልና እንደሚበረታ ማመሳከር የናንተ ፈንታ ነው ። ባለፉት ዘመናት የነበሩትም ፈረሰኞች በዕድሜያቸው እርዝማኔ ውስጥ ብዙ ሥቃይና ችግር ደርሰባቸው እንደዛቀጡበት የታወቀ ቢሆንም ፤ አንዳንዶቹ በክንዳቸው ኃይል ተነሳስተው ንጉሥ ነገሥት ለመሆን በቅተዋል ። ለዚህም ዕድል ለመቧቃት የቻሉት እውነት ይመስክርብኝ ዋጋውን በላባቸውና በደማቸው ከከፈሉ በኋላ መሆኑን እምልበታለሁ ። ምናልባት የነዚህ ፈረሰ ኞች አቃቢ የሆነ የፋቅራና የአስማተኛ እርዳታ ቢጓደልባቸው ኖሮ በርግጥ ቅስማቸው ተሰብሮ የፍላጐታቸው አቅል ርቆአቸው ተስፋቸውም በክጎደት ተደምስሶ የትም ባከነው ይቀሩ ነበር'' ሲል ማስረዳቱን ጨረሰ ።

መንገደኛውም መለሰ ፤ ''እኔም ይህንኑ አሰተያየት ከልብ ደጋፊ ነኝ ፤ ነገር ግን በፈረሰኞች ተግባር ውስጥ ሕገ ወጥ በመ ሆኑ የታዘብኩት አንድ መጥፎ ልማድ አለ ፤ ይኸውም አንድ ታላቅና አደገኛ የሆነ ውጊያ ለመጀመር በግጥሚያ መስመር ላይ ሲገኝ ሕይወታቸውን የሚቀስፍ አደጋ እንደሚደርስባቸውና ለመ ዳንም ዕድል ካለገዛቸው በስተቀር ከመሞት እንደማይተርፉ እያወቁት ማናቸውም ንጹሕ እውነተኛ ሲያደርግ እንደሚገባው ሁሉ የሚጋጠመበት ነጥብ ላይ የኃጢአት ሥርኤት ለመለመን ወደ አምላክ መማጠንን በፍጹም አስታውሰውት አለማወቃቸውን ነው ። እንዲያውም አፍራሻውን ወደ አምላክ መማጠንን ወደ ጐን ትተው አምላኮቻቸው ይመስል ወደሚያፈቅሩአቸው ሴቶች በመማጠን እጅግ በበዛ ጸሎትና ምሕላ ሲማለጡባቸው ይሰማ ሉ ። ስለዚህ በዚህ ረገድ ያለው አደራረጋቸው ሲታይ ከደግነት ይልቅ ክፋዎች የሚያሰኛቸውን ትዝብት የፈጸሙ ናቸው ።

''ወንድሜ ሆይ'' አለ ዶን ኪሾት ፤ ''ጉዳዩ ከዚህ በተለየ አኳኋን ሊፈጸም አይችልም ። ከዚህ የተለየ ወግና ሥርዓት የሚከ ተል ዙዋሪ ፈረሰኛ ቢኖር ከፍ ያለ ውርደት ላይ እንደሚወድቅ አይጠረጠርም ። ምክንያቱም ይህ አደራረግ በዙዋሪ ፈረሰኛነት ሕግ ውስጥ የኖረ ልማድ ስለሆነ ዛሬ እኔ ዘንድ ሲደርስ መሻር አይገባውም ። አንድ ዙዋሪ ፈረሰኛ ከፍተኛ የሆነ የጦር ጉዳይ በሚያከናውንበት ጊዜ ዘወትር የወዳጁን መልክ በዓይኑ ብረት ላይ መቅረጽ ስለሚገባው በሚዋጋበት ሰዓት ዓይኑን ቱና አድርጐ በፍቅራዊነትና ባሳዛኝነት አኳኋን ባይነ ሕሊናው እየተመ ለከተ ከዚህ ካልታመነው እርምጃው በሕይወት እንዲመለስላት እንድትጠብቀውና እንድትፈቅደው መለመን አለበት ። ይህም ልመናው እንዲሰማለት ድምጹን ከፍ አድርጐ ባይናገርም በሙሉ ልቡ በሷ የተማጠነ መሆኑን የሚያስረዳ አንዳች ነገር በጥርሶቹ አፍኖ መናገር ግዴታው ነው ። ስለዚህም ጉዳይ በታሪክ ውስጥ የተጻፈ ብዙ ምሳሌዎች ይገኛሉ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ይህንን ግዴታ ቢያስቀድሙ በእግዚአብሔር ከፍተኛ ጠባቂነት ላይማ ጠኑ ሊቀሩ ይችላሉ ብሎ መከራከር አግባብ ያለው አይመስል ኝም ። ይህንንም የምለው በውጊያው ስዓት ከወይዛዝርታቸው

ጫፍ ጠይቀን ስለምናገኘው ነው ። ይህንንም ስናደርግ ለማናቸውም ችግር ዕርዳታና መጠለያ እግኝተን ሳይሆን በጠራው ስማይ ሥር ሁነን ፤ የቢጋውን ነዲድ ፀሐይና የክረምቱን አንሰፍሰፊ ውርጭና ብርድ ታግሰን ነው ። ስለዚህ እኛ ዙዋሪ ፈረሰኞች በምድር ላይ የምንገኝ የአምላክ ሚኒስትሮችና መሣሪያዎች ስለ ሆንን ፍርዱን ለዓለም የሚያከፋፍለው በኛ በእንደራሴዎቹ አማካይነት ነው'' ።

''መቸም የጦርነት ጉዳይና እንዲሁም እሱን የሚጠቅሱትና የሚመለከቱት ጉዳዮች ሁሉ ያለችግር ፤ ያለላብ ማንጠ ፍጠፍ የሚፈጸሙ ስላይደሉ አምላክ ደካማዎችን እንዲረዳላቸው በማለት በጸጥታ ሥፍራንና በረፍት ላይ ተቀምጠው ከሚለም ኑት ባሕታውያን ይልቅ የበለጠ ድካምና ፍዳ የሚደርስባቸው የዙዋሪ ፈረሰኛነትን ተግባር በሚያከናውኑት ከርታታ ፈረሰኞች ላይ መሆኑ ለማንም ቢሆን የተሰወረ አይደለም'' ።

''የዙዋሪ ፈረሰኛነት ተግባር እንደመነኮሳቱ ተግባር ምኞት ያለበት ነው ብዬ ለመናገር አልደፍርም ። እንዲያውም ትዝም አይለኝም ። እኔ አረጋግጬ ለመናገር የምችለው እኔ ራሴ የምሰቃይበትን ብቻ ስለሆነ የፈረሰኛነት ተግባር ያለጥርጥር አድካሚ አማቃቂ ፤ አማሳኝ አሣረኛ ፤ ለረሀብና ለውኃ ጥም የተ ጋለጠ ፤ ቡቲታም እድፋም መሆኑን ሳስረዳችሁ የምኞቴን ወገን ማመዛዘንና የማናችን ጉስቁልና እንደሚበረታ ማመሳከር የናንተ ፈንታ ነው ። ባለፉት ዘመናት የነበሩትም ፈረሰኞች በዕድሜያቸው እርዝማኔ ውስጥ ብዙ ሥቃይና ችግር ደርሶባቸው እንደዛቀጡበት የታወቀ ቢሆንም ፤ አንዳንዶቹ በክንዳቸው ኃይል ተነሳስተው ንጉሥ ነገሥት ለመሆን በቅተዋል ። ለዚህም ዕድል ለመብቃት የቻሉት እውነት ይመስክርብኝ ዋጋውን በላባቸውና በደማቸው ከከፈሉ በኋላ መሆኑን እምልበታለሁ ። ምናልባት የነዚህ ፈረሰኞች አቃቢ የሆነ የፋቅራና የአስማተኛ እርዳታ ቢጓደልባቸው ኖሮ በርግጥ ቅስማቸው ተሰብሮ የፍላጐታቸው አቅል ርቆአቸው ተስፋቸውም በክጎደት ተደምስሶ የትም ባከነው ይቀሩ ነበር'' ሲል ማስረዳቱን ጨረሰ ።

መንገደኛውም መለሰ ፤ ''እኔም ይሀንኑ አስተያየት ከልብ ደጋፊ ነኝ ፤ ነገር ግን በፈረሰኞች ተግባር ውስጥ ሕገ ወጥ በሙ ሆኑ የታዘብኩት አንድ መጥፎ ልማድ አለ ፤ ይኸውም አንድ ታላቅና አደገኛ የሆነ ውጊያ ለመጀመር በግጥሚያ መስመር ላይ ሲገኝ ሕይወታቸውን የሚቀስፍ አደጋ እንደሚደርስባቸውና ለመ ዳንም ዕድል ካላገዛቸው በስተቀር ከመሞት እንደማይተርፉ እያወቁት ማናቸውም ንጹሕ እውነተኛ ሲያደርግ እንደሚገባው ሁሉ የሚጋጠሙበት ነጥብ ላይ የኃጢአት ሥርኤት ለመለመን ወደ አምላክ መማጠንን በፍጹም አስታውሰውት አለማወቃቸውን ነው ። እንዲያውም አፍራሻውን ወደ አምላክ መማጠንን ወደ ጐን ትተው አምላኮቻቸው ይመስል ወደሚያፈቅሩአቸው ሴቶች በመማጠን እጅግ በበዛ ጸሎትና ምሕላ ሲማለጡባቸው ይሰማ ሉ ። ስለዚህ በዚህ ረገድ ያለው አደራረጋቸው ሲታይ ከደግነት ይልቅ ክፉዎች የሚያስኛቸውን ትዝብት የፈጸሙ ናቸው ።

''ወንድሜ ሆይ'' አለ ዶን ኪሾት ፤ ''ጉዳዩ ከዚህ በተለየ አኳኋን ሊፈጸም አይችልም ። ከዚህ የተለየ ወግና ሥርዓት የሚከ ተል ዙዋሪ ፈረሰኛ ቢኖር ከፍ ያለ ውርደት ላይ እንደሚወድቅ አይጠረጠርም ። ምክንያቱም ይህ አደራረግ በዙዋሪ ፈረሰኛነት ሕግ ውስጥ የኖረ ልማድ ስለሆነ ዛሬ እኔ ዘንድ ሲደርስ መሻር አይገባውም ። አንድ ዙዋሪ ፈረሰኛ ከፍተኛ የሆነ የጦር ጉዳይ በሚያከናውንበት ጊዜ ዘወትር የወዳጁን መልክ በዓይኑ ብረት ላይ መቅረጽ ስለሚገባው በሚዋጋበት ሰዓት ዓይኑን ቀና አድርጐ በፍቅራዊነትና ባሳዛኝነት አኳኋን ባይነ ሕሊናው እየተመ ለከተ ከዚህ ካልታመነው እርምጃው በሕይወት እንዲመለስለት እንድትጠብቀውና እንድትፈቅደው መለመን አለበት ። ይህም ልመናው እንዲሰማለት ድምጹን ከፍ አድርጐ ባይናገርም በሙሉ ልቡ በሷ የተማጠነ መሆኑን የሚያስረዳ አንዳች ነገር በጥርሶቹ አፍኖ መናገር ግዴታው ነው ። ስለዚህም ጉዳይ በታሪክ ውስጥ የተጻፈ ብዙ ምሳሌዎች ይገኛሉ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ይህንን ግዴታ ቢያስቀድሙ በእግዚአብሔር ከፍተኛ ጠባቂነት ሳይማ ጠኑ ሊቀሩ ይችላሉ ብሎ መከራከር አግባብ ያለው አይመስለ ኝም ። ይህንንም የምለው በውጊያው ሰዓት ከወይዛዝርታቸው

ሚፍ ጠይቀን ስለምናገኘው ነው ። ይህንንም ስናደርግ ለማናቸ
ውም ችግር ዕርዳታና መጠለያ አግኝተን ሳይሆን በጠራው ሰማይ
ሥር ሁነን ፤ የበጋውን ነዲድ ፀሐይና የክረምቱን አንሰፍሳፊ
ውርጭና ብርድ ታግሰን ነው ። ስለዚህ እኛ ዙዋሪ ፈረሰኞች
በምድር ላይ የምንገኝ የአምላክ ሚኒስትሮችና መሣሪያዎች ስለ
ሆንን ፍርዱን ለዓለም የሚያከፋፍለው በኛ በእንደራሴዎቹ አማ
ካይነት ነው" ።

"መቸም የጦርነት ጉዳይና እንዲሁም እሱን የሚጠቅሱትና
የሚመለከቱት ጉዳዮች ሁሉ ያለድካምና ያለችግር ፤ ያለላብ ማንጠ
ፍጠፍ የሚፈጸሙ ስላይደሉ አምላክ ደካማዎችን እንዲረዳላቸው
በማለት በጸጥታ ሥፍራንና በረፍት ላይ ተቀምጠው ከሚሰም
ኑት ባሕታውያን ይልቅ የበለጠ ድካምና ፍዳ የሚደርስባቸው
የዙዋሪ ፈረሰኞነትን ተግባር በሚያከናውኑት ከርታታ ፈረሰ
ኞች ላይ መሆኑ ለማንም ቢሆን የተሰወረ አይደለም" ።

"የዙዋሪ ፈረሰኛነት ተግባር እንደመነኮሳቱ ተግባር
ምኞት ያለበት ነው ብዬ ለመናገር አልደፍርም ። እንዲያውም
ትዝም አይለኝም ። እኔ አረጋግጬ ለመናገር የምችለው እኔ ራሴ
የምሰቃይበትን ብቻ ስለሆነ የፈረሰኛነት ተግባር ያለጥርጥር
አድካሚ አማቃቂ ፤ አማሳኝ አሣሪኛ ፤ ለረሀብና ለውኃ ጥም የተ
ጋለጠ ፤ ቡቱቷም እድፋም መሆኑን ሳስረዳችሁ የምኞቱን ወገን
ማመዛዘንና የማናችን ጉስቁልና እንደሚበረታ ማመሳከር የናንተ
ፈንታ ነው ። ባለፉት ዘመናት የነበሩትም ፈረሰኞች በዕድሜያቸው
እርዝመኔ ውስጥ ብዙ ሥቃይና ችግር ደርሶባቸው እንደዛቀጡበት
የታወቀ ቢሆንም ፤ አንዳንዶቹ በክንዳቸው ኃይል ተነሳስተው
ንጉሥ ነገሥት ለመሆን በቅተዋል ። ለዚህም ዕድል ለመቢቃት
የቻሉት እውነት ይመስክርብኝ ዋጋውን በላባቸውና በደማቸው
ከከፈሉ በኋላ መሆኑን እምልበታለሁ ። ምናልባት የነዚህ ፈረሰ
ኞች አቃቢ የሆነ የፉቅራና የአስማተኛ እርዳታ ቢጓደልባቸው
ኖሮ በርግጥ ቅስማቸው ተሰብሮ የፍላጐታቸው አቅል ርቆአቸው
ተስፋቸውም በክኅደት ተደምስሶ የትም ባክነው ይቀሩ ነበር"
ሲል ማስረዳቱን ጨረሰ ።

መንገደኛውም መለሰ ፤ "እኔም ይህንኑ አስተያየት ከልብ
ደጋፊ ነኝ ፤ ነገር ግን በፈረሰኞች ተግባር ውስጥ ሕገ ወጥ በመ
ሆኑ የታዘብኩት አንድ መጥፎ ልማድ አለ ፤ ይኸውም አንድ
ታላቅና አደገኛ የሆነ ውጊያ ለመጀመር በግዥያ መስመር ላይ
ሲገኝ ሕይወታቸውን የሚቀስፍ አዲጋ እንደሚደርስባቸውና ለመ
ዳንም ዕድል ካላገዛቸው በስተቀር ከመሞት እንደማይተርፉ
እያወቁት ማናቸውም ንጹሕ እውነተኛ ሊያደርግ እንደሚገባው
ሁሉ የሚጋጠሙበት ነጥብ ላይ የኃጢአት ሥርኡት ለመለመን
ወደ አምላክ መማጠንን በፍጹም አስታውሰውት አለማወቃቸውን
ነው ። እንዲያውም አፍራሻውን ወደ አምላክ መማጠንን ወደ
ጐን ትተው አምላኮቻቸው ይመስል ወደሚያፈቅሩአቸው ሴቶች
በመማጠን እጅግ በበዛ ጸሎትና ምሕላ ሲማለጡባቸው ይስማ
ሉ ። ስለዚህ በዚህ ረገድ ያለው አደራረጋቸው ሲታይ ከደግነት
ይልቅ ክፉዎች የሚያሰኛቸውን ትዝብት የፈጸሙ ናቸው ።

"ወንድሜ ሆይ" አለ ዶን ኪሾት ፤ "ጉዳዩ ከዚህ በተለየ
አኳኋን ሊፈጸም አይችልም ። ከዚህ የተለየ ወግና ሥርዓት የሚከ
ተል ዙዋሪ ፈረሰኛ ቢኖር ከፍ ያለ ውርደት ላይ እንደሚወድቅ
አይጠረጠርም ። ምክንያቱም ይህ አደራረግ በዙዋሪ ፈረሰኛነት
ሕግ ውስጥ የኖረ ልማድ ስለሆነ ዛሬ እኔ ዘንድ ሲደርስ መሻር
አይገባውም ። አንድ ዙዋሪ ፈረሰኛ ከፍተኛ የሆነ የጦር ጉዳይ
በሚያከናውንበት ጊዜ ዘወትር የወዳጁን መልክ በዓይኑ ብረት
ላይ መቅረጽ ስለሚገባው በሚዋጋበት ሰዓት ዓይኑን ቀና
አድርጐ በፍቅራዊነትና ባሳዛኝነት አኳኋን ባይን ሕሊናው እየተመ
ለከተ ከዚህ ካልታመነው እርምጃው በሕይወት እንዲመለሰላት
እንድትጠብቀውና እንድትፈቅደው መለመን አለበት ። ይህም
ልመናው እንዲሰማለት ድምጹን ከፍ አድርጐ ባይናገርም በሙሉ
ልቡ በሷ የተማመነ መሆኑን የሚያስረዳ እንዳች ነገር በጥርሶቹ
አፍኖ መናገር ግዴታው ነው ። ስለዚህም ጉዳይ በታሪክ ውስጥ
የተጻፈ ብዙ ምሳሌዎች ይገኛሉ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ይህንን
ግዴታ ቢያስቀድሙ በእግዚአብሔር ከፍተኛ ጠባቂነት ሳይማ
ጠኑ ሊቀሩ ይችላሉ ብሎ መከራከር አግባብ ያለው አይመስለ
ኝም ። ይህንንም የምለው በውጊያው ሰዓት ከወይዛዝርታቸው

ቀጥሎ እግዚአብሔርንም የሚለምኑበት ጊዜና ፋታ እንደማያጡ እርግጠኛ ስለሆንኩ ነው ።

መንገደኛውም መለሰ "አውንም ቢሆን ከዚህ ጭብጥዎ ውስጥ ገና ያልገባኝ አንድ ነገር አለ ፤ ይኸውም አብዛኛውን ጊዜ ባነበብኳቸው መጻሕፍት ውስጥ አረጋግጬ እንደተረዳሁት ዙዋሪ ፈረሰኞች ድንገት ተገናኝተው መነጋገር እንደጀመሩ ወዲያውኑ ምስጢሩ ባልታወቀ ምክንያት አንደኛው በቁጣ ቱማ ይሉና ፈረሶቻቸውን አዙረው የውጊያ መነሻ ሥፍራ ይይዛሉ ። ምንም አታካራ ሳያበዙና ገላጋይም ሳይጠብቁ የፈረሶቻቸውን ልጓም ለቅቀው ሽምጥ አስነስተው በጦር ለመዘናጠል በሚመጡበት ጊዜ መንገዳቸው ላይ የሚግጠኑት በሴቶቻቸው ስም ብቻ ነው ። ነገር ግን አበክሮ እንደሚደርሰው ከሁለት አንደኛው ፈረሰኛ በወደረኛው ጦር መሐል ለመሐል ተወግቶ ከፈረሱ ላይ ተዘንጥፎ እመሬት ላይ ዘፍ ሲል ይታያል ። ሁለተኛውም መወጋት ስለማይቀርለት እሱም የፈረሱን ጋማ ጨምድዶ ይዞ አንገቱ ላይ ካልተደፋ በቀር እንደዚያኛው መሬት ላይ ወድቆ መንከባለሉ የማይቀርለት ነው ። ስለዚህ ይህን ያህል በተጣደፈው ውጊያ መካከል ሚቹ ፈረሰኛ ጊዜና ፋታ አግኝቶ ወደ ጌታው ለመግጠን ቻለ ማለት በውነቱ ከመታመን እጅግ የራቀ ነው ። እንደኔ ቢሆን ግን ለመዘናጠል በሚመጡበት ሰዓት ሴቶቻቸውን ለመግጠን ሲሉ የተናገሩትን ቃል የሚያከብር እውነተኛ የሆነ ሰው እንደ ሚያደርገውና ማድረግም እንደሚገባው ሁሉ አሰቀድሞ ለእውነት ቢያደርጉት ኖሮ የተሻለ በሆነ ነበር ባይ ነኝ ። ይህንንም ስላልኩ እኔ በበኩሌ እንደታዘብኩት መቸም ዙዋሪ ፈረሰኞች ሲባሉ ሁሉም ፍቅር የያዛቸው ስላልሆኑ የሚግጠኑባቸው ሴቶች እንደ ሌሉ እርግጠኛ በመሆኔ እንዳንዶቹ ከዚህ ፈተና እንደሚርቁ እገምታለሁ" አለው ።

"ይህ ከቶ ሊሆን አይችልም" ሲል ዶን ኪሾት ተከራከረ ፤ "የሚያፈቅራት ሴት የሌለው ዙዋሪ ፈረሰኛ ፈጽሞ ሊኖር አይችልም ፤ ምክንያቱም በሥነ ፍጥረት ሕግ ሰማያት ከዋክብት እንዳሏቸው ሁሉ እነሱም የሚያፈቅሩአቸው ሴቶች እንዳሉዋቸው የታወቀና የታመነ ነገር ነው ። ከዚህም በቀር እስከዛሬ

ድረስ ከዙዋሪ ፈረሰኞች መካከል ያለሴትና ያለፍቅር የሚገኝ ፈረሰኛ መኖሩን የሚያስረዳ አንድም ታሪክ አይገኝም ። በውነቱ የሚያፈቅራት ሴት የሌለው ፈረሰኛ ቢኖር ኖሮ በዚህ ምክንያት ብቻ ዋራዝ ነጠቅ ይባላል እንጂ ቱባ ፈረሰኛ ሊባል ባልተገባውም ነበር ። ወደ ፈረሰኝነት ምሽግ ውስጥ ገብቷል ቢባል እንኳ በፊት ለፊቱ በር በኩል ሳይሆን እንደሴባና እንደወሰላታ በም ሽጉ ውድም ተንጠላጥሎ ፤ ወይም ባንድ ቀዳዳ ሾልኮ የገባ ፋዲታ የሚባል ነው ። ይህንንም በማድረጉ ዘወትር በሐፍረት ሲሸማቀቅ የሚኖርና አንድ ቀን ነውሩ ሲገለጥበት ተባርሮ ወጥቶ ከውርደት ላይ የሚወድቅ መሆኑ የማይዛባ ነው ።

"ይህም ቢሆን" አለ መንገደኛው" በትክክል አሳስታው ሰውም እንጂ የጀግናውን የጋው ውላው አማዲስን ወንድም የዶን ጋላዋርን ታሪክ እንዳነበብኩት በግዋሚያው ጊዜ እንደሌሎቹ በስሟ የሚማጠንበት አንዲት የተወሰነባት ሴት እንደሌለችው ያስረዳል ። ይሁን እንጂ በዚህ ምክንያት ተነቅፎ የጀግንነቱ ዝና አልተገሠሠበትም ። ይልቁንም በዚህ አኳኋን እያሙትና እያሸማ ጠጡት ስሙ የታወቀና በጀግንነቱም የላቀ ፈረሰኛ ለመሆን ችሏል" ።

"ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል መለሰ ወንድሜ ሆይ" አንዲት የነጎት ወፍ ብቻዋን ስትበር በመታየቷ ለጸደይ መግባት ምልክት ልትሆን አትችልም ይባላል ። ስለዚህ እኔ እንደማውቀው ይህ ፈረሰኛ ለማንም ባልተገለጸ ምስጢር የጸና ፍቅር አድሮበት ነበር። ከዚህም በስተቀር ይህ ፈረሰኛ በተፈጥሮ ጠባዩ ያያትን ሴት ሁሉ መከጀልና መውደድ ያበዛ ስለነበረ ይህን ጠባዩን ሊታገስ ባለመቻሉ ብቻ የተወሰነባት ሴት የለውም ተብሎ ታምቶ ይሆ ናል እንጂ እንደሕጉ የፈቃዱ ፍጹም እመቤት የሆነች አንዲት ሴት እንደነበረችው ሊረጋገጥ ተችሏል ። በግዋሚያውም ጊዜ ዘወትር በሊው ስም ሲማጠን ተሰምቷል ። ይህም በጣም በጠበቀ ምስጢር የተያዘ ነው እንጂ እንደሌሎቹ በይፋ ሲነገር የተሰማ አይደለም ። እንዲህም የሚሆነው ሁልጊዜ ዓይነፋርና ምስጢሩን ደባቂ ፈረሰኛ በመሆኑ በተቻለው መጠን ስለሚጠነቀቅ ነው ።

መንገደኛውም እንዲህ ሲል ጠየቀ "መቸም ዙዋሪ ፈረሰኞች ሁሉ ፍቅር እንዲያድርባቸው ሕጉ የሚያስገድዳቸው ከሆነ እርስዎም የዚሁ ተግባር ባልደረባ በመሆንዎ ፍቅር አድርብዎታል ማለት ነዋ? እርስዎም እንደዱን ጋላዎር ምስጢርዎን ለመደበቅ የማይጨነቁ ከሆነ የሚያፈቅሯትን ሴት አገሯን ፣ ዘሯን ፣ ውበቷን ፣ ገልጠው እንዲነግሩን በነዚህ በጉዞ ጓደኞቼና በኔም ስም ሞምር አለምንዎታለሁ ። ይችም ሴት የክቡርነትዎ ሁኔታ እንደሚገልጠው ይህን የመሰለ ጀግና ፈረሰኛ ያፈቀራትና የሚያገለግላት መሆኗን ድፍን ዓለም ሲያውቅላት በዕድለኛነቷ የምትደሰት ትሆናለች" አለው ።

ይህ ጥያቄ ባሳደረበት ስሜት ዶን ኪሾት በጣም ከተነፈሰ በኋላ እንዲህ ሲል ማስረዳት ጀመረ ፤

"ጣፋጭ ጠላቴ እኔ የማፈቅራትና የማገለግላት መሆኑን ድፍን ዓለም ቢያውቅላት የምትፈቅድ መሆን አለመሆኗን አረጋግጬ ለማወቅ ባለመቻሌ ቅሬታ ሳይሰማኝ አልቀረም ። ይሁን እንጂ ከናንተ ዘንድ ከፍ ባለ ትሕትና የቀረበልኝን ልመና እንድፈጽም ሕሊናዬ ስለሚያስገድደኝ ልነግራችሁ እፈቅዳለሁ ። ይኸውም ፤ ስሟ ዱልቺኒያ ፤ አገሯ ቶቦዛ ፤ አውራጃው ማንቻ ፤ የክብር ደረጃዋ ቢያንስ ቢያንስ ልዕልት መሆኗን እነልጽላችኋለሁ ። ከዚህ በስተቀር ለኔ ንግሥቴና እመቤቴ በመሆኗ በሥነ ፍጥረቷም ከሔዋን ልጆች ሁሉ የምትበልጥ ውብ ስለሆነች በሕይወት ያሉትና ሞተው ያለፉት ባለቅኔዎች ሁሉ በቁንጅናቸው መደነቂያ የሆኑትን ሴቶቻቸውን ለማሞገስ ሲሉ በቅኔያቸው ውስጥ እያነቡ የተቀኙትን ምሥጢራዊ ምስጋናና መወድስ ፤ እንዲሁም እጹብ ድንቅ ሆኖ ለሰው ልጅ ረቂቅነት የተሰጠውን ማናቸውንም ዓይነት ምሳሌ ሁሉ ጠቅላላ የያዘች ነች ። በተለይም በበኩሴ ያየሁትን ያህል ስለውበቷ ልዘረዝር ላችሁ የምችለው ፤ ጸጉሮቿ የሐር ጉንጉን ፤ ግንባርዋ መስታወት ፤ ቅንድቧ ቀስተ ዳመና ፤ አይኖቿ ፀሐይ ፤ ጉንጮቿ የፈነዱ ጽጌረዳዎች ከንፈሮቿ የማር እንጉቻዎች ፤ ጥርሶቿ በረዶዎች ፤ አንገቷ ብርሌ ፤ ደረቷ እብነ በረድ ፤ ጣቶቿ የዝሆን ጥርስ ፤ ገላዋ አመልማሎ ፤ መሆኑንና እንዲሁም የእንከኗን ወገን ከሰው ዓይን የሚ

ሠውርላት የጸጋ መጋረጃ የተጐናጸፈች መሆኗን ነው ። እኔ እንደ ማስበውና እንደማልመው ውበቷን በጥንቃቄ አስተውሎ የሚመለከታት ሁሉ እያጋነነ ያደንቃታል እንጂ ከቶ ወደረኛ ሊያገኛት እንደማይችል ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ" ።

ቪባልዶም እንዲህ ሲል ጠየቀ "እኛ በተለይ ለማወቅ የምንሻው ቤተሰቦቿን ፤ ትውልዷን ፤ የዘሯን ጥንተ መሠረት አፈላለስ ነው" አለ ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል መለሰ "የትውልዷ አፈላለስ ከጥንቶቹ ኩርሲዎች ፤ ከጋዮችና ከሮማውያን ቪፒዎኖች ፤ የሚመጣ አይደለም ፤ ወይም ደግሞ ከዛሬዎቹ ኩሎናዎችና ኦርሲኒዎች ፤ ወይም ከሞጋንዳዎችና ከየካታሉኛው ሬኳኔሶች አይደለም፤ ወይም ከሬቤላስ ፤ ከቫሌንሳው ቫላኖባስ ከፖላፎከስ ፤ ከኑዛሶች ፤ ከሮካቤርቲዎች ፤ ከኮሬላዎች ፤ ከሎናዎች ፤ ከአላጐኖች ፤ ከኡሪያዎች ፤ ከርክሶች ፤ ወይም ከየአራጐናው ጐሪያዎች ፤ ከሴርዳዎን ፤ ከማንሪኬዎች ፤ ከሜዶሳዎች ፤ ከየካስቲሊያው ጉዝማኖች ፤ ከአሴን ካስትሮዎች ፤ ከፖላኖች ፤ ከየፖርቱጋሉ ሚኔሰዎች አይደለም ፤ ነገር ግን የማንቻው ቶቦዛ ተወላጅ ነች ። ቤተሰቦቿም በአውነቱ በዘመናዊነታቸው የሚኩሩ ባለጊዜዎች ናቸው ። እንዲሁም ለመጪው ትውልድ ታዳጊነት የሚኖራቸው የተከበሩ ዘሮች ለማፍራት መሠረት ለመሆን የታጨች እድለኛ ሴት ናት ። ከዚህ ማስረጃ የበለጠ በመፈለግ ሌላ ጥያቄ ብታቀርቡልኝ ዜርቢኖ የሚባለው ጀግና በኦርላንዶ መሣሪያዎች ምርኩ ላይ ያደረገውን ውልና መልስ በስተቀር ሌላ አጥጋቢ መልስ ልሰጣችሁ አልችልም ፤ ይኸውም ውል ፤ .....ማንም እንዳይነካት፤

ከኦርላንዶ ጋር አይቻልምና መለካካት ...የሚል ነው አለው ።

ያም እንዲህ ሲል መለሰ "ምንም እንኳ የኔ ዝርያ የላፊዶ ተወላጅ ጊዜ ያነሳው የደሀ ወገን ቢሆንና ይህንም ክቡርነትዎ የጠሩልኝን የመሰለ የትውልድ ስም ከዚህ ቀደም ሲጠራ ስምቼ ባላውቅም በውነቱ የኔን ዝርያ ከየማንቻው ቶቦዛ ጋር

በጭራሽ ላስተካክለው አልምክርም ፤ እንዲያውም ይህን በመና ገራ ከድፍረት እንዳይቆጥሩብኝ ይቅርታዎን እለምናለሁ'' አለ ።

''ይህም የሚቻልና የሚሆን ነገር ነውና እንጂ አይመስለኝም ፤ በውነቱ አደናገረኝ ለማለት እችላለሁ'' አለ ዶን ኪሾት ።

ይህ ሁሉ ሐተታ በሚጐርፍበት ጊዜ ሌሎቹ ሰዎች የንግግሩን ፍሬ ለማጠንከር ከፍ ባለ ጥንቃቄ ነቅተው ያዳምጡ ነበርና በንግግሩና በሐሳቡ አገላለጥ ብርሀን እንደተረዱት እረኞቹም ሆኑ ፍየል አርቢዎች የዶን ኪሾታችንን ፍጹም የሆነ የሕሊና ጉድለት ለማረጋገጥ ቻሉ ።

ሳንቾ ፓንቻ ግን ይህን ሐሳብ የሚገልጠውና ሐተታውንም የሚያጐርፈው ማን እንደሆነ ከልጅነቱ ጀምሮ ስለሚያውቀውና ጥቂትም ጥርጣሬ ቢገባው ይህን ያህል ዘመን በቶቦዞ አቅራቢያ ሲኖር ይህን የዘር ስምና ይህችን ልዕልት ሲያነሷት በፍጹም ባለ መስማቱ የተነሳ የውቢቷ ዱልቺኒያን ጉዳይ ለማመን ስለሆነ ከዚህ በስተቀር ሌላውን ጌታው የሚናገረውን ሁሉ የወርቅ ምዝምዝ ያህል ቆጥሮት ነበር ።

በዚህ ጉዳይ ላይ እየተነጋገሩ በሚጓዙበት ጊዜ በሁለት ረጃጅም ተራራዎች መካከል በሚገኙት ሸለቆዎች አኳያ ጥቂቁር ደበሎ የለበሱና በእራሳቸውም ላይ የአረማ አክሊል የጐነጐኑ ቆይቶም በቅርብ እንደታየው እኩሌታዎቹ የዘንባባ ፤ እኩሌታዎቹ የደረሆ ቅጠል የጠመጠሙ ሃያ የሚሆኑ እረኞች ተከታትለው ቁልቁለቱን ሲወርዱ በሩቁ አዩዋቸው ። ከነዚህም ስድስቶቹ በአበባና በልዩ ልዩ ለምለም ቅጠል የተሸፈነ ቃሬዛ ተሸክመው ነበር ። እዚህ ካሉት ፍየል አርቢዎች አንደኛው አነሳና ለመንገደኞቹ እንዲህ ሲል ነገራቸው ።

''እነዚያ ቁልቁለቱን የሚወርዱት ሰዎች የተሸከሙት የጂሮ ሶስቶሞስን አስከሬን ነው ፤ የሚያጉዙትም እሱ ለመቀበር ወደ መረጠው ከዚያ ኮረብታ ግርጌ ወደሚገኘው ሥፍራ ነው ። በዚህን ጊዜ ሁሉም ቶሎ እቦታው ለመድረስ እርምጃቸውን አፋጠኑና እንዚያ አስከሬኑን እመሬት ላይ አሳርፈው አራቱ እረኞች

ካንዱ ጫንጫ ሥፍራ ላይ መቃብሩን በሚቆፍሩበት ሰዓት ደረሱባቸው ። በተገናኙም ጊዜ የትሕትና ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ዶን ኪሾትና የጉዞ ጓደኞቹ ወደ ቃሬዛው ተጠግተው ሲመለከቱ በአበባና በቅጠል የተሸፈነው የሬሳ መልክ ለማየት ቻሉ ፤ በድኑም የለበሰው የእረኛ ልብስ ነበር ። እድሜውም በግምት 30 ዓመት የሚሆነው ጐልማሳ ስለሚመስል ፤ ምንም እንኳ በመሞቱ ምክንያት ወዙ ተመጥጦ መልኩ ቢጠወልግ በሕይወቱ ሳለ ሰውነቱ ደርባባና መልከ ቀና እንደነበረ የሚያስረዳ ሎጋንት ይታይበት ነበር ። በስተጐኑም እዚያው እቃሬዛው ላይ አንዳንድ መጽሐፎችና እንዲሁም የታጠፉና የተገለጡ ጽሑፎች ይገኙ ነበር ። በዚህ አኳኋን ዓይናቸውን ተከለው የሚመለከቱት ሰዎችም ሆኑ እነዚህ ጉድጓዱን የሚቆፍሩት እረኞች ሌሎችም በዙሪያው የነበሩት ኃዘንተኞች ሁሉ በጸጥታና በዝምታ አንገታቸውን ደፍተው በትካዜ መንፈስ ይታዩ ነበር ። በመጨረሻው አስከሬኑን ተሸክመው ከመጡት ሰዎች አንደኛው እንዲህ ሲል ዝምታውን ከፈተ ።

''ወንድሜ አምብሮጂዎ ሆይ ፤ ሚቹ ወዳጃችን የተናዘዘውን ቃል አክብረን በትክክል እንድንፈጽም የምትፈቅድ ከሆነ ጂሮ ሶስቶሞስ ለመቃብሩ የመረጠው ሥፍራ ይህ አሁን የሚቆፈረው መሆን አለመሆኑን ደህና አድርገህ ማጣራት አለብህ'' አለው ።

አምብሮጂዎም መለሰ ''አዎ ወንድሜ ሆይ ፤ ይሽው ሥፍራ ነው ። ያልታደለው ወዳጄ ዘወትር እየተቀመጠ ያዩጋውን ሁኔታ ሲያዋየኝ የነበረው እዚሁ ሥፍራ ነው ። ያቺንም የሰው ዘር ደመኛ ጠላት የሆነችውን ሴት ለመጀመሪያ ጊዜ ያያት እዚሁ ቆማ ሳለ ነው ። በመጀመሪያ ጊዜ ጂሮሶስቶሞስ እውነተኛውን የፍቅር ስሜቱን ለማርቼላ የነለጠላት እዚሁ ሥፍራ ነው ። በመጨረሻው ፍጹም ተስፋ ቆርጦ በዱር ለመንከራተት ያበቃውን የማርቼላን የእምቢታ መልስ የሰማው እዚሁ ሥፍራ ነው ። እሱም ከዚያ ወዲህ በጉስቁልና ኑሮ ተጨብጦ ብዙ ከተሰቃየ በኋላ ሕይወቱን ለማሳለፍ ቆርጦ የፈጸመው ከዚህ ኩተረገመ ሥፍራ ባገኘው ጠንቅ ነው ። በእድሉ ላይ ለደረሰበት ብስጭትና ሥቃይ ኗሪ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ዘለዓለማዊ መረሳት በሚገኝበት

ምድረ በዳ በሆነ ሥፍራ ለመቀበር የመረጠው እርሱ እራሱ ነው።
‘ብሎ ካረጋገጠ በኋላ ንግግሩን በመቀጠል ፊቱን ወደ ዶን ኪሾ
ትና ወደ መንገደኞቹ መለሰና እንዲህ ሲል አስረዳ።

“ክቡራን ጌቶቼና ወንድሞቼ ሆይ፤ ይህ በሚያሳዝን አስተ
ያየት የምትአስተውሱት ሰውነት አምላካችን የጸጋውን እጅግ
ከፍ ያለ ድርሻ ያኖረበትን ረቂቅ ነፍስ መልሶ ያስረከበ በድን
ነው። በብልህነቱና በትሑትነቱ፣ በደግነቱ አምሳል የማይገኝለት
የተወዳጁ የጂሮሶስቶሞስ አካላት ይህ ተንጋልሎ ለመፍረስ ተዘ
ጋጅቶ የምታዩት ነው። በወዳጅነቱ ወላንላ፤ በቸርነቱ ሚዛን
የሌለው፤ በጭምትነቱ የታፈረ፤ በተጨዋችነቱ የተወደደ፤ በጠቅ
ላላው ደግና ብሩክ ሰው የሚያሰኙት ባሕርያት ሰብስቦ የያዘ
ጐልማሳ ነበር እንጂ ሌሎቹ ሰዎች በምቀኝነት እንደሚሉት
ደግነት ሲበዛ ጅልነት ያሰኛል በተባለው አነጋገር የሚተረጐም
አልነበረም። ቢያፈቅር ተጠላ፤ ቢያመልክ ተነቀፈ፤ እንዲህን
አውሬ ለመነ አልሰማችውም፤ ድንጋይ ልቧን ተማጠነ አላሳ
ነችውም፤ ነፍሷን ተከተለ አልደረሰባትም፤ በበረሀ ውስጥ ጮኸ
ሰሚ አላገኘም፤ ለውለታ ቢሏ አገለገለ አልተባረከለትም፤ ለዚሁ
ሁሉ ድካሙ የተቀበለው ዋጋ ገና ልጅነቱን አስጊጦ ሳይጨርስ
በሞት ወጥመድ ውስጥ ገብቶ ባጭር መቀጨት ሆነ። የሞቱ
ምክንያት የሆነችው እንዲት ወዶ ገብ እረኛ ናት፤ ታሪኳ በሰ
ዎች ዘንድ መታሰቢያነቱን እንደያዘ ለዘለቀታው እንዲኖር ለማ
ድረግ የሚቹ ዋና ምኞት ነበር። ዳሩ ግን እሬሳው ተቀብሮ ግባ
መሬቱ እንደተፈጸመ ወዲያውኑ በእሳት እንዳቃጥላቸው በመጨረሻ
ቃሉ ባያስምለኝ ኖሮ እነዚህ በአጠገቡ ተበታትነው የምታዩዋ
ቸው ወረቀቶች የእረኛይቱን ጭካኔ ጉምዣነት የቱን ያህል
እንደሚያንፈግፍ ያሳምኗችሁ ነበር” አላቸው።

ቪባልዶም እንዲህ ሲል መለሰለት” ከወረቀቶቹ ባለቤት
ይልቅ አንተ ባላደራው በበለጠ ጭካኔና በማይገባ ጥብቅነት
ትእዛዝ ለመፈጸም በመዘጋጀትህ ስህተተኛ ሊሉህ የምትበቃ ነህ።
ምክንያቱም ማናቸውም ቋሚ ወይም ሟች ዘመድ ከሚገባው
አደራረግ ውጭ የሆነ አደራ እንዲፈጸምለት ሲጠይቅ እሱ ያለ
ውን ተከትሎ መፈጸሙ ከአደራ ጠባቂነት ወይም ከትክክለኛ

ነት ማስቆጠሩ ቀርቶ ግብዝነቱን የሚገልጥበት ይሆናል። መለ
ኮታዊው ማንቶባኖ እንኳ በኑዛዜው ላይ የተናገረው ቃል ሁሉ
እንዲፈጸምለት ባላደራው ንጉሠ ነገሥት አውጉስጢኖስ ፈቅዶ
ቢሆን ኖሮ በውነቱ ትክክለኛ ነገር እንዳላደረገ ተቆጥሮ ታሪኩ
እስከ ዛሬ ድረስ ሲነቀፍ በኖረ ነበር። ስለዚህ አንተም ብትሆን
ወንድሜ አምብሮጂዎ፤ ከልብ የምስጥህን ምክር ትቀበለኝ እንደሆነ
የወዳጅህን አስከሬን ከቀበርህ በኋላ ለስሙ መጠሪያ ዝክር የሚ
ሆኑትን ድርሰቶቹን ብታቃጥላቸው ይቅርታ የሌለው ጥፋት ማድ
ረግህ ስለሆነ በሃሳብህ እንዳትገፋበት እከለክልሃለሁ። እገፋበ
ታለሁ ብለህ የምትአመር ቢሆን ግን እራስህን በሞኝነት አስገ
ምቶ ታሪክህን ደግሞ በበደለኛነት አስመዝግቦ ለዘለዓለሞ ሲያ
ስወቅስህ የሚኖር ተግባር መፈጸምህን አውቀህ ግባበት።

“ሟቹ ወዳጅህ በሕይወቱ ሳለ የደረሰበት የፍቅር ጭቆና
አንገፍግፎት ሕይወቱን እንኳ ሳይመርጥ ሰውቶ ላንተ ለጓደኛው
ደግሞ ይህን አደራ በመሐላ አጠንክሮ ቢጥልብህም አንተ በአ
ስተያየትህ አመዛዝነህ ማሻሻልና ተግቢውን መፍረድ አለብህ።
እንዲያውም ያላንዳች ማመንታት አንተ ማድረግ የሚገባህና
ለወዳጅነትህም በቂ ምስክር ሊሆን የሚችለው ድርሰቶቹን በክ
ብር ሥፍራ አስቀምጠህ ቢቻልህም በማሳተም አራብተህ የወዳጅ
ጠላት የሆነችው የማርቼላ መራር ጭካኔ የቱን ያህል አሰቃቂ
እንደነበረ ላገር በማሳወቅ ታሪኳ ለዘለዓለም እንደተጠላና እንደ
ተሰደበ እንዲኖር ብታደርግ ነው። ይህም አደራረግህ የወዳጅህን
ሞት እንደተበቀልህለት የሚያስቆጥር ሲሆን ለመጪውም ትው
ልድ ደግሞ በተሰይም ለጐልማሳዎች መቀጣጫ ሆኖ ይህን
ከመሰለው የፍቅር ጠንቅ ከሚያስከትለው የመከራ አዘቅት
ውስጥ እንዳይጠልቁ የሚያስጠነቅቅ ምሳሌ ሆናለቸው ይኖራል።

“ታሪኩን ለማወቅ ያህል እንደሆነ እኔና ሌሎቹም እዚህ
የሚገኙት ታዛቢዎች ሁሉ በፍቅር የነደዱውና ተስፋ የቆረጠው
ወዳጅህ የሞተበትን ምክንያት በጥልቅ ተረድተነዋል። የእንተ
ንና የሱንም የጠበቀ ወዳጅነት እናውቀዋለን። ከመሞቱም በፊት
የሰጠህን ትእዛዝና ያሰማለህንም መሐላ ሰምተናል። በዚህ በሚ
ያሳዝነው ታሪክ ብርሀን የማርቼላ ጭካኔ የቱን ያህል የሚያሰቅቅ

እንደነበረ ፤ የጂሮሰሰቶሞስም ፍቅር የቱን ያህል የጋለ እንደነበረ ፤ አንተም የወዳጅህን ፍቅር በማጥበቅ ረገድ ያሳየኸው መታመንና ቁም ነገራምነት የቱን ያህል የተቀደሰ እንደሆነ በቀላሉ ለመረዳት ችለናል ። ስለዚህ የፍቅር ማዕበል ያናወጸው አዕምሮአችው የገመተውንና ትክክለኛም መስሎ የታያቸውን በመከተል ያለልንም የሚጋልቡት አንዳንድ የክንፍ ሰዎች የሚሰጡትን ትእዛዝ መፈጸም በውነቱ ታላቅ ጅልነት ነው ።

"ትናንትና የጂሮሰሰቶሞስን መሞትና በዚሁ ቀበሌ መቀበር ሰምተን ለወሬው በመጓጓት ብቻ ሳይሆን በኃዘን ስሜት ተገፋፍተን ወሬውን ከአረኞች ስንሰማ እጅግ አድርጐ ያሳዘነን ታሪክ እቦታው ላይ ተገኝተን ሁኔታውን በዓይናችን ለማየት ስንል የመንገዳችንን አቅጣጫ ትተን ወደዚህ መጣን ። ይህን በማሰብ ወዳጄ ኤምብሮጂዎ ሆይ ፤ በዚህ በጐ ስሜታችንና እንዲሁም የሚቻለን ቢሆን ወዳጅና ዘመዶቹን ለማጽናናትና የሀዘኑ ተካፋዮች ለመሆን ላደረብን ጽኑ ፍላጐት ካሣ ይሆነን ዘንድ በበኩሌ እጥብቁ የምለምንህ መልካም ፈቃድህ ሆኖ እነዚህን ድርሰቶች እንዳታቃጥላቸውና እኔም ከነሱ መካከል ጥቂቶቹን መርጨ እንድወስድ እሺ እንድትለኝ ነው" ። ካለ በኋላ የአረኛውን መልስና የተስማሚነት ፈቃድ ሳይጠብቅ እጁን ሰደደና ቅርብ ከሚገኙት ድርሰቶች አንደኛውን ጥራዝ አንስቶ ወሰደ ። አምብሮጂዎም ይህን አወሳሰድ ተመለከተና እንዲህ አለ ።

"ወንድሜ ሆይ ፤ ለፍላጐትህ የሚጠቅምህ ከሆነ ያንኑ ያነሳኸውን እንድትወስድ ፈቅጄልሀለሁ ፤ ዳሩ ግን የተቀሩት እንዳላቃጥላቸው በማለት ያቀረብህልኝን ልመና እንድፈጽም ማሰብህ ከንቱ ምኞት ነው" ፤ አለው ።

ቪባልዶም ድርሰቱ የሚለውን ለማወቅ በጣም ቸኩሎ ነበርና አንዱን ገጽ ገልጦ ሲያነብ "የብስጭት እንጉርጉሮ" የሚለውን አርእስት ተመለከተ ። አብሮጂዎም ይህን እንደሰማ እንዲህ ሲል አስረዳ ። "ጌቶቼ ሆይ ፤ በዚህ አርእስት ሥር የተጻፈው ግጥም ሚቹ ወዳጄ በመጨረሻው ጊዜ የጻፈው ነው ። ዕድለ ቢስነቱ ወደየትኛው አደጋ ላይ እንደጣለው እሱ ላይ ተጽፎ

ታግኙታላችሁ ። ካለ በኋላ ሁሉም ለመሰማት እንዲችሉ ድምጽህን ከፍ አድርግና አንብብላቸው ፤ መቸም ጉድጓዱ ተቆፍሮ እስኪያልቅ ድረስ በቂ ጊዜ ስላሳችሁ እሱን እየሰማችሁ ለመጠበቅ ትችላላችሁ አላቸው ።

ቪባልዶም "መልካም ፈቃዴ ነው አለና ለማንበብ ተዘጋጀ "እነዚያም ዙሪያውን ከብበው ንግግሩን የሚያዳምጡት ሰዎች የሁሉም ፍላጐት አንድ ዓይነት ነበርና በድርሰቱ ላይ የተገጠመውን ግላብ ለመሰማት ሲሉ አንባቢውን ከመካከል አድርገው ክባቸውን አጥብበው ቆሙ ። አንባቢውም ድምጹን ከፍ አድርጎ ቀጥሎ ያለውን ግጥም ማሰማት ጀመረ ።

ምዕራፍ 14

የሚቹ እረኛ የጂሮሶስቶሞስ የብስጭት ግጥም የሚሰማበትና ሌሎችም የትካዜ ሁኔታዎች በሰፈው የሚገለጡበት ታሪክ ።

የጂሮሶስቶሞስ እንጉርጉሮ

"አንቺ ጨካኝ አውሬ ታሪክሽ የከፋ ፣
ትፈቅጂ ይሆናል ዝናሽ እንዲሰፋፋ ።
ጐምዛዛው ችክታሽ ከራት የመረረው
ደስ ይልሽ ይሆናል ቢሰማልሽ ወሬው
ከአፍ ወዳፍ ዘምቶ ካገርም ወዳገር
በቅብብል ዘልቆ እስከ አጽናፍ ቢነገር
ያስመካሽ ይሆናል ይህ ያንቺው ድርቅና
መጠኑ ያልታወቀ ሚዛን የለው ቁና
እኔ ሳከትምልሽ ዓለም ላንቺ ቀርታ
የምታደርጊውን አዳዲስ ሁኔታ
ለመስማት ስጠብቅ ነቅቼ በርጋታ
የገሀነም እሳት የሰቃዩ ቦታ
ተሳላኪ ሆኖ የልቅሶሽን ድምጥ
ያሰማኛል ለኔ የፃርሽን ምጥ
የተከዘው ልቤም ፃርሽን ሲሰማ
ይበልሽ አበጀ እያለ በዜማ
ምስጋና ያቀርባል ምንም ሳያቅማማ
ስሜቱን ይገልጣል የበቀሉን መንፈስ
አንቺን ለማሳረር እስከቻለ ድረስ ።
ጉሮሮዬ ዝጉ ድምጼ ቢጐረንን
ልሳኔም ቢዘጋ ትንፋሼም ቢታፈን
ለሚዜም አይሰንፍም የደስታ ዘፈን ።

የኔን ሕማምና ያንቺንም መከራ
ለአድማጮች ሊናገር ለሰሚም ሊያወራ

የጂሮሶስቶሞስ እንጉርጉሮ ይቀጥላል

"ከሚበረታታው ፍላጐቴ ጋራ
ትክክል ጐልምሶ አብሮ የሚንጠራራ
ያስደንጋጩ ድምጼ ነጐድጓድ ጩኸት
መሆኑን እወቂው የመብረቅ መዓት ።
በደሌን ስናገር በበለጠ ቁጣ
ያልታደለው ልቤን ሰንጥቆት ሲወጣ
ነበልባል ቃጠሎ ሆኖ እየነደደ
ባንች ላይ ይወርዳል እየተጐረደ ።
እንግዲህ አድምጪኝ ጀሮሽን አንቂና
ነገር ግን አይደለም የደስታ ቃና
ይቅርታን የሚሰጥ አንቺን የሚያጽናና
እርግማን እንጂ ነው ሳደረግሺው ከሀዲት
ተገዶ የወጣው ከከሰለው ደረት
የኔን መቁሰልና ያንቺን አቁሳይነት
አፍርጦ የሚናገር መስክሮ በውነት
የኔው እሪታ ነው የጭንቄ እንፋሎት ።
ምሳሌ ስሰጥሽ ምንም ሳላሳስት
ተወዘቺ እንግዲህ በልቤ ፍም እሳት
የአራዊታት ንጉሥ የአንበሳው ግሣት
የከፉይቱ ተኩላ አስደንጋጩ ጩኸት
የእባብ ሰለክላካው የሚቀፈው ፉጨት
የሚያስፈራው ጭራቅ ዘግናኙ ማቅራራት
የነደቢሱ ወፍ የቁራ ማሟረት
ያልታመነው ባህር ያነሳው ማዕበል
ሁከቱ ጸጥ እንዲል ከነፋስ ሲታገል
በኃይል የሚሰማው የሞገድ ጅውታ
ተሸናፊው ኩርማ ሲያንራ በማታ
ከአውራ ተነጥላ ብቻዋን የቀረች
ዕርግብ ስታላዝን እየተማረረች

ያልቀናው ጉጉትም በብስጭት ዜማ
የተመቀኙትን አማርሮ ሲያስማ

የጂሮሶስቶሞስ እንጉርጉሮ ይቀጥላል ፥

"በገሀነም እሳት ገብተው የታጐሩት
የጥቁር ሰይጣናት ዋይታና ጩኸት
የነፍሴን መንሰቅሰቅ ለቅሶና ትካዜ
እነዚህ ያድቡት ያድምቁት በባዜ
ሰሚን ግራ ይግባው ጆሮዎቹ ይደንቁሩ
ድበልቅልቅ ያድርጉት ይሸበር አገሩ
ጤና የነሳኝን መርዘኛ ቁስል
ሰዎች እንዲያውቁልኝ ለማሳየት ስል
አዲስ ዘዴ ሰሻ ያንጋገር ፈሊጥ
ጭንቄን መከራዬን አሳሬን የሚገልጥ
ይህ ነው የመረጥሁት ከሁሉ የሚበልጥ ።
የአባ ታጐ አሸዋ የበረሃው ወገን
ወይም ስመጥሩው የቤቱ ወይራ ደን (ሰፊ
ይሆን የመሰለ ድብልቅልቅ ሙሽት
የገደል ማሚቶ ቢያስተጋባለት
ለመስማት አይችልም ምንም ቢሆን ከቶ
ዋይታው ቢበዛ ጩኸቱ በርክቶ ።
ተስፋ ቢስ የሆነው ይህ የኔ ስቃይ
በአሸዋው ክምር ውስጥ በአናቱ ላይ
ወይም በጠሊቁ አረንጓ ውስጥ ገብቶ
ተመጥጦ ቢቀርም እልም ብሎ በክቶ
በሞተች ምላሴ የተናገርኩት ቃል
በአየር እየዋኘ እንዲህ አለ ሲባል
ድምጼ ሕያው ሆኖ ዘላለም ይኖራል ።
ወይም ደግሞ እንዲሁ ይዝው ድምጼ ዘልቆ
በደረቁ ሜዳ በችፍግ ሸለቆ
ጭው ባለው በረሀ በሚያስፈራው ዱር
የዱካ ምልክት ወይም የሰው ዘር

የጂሮሶስቶሞስ እንጉርጉሮ ይቀጥላል ፤

ፈጭራሽ በሌለበት ምድረ በዳ ውስጥ
ፀሐይም ብርሃኗን ምን ጊዜም ሳትሰጥ
ጨለማ ነግሦበት በሚቀፈው ሥፍራ
ወይም በነጭ አባይ ሜዳና ተራራ

በመርዘኛ አራዊት መኖሪያ መካከል
በዱር በደገላው በጅረት በገደል
እየተላለፈ ሲሰማ እንደደወል

ማጣራት ያልቻለው ደንቆሮው ማሚቶ
የሕመሜን ጩኸት ስልቱን አስተጋብቶ
በተቻለው መጠን አበጥሮ ቃኙት
ምንኛን ጨካኝነት ምክንያቱን አጉልቶ

መላልሶ ያሰማል ያሳሬን ስሞታ
ላጭሩ ሕይወቴ እንዲሆን ውለታ
እስከ አጽናፍ ተዳርሶ በሠፈው ምድር
ሲያስታውስ ይኖራል የኔን ብርቱ ግር ።
ንቀትም ይገድላል ልብን በማሸፈት
መጠራጠር ደግሞ በውኑት ወይም ባሰት
እስኪጣራ ድረስ ያስጨርሳል ትእግሥት
ቅናትም እንዲሁ አንጐልን አናውጦ
ልብን አኩማትሮ መንፈስን በጥብጦ
አፍርሶ ይገድላል በበዛ ጭካኔ
ይቅርታ የለውም የሚያስታግስ መጥኔ

ተለያይቶም መኖር ለረዘመ ርቀት
ነፍስን ያስጨንቃል ወጥሮ በናፍቆት
የመረሳሳትም ፍራቻና ሥጋት
ሰቀቀን በመሆን ከሴት እስከ ንጋት
ጸጥታ እየነሳ በቅዠት ማስዋንት
ሥራው ስለሆነ የጠባዩ ዓይነት
የተሻለ ዕድል በቶሎ ለማግኘት
ተስፋን የሚያጽናና አይሆንም ደጋፊ
ያባብሳል እንጂ እየሆነ ገፊ ።

የጂሮሶስቶሞስ እንጉርጉሮ ይቀጥላል ፤

«ይህ ሁሉ መጥፎ እጣ ተከማችቶ አንድነት
ከቶ የማይቀረውን እርግጠኛውን ሞት
ያመጣል በራስ ላይ ጐትቶ በገመድ
ማንም እያስጥለው ወዳጅ ወይም ዘመድ ።
እኔ ያልታደልኩት አግረኛውን ግን
በቅናት ፥ በርቀት ፥ በንቀት ፥ ስበግን
ለሚገድለኝ ጠላት ለልብ ጥርጣሬ
ዓላማ ሆኜለት በመነጣጠሬ
መመከት አቅቶኝ ዝቡ ተግትሬ
ናላዬ ተናውጦ ባሳብ ተወጥሬ
ዕድሌን ስጠብቅ ከነገ ከዛሬ
ለሞት ዝግጁ ሆኜ በመኖሬ
እነሆ አገኘሁ የጠበቅሁትን
እንቺም ደስ ይበልሽ ስታውቂው ሞቴን ።
በሕይወቴ ሳለሁ ተነቅፌ ብጣል
የልቤ ፍም እሳት በመንደድ ሲቃጠል
በብዙ ስቃዮች በጭንቅም መካከል
የኔው እስተያየት የተስፋዬም ጥላ
ሸሽቶኝ ስለሄደ አጋልጦኝ ከኋላ
ላየው ሳልችል ቀረሁ ብሮጥ በችካላ ።
እኔም በበኩሌ በመቁረጤ ተስፋ
ምንም አልፈለገው ላየውም አልሰፋ
እንዲያውም ጭራሹን በሕመሜ ውስጥ
በውል ለመዘፈቅ ቆርጬ ስሮጥ
ተስፋን ለዘላለም ለመሸሽ አጥብቄ
ተነሳስቻለሁ አምርሬ ታጥቄ ።
ኧረ ለመሆኑ ምናልባት ተሳምዶ
ባለተስፋ መሆን ወይም በቁርጥ ከዶ መቁረጥ

የጂሮሶስቶሞስ እንጉርጉሮ ይቀጥላል ፥

«ሁሉንም ባንድ ጊዜ ማድረግ ይቻላል?
እኔስ አይመስለኝም አላምንም በውል ።

ወይስ ደግሞ እንዲሁ የመቁረጡ ምክንያት
ይበልጥ ተረጋግጦ ሲሆን የሚያምኑበት
በዚያን ጊዜ ማድረግ ይሻል ይሆን ይሆን?
እንጃ ግራ ገባኝ በዚህም አኳኋን ።
የሚያሳርር ቅናት ከፊቴ ሲደቀን
እሱን እንዳላየው አይኔን ለመጨፈን
እንዴት እችላለሁ ይህን ላደርገው
በነፍስያዬ ላይ በተከፈተው
ከሺህ ቦታ ቆስሎ በተነደለው
በኩል አሾልኬ በአኳያው ሳየው ።
አብሻቂ ሁኔታ በጉልህ እያየ
የመናቅን ውርደት ሁሉ እየገበየ
ሥውር ጥርጣሬ በልቡ እየጋየ
አወይ ክፉ እድል መራራ ሥውር
ግራ የሚያጋባ የሚያደናግር
ሐቁ አደራረግ ንጹሁ ዕውነት
ተለውጦ ሲገኝ ተውጦ ባሰት
ኧረ ማነው ደፋር መካች ፊት ለፊት
ወሰን ባልተሰጠው ጠንካራ ትእግሥት
በሩን ላቶ ክህደት ፈጥኖ የማይከፍት?
ቅናት ሆይ ጨካኙ አረመኔው ነብር
በፍቅር ግዛት ውስጥ አምጸህ የምትኖር
እባክህን ስጠኝ ጩቤህን መዘህ
ወይም ገመድ ስጠኝ አትንፈግ አይዘህ
የልብህ እንዲደርስ ደስም እንዲልህ
ነገር ግን ወየውሌ በጨካኝነት ድል
ያንተው መታሰቢያ የኔውም መበደል

የጂሮሶስቶሞስ እንጉርጉሮ ይቀጥላል ፥

«አንዱን ሴላው በልጦት ተረቺው ታግቶ
ተሸንፎ ይቀራል ተደምስሶ ጠፍቶ
ከኔው ጋር አንድነት እመቃብር ገብቶ ።
እንግዲህ ላርፍ ነኝ ሞቼ ነፍሴ አልፋ
በሞት ወይም በሕይወት የደስታ ተስፋ

ምን ጊዜም ሳይኖረኝ እስከ ዘላለም
እንደማታ ጥላ እንደሌሊት ሕልም
እንደ ትኩስ ወረት እንደ ቀላጭ ስም
ብኩን ምኞት ሆኖ ይበተን የትም
ያፈቀርኩበት ቀን ሰዓቱ ይረገም ።

እንግዲህ የምለው አውጥቼ አውርጄ
ለማፍቀርም ምክንያት እንዳለው ፈርጄ
ዛሬ ተገላግላ ነጻ የወጣች ነፍስ
ለጨካኝ ጠላቷ ለፍቅር ስታለቅስ
ይራራል በማለት በተስፋ እየለፋች
ተረግጣ ተገዝታ ባሪያ ሆና ኖረች ።

ያቺ የዘወትሯ ገዳዬ ጉበል
ነፍሷም እጅግ ውብ ናት እንደአካሏ ምስል
ከሀሳቤ ጋራ አለመግባባታ
ጥፋቱ የኔ ነው በሁሉም ሁኔታ
መርጫለሁና ሞትን በቀጥታ

እንዲህ በመሆኑ ጥፋትን ወርሼ
ከዚህ ዓለም ስቃይ ጣጣዬን ጨርሼ
ዳግመኛ ላልመጣ መቸም ተመልሼ
ለስንብት ስሄድ ቸኩዬ በብርቱ
ፍቅር በዚህ ሰላም በሆነው ግዛቱ
የሚያውከው ላይኖር ጸጥታ ማግኘቱ
ታላቅ እረፍቱ ነው ሥጋት የሌለበት
ባላጋራው እኔ ከተወገድኩለት ።

<u>የጂሮሶስቶሞስ እንጉርጉሮ ይቀጥላል ፥</u>

አጉራ ጠናኝ ብዬ በዚህ መረታቴ
የገመድ ማተቤን አግብቼ ባንገቴ
ያለማወላወል ሽምቅቂ በጣቴ
የእልፈቴን ሰዓት በቶሎ አጣድፌ
ጻሬን ሳላበዛ ፈጥኜ አልፌ
ለክርሳሙ መሬት ሥጋዬን ጋብገር
ባንጄ ስጠፋ እንደጉም ተጉገር
በፈቃዴ እንጂ ነው አይደለም ታዝገር ።

ለመጨውም ዘመን ክብርና ምስጋና
ለስሚ መጠሪያ ለታሪኬም ዜና
ፍቅርን ድል ለመንሳት ሳይኖረኝ እድል
በረቂቅ መሣሪያው ልቤን ሲነድል
መድኃኒት አጥቼ ለመከላከል
ከዚህ መጥፎ አደጋ ለመገላገል
አስገዳጅ ሳይኖረኝ እራሴን ስገድል
የስሪቴ ጉንጉን የዘንባባ አክሊል
በራሴ ላልደፋ በቁም ሳልታጀብ
እንዲቦጫጭቀው በድኔን ተኩላና ጅብ
መርጨ ነበረ ምስጢራን ሰውሬ
ጭራሽ እንዳታየኝ ያቺ ጨካኝ አውሬ

ይህም ሳይሆን ቢቀር ምናምንቴ ሆኜ
ማለቅ ይገባኛል እንደ ጢስ በንጄ ።
አንቺ ግን ክፉይቱ ባየለ ጭካኔ
ሕይወቴን ለማጥፋት ምክንያት ሆኖ ለኔ
የሚያስገድደኝን እራሴን ለመግደል
እጅግ አያበዛሽ የሠራሽኝ በደል
በጣም አስመርሮ አሳጣኝ መድረሻ
መታገሥ አቃተኝ እስከ መጨረሻ
የቆሰለው ልቤ ጤና ስለነሳኝ
ሕይወቴን ለማጥፋት ምንም አላሳሳኝ

<u>የጂሮሶስቶሞስ እንጉርጉሮ ይቀጥላል ፥</u>

« የልቤ አቆሳሰል ሆኖ ምስክር
በቀስትሽ ተወግቶ ደሙ ሲነዝር
የቆምኩብት መሬት ጨቅይቶ ነበር
አንቺ ግን ከደሽው በመከራከር
ሐሰት ነው ትያለሽ ይህንን ነገር
ማን ይሚነትሻል ከማመን በቀር ።
ይህን ልተውና የኔን ጉዳት ላውጋ
በጭካኔሽ ምክንያት ላገኘኝ አደጋ
በደስታ ስክፍል ይህን የደም ዋጋ

ይገባዋል ስትይ ምናልባት መዘነሽ
ብትመለከችኝ በርሀራሄ አስተውለሽ
ጸጸት ቢማርክሽ ሕሊና ቢወቅስሽ
በኔ መሞት ምክንያት ዓይኖችሽ ቢያለቅሱ
በደም እንባ አብጠው ለመፍረጥ ቢደርሱ
በሕልምሽ መጥቼ መንፈስሽ ቢታወክ
ሰውነትሽ ቢርድ ልብሽ ቢብረከረክ
ለማልጠቀመው የስግይ እንግዳ
ከእንግዲህ አልሻም ካሳ ካንቺ ዘንዳ
ተይው እንዳትገቢ ለኔ ብለሽ ዕዳ ።

ነፍሴ ያንቺ ግዳይ ሆና እንድትቀር
ፈርጀባታለሁ ሳልፈራና ሳልቸር
ደስ አይልሽምና ይህ ካልሆነ በቀር
እንዲያውም ይግረምሽ የቀብሬ ሥርዓት
በሚፈጸምበት ልክ በዚያን ሰዓት
ጨፍሪ ዝፈኚ ተቀቢ ተኳይ
እስክስታ ውረጂ ፈንድቂ እልል በይ ·

ይህን ስታደርጊ አይቶ የታዘበሽ
ጠላትሽም ቢሆን ወይም ደግሞ ወዳጅሽ
ለጭፋሮሽና ለፈገግታው ሳቅሽ
ላደረብሽ ስሜት የሚሰጠው ትርጉም
መሆንሽን ይገልጣል ልበ ክፉ እርጉም ።

የጂሮሶስቶሞስ እንጉርጉሮ ይቀጥላል ፥

«በደረሰ ቁጥር የዘመን አውዳመት
የደስታ በዓል ሆኖሽ የኔ መሞት
ዝክሩን እያከበረሽ በየድግስሽ ዕለት
እንድትደሰቺ አመኛለሁ በውነት ።

ይህን ምክር ሳንቺ መስጠት ባይገባም
ምክንያቱን ልንገርሽ ስሚኝ አንቺ ተርባም
ሕይወቴ ተፋጥኖ ፍጻሜ እንዲያገኝ
የምትጠብቂው ዋናው የፍርድ ይግባኝ

መሆኑን አውቃለሁ በርግጥ አሳምሬ
መቸም ቸኩለሻል አንቺ ጨካኝ አውሬ
ቶሎ ለመጠቀም በሚጠፋው ክብሬ
ወዶ አብዶ ሞተ ብለሽ በማዋራት
አገር እንዲያውቅልሽ ዝናሽን ለማኩራት
ዓላማሽ ይኸው ነው የክቡ እምብርት
ሄዶ የሚወጋው የደገንሽው ቀስት
እንግዲህ ቶሎ ይምጣ ደርሷልና ያወቅት
ታንታሎ ከሲኦል ከእንጦርጦስ አዘቅት
በርሀብ ተንገብግቦ አፉን ይክፈትና
ተረክቦ ይዋጣት ነፍሴን ከደመና ።
ሲሲፎም ይከተል በደፍጣጭ ከባዱ
ታንታሎ ሳይውጣት ሳያገባት ሆዱ
ነጥቆ በመንጠል ያገኘውን ብልት
አድቅቆ እንዲፈጨው በከራንቻው ሹለት
ቲሲዩም ጆቢራውን ይዞ እየመራ
ኢሲዩኔም እንዲሁ ዓይኑን እያበራ
መኩራኩር እግሩን እያንከባለለ
ቅርጫ እንዳያመልጠው ጥርሱን እንዳጋለ
ገፍቶ እያዳፋ ቅደሚ እያለ
የዘላለም ድካም ሥቃይ ተቀባዮች
የሆኑትን አምላ እህትማማቾች

የጂሮሶስቶሞስ እንጉርጉሮ ይቀጥላል ፥

« አሰልፎ ይጠብቅ ነፍሴን ለመቀበል
ተቀራምቶው ይብሏት በደራጉን በቀል
ሁሉም ተሰብስበው አንድነት በብዛት
ቡጭቅጭቅ አድርገው ቆርሰው ይካፈሏት ።
አስጨንቆ ገዳይ የሥቃይ ፃዕረ ሞት
ይግባና ከልቤ አርፎ ይቀመጥበት ።
ተሰፋ በቆረጠ መንፈስ ተሰባብሮ
በትካዜ ዶማ ልቡ ተቆፍሮ
በፍቅር አለንጋ ተገርፎ ለደማ
በነጣቂ ጠላት ነፍሱ ለተቀማ

ፍትሐት ይገባዋል ተብሎ ቢፈረድ
በፈሳዱ ዙሪያ ዘፈን ይረገድ
በለዘብታ ሙሾ በለስላሳ ዜማ
ይነበብ ግንዘቱ ጮልቶ ሳይሰማ ።

ይህም ይሁን ተብሎ ቢደረግ ምናልባት
አንዲት ቁራጭ ከፈን ተነፍጐ ያላባት
ወድቆ የሚቀረው የተጣለው በድኔ
ማንንም እንዳይወቅስ ገዝቼአለሁ እኔ

የገሃነም እሳት ጠባቂው በረኛ
ባለሦስት ጭንቅላት ቀላፊው መጋኛ
አንድ ሺህ ከይሲዎች አንድ ሺህ ጋኔኖች
ነባር ጭፍራዎቹን ቀና ተከታዮች
በሰልፍ ተራ አግብቶ ሁሉን በማንጋጋት
ነፍሴን አስጨንቀው በሃዘን ያጅቧት ።

መቸም ቢሆን ሕጉ ጥንቱን ሲመሠረት
በፍቅር ተነድፎ በጠንቁ ለሚሞት
ከዚህ የተሻለ የመቃብር ሥርዓት
የሚቻል አይመስልም የሚፈጸምለት ።

የጂሮሰስቶሞስ እንጉርጉሮ ይቀጥላል ፣

እስካሁን የኖርከው አብረኸኝ ሳትለይ
«የብስጭት ግጥም» ወዳጄ ልቤ ሆይ
እንግዲህ ልምከርህ ስማኝና ልመት
ከዚህ ካስተካዙ ከኔ ንደኝነት
ስትነጠል በግድ ተግንጥለህ ስትቀር
በለቅሶ አትንሰቅሰቅ አይዘህ በርታ ድፊር ።

እንዲያውም ልንገርህ አንተ እንደትፈጠር
ያደረገችው ሴት ሃሳቢ ሲጀመር
የኔ አለመታደል እየከፋ ሲብስ
የኒ ደስታ ግን ፋፍቶ በመታደስ
ይበልጥ እየጐላ የሚያስፈነድቅ
እንዲሆን ጥረቷ መሆኑን እወቅ ።

ስለዚህ የምልህ አሁንም ደግሚ
በመቃብሬ ላይ ብትሆንም ወንድሜ
ፊትህ ፈገግ ይበል ይጽናና ልብህ
የተካሸነት መልክ አይታይብህ ።

የሚለው ድርሰት ተነብቦ ተፈጸመ ።

ይሆን የጂሮሰስቶሞስን እንጉርጉሮ ሲያዳምጡ የነበሩትም ሰዎች ሁሉ የስሜቱ አገላለጥ አስደስቷቸው ነበር ። እንባቢው እንደሚለው ግን ይህ በግጥሙ ላይ የጐረፈው ወቀሳ ስለ ማርቼላ ጠባይ ጭምትነትና ስለአብነቷ በሴሎች ሰዎች ዘንድ ሲወራ ከተሰማው ዝናዋ ጋር ሲተያይ በጭራሽ የሚመሳሰል አይደ ለም ፣ ምክንያቱም በዚህ እንጉርጉሮው ውስጥ ጂሮሰስቶሞስ የገለ ጠው የብስጭት ስሜት ስለቅናት ፣ ስለጥርጣሬ ፣ ስለ መራራቅ ፣ መበደሉን ስለሆነ ፤ ይህ ሁሉ ብስጭቱ ማርቼላ የገበየችውን መል ካም ስምና መልካም ዝና ዝቅ አድርጐ የሚያስገምትባት ሊሆን አይችልም በማለት የግል ትችቱን አስማ ። አምብሮጂዬም የባ ልንጀራውን የጠበቀ ልባዊ ምስጢር ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነበርና እንዲህ ሲል ለትችቱ መልሱን ሰጠ ።

« የተከበራችሁ ጌቶቼ ሆይ ፣ ይህ አሁን የሰማችሁት የግ ጥም ድርሰት በውነት የሆነ ነገር መሆኑን እምናችሁ ያደረባች ሁን ጥርጣሬ ለማስወገድ ትችሉ ዘንድ ያልታደለውና አሳረኛው ወዳጄ ይህን ድርሰት የጻፈው ከማርቼላ እርቆ በሚኝበት ጊዜ መሆኑን ብታውቁት እወዳለሁ ። በገዛ ፈቃዱ የራቀበትም ምክን ያት ምናልባት ይህ ከሷ ርቆ መኖሩ የተሰመደውን የማስረ ሳት ጠባይ ሊፈጥርበት ይችል እንደሆነ ለማየት ነበር ። መቸም ርቆ የሚኖር አፍቃሪ በናፍቆት የሚያስጨንቀው ትዝ ታና በቅናትም የሚያንገበግበው መጠራጠር ሊደርስበት መቻሉ የማይቀር ነገር ስለሆነ ጂሮሰስቶሞስንም የሚታሰብ ቅናትና የሚ ያስፈራ ጥርጣሬ እውነት እንደሆነ ያህል በትውስታው እየተደ ቀነ ይጐጠጠው ነበር ። ስለዚህ በማርቼላ አብነት ላይ የታ ወጀው የስመ ጥሩነት ዝና እውነተኛነቱ ከዚህ ከሰማችሁት ድር ሰት ጋር የተያያዘ ነው ። ይህም ሲሆን ከጨካኝነቷ በስተቀር

ጥቂት ትዕቢተኛና በጣምም ሰው ናቂ በመሆኑ ይህ የሚመ
ቀኙት ባህሪዋ ከዚህ እልፍ ያለ ሌላ ዓይነት ስሜትና ጠባይ
ሊኖረው የሚችል አይደለም ።

«እንግዲያውስ ይህ ከሆነ እውነት ሊሆን ይችላል» ሲል
ቪቫልዶ መለሰ ፥ ቀጥሎም ከዚያ ከመቃጠል ካተረፋቸው ወረ
ቀቶች ውስጥ ሁለተኛውን ቅጠል ለማንበብ ሲዘጋጅ በአንድ
አስደናቂ በሆነ ትርኢት ተጸረጠ ፥/ በእርግጥም አስደናቂነቱ እንደ
ተአምር የሚቆጠር ነበር/ ወዲያውኑ ይህ ትርኢት ለአስተያየቱ
ተከሰተለት ።

ከግርጌው መቃብሩ ከሚቆፈርበት ካንዲት ኮረብታ ጫፍ
ላይ እረኛይቱ ማርቼላ ብቅ ብላ በታየች ጊዜ የመልኳ ማማር
እጅግ አድርጐ የሚያስደነግጥ ስለነበረ ይኸው ውበቷ የተወራ
ውን ዝናዋን በጣም ልቆ የሚበልጠው ሆኖ ተገኘ ። በመቃብሩ
ሥፍራ ከተሰበሰቡትም ካሁን ቀደም አይተዋት ከማያውቋት
ሰዎች መካከል የመደነቃቸው ብዛት በዝምታ ፈዝዘው ያስተ
ውሷት ጀመር ። እነዚያ ዘወትር ሊያይዋት የከረሙትም ቢሆኑ
ካሳይዋት ሰዎች ባላነሰ መገረም ማስተዋላቸውን አልተውም
ነበር ። ዳሩ ግን አምብሮጂዎ የሚባለው እንደተመለከታት ወዲ
ያውኑ ግልጥ በሆነ መቀየም እንዲህ ሲል ተናገራት ።

«የነዚህ ተራራዎች ባለቤት የሆንሺው አንቺ ክቡይቱ ገበሎ
ሆይ! አሁን የመጣሽው ምናልባት ያንቺ እዚህ መገኘት ከዚህ
ካልታደለው ሚች ቁስል ውስጥ ትኩስ ደም የሚንቆረቆር መሆ
ኑን ለማየት ነውን? ወይስ የማይዳኘው ጠባይሽና የጨካኝነት
ተግባርሽ ባስገኘው ውጤት የተሰማሽን ደስታና ኩራት ለመግ
ለጽ ነውን የመጣሽው? ወይስ ደግሞ እዚህ ኮረብታ ላይ
ቆመሽ እንደ እርህራሄ ቢሱ ኔሮን ዳግማዊት ሆነሽ የሮማሽን
የቃጠሎ ነበልባል ለማየት ነውን? ወይም ውለታቢሷ ልጅ በአ
ባቷ በታርኲይኖ በድን ላይ እንዳደረገችው ሁሉ አንቺም ይህን
ያልታደለውን በድን በጭካኔ ለመረጋገጥ ነውን፡ አይዞሽ! ተበ
ረታችና የመጣሽበትን ምክንያትና ፍላጐትሽም ምን እንደሆነ
ተናገሪ ። የጂሮሶስ ቶሞስም ሐሳብ በሕይወቱ ሳለ ያንቺን ፈቃድ
ለመፈጸም ምን ጊዜም ያልቦዘነ መሆኑን እኔም እራሴ አሳምሬ

ስለማውቀው ዛሬ ሞቶ ቢለየንም ወዳጆቹ ተብለን የምንጠራው
ሰዎች ሁሉ የምትሰጪውን ትእዛዝ ስለእርሱ ሆነን ለመቀበል
ዝግጁዎች በመሆናችን ፍላጐትሽን ከመግለጥ አትዘግይ» ብሎ
ንግግሩን ጨረሰ ።

«አምብሮጂዎ ሆይ! እኔ እዚህ የመጣሁበት ዋናው ምክ
ንያት አሁን አንተ ከተናገርካቸው ውስጥ አንደኛቸውንም ግፍ
ለማድረግ አይደለም» ስትል ማርቼላ መልሷን መስጠት ጀመረች።

«የኔ አመጣጥ ግን ስለጂሮሶስ ቶሞስ መሰቅየትና መሞት
እኔን በደለኛ አድርገው ስሜን በክፉ የሚያነሱትን ሰዎች ሁሉ
ለማስተባበልና በእምነታቸውም እጅግ የተሳሳቱ መሆናቸውን
አስረድቼ ተከላክዬ እራሴን ከደሙ ንጹሕ ለማድረግ ብቻ ነው ።
መቸም ቢሆን ትክክለኛ አእምሮ ላላቸው ሰዎች ሁሉ እውነትን
ቁልጭ አድርጐ ለማስረዳት ብዙ ጊዜና ብዙም ቃላት የማይ
ፈጅ ስለሆነ እዚህ ያሳችሁት ሰዎች ሁሉ የማስረዳችሁን እንድ
ትአዳምጡኝ አጥብቄ እለምናችኋለሁ ።

«እናንተው እራሳችሁ መስክራችሁ እንደተናገራችሁት ሁሉ
በዚህ ዓለም ላይ ቆንጆ ሆኜ ተፈጥሬአለሁ፤ይህም ቁንጅናዬ ያለ
መጠን ያስደነቀ በመሆኑ ምክንያት አይታችሁ ለመተው በማ
ትችሉበት አካኋን እንድትአፈቅሩኝ ባልታወቀ ኃይል ተገድዳ
ችኋል ። እናንተ በቁንጅናዬ ብርቅነት ተገድዳችሁ ለገለማችሁ
ልኝ የፍቅር ስሜት እኔ ደግሞ ለውጡን እናንተን በማፍቀር እን
ድመልስ መገደድ እንደሚገባኝ የምትጠይቁ ሆናችኋል ።

ግሌ የትውልድ አጋጣሚ ሆኖ በተሰጠኝ ያልተፈጥሮ ብል
ህነቴ እንደማውቀው ማናቸውም የተዋበ ነገር ሁሉ በሕላዊ የመ
ውደድ ስጦታ እንዳለው አረጋግጣለሁ ። ይሁን እንጂ በውበቱ
ማራኪነት መወደድን ያገኘው ነገር ሁሉ ሲፈጠር ተወዳጅ
በመሆኑ ብቻ ለተቀባው የመወደድ ፀጋ ብድሩን በመውደድ
እንዲመልስ የሚገደድበት ምክንያት ከቶ ሊገባኝ አልቻለም ። አብዛ
ኛውን ጊዜ እንደሚደርሰው ያ ውበትን የወደደው ሰው ምና
ልባት መልክ ጥፉ ቢሆን ኖሮ መቸም አስቀያሚ የሆነው ሁሉ
የመጠላት እድል ስላለው «አንቺ ቆንጆ በመሆንሽ አፈቀርኩሽ

እኔ ግን ምንም መልክ ጥፉ ብሆን ልታፈቅረኝ ይገባሻል» ብሎ የሚጠይቅ ሰው ቢኖር በእውነቱ መጥፎ አነጋገር በሆነ ነበር።

ከዚህም በስተቀር ተመሳሳይ ቁንጅና ያላቸውም ሰዎች ቢሆኑም እንኳ በዚህ ምክንያት ብቻ የመፈቀር ዝንባሌያቸው እጣ ክፍላቸው እኩል ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም አንዳንዱ ቁንጅና ላይን ሲያስደስት ፍላጐትን የማይማርክ ሆኖ ስለሚገኝ የሚታዩት ቁንጅናዎች ሁሉ ከፍቅር ላይ የሚጥሉ ስላልሆኑ ነው።

ቁንጅናዎች ሁሉ ፍቅር ላይ የሚጥሉና ፍላጐትን የሚማርኩ ቢሆኑ ኖሮ የሰው ሁሉ ፍላጐት በየትኛው ቁንጅና ላይ ቀልቡን ለማሳረፍ እንደሚችል ቅጡ ጠፍቶት የሚጨባጠውን በማጣት የተሳከረና የባዘነ ይሆን ነበር። ምክንያቱም ቁንጅናዎች የበዙትን ያህል ፍላጐቶችም ያንኑ ያህል የበዙ ስለሚሆኑ ነው። በዚህ ሁኔታ አስገዳጅነት በተፈጥሮ ሕግ ውስጥ የመፋቀር መንፈስ በሥውር ጥምድ ተደንግጐ የሚገኝ ሆኗል። እኔም በእድሜ ከበሰሉት ሰዎች አነጋገር እንደሰማሁት እውነተኛና ዘላቂ ፍቅር ሊሆን የሚችለው የጋራ ፍቅር ሲሆንና ያላንዳች አስገዳጅ ነገር በውዴታ ፈቃድ የተቀበሉት ሲሆን ብቻ ነው ይላሉ።

ይህን አስተያየት የምታምኑበት ከሆናችሁ እናንተ እንደ ምትሉት እኔን ስለቁንጅናዬ በመውደዳችሁ ምክንያት እኔ ደግሞ ያለውዴታዬ ፍላጐቴን ለፈቃዳችሁ እንዳስገዛ የምትአስገድዱኝ ስለምን ነው? አስቲ ላስፈርዳችሁ። በዚህ ዓለም ላይ ቆንጆ ሆኜ እንድታይ የሠራኝ አምላክ ምናልባት መልክ ጥፉ እድርጐ ሠርቶኝ ቢሆን ኖሮ እናንተ ሳታፈቅሩኝ ቀራችሁ ብዬ ባማርርባችሁ ትክክለኛ ምክንያት ይኖረኝ ነበርን? በሌላ በኩል ደግሞ ልትአመዛዝኑት የሚገባችሁ ጉዳይ አለ፣ ይህን የእን ቁንጅና እኔ እራሴ ጠይቄና ለምኜ ወይም ተሻምቼ ያገኘሁት? አይ ደለም። ነገር ግን እንደዚሁ እንደምታዩኝ እኔ ሳልጠይቅና ሳልመርጥ የጊዜው ታሪክ በፈቃዱ ይሁን ብሎ በፀጋው የሰጠኝ መሆኑን ነው። ስለዚህ እባብ ነድፉ እንድትገድል ተፈጥሮ በሰጣት

የመርዝ መሣሪያዋ ልትወቀስበት የማይገባትን ያህል እኔም በቁንጅናዬ ምክንያት ጉዳት ባስከትል በደለኛ ሆኜ ልወቀስ የማይገኝ መሆኔን አረጋግጥላችኋለሁ። የጨዋ ሴት ቁንጅና እንደ ሩቅ እሳትና እንደተላለ ሠይፍ የሚቆጠር ነው። ያልቀረበውን አይሰይፍም። ያልደረሰበትን አይፈጅም። ክብርና ኩሩነት የነፍስ ጌጦች ናቸው፣ እነዚህ ያልኖሩት አካል ቆንጆም ቢሆን መስሎ ሊታይ አይበቃም። እንግዲህ የሰው ልጅ ጨዋነት አካላቱንና ነፍሱን ከሚያስጌጡትና ከሚያሳምሩት አብነቶች አንዱ ሲሆን አንዲት ቆንጆ ሴት በቁንጅናዋ ምክንያት በመወደዷ ብቻ ስሜቷ ሳያዘንብል የግል ደስታውን ለመሙላት ሲል ባለው ኃይልና ባለው ጥበብ ክብሯንና ጨዋነቷን ለመጣፈፍ የሚደክመውን ሰው ፍላጐት ለመፈጸም ስትል መብቷን መስዋዕት ማድረግ ይገባታልን?።

ይህ ከቶ የማይደረግ መከራ ነው። እኔ ወትሮም ስወለድ ነፃ ሆኜ ስለሆነ ይህንኑ ነፃነቴን ለማንም ሳላስነካ ለመኖር እንድችል ይህን ሞር ያለ ኑሮ የሚገኝበት ቀበሌ መርጬ መጥቼአለሁ። እነዚህ ተራራዎች ያበቀሏቸው ዛፎች ጓደኞቼ ናቸው። የነዚህ ወንዞች የጠሩ ውሃዎች መስታወቶቼ ናቸው። ምስጠራን የማካፍላቸውና ቁንጅናዬንም የምጋብዛቸው ለዛፎችና ለወንዞቼ ብቻ ነው። እኔ የሩቅ እሳትና የተሳልኩ ሰይፍ ነኝ። በቁንጅናዬ ተማርከው ያፈቀሩኝን ሰዎች ሁሉ በተናገርኳቸው ቃል ተሰፋ አስቆርጬ አግልያቸዋለሁ። እንግዲህ የሰው ፍላጐት ሁሉ ተሰፋን እየተመገበ የሚኖር የነፋስ መታወቂያ ስልቻ ከሆነና ከኔ በኩል ለጂሮሰስ ቶሞስም ሆነ ለሌሎቹ እረኞች አንዳችም ተሰፋ ሳልሰጥ በቁርጠኛ ቃሌ ፀንቼ ስገኝ በመካከሉ ይህን የመሰለ የሞት አደጋ ቢደርስና ወደፊትም ቢቀጥል የሚሞቱትን ሰዎች ሁሉ የሚገድሳቸው ከኔ መጨከን ይልቅ የገዛ እራሳቸው በተሰፋ መታመቅና ደካማነት ነው። እነዚያ አፈቀርናት የሚሉት ሰዎች ሃሳባቸው ቁም ነገርና ጨዋነት ያለው ሆኖ በዚህ ምክንያት ከሃሳባቸው ጋር እንድግባባ በሕሊና በኩል መገደድ ካበረብኝ ቢባልም እንኳ ከኔ በኩል እዚሁ አሁን የጂሮሰስ ቶሞስን መቃብር ከሚቆፈርበት ሥፍራ ላይ ተገናኙትን እሱ የሰሜቱን ቁርጠኛነት በገለጠልኝ ጊዜ የኔ ቁርጠኛ ስሜት ደግሞ

ለዘወትር ድንግላዊት ሆኜ መኖርንና ከብቸኛነቴም የማበቅለውን ፍሬና የቁንጅናዬን አበባ ለምድሪቷ ብቻ መስጠትን መሆኑን አረጋግጬ ነግሬው ነበር ።

እሱ ግን ይህን ቁርጠኛ ማስጠንቀቂያዬን መቀበል አቅቶት ከተስፋው ጋር ለመተናነቅ ሲፈልግና በነፋሱም ላይ ለመንሳፈፍ ሲሞክር ወድቆ በችላ ባይነቱ ሐይቅ ውስጥ ሰጥሞ ቢቀር ማንን ሊያስደንቅ ይችላል? ፥ እኔ ፊት ሰጥቸው ፣ አይዞህ ! ብዬው ቢሆን ኖሮ ሐሳዊት እሆን ነበር ፣ በድለላ ሽንግዬውም ቢሆን ኖሮ እጅግ የምወደውን ስሜቴንና ክብሬን እንደገደልሁትና እቅዴንም እንዳፈረስኩት ያህል ይቆጠር ነበር ። ዳሩ ግን ይህን ሁሉ ሳላደርግ ፍጹም ተስፋ ያስቆረጥኩት መሆኔን በበኩሉ ለመረዳት ባለመፈለጉ ብቻ ከራሱ ተስፋ ጋር ታገለ ። ሳይጠላም ሳይወደድም በከንቱ ተበሳጨ ። ይህን ሁሉ ሁኔታ ከተመለከታችሁ በኋላ በሱ ላይ ለደረሰው ሥቃይና ሞት እኔ ኃላፊ ሆኜ በበደለኛነት መወቀስና ጥፋቱ በኔ መታየት የሚገባው መሆን አለመሆኑን ፍረዱኝ ።

የተካደ ሰው ሊበሳጭ ይገባዋል ። ተስፋ ተሰጥቶት ቃሉ ሳይጠበቅለት የቀረ ሰው ሊያዝን ይገባዋል ። መልካም አቀባበልና ቀረቤታ ከኔ ያገኘ እንዳለ በተስፋ ሊጽናና ይገባዋል ። የጋብቻነት ስሜቱን የገለጥኩለት ሰው እንዳለ ሊመካበት ይችላል ። ዳሩ ግን ተስፋ ወይም ክህደት ወይም መልካም አቀባበል ወይም የስሜቴን ዝንባሌ ከኔ ያላገኘ ሰው ጨካኝ ነች ፣ ነፍሰ ገዳይ ነች ፣ ብሎ ሊጠራኝ በፍጹም አይገባውም ።

የኔ ዕድል ለፍቅር እንዲያዘነብል አስካሁን ድረስ ፈጣሪዬ አልፈቀደልኝም ። ስለዚህ በገዛ ውዴታ ፈቃዴ ለማፍቀር እንደሚባኝ ማመን ታላቅ ስሕተት ነው ። ይህ በጠቅላላው የምስጠው ማስጠንቀቂያዬ በልዩ ልዩ ስሜታቸው እየተገፋፋ ጤና ለሚነሱኝ ሁሉ ገደብ ሆኖ እንዲያግዳቸው እመኛለሁ ። እንዲሁም ከዛሬ አንስቶ ወደፊት ሌላ ሰው በኔ ስም አሳብቦ ቢሞት እሚሞቱ በቅናትና በመናቅ አለመሆኑን ለማንም እንዲታወቅልኝ አሰምቼአለሁ ። ምክንያቱም ማንንም የማታፈቅር ሴት

በማንም ዘንድ ቅናት እንዲፈጠርበት ለማድረግ አትችልም ። ተስፋ ማስቆረጥም ከንቀት ጋር ሊታሰብ የሚገባው ነገር አይደለም ። አውሬና ገበሎ የሚለኝ ሁሉ እንደመጥፎና እንደአደገኛ ነገር ቆጥሮ ይራቀኝ ይተወኝ ። ውለታ ቢስ የሚለኝ ሁሉ አይከተለኝ ፥ ምክንያቱም ይህች አውሬ ፣ ይህች ውለታ ቢስ ፣ ይህች ፣ ጨካኝ ይህች ፣ ወረተኛ በርግጥ ሰዳቢዎቿን ለመፈለግ አትሄድባቸውም ። አገልግሎቷንም አትሰጣቸውም ። ልታውቃቸውም አትሻም ። በማናቸውም አኳኋን አትከተላቸውምና ነው ። የገዛ እራሱ ትእግሥት ማጣትና የገዛ እራሱ የጋለ ፍላጐት ጂሮሶስ ቶምስን ቢገድለው የኔን የጨዋነት እርምጃ ማሰናከልና የጨመተ ጠባዬን መንቀፍ ይገባልን? በጫካ ዛፎች መካከል እየኖርኩ ንጽሕናዬን ለመጠበቅ ሰችል ከሰዎች ጋር ተቀላቅዬ እንድኖር በመፈለግ ንጽሕናዬን ለማሳደፍ ሰምን ይጣጣሩልኛል? እንደምታውቁት እኔ ለራሴ የተጎረፈረፈ ዓለማዊ ፀጋ የታደልኩ ስለሆነ የሌሎቹን ሃብትና ብልፅግና የምፈልግ አይደለሁም ። ነፃ ስለሆንኩ ማንም እንዲገዛኝ አልሻም ። ማንንም አልጣላም ማንንም አልወድም ። ይህኛውን አታልዬ ያኛውን አይዞህ አልልም ፣ ካንዱ ጋር ቀልድና ድሪያ አላደርግም ። ከሌላውም ጋር የደስታውን ተካፋይ አልሆንም ። እኔን የሚያሰደስተኝ በነዚህ ቀበሌዎች ዘወትር የማገኛቸው ባልንጀራዎቼ ልጃገረዶች የሚያሰሙኝ ሽር የሌለበት ጨዋታቸውና የፍየሎቼ መንጋ ጥበቃ ብቻ ናቸው ። የኔ ፍላጐት ይህን ተራራ አልፎ አይሔድም ። ምናልባትም ቢያልፍ እንኳ የሰማያትን ጌጥና ማማር ለማስተዋል ነው ። ይህም ነፍሴ ወደ ጥንታዊው መኖሪያዬ ለመመለስ የምታደርገው እርምጃ እየመራት ነው ።

ማርቼላ ይህን ተናግራ ስታበቃ ሌላ መልስ ለመስማት ሳትጠብቅ የሚመለከታትም ሰዎች ሁሉ ስለ አእምሮዋ መራቅና ስለ ቁንጅናዋ አስደናቂነት በመገረም እንደፈዘዙ ትታቸው ጀርባዋን አዞረችና ከቅርቧ ወዳለው ችፍግ ጫካ ውስጥ ገባች ። አንዳንዶቹ ሰዎች ከሚያምሩት ዓይኖቿ ቀፀላ በተወረወረው ኃይለኛ ቀስት ተወግተው ያንን በቅርቡ ያሰማቻቸውን ግልጥ የሆነ ማስጠንቀቂያ በመዘንጋት ሊከታተሏት ቃጥቷቸው ነበር ።

ዶን ኪሾት ግን ይህን የገነፈለ የጠላፊነት መንፈስ በተ
መለከተ ጊዜ ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ሴቶች ለመርዳት
ባለው ኃላፊነት መሠረት የፈረሰኛነት ተግባሩን በገቢር ላይ
ለማዋል ይህ የተገኘው አጋጣሚው ምቹ ስለመሰለው እጁን
በጦራዩው መከደ ላይ አሳረፈና ከፍ ባለና ግልጥ በሆነ ቃል
እንዲህ አላቸው ።

« ሁኔታውና ደረጃው ማናቸውም ዓይነት የሆነ ሰው ሁሉ
ዘንካታዋን ማርቼላን ለመጥለፍና ለማሳደድ ቢሞክር ከቁጣዬ
እንፋሎት የሚወጣውን ቅጣት በእንገቱ ላይ መቀበሉን ይወቅ ።
ውቢቱ ማርቼላ ግልጥና በቂ በሆነ ምክንያት የሰጠችው ማስ
ረጃ ለጂሮሶስ ቶምስ መሞት እሷን የሚያስወቅሰው ጥፋት ያነሰ
እንዲያውም በተሻለ አነጋገር ፈጽሞ የሌለ መሆኑን የሚያስገ
ነዝብ ነው ። በንግግሯ ላይ የዘረዘረችው ሁሉ ተደምሮ ሲታይ
በማናቸውም አኳኋን ቅንጣት ያህል እንኳን ሳታፈቅራቸው
እነሱ በቁንጅናዋ ተሸንፈው ያፈቀሯት ሰዎች ፍላጐት ከማስ
ደሰት የራቀች ጥጹም ገለልተኛ መሆኗን በጉልህ የሚመ
ለክርላት ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ የቁንጅናዋ መግነዝነ
ትና እንዲሁም የምትኖርበት እጅግ ስድ የሆነው ይህ ስፍራ
የሚሰጠው ምቹት እንደሚፈቅደው እሷን ለመከተልና ለማሳ
ደድ እስካሁን ድረስ ጐሪምሳዎቹ ያደረጉት ሙከራ የሚገባ ነው
ተብሎ ሊታለፍ የሚቻል ይሆናል ። አሁን ግን ቁርጠኛ ማስ
ጠንቀቂያዋን በጉባዔ ፊት ካሰማች ወዲህ በዓለም ላይ የሚ
ኖሩት ቅን ልቦና ያላቸው ሰዎች ሁሉ ይህ ምኞቷ እውነት እን
ዲሆንላት በክብርና በመልካም ግምት ሊመለከቷትና ሊጠብቋት
ይገባቸዋል እንጂ የሰጠችውን ገደብ ጥሶ ክብሯን ለመድፈር
መሞከር ከፍ ያለ ወንጀል ነው ። እሷም እንደገለጠችው ያለ
ጥርጥር ይህን በመሰለ የጨዋነት ስሜት ከፈተና ርቀው ለመ
ኖር ከሚመርጡት ሴቶች መካከል ቆርጣ ለማድረጓ መታመን
የሚገባት በዓለም ላይ ብቻዋን የምትገኝ ሴት ስለሆነች የጠ
የቀችው ክብር በውነት የሚያንሳት ነው ።

የዶን ኪሾትን ዛቻ በመፍራት ይሁን ወይም ደግሞ አም
ብሮጂዎ ለወዳጃቸው የሚገባውን የቀብር ሥነ ሥርዓት አፈ

ጻጸም ለማጣደፍ ጓደኞቹን በማነቃቃት ይሁን አልታወቀም ።
እነዚያ ማርቼላን ለማሳደድ አሾትለው የተነሱት እረኞች አን
ዳቸውም ቢሆኑ በሃሳባቸው ገፍተው በጣም አልራቁም ነበር ።

መቃብሩ ተቆፍሮ ካለቀና የጂሮሶስ ቶሞስም ድርሰቶች ከተ
ቃጠሉ በኋላ ዙሪያውን የከበቡት ጓደኞቹና ዘመዶቹ በእንባ
እየተራጩ በደኑ ወደ መቃብሩ ወርዶ ግብዓተ መሬቱ ተፈ
ጸመ ። ጓደኞቹ ከመቃብሩ ላይ አንድ ትልቅ ሞላላ ድንጋይ ተከ
ሉበትና አምብሮጂዎ ጊዜ ሲያገኝ እንድ ዝክረ-ጽሑፍ እንዲ
ያለቀርጽበት አሳሰቡት ። እሱም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ቃል የሚ
ነበብበት ዝክረ-ጽሑፍ እንዲቀረጽበት ማስቡን ገለጠላቸው ።
ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።

«በፍቅር ስሜቱ እየተመራ ተስፋ በሚያስቆርጥ እርምጃ»

«የማሰነው የአናቃሪው እረኛ የቀዘቀዘውና ፍዳውን ያየው»

«በድን እዚህ ሥፍራ ተጋድሟል ።

«ባንዲት ቆንጆ ውለታ ቢስ ወንበዴ ጨካኝነት ምክ
ንያት ሰለተበሳጨ መኖርን ጠልቶ በገዛ እጅ ታንቆ ሞተ»

«ይህ ሥፍራ አመጿኛው ፍቅር የጭካኔ ግዛቱን የዘረ
ጋበት የመጨረሻው ወሰኑ ነው» ይላል ።

ከዚህ በኋላ ሀዘንተኞቹ ሁሉ አበባና ቅጠል እየቆረጡ
በመቃብሩ ላይ ነስንሰው ፤ ለወዳጁም ለአምብሮጂዎ የሚጽናኛ
ቃል ተናግረው ሲያበቁ ሁሉም ወደ የተግባራቸው ለመሄድ ተበ
ተኑ ። ቪቫልዶና ጓደኛው ዶን ኪሾትም ጭምር ይህንኑ ዓይ
ነት ማጽናኛ ቃል ተናገሩ ። ዶን ኪሾት በተለይ ትናንት ላስ
ተናገዱት ፍየል አርቢዎች ስለመልካም አቀባበላቸው የልብ
ምስጋናውን ካቀረበላቸው በኋላ ተሰነባበታቸውና ተለያዩ ።

ጉዞአቸውንም በሚጀምሩበት ጊዜ ቪቫልዶና ጓደኛው አነ
ሱና ዶን ኪሾትን «ለምን ከኛ ጋር ወደ ሲቪሊያ አይሄዱም ?
በኛ ይሁንብዎትና ይምጡ ፤ ግድየልዎትም ይምጡ ፤ ሲቪሊያ
ለአጋጣሚ መነኛ ሆነ ተብሎ የተሠራ ከተማ ነው ። በዚህ ከተማ
ውስጥ በየማዕዘኑና በየጥግጥ አንዳንድ አጋጣሚ ይገኝበታል ።

ብዙ አጋጣሚዎች እንደልብ የሚገኙበት ከሲቪሊያ የበለጠ ከተማ የትም ቢሄዱ አያገኙም» አሉት ። ዶን ኪሾትም እነዚህ ሰዎች አስበው ለሰጡት መረጃና ስለትህትናቸውም ስለ ግብ ዣቸውም ጭምር ካመሰገናቸው በኋላ በዚህ አውን በሚገኙ በት ቀበሌ አካባቢ ያሉት ደኖች በወንበዴዎች የታጨቁ መሆ ናቸውን ወሬ ሰምቶአልና ተራራዎችንና ሸለቆዎችን ሁሉ አንድ ባንድ እየበረበረ ወንበዴዎችን ጠራርጐ ከመጨረስና ቀበሌ ውን ሰላም ከማድረጉ በፊት ለጊዜው ወዲ ሲቪሊያ መሄድ የማ ይገባውና እሱም የማይፈቅድ መሆኑን ገለጠላቸው ። ሁለቱም መንገደኞች ይህን በመስለው ታላቅ ሃሳብ መካከል ገብተው እቅዱን ለማስለወጥ ስላልፈቀዱ እንደገና ተሰነባብተው ወዲ አሰኘው ሥፍራ እንዲሄድ ይቅናህ ብለውት ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። በጉዞአቸውም ላይ የማርቼላና የጂሮሶስ ቶሞስ የፍቅር ታሪክ የዶን ኪሾትም ጉረኛነት እየሄዱ ለሚያደርጉት ጭውውት በር ከት ያለ የወሬ አርዕስትና ምንጭ ያፈልቅላቸው ነበር ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ዶን ኪሾት የማርቼላን ዱካ ተከታትሎ ለመፈለግና ቢያገኛትም እራሱም ጭምር አገልጋይዋ ሆኖ ለመ ኖር ቁርጥ ሐሳብ አድርጐ ነበር ። ዳሩ ግን ለዚህ ለሁለተኛው ክፍለ ታሪክ እዚህ ላይ ፍጻሜ ሲስጠው በተከታዩ እውነተኛ ታሪክ ላይ እንደሚገለጠው ማርቼላን ለመፈለግ የወጠነው ሃሳብ እንደተመኘው ሳይሆን በሌላ ብርቱ በሆነ ምክንያት ተቋረጠ በት ።

ም ዕ ራ ፍ 15

ዶን ኪሾት እርሀራሄ ከሌላቸው ያንዳሶች ጋር ባደረገው ግጭት የወደቀበት መዋፎ አደጋ ይተረካል ።

ሊቁ ደራሲ ሰይድ አህመድ ቤኒንጂላ እንደሚተርከው ዶን ኪሾት በጂሮሶስ ቶሞስ ሥርዓተ ቀብር ላይ የተገናኛቸውን ሰቀ ስተኞችና እንዲሁም በተለይ ትናንትና በጐጆአቸው አሳ ድረው ያስተናገዱትን ፍየል አርቢዎች ፥ እነዚያን በማጽናና ትና እነዚህን በማመሰገን ተሰነባብቶ ከጨረሰ በኋላ ወዲያውኑ እዚያው አረኛይቱ ማርቼላ ስትገባ ወደ ታየችበት ጫካ ውስጥ ከጋሻ ጃግሬው ጋር አብሮ መግባቱን ተነግሯል ። በጫካው ውስጥ ሁለቱ ከርታታዎች ማርቼላ የሄደችበትን ዱካ ተከትለው በየቦታው እየፈለጉ ከሁለት ሰዓት ይበልጥ ላይና ታች ተንገዋለው በፍጹም ሊያገኟት ሳይችሉ በከንቱ ከደከሙ በኋላ በስተፊታቸው በኩል የለመለመ የሣር ቡቃያ የሞላበትና በመ ካከሉም ኩለል ያለች ቀዝቃዛ ምንጭ ውሃ አቋርጣ በምትፈ ስበት መስክ ላይ ደረሱ ። የመስኩ ልምላሜና ማማር ፤ የም ንጪ ውሀ ጥራት የዛፎቹ ጥላ በራድነት በዚያን ሰዓት እየ በረታ የሚሰማውን የፀሐይ ግለት ከጥላ ሥር አረፍት አድር ገው እንዲያሳልፉ ከመጋበዝም አልፎ የሚያስገድዳቸው ሆኖ አገኙት ። ስለዚህ ዶን ኪሾትና ሳንቾ ፖንቾ ከዚሁ ሥፍራ እረ ፍት ለማድረግ ባንድ ዓይነት ሃሳብ በመስማማታቸው ከየኮር ቻቸው ላይ ወረዱና ከብቶቻቸውን በመስኩ ላይ በብዛት የበ ቀሉትን ሣሮች እንዲግጡ ነፃ ከለቀቋቸው በኋላ እነሱም ተር በው ነበርና ወዲያውኑ የስንቅ ቦርሳቸውን አውርደው በጌታና በአሽከር መካከል እምብዛም መግደርደር ሳይደረግ በመልካም ጓደኝነትና በፍቅር መንፈስ እየተገባበዙ ያንኑ ያገኙትን ተካ ፍለው ይበሉ ጀመር ።

ይህም ሲሆን ደኑ ርዝመቱ እጅግ የረጋና ፍሰቱ የሰ
ነሳ መሆኑን ሰንጂ ዝቅ ሲልም ስለሚያውቀው የኮረጃ
ሚሄ ባህሪውን በሞላ ተገንዝቦ ቢያሽከረክመውም እንኳ ወደ
ቅብብሎት ፈተና ሊያገኙት እንደሚችሉ አረጋግጦ ነበርና በዚህ ስጽ
አምነት ያርገዝናቸው እሞር በጠፍጥ ሳይበላሽ እንዲሁ ያቸው
ለቀቁት ነበር ። ጀሩ ግን የመጠር ዕድል ለተሰጠው ጋሪ ነገ
ሥፍራ እየመረጡ ይሰቀሳሉ ስለነበረ የተሰማሙበት ነገር ሰው
ደን ከደረሰ ያደረሰበትን ጉዳት አለማርተውበት ነበር ።

መልኩም ቢሆን የፍጥረትን ባሕርይ መልክት ሊሰጥ የነበ
መሰነ የሚያስቸግር ነገር ስለሆነ ያ ሞቂው ነገር እንደለመመውና ምን
ሬው ርዝመቱ አውን በውን ጠበቅ ያለ ጠበቃን አንገቱ ቀና አደ
እንደገፋፋው ሳይታወቅ ስለተቀለበሰበት ከፈረሰ ወይ
ርጉ ጠፈን ነገሰ በኋላ ዓለምን ለመግለጥ ሲል በንቅት መንፈስ
ሳይፈቀድለት የልዑን ስጦታ ለመግለጥ ተቀለቀለ ። እነዚያ ፈረ
እያስመለመ ሃያና ከፈረሰኛ መነሰለው እየጉያውን እየነጨ
ሰኑ ግን ከእነርሱም መነሰለው ዛራቸውን ፍሬ የመጠውን
ይልቅ ያላገኙት መሆኑ ነው ሲባል የነበ በአርግጠኛ እየ
በዙሪያ ማነሰለን መርጠው በመቀበል ፈንታ በዚህን ጊዜ
አዲስ አንግል በትኩረት እየጎነበሰ ያመረቻቸ ያለፈውና
መቱ በጥርስቸው እየነከሰ የቀሩትን ፍሬ በጥፋት ያለ
ምንም ያህል ሳያቆሙ ደጋግመው ከሰጡት ጉዳት ያለከተለው መሆኑ
ቀሩት ። የነበሩን ደግሞ ከነበሩበት ከጠቡበት ሳይነሱ
ያመጣቸው ቀድሞ በአርገጡት መተራመሳቸውን ነበር ።

ርገዝናቸውን ከጠበቁ እየደረሱ ማግሽ ሬሳ ሆኖ እስኪወድቅ
ድረስ አበራየት ። ይህንንም በርዝናቸው ላይ የወረደውን የጭ
ነትዲንጅ የተመለከቱት ደን ኪቪትና ሳንጅ ፖንጅ በንጹት
ገለው ቅንፋቸው እስኪቆረጥ ድረስ እየርጡ ለበርታ ሰመ
ድረስ በማይዳሰስ ጊዜ ደን ኪቪት አነሰና ሳንጅን እንጂህ አለው።

« የምወደህ ሳንጅ ፣ እኔ እንደማየው አንዘህ ለማጭር
የምንሄድበት ሰዎች በሁኔታው ዝቅ ያለ መጽዳምና እንጂ
ፈረሰኞች አለመሰሰትም ። ስለዚህ የሌሎችን ጉዳት ለመከ
ቢቅ ሕይወታችንን አለመስጠት የተከበርን ሆነን ለመ
ዓይናችን እያየ በርገዝናንት ላይ የወደቁትን ሰዎች ለመቅ
አንተም ያህንኛ መታገስ ልትችል እንደማትችል ።

« ለመሆኑ ምን ዓይነት በቀል እንድንከተልለት ነው ያሰ
ፈለከው ? ሲል ሳንጅ ሰምቶ ሳንጅ ፣ እንዲያውም እኛ ግን ሁላት ብቻ ነን ለማለት እደፍራለሁ ።

« እኔ ስለመሆኑ ሰው እቆጠራለሁ ። ሲል መለሰ ደሉ ደን
ኪቪት ። ከዚህ ሌላ ትርፍ ቃል ሳይናገር ጉሬዳውን መዘር
በሚንሰፍጅ ላይ ተከመረባቸው ። ሳንጅም ደፍሮ ደፍርት አር
ሰይ ሆኖ መጨውን ሲሰቀሰቀው እኩም ይህንት ደፍ
ረት ተሰማውት ከኪቪት ጉሬዳውን ሳነሰፈ ። በመጀመሪያው
ጫጋ ደን ኪቪት የለበሰውን ለንዳጅ ሲንደር አንዳንድ ጋሪ ነጂ ሊሰ
ነደው ሳይ ከሁለት ላይ ተርትር ከፍት
ነው ብዙዎች ሆነው ሳሉ ሁለት ሰዎች ብቻቸውን ገጠመው
ነው ። እደፍጅም በመጨረሻ እፍረት ደግሞ ሰመጣጣ ሆነ
መጣከለ የሚያሰው ሳይ ሰዎች ሁሉ ሰመጣጣ ሆነ ደሉ ደፋሩ
ሰዎች ሁሉ ሰመጣጣ ሆነ ደሉ ደፋሩ ሰዎች ሁሉ ሰመጣጣ ሆነ

ተወቅጦ ለመድቀቅ በቃ ። ያጋጣሚው ክፋት ደግሞ ዶን ኪሾት ተሸንፎ የወደቀው እስካሁን ድረስ ካልተነሳው ከሮንዜናንቴ እግር ሥር ስለሆነ ከዱላው ይበልጥ ያሳዘነው ጉዳት በዚህ አወዳደቁ የተሰማው ውርደት ነበር ። እንግዲህ በነዚህ ከርታቶች ላይ በደረሰው አደጋ ብርሃን እንደሚታየው በተናደዱ ባላገሮች እጅ የተጨበጠ ሽመል በምን ዓይነት አጨካከንና በምን ያህል ክብደት እንደሚሰነዘርና የቱን ያህል ጉዳት እንደሚያመጣ ለመረዳት አያቅትም ። ያንጓሶቹም ይህን ያደረጉትን ከባድ አደጋ በተመለከቱ ጊዜ በተቻላቸው ፍጥነት ፈረሶቻቸውን ሰብስበው እየነዱ ሁለቱን አጋጣሚ ፈላጊዎች ከሰውነታቸው ጉዳት ይበልጥ መንፈሳቸውን በቂም መርዘው እንደወደቁ ትተዋቸው ተጓዱ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ነፍስ ዘርቶ ለመንቃት የቻለው ሳንቾ ስለሆነ ከጌታው ጎን ወድቆ ይገኝ ነበርና በቀሰስተኛና በተዳከመ ድምጽ እንዲህ ሲል ተጣራ ። « ጌታዩ ዶን ኪሾት ፣ እህ ፣ ወይኔ ጌታዩ ዶን ኪሾት» ።

ዶን ኪሾትም የድምጽ ቀሰስተኛነት ከሳንቾ ሳያንስ ነገር ግን ንዴት ባነቀውና በጋግርት አነጋገር » ምን ትፈልጋለህ ወዳጄ ሳንቾ ሲል መለሰለት ።

ሳንቾም የሚፈልገውን በማስረዳት « የሚቻልዎትና የሚገኝልዎት ቢሆን ከዚያ የሰውነት ማሸጊያ ከሆነው መድኃኒት ሁለት ጉንጪት ቢያጠጡኝ ፈቃዴ ነበር ። መቼም ቁስልን ለማሻር የሚረዳ አብነት ከሆነ የአጥንትንም ስብራት ሳይጠግን የሚቀር አይመስለኝም » ።

« ወይኔ ዕድለ ቢሱ» ሲል መለሰ ዶን ኪሾት ። ይህን ተአምራዊ መጠጥ አሁን እዚህ ኖሮኝ ቢሆን ኖሮ ሌላ አንዳች ነገር አይቸግረኝም ነበር ። ዳሩ ግን ከዛሬ አንስቶ ሁለት ቀን ከማለፉ በፊት ምናልባት ዲያብሎስ እንደ ጅራት ተከትሎ ያላስናከለን እንደ ሆነ መጠጡን አስናድቼ ከእጄ የማላወጣው መሆኑን በፈረሰኛነት ክህነቴ እምልልሃለሁ ። ይህን ባላደርግ ግን እጆቹ ሽባ ሆነው ይቅሩ » አለው ።

«እረ ለመሆኑ ከዚህ ሥፍራ (ካሉበት ኮንዲሽን) ችለን ለመነሳት ምን ያህል ጊዜ የሚፈጅብን ይመስልዎታል ሲል ጠየቀ» ሳንቾ ።

« በውነቱ እንጃ እንግዲህ ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈጅብን ! ፣ እንደኔ አስተያየት ከሆነ ግን በዚህን ቀን ብዬ ልነግርህ የምችል አይመስለኝም » ሲል ከፉኛ የተደቆሰው ፈረሰኛ መለሰለት ። ንግግሩን በመቀጠል « የሆነው ሆኖ ስህተቱ የኔ መሆኑን አልጠራጠርም ፣ ምክንያቱም እንደኔ የተካኑ ፈረሰኞች ባልሆኑት መደዴ ሰዎች ላይ ጐራዴዬን መምዘዝ የማይገባኝ መሆኑን እያወቅሁ ዘንግቼ በመምዘዜ የፈረሰኛነትን የግጥሚያ ደንብ ስለአፈረስኩ የውጊያ አምላክ ይህን ከባድ ቅጣት እንድንቀበል መፍረዱን አምናለሁ ። ስለዚህ ወዳጄ ሳንቾ አሁን አጠንክሬ የምሰጥህ ምክር ለሁላታችንም በጉንነት በጣም የሚጠቅም ቁም ነገር ስለሆነ ከዛሬ ጀምረህ በልቦናህ ቀርፀህ ልትይዘው ይገባሃል ። ይኸውም ወደፊት በምናደርገው ግጥሚያ ላይ የዛሬዎቹን የመሰሉ የተካለቡ ወሮበሎች አንዳች አደጋ ሊጥሉብን ሲወናዱ ባየሃቸው ጊዜ እኔ መቼም ቢሆን አላደርገውምና ጐራዴውን በነሱ ላይ ይመዝዛል ብለህ እኔን እንዳትጠብቀኝ ። አንተው ራስህ ጐራዴህን መዝዘህ የተሻለ መስሎ በታየህ አኳኋን እንዳሰኘህ ልትቀጣቸው ትችላለህ ። ምናልባት ደግሞ እነዚህን ወሮበሎች ለማገዝ የተካኑ ፈረሰኞች ረዳት ሆነው የመጡ እንደሆን ይህ ተግባር እኔን የሚመለከት በመሆኑ በዚያን ጊዜ ያለኝን ኃይልና ብርታት አሟጥጬ የተከላካይነት ግዳጄን ለመፈጸም አልፈ መጋፈጡን አውቅበታለሁ ። መቼም እስካሁን ድረስ አብረኸኝ ስትዞር እኔ ባደረግኋቸው ግጥሚያዎች ላይ ሁሉ ያልተለየኸኝ በመሆንህ የዚህ የኃይለኛው ቀኝ ክንዴ ብርታትና ጀግንነት ወደየትኛው ወሰን እንደደረሰ በሺህ በሚቆጠር ማስረጃና ፈተና ያየኸው ስለሆነ ለጥቃትህ ተበቃይ አጣለሁ ብለህ የምትሰጋ አይመስለኝም ።

ምስኪኑ ፈረሰኛ ቢስካሊያውን ካሸነፈ ወዲህ ልቡ ተብቶ መጉልበቱ ተሰምቶት በጣም ጉረኛ ሆኖ ስለነበር ይህን የተናገረውን የዚያን የግጥሚያ ድል መርከሪያ በማድረግ ነው ።

ለሳንኑ ግን ይህ የጌታው ምክርና ማስጠንቀቂያ እምብዛም አል ተሰማውም ነበርና መልሱን ሳይሰጥ ለመትው ስላልፈለገ እን ዲህ ሲል አስተያየቱን ገለጠለት ።

«ጌታዬ ሆይ! እኔ ከተወለድሁበት ጊዜ አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ከሰው ጋር ተጣልቼ የማላውቅ የረጋሁና ፀጥ ያልሁ ሰው በመሆኔ ማናቸውንም የተሠራብኝን በደልና ግፍ ታግሼ ማሳ ለፍን የማውቅ ነኝ ። ምክንያቱም የማሳድጋቸው ሚስትና ልጆች ስላሉኝ ዘወትር የምጣጣረው ለነሱ ተርፌ ለመገኘት ስለሆነ አደጋን አጥብቄ መሸሽ አለብኝ ። ስለዚህ እኔም በበኩሌ የምሰጥዎት ምክርና ማስጠንቀቂያ በወሮበሎ ችም ሆነ በፈረሰኞች ላይ ጉራዴ መዘዝ አደጋ ለመጣል በፍ ጹም የማልሞክር መሆኔን እንዲያውቁልኝ ነው ። እንዲያውም ከዛሬ አንስቼ ወደፊት አምላክ ወደርሱ እስኪጠራኝ ድረስ ባለ ፈው ጊዜ በድለውኝ የነበሩት ፣ አሁንም የበደሉኝን ፣ ወደፊ ትም የሚበድሉኝንና ወይም ሲበድሉኝ የዶለቱትን ሁሉ በሁ ኔታቸው ታላላቅ ወይም ታናናሽ ፣ ባለፀጋ ወይም ድሀ መኳንን ወይም ተራ ሰዎች ቢሆኑ በማናቸውም ዓይነት ማዕረግና ደረጃ ላይ የሚገኙትን ሁሉ ሳልመርጥና ሳላበልጥ በጠቅላላው ይቅር ለእግዚአብሔር ብያቸዋለሁ ።

ጌትየው ይህን የጋሻ ጃግሬውን ንግግር በሰማ ጊዜ እንዲህ ሲል መለሰለት ፣ ዎንቻ ሆይ! በእግማትህ እጅግ የተሰላ ትህ መሆንክን ለማስገንዘብ ያለ ብዙ ድካምና ያለመታወክ እንደልቤ ሊያናረግኝ የሚችል በቂ ትንፋሽ ቢኖረኝና ይህም የታላቁ ሕመም ጥቂት ፋታ ቢሰጠኝ ኖሮ ፈቃዴ ነበር ። የሆ ነው ሆኖ መቸም እትረባምና እስቲ ጥቂት አዳምጠኝና የቻል ኩትን ያህል ላስረዳህ ። እስካሁን ድረስ እጅግ ተቃራኒዎችን የሆነው ዕድላችን ባነፋፈሱ እኛን ለመደገፍ ፈቃደኛ ሆኖ አት ጣጫውን ቢለውጥና የፍላጐታችን መጋረጃ እየነፋ ያሳንዳች አደጋና መሰናክል መርቶ ተሰፋ ወደ ሰጠሁህ ደሴት ወደብ ቢያደር ሰን እኔ የደሴቷ ባለቤት ከሆንኩ በኋላ አንተን ገገርዋ አድርጌ ስሾምህ በዚያን ጊዜ ምን ልትሆን ይሆን? እንግዲህ ቅድም በተ ናገርኳቸው ንግግሮችህ ለማሰረዳት እንደሞክርከው አንተ ከዚህ

ቀደም የተካንህ ፈረሰኛ ባለመሆንህና አሁንም ለመሆን ባለ መፈለግህ የተሠራብህን በደል ለመበቀልና ግዛትህን ለመከላ ከል ድፍረትና መልካም ፈቃድ ከጐደለህ አንድ አነረ ገገር ሊያ ደርገው የማይገባውን ከፍ ያለ ጉድለት ፈጽመህ መገኘትህ እይ ደለምን ?

ስለዚህ አንተ በተለይ ማወቅና በጥልቅ መገንዘብ የሚ ገባህ በጦርነት ላይ ድል ሆነው በተያዙት የመንግሥት ግዛ ቶችና አውራጃዎች ውስጥ አንሩ ነና ሳይረጋጋ በአፍላው ግር ግር ሰሞን የአገሩ ነዋሪ ሕዝቦች ለአዲሶች መሪዎች ሰላማዊ ሆነው ለመገዛት መንፈሳቸው ፀጥ ያለና ልባቸውም የታመነ ሆኖ ስለማይገኝ በዚያን ጊዜ «በድፍርስ ውስጥ ማጥመድ» እንደሚባለው ተረት ጥንካሬንና ብርታትን ዋና መሣሪያ በማ ድረግና አንዳንዱም ጭካኔን በማሳየት ሴረኞቹን ወህኒ ቤት በማጕር ሰላም እንዲገኝ በመጣጣር ፈንታ ነገሩን ወደ ድሮ ው ሁኔታ ለመለወጥ ሙከራና ሴራ ያደርጋሉ ከሚባሉት ወገ ኖች የሚወራውን ወሬ ሰምቶ መሸበርና መፍራት በገዛ እጅ መገሰትና ውርደትን ማትረፍ መሆኑን ነው ።

ስለዚህ አዲሱ መሪ ዘዴ አዋቂ ሆኖ ዘወትር ተፈሪነትንና አክናፊነትን እንደያዘ ለመዝለቅና ጥቅሙንና የገገርነት ክብሩ ነም ለመጠበቅ እንዲችል አስተዋይና ብልህ መሆን ፣ እንደዚ ሁም ደግሞ በማናቸውም ጊዜ በሚደርሰው ድንገተኛ አደጋ ላይ ጠላትን ለመከላከልም ሆነ ለማጥቃት እንዲችል ልበ ደፋር ጀግና መሆን ዋና ግዴታው መሆኑን ማመን አለበህ ።

« ለዚህ አሁን ላስረዱኝ ጉዳይ የሚያገለግል ከሆነ» ሲል መለሰ ሳንቾ » ለገገርነት የሚያስፈልገው ብልህነትና ደፍረት እንዲኖረኝ ለማድረግ እጣጣር ነበር ። ጻሩ ግን ባሁኑ ሰዓት ይበ ልጥ የሚጠቅመኝ ከምክር ይልቅ የታሩቁን ሕመም የማስታ ግስበት ሕክምና ባገኝ መሆኑን በመሃይም እምነቴ እምልል ዎታለሁ ። ለጊዜው ልናስብበት የሚገባን ተቀዳሚው ጉዳይ የጨናችን ደህንነት ስለሆነ ከዚህ ስፍራ ለመነሳት የምንችል እንደሆነ እንሞክር ። ለዚህ ለዛሬው አደጋ ዋናው ሰበብና ምክ

ንያት የሆነው ርዜናንቴ በመሆኑ ምንም እንኳ ሊታዘንለት ባይገባ እሱንም ተረዳድተን እናንሳው ። በውነቱ እንደኔ ንፁሕና የረጋ ሰው አድርጌ ስለምገምተው ምን ጊዜም እንዲህ ያለ የጠብ እሜሪነት መንፈስ ከርዜናንቴ ጠባይ ይመነጫል ብዬ አልጠበቅሁም ነበር ። የሰውን ጠባይ በትክክል መርምሮና ለይቶ ለማወቅ ረገርም ጊዜ ያስፈልጋል የሚሉት ሊታውንት እዚህ ላይ እውነት አላቸው ። በዚህ አኳኋን ሲታይ በዚህ ዓለም የራሱን እንጂ የሌላውን ሁኔታ አውቃለሁ በማለት ምን ጊዜም እርግጠኛ ሆኖ ለመመስከር አይቻልም ። ከቡርነትም ያንን ያል ታደለውን ዙዋሪ ፈረሰኛ በጉራዴ አራግበው ከጣሉት ወዲህ ምንም ያህል ሳንርቅ እንደዚህ ተፋጥኖ እንዲህ ያለ የዱላ ነጉድጓድ ወርዶ በጀርባችንና በታፋችን ላይ ይዘንብብናል ብሎ ከመከለላችን ያስበ ማን ኖሮአል? ።

«እባክህን ሳንቾ ያንተን መጐዳት ተወው አታንሳው » ሲል መለሰ ዶን ኪሾት « ያንተ ገላ ብዙ ጉስቁልናና የችግር ኑሮ ተላምዶና ደድሮ ያደገ ስለሆነ እንዲህ በቀላሉ ሰዱላ የሚበገር አይደለም ። የኔው ግን ከሆላንድ ሽማና በምቹ ፍራሽ ተቀግጥሎ እና ተለሳልሶ ያደገ ስለሆነ የዚህ ድብደባ ሕመም ይበልጥ እንደሚሰማው ግልጥ ነው ። እኔ እንደሚመስለኝ ምን እንደሚመስለኝ እላለሁ እንዲያውም በርግጥ እንደማምነው ይህን የመሳሰሉት እንቅፋቶች ሁሉ ከጦረኛነት ተግባር ጋር በጥብቅ የተያያዙ ሆነው የደረሱ መሆናቸውን ባልረዳው ኖሮ መደፈራችንና መጠቃታችንን ሳስብው በንዴትና በእፍረት ብቻ ሳልሞት አልቀርም ነበር ።

ዊታዱ ሆይ» ፥ ሲል መለሰ ጋሻ ጃግሬው «መቸም እኛ ዚህ እደጋዎች ሁሉ የፈረሰኝነት ተግባር የሚያፈራቸው ፍሬዎች ከሆኑ የተወሰነ የማለቂያ ዘመን እንዳላቸው ወይም ደግሞ በየቱኑ የሚለቀሙ እንደሆነ እስቲ አጣርተው ይንገሩኝ ፥ በኔ አስተያየት ግን ከእንግዲህ ወዲህ ይህን የመሰለ ሁለት ምርኮ ያመረትን እንደሆነ በሶስተኛው ምርት አምላክ በማያልቀው ምህረቱ ካላተረፈን በስተቀር ወደጉተራ መከተታችን የማይቀር ይመስለኛል አለ ።

«ወዳጄ ሳንቾ» ሲል መለሰ ዶን ኪሾት « የዙዋሪ ፈረሰኞች ሕይወት ለሺህ አደጋና ለሺህ መጥፎ ዕድል የተጋለጠ መሆኑን ልታውቀው ይገባሃል ። በሌላ በኩል ደግሞ ታሪካቸውን አጣርቼ በማውቀው በብዙዎቹ ፈረሰኞች ላይ የደረሰው ሁኔታ እንደሚገልጠው ዙዋሪ ፈረሰኞች ዘወትር የሚገኙት ወደ ንጉሥነት ወይም ወደ ንጉሠ ነገሥትነት ደረጃ ላይ ሊያደርሳቸው በሚችል አፋፍና አቅራቢያ ላይ ነው ። ያሁኑ ሕመሜ ታግሶልኝ በብዙ ለመናገር የሚፈቀድልኝ ቢሆን ኖሮ መጀመሪያም ሆነ መጨረሻ በልዩ ልዩ አደጋና መከራ ውስጥ ሲፈትኑ ከቆዩ በኋላ በከንዳቸው ብርታትና ጀግንነት ብቻ ተራም ደው ከፍ ብሎ ወደጠቀስኩልህ ታላቅ ማዕረግና ደረጃ ላይ ለመድረስ የበቁትን በዝርዝር እየጠራሁ አስረዳህ ነበር ። ይሁን እንጂ ባሁኑ ሁኔታዬ የአንዳንዶቹን ፈረሰኞች ብቻ ታሪካቸውን ባጭሩ ልተርክልህ እችላለሁ ። ለምሳሌ ጀግናው የጋውላው አማዲስ በደመኛው ጠላቱ በአርካላዎ እጅ ገብቶ በነበረበት ጊዜ ተረጋግጦ ሊታወቅ እንደተቻለው ይሽው ጠላቱ አሥረኛው አድርጉት ሳለ በመኖሪያ ግንቡ መስክ ላይ ከሚገኘው ምሰሶ ጋር የፊጥኝ አሥሮ በገዛ ፈረሱ የልጓም ዛብ ሁለት መቶ ግር ፋት ገርፎታል ። አንደኛው ደግሞ እጅግ ሃይማኖተኛ የሆነው የምስጢር ደራሲ እንደሚተርከው የፈቦው ፈረሰኛ አንድ ቀን ወዳጅ ግንብ ውስጥ ገብቶ በመገኘቱ ምክንያት ከእግሩ ሥር ድንገት በተከፈተው ቀዳዳ ውስጥ ቁልቁል ቮልክ ካንድ ጠሊቅ ጉድጓድ ውስጥ ከወደቀ በኋላ ግን እንዳሰረውና ግን እንደተበተበው ሳይታወቅ እግሩና እጁ ታሥሮ ስለተገኘ እዚያው እንዳለ የበረዶና የጠጠር እጥበት በሚባለው ማሰቃያ አናቱን ክፉኛ ሲያስወቅሩት እንደነበርና ይህም አሳዛኝ ሥቃይ በታላቁ ወዳጁ ባንድ ብልሀ እርዳታ ባይታገድለትና በምትሐት ተጐትቶ ከጉድጓድ ውስጥ ባይወጣ ኖሮ ያልታደለው ፈረሰኛ በመሬረ ጣር ሕይወቱ ያልፍ እንደነበረ ሊረጋገጥ ተችሏል ። ስለዚህ እነዚህን የመሳሰሉ ጀግና ሰዎች በዘመናቸው የተቀበሉትን ሥቃይና መከራ እኔም መቀበል እንደሚገባኝ አውቄ መታገስ አለብኝ ። እንዲያውም አሁን እኛ ተሰቃይተናል ብለን ከምናገርረው ይበልጥ በነሱ ላይ የደረሰው ሥቃይም በጣም የሚያመዝን ነው ። ከዚህ ሌላ ደግሞ ባጋጣሚ ምክንያት በእጅ

ንያት የሆነው ሮዜናንቴ በመሆኑ ምንም እንኳ ሊታዘንለት ባይ ገባ እሱንም ተረዳድተን እናንሳው ። በውነቱ እንደኔ ንፁሕና የረጋ ሰው አድርጌ ስለምገምተው ምን ጊዜም እንዲህ ያለ የጠባ አሜሪነት መንፈስ ከሮዜናንቴ ጠባይ ይመነጫል ብዬ አልጠ በቅሁም ነበር ። የሰውን ጠባይ በትክክል መርምሮና ለይቶ ለማ ወቅ ረዥም ጊዜ ያስፈልጋል የሚሉት ሊታውንት እዚህ ላይ እውነት አላቸው ። በዚህ አኳኋን ሲታይ በዚህ ዓለም የራሱን እንጂ የሌላውን ሁኔታ አውቃለሁ በማለት ምን ጊዜም እርግ ጠኛ ሆኖ ለመመስከር አይቻልም ። ከቡርነትም ያንን ያል ታደለውን ዙዋሪ ፈረስኛ በጉራዴ አራግፎው ከጣሉት ወዲህ ምንም ያህል ሳንርቅ እንደዚህ ተፋጥኖ እንዲህ ያለ የዱላ ነጉ ድጓድ ወርዶ በጀርባችንና በታፋችን ላይ ይዘንብብናል ብሎ ከመካከላችን ያስበ ማን ኖሮአል ? ።

«አባከሀን ሳንቾ ያንተን መኰዳት ተወው አታንሳው » ሲል መለሰ ዶን ኪሾት « ያንተ ገላ ብዙ ጉስቁልናና የችግር ኑሮ ተላምዶና ደድሮ ያደገ ስለሆነ እንዲህ በቀላሉ ለዱላ የማ በገር አይደለም ። የኔው ግን ከሆላንድ ሽማና በምቹ ፍራሽ ተቀ ማጥሎ እና ተለሳልሶ ያደገ ስለሆነ የዚህ ድብደባ ሕመም ይበ ልጥ እንደሚሰማው ግልጥ ነው ። እኔ እንደሚመስለኝ ምን እንደሚመስለኝ እላለሁ እንዲያውም በርግጥ እንደማምነው ይህን የመሰሰሉት እንቅፋቶች ሁሉ ከጦረኛነት ተግባር ጋር በጥብቅ የተያያዙ ሆነው የደረሱ መሆናቸውን ባልረዳው ኖሮ መደፈራችንና መጠቃታችንን ሳስበው በንዴትና በእፍረት ብቻ ሳልሞት አልቀርም ነበር ።

«ጌታዬ ሆይ» ፣ ሲል መለሰ ጋሻ ጃግሬው «መቸም እነ ዚህ አደጋዎች ሁሉ የፈረሰኛነት ተግባር የሚያፈራቸው ፍሬ ዎች ከሆኑ የተወሰነ የማለቂያ ዘመን እንዳላቸው ወይም ደግሞ በየቀኑ የሚለቀሙ እንደሆነ እስቲ አጣርተው ይንገሩኝ ፣ በኔ አስተያየት ግን ከአንገዚህ ወዲህ ይህን የመሰለ ሁለት ምርት ያመረትን እንደሆነ በሶስተኛው ምርት እምላክ በማያልቀው ምህረቱ ካላተረፈን በስተቀር ወደጉተራ መከተታችን የግይ ቀር ይመስለኛል አለ ።

«ወዳጄ ሳንቾ» ሲል መለሰ ዶን ኪሾት « የዙዋሪ ፈረ ሰኞች ሕይወት ለሺህ አደጋና ለሺህ መዋር ዕድል የተጋለጠ መሆኑን ልታውቀው ይገባሃል ። በሌላ በኩል ደግሞ ታሪክች ውን አጣርቼ በማውቀው በብዙዎቹ ፈረሰኞች ላይ የደረሰው ሁኔታ እንደሚገልጠው ዙዋሪ ፈረሰኞች ዘወትር የሚገኙት ወደ ንጉሥነት ወይም ወደ ንጉሠ ነገሥትነት ደረጃ ላይ ሊያ ደርሳቸው በሚችል አፋፍና አቅራቢያ ላይ ነው ። ያሁኑ ሕመሜ ታማሶልኝ በብዙ ለመናገር የሚፈቀድልኝ ቢሆን ኖሮ መጀመ ሪያም ሆነ መጨረሻ በልዩ ልዩ አደጋና መከራ ውስጥ ሲፈ ቃት ከቆዩ በኋላ በክንዳቸው ብርታትና ጀግንነት ብቻ ተራም ዱው ከፍ ብሎ ወደጠቀስኩልህ ታላቅ ማዕረግና ደረጃ ላይ ለመ ድረስ የበቁትን በዝርዝር እየጠራሁ አስረዳህ ነበር ። ይሁን እንጂ ባሁኑ ሁኔታዬ የአንዳንዶቹን ፈረሰኞች ብቻ ታሪክቸውን ባጭሩ ልተርክልህ እችላለሁ ። ሰምሳሴ ጀግናው የጋውላው አማ ዜሰ በደመኛው ጠላቱ በአርካላዎ አጅ ገብቶ በነበረበት ጊዜ ሕረጋጣ ሊታወቅ እንደተቻለው ይሽው ጠላቱ አሥረኛው ሕድርጉት ሳለ በመናሪያ ግንቡ መስክ ላይ ከሚገኘው ምሰሶ ጋር የፊጥኝ አሥሮ በገዛ ፈረሱ የልጓም ዛብ ሁለት ሙቶ ግር ፉት ገርፎታል ። እንደኛው ደግሞ እጅግ ሃይማኖተኛ የሆነው ቆስጠር ደራሲ እንደሚተርከው የፈቦው ፈረሰኛ አንድ ቀን ሞሮንድ ግንብ ውስጥ ገብቶ በመገኘቱ ምክንያት ከእግሩ ሥር ሰንገት በተከፈተው ቀዳዳ ውስጥ ቁልቁል ሾልኮ ካንድ ጠሊት ሞሮንድ ውስጥ ከወደቀ በኋላ ማን እንዳሰረውና ማን እንደተበ ሞው ሳይታወቅ እግሩና እጁ ታሥሮ ስለተገኘ እዚያው እን ሰ የበረዶና የጠጠር እጥበት በሚባለው ማሰቃያ አናቱን ክፉኛ ያስመቅሩት እንደነበርና ይህም አሳዛኝ ሥቃይ በታላቁ ወዳጁ ንድ ብልህ እርዳታ ባይታገድለትና በምትሐት ተጉትቶ ከጉ ድጓድ ውስጥ ባይወጣ ኖሮ ያልታደለው ፈረሰኛ በመረረ ጣር ሞው ያልፍ እንደነበረ ሊረጋገጥ ተችሏል ። ስለዚህ እነዚ ሞ የመሰሰሉ ጀግና ሰዎች በዘመናቸው የተቀበሉትን ሥቃ ሽ መከራ እኔም መቀበል እንደሚገባኝ አውቄ መታገስ አለ ብ ። እንዲያውም እሁን እኛ ተሰቃይተናል ብለን ከምናማ ሮው ይበልጥ በነሱ ላይ የደረሰው ሥቃይም በጣም የሚያመ ም ነው ። ከዚህ ሌላ ደግሞ ባጋጣሚ ምክንያት በእጅ

ላይ በተገኘ መሣሪያ ተመትቶ መቁሰል ክብርን የሚቀንስ ጥቃት ሆኖ መቆጠር የለበትም ። ይህም በፈረሰኛነት ደንብ ውስጥ በጣም ግልጥ በሆነ ድንጋጌ ተጽፎ ይገኛል ። ለምሳሌ እንድ ጫማ ሰፊ በእጁ የያዘውን የጫማ መሰጉጃ ወርውሮ ንጉ ኛውን ቢመታው ምንም እንኳ መሰጉጃው ከእንጨት የተሠራ መሆኑ ቢታወቅ በዚህ ምክንያት ብቻ የተመታው ሰው በጽሳ ተደብድቧል ለማለት አይችልም ። ይህንንም የምልህ በዚህ አም ባንሮ ውስጥ ክቱኛ መደብደባችን ቢሰማንም ክብራችንን የሚ ቀንስ ጥቃት ተፈጽሞብናል ብለን እንዳናስብ ነው ። ምክንያ ቱም እነዚያ ወሮበሎች እኛን የደበደቡበት መሣሪያ ያው በእ ጃቸው ይዘውት የነበረው ሽመል ነው እንጂ እኔ እንደማስ ስታውሰው ከመካከላቸው ጉራዴና ሰይፍ ወይም ጩቤ የያዘ እንድም ሰው ስለሌለባቸው ነው» አለው ።

«ለኔ ግን» አለ ሳንቾ ሰምቶ የያዙትን መሣሪያ ለይቼ የማ ይጠት ጊዜ አልሰጡኝም ነበር ። ምክንያቱም እኔ ቮተሌን ጥና ከመጨበጤ እንዴ እንኳ ለመሰንዘር ሳልችል ወዲያውኑ በሽ መላቸው እርምታ ጀርባዬን ሰለቀደሱት ማያዬን ከዓይኔ አው ልቀው ብርታቴንም ከጉልበቴ ነጥቀው እስካሁን ድረስ ወድቄ ከምገኝበት ሥፍራ ላይ ስለዘረጉኝ እንኳንስ መሣሪያቸውን ልቆ ጥና እስከነመፈጠራም አላውቅም ነበር ። አውንም ቢሆን ይህ የቆመል ድብደባ ትርጉሙ ጥቃት ወይም ንቀት መሆን አለመ ሆኑን ሳላውት መቅረቴ አልጨነቀኝም ። እኔን የጨነቀኝ የሰ ውነቴ መድቀቅና እንዲሁም የድብደባው ኃይል እስከ ዘላለም የማልረሳውና ለንቡረና ቁስል ከትውስታዬና በጀርባዬ እን ጻሁም በታሉ ላይ አትሞብኝ መቅረቴን ሳስበው ብቻ ነው ።

«አይዞህ፣ ሳንቾ እንደታጋሽነትህ ተጽናና» ሲል ዶን ኪሾት መለከኩን ቀጠለ ፣ ጊዜ የማያስረሳው የመከራ ቀንና ሞት የማ ይደመስሰው ሕመም ክቶ በዓለም ላይ እደግኝም ና ሁሉም ኃላ ፊና ጠፊ መሆኑን ተረድተህ መቻል አለብህ» አለው ።

« በውነቱ እስካሁን ድረስ ላይነግሩኝ የቀረው ይህ የአ ሁኑ ምክር ብቻ ነበር» ሲል መለሰ ሳንቾ አረ ለመሆኑ በዚህ አነጋገራዎ ሊያስረዱኝ የሞከሩት ከቶ ምን ይሆን ? በጊዜ ብዛት ከሚያልፍ መከራና በሞት ከሚጠቃለል ደዌ ይበልጥ የከፉ ሌላ ምን ዓይነት አደጋ በዓለም ላይ ሊኖር የሚችል ይመስልዎታል? ይህ በኛ ላይ የደረሰው አደጋ ያስከተለው ሕመም በተላል ኔነ ምናና በጥቂት መድኃኒት የሚድን ነገር ቢሆን እንኳ ጉዳቴ ያነስ በሆነ ነበር ። ጻሩ ግን እኔ እንደማየው በዚህ አደጋ ላይ የቆሰለውን ገላችንንና የተሰበረውን አጥንታችንን አክሞና ወግኖ ለማዳን ቢፈልግ ያንድ ሆስፒታል ሐኪሞችና መድኃኒቶች እንደ ማይበቃው ለማረጋገጥ እደፍራለሁ ።

«እባክህን እርሳው ሳንቾ» ሲል ቀጠለ ዶን ኪሾት ፣ ፈት ህን አጨፍግህ መነጫነጭህን ተወውና ለሥጥር ዕድል መል ካም ፊት ለማሳየት ሞክር ። እኔም እንደዚሁ አደረጋለሁ ። ላውን ግን እስቲ ተነሱተን ሮዜናንቴም እንዴት እንደሆነ እንየው ። መቸም ይህ ያልታደለው እንስሳ እንደበት ኖሮት ለመናገር የሚ ችል ቢሆን ኖሮ ከሁላችንም ይበልጥ መደብደቡን አይደብቅ ንም ነበር ።

« ይህስ ምንም አያስደንቀንም» አለ ሳንቾ ፣ እሱም በበኩሉ ዙሞሪ ፈረሰኛ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ደርሻውን ማግኘት ይገ ባዋል ። ይልቁንስ እኔን በጣም ያስደነቀኝ እኛን እንዲህ አድ ርገው አጥልምለው ሲጥሉን የኔይቴ አህያ አንዳች ነገር ሳይ ነካት በሰላም መትረፏን በማየቴ ነው ።

«ደግነቱ» ሲል መለሰ ዶን ኪሾት ፣ መጥፎ ዕድል ከማ ናቸውም አደጋ ውስጥ ለመዳን የሚቻልበት ዘዴ እንዲገኝ አንድ የመሽሎኪያ በር ዘወትር ከፍታ ትተዋለች ። ይህንንም ግለቴ ይህች ጥሩ ክብት በአሁኑ ጊዜ እኔን ተሸክማ በማጓጓዝ ቁስ ሌን ለመታከም ወደ ምችልበት ወደ አንድ ግንብ ሊታደርሰኝ በመቻሏ የሮዜናንቴን ጉድለት መለየቷን ሳስገነዝብህ ነው ። እንዲህ ያለውን የክብት አቀማመጥ ፈሊጥ በጭራሽ ከውርደት ልቆጥረው የማልችልበት በቂ ምክንያት አለኝ ። ይኸውም ለደከተኛው የሩዝ አምላክ የቲበስ ከተማ አስተማሪ የሆነው ያ ደጉ ሽማግሌ ሲሉና ባለሙቶ በር ወደሆነችው ከተማ ወጣ

ጊዜ መልካም ፈቃዱ ሆኖ ባንዲት በምታምር አህያ ላይ ተቀምጦ እንደነበረ ያነበብኩትን ታሪክ አስታውሳለሁ ።

« ምናልባት እርስዎ እንዳሉት ሊሆን ይችል ይሆናል » ሲል መለሰ ሳንቾ» ዳሩ ግን እኔ እንደሰማሁት ይህ ሽማግሌው ሲሌኖ የተቀመጠው በደንበኛው አቀማመጥ ስለሆነ ከርሱ ጋር ለመመሳሰል ከመፈለግም በፊት በአህያ ላይ ተቀምጦ መሄድና በጀንያ እንደተከተተ ፍግ አግድም ተጭኖ መነዳት እጅግ የተ ራራቀ ልዩነት ያለው መሆኑን ማወቅ ይኖርብዎታል» አለው ።

«አቀማመጡን የለመጠው የቁስሉ ሕመም ስለሆነ በኔ አይፈረድም» ሲል ዶን ኪሾት ማስረዳት ጀመረ ። ይህም ቢሆን በውጊያ ላይ የተገኘ ቁስል የቆሳዩን ክብር ይበልጥ ያስጌጠ ዋል እንጂ አያጐድፍበትም ። ስለዚህ ወዳጄ ፖንቻ ክርክሩን ትተህ ቅድም እንዳልኩህ ተነስና በመስለህና ባስኘህ አካኋን ባህያህ ላይ አስተምጠኝ ። ከዚያም በኋላ ጊዜው ከመጨለሙ በፊት ይህን ውድማ ቀበሌ ለቅቀን እንሂድ አለው ።

« ዘንጉት እንደ » ሲል አስታወሰ ሳንቾ ዙዋሪ ፈረሰኞች ሁሉ የዓመቱን አብዛኛውን ወራት በውድማ ቀበሌና በበረሃ ውስጥ ማደር ይገባቸዋል ፤ እንዲያውም ይህን ለማድረግ የቻሉ እንደሆነ ከታላቅ ዕድል ይቆጥሩታል ፤ አላሉኝም ወይ ? ብሎ ጠየ ቀው ።

«እምን ማለቴንስ ብዙህ ነበር » ሲል ዶን ኪሾት መለ ሰስት ። ዳሩ ግን በበረሀ ውስጥ የሚያድሩት ሌላ ማደርያ በታ ሲያጡ ወይም ፍቅር የያዛቸው ሲሆኑ ነው እንጂ ባሁኑ ሁናቴ ላይ ሲገኙ አይደለም ። ለእደራረጉ እርግጠኛነት እንደሆነ ግን አያሌ ዙዋሪ ፈረሰኞች ሴቶቻቸው ምንም ሳያውቁላቸው ሀሳ ቴን ዓመት አከታትለው በአሰት ደንጊያ ላይ ተኝተው ለፀሐይ ለጨለማና ለቁር ተጋልጠው እንደሚኖሩ የታወቀ ነው ። ከነ ዚህ ፈረሰኞች አንዱ አማዲስ ስለሆነ ስሙን «ቤልቴኔብሮዝ» አሰኝቶ በትክክል አላስታወሰውም እንጂ ለስምንት ዓመት ይሁን ወይም ለስምንት ወር ጊዜ ምክንያቴን አጣርቼ ባላመ ቀውም ወይዘሮ እሪያና አበላጭታው ቡባዔ ገብቶ መኖሪያውን

ፔኖፖብራ ውስጥ በተባለው ቋጥኝ ላይ አድርጉ ነበር ይባላል ። የሆነው ሆኖ ሳንቾ ላሁን ይህን ታሪክ ወደጉን ትተን በርንዚናንቴ ላይ የደረሰውን ዓይነት አደጋ ተደግሞ በአህያይቱ ላይ እንዳይ ደርስ አባከህን ፈጠን ብለህ ተነሳ ።

«ይህ ብቻ ነበር የቀረው » አለና ሳንቾ ፥ ይህን የደቆሰ ውን አደጋ ያመጣበትን ሰው እያመረረ ሰላሳ ጊዜ አቃሰቱ ፥ ሰልሳ ጊዜ አምጠ ፥ መቶ ሃያ ጊዜ ተሳድበና ተራግሞ ለመነሳት ቱና ብሎ አጋግሽ ላይ ሲደርስ ፈጽሞ ለመቆም ሳይችል እንደደ ጋን ጐብጦ ቀረ ። ሆኖም በዚህ በሚያሲቃይ ሁኔታ እንዳጐነበሰ ሄዶ አህያይቱን መጫን የማይቀር ዕዳ ሆነበት ። አህያይቱም ሳሯን በነቄነት ስትኰመኩም በመዋኗ ጠግባ ቆማ ነበርና እሷን ለማምጣት ሩቅ ከመሄድ አድናዋለች ። ቀጥሎም ሮዚናንቴን ጐት ጉቶ አነሳው ። በውነቱ የብስጭት ስሜቱን የሚገልጥበት እንደ በት ቢኖረው ኖሮ ርዚናንቴም ላይ የደረሰው አደጋ በጌታውና በሳንቾ ላይ ከደረሰው የሚበልጥ በመሆኑ በዝምታ እንደታፈነ የሚያስቀረው አልነበረም ። መከረኛው ሳንቾ ዶን ኪሾትንም ደግፎ አነሳውና በሆዱ በኩል ደፍቶ በአህያይቱ ላይ ከጫነው በኋላ ሮንዚናንቴን ከኋላ ደጀን አድርጉ አህያይቱን በሉተሞ እየሳበ ወደ አውራው መንገድ የሚያገባ መስሎ የታየውን አቅጣጫ ይዞ ጉዞውን ጀመረ ። ይህም ሆኖ አንድ መረባ የሚ ሆን መንገድ እንደሄደ ዕድሉን ከመጥፎ ወደ ደህና በመለወጥ ለማታለል የሚረዳው ዕድሉ እየመራው ወደ አውራው መንገድ ለመድረስ ቻለና ጥቂት እንደተራመደ ደግሞ እሱ እንደሚያ ውቀው አንድ የመንገድ ዳር ሆቴል ተከሰተለት ። ለዶን ኪሾት ግን ይህ ሆቴል በግዴታ የመስፍን ማንብ መሆን ነበረበት ።

ሳንቾ ይህንኑ አውቆ ሆቴል መሆኑን እበክሮ አስጠነቀቀው። ጌታው ደግሞ የመስፍን ግንብ ነው ብሎ ድርቅ አለ ። በዚህ አኳኋን ክርክራቸው እየተራዘመ ስለሄደ ከመቆረጡ በፊት እሆ ቴል ለመድረስ ጊዜ አገኙ ። በዚህን ጊዜ ሳንቾ በብስጭቱ ላይ ይህ አጉል ክርክር ተጨምሮ እራሱን ስላዞረው ሆቴል መሆኑን ልጌታው ለማረጋገጥ ሲል ከብቶቹን ከነጭነታቸው እያግተለተለ ወደ ሆቴሉ ገባ ።

ምዕራፍ 16

ብልሁ መኰንን ፈረስኛው ዶን ኪሾት እሱ የመስፍን ግንብ ብሎ በሰየመው ሆቴል ውስጥ የደረሰበት ሁኔታ ይተረካል ።

ዶን ኪሾት በአህያ ላይ በሆዱ ተደፍቶ አግድም ተጭኖ ሲመጣ ሆቴለኛው እንደልማዱ እንግዳ ለመቀበል ወጥቶ አየውና ምን ዓይነት አደጋ እንዳገኘው ሳንቾን ጠየቀው ።

«ምንም አይደል ቀላል ጉዳት ነው ፤ ሲል መለሰ ሳንቾ ። አገር ሊቃኙ ከረጅም ቋጥኝ ድንጋይ ላይ ወጥተው ሳለ ድንገት አዳልጧቸው ተንከባልለው ስለወደቁ ታፋቸውን ወለም ብሏቸዋል» አለው ።

የሆቴለኛውም ሚስት እዚያው ቆማ ስታዳምጥ ነበረችና ይህን የመሰለውን የሆቴለኛነት ባሉትና ማደሪያቸው እድርገው ከሚኖሩት ሴቶች መካከል በጣም የተለየ ጠባይ ያላት በመሰሎቿ ላይ በደረሰው አደጋ ከልብ የምታዝን እርህሩህና ደግ ሴት ስለሆነች ወዲያው በፍጥነት ዶን ኪሾትን ተቀብላ ከዳበረችው ልጅዋ ጋር እየተረዳዳች ታስታምመው ጀመር ። ልጂቷም የደስ ደስ ያላት ደማም ብላቴና ነበረች ።

እንዲሁም ደግሞ በዚሁ ሆቴል ውስጥ ተቀጥራ የምትኣገለግል እንዲት የአስቱሪያ ተወላጅ የሆነች ገረድ ነበረች ። የፊቷ ቅርጽ ሠፊ ፤ አገጯ ጠፍጣፋ ፥ አፍንጫዋ ደፍጣጣ ፤ አንዱ ዓይኗ ሸውራራ ሆኖ ሁለተኛው ደግሞ የተጠናረ ቢሆንም የቀረው ሰውነቷ አፈጣጠር ደንደርነት ሌላውን ሴንቲ ሁሉ የሚከስ ላት ነበር ። ይህም ሆኖ ከእግርዋ እንስቶ እሰከ እራሷ ድረስ ቁመቷ ከሰባት ጋት የማይበልጥ ድብልብል ስለሆነች ትክሻ

ዋም መጠነኛ ጉብጠት የተጫነው ስለሆነ ይህ ጭነት እየከ በዳት ከማትፈልገው ይበልጥ ዓይኗን ወደ መሬት አቀርቅራ እን ድታይ አስገድዷት ነበር ። ይህች ዶለዝ ገረድ ከብላቴናይቱ ጋር በመተጋገዝ ሁለት ሆነው እሆቴሉ ውስጥ ከተሠራው ከቆጡ ላይ አንድ የማይረባ አልጋ ሰዶን ኪሾት ዘረጉለት ። ይህም ቆጥ በዱሮው ጊዜ ለብዙ ዓመት የገፈራ ማከማቻ ሆኖ ማገልገሉን የሚያስረዳ አንዳንድ የጉድፍ እርጋፊ ምልክት ሆኖ ይታይበ ታል ። እንዲሁም ደግሞ አንድ ነጋዴ እዚሁ ቆጥ ላይ ለማደር መኝታውን ከዶን ኪሾት አልጋ ጥቂት ፈቀቅ አድርጉ አን ጥፎ ነበር ። ምንም እንኳ የነጋዴው ምኝታ የተነጠፈው በበ ቅሎው ጪቅና መደላድል ቢሆን በምቹነቱ ከዶን ኪሾት አልጋ መቶ እጅ የሚበልጥ ነበር ። ምክንያቱም የዶን ኪሾት አልጋ የተሠራው በአራት ቋሚና በሁለት አግዳሚ እንጨት ፥ በጥ ቂትም እርብራብ ስለሆነ ከአሠራሩ ልልነትና ከአቋቋሙም ተዛ ነፍነት የተነሳ እግሩ እየተወናገረ የሚዋልል ስለሆነ ነው ። ፍራሹም የመሳሳቱ ብዛት ዲሬቶ የሚመስልና በውስጡም የተጐሰጐሰው ነገር በጣም የደደረ ከመሆኑ የተነሣ ባንዳንድ ቾርትር በኩል አፈት ልኮ የወጣው ጠጉር ባይታይ ኖሮ በእጅ ሲነኩት እጐረባበጡ በውስጡ ያለው ከጠጉር ይልቅ ጠጠር የተሞላበት ይመስል ነበር ። ገላ ነኩ ንጣፍ ደግሞ እንደ ቆዳ የከቸረ ፥ ብርድልብሱም ዘርዛራ በመሆኑ ድርና ማጉ አንድ ባንድ የሚቆጠር ሸክሸክ ነበር ። ይህም ሆኖ ዶን ኪሾት ሌላ ማማረጫ ስለሌለው በዚሁ በተ ነጠፈለት መጥፎ አልጋ ላይ ወጥቶ ጋደም አለ ።

ከዚህ በኋላ ሆቴለኛይቱና ልጅዋ ሆነው ቁስሉን እየፈለጉ መድኃኒት እየቀቡ በሻሽ ሲያሰሩለት ማሬቶሪኒዝ የምትባለዋ አስቱሪያዊት ደግሞ መብራት ይዛ ቆማ ነበር ። ሆቴለኛይቱ የዶን ኪሾትን ቁስል በምታስርበት ጊዜ በሰውነቱ ላይ ከቁስል ይልቅ የበለዘ ሰንበር በዝቶበት ስለአየች ይህ አቆሳሰል ከው ድቀት የተገኘ ከመምሰሉ ይልቅ ይበልጥ ወደ ድብደባ ይጠ ጋል ስትል ጥርጣሬዋን ገለጠች ።

« የለም ደብደባስ አይደለም » ሲል ሳንቾ ተከራከረ ጌታዬ የወደቁበት ቋጥኝ ከስሩ በጣም የቦለና ጉጥ የሞላባቸው ድን

ጊያዎች ስለነበሩ ወድቀው በሚንከባለሉበት ጊዜ ሰውነታቸው ከየሹለቱና ከየጉጡ ጋር በመጋጨቱ ምክንያት ይህን ምልክ ትና ሰንበር አደረገባቸው በማለት ካስረዳ በኋላ ንግግሩን በመ ቀጠል እባክዎ የኔ እመቤት ይህን ዓይነት ሕክምና የሚያስ ፈልገው ሌላም ሰው አይታጣምና ከሻሹና ከመድኃኒቱ ቀንሰው ያስተርፉ ይህንንም ማለቴ እኔም ጀርባዬንና ታፋዬን ውስጡን እየነዘረ ይቆረጥመኛል አለ ።

« እንግዲያውማ እርስዎም ወድቀዋል ማለት ነዋ ? ሰትል ሆቴለኛይቱ ጠየቀችው ።

« የለም መውደቅስ አልወደቅሁም » ሲል ሳንቾ መለሰ ። ዳሩ ግን ጌታዬ በኃይል ተምዘግዝገው ሲወድቁ በማየቴ ደን ግጬ ሰውነቴ ክፉኛ ስለተሰቀጠጠ ከዚያ ወዲህ እኔም ሰውነቴን ነዘረኝ ። በዱላ እንደተደበደብኩ ያህል ሁለመናዬ ቁስል ሆኖ ያመኛል ። አላት ።

« ይህ በርግጥ ሊደርስ የሚችል ነገር ነው » አለች ብላ ቴናይቱ ፤ ለምሳሌ በእኔ ላይ ብዙ ጊዜ እንዲህ ያለ ነገር ደር ሶብኝ እንደነበረ አስታውሳለሁ ። ይኸውም ዘወትር ሌሊት በሕልሜ ረጅም ስነነት ላይ ወጥቼ ይመስለኛል ከዚያ አንሸራቶኝ ቁልቁል ተወርውሬ እየወደቅሁ በፍጹም መሬት ለመንካት ሳልችል ጅው ብዬ ስወርድ እንደቅዠት ሆኖ እየታየኝ በድንጋጤ ባንኜ ስነቃ በእውነት እንደወደቅሁ ያህል ፊቴ ፍም መስሎ ሰውነቴ ሁሉ ድቅት ብሎ አምሳ አገኘዋለሁ ።

« እዬ የኔ ወይዘሪት» ሲል መለሰላት ሳንቾ ። « መቸ አንቺ እንዳልሽው በሕልም የደረሰ ሆነና እንዲህም ቢሆንልኝ ኖሮ መልካም ነበር ። እኔ ግን ሕመሙ የተሰማኝ በፍጹም ሳልተኛና እንዳች ሕልም ሳላይ ዓይኔን ኋውጥቼ እያየሁ ቀን ሰቀን በደረሰብኝ ድንጋጤ ነው ። ያውም እንዳሁኑ ሳልፈዘዝ በጣም ነቅቼ በምነሳበት ጊዜ ከጌታዬ ከዶን ኪሾት ጥቂት አነሰ በሚል መጠን ሰውነቴ ለመገጣጠብ ቢቃ» አሳት ።

«ለመሆኑ ፈረሰኛው ግን ይባላል» ሰትል አስቲሪያይቱ ማርቶርኔስ ጠየቀች ።

ኅ ፍኖ ፎቲ

«ስሙ የማንቻው ዶን ኪሾት ይባላል» ሲል መለሰ ሳንቾ ። ከብዙ ጊዜ ወዲህ በዓለም ላይ ከታዩት ከምርጦቹና ከብርቱ ዎቹ ዙዋሪ ፈረሰኞች መካከል አንዱ ነው ።

« ዙዋሪ ፈረሰኛ ማለትሳ ምን ማለት ነው » ብላ ጠየቀች ገረዲቷ ።

ሳንቾም እንዲህ ሲል መለሰላት ፤ እህቴ ሆይ ! እስከ ዛሬ ድረስ ይህን ነገር አለማወቅሽ ከዚህ ዓለም ብርሃን በጣም ርቀሽ ወደ ጨለማው ውኃን የምትገኚ ፍጹም እንግዳ በመሆንሽ ነረ መኝ ። ስለዚህ በበኩሌ ከታሪኩም ከተግባሩም ጠቅሼ ባጭሩ በሁለትና በሶስት ቃላት ላስረዳሽ እችላለሁ ። ዙዋሪ ፈረሰኛ ማለት እንዳንድ ሰሞን በድንገትና በቅጽበተ ዓይን በዱላ ተደ ብድቦ ወድቆ ሲያቃስት የሚገኝ ወይም ደግሞ አፍራሻውን በድል አድራጊነት ስሙ ተነሳስቶ ንጉሠ ነገሥት ለመሆን የሚችል መሆኑን ነው ። ዛሬ ግን ይህ ፈረሰኛ ከነጋሻ ጃግሬው በመላው ዓለም ላይ በጣም ዕድለቢስና መከረኛ ሆኖ ይገኛል። ነገ ወይም ተነገ ወዲያ ደግሞ በዱላ እየተጠለዘ አብሮት ለማ ቀቀውና በታማኝነት ሳገለገለው ጋሻ ጃግሬ የሚሰጠው ሁለት ወይም ሶስት የሚሆኑ ሰፊ ግዛቶች ይኖሩታል አላት ።

« ነገሩ እንዲህ ከሆነማ ታዲያ ምነው እርስዎ እንዲህ ላለው ደግ ጌታ ጋሻ ጃግሬ ሆነው ሳለ በሁኔታው እንደ ሚገመተው ቢያንስ ቢያንስ የምስለኔነት ሹመት እንኳ ያገኙ አይመስሉም» ሰትል ሆቴለኛይቱ ጠየቀችው ።

«ከተገናኘን በጣም ቅርብ ጊዜያችን ስለሆነ በችኮላ የሚ ደረስበት ነገር አይደለም ሲል መለሰ ሳንቾ » አጋጣሚያች ንን ለመፈለግ ዙረት ከጀመርን ገና አንድ ወራችን እንኳ አልሞ ላንም ። በዚህም ጊዜ ውስጥ እስካሁን ድረስ ይህን የመሰለውን ማዕረግ ሊያስገኝልን የሚችል ዕድል አላጋጠመንም ። አንዳንድ ጊዜ እንደሚደርሰው አንድ ደህና ነገር ለማግኘት ስንመኝ ሌላ ያልታ ሰበ ክፉ ነገር ከተፍ ብሎ ይገኛል ። ይሁን እንጂ እውነት ሆኖ ጌታዬ ከዚህ ቁስላቸው ወይም ወለምታቸው የዳኑልኝ እንደ ሆነ እኔም ከድንጋጤ ባገኘሁት ሕመም ለዘላለም ሽባ ሆኜ እን

ደግልቀር እርግጠኛ ስለሆንኩ አሁን በልቤ ውስጥ የተመሠረተውን ታላቅ ተስፋ ሌላው ቀርቶ በድፍን እስፖኒያ ውስጥ የሚገኘውን ከፍ ያለ የክብር ሹመት መርጠው ቢሰጡኝ እንኳ በፍጹም አልለውጠውም» አላት ።

ይህ ሁሉ ወሬ በሚወራበትና ጥያቄም በሚያረግበት ጊዜ ዶን ኪሾት ንግግራቸውን ተጠንቅቆ ያዳምጥ ነበርና የተ ቻለውን ያህል ተነስቶ አልጋው ላይ ከተቀመጠ በኋላ የሆቴ ለኛይቱን እጅ ጨበጠና እንዲህ ሲል ሃሳቡን ገለጠላት ።

« ደርባባይቱ ወይዘሮ ሆይ! በዚህ በተከበረው ግንብም ውስጥ እኔን የሚያህል የከበረ እንግዳ ለማስተናገድ በመቻልም የእድልዎን ታላቅነት ለመገመት እንደሚችል ይመኑኝ ። ይህ ነንም የምልዎት ምንም እንኳ እራሱን በራሱ የሚያመሰግን ሰው ዋጋውን ያቃልላል የሚባለውን ትዝብት በመስጋት እኔ እራሴን በራሴ ሳመሰግነው ባልፈልግም በተለይ እንድናገር የያነ ፋፋኝ ይህን እጅግ ከፍ ያለ አስተያየት የሚሰጠውን ጀግንነ ቱን ሳልገልጥልዎ ማለፍ የማይገባኝ ሆኖ ስለአገኘሁት ብቻ ነው ። እኔ ባልነግርዎትም ቅሉ ጋሻ ጃግሬዬ ማን እንደሆንሁ አብራርቶ ሊያስረዳዎ ይችላል ። በእኔ በኩል በተለይ ላረጋግጥ ልዎ የምፈቅደው በሕይወቴ እስካለሁበት ጊዜ ድረስ ይህን ያደረጉልኝን ታላቅ ወሮታና አገልግሎት ለዘለዓለም በትውስ ታቴ ውስጥ ቀርጬ የማኖረውና ውለታዎን ለመክፈል የሕሊና ግዴታ ያለብኝ መሆኑን ነው ። ከዚህም በሰተቀር ያግም የጊዜው አጋጣሚ ሆኖ በልቤ ውስጥ የበቀለውን ፍቅር ያጠባበቁንና ያኮታኰቱን ደንብ በጥንቃቄ እንድፈጽም ባልገደድና እንዲሁም አሁን ስሜን በጥርሶቼ እጥር ውስጥ ከብቤ የያዝኩት የዚያች የውለታቢሷ ውብ ዓይኖች ሰንዝር እንዳልላወስ እግር ተወርች አስረውና ዉቁነው ባይዙኝ ኖሮ ለወዳጅነታችን ማጠንከሪያ እንዲሆን የዚህችቁየቆንጆይቱ ልጅዎ ዓይኖች የነባኑቱ ባለቤቶች ሊሆኑ ይችሉ ነበር ።

ሆቴለኛይቱና ልጅዋ ፣ ያችም ምስኪኗ ማሪቶርኔስ ይህን የዙዋሪ ፈረሰኛውን ንግግር በሰሙ ጊዜ በግሪክ ቋንቋ የተና ገረ መሰሉ ስለተሰማችው ፍቺው ኤልጋባቸው ብሉ ሁሉም በመ ገረም ፈዝዘው ይመለከቱት ነበር ። ይህም ሆኖ ይህ ሐተታ ሁሉ ግጣው እነሱን ለማመሰገንና ለመመረቅ መሆኑ በቀላሉ ሊገ ባቸው ቻለ ። ይሁን እንጂ ሌቶች ይሆን የመሰለ ቄንጠኛ እን ጋዣ ሰምተው የማያውቁ ስለሆኑ ሁሉም እሱን እያዩ ወዲያው ደግሞ መለስ ብለው እርስ በእርሳቸው እየተያዩ በዶን ኪሾት ውኔታ ላይ ከሌሎች ሰዎች የተለየ ነገር ያለበት መሆኑን ይታ ዘቡ ነበር ። ስለዚህ እነሱም በአጸራሹ መንገድ በተለመደው የጣላገር አነጋገር ለምሲጋናውና ለምረቃው ለውጡን ሰጥተው ወደየሥራቸው ሲሄዱ ማርቶርኒዛ ብቻዋን ቀርታ ሳንቾም እንደ ጌታው ሕክምና ፈላጊ ነበርና ታክመው ጀመር ።

ይህ ከሆነ በኋላ አሁን ደግሞ ሌላ መታወቅ የሚገባው አንድ ነገር አለ ። ይሽውም ነጋዲው ከቀኑ ቀደም ብሎ ከገረዶቷ ጋር ባደረገው ንግግር ሌሊት እሱ ዘንድ መጥታ እንድትተኛ ለምኒት ስለነበረ እሷም እሺ ብላ እንግዶቹ ወጥተው ባለቤቶችም ተኝ ተው ሆቴሉ ጭር ካለ በኋላ እሱ ዘንድ ሄዳ ልትአድርና ልታ ስደስተው ቃል ገብታለት መቃጠራቸውን ነው ።

የዚህችን ገረድ ጠባይ የሚያውቁት ሰዎች እንደሚ ሉት ይህን የመሰለ ቀጠሮ እንኳንስ እዚህ እቅርቡ ይቅርና ምስ ክር በሌለበት በተራራ ሜፍ ላይ ብትቃርም እንኳን የቀጠሮ አጥባቂነቷ ብዛት ምንም ቢሆን ሳታደርገው የምትቀር አይደ ለችም ይሏት ነበር ። እሷም እንደምትለው እድለ ቢስነትና ዓይቶ ግጣት በሰው እጅ ላይ ጥፋት በዚህ ምክንያት ሆቴል ቤት ግርድና ብትቀጠርም ከውርደት የሚቆጠር ኑር አይደለም በማለት ቀድሞ እራሷን የቻለች እመቤት መሆኗን እያነሳች በትምክህት ትናገር ነበር ።

እንግዲህ ያ በጣም ደረቅና የአጭር ወንጋራ የሆነው የዶን ኪሾት ጉርብጣ አልጋ ወደገፈራ ማክሣቻው የጋጣ ቆጥ ላይ ቁመጡ መጀመሪያ ተነጥፎ የሚገኘው ነበር ። ከሱ ለጥቆ ያለው ደግሞ የሳንቾ መኝታ ነው ። የተነጠፈው በአረግ ግጠራ ላይ ሆኖ ብርድ ልብሱ ከሱፍ ይልቅ የቃጫ ኪሻ የሚመስል ነበር ።

ከነዚህ ከሁለቱ አልጋዎች አልፍ ሲል የሚገኘው የነጋዴው መኝታ ነው ። የሱም አነጣጠፍ ቅድም እንዳየነው የሁለቱን ምርጥ በቅሎዎች ዳውላና የጢቅ ግላስ ደራርቦ ነው ። ነጋዴው የሚነዳቸው በቅሎዎች ዘራቸው የታወቀ ገለቸው እንደተልባ የተለጠለጠ አሥራሁለት ወደሎች ነበሩ ። የዚህ ታሪክ ደራሲ እንደሚ ተርከው ይህ ነጋዴ በአርሼላምስ ከታወቁት ሀብታም ነጋዴ ዎች አንዱ በመሆኑ በጣም ስለሚያውቀውና እንዲያውም ለደ ራሲው ቅርብ የሥጋ ዘመዱ ስለሆነ ሁኔታውን በተለይ አብ ራርቶ ጠቅሰታል ። ይህም ሆኖ ደራሲው ሰይድ አህመድ ቤኒንጌል በተፈጥሮው በጣም ዝርዝር ወደሆኑት ጉዳዮች ውስጥ መግባት የሚወድ በመሆኑ የተነሳ የሚጽፈው ወሬ ሁሉ በዚህ መጠን ትክክለኛና የተለቀመ ነበር ። እስካሁንም ድረስ በተተረከው ውስጥ በግልጥ እንደሚታየው ምንም እንኳ እስከዚህ ድረስ አያሌ ጥቃቅን ዝርዝሮችና ደቃቅ ነገሮች ቢገኙበት ደራሲው ይህ ንኑ ሳያሰማ በዝምታ ሸፍኖ ለማለፍ አልፈለገም ነበር ።

ስለዚህ በተፈጥሮ ዝንጉነታቸው ወይም ደግሞ በስንፍና ቸውና በድንቁርናቸው ምክንያት የድርሰታቸውን መሳዛ በቀ ለሙ መድ ውስጥ ትተው ድርጊቶችን በጣም አጣድፈውና አሳ ጥረው የሚተርኩት ምርጥ የተባሉት ደራሲያን ሁሉ የአጻጻ ፋቸውን ምሳሌና ዘይቤ ከዚህ ዓይነት አተራረክ ቢቆጹት ኖሮ ይበልጥ ጣእም ያለው ይሆንላቸው ነበር ። ይህም ስለተባለ በተሰይ «የሪካሞንቴው ታብላንቲን» ታሪክና እንዲሁም የኩንቴ ቱሚላስ ድርጊት የሚተርክበትን መጽሐፍ የጻፉት ደራሲያን ገሸ ምስጋና ይገባቸዋል ። በእውነቱ ማናቸውንም ድርጊት በምን ያህል ትክክ ለኛነት አበጥረውና ዘርዝረው ፤ አብራርተው እንደጻፉት ሲታይ አስተዋይነታቸው እጅግ የሚያስደንቅ ነው ።

ከላይ ምን ብዬ ነበር ፤ እነሆ እንግዲህ ነጋዴው አጋሰሶችን ከታሰሩበት ሥፍራ ጉብኙት ለእራታቸውም ሁለተኛውን ድርሻ ገብስ አከፋፍሎ ከተመለሰ በኋላ በቀጥታ ወደ መኝታው ቆሞ ወጣና ከመደብሩ ላይ ተጋድሞ ቀጠሮ አጥባቂቷን ማሪተርኔስን ይጠብቅ ጀመር ። ሳንኾም መላ ሰውነቱ በቅባት ተለቅልቆ በሻሽ እንደተተበተበ በጀርባው ተንጋሎ ለመተኛትም እየከ ጀለ የታፋው ሕመም ግን እንቅልፍ ነስቶት እየተማረረ ያታ ስት ነበር ። ዶን ኪሾትም በበኩሉ የሚሰማው ከባድ ሕመም እያሰቃየው ዓይኖቹን እንደ ጥንቸል እንዳፈጠጠ ተጋድሞ ነበር ። በሆቴሉም ውስጥ ታሳቅ ፀጥታ ነግሦ ዙሪያው ጭር ብሎ ስለ ነበረ በሆቴሉ በስተቡሩ አኳያ ከማዕዘኑ መግቢያ መሃል ላይ ከተንጠለጠለው አንድ ፋኖስ በስተቀር በምድረ ግቢው ሌላ ሙብ ራት አይታይም ነበር ። ይህ በሆቴል ከተለመደው ውካታና ጫጫታ የተለየው ፀጥታ የሚሰጠው የአእምሮ እረፍትና ሠላም ዙዋሪው ፈረሰኛችን ለእብደቱና ለአደጋው ምክንያት በሆኑት መጻሕፍት ውስጥ በየገጻቸው ላይ ተጽፈው የሚገኙትን የፍ ቅር ሁኔታዎች ለማስታወስ ስለረዳው ለሰሚ እጅግ አድርጉ የሚያስገርምና ማንም አስቦት የማያውቀውን የቅሌት መንፈስ ፈጠረበት ። መቼም ብዙ ጊዜ እንዳስረዳነው ፈረሰኛው የሚያድር ባቸው ሆቴሎች ሁሉ በሱ አስተያየት የመስፍን ግንቦች ስለሆኑ የዛፊውንም ሌሊት ባንድ ስመ ጥሩ በሆነ የመስፍን ግንብ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን በአእምሮው ውስጥ ቀረፀ ። እንዲሁም ደግሞ የሆቴሉኛው ልጅ የመስፍኑ ልጅ መስላ ታየችው ። ይህችም ብላቴና በፈረሰኛው ትክለ መልካምነትና የትህትና ጠባይ ተማ ርካ ልቧ በጽኑ ፍቅር በመነደፏ የተነሳ ሌሊት ከቤተሰቦቿ ተደብቃ ወደሱ የምትመጣና አብራው የምታድር ለመሆኗ ታል የገባች መሆኑን በሃሳቡ አረጋገጠ ። ይህን በአንጐሉ ውስጥ ያገባውን የቅዠት ትዝታ እውነተኛ ነገር አድርጐ ስለቆጠረው በዚህ ምክንያት እስካሁን ድረስ በፍጹም ታማ ኝነት ጠብቆ ባቆየው ንፁህነቱ ላይ የሚደርሰውን ከባድ የክሃዲነት ፈተና በማሰብ ይጨነቅ ጀመር ። ባንድ በኩል ደግሞ ይህን አደገኛ ፈተና ለማሸነፍ የሚችልበትን ብርታት ለማግኘት ሲል መንፈሱን ይበጠብጠው ጀመር ። በዚህ አኳ ኋን የባሰውን ጤናው ታውኮ የተረፈውንም አንጐሉን ካደነ ዘዘው በኋላ በመጨረሻው ውሳኔ እንኳንስ የመስፍኑ ልጅና በቁ ንጅናዋ የተደነቀችው ንግሥት ጄኔቭራ እራሷ ከሞግዚቷ ቺን ታዮና ጋር መጥታ ብትለምነው የሱን እመቤት የዱልቺኔያን ክብር የሚነካ አንዳች የውስልትና ሥራ ከመሥራት ለመታ ገድ መስዋዕት ለመሆን በልቡ ቆርጠ ።

በዚህ የተዘበራረቀ ሃሳብ ውስጣው ተወርሮ በሚገኝበት ጊዜ በእድሉ መጥፎነት ልክ በዚያኑ ሰዓት ባለቀጠሮይቱ አስቴሪያዊት ከተፍ አለች ። እሷም የውስጥ ልብሷን ብቻ እንደለበሰች ኮሽታ እንዳይሰማባት ጫማዋን አውልቃ ፀጉሯንም ሸብ ልላ በጨርቅ አስራ በቀስታ እርምጃ እየተራመደች ሶስቱም ሰዎች መደተኙበት ቆጥ ላይ ከወጣች በኋላ በዳበሳ ነጋዴውን ትፈልግ ጀመር ። ዳሩ ግን ቦታው ጠፍቶባት ስትንገዋለል ዶን ኪሾት ስለሰማት ምንም እንኳ ቁስልና መለምታው ቢያስቸግረው ተነስቶ አልጋው ላይ ተቀመጠና በሕልሙ ሲያያትና ሲጨነቅባት የነበረችውን ተወዳጅዋን የመስፍኑን ልጅ ለመቀበል እጁን ዘርግቶ ይጠባበቅ ጀመር ። አስቴሪያዊቷም ድምጿን አጥፍታ ጉንበስ ብላ ወዳጅዋን ለመፈለግ እጅዋን ሰድዳ ስትዳብስ እንዳጋጣሚ ከዶን ኪሾት እጅ ጋር ስለተገናኘች ክንዷን ጨበጠና እንዳንዳች ቃል ሳይናገር ጉትቶ እጉኑ አስቀመጣት። ከዚያም በኋላ ሰውነቷን ዳብሶ የውስጥ ልብሷን ነካ ፥ ምንም እንኳ የውስጥ ልብሷ ከክሩይ ጨርቅ የተሰራ በለሴ ቢሆን ሰሱ የረቀቀ ሐር መሰሎ ታየው ። በእጅዋም ላይ አምባር አገኘ ። ይህም አምባር የቁርበት አሊምና የዶቃ ስክ ቢሆን የምስራቅ አልማዝ መስሎ ታየው ። ፀጉሯም እንደጋማ ጠጉር የከረደደም ቢሆን በጣም ዘማና የወርቅ ነዶ በመሆኑ ያብረቅራቂነቱ ኃይል የፀሐይን ብርሃን የሚያጨልም መስሎ ታየው ። የነጭ ሽንኩርት ጠረን የሚሸተው ትንፋሿ ደግሞ ልብ የሚያናውጥ ናርዶስ ሽቱ ሆኖ ተሰማው ። በጠቅላላው ነገሩን አሳጥሮ ለመጨረስ እንዲመች በዚያው በአነበበው መጽሐፍ ላይ ሁኔታዋ ተጽፎ ከሚገኘው ልዕልት ጋር በማመሳሰል የሰውነቷን ቅርጽና አፈጣጠር አለባበሷንና ጌጧን መዓዛዋን በሙሉ ይህችኛዋም የያዘች አድርጉ በሃሳቡ ተረጐመ። ይህችም በታሪኩ ውስጥ የምትገኘው ልዕልት በፍቅር ተሸንፋ በጣም ቆስሎ የተኛውን ፈረሰኛ ለመገናኘት ሄዳ እንደነበርና ሌላም ከዚህ ሁኔታ ጋር የተየያዘ ዝርዝር ነገር ሁሉ በሚተረከው ልብ ወለድ ታሪክ ላይ ተጽፎ የሚገኝ ነበር ። ስለዚህ የዚህ የምስኪኑ ፈረሰኛ አእምሮ ከሕፃን ልጅ ያነሰ ደካማ ባይሆን ኖሮ የገረዲቷን ገላ በመዳሰስ የተሰማውም ሆነ ። ከትንፋሿ ያሸተተው፥ እንዲሁም የነበራት ሌላው ጠረኗ ሁሉ አንድነት ሆኖ ነጋዴ ሳልሆኑ

ለማናቸውም ሰው ቢሰማ ኖሮ ወዲያውኑ አትልሽልሾ የሚያስታውክ ስለነበረ ይህ ጉድለት ብቻ ከመታለል ሊያድነው ይችል ነበር ። እሱ ግን የጅልነቱ ብዛት በክንዱ ያቀፋት የቁንጅና ንግሥት መሆኗን እምኖ ነበርና በውል አጥብቆ አቅፎ በተለሳለሰና በማቆላመጥ አነጋገር እንዲህ ይላት ጀመር ።

« እጅግ የተከበርሽውና ፀጋ የተሞላሽው ልዕልት ሆይ ! በፊቴ ላይ የሚያንፀባረቀውን ታላቁን የውበትሽን ፀዳል በማየቴ ይህን እጅግ ከፍ ያለውን ወሮታ ለመክፈል የሚናርብኝን ግዴታ ለመፈጸም በምችልበት ሁኔታ ላይ ለመገኘት ምንኛ ፈቃዴ እንደነበረ የምገልጥበት አንደበት ያጥረኛል ። ዳሩ ግን አጉል ዕድል ደጉችን እየተከታተለ ከማሰናከል ምንግዜም የማይደክመው በመሆኑ ክፉኛ ተጉድቼ ቆሰዬ እዚህ አልጋ ላይ እንድገኝ አድርጐኛል ። በበኩሌ ፍቅራዊ ፍላጐትሽን ለመፈጸም ፈቃደኛ ብሆንም እንኳን የአሁኑ ሁኔታዬ እንዳልችል አድርጐኛል። በዚህም አለመቻሌ ላይ ሌላ ይበልጥ ከፍ ያለ መሰናክል ተጨምሮበታል ። ይኸውም የሃሳቤን የምስጢር ቁልፍ ለያዘችው ለአመቤቴ ለወደር የሌሽ የተቦዘይቱ ዱልቺያ የገባሁት የታማኝነት ቃል ኪዳን ነው ። ይህ መሰናክል ባይኖርብኝ ኖሮ ይህን በታላቅ ለጋስነት የቀረበልኝን ዕድለኛ እጋጣሚና መልካም ሰጦታ ገፍቼ ለመመለስ እስከዚህ ድረስ የጀልሁ ፈረሰኛ አል ሆንም ነበር » አላት ።

ማሪቶርኔስ ግን ይህን ለሚያህል ጊዜ ከዶን ኪሾት ጋር ያሰው ውዴታው ምስጢር ይዛ በመቆየቷ ነጋዴው ምን ይለኝ ይሆን በማለት ክፉኛ ስለሰጋች ሰውነቷ በላብ ተዘፍቆ ነበር ። ዶን ኪሾትም እያከታተለ የሚናገረውን ሐተታ ለመስማት እንዳችፍላጐት ሳይኖራት ከእጁ አምልጣ ለመሄድ ብቻ በተቻላት መጠን ትታገለው ነበር ። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ መንተት እየሆነ አንዲት ቃል እንኳ አምልጧት ድምጽ አላሰማችም ነበር።

ያ ጐረምሳ ነጋዴ ደግሞ ከቀድሞ ጀምሮ ያንን መጥፎ ፍላጐቱን ለመፈጸም ሲል እንደጐመጀ የማሪቶሪኔስን መምጣት ነቅቶና እንቅቶ ይጠባበቅ ነበርና ገረዲቱ ወደ ቆጡ ከወጣች በት ጊዜ እንስቶ እዚሁ እመካከላቸው መኖሯን አውቆ ዶን

ኪሾት የሚናገረውን ሁሉ ተጠንቅቆ ያዳምጥ ነበር ። በዚህ ሁኔታ አድብቶ እንደተቀመጠ ብዙ ሰዓት ከጠበቀ በኋላ ትእ ግሥቱን ስለጨረሰ ፥ እንዲሁም ደግሞ አስቴሪያይቱ ታልሞን ያልጠበቀች ሆና በሌላ ሰው የለመጠችው ስለመሰለው በዚህ አኳኋን በመታለሉ ቅናትና ንዴት አቁነጠነጠውና ከመኝታው ተነስቶ በዝግታ ሄዶ ከዶን ኪሾት አልጋ ጫፍ ላይ ተቀመጠ ። እዚያም እንደሆነ የሹክሹክታቸው ምስጢር ፍጻሜው ምን እን ደሆነ ለማወቅ አደፍጦ ቢያዳምጥም አልሰማው አለ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ገረዲቷ ከዶን ኪሾት እጅ ለመላቀቅ ስትታገል እሱ ደግሞ አጠገቡ እንድትቆይ ለማድረግ ሲጐትታት በመስ ማቱ ይሀን አጉል ልፊያቸውን ስላልወደደ እጁን ሠነዘረና ፍቅር ያጠቃውን ፈረሰኛ በዚያ በሚሸሸው ጉንጩ ላይ አንድ ኃይ ለኛ ቡጢ ቢያሳርፍበት በአፉ ውስጥ ደም ሞላበት ። በዚህ ብቻ የልቡ ስላልደረሰ ዘሎ አልጋው ላይ ወጣና በዱላ የቆሰለውን ታፋውን እየረገጠ ይጨፍርበት ጀመር ። አልጋውም ወደኋላ ራቅ ብሰን እንዳስረዳነው ሥራው ግብዝ በመሆኑ ምክንያት ረግቶ የቆመ አልነበረምና የነጋዴው ክብደት ሲታከልበት ጊዜ ሚዛኑ ባንድ ወገን አጋድሎ በቋፍ የነበረው አልጋ ወላልቆ ወደ መሬት ለሽ አለ ። በዚህ ጓንታ ሆቴለኛው ተሸብሮ ከአ ንቅልፉ ነቅቶ ከተነሳ በኋላ ጉሮሮው እስቲሰነጠቅ ድረስ ማር ቶርኔስን ይጠራት ጀመር ። እሷም ፊርታ ለጥሪው ስላልመለ ሰችለት በዚህ ጓንታ ውስጥ እሷ እንዳለችበት ሆቴለኛው በቶሎ ገባው ። በዚህ ጥርጣሬ ካልጋው ላይ ወርዶ መብራት አብርቶ ጓንታውን ወደሰማበት ቆጥ ላይ ወጣ ። ገረዲቷም የጌ ታዋን መምጣት በሰማች ጊዜ ሰውዬው ክፉ ተደበደቢ መሆ ኑን ታውቃለችና በፍርሃት እየተንቀጠቀጠች ወደ ሳንቾ አልጋ ሸሸችና እሆዱ ላይ ወጥታ ጭብጥብጥ ብላ ተሸጉጠች ። እሱም እንቅልፉን ሲያባብል ውሎ ገና ተኝቶ ማሸለቡ ስለነበረ ሰጊ ዜው ቶሎ አልነቃም ነበር ። ሆቴለኛውም ድምጹን ከፍ አድ ርጐ በቁጣ እየጮኸ ወደ መካከላቸው ገባ ።

« ወዴት ነሽ አንቺ ሸርሙጣ ፥ ይሀን ቆጥ የምታተራም ሽው ያለጥርጥር አንቺ ነሽ! ነይ ውጭ ከዚህ አንቺ አለሌ ጋለ ሞታ ፥ እያለ የስድብ መዓት ያወርድባት ጀመር ።

እዚህ ነጥብ ላይ የሆቴለኛው ጩኸት ሳንቾን ስለቀሰቀ ሰው ባንና ተነሳ ። ወዲያውም በሆዱ ላይ የተጫነው ሸክም ከብዶ ስለተሰማው አጋንንቶች የሠፈሩበት መስሎት እንደባባ በቡጢ ወዲያና ወዲህ እየመታ ማሪቶሪኔስን ደህና አድርጐ ይጠ ልዛት ጀመር ። በዚህ አኳኋን በመመታቷ ክፉኛ ስለተናደደች ፍራቷን ሁሉ ተወችና እሷም በበኩሏ ሳንቾን በርከት አድርጋ በቡጢ እየደመለች የመትኖት ፍላጐቷን አስወገደችለት ። ሳን ቾም መቺው ማን እንደሆነ ሳያውቅ ክፋኛ በመመታቱ በንዴት ስለጋለ ተጣጥሮ ተነሳና ማሪቶርኔስን ጨምድዶ ከያዘ በኋላ በዚህ ዓለም ላይ በጣም የሚያስቅና በጣም የመረረ ጠብ ፈጥ ረው በቡጢና በንከሻ በቡጨራና በጉሸምታ ይናረቱ ጀመር ። ነጋዴውም ደግሞ በሆቴለኛው መብራት ብርሃን ወዳጁ በእንዴት ያለ ጭንቅ ውስጥ ተወጥራ እንደምትገኝ ስላየ ዶን ኪሾትን ለቀቀና ሊረዳት ወደርሷ ሲሄድ ሆቴለኛውም ተከተለው ። ዳሩ ግን የሆቴለኛው አካሄድ በሌላ ዓይነት ንዴትና ስሜት ነበር ። ምክንያቱም የዚህ አባጓሮ እና ረብሻ ዋና ሰበብ የሆነችው ማሪ ቶርኔስ መሆኗን በበኩሉ እርግጠኛ ሆና ስላመነ በዚህ ጥፋቷ ሊቀጣት በማሰብ ነው ። ለዚህም ጠብ የተሰጠው ምሳሌ «ድመት አይጥን ፥ አይጥ ጅራፍን ፥ ጅራፍ በሬን ፥ እንደሚበላው ስለሆነ ነጋዴው ኪሾትን ፤ ሳንቾ ገረዲቷን ፤ ገረዲቷ ሳንቾን ፤ ሆቴለኛው ገረዲቷን በመምታት ያላንዳች ገላጋይና ያላንዳች እረፍት እንደ እብድ ይዋቁ ነበር ። የባሰውን ደግሞ ሁኔታውን ያከፋው በፍ ጅቱ መካከል የሆቴለኛው መብራት መጥፋት ነው ። በዚህን ጊዜ ሁሉም በጨለማ ውስጥ ሆነው አንዱ ባንዱ ላይ እንደተ ዛዘሉ የዕውር በትር እንደሚባለው ቦታ ሳይለዩ ለሞት በሚ ያስጋ አመታት መከሳከሳቸውን ቀጠሉ ። ከመላ ሰውነታቸው አንዳች እንኳን በትር ያላረፈበት ስፍራ አልነበረም ።

እንዳጋጣሚ ደግሞ የዚያን ዕለት ማታ የድሮው የቶሌዶ አገር የወንድማማችነት አድር የጉበዝ አለቃ የሆኑት ሽማግሌ ሰው በሆቴሉ አደረው ነበርና ይሀን እየተጋጋለ የሚሄደውን ድብልቅልቅና ሁካታ በሰሙ ጊዜ ከእጃቸው የማይለዩትን ምር ኩዛቸውን እና የቅርቆሮ ሳጥናቸውን ከግል ሰነዳቸው ጋር ይዘው በጨለማ ውስጥ እየጮኹ ወደ ቆጡ አመሩ ። እዚያም

እንደደረሱ በሕግ ስም ቁሙ ፤ በዕድር ስም ቁሙ ፤ እያሉ ያወጣዙ ጀመር ።

እንዲህ እያሉ ወደሰዎቹ ሲጠጉ መጀመሪያ አግራቸውን ያደናቀፈው ዶን ኪሾት ነበር ። እሱም ከተሰበረው የአልጋ እንጨት ላይ ወድቆ ሕሊናውን እንደሳተ አፉን ወደላይ እንዳንጋጠጠ ተዘርግቶ ሰለነበረ ዝቅ ብለው እጃቸውን ሰደው በዳበሳ እየተመ ተመ እሪዙን ጨምድደው ከያዙ በኋላ ጩኸታቸውን ሳያቋ ርጡ « የሕግ ያለህ ድረሱ ሰው ተላለቀ » እያሉ እርዳታ ይጠ ይቁ ጀመር ።

ዳሩ ግን የተያዘው እሥረኛ ጥቂት እንኳ የማይንቀሳቀስ በመሆኑ የሞተ ሰለመሰላቸው እና በውስጡም የሚገኙት ሰዎች ሁሉ የሱ ገዳዮች ስላደረጓቸው በዚህ ጥርጣሬ ድምጻቸውን ከቅድሙ ይበልጥ አጉልተው ኡኡታቸውን አስተጋቡ ።

«የሆቴሉ በር ይዘጋ ! ከዚህ ቆጥ ላይ አንድ ሰው ተገድ ሏልና ማንም ሰው ከዚህ እንዳይወጣ» ። ብለው አስጠነቀቁ ። በዚህ ማስጠንቀቂያ ጩኸት ተዋጊዎቹ ስለተደናገጡ ልክ ድም ጹን እንደሰሙ ወዲያው ሁሉም መሣታታቸውን አቋርጠው ፀጥ አሉ ። ሆቴለኛውም ሹልክ ብሎ ወደ መኝታ ክፍሉ ሄደ ። ኑጋዴውም ወደ መደብሩ ተመለሰ ። ገረዷም ወደ ጓዳዋ ገባች። እነዚያ ሁለቱ መከረኞች ዶን ኪሾትና ሳንቾ ግን ሌላ መሄጃ ስለሌላቸው ከወደቁበትም ለመነሳት ስለማይችሉ እዚያው እወደ ቁበት ቦታ ብቻቸውን ቀሩ ። የጉበዝ አለቃውም እስካሁን ጨብጠውት የነበረውን የዶን ኪሾትን ሪዝ ለቀቁለትና መላ ራት ፈልገው ወንጀለኛውን መርምረው ለማሰር ወጡ ። ዳሩ ግን ሆቴለኛው ወደ መኝታ ክፍሉ በተመለሰ ጊዜ በሆቴሉ መግቢያ በር ሲበራ የነበረውን ፋኖስ ሆነ ብሎ አጥፍቶት ስለነበረ መብራት ለማግኘት አልቻሉም ። ስለዚህ ወደ ወጥቤቱ ምድጃ ሄደው እሳት ለማንደድ እየተንጐዳጐዱ ብዙ ጊዜ ከፈ ጀባቸው በኋላ በመጨረሻው አንዲት ኩራዝ ለማያያዝ ቻሉ ።

ምዕራፍ 17

ቆፍጣናው ዶን ኪሾት ለገዛ ጥዳቱ የመስፍን ማንብ ብሎ በሰየመው ሆቴል ውስጥ ከጋሻ ጃግሬው ከሳንቾ ፖንቻ ጋር የተቀበሉት ስፍር ቁጥር የሌለው አግርና ፍዳ መተረኩ ይቀጥላል ።

እስከዚያው ድረስ ዶን ኪሾት ነፍስ ዘርቶ ፡ ሰውነቱን ካወቀ በኋላ በመጀመሪያው ቀን « በሽመል ሸለቆ » ላይ ኮደብድቦ ወድቆ በነበረበት ጊዜ ጋሻ ጃግሬው በጠራበት በዚያው ዓይ ነት ቀሰስተኛ ድምጽ እንዲህ እያለ ይጠራው ጀመር ።

«ወዳጄ ሳንቾ ተኝተሃል ? ተኝተሃል ፤ የኔ ወዳጅ ሳንቾ

«እንዶምን አደርገህ ነው ተኛ የሚሉኝ ! እምላክ ሞቴን ባቀረበውና ለመሆኑ የትኛው ጤናዬ ነው የማያስተኛኝ አለ። ሳንቾ እንደተበሳጨና እንደበገነ በክፋት የተበከሉና የተሰበሰቡ ተንኮለኞች ሁሉ ዛሬ ሌሊት ተሰብስበው በላዬ ላይ ሲጨፍሩ ሩብኝ እየሰማኋቸው ምኑን ተኛሁት»

..... «እሁን እንዳልከው ዛሬ ሌሊት የደረሰብን ሁኔታ በጂ ያብሎስ ሕቅድ የተመራ ለመሆኑ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ መሆን ትችላለህ» ሲል መለሰለት ዶን ኪሾት » .... ምክንያቱም ፡ ወይም እኔ ነጉላ ሆኜ ይሆናል ፡ ወይም ደግሞ ይህ ግንብ ያለጥርጥር በተበብ ኃይል የተመረረ መሆን አለበት ። የሆነው ሆኖ በተ ላይ አሁን ልነግርህ ያለብኩትን ምስጢር እኔ እስክሞትልህ ድረስ ለማንም ቢሆን እንዳታወጣው እስቀድመህ እንድትም ልልኝ እፈልጋለሁ » አለው ።

«በደስታ እምልልዎታለሁ» ሲል መለሰ ሳንቾ ፡

እንደደረሱ በሕግ ስም ቁሙ ፤ በፅድር ስም ቁሙ ፤ እያሉ ያውጠጡ ጀመር ።

እንዲህ እያሉ ወደሰዎቹ ሲጠጉ መጀመሪያ አግራቸውን ያደናቀፈው ዶን ኪሾት ነበር ። እሱም ከተሰበረው የአልጋ እንጨት ላይ ወድቆ ሕሊናውን እንደሳተ አፉን ወደላይ እንዳንጋጠጠ ተዘርግቶ ስለነበረ ዝቅ ብለው እጃቸውን ሰደው በዳበሳ እየተመ ተሙ እሪዙን ጨምድደው ከያዙ በኋላ ጩኸታቸውን ሳያቋ ርጡ « የሕግ ያለህ ድረሱ ሰው ተላለቀ » እያሉ እርዳታ ይጠ ይቁ ጀመር ።

ዳሩ ግን የተያዘው እሥረኛ ጥቂት እንኳ የማይንቀሳቀስ በመሆኑ የሞተ ስለመሰላቸው እና በውስጡም የሚገኙት ሰዎች ሁሉ የሱ ገዳዮች ስላደረጓቸው በዚህ ጥርጣሬ ድምጻቸውን ከቅድመ ይበልጥ አጉልተው አሰታቸውን አስተጋቡ ።

«የሆቴሉ በር ይዘጋ ! ከዚህ ቆጥ ላይ አንድ ሰው ተገድ ሏልና ግንም ሰው ከዚህ እንዳይወጣ» ። ብለው አሰጠነቀቁ ። በዚህ ማስጠንቀቂያ ጩኸት ተሞጊዎቹ ስለተደናገጡ ልክ ድም ጹን እንደሰሙ ወዲያው ሁሉም መሣታታቸውን አቋርጠው ፀጥ አሉ ። ሆቴለኛውም ሹልክ ብሎ ወደ መኝታ ክፍሉ ሄደ ። ነጋዴውም ወደ መደብሩ ተመለሰ ። ገረዷም ወደ ጓዳዋ ገባች። እነዚያ ሁለቱ መከረኞች ዶን ኪሾትና ሳንቾ ግን ሌላ መሄጃ ስለሌላቸው ከወደቁበትም ለመነሳት ስለማይችሉ እዚያው እወደ ቁበት ቦታ ብቻቸውን ቀሩ ። የጮበዝ አሊቃውም እስካሁን ጨብጠውት የነበረውን የዶን ኪሾትን ሬዝ ለተቁለትና መብ ራት ፈልገው ወንጀለኛውን መርምረው ለማሰር ወጡ ። ዳሩ ግን ሆቴለኛው ወደ መኝታ ክፍሉ በተመለሰ ጊዜ በሆቴሉ መግቢያ በር ሲበራ የነበረውን ፋኖስ ሆነ ብሎ አጥፍቶት ስለነበረ መብራት ለማግኘት አልቻሉም ። ስለዚህ ወደ ወጥቤቱ ምድጃ ሄደው እሳት ለማንደድ እየተንጐዳጐዱ ብዙ ጊዜ ከፊ ጀባቸው በኋላ በመጨረሻው እንዲት ኩራዝ ለማያያዝ ቻሉ ።

ምዕራፍ 17

ቆፍጣናው ዶን ኪሾት ለገዛ ጉዳቱ የመስፍን ግንብ ብሎ በሰየመው ሆቴል ውስጥ ከጋሻ ጃግሬው ከሳንቾ ፓንቻ ጋር የተቀበሉት ስፍር ቁጥር የሌለው እግርና ፍዳ መተረኩ ይቀጥላል ።

እስከዚያው ድረስ ዶን ኪሾት ነፍስ ዘርቶ ፡ ሰውነቱን ካወቀ በኋላ በመጀመሪያው ቀን « በሽመል ሽለቆ » ላይ ተደብድቦ ወድቆ በነበረበት ጊዜ ጋሻ ጃግሬው በጠራበት በዚያው ዓይ ነት ቀለስተኛ ድምጽ እንዲህ እያለ ይጠራው ጀመር ።

«ወዳጄ ሳንቾ ተኝተሃል ? ተኝተሃል ፤ የኔ ወዳጅ ሳንቾ

«እንደምን አድርገህ ነው ተኛ የሚሉኝ ! አምላክ ሞቴን ባቀረበውና ሊመሆኑ የትኛው ጤናዬ ነው የሚያሰተኙኝ እሰ ሳንቾ እንደተበሳጨና እንደበገነ በክፋት የተበከሉና የተሰበሰቡ ተንኮለኞች ሁሉ ዛሬ ሌሊት ተሰብስበው በላዩ ላይ ሲጨና ሩብኝ እየሰማኋቸው ምኑን ተኛሁት»

..... « እሁን እንዳልከው ዛሬ ሌሊት የደረሰብን ሁኔታ በጂ ያብሎስ እቅድ የተመራ ለመሆኑ መሉ በመሉ እርግጠኛ መሆን ትችላለህ» ሲል መልሰለት ዶን ኪሾት » .... ምክንያቱም ፡ ወይም እኔ ነጉላ ሆኜ ይሆናል ፡ ወይም ደግሞ ይህ ግንብ ያለጥርጥር በተበብ ኃይል የተወረረ መሆን አለበት ። የሆነው ሆኖ በተ ለይ አሁን ልነግርህ ያሰብኩትን ምስጢር እኔ እስከሞትልህ ድረስ ለማንም ቢሆን እንዳታወጣው እስቀድመህ እንድትም ልልኝ እፈልጋለው » አለው ።

«በደስታ እምልልዎታለሁ» ሲል መለሰ ሳንቾ ፡

« የመሐላ ቃልህን እንድትሰጠኝ የፈለግሁበት ምክንያት ሲል ማሰረዳቱን ቀጠለ ዶን ኪሾት በምስጢር የተደረገ ነገር ሁሉ አንድ ቀን ይፋ ወጥቶ ወሬው ተዛምቶ በመሰማቱ የማንም ክብር እንዲነካና የማንም ስም እንዲጠፋ ስለማልፈ ቅድና ደስም ስለማይሰኝ ብቻ ነው » አለው ።

እኔም ደጋግሜ የማረጋግጥልዎ « ሲል መለሰ ሳንቾ » እር ስዎ ከሞቱልኝ በኋላ ነው ። እንጂ በሕይወት እያሉ ለማንም በሆን ላለወራ መሐላው ይድረስብኝ ። ዳሩ ግን የልዩ አጋጣሚ ኃይል ሆኖ ይህን ምስጢር ነገ ዋዋት ለማውራት እንዲያበቃኝ እጸልያለሁ አለው ።

« እንዴት በል ሳንቾ ሲል ተገረመ ዶን ኪሾት .... ለመሆኑ እስከዚህ ድረስ በድያለሁ እንዴ እንዲህ በቅርብ ሞቴን ለማ የት የቸኮልከው » ....

.... «የለም ይህን ማለቴስ አይደለም ። ሲል መለሰ ሳንቾ» ዳሩ ግን እንኳንስ የሌላ ሰው ምስጢር ለመደበቅ መቻሌ ይቅ ርና የራሴንም ምስጢር ቢሆን ለረዥም ጊዜ ደብቄ ማቆየት በፍጹም ስለማያሰችለኝ መሐላየን ለመጠበቅ ስል ብዙ ጊዜ በሆዴ ውስጥ ቀብሬ በማቆየቴ ምክንያት ሥራይ እንዳይሆንብኝና ምስ ጢሩም ተበላሽቶ እንዲቀር ባለመፈለጌ ብቻ ነው ።

« በዚህ ባልከውም ሆነ ወይም በሌላ በተሠወረ ምክን ያት » ሲል ዶን ኪሾት አስተያየቱን ገለጠ ። አንተ ከምትም ልልኝ መሐላ ይልቅ ስለኔ ባለህ ፍቅርና በጐ አስተያየት ላይ የበለጠ እምነት ስለማደርግ መጠራጠሬን ትቼ ምስጢሩን ልገ ልጥልህ እፈቅዳለሁ ። ይኸውም ዛሬ ሌሊት በሕይወቴ ውስጥ ደርሶብኝ የማያውቅ እጅግ የሚያስደንቅ ጉድ የሆነ አጋጣሚ ደርሶብኛል ብልህ ምናልባት አታምነኝ ይሆናል ። ነገሩን ባጭር ቃል ልንገርህ ከጥቂት ሰዓት በፊት የመስፍኑ ልጅ እኔ ዘንድ ለማደር ፍቅር አጥወልውሏት መጥታ ነበር ። ይህችም ቤት በጠቅላላው ሁኔታዋ እንዳየኋት በዚህች ምድር ላይ ከተፈ ጠሩት ቤቶች ሁሉ በቁንጅናዋና በደም ግባትዋ ፣ በትሕትና ጠባይዋ ወደር የማይገኝላት ምልኢተ ኩሉ የሆነች ወይዘሮ

ልንገርህ

ናት ። ወዳጄ ሳንቾ ምን ብዬ ልንገርህ የሰውነቷ ፀጋና ልስላሴ የንግግሯ ለዛና ጣዕም ፣ የልቧ ኃይልና ሞገስ ፣ ሌሎችም እጅግ የበዙት የሥነ ፍጥረቷ ሽልማቶችና ጌጦች የዚህን ዓለም ተድ ላና ክብር የሚያስንቁና ፍጹም ታማኝነትን የሚያስከዱ ናቸው ። ስለዚህ ለእመቤቴ ለተበዘይቱ ዱልቼኔያ ያለኝን የጠበቀ ታማ ኝነቴን ሳላወላውል ጠብቄ ለመዝለቅ ስል የዚህችን ወይዘሮ ሁኔታ በዝምታ አደበስብሼ ማለፍ ይገባኛል ። ሆኖም በተለይ ልንግርህ የምችለው እድሌ አሳክቶ ሰጥቶኝ በእጄ የጨበጥሁ ትን ታላቅ ሀብትና ንዋይ አይቶ የተመቀኘኝ ጠላት ቀንቶብኝ ይሆን ? ወይም ደግሞ ነገሩ ይበልጥ እርግጠኛ በመሆኑ ላም ንበት እንደምችለው ፣ ቅድሞ እንደተጨዋወትነው ይህ ግንብ በአስማት የተወረረ በመሆኑ ይሆን አላወቅሁም እንጂ ከዚች ውብ ብላቴና ጋር ፍቅራዊና መዓዛዊ የሆነ የምስጢር ፣ ጭውውት ይዘን ፣ ልባችን በጥልቅ ሰሜት ተመስጠ በወዲያኛው ዓለም ውስጥ በትፍስሕት ሕይወት አልፍኝ በምንገኝበት በአፍላው ጊዜ እኔ ሳላየውና ከወዴት እንደመጣ ሳላውቀው ባንድ በሰ ማይ ጠቀስ ጃዊግ ክንድ ላይ የተጣበቀ እጅ ተሠንዝሮ ይህ ነው በማይባል አመታት መንጋጋዬን አራግፎ ስለጣለኝ ! ይኸውልህ ? እስካሁን ድረስ ባፌ ሙሉ ደም ተጉንጭቼ እገኛለሁ .... »

ከዚያም አከታትሎ ቁጥሩን በማላውቀው እርግጫና ጡጫ እንደቅሪላ ካለፋኝ በኋላ ከአልጋዬ ላይ ገልብጦ እመፊት ላይ ጥሎኝ ጠፋ ። በዚህ የተነሣ ያንን የምታውቀውን ትናንት በሮ ንዜናንቱ ከልፍልፍነት ምክንያት እነዚያ ጉረደግዎች ደብ ድበው ካቆሰሉን ይበልጥ ይህ የዛሬው ደግሞ የባሰ ሰውነቴን አሰያይቶታል ። ይህን ሁኔታ መሠረት በማድረግ ይህች የውበት አክሊል የሆነችው ወይዘሮ በምትሀት ኃይል ተሰውሮ በዚህ ግንብ የሚገኝ አንድ አረብ የሚጠብቃትና የሚከላከልላት መሆ ኑንና ለኔም ያልተፈቀደልኝ መሆኗን ለማረጋገጥ ችያለሁ ።

« በውነቱ ለርስም ብቻ ሳይሆን ለኔም ያልተፈቀደችልኝ መሆኗን ለማረጋገጥ ችያለሁ » አለ ሳንቾ ይህንንም የምለው እኔን የወገሩኝ ዓረቦች ብዛታቸው ያለጥርጥር ከአራት መቶ ቢበ ልጡ እንጂ ስለማያንሱ የዛሬውን ሌሊት እደጋ ከያንዳንዱ ሽመል

ጋር ሳመዛዝነው የያንጓሶቹ ሽመል ጣዕሙ እንደ ስኳር የሚቆጠር ነው ። መቸስ ምን ይደረጋል ! አጋጣሚ ያመጣብንን ሁኔታ ተቀብለን ከማመስገንና ከዚህ የባሰ አታምጣ ከማለት በስተቀር ሌላ መላ አይገኝለትም።የሆነው ሆኖ ጌታዬ ዶን ኪሾት እስቲ ፈቃድዎ ይሁንና አንድ ጥያቄ ልጠይቅዎ። ለመሆኑ ይህን እራስ በራስ ተንባብሮ የመጣብንን የሚያንገፈግፍ አጋጣሚ ምን ብለው ሊሰይሙት ይችላሉ ? እንዴ እንደሆነ ይህን የዛሬውን ማዕበል እንደአወጣጣችን ተወጥተ ተነዋል ። ኧረ ለመሆኑ የወደፊቱ አካሄዳችን እንዴት ሊሆን ይሆን ? ይህ አደጋ በርስዎ ላይ ቢደርስም እንኳ ከዚያች የውበት አክሊል ከሚሏት ሴት ጋር በፍቅር ስሜት ተቃቅፈው ሲደሰቱ በመቆየትዎ የጉዳትዎን ካሣ አግኝተዋል ለማለት ይቻል ይሆናል። ስለዚህ የርስዎን የተካሰ ጉዳት ወደ ጐን ትቼ የኔን የመከረኛውን አደጋ ልናገር ። እኔ ከእንግዲህ ወዲህ በሕይወቱ ሙሉ ይደርስብኛል ብዬ የማልጠብቀውና ምናልባት የሚደርስብኝም ቢሆን ቅሉ ከሁሉ የበለጠ አድርጌ ሳስታውሰው የምኖረውን የጡጫ ናዳ ከማግኘቴ በስተቀር ሌላ የተካስኩት ነገር የለም ። ኧረ ምን ባደረግሁና በየትኛው አበሳዬ ነው በኔ ላይ አደጋው እየበረከተ የሚደርሰው ? ወይኔ ያልታደልኩት ! ወይኔ መናጢው! ለዚህ ሁሉ መከራ ያበቃችን ፣ ወልዳ በዚህ ዓለም ላይ የጣለችኝ እናቴ ስለሆነች እርጉም ትሁን ። እኔ የተካንሁ ፈረሰኛ አይደለሁም ፤ ወይም ወደፊት የተካንሁ ፈረሰኛ ለመሆን አንዳች ፍላጐትና ምኞት የለኝም ። በኔ ላይ የሚደርሰው የመከራውና የአደጋው ድርሻ ዘወትር እየተጫጫነ የሚከመረው ምክንያቱ ምን ይሆን ? ከዚሁ ሁሉ ስቃይ ምቼ ብገላገል የሚሻለኝ አል ነበረምን ! ወይኔ ሳንቾ ! ወይኔ ያቺ ቀን ! ወይኔ ያቺ ሰዓት ! እያለ በመንሰቅሰቅ እንባውን ያጉርፈው ጀመር ።

« ሳንቾ ምን መሆንህ ነው ? ምንድን ነው የምትለው ! ለመሆኑ እንተም በጡጫ ተመትተሃል እንዴ ! ሲል ዶን ኪሾት ጠየቀው ።

« እስካሁን የምነግርዎት ምንድነው ከነትጋራሞች ዘርማ ንዘሮቹ ጋር የድራኛችን ድምጥማጡ ይጥፋና ማን ኖሯል ቅድም ሲነረት የዋለው እኔው እራሴ አልነበርኩምን ? የምነረትበትን

ምክንያት ሳላውቀው ጠላቶቼን ሳላያቸው ወዲያና ወዲህ እየ ተቀባበሉ ሲያላጉኝ ሲያሰቃዩኝ የዋሉት ምን ስላደረግሁ ነው ? ።

« ወዳጄ ሆይ » አለ ዶን ኪሾት « እስከዚህ ድረስ ተስፋ በመቁረጥ ክፉኛ አትበሳጭ አይዞህ ! ይህን መከራ በትዕግሥት ለማሸነፍ ካልቻልህ ወደ ደህናው ቀን ለመዝለቅ የማትችል ሃሳበ ደካማ ሆነህ መቅረትህ ነው ። ይህችን ዓለም ተጀምሮ እስቲ ጨረስ በደስታ ያሳለፋት ፍጡር ከቶ ፈልገህ ለማግኘት አትችልም ። መከራና ደስታ መንታዎች ስለሆኑ እየተፈራረቁ ሰውን ከመጐብኘት ምን ጊዜም አቋርጠው አያውቁም ። ስለዚህ እንደ አመጣጣቸው ለመቀበል ብርቱና ታጋሽ መሆን አለብህ ። እኔም አሁኑኑ ተነስቼ ያንን የነገርኩህን ዕፀ ፈውስ በቶሎ እቀምምና ከሱ አንዳንድ ጉንጨት እንደጠጣን ወዲያውኑ በቅጽበት ዓይን ድነን ፍጹም ጤናማዎች እንሆናለን ። እያለ በተቻለው መጠን ተስፋ እንዳይቆርጥና ተማርሮ እንዳይከዳው እየሰበከ ያጽናናው ጀመር ።

እነዚህ ሁለቱ ሰዎች ይህን የደረሰባቸውን ሁኔታ አንስተው በሚወያዩበት ጊዜ የጐበዝ አለቃው ኩራዛቸውን አብርተው ያንን ሞተ የተባለውን ሰው ለማየት ተመልሰው መጡ ። ቆጡን ወጥተው እበሩ ሲደርሱ ሳንቾ አይቷቸው ኖሮ የማታ ልብስ የለበሰና እራሱን በመሐረብ ያሰረ ፣ በእጁ ኩራዝ የያዘ መልኩ የሚያስፈራ ሰው ሲመጣ በሩቁ በተመለከተ ጊዜ እየተንቀጠቀጠ ጌታውን እንዲህ ሲል ጠየቀ ።

« ጌታዬ ሆይ ፣ ያ ቅድም የነገሩኝ በምትሐት የተሠወረው ዓረብ ምናልባት ይህ በእጁ የተረፈውን ጡጫ ሊያራግፍብን ወደኛ የሚመጣው አይመስልዎትምን ?

« ዓረብ ሊሆን አይችልም » ሲል መለሰ ዶን ኪሾት "ምክንያቱም በምትሐት የተሠወሩት ሰዎች ለማንም ቢሆን ተገልጠው አይታዩም" ።

« ላይን አይታዩ እንጂ ኰቴያቸው መሰማቱ አይቀርም፤ « እስ ሳንቾ» እንዲያውም ትከሻዬን ቀጥቅጧልና አንዳች አደጋ እንደሚመጣብን ሥጋቼአለሁ ።

« ታልክስ እኔም ትክሻዬን ቀርታል » አለ ዶን ኪሾት «ቢሆንም ይህ ኮቴውን የምንሰማው በምትሐት የተዳኘው ዓረብ ነው ብለን ለማረጋገጥ በቂ ማስረጃ ሊሆነን አይችልም » አለው።

ይህን በሚባባሉበት ጊዜ የጐበዝ አለቃው እየተጠጓቸው መጡ ። ዳሩ ግን ሰዎቹ በረጋ መንፈስ እርስ በእርሳቸው ሲነ ጋገሩ በመስማታቸው የሚሉት ቅጡ ጠፍቶአቸው ዲዳ ሆነው ቀሩ ። ባንድ በኩል ደግሞ ዶን ኪሾት እስካሁንም ድረስ ከወ ደቀበት ሥፍራ ለመንቀሳቀስ ሳይችል በቁስል ማሰሪያው ሻሽ እንደተተበተበ አቶን ሽቅብ እንጋጥሞ በዚያው በቅድሙ ሁኔታ ተንጋሎ ይገኝ ነበርና የጐበዝ አለቃው አጠገቡ ቀርበው እን ዲህ ሲሉ ጠየቁት ።

«ስማህ ወይ ወዳጄ ! አንተን ነው የምጠይቀው ? እረ ቅድም ምን ሆነህ ነበር? » ።

« እኔ አንተን ብሆን ኖሮ» ሲል መለሰ ዶን ኪሾት በተ ሻለ የትሕትና አነጋገር እጠይቅህ ነበር እንጂ እንዲህ እንዳንተ አልቆናጠርም ነበር ። አንተ ጅል እረኛዋ እረ ለመሆኑ እዚህ ሥፍራ ዙዋሪ ፈረሰኛችን እንዲህ ባለው አነጋገር ማመናጨቅ የተለመደ ነውን ? አለው ።

« የጐበዝ አለቃው ይህ ሁኔታው እጅግ የኰሰሰ ሰው በዚህ አኳኋን ሲያዋርዳቸው በሰሙት ጊዜ ትዕግሥታቸውን ስለጨ ረሱ በእጃቸው የያዙትን ጋዝ የተሞላች ኩራዝ አነሱና ጭን ቅላቱ ላይ ወርውረው ቢመቱት ለጥቂት ሳይፈነክቱት ቀሩ ። ከዚያም በኋላ በጨለማ ውስጥ ትተዋቸው በፍጥነት ወጥተው ሄዱ ።

ጌታዬ ሆይ ! ሲል ተጣራ ሳንቾ ይህ ስንጠራጠረው የነ በረው ነገር ያው በምትሐት የተሠወረው ዓረብ መሆኑ እነሆ ተረጋ ገጠ ። በኔ አስተያየት ይህ አዋቂ ዓረብ ገንዘብ አፍሶ መስጠ ቱን ለሌሎቹ ፥ ጡጫንና በጭንቅላት ላይ ኩራዝ ውርወራን ለኛ አዘጋጅቶ የመጣ ይመስለኛል" ። አለው ።

«እዚህ ላይ እውነት አልህ ለማለት እደፍራለሁ "፤ ሲል መለሰ ዶን ኪሾት ። ዳሩ ግን በምትሐት ጉዳይ ላይ ይህን ያህል መናደድና መደነቅ ከንቱ ነገር ነው ። ምክንያቱም ሁሉም የሰ መመን ትርኢቶች ስለሆኑ ለመበቀል ብንፈልግም እንኳ ጉም እንደመዝገንና ከጥላ ጋር እንደ መጋጠም ያህል የሚቆጠር መሆ ኑን ማወቅ አለብህ ። ስለዚህ ሳንቾ ሆይ ! የምትችል እንደሆነ ተነስተህ የግንቡ ገገር ዘንድ ሂድና ጥቂት ዘይት ፥ የወይን ጠጅና ጨው ፥ ሰናፍጭ ጭምር ለምነህ አምጣልኝ ። ይህን ካገኘሁ በኋላ ያንን ተአምራዊ አብነት እቀምማለሁ ። ከትናትናው ይልቅ ዛሬ ይህ ቀላዋጭ ሥራ ፈት የመታኝ በትር መንጋጋዬንና ጭን ቅላቴን አቁስሎ ብዙም ደም ስለአፈሰሰብኝ የአብነቱ አስፈ ላጊነት ይበልጥ የሚረዳኝ ባሁኑ ሰዓት ነው " አለው ።

ሳንቾም የታፋው ቁስልና የአጥንቱ ስብራት እየቆጠቆጠው ተንገዳግዶ ተነሳና በጨለማ እየተደናበረ ሆቴለኛው ወደተኛ በት ክፍል አመራ ። ዳሩ ግን የጐበዝ አለቃው ቅድም ኩራ ዙን ወርውረው የመቱት ሰውዬ ምን ዓይነት አደጋ ደርሶበት እንደሆነ ለማወቅ ሲሉ እበሩ ሥር ተለጥፈው ንግግራቸውን ያዳምጡ ስለነበረ ሳንቾ በሩን እንደወጣ ወዲያውኑ ፊት ለፊት ግጭት ስለተገናኙ ደነገጠና እንዲህ ሲል ጠየቃቸው ።

«ጌታዬ ሆይ ! ግን እንደሆኑ ሰይቼ ባለማወቄ ይቅርታ ያድርጉልኝና መልካም ፈቃድዎ ሆኖ ትንሽ ሰናፍጭና ፤ ዘይት ፤ ጨው ፤ የወይን ጠጅ ፤ ቆንጥረው እንዲሰጡኝ እለምንዎታለሁ ። ይህንንም የፈለግሁበት ምክንያት በምድር ላይ ከነበሩት ከም ርጥ ዙዋሪ ፈረሰኛ አንዱ የሆነው ጌታዬ ዶን ኪሾት በምት ሐት የተሠወረ ዓረብ እዚህ ሆቴል ውስጥ አግኙትና በብርቱ አቁስሎት እዚያ እቆጡ ላይ ወድቆ የሚገኝ ስለሆነ እሱን ለማከሚያ የሚሆን አብነት ለመቀመም ነው " አለው ።

የጐበዝ አለቃውም ይህን አነጋገር በሰሙ ጊዜ እስካሁን ድረስ በከንቱ ሲዳረቁ የቆዩት ከእበዱ ሰዎች ጋር መሆኑን አሰቡ ። መቸም ጊዜው ወደ መንጋቱ ተቃርቦ ነበርና የሆቴሉን በር ከፍተው ሆቴለኛውን ከጠሩለት በኋላ ይህ የቀሀ ሰው የሚ

ፈልገውን ነገሩለት ። ሦቴለኛውም የተጠየቀውን ነገር ለሳንቾ ስለሰጠ ተቀብሎ ለዶን ኪሾት ወሰደለት ።

ያም ከወደቀበት ተነስቶ በሁለት እጁ እራሱን ይዞ ተቀምጦ በኩራዙ የተመታውን ግንባር እየዳበሰ መቺውን ይራገም ነበር ። ይህም ኩራዝ ሁሰት ቦታ ላይ ቀንድ ሊያበቅል ያጐነቆለ ወይፈን አስመስሎ ግንባሩን ከማሳበጡ በስተቀር በጣም አላቆሰለውም ነበር ፤ እሱ ግን ደሙ የፈሰሰ የመሰለው በፊቱ ላይ የሚን ቆረቆረውን ላብ ዓይቶ ነው እንጂ ደም አልነበረም ። በመጨረሻም የተላከለትን መመጠኛ ተረክቦ በግምት እየለካ ቀይጦ ካማሰለው በኋላ በትክክለኛው መዋሃድ ላይ የደረሰ እስኪመስለው ድረስ እሻት ላይ ጥዶ አፈሳው ። ቀጥሎም የሚገሰብጥበት አንድ ብልቃጥ እንዲሰጠው ጠየቀ ። ዳሩ ግን በሦቴሉ ውስጥ ብልቃጥ በፍጹም የሌለ ስለሆነ ሦቴለኛው አንድ ባዶ የዘይት ጣሳ ፈልጐ በቾ ሮታው ሽለመውና በዚያ ውስጥ አጋባው ። ከዚህ በኋላ በተለ መደው አባባል እየደገመ ሥርዓቱ ቅመማውን ፈጸመ ።

በዚህም ሥርዓተ ቅመማ ላይ ሳንቾና ሦቴለኛው የጐበዝ አለ ቃውም ጭምር ታዛቢዎች ሆነው ይገኙ ነበር ። ነጋዴው ግን ማለዳ ተነስቶ በቅሎዎቹን ለመጐብኘት መጥቶ ስለነበር በመ ከከላቸው አልተገኘም ።

ዶን ኪሾትም ለዚህ ለተአምራዊ አብነት የሰጠውን የፈ ዋሽነት ችሎታ ለማረጋገጥ ሲል እራሱን ለመፈተን ሲል በጣም ቸኩሎ ስለነበረ ከጣሳው ተርፎ ባፈላበት ድስት ውስጥ ዘቅጦ የቀረውን ጨልጦ ጠጣው ። ይህም ሁለት መጸዚያ ያህል ቢመ ጣው ነው ። መጠጡ ከኮርሮው ወርዶ ገና ወደጨጓራው ከመ ድረሱ ወዲያውኑ ሽቅብ ገንፍሎ በጋይል ማስታወክ ስለጀመ ረው ትውከቱ ሳያቋርጥ ቀጥሎ ከጨጓራው ውስጥ ያለ የሱ ለው ሁሉ ተሟጥጦ እስኪያልቅ ድረስ እየለበቀ አስወጣው የትው ከቱ ኃይል እስጨንቆት ሰውነቱ በመናወጡ ምክንያት የላቡ መጎ ቅርቅር ስለተሰማው በብርድልብሱ ሸፍፍነው ብቻውን እንዲተ ውት ሰምቾን ለመናቸው ። እነዚያም ይህንኑ ፈቃዱን በመፈጸም ልብሱን ደራርበው በደንብ ከሸፋፈኑት በኋላ ከባድ እንቅልፍ

ወሰዶት ተኛ ። ከሶስት ሰዓት ይበልጥ ተኝቶ ከነቃ በኋላ እውነትም እሱ እንዳለው ሆዱን በጣም ቀለል ብሎት ቁስሉም በጣም ተሽሎት በጐነቱ ስለተሰማው ጨርሶ የዳነ መሆኑንና « የፌድሮብራዚዩ » እውነተኛውን ዕፀ ፈውስ አቀማመም ምስጢር አግኝቶ አብነቱ ያለ ስህተት የተዋጣለት መሆኑን ለማመን በቃ ። በዚህ መድኃኒት በመተማመን ከእንግዲህ ወዲያ ያላንዳች ፍርሃትና ሥጋት የቱን ያህል አደገኛም ቢሆን በማናቸውም ዓይነት አምባጓሮና ጥል ፣ ውጊያና ፣ ጦርነት ውስጥ ገብቶ ለመራኮት የሚችል መሆኑን አረጋገጠ ።

ጌታው ሳንቾ ፖንቻ ይህን ሁኔታ በጥንቃቄ ሲመለከት ነበርና ገዢው በጥቂት ሰዓት ውስጥ መፈወሱን በማየቱ የመድኃኒቱን ተአምራዊነት እጅግ አድርጐ እያደነቀ እሱም በድስቱ ውስጥ የተረፈውን ጭላጭ ለመጠጣት እንዲፈቅድለት ጌታውን ለመ ነው። ዶን ኪሾትም ወስዶ እንዲጋበዝ ስለፈቀደለት ሳንቾ ድስ ቱን በሁለት እጁ አንስቶ በፍጹም እምነትና በሙሉ ፈቃደኛነት እያንገራገጨ በመጠጣት ከጌታው ጥቂት አነስ የሚል መጠን ወደከርሱ ሰደደ ። ዳሩ ግን ያልታደለው ሳንቾ ጨንጓራው እንደ ዶን ኪሾት በጣም የተለሳለሰ አልነበረምና ከማስታወኩ በፊት ቋቋና ጉግጫ እየተፈታተነው ፣ ቀዝቃዛ ላብ እያላበው ነፍሱ በጭንቅና በጣር መካከል ተጣበበች ። በዚያን ሰዓት ያደረገው ትግልና መንቀራጠጥ ሰውነቱን ክፉኛ ስላናወጠው ወደመጨ ረሻው የፍጻሜ ሰዓት ላይ የደረሰ መሆኑን አመነ ። እስከዚህም ጭረስ መስቃየቱ ተስፋ በሚያስቆርጥ ማክተሚያ ላይ ያደ ርሰው ስለመሰለው የጠጣውን መድኃኒትና እንዲጠጣም የፈቀ ደለትን ነፍስ ገዳይ ይራገም ጀመር ። ዶን ኪሾትም ጋሻ ጃግሬው የሚገኝበትን የጭንቅ ሁኔታ በተመለከተ ጊዜ እንዲህ ሲል አስ ረዳው ።

« ሳንቾ ሆይ ! እኔ እንደማምነው ይህን ሁሉ ጭንቀት ያመ ጣብህ አንተ የተካንህ ፈረሰኛ ባለመሆንህ ይመስለኛል ። ምክ ንያቱም ይህ መድኃኒት ፈረሰኛ ያልሆኑትን ሰዎች የሚፀናወ ታቸው በመሆኑ ሳይሆን አይቀርም አለው ።

«በኔና በዘር ማንዘሮቼ ላይ መዓትና መቅሰፍት ይውረድ ብን » አለ ሳንቾ እንደባባ ''እርስዎ ይህንን እያወቁ ለምን ስጠ ጣው እያዩ ዝም አሉኝ ? ሆነ ብለው ያደረጉት ተንኮል ቢሆን አይደለምን ? እያለ ያቃስት ጀመር ።

መጠጡ ሥራውን ሲሰራ ቆይቶ በሆዱ ውስጥ ተተኩሰና ቡሽ እንደተከፈተ ሻምፓኝ ስለገነፈለ አሣረኛው ጋሻ ጃግሬ በላ ይኛውና በታችኛው በር እያስፈተለከ መኝታው ላይ ዘፈዘፈው ለብሶት የነበረው የኬሻ ብርድ ልብስ በአጉል አኳኋን ተበ ክሎ ስለበሸቀጠ ለምንም የማይረባ ሆኖ ተጣለ ። በኃይል የመ ጨነቁ የመጠበቡ ብዛት መላው ሰውነቱ በሳብ ተዘፍቆ መተ ንፈስ ስለአቃተው እሱ የጭንቁ ባለቤት ብቻ ሳይሆን ዙሪያ ውን ከብበው የሚያዩት ሰዎች ሁሉ የማከተሚያው ሰዓት የተቃረበ መስሏቸው ተደናገጡ ። ይህም ብርቱ ጣር ሁለት ሰዓት ያህል ቆይቶ ጥቂት ፋታ ከሰጠው በኋላ ፊቱ አመድ መስሎ ተዳክሞ መቆም አቅቶት ተዝለፈለፈ እንጂ እንደጌታው ሕመም ተቃልሎለት ወዲያውኑ በጐ አልሆነም ነበር ።

ዶን ኪሾት ግን ከላይ እንደተባለው በጣም ተሸሎት ሰው ነቱ ስለነቃ አጋጣሚውን ለመፈለግ ወደዙረቱ ለመነሳት ተቻ ኮለ ። ምክንያቱም ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ አሁን ይህን ተአ ምራዊ መጠጥ ቀምሞ በመያዙ በልቡ ሙሉ እምነት ስለአ ሳደረ ከእንግዲህ ወዲያ እዚህ ስፍራ ተቀምጠ በችላ ባይነት የሚ ያሳልፈው ጊዜ ሁሉ የሱን እርዳታ ከሚጠባበቁት የተበደሉ ሰዎችና ከዓለሙም ላይ ሠርቆ እንደሚወስድ ያህል ስለቆጠ ረው ነው ። ይህ የችኩልነት መንፈሱ ትዕግሥት አሳጥቶ ስለ ጐተጐተው ተነስቶ ቸጥቁን ታጠቀና እሱው እራሱ ሮንዚናን ቴንና አህያይቱን ቁና ፤ የሳንቾንም ልብስ አልብሶ ፤ አህያው ላይ እንዲወጣ አግዞት እሱም እራሱ አፈረሱ ላይ ከወጣ በኋላ በሆቴሉ ባንዱ ማዕዘን ጥግ የተደገፈ አንድ አንካሴ መሣይ አይቶ ስለጦር ሊጠቀምበት ወስዶ ለጉዞው ተዘጋጀ ። በሆቴሉ ውስጥ የነበሩትም ከሃያ የሚበልጡ ሰዎች ተሰብስበው በአኳኋኑ እየ ተገረሙ አተኩረው ይመለከቱት ነበር ። የሆቴሉኛውም ልጅ ሁኔታው በጣም አስገርሟት ትመለከተው ነበር ።

እሱም በበኩሉ ዓይኑን ከሰ ላይ ሳይነቅል ትክ ብሎ እያየ አልፎ አልፎ ከታች ከሆዱ አዘቅት ፈንድቶ የወጣ የሚመስል ትን ፋሽ ይተነፍስ ነበር ። ሌሎች ሰዎች ይህን አተነፋፈሱን ሰም ተው የታፋው ሕመም የሚያስምጠው መስሏቸው ነበር ። በተ ለይም ይህን አተነፋፈሱን የሕመም ምክንያት መሆኑን የሚ ያረጋግጡ ሌሊቱ ቁስሉን ሲታከም ጉዳቱን በቅርብ ሆነው ያዩ ለት ሰዎች ናቸው ።

ሁለቱም ከብቶቻቸው ላይ ከወጡ በኋላ ዶን ኪሾት እበሩ ላይ ሲደርስ በረጋና በአክብሮት ድምጽ ሆቴለኛውን ጠርቶ እን ዲህ አለው ።

« ክቡር የግንቡ መስፍን ሆይ ! በዚህ በታላቁ ግንብዎ ውስጥ የተቀበልኩት መስተንግዶ እጅግ ከፍ ያለና የበዛ ስለሆነ እስከ እድሜ ልኬ ድረስ ውለታዎን የማውቅና አጋጣሚ ሲፈቅድ ልኝ እጥፍ አድርጌ ለመመለስ በጣም የሚያስገድደኝ ሆኖ አግ ኝቸዋለሁ ። ምናልባት ከዚህ ቀደም ያስቀየመዎት ወይም የበ ደለዎት ትእቢተኛ ሰው ኖሮ እሱን በመበቀል ይህን ውለታ ዎን ለመመለስ የምችል ብሆን ዋናው ተግባሬ ለዚሁ ጉዳይ የተመ ደበና ማናቸውንም ትእቢተኛ በመቅጣት ፥ የተበደሉትን ሰዎ ችና ጥቃት በመበቀል ፥ ደካማዎችን በመርዳት ላይ የተመሠ ረተ መሆኑን እንዲያውቁልኝ እወዳለሁ ። ስለዚህ ትዝ የሚል ዎት ጠላት ወይም ባላጋራ እንዳለ ትውስታዎን በርብረው ጨም ቀው ፈልጉና በኔ ላይ የሚጥሉትን ይህን የመሰለ ቂም ያሳደ ሩበት ሰው እንዳለ ባንድ ጥቅሻ አሳይተውኝ ዘወር ከማለት በስተቀር ሌላ ሃሳብ የለብዎትም ። እኔም የልብዎን አድርሼ ውለታዎን ከፍዬ ሙሉ በሙሉ ሳላስደስትዎት እንደማልቀር በተቀበልኩት የፈረሰኛነት ክህነት ቃል ገብቼልዎታለሁ» አለው።

ሆቴለኛው ንግግሩን በርጋታ ካዳመጠው በኋላ መልሱን ደግሞ እንዲህ ሲል በበለጠ እርጋታ ፈዝ መለሰለት ።

« ጌታው ፈረሰኛ ሆይ ! ክቡርነትዎ ማናቸውንም ዓይነት ጥቃት እንዲበቀሉልኝ አልፈለግም ። ምክንያቱም ያጠቃኝን ወይም ሊያጠቃኝ የፈለገውን ሁሉ እኔው እራሴ እንዳሰኘኝና እን

ዳስፈለገኝ አድርጌ መበቀሉን አውቅበታለሁ ። ስለዚህ ለተደ ረገልዎት መስተንግዶ ዋጋ ፥ ለመኝታና ለምግብ ፥ ለሁለቱ ከብ ቶች የገፈራና የገብስ ሂሳብ ፥ ከዚህም ሌላ ዛሬ ሌሊት በዚህ ሆቴል ውስጥ ላደረጉት ጉዳት የተገመተውን ካሣ ከከፈሉኝ ይበቃኛል ፤ በሌላው ነገር አላደክምዎትም» አለው ።

« እንዴት አባክዎ ይህ የሆቴል ቤት ኖሯል እንዴ?» ሲል ጠየቀ ዶን ኪሾት ።

«እንዴታ ፤ ያውም ከምርጦቹና ከጽዱዎቹ ሆቴሎች አንዱ ነዋ » ሲል ሆቴለኛው አረጋገጠለት ።

«ግሩም ነው!» አለ ዶን ኪሾት ለካስ እስካሁን ድረስ በተ ሳሳተ እምነት ላይ ኖሬአለሁ ። እኔ ምን ጊዜም የመስፍን ግንብ ያውም የማይከፋው ዓይነት መሆኑን አምኜ ነበር ። ሆኖም ግን ብነቱ ቀርቶ ሆቴል መሆኑ ከተረጋገጠ ዘንድ የሂሳቡን ደብ ተር በቀይ እርሳስ ከመሠረዝ በስተቀር ሌላ የሚያስቸግር ነገር የለም ምክንያቱም እስካሁን ድረስ የሆቴል ሂሣብ የከፈለ ፈረሰኛ መኖሩን በፈረሰኝነት ታሪክ ውስጥ ስላላነበብሁ በበኩሌ ሂሣብ በመክፈል ዘዋሪ ፈረሰኞች የደነገጉትን ደንብ ለማፍረስ ስለ ማልችል ነው ። ከጥንት ጀምሮ ሲተላለፍ የመጣው ልማድ እን ደሚያስረዳው እነሱ በዋሉበትና ባደሩበት ሆቴል ወይም የመስፍን ግንብ ከሚደረግላቸው ነጻ የክብር አቀባበል በስተቀር ገንዘብ ተጠ ይቀው አያውቁም ። እርስዎ እንደሚሉት ለሆቴልዎ ኪራይ እን ዲከፈልዎ የጠየቁት ሂሣብ ምናልባት ሊከፈልዎ የሚገባ ይሆን ይሆ ናል? ። ዳሩ ግን ዘዋሪ ፈረሰኞች በዚህ ቀንበር በሆነ ሥራ ተጠ ምደው አጋጣሚያቸውን ለመፈለግ በቀንና በሌሊት ፥ በበጋ እና በክረምት ፥ በእግርና በፈረስ ፥ በብርድና በሙቀት ፥ ለረ ሃብና ለውሃ ጥም ተጋልጠው ለሰማዩ ቴግብና ለምድሩ ሐሩር መከተው ላደረጉት ብርቱ ተጋድሎና ድካም ዋጋቸውና ውለ ታቸው ይሆን ዘንድ ማናቸውም ዓይነት አስደሳች አቀባበል እንዲደረግላቸው ነፃ መብትና ልዩ ድርጉ ስለተሰጣቸው ይህን በመላው ዓለም የታወቀውን ማኅበራዊ ግዴታ ለማጓደል መፈ ለግ በውነቱ አዙሮ አለማየት ነው ።

« ይህ ጉዳይ ሲል መለሰ ሆቴለኛው «በፍጹም እኔን የሚ መለከትና በኔ ላይ የሚፀና አይደለም ስለዚህ እኔ ጥቅሜን ከመ ጠበቅ በስተቀር ሌላ ታሪክና ልማድ አላውቅምና የፈረሰኞችን ጉረትና ወግ መዘብዘቡን ትተው ለብዙ ሳንዳረስ ማግኘት የሚ ገባኝን ገንዘቤን ይክፈሉኝ » አለው ።

«እርስዎ በውነቱ ገትጋታ ባላገርና ገብጋባ ቸርቻሪ ነዎት» ሲል በቁጣ ከመለሰለት በኋላ አንካሴውን አጓመደና ሮንዚናን ቴን ኩርኩሮ አሰነስቶ ማንም ሊያግደው ሳይችል ፤ ጋሻጃግሬ ውም ተከትሎት እንደሆነ ዞሮ ሳይመለከት ፤ እየጋለበ ከሆቴሉ ግቢ ወጥቶ ራቅ ብሎ ሄደ ።

ሆቴለኛው ሲጨታጨቅ ውሎ ሂሣቡን ሳይቀበል ፈረሰኛው ማምለጡን በተመለከተ ጊዜ ሳንቾ ፓንቻን ይዞ ለማስከፈል ተን ደርድሮ ሄደ ። ሳንቾ ግን ጌታው ለመክፈል ያልፈቀደውን እሱም ለመክፈል የማይፈቅድ መሆኑን አስታወቀ ። ምክንያቱም እሱም የዙዋሪ ፈረሰኛ ጋሻጃግሬ እንደመሆኑ መጠን ለጌታው የታወቀ ለት መብትና ማመካኛ ደንብ ለሱም የሚረጋለት መሆኑን መሠ ረት በማድረግ ነው ። በዚህ አነጋገር ሆቴለኛው በንዴት ስለ ሠፈ የሳንቾን ጢም ጨምድዶ ያዘና ገንዘቡን ያልከፈለው እን ደሆነ በአጉል አካሄን አንገላቶት የሚያስተፋው መሆኑን በዛቻ አስጠነቀቀው ።

«አዬ እንደሆንኩ» አለ ሳንቾ ብታንገላታኝም ብትገድለኝም ያፈቀደህን አድርገኝ እንጂ አንዲት ቤሳ እንኳ አልከፍልህም ። ምክንያቱም ጌታዬ የተቀበሉት የፈረሰኞች ደንብ የሚያዝዘው በልቶ መሸሽን ስለሆነ ይህ ጥንታዊና በጣም ጥሩ የሆነው የዙ ዋሪ ፈረሰኞች ልማድ እኔ ዘንድ ሲደርስ ተሽሮ ተረስቶና ወድቆ መቅረት አይገባውም ። እንዲያውም ይህን የመሰለውን ትክክለኛ መብትና ድርጉ እፍርሽ በመገኘቴ ወደፊት የሚተኩት የዙዋሪ ፈረሰኞች ጋሻጃግሬዎች ሁሉ በኔ እንዲያማርሩብኝና አጥንቴን ሲወቅሱት እንዲኖሩ አልፈቅድም» አለው ።

ያልታደለው ሳንቾ የኩስቡ መዋርነት በሆቴሉ ውስጥ ከሠፈሩት ሰዎች መካከል ከሴንቪያ የመጡ አራት የቡትቶ

ጨርቅ ደላላዎችና ዕስት የጉርደባ ተዘዋዋሪ ሸቅጮች ሁለት የሲቪሊያ ነጋዴዎች እንዲገኙ አዘዘበት ። እነዚህም ሰዎች ሁሉ ፈዘኞችና ሰካራሞች ደብረ በጥብሶች ስለሆኑ ባንድ ዓይነት የተንኮል መንፈስ ተገፋፍተው ሳንቾን ከበቡትና ከአህያው ላይ ዘርጥጠው አወረዱት ።

ከዚያም በኋላ ከመካከላቸው አንደኛው ወደ ሆቴሉ ሮጠና ከሆቴሉኛው አልጋ ላይ አንዱን ብርድ ልብስ ገፎ አምጥቶ ሰጣቸው ፣ ሁሉም ሳንቾን ታግለው በብርድ ልብሱ ላይ ወረወሩት ። ቀጥለውም ቀና ብለው ወደላይ ቢመለከቱ የጣሪያው ቅርብነት ለተንኮል ሥራቸው ማከናወኛ የሚያመች ሆኖ ስላገኙት ሸክማቸውን ይዘው ከሰማይ በስተቀር ሌላ ጣሪያ በሌለበት መስክ ላይ አወጡት ። እንደገና ብርድልብሱን አን ጥፈው ሳንቾን እመካከሉ ላይ ከአጋደሙት በኋላ አራቱም ሰዎች የብርድልብሱን አራት ማዕዘን ጫፍ ጨብጠው ይዘው የፈረ ደበትን ሳንቾ በመንሽ እንደሚወረወር ምርት ሽቅብ ወዳየር እየጓኑ በነፍሱ ይጫወቱበት ጀመር ።

ያልታደለው ጓኜ የሚያሰማው አሪታ በጎይል የሚያሰተጋባ ስለነበረ ወዲያውኑ ወደ ዶን ኪሾት ጆሮ ለመድረስ ቻለ ። ያም ቆም ብሎ የአሪታውን አቅጣጫ ሲያዳምጥ በመጀመሪያው ጊዜ ስሜቱ አንዳች አዲስ አጋጣሚ የተገኘለት መስሎት ነበር ። እየቆየ ሲያጣራ ግን እሪታው የጋሻ ጃግሬው ድምጽ መሆኑን ለይቶ ሰላወቀ ፈረሱን አዞረና እየጋለበ ወደ ሆቴሉ ተመለሰ ። ዳሩ ግን እዚያ ሲደርስ በሩ ዝግ ሆኖ ስለአገኘው መባቢያ ለመ ፈለግ የውድሞውን ዙሪያ ገባንደአለሉ ይዘር ጀመር ። በመስኩ አጥር አጠገብ እንደደረሰ የአጥሩ ቁመት በጣም ረጂም አል ነበረምና ተንጠራርቶ ሲመለከት በሳንቾ ላይ የሚፈጸመውን አጉል ቀልድ ለማየት ቻለ ።

ዶን ኪሾት እዚያው ቆሞ በሚመለከትበትም ጊዜ ሳንቾ በአየር ላይ ሽቅብና ቁልቁል እየተመላለሰ በታላቅ ቅልጥፍና እና ፍጥነት ሲንር አይቶ ንዴት ባያቃጥለው ኖሮ በውነቱ የሚ ሠራው ተንኮል እሱንም ሳያስቀው የሚቀር አልነበረም ። ስለ

ዚህ በቀልዳቸው ተናድዶ ከኮርቻው ላይ ተነስቶ እርካቡ ላይ ቆመና በአጥሩ ላይ ተንጠልጥሎ ሰማለፍ ሞክሮ ነበር ። ዳሩ ግን ሰውነቱ ቆሳስሎ ታፋውም ተደቁሶ ገና ገመምተኛ በመ ሆኑ በሙከራው ለመዝለቅ ስላልቻለ እዚያው ኮርቻው ላይ እን ደተቀመጠ እነዚያን ሳንቾን የሚያራግቡትን ሰዎች ተደጋግሞ ሊነገር በማይቻል አኳኋን በዛቻና በስድብ ይጨፈጭፋቸው ጀመር ። እነሱም ይህን ፈርተው በሳንቾ ላይ መጫወታቸው ንና ማሰቃየታቸውን የሚተው ሰዎች አልነበሩም ። ከፊተኛው ይበልጥ እየጣደፉ ማጓናቸውን ቀጠሉ ። ሳንቾም ካሁን አሁን ይተውኛል ሲል እየጨከኑበት ስለሄዱ ያለ ክንፍ በሚበርበት ጊዜ ትንፋሹ እየተቆራረጠ እንዴ በዛቻ አንዴም በልመና እየ ወተወተ ይለፈልፍ ነበር ። ሆኖም እነሱ ደክሚቸው እስኪተ ውት ድረስ ይህ ውትወታውና ልመናው ምንም ሊረዳው አል ቻለም ነበር ። በዚህ አኳኋን ሲጫወቱበት ቆይተው ስለሰለቻ ቸው ከብርድ ልብሱ ላይ አውርደው አህያውን አቅርበው ከጫ ኑት በኋላ በማቁ ሸፍነው እንዲሄድ ነፃ ለቀቁት ።

ማርቶርኔስ ያልናትም አስቱሪያዊት በጣም ልበ ርሀሩህ ስለሆነች ሳንቾ በዚህ ሁኔታ መናበዙን ዓይታ አዘነችለትና አንድ ኩባያ ውሃ ልትሰጠው ፈልጋ ቀዝቃዛ እንዲሆንለት በማለት ከጉድጓዱ ውስጥ ቀድታ አመጣችለት ። ሳንቾም አመስግኖ ተቀ በለና ለመጠጣት ወደ አፉ ሲያስጠጋ ዶን ኪሾት በሩቅ ይመለ ከተው ኖሮ እንዲህ ሲል ጮኾ ሲናገር ሰማውና ገና ሳይቀምስ ወዲያውኑ አቋረጠ ።

« የኔ ልጅ ሳንቾ ፣ ልብ አድርግ እንዳትጠጣ ፣ የጠጣህ ፣ እንደሆነ መሞትህን እወቀው » አሰና የመድኃኒቱን ጣሳ እያሳየ « ይኸውልህ ተአምራዊውን መጠጥ ይገድለሀሉና ከዚህ ሁለት ጠብታ እንደጠጣህ በቅጽበት እንደምትድን እርግጠኛ ሁን » አለው ።

ሳንቾም ይህን ጥሪና ምክር ሲሰማ ፊቱን አዞረና ከዚያ ያኖው ይበልጥ እየጮኸ እንዲህ አለው ። « ለመሆኑ እኔ የተ ካንሁ ፈረሰኛ አለመሆኔን ክቡርነትዎ ዘንግተውት ነውን ይህን መርዝ ጠጣ የሚሉኝ ወይም ደግሞ ዛሬ ሌሊት በሆዴ

ውስጥ ተርፎ የቀረው ያንኑ ጥቂቱን አንጀቴን አስታውኬ እን ድጨርሰው ነው የሚፈልጉት ይበሉ ጌታዬ ይህን የሰይጣን መጠ ጥን እዚያው ለአራስዎና ለዲያብሎሶች ይጋብዙዋቸውና እኔን በሰላም እንድጠጣ ይተውኝ » አለው ።

ይሁን ተናግሮ መጨረሱና ውሀውን መጠጣት መጀመሩ ባንድ አፍታ የተፈጸመ ሥራ ነበር ። ዳሩ ግን በመጀመሪያው ቅምሻ ላይ ውሀ መሆኑን ስላወቀ መጠጣቱን ለመቀጠል አል ፈለገም ነበርና የወይን ጠጅ እንድትአመጣለት ማሪቶርኔዝን ለመናት ። እሷም ምንም እንኳ ባፈጣጠሯ እንደዚህ ባይተዋር ብትሆን ምን ጊዜም የዓላማዋን ቀጥተኛነት እርሮዋን የያዘች» ናት ስለሚሏት በቅን ልቦና ተልካ የገዛ ገንዘቧን ከፍላ የወይን ጠጅን ገዝታ አመጣችለት ።

እሱም ስለቸርነቷ አመስግኖ ተቀበለና ጠጥቶ ከጨረሰ በኋላ ምንም እንኳ በዚያው በተለመደው ሂሣቡ ይህም ማለት እራሱን በማስኮዳት ዋጋውን የከፈለው ቢሆንም በገንዘብ ረገድ ላንድም ነገር አንዲት ቤሳ ከኪሱ አውጥቶ ሳይከፍል አሸንፎ በመሄዱ በጣም እንደተደሰተ አህያውን በተረከዙ ሁለት ጊዜ ኮርኩሮ መንገድ ሲጀምር የሆቴሉን በር በረገዱለትና ወጣ ። ይሁን እንጂ ሆቴለኛው በዕዳው አስቦ ቦርሳውን በመያዝ አስ ቀርቶበት ነበር ። ሳንቾ ግን ሆቴሉን በለቀቀበት ጊዜ አንኮሰ ተበ ጥብጦ ነበርና ሆቴለኛው ቦርሳውን አስቀርቶት ሂሚቡን በገዛ እጁ መክፈልን እንዳወቀበት በጭራሽ ረስቶት ነበር ። ሳንቾ ወጥቶ መሄዱን ሆቴለኛው ከተመለከተ በኋላ ዶን ኪሾትን በመስ ጋት ለጥንቃቄ ሲል በሩን ደህና አድርጉ ለመቀርቀር ፈልጉ ነበር ። እነዚያ አራጋቢዎች ግን ክፍቱን እንዲቀመጥ ፈልገው እንዳይዘጋ ከለከሉት ። ምክንያቱም ሰዎች ጥጋበኞች ስለሆኑ ዶን ኪሾት ሌላው ቀርቶ ከውነተኞቹ « የክብ ጠረጴዛ » ዙዋሪ ፈረሰኞች አንዱ ቢሆንም እንኳ ከጤና ቅንጣት የማይቆጥሩ በመሆናቸው ነበር ።

ምዕራፍ 18

በጌትየው በዶን ኪሾትና በጋሻጃግሬው በሳንቾ ፓንዛ መካከል የተደረገውን አስደሳች ንግግር የሚጠቅስና እንዲሁም መተረክ የሚገባቸው የሌሎች ጥሩም የሆኑ አጋጣሚዎች ሁኔታ ይተረካል ።

ሳንቾ ከሆቴሉ ወጥቶ ከጌታው ጋር በተገናኘበት ሰዓት በጣም ተዳክሞ ነብዙ ስለነበረ ሌላው ቀርቶ አህያውንእንኳ ውሸ ለማ ለት ተሰኖት ነበር ። ዶን ኪሾትም በዚህ ሁኔታ ተዝለፍልፎ ሲመጣ አየውና እንዲህ አለው ።

« የኔ ደጉ ሳንቾ መጣህልኝ ? ይህ ግንብ ወይም ሆቴል በር ግጥ በምትሐት የተወረረ መሆኑን ከቅድሙ ይልቅ ገና አሁን አመንኩ ። ለመሆኑ እነዚያ ባንተ ላይ በጭካኔ ሲያላግጡብህ የነበሩት ሰዎች የሌላ ዓለም ፍጥረታት ወይም ጭራቆች ካል ሆኑ በስተቀር ሌላ ምን ዓይነት ሰዎች ለመሆን የሚችሉ ይመ ስልሃል ? ይህንንም አስተያየት ለማረጋገጥ የበቃሁት ከመስኩ አጥር ውጭ ሆኜ ያንን የሚያሳዝነውን የስቃይህን ልዩ ልዩ አደራረግ በምመለከትበት ጊዜ በደረሰብኝ መታገድ እንደ ተገነዘብኩት አጥሩን ለመዝለል ቀርቶ ከነአካቴውም ከሮንዜ ናንቴ ላይ እንኳ ለመነሳት ያልቻልኩበት ምክንያት በአስማት አፍዝዘውኝ መሆኑ ስለገባኝ ነው ። በዚህ አኳኋን ባልታገድና አጥሩን ዘልዬ ለማለፍ ወይም ለመንቀሳቀስ ችዬ ቢሆን ኖሮ እነዚያ ወስላቶች ለሠሩት ተንኰል ቅጣታቸውን በመስጠት ለዘለ ዓለም ሲያስታውሱት እንደሚኖሩ አድርጌ ጥቃትህን እበቀልህ እንደነበረ በፈረሰኛነት ክህነቴ ክብር እምልልሃለሁ ። ይህንንም ለማድረግ ቆርጬ የነበረው ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ ደጋግሜ እንደነገርሁህ አንድ የተካነ ፈረሰኛ የሚያጣድፍና ከባድ የሆነ

ችግር አጋጥሞት ሕይወቴንና ክብሩን ለመከላከል ካልሆነ በስተቀር ፈረሰኞች ካልሆኑት ሰዎች ጋር ውጊያ እንዲገጥም የፈረሰኛነት ደንብ የማይፈቅድለት በመሆኑ ደንቡን የማፈርስ መሆኔን እያወቅሁት ነው ።

« ጠላቶቼ ፈረሰኞች ቢሆኑም ባይሆኑም አለ ሳንቾ የምችል ብሆን ኖሮ እኔው እራሴ እበቀላቸው ነበር ። ዳሩ ግን ሳልችል በመቅረቴ እንደተጠቃሁ ቀረሁ ። የሆነው ሆኖ በኔ አስተያየት እነዚያ የተጫወቱብኝ ሰዎች እንደኛው በአጥንትና በሥጋ የተፈጠሩ ሰዎች ናቸው እንጂ እርስዎ እንደሚሉት ጭራቆች ወይም በምትሐት የተሠሩ ሰዎች አይደሉም ። ሁሉም ደንበኛ የክርስትና ስም ነበራቸው ። እኔንም በሚያራግቡበት ጊዜ እርስ በእርሳቸው በየስማቸው ሲጠራሩ ደህና አድርጌ ሰምቻቸዋለሁ ።

ለምሳሌ እንደኛው ጴጥሮስ ማርቲኔዝ ፥ ሁለተኛው ደግሞ ቲኖ ሪዬ ሔርናንዲዝ ይባላል ። ሆቴልኛውንም ዮሐንስ (ፖሎሜንቬ) ፖሎሜኬ « አባ ግራኝ» ብለው ሲጠሩት ሰምቻለሁ ። ስለዚህ የተከበሩት ጌታዬ የመስኩን አጥር ለመገለልም ሆነ ከፈረስዎ ላይ ለመንቀሳቀስ ያልቻሉት በሌላ አዳካሚ ምክንያት እንደሆነ ነው እንጂ በምትሐት ተይዘው እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ ።

በዚህን ሰሞን ከደረሱብን መከራዎች የተገኘውን ውጤት ላመዛዝነው ይህ እየዞርን የምንፈልገው አጋጣሚ ካነሰ ወደ ባስ ጉዳት ላይ እየጣለን ቆይቶ በመጨረሻ ላይ መሞታችንን ወይም በሕይወት መቆማችንን ለይተን ለማወቅ በማንችልበት አኳኋን እጅግ የበዛ አደጋ አከታትሎ አውርዶብናል ። ሁለተኛው ደግሞ በኔ በደንቆሮው አስተያየት እንደምገምተው ልናደርገው የሚገባንና የተሻለ በመሆኑም ሊመረጥ የሚገባው ፥ ጥንትም ሲባል እንደሰማሁት ከሄሮድስ ወደ ኢሳሞስ ፥ ከምጣድ ወደረመጥ ፤ ከመጥበሻ ወደ ፍም መጋባታችንን ትተን ልክ ባሁኑ የመከር ወቅት ላይ ወደ አገራችን ተመልሰን በሠላምና በፀጥታ የዱሮ ሥራችንን ብንቀጥልና ጉዳያችንን ብናጠናቅቅ ነው ።

«አወይ የኔ ሳንቾ»! «አለ ዶን ኪሾት» ባሁኑ አነጋገርህ ስገምትህ ስለፈረሰኛነት ጉዳይ ሊገባህ የሚችለው ምስጢር በጣም ያነሰ መሆኑን እረዳዋለሁ ። ስለዚህ አይዞህ ! ዝም በል ! እስከዚህ ድረስ ሆደባሻ አትሁን ትእግሥትም ይኑርህ ፥ ይህን የፈረሰኛነት ተግባር ማከናወን በዓለም ላይ የቱን ያህል የሚያስከብር ሞያ መሆኑን በገዛ ዓይኖችህ የምታይበት ቀን በቶሎ እንደሚመጣ እመን ። ኧረ በል እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ ! በዚህ ዓለም ላይ ስትኖር የሰውን ልጅ ታላቅነት የሚያጐላና የክብሩን ደረጃ ከፍ የሚያደርግ በጦርነት ላይ ድል ከማድረግ ወይም በገዛ ጠላት ላይ ከመግነን የበለጠ ምን ዓይነት ደስታ ሊኖር የሚችል ይመስልሃል ? ምንስ ዓይነት ተወዳጅ ነገር ሊተካከለው ይችል ይመስልሃል ? ያለጥርጥር አንዳች ነገር አታገኝም ።

«እርግጥ ላይገኝ ይችል ይሆናል» ሲል መለሰ ሳንቾ «መቼም ለኔ ይህን የመሰለው ነገር እንደማይገባኝ እርስዎም አውቀውታልና በበኩሌ ለጌታዬ የምገልጠው አስተያየት እኛ ዙዋሪ ፈረሰኞች ከሆንበት ጊዜ አንስቶ ወይም በተሻለ አነጋገር ክቡር ነትዎ ዙዋሪ ፈረሰኛ ከሆኑበት ጊዜ አንስቶ እኔ እንደሆንኩ በናንተ የክብር መዝገብ ውስጥ ገብቼ ለመቆጠር አልችልምና ከዚያ ከቢስካሊያው በስተቀር ሌላ አንድም ጦርነት ድል አልተደረገም ። ይህም የቢስካሊያውም ቢሆን ክቡርነትዎ ድል ለማድረግ የቻሉት ግማሽ ጆሮዎንና ግማሽ የራስ ቁርዎን አስቆርጠው ነው ። ከዚያን ጊዜ ወዲህ የተገኘው ድል በማኩራት ፋንታ የሚያዋርድ በሽመል ላይ ፥ ሽመል በቡጢ ላይ ቡጢ፤ እየተደራረበ መሆኑን አይዘነጉትም ። በተለይም ደግሞ እኔ በተጨማሪ የብርድልብስ ጉኖሽ አግኝቼአለሁ ። ክቡርነትዎ እንደሚሉት ከድል አድራጊነት የሚገኘው ክብርና ደስታ ምን ያህል የኩራትና የደስታ ስሜት እንደሚያሳድርና የደስታውና የክብሩም ወሰን እምን እንደሚደርስ ለማወቅ ስል እንኳ ጠላቴን ለመበቀል እንዳልሞክር የዶረሰብን አደጋ ሁሉ የተፈጸመው በማይታዩትና በማይዳሰሱት (በጥቂቶ ዘተራቀቁ) ሰዎች አማካይነት ነው ።

«ይህ አሁን የተናገርከው ይልቅ» አለ ዶን ኪሾት» በውነቱ እኔንም በጣም የሚቆረቁረኝ ነገር ነው ። አንተንም እንደኔው እንደ

ቆረቆረሀ ይገባኛል ። ለወደፊቱ ግን የጥበቡን ማጥፊያ ዘዴ ለማ ግኘት እደክምበታለሁ ። ይኸውም ታጣቂውን ፈረሰኛ ከማና ቸውም ዓይነት የአስማት ኃይል ነፃ ሊያደርገው የሚችል በልዩ ጥበብና በረቀቀ ምስጢር ተከውኖ የተሰራ ሠይፍ ፈልጌ ለማ ግኘት እችል ይሆናል ። ይህም ሰይፍ አማዲሰን በዘመኑ « ባለ ሰይፈ ነበልባሉ ፈረሰኛ» እያሰኘኢያስጠራው የኖረና ጥንት በመላው ዓለም የነበሩ ዙዋሪ ፈረሰኞች ታጥቀውት የማያው ቁት ምርጥ ሰይፍ ነበር ። ምክንያቱም ከዚህ በላይ ከተነገረው አብነቱ ሌላ ስለቱ ከምላጭ ይበልጥ የሚቆርጥና እንደዚሁም የቴን ያህል የተባና የምትሐት ድግምት የተደገመበት መሳሪያ ቢሆን በፍጹም ሊመክተው ስለማይችል ነው ።

« እንግዲያውስ እኔ ምንም አልታደልኩም ማለት ነዋ»! አለ ሳንቾ ምክንያቱም ምናልባት ይህን የተመኙትን ዓይነት ሰይፍ ለማግኘት የቀናዎት እንደሆነ እንደዚያው እንደመፍትሔው አገልጋይነቱ ለተካኑት ፈረሰኞች ብቻ ስለሚሆንና ለጋሻ ጃግ ሬዎች ግን ያገኙት ሁሉ ገንዘባቸው ስለሆነ ይህን ሰይፍ ቢታጠቁትም ለመከራ አሳልፎ እንደሚሰጣቸው ስለማልጠራ ጠር ነው ።

« አይዘህ ሳንቾ አትፍራ ! ከእንግዲህ ወዲህ ሁኔታው እን ደሚጠበቅህ አመንና ልብህን አጽናናው ።

እንግዲህ በዚያው በሚጓዙበት መንገድ ላይ ከፊት ለፊታ ቸው በኩል ወደነሱ የሚመጣ የአቧራ ጉም ዶን ኪሾት አይቶ ንግ ግሩን እስከ አቋረጠበት ሰዓት ድረስ ሁለቱ ዙዋሪዎች እየሄዱ ሲነጋገሩ የነበሩት ይህን ከላይ የተጠቀሰውን ጉዳይ አንስተው ነበር ። ስለዚህ ዶን ኪሾት አቧራውን አየና ወደ ሳንቾ መለስ ብሎ እንዲህ አለው ።

« ሳንቾ ይህን የዛሬውን ቀን እስካሁን ድረስ ዕድሌ ደብቆ ያስቀመጠልኝ በጐ ነገር ምን ዓይነት እንደሆነ ተገልጠ የሚ ታይበት ቀን ነው ። ይህ የዛሬው ቀን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የክንዴ ኃይለኛነት የሚገመትበት ቀን ነው ። እንደዚሁም በጀግ ኖች የጎድል መጽሐፍ ላይ ተጽፎ ለመጪው ዘመናትና

ትውልድ የሚተላለፍ ተግባር የምፈጽምበት ይህ የዛሬው ቀን እንደሚሆን አምናለሁ ። በስተፊታችን የሚቦነውን አቧራ ታየ ዋለህ? ፤ በል እንግዲህ አደምጠኝ ፤ ይህ አቧራ ቁጥራቸውና ዓይ ነታቸው ብዙ በሆኑ ሰዎች የተሠራ ታላቅ የጦር ሠራዊት በሰ ልፍ ሲጓዝ ያነሳው ነው ።

«እንግዲያውማ ሠራዊቱ በሁለት የተከፈለ መሆን አለበታ!?» «አለ ሳንቾ» በስተኋላችንም ይህንኑ የመሰለ ሌላ አቧራ ይታያል ።

ዶን ኪሾት ወደኋላው ዞሮ ቢመለከት እውነትም አቧራ ስለሚታይ ይበልጥ ተደስቶ በዚህ በሰፊው ሜዳ ላይ ተጋጥመው ለመራኮት የሚመጡ የሁለት ወገን ሠራዊታት መሆናቸውን አሰበ። ምክንያቱም በየጊዜውና በየሰዓቱ በራሱ ውስጥ ሞልተው የሚ ታዩት ትርኢቶች ሁሉ በፈረሰኛነት መጽሐፍ ላይ ተጽፈው የሚተረኩት የጦርነትና የአስማት ድርጊቶች ፤ የተዘበራረቁ አጋ ጣሚዎች ፤ የፍቅር ሁኔታዎችና ዛቻዎች ስለሆኑ ፤ የሚናገረውና የሚያስበው የሚያደርገው ማናቸውም ነገር ሁሉ ይህን ከመ ሰለው አርእስት የሚቀዳ ነበር ። ዳሩ ግን ይህ ከፊቱም ከኋላ ውም ሲነሳ ያነው አቧራ በሁለት የተከፈሉ የበግ መንጋዎች በዚያው መንገድ ለመተላለፍ እየተነዱ ሲመጡ ያነሱት ነበር ። ይሁን እንጂ የአቧራው አነሳስ በሩቁ ሆኖ ለሚመለከት ሰው በው ስጡ ያለው ምን እንደሆነ ለመለየት የሚያስቸግር ስለሆነ ዶን ኪሾት መጪዎቹ የጦር ሠራዊታት መሆናቸውን አጥብቆ ካረ ጋገጠ በኋላ ሳንቾም ይህንኑ እምኖ መቀበል ግዴታ ስለሆነ በት እንዲህ ሲል ጥያቄውን አቀረበ ።

« ጌታዬ ሆይ ! ነገሩስ ይሁን በጅቷል ! እኛ ደግሞ በዚህ ውጊያ ውስጥ ምን ማድረግ ይገባናል »

« ምን ማድረግ ይገባናል ትላለህ ሳንቾ» ? ሲል ጠየቀ ዶን ኪሾት እንደተለመደው ደካማዎችንና እርዳታ ፈላጊዎችን ማገዝ በነሱ ጉን መሰለፍ ነዋ ። ለካንስ እስከዚህ ድረስ ቂል ኖረሃል። ይልቅስ የምንግርህን አድምጠኝ አሁን በስተፊታችን ያለው ሠራዊት የዘመተውና የሚመራው የታላቁ የትራፖባና ደሴት ጌታ ኃያሉ ንጉሠ ነገሥት አሊፋን ፋሮኔ ነው ። ሁለተኛው በስ

ተጀርባችን የሚመጣው ደግሞ የዚህ ንጉሠ ነገሥት ጠላት የሆነ የጋራማቴዎች ንጉሥ ፔንታፖሌና ነው ። የፈረስ ስሙም «ባለ ጉርድ እጅጌ» ይባላል ። ምክንያቱም ዘወትር ወደ ጦርነት መሐል ሲገባ ቀኝ ክንዱን አራቁቶ ነው ።

እነዚህ ሁለቱ ንጉሦች እስከዚህ ድረስ የተጣሉበት ምክንያት በምን የተነሳ ነው ሲል ሳንቾ ጠየቀ ።

«የተጣሉበት ምክንያት ሲል ዶን ኪሾት ማስረዳት ጀመረ።» ይህ አሊፋንፋሮኔ የሚባለው ንጉሥ አከራካሪ ሁኔታ ያለው ሆኖ ሳለ የፒንታፖሊናን ልጅ አፈቀረ ። ይህችም ብላቴና እጅግ የተዋበች ትሁት ነበረች ። ዳሩ ግን ብላቴናይቱ የክርስቲያን ልጅ በመ ሆኗ ምክንያት ይህ አረመኔው ንጉሥ የሐሳዊ መሲሁን የመሐ መድን ሕግ ትቶ በሰ ሃይማኖት ካልተጠመቀ በስተቀር አባቷ ሊድርለት ስላልፈቀደ በዚሁ ተቀያይመው ዘወትር ደም እንደ ተፋሰሱ ይኖራሉ አለው ።

« የሸንጐቤቴ ያለህ» ሲል ተደነቀ ሳንቾ የጥላቻው መነሻ ይህ የሃይማኖት ጉዳይ ከሆነማ ፔንታፖሊና በሃይማኖቱ ፀንቶ እስከ መጨረሻው መጋደል አለበት ። የሚዋጋበትም ምክንያት ትክክለኛና እውነተኛ ስለሆነ እኔም ባለኝ ኣቅሜ ልረዳው ፈቃ ደኛ ነኝ አለ ።

ሳንቾ ሆይ! ይህን ካደረግህማ የሚገባህን ተግባር ፈጸ ምህ ማለት ነው ። ምክንያቱም ይህን በመሰለው የክተት ጦር ነት ውስጥ ገብተህ ለመዋጋት የፈረሰኛነት ክህነት እንዲኖርህ አትጠየቅም ።

« ይህ የአሁኑ ሃሳብ በጣም ይስማማኛል አለ ሳንቾ። ሆኖም በውጊያው ላይ የሚገኘው ሠራዊት ለመግደልና ለመማረክ መሽ ቀዳደሙን ትቶ ክህነት ያለውንና የሌለውን የሚመረምር ዳኛ ስለ ሌለ እርስዎም ባይነግሩኝ የሚከለክለኝ ሰው አለመኖሩን አውቄዋ ለሁ ። ይልቁንስ አሁን የማማክርዎት ጉዳይ እስከዛሬ ድረስ እንደሚደረገው በጦርነት ውስጥ ለመግባት ፈረሰኛ ወይም በቅ ሎኛ ሆኖ ነው እንጂ ምንም ቢችግር አህየኛ ሆኖ መግጠም

የሚፈቀድ ስላልመሰለኝ አህያዬን ወዴት አስሬ ላቆያት? ፤ ጦር ነቱ ካለቀሳ በኋላ እንደገና ለማግኘት እርግጠኛ ነኝን ?

« ይህ ጥያቄ እውነት ነው አለ «ዶን ኪሾት» በበኩሉ ግን የተሻለ ነው ብዬ የምስጥህ ምክር አህያዬቱ ብትጠፋም ብት ገኝም እድሏ እንዳወጣ ያውጣት ብሎ ነፃ መልቀቅ ነው ። ምክ ንያቱም ጦርነቱን ድል በምናደርግበት ጊዜ ለማግረጥ እስኪ ስለችን ድረስ ብዙ የምርኮ ፈረሶች ስለሚኖሩን ያሰኘህን ያህል እየነዳህ ለመውሰድ ትችላለህ ። ሮንዚናንቴም ወደ ማርጀቱ ስለተቃረበ እሱንም በሌላ ፈረስ መለወጤ አይቀርም ። ሳሁን ግን በነዚሁ እየተጠጉ በሚመጡት በሁለቱ የጦር ሰራዊታት ውስጥ የሚገኙትን ዋና ጦር ቀማሽ ፈረሰኞች ለይቼ ላስጠናህ ስለምፈልግ የማሳይህን ልብ አድርገህ ተመልከት ። እንዲያውም ይበልጥ አጣርተህ ለማየትና ለመለየት እንዲመችህ በደንብ ለመ መልከት ወደሚቻልበት አዚያ ጉብታ ላይ እንውጣ አለውና ተያይዘው ወዳንድ ጉብታ ላይ ወጥተው ቆሙ ። እዚህም ላይ ሆነው የአቧራው ጉም ዓይናቸውን ጋርዶ ማየት ባይከ ለክላቸው ኖሮ ዶን ኪሾት የጦር ሠራዊት የሚላቸውን ሁለት የበግ መንጋዎች በግልጥ ለማየት ይችሉ ነበር ።

ዶን ኪሾትም የሌለውንና ያላየውን ነገር በቅዠት መንፈሱ እየፈጠረ የተዋጊዎችን ስምና መልክ ፣ የመሣሪያቸውን ዓይነትና ዋራት ፣ እየለየ በአንካሴው እየጠቀሰ በማሳየቱ ድምጹን ከፍ አድርጐ እንዲህ ይል ጀመር ።

«ያ በወርቅ የተኰላ መሣሪያ የለበሰውና እንዲሁም ባንዲት ብላቴና እግር ሥር ተኝቶ ዘውድ የጫነ አንበሳ የተሳለበት ጋሻ የያዘው ፈረሰኛ «የብሩ ድልድይ ጌታ» የተባለው ጀግናው ላውርካ ልክ ነው ። ሁለተኛው ደግሞ የወርቅ አበባ ቅርጽ ያለበት ጥሩራ የለበሰውና እንዲሁም መደቡ ሰማያዊ ሆኖ በላዩ ላይ ሶስት የብር ዘውዶች የተጌጠበት ጋሻ የያዘው የኪሮሲያ ታላቁ መስፍን ተፈ ሪው ሚኮሌምቦ ነው። ከርሱ በስተቀኝ በኩል ያለው ሰውነቱ ግዙፍ የሆነው የሶስቱ ዓረብ አገሮች ጌታ የተባለው ነፍሰቢሱ የቦሎቼው ብራንዳባርባራን ነው ። የለበሰውም ጥሩራ እባብ ሰንኮፍ ቅርጽ

ሆኖ ስለጋሻም የያዘው አንድ የበር መዝጊያ ሳንቃ ነው። ስለዚህም ሳንቃ ሰዎች እንደሚተርኩት ሶምሶን ጠላቶቹን ለመበቀል አብሮ በሞተበት ጊዜ ካፈረሰው ምኩራብ የአንደኛው በር መዝጊያ የነበረው ነው ይባላል ። አሁን ደግሞ ዓይኖችህን ወደ ሁለተኛው ክፍለ ሠራዊት አዙርና የጦር አዝማቹን ፊትአውራሪ ሠራዊት ተመልከት ። ያ በሠራዊቱ ታጅቦ ሲተም የሚታየው ያዲሲቷ ቢስካሊያ መስፍን የካርሶናው ቴሞኔሉ ነው ። የለበሰውም ጥሩራ የመደቡ ሩብ ሰሚያዊ ፣ ሩብ ነጭ ፣ ሩብ አረንጓዴ ፣ ሩብ ቢጫ ሆኖ በአራት ማዕዘን የተሠራ ነው ። የጋሻውም መደብ መልኩ ዳለቻ ሆኖ በስጉዱ ላይ አንድ የወርቅ ድመት የተሳለችበትና እንዲሁም ትርጉም ባለው አነጋገር ሚያው የሚል ፊደል የተጻፈበት ነው ። የዚህም ምሳሌ የእመቤቱ የሰሚ የመጀመሪያው ፊደል ነው ። ይሽውም የአልጋርቬው መስፍን የልዑል አልፌ ፓኳን ልጅ የወደር የለሽ ልዕልት ሚያውሊና ሙሉ ስሚ ነው ይባላል ። ሌላኛው በዚያች በስቅስቋ ባዝራ ላይ ጉብ ያለውና እንደበረዶ የነጣ መሣሪያ የያዘው ፣ አንዳች የጀብዱ ሥራ ምልክት የሌለበት ልሙጥ ጋሻ ያነገበው ፣ የፈረንሳይ ተወላጅ የሆነ አዲስገብ ፈረሰኛ ነው። ስሙም ኢጥሮስ ፖፒን የሚባለው የአትሪክ ጉልቶች ጌታ ነው ። ወዲህኛው ባለ መኰርኰሪያው ተረከዙ የዚያቺን የዝጉርጉራን እና የፈጣኒን ሜዳ አሀያ ወገብ የሚጉሸመውና እንዲሁም በመሣሪያው ላይ ሰማያዊ ጽዋዎች የተቀረጹበት ኃያሉ የኦርቢያ መስፍን የዱኔ ኤስፖርታፊላርዶ ነው። በጋሻው ላይ የሚገኘው የጀብዱ ምልክት የሴሪቲ ተክል ያለበት ሆኖ በካስቲሊያ ቋንቋ ከሥሩ « ራስትሪያ ሚ ሱዊርቴ » (ዕጣዬን ተከተል) የሚል ጽሑፍ ይነበባል ።

በዚህ አኳኋን በፊተኛውም ሆነ በኋለኛው የጦር ሠራዊት ውስጥ በቅዠት መንፈሱ የሚያያቸውን ብዙ ፈረሰኞች በዝርዝር እየጠራ የሁሉንም ማዕረጋቸውን ፣ የጦር መሣሪያቸውን ፣ ቀለማቸውን ፣ የጀብዱ ምልክታቸውን ፣ ቃለ ምሳሌያቸውን እያመለከተ ከመጠን ያለፈ እብደቱ ያቃዠውን ሁሉ ከለፈለፈ በኋላ እንደገና ደግሞ በመቀጠል የሚከተለውን መናገር ጀመረ ።

« ይህ በስተግንባራችን ያለው ፈረንሳዊ ጦር ከልዩ ልዩ አገር ሰዎች የተገነባ ነው ። በዚህም ጦር ሠራዊት ውስጥ

የስመ ጥሩውን ከሳንቶ ጣፋጭ ውሀ የሚጠጡት ሰዎች ይገኙበታል ። እነዚያ በማርሲሊያ ገጠር የሚኳትኑት ባላሮች ፣ እነዚያ የሃብታሙን ዓረብ ረቂቅና ደቃቅ ወርቅ የሚያንጓልሉት ሰዎች እነዚያ የስመ ጥሩዎቹን የቴርሞ ዶንቴን ወንዞች የጠሩትንና ንጹህ የሆኑትን ቀዝቃዛ ውሀዎች እንደልባቸው የሚያገኙትን ሰዎች እነዚያ በብዙና በልዩ ልዩ መንገድ የፖቶሎን ወርቅ የሚለቅሙት ሰዎች እነዚያ በቃላቸው የማይረጉትና የማይታመኑት ወላዋዮች ኑሚዲዎች ፣ እነዚያ በቀስታቸውና በወሰፈ ንጥራቸው የታወቁት ፋርሶች ፣ እነዚያ እየሸሹ የሚዋጉት ፖርቲዎችና ሚዴዎች ፣ እነዚያ ዘላን የበረሀ አረቦች ፣ እነዚያ ልባቸው ጥቁር ቆዳቸው ነጭ የሆኑቪታዎች ፤ እነዚያ በቃጭልና በዶቃ ያጌጡትና ከንፈራቸውን የተበሱት ኢትዮጵያዎች ፣ ሌሎችም መልካቸውን የማያቸውና የማውቃቸው ስማቸውን ግን ለጊዜው የማላስታውሳቸው ሁልቆ መሣፍርት የሌላቸው አገሮች ሁሉ ሕዝባቸው ተቀያይጦ ይገኝበታል ።

በዚህኛው በሌለኛው በስተፊታችን በሚመጣው ፊት/ወራሪ ጦር ውስጥ ደግሞ እነዚያ ከቤቱ የወይራ ደን ሥር የሚፈል ቁትን ብርጭቆ የሚመስሉ ፏፏቴዎች የሚጠጡት ፣ እነዚያ ዘወትር የሞላውንና ወርቅማ የሆነውን የታጉን ጅረት መልኩን የሚያደፈርሱት ፣ እነዚያ የመለኮታዊውን ጄኔል ጤና ሰጪ የጠበል ውሀ እንደልብ የሚያገኙት ፣ እነዚያ ለከብት ማሰማሪያ ምቹ በሆኑትና በበለፀጉት ሜዳዎች ላይ ሲራወጡ የሚውሉት አረኞች ፣ እነዚያ በጃሪስ የርቀ ሠላም ሜዳ ላይ ሲጫወቱና ሲቧርቁ የሚውሉት ሥራ ፈቶች ፣ እነዚያ የወርቅ ጉን ጉን አክሊል የሚያደርጉት ሃብታሞች ማንቼናዎች እነዚያ የብረት ልብስ የሚለብሱ ከጥንታውያን ጌታዎች ደም የፈለሱ ዝርያዎች ፣ እነዚያ በውሃው ጥራት ስመጥሩ በሆነው በፔስዌርኃ መልካ ገላቸውን የሚታጠቡት ሰዎች ፣ እነዚያ በአውራረዱ በጥልቅነት በታወቀው በጥምዝምዙ ጓዲያና ወንዝ ዳር ሰዳር ሠፈና ጨፈጨያማ በሆነው መስክ ላይ መንጋዎቻቸውን አሠማር ተው የሚያግዱት እረኞች ፣ እነዚያ ከፔሬኔይ ደንና ከኩሬው እፔኔና በረዶዋም ተረተሮች ላይ እየነፈሱ በሚመጡት ብርዳም አየሮች የሚንቀጠቀጡት ሰዎች ፣ በሰብሳቢ ቃል ፤ እነዚያ አውሮፓ

በወሰኗ ከብባና አቅፋ በያዘቻቸው አገሮች የሚወለዱት ሁሉ ይገ ኙበታል ።

« ኢየሱስ ማረኝ ስንቶቹን አውራጃዎች ጠራቸው ፤ ስንቶ ቹን አገሮች አነሳቸው ፤ ለያንዳንዳቸው የሚገባቸውን ስያሜ በሚ ያስደንቅ ፍጡንነት እየሰጠ ዘረዘራቸው ፤ በውነቱ በጣም የሚገርም እብደት ነው ። መቸም አፍታ ዕድሜ ባላቸው በልበ ወለድ ድር ሰቶቹ ስም ውስጥ እንደ ጢፍ ተነከሮአልና የሚናገረው ሁሉ ያንኑ የድርሰቱን ንባብ እየከላለሰ ነበር ። ሳንቾም አንዳች ቃል ለመናገር ፋታ ሳያገኝ ጌታው የሚቃዣውን ሁሉ አፉን ከፍቶ ያዳምጥ ነበር ።

«አንዳንዴም እውነት እየመሰለው ጌታው የሰየማቸውን ፈረሰኞችና ጀዊሣዎች ለማየት ግራና ቀኝ ይገላመጥ ነበር» ።

ዳሩ ግን አንዳች ነገር ለማየት ስለአልቻለ መጨረሻው እንዲህ ሲል ጌታውን ጠየቀው ።

«ጌታዬ ሆይ ! አሁን ክቡርነትዎ ከጠሯቸው ውስጥ አንድም፤ ሰው አንድም ጀዊሣ አንድም ፈረሰኛ በመሀል መታየቱ ቀርቶ ጥላቸው እንኳ የታየ እንደሆነ ዲያብሎስ ነፍሴን ነጥቆ ይውሰ ዳት ። እንደዛሬው ሴሊት ጭራቆች የአስማት ጉዳይ ይሆንን ?

«እኔ እንደሆንኩ እንኳን ይህንን ያህል ሠራዊትና አንድ ሰው እናኳን አልታየኝም» ።

« ምን ማለትህ ነው አለው ዶን ኪሾት » አይንህ ቢታ ወር ጆሮህ አልተዶፈነም ፥ የቀረው ቢቀር የፈረሶቹ ማሽካካት ፥ የእምቢልታው መነፋት ፥ የከበሮዎች መጐሰም ሲያስተጋባ አይ ሰማህምን ?

« እኔ ግን አለ ሳንቾ የብዙ ጠቦቶችና የብዙ ሙክቶች ጩኸት በስተቀር ሌላ ድምጽ አይሰማኝም ።

ይህ ንግግር በሚደረግበት ጊዜ ከፊትም ከኋላም የሚመ ጡት የበግ መንጋዎች ተቃርበው ነበርና እውነትም ሳንቾ እን ደሚለው ጩኸታቸው ጐልቶ ይሰማ ነበር ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል መለሰለት «ሳንቾ ሆይ ! ፊት ለፊት ታላቅ ፍርሃት ዓይንህን እያንበገበገ ጆሮህንም እየኮ ረኮረ እንዳታይና እንዳትሰማ ሊያደርግህ እንደሚችል አውቃ ለሁ ። የፍርሃትም ዋናው ጠባዩ መንፈስን ማወክና ማናቸውም ነገር በእውነተኛው መልኩ እንዳይታይ አድርጐ ማደናገር ነው ። መሪነት ሲባል (በውርስ ጊዜ ልባሙ ፈሪውን ልባም ያደር ገዋል ። በፈሪ ላይ ፍርሃትን ፥ በጐበገ ላይ ድፍረትን ያበዛል ። ፈርተህ እንደሆነ ወዳንዱ ጥግ ተሸሸጥና እኔን ለብቻዬ ተወኝ። እኔ እንደሆንኩ ወገኑ ሆኜ የምዋጋለት ክፍል ድል አድራጊ ነት እንዲያገኝ ለመርዳት ብቻዬን እበቃለሁ አለው ።

ይህን ከተናገረ በኋላ ሮንዚናንቴን ኮርኩሮ ይውጣ አን ካሴውን ዘቅዝቆ ከጉበታው ላይ እንደመብረቅ ተፈንቅሎ ወርዶ ሽምጡን ለቀቀ ። ሳንቾም እዚያው ላይ እንደቆመ እንዲህ እያለ ይጮህ ጀመር ።

« ጌታዬ ዶን ኪሾት ወደኋላዎ ይመለሱ ፥ ስለእውነት ብለው ይመለሱ ፥ እንዳይታለሉ ፥ የበግ መክቶች ናቸው ብዬዎታለሁ ፤ ወይኔ መከረኛው ምነው የተወለድኩ ዕለት ሞቼ በቀረሁት፤ ለመ ሆኑ ምን ዓይነት እብድ ኖረዋል የምከተለው ኋላ አይሆንም መሳቂያ እንዳይሆኑ ይመለሱ ፥ ጀዊሣም ፈረሰኛም ድመትም ጥሩራም የለም ። እርስዎ እንዳሉት ሩብም ሙሉም ጋሻ የለም ፤ ሰማያዊ ፅዋም ሰይጣንም የለም ፥ እባክዎ ይቅርብዎት ይመለሱ። ምን ሊያደርጉ ይሆን? ወይኔ አሳረኛው ፥ ወይኔ እድለቢሱ ፥ ወይኔ እርጉሙ ፥ እርስዎን የምከተለው ፥ እያለ ጢሙን እየነጨና እየ ተማፀነ ይማረር ነበር ።

ዶን ኪሾት ግን አንድ ጊዜም እንኳ ፊቱን አልመለሰም ። እንዲያውም በጉላ ድምጽ እየፎከረ እንዲህ እያለ ይሄድ ነበር ።

« ተው አርጋ በለው ፥ በርታ በለው ፥ እናንተ በጐበዙ ንጉሠ ነገሥት በባለ ጉርድ እጅጌው ፔንቴፖሊኖ ሰንደቅ ዓላማ ሥር የምትመሩትና የምትዋጉት ፈረሰኞች ሆይ ! ሁላችሁም ተከተሉኝ ፥ በንጣፋችሁ ጠላት በትራፖባኖው ደሴት መስፍን በአሊፋንፋሮኔ ላይ የምፈጽመውን በቀል ታያላችሁ ።

ይህን ከተናገረ በኋላ በበጐቹ ሠራዊት መካከል ገባና በእውነተኛ ደመኛ ጠላቶቹን የሚዋጋ ይመስል በብዙ ድፍረትና በብዙ ግምረር እነዚያን የዋሃን እንስሳት በጦር ይሸጥባቸው ጀመር ። መንጋዎችንም የሚነዱት እረኞችና ባለቤቶች ይህን ያልታሰበ አደጋ በማየታቸው ተደናግጠው እየጮኹ እንዲተው ያወግዙት ነበር ። ዳሩ ግን ጩኸታቸው ለምንም እንዳልረባና መልስም እን ዳልሰጣቸው ከተረዱ በኋላ ወንጭፋቸውን ከየወገባቸው ላይ ፈቱና ቡጢ በሚያክል ኰረትና ጓል እያነሱ በመወርወር በጀሮ ግንዱ ሥር ያስፋጩበት ጀመር ። ዶን ኪሾትም ለመጀመሪያ ጊዜ የተ ወነጨፈውን ድንጋይ ከጉዳይ አልቆጠረውም ነበር ። እንዲያ ውም መንጋዎችን እያተራመሰ በመካከላቸው ወዲያና ወዲህ እየጋለበ እንዲህ ማለቱን ቀጠለ ።

ወዬት ነህ ትእቢተኛው አጄኡንፍሮኔ ብቅ በል እንግዲህ ፤ ጀግናውን ንጉሥ የጋራማንቴውን ፔንታፖሊኖ ያላቅምህ እየ ተነኰስህ በማስቸገር የሚገባህን ቅጣት ለመስጠት ካንተ ጋር አንድ ላንድ ገጥሜ ነፍስህን ከሥጋህ ለመለየት ቆርጬ የመ ጣሁት አንድ ጠልጣላ ፈረሰኛ ስለሆንኩ ወንድነትህ እንዲታይ ፈንጠር ብለህ ከመካከል ውጣ ።

እዚህ ነጥብ ላይ ሲደርስ እነሆ አንድ የድንጋይ አለሎ ተወርውሮ ጐኑን ቢመታው ሁለቱን የጐድን አጥንት ጠረመ ሰበት ። በዚህም ምት ስሜት መሞቱን ፣ ወይም በብርቱ የቆ ሰለ መሆኑን ስለአመነ ያንን ቀምሞ የያዘውን ተዓምራዊ አብ ነት አስታወሰና ጣሳውን ከብብቱ ወደአፉ ወስዶ ይጠጣ ጀመር ። ዳሩ ግን ለመድኃኒት ይበቃል ብሎ የገመተውን ያህል ከጉሮ ሮው ከማውረዱ በፊት እነሆ ደግሞ ሌላ ሙልሙል ተወርውሮ ጣሳውን ሙሉ ለሙሉ መትቶ አነካክተበት ። እግረ መንገዱን ደግሞ ሶስት ወይም አራት ጥርሶቹን አርግፎለት ከእጁም ጣት ሁለቱን ሰብሮለት አለፈ ። የመጀመሪያውም ሆነ ሁለ ተኛው አመታት ኃይለኛ ስለነበር ያልታደለው ፈረሰኛ በብ ርቱ እንደተጐዳ ከኮርቻው ላይ ተዘንጥፎ መውደቅ ግዴታ ሆነ በት ። እረኞቹም ተጠግተው ሲያዩት የሞተ መስሏቸው ስለፈሩ በፍጥነትና በጥድፊያ መንጋዎቻቸውን ሰበሰቡና የሞቱትንም ከስ

ድስት የሚበልጡ በጐች በጫንቃቸው ላይ ተሸክመው ሌላ ነገር ለማወቅ ሳይሹ ከዚያ ስፍራ በሩጫ እየሸሹ ራቁ ።

ሳንቾም ይህ ሁሉ ረብሻ በሚሆንበት ጊዜ እዚያው እጥ ብታው ላይ እንደቆመ ከጌታው ጋር የተዋወቀበትን ቀንና ሰዓት እየረገመ ፣ በንዴት ጢሙን እየነጨ ፣ ዕድለቢስነቱን በማማ ረር ጌታው የሚሠራውን የዕብደት ሥራ ይመለከት ነበርና ጌታው ተመትቶ መውደቁን እረኞቹም ሸሽተው መራቃቸውን ከአየ በኋላ እየተበሳጨ ከጉብታው ላይ ወርዶ ወደሱ ሄደ ። ዶን ኪሾ ትም በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ቢገኝም ሕሊናውን አልሳተም ነበርና ሳንቾም አጠገቡ እንደደረሰ እንዲህ አለው ።

« ጌታው ዶን ኪሾት እነዚያ ሊገጥሟቸው የሄዱባቸው የበግ መንጋዎች እንጂ የጦር ሠራዊት አለመሆናቸውን ደጋ ግሜ እያስረዳሁ ወደ ኋላዎ ይመለሱ ብዬ አላስጠነቀቅሆት ምን?

« ማስጠንቀቁንስ አስጠንቅቀኸኝ ነበር አለ ዶን ኪሾት » ዳሩ ግን ምን ይደረግ ያ ጠላቱ አመፀኛው ፉቅራ የሠራ ዊታትን መልክ ለውጦ እንዲሠወሩ አደረጋቸው ። ሳንቾ ሆይ ! እነዚህ አስማተኞች የፈለጉትን ነገር በፈለጉት መልክ ለውጠው ላንተ መስሎ እንዲታይ ማድረግ የማይሳናቸው መሆናቸውን ማወቅ ይገባሃል ።

ይህ የሚከታተለኝ እርኩስ አስማተኛ በዚህ ጦርነት ላይ ላገ ኘው እኽል በነበረው የአሸናፊነት ክብር የሚመቀኝ በመሆኑ የጠላትን ጦር ሠራዊታት ወደ በግ መንጋነት ለወጣቸው ። ቃሌን ለማመን ቅር የሚልህ እንደሆነ እኔ የነገርኩህ እውነት መሆን አለመሆኑን በዓይንህ ዓይተህ ለመረዳት እንድትችል እንዲህ አድርግ ፣ አህያህ ላይ ውጣና ቀስ እያልክ በዱካቸው ተከተላ ቸው ። ከዚህ ጥቂት ራቅ እንዳሉ ወዲያውኑ የበግ መንጋነታ ቸው ቀርቶ ቅድም ዘርዝሬ እንደነገርኩህ ደንበኛ ሰዎች ሆነው ታገኛቸዋለህ ። ዳሩ ግን ባሁኑ ሰዓት ያንተን እርዳታ በጣም እፈልገዋለሁና በቶሎ አትሂድብኝ ። መቸም አንድ ጥርስ እንኳ ተርፎ የቀረኝ አልመሰለኝምና በልስቲ ተጠጋና ምን ያህል ጥር ሶች እንደጐደሉብኝ አይተህ ንገረኝ » አለው ።

ሳንቾም ትእዛዙን ተቀበለና በውል ለማየት እንዲመቸው ዓይኑን ወደ አፉ ውስጥ ከተተ፤ ለማለት በሚያስችል አኳኋን እንደእንጥል ቆራጭ ተጠግቶ ከንፈሩን እየፈለቀቀ ይመረምር ጀመር። ዳሩ ግን በዶን ኪሾት ሆድ ውስጥ ሲገለባበጥ የቆየው ያ ቅድም የጠጣው ተአምራዊ መድኃኒት ሲሰራ ውሎ ልክ በዚህን ሰዓት ስለባረቀ በውስጡ ያለው ቡልቅታ በኃይል ወጥቶ የታጋሹን ጋሻ ጃግሬ ፊት በሙሉ አጥለቅልቆ ቢያለብሰው የኋ ሊት ፈንግሎ ጣለው።

ሳንቾም በዚህ የዱብ እዳ አደጋ ደንግጦ ከተነሳ በኋላ እን ዲህ አለ፤ «የሰላም» ያለህ አውን ባሁን የምንፍርጀ ነው የደረሰብኝ? ይህ ሰው ድም ካስታወከው ያሰጥርጥር ለሞት በሚያስጋው አኳኋን ቆስሏል ማለት ነው።

ዳሩ ግን የተተፋውን ነገር ለማወቅ ፊቱን ጠራርጐ ቢያ የው በቀለሙም ፣ በሽታውም በጣሙም ፣ ቅድም ከጣሳው ውስጥ ሲጠጣው የነበረው መፍትሔ እንጂ ደም አለመሆኑን ተረዳው። በዚህም ጊዜ የመድኃኒቱ ሽታና ጣዕም ስለአቅለሸለሸው እሱም በበኩሉ ምንም ያህል ሳይቆይ በጌታው ላይ ቾለበስበት። በዚህ አኳኋን ሁለቱም እንዳልሆነ ሆነው ተሠራሩ። ሳንቾ ፈጥኖ ተነሳና ዶን ኪሾትን ለማከሚያና ለማጽጃ የሚሆን ጨርቅና ቅባት ለማምጣት ወደ አህያው ሮጠ። ዳሩ ግን መመከኪያቸው ሁሉ የነበረበትን ሻንጣ ሆቴሰኛው አስቀርቶት ኖሮ አለመገኘቱን ሲያስበው ጊዜ ባንድ አፍታ እብድ ሊሆን ምንም አል ቀረውም ነበር። እንደገና የተለመደውን የእርግማን መዓት አከታትሎ ካወረደ በኋላ ያቺን ተስፋ የተደረገችለትን የደሴት ግዝነትና እስካሁንም ድረስ ያገለገለበትን ደመወዝ ጭምር የሚያሰጣውም ቢሆን ጌታውን እዚያው እወደቀበት ቦታ ጐል ቶት ወደአገሩ ለመመለስ በልቡ አቀደ። ሳንቾ በዚህ ሁኔታ ፊቱን አኬማትሮ በሚበሳጭበት ጊዜ ዶን ኪሾት ከወደቀበት ተጣጥሮ ተነሳና ጥርሶቹ ጨርሰው እንዳይረግፉበት አፉን በግራ እጁ አፍኖ ይዞ ፣ በቀኝ እጁ ደግሞ የሮዜናንቴን ልጓም እየሳበ «መቸም ፊረሱ ታማኝና በደንብ ስልጥኖ ያደገ ስለሆነ ከአጠ ገቡ አልተንቀሳቀሰም ነበርና» ወደ ጋሻ ጃግሬው ሄደ።

ያኖውም በደረቱ አህያይቱን ተደግፎ ፣ ሁለቱንም መዳፎቹን እጉንጮቹ ላይ አድርጐ በሚያስጨንቅ ሃሳብ እንደተወጠረ ሰው ሆኖ አገኘው። እንደአካሄዱ ፈጥኖ በመመለስ ፈንታ በዚህ አኳ ኋን በጥልቅ ትካዜ ፊቱ ተጨማደዶ በማየቱ ግራጣባውና እን ዲህ ሲል ያጽናናው ጀመር።

«ስማኝ ሳንቾ አንድ ሰው ከሌላው ይብልጥ ካልሰራ የሌላውን ያህል ዋጋ ሊኖረው አይችልም። ይህ በኛ ላይ የዘ ነበው የስምኑ ማእበልና ውሽንፍር ወደፊት በቅርቡ የሚያበ ራና የጉዳያችንን መቃናት የሚያስተማምን ምልክት ነው። ምክ ንያቱም ከፉና በጐ ነገር ለዘለዓለም እንዲኖሩ ሆነው ስለተፈ ጠሩ እና እንዲሁም ክፉው ነገር ብዙ ጊዜ በኛ ላይ ስለቆየብን ከአንግዲህ ወዲያ የሚተካው በጐ ነገር ቅርባችን መሆኑን ለማ ረጋገጥ እንችላለን። ስለዚህ አንተን በማይነካውና በፍጹም ባል ደረሰብህ በተለይ በኔ ላይ ብቻ በደረሰው አደጋ እስከዚህ ድረስ መመረርና መበሳጨት አይገባህም» አለው።

«እንዴት ነው የሚሉት ፥ እንደምን እኔን አይነካኝም?» ሲል ጠየቀ ሳንቾ አረ ለመሆኑ ትናንትና በዚያ ሆቴል ውስጥ በብርድ ልብስ ተገንዘ ሽቅብ ሲጓንጉኝ ሳይሰማ ኖሯል ያባቴ የባህር ልጅ ሳንቾ አልነበረምን? ዛሬስ ደግሞ ሙሉ ጠቃሚ እቃ እንደ ያዘ የጠፋው የውዴላ ቦርሳ ምናልባት የሌላ ሰው ኖሮአልን? እንተን አይነካህም የሚባለው ከመንካትም አልፎ ልቡን ጭምር ቦጭቆ ወስዶታል» አለው።

«እንዴት በል ቦርሳውም ጠፍቶብሃል እንዴ» ሲል ዶን ኪሾት ጠየቀው።

«አምን እልም ብሎ ጠፍቶብኛል» ሲል አረጋገጠ ሳንቾ እንደተናደደ።

«እንግዲያውማ ለዛሬ ማታ እራታችንን የምንበላው ምንም የለን ማለት ነዋ» ሲል ጠየቀው ዶን ኪሾት።

በእርግጥ የለንም «ሲል መለሰ ሳንቾ ንግግሩን በመቀጠል» ባለፈው ጊዜ ክቡርነትዎ የነገሩኝን እንደማስታውሰው እነዚያ

እንደርስዎ ዕድል የከዳቸው ዙዋሪ ፈረሰኞች አሁን እኛ በም ንገኝበት ሁኔታና እንዲሁም በክፉ ቀን ዘመን ከጫካና ከሜዳ እየለቀሙ እርሃባቸውን ይከላከሉበታል ያሉኝን ዓይነት ፍሬዎችና ቅጠላ ቅጠሎች በዚህ መስክ ላይ አግኝተን ለቅመን ለመብላት ካልቻልን በስተቀር ሆዳችን እንደተጣበቀ ጦማችንን ተያፍተን ማደራችን ነው» አለው ።

« የሆነው ሆኖ » ሲል መለሰ ዶን ኪሾት ባሁኑ ሰዓት ያደ ረብኝ የምግብ ፍላጐት የሐመልማሎች ሲቅ ዲዩስኮሪዴ ተበ ይነታቸውን በዝርዝር ከጻፋቸው እና ዶክተር ላጐናም በስዕል አንስቶ ካሳያቸው የዓለም ቅጠላቅጠሎች ሁሉ ይልቅ ቁራሽ ዳቦና ጥቂት ጎንፎ ከሁለት የአሳ ጥብስ ጋር ባገኝ በደስታ እበላ ነበር ። ዳሩ ግን ለማይገኘው ነገር መጓጓት ከንቱ ስለሆነ መል ካሙ ሳንቾ አህያህ ላይ ውጣና ወደምሄድበት ተከተለኝ ። አይ ዘህ አታስብ ፣ የማናቸውንም ፍጥረት ውሎና አዳር የፀደነገ ውና ያደራጀው አምላክ የከፈተልንን ጉሮሮ ሳይዘጋው አያድ ርምና እሱው ይጨነቅበት ።

ተፈጥሮ በኪነ ጥበቡ እኛ እራሳችንን መርዳት ለምንችለው ለሰ ዎች ከሚያደርገው ቸርነት ይበልጥ ያየሩን በራሪዎችና ትንኞች ፣ የምድርን ትሳትሎች ፣ የባሕርን ተርመስሚሾች ሁሉ መግቦና አጥግቦ ስለሚያሳድራቸው ለነሱ ያሰበ አምላክ እኛን የሚረ ሳን አይምሰልህ ። እንኳንስ እኛን ለሰው አገልግሎት ስንል ዓለምን የምንዞረውን ከመርዳት ችላ ሊል ይቅርና በቸ፤ነቱ ሠፊነትና በርህራሄው ታሳቅነት ፀሐይን ለደገሎች ለክፉዎችም ያወ ጣላቸዋል ፣ ዝናምን ለምሕረትም ለጥፋትም ያዘንብላቸዋል ። በዓለም ላይ ከረድኤቱ የማይሳተፍ ፍጡር ከቶ አይገኝም» አለው።

« ክቡርነትዎ ጠቃሚ የሚሆንብትን ሰጦታዎን ቢያውቁት ኖሮ » አለሳንቾ ከዙዋሪ ፈረሰኛነት ይልቅ ለሰባኪነት በጣም የተገቡ ነበሩ ። በዚህ ዓይነት ልብን ጠልቆ በሚነካ አሰባበክዎ ብዙ አሕዛብ ለማሳመን እንደሚችሉ እርግጠኛ ነኝ ።

« ውድ ሳንቾ ሆይ ! ሲል መለሰ ዶን ኪሾት ዙዋሪ ፈረ ሰኞች ሲባሉ በጠቅላላው ሁሉን ነገር አዋቂዎች ናቸው ። ሁሉ

ንም ማወቅ ይገባቸዋል ። ምክንያቱም ባለፉት ክፍለ ዘመናት ከነበሩ ዙዋሪ ፈረሶች አብዛኛዎቹ በፈረንሳይ ዩኒቨርስቲ የተ መረቁ ሊቆች ይመስል በማናቸውም የጦር ሜዳ ሠፈር ላይ በሚ ነሳው ብርቱ ክርክርና በሚደረገው የጉባኤ ንግግር ሃሳባቸውን ለመስጠትና ነቀፌታ ለማድረግ ፣ ትችት ለማቅረብ የተሟላ ችሎ ታና ስሚነት የበለፀገ ጥልቅ አስተያየት ስላላቸው እና ይህን የመሳሰለውንም አፍአዊ ጦርነት ለማሸነፍ ዝግጁዎች ስለነ በሩ በዚህ የተነሳ «ጦር ብዕርን አይቀርጸውም ብዕርም ጦርን አይስለውም » ተብሎ ተወስኗል ።

እርስዎ እንዳሉት ይሆን ይሆናል «ሲል መለሰ ሳንቾ » የሆነው ሆኖ ላሁን ከዚህ ስፍራ እንነሳና ዛሬ ሌሊት ለማደር የምንችልበትን ቦታ በጊዜ እንፈልግ ። በእውነት ጀንተን ከተዘጋጀን በብርድልብስ የሚያራግቡ ሸረኞች ፣ በዙሪ የሚማቱ ጭራቆችና በምትሐት የሚያፈዝዙ ዓረቦች የማይገኙበት ሰላማዊ ቦታ ያጋጥመን ። ምናልባት ከእንግዲህ ወዲህ ይሆን የመሰለ ሰይጣናዊ ሥራ ያገኘን እንደሆነ ማናቸውንም ነገር ከንብዬ ጥዬ ወደ አገሬ መሄድ እትጭ ያለው ቁርጥ ሃሳብ ነው » አለው ።

«ልጄ ሆይ በትክክለኛ ሥራህላይ ተማመን አለ ዶን ኪሾት። ላሁን ተነሳና እንተ ወዳፈለግኸው አቅጣጫ ምራኝ ። ለዛሬ የማደሪያ ቦታ የመምረጡን ኃላፊነት ላንተ ለመልቀቅ ፈቅጀ አለሁ ። «አለውና» እስቲ ከመነሳትህ በፊት እጅህን ወደአፈ ስደ ድና ባንድ ጣትህ እየነካህ ከላይኛው መንጋጋዬ በስተግራ በኩል ስንት ጥርሶች እንደጐደሉ እይልኝ ። ምክንያቱም ሕመሙ በጣም የሚሰማኝ ልክ እዚሁ ቦታ ላይ ነው ።

ሳንቾም ጣቱን ወደ አፉ ከተተና መንጋጋውን ከዳሰሰው በኋላ እንዲህ ሲል ጠየቀው ።

« ቀድሞ ከዚህ ወገን ስንት ጥርሶች ነበሩዎት » ?

« አራት ነበሩኝ ሲል መለሰ ዶን ኪሾት « የውም የአእ ምሮ ጥርሴን ሳልቆጥር ነው ። የቀሩት ግን በሙሉ ከነጤናቸው እንዳሉ ናቸው » ።

« ደህና አድርገው ያስታውሱና ይቁጠሩት » ሲል መከረ ሳንቾ ።

« አምስት መሆናቸው ቢቀር አራት ናቸው እያልኩህ «ሲል መለሰ ዶን ኪሾት »

« ከተወለድኩ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ አንድም ጥርስ ተነ ቃንቆብኝ አላስወለቅሁም ፣ አንድም ጥርስ አውቆ አልተነቀ ለብኝም ፣ ሌላው ቀርቶ ብልዛትም ሽርፍታም ነክቶኝ አያው ቅም ጥርሶቼ ሁሉ ክክ እንደመሰሉ ተደርድረው ነበር ።

« በደንብ ቆጥረው ይንገሩኝ ያልኩበት ምክንያት ሲል ማስረዳት ጀመረ ሳንቾ በዚህ በታችኛው በኩል እኔ እንደማ የው ከሁለት ጥርስ ተግማሽ በስተቀር ሌላ የለምትም ። በላይ ኛው በኩል ደግሞ ግማሽም ሙሉም ስለሌለበት የሚታየው እንደመዳፍዎ የዳለጠ ድድ ብቻ ነው አለው ።

« ወይኔ ያልታደልኩት » አለ ዶን ኪሾት ይህን የሚያ ሳዝን መርዶ ከጋሻጃግሬው እንደበት በሰማ ጊዜ « ጥርሴን ከሚ ያወልቁብኝ ጐራዴ የምጨብጥበትን የቀኝ ክንዴን አይሁን እንጂ የግራውን ክንዴን ቆርጠው በወሰዱት ኖሮ ይሻ ለኝ ነበር ። ማኘኪያ ጥርስ የሌለው አፍ መጅ እንደሌ ለው ወፍጮ የሚቆጠር ነው ። ካንድ አልማዝ ይልቅ አንድ ጥርስ የበለጠ ዋጋ እንዳለው ሊገመት ይገባዋል ። መቸስ ምን ይደረጋል ፣ የዙዋሪ ፈረሰኝነትን ጠንካራ ሕግ የምንፈጽመው ሰዎች ሁሉ ይህን የመሰለውንም ጉዳት ለመቀበል ምንጊዜም ቢሆን የተገደድንና የተጋለጥን ነን ። ወዳጄ ሳንቾ ሆይ በል እን ግዲህ አህያህ ላይ ውጣና መንገዱን ምራኝ ። እኔም እንተ በፈ ለግኸው እርምጃ እከተልሃለሁ አለው ።

ሳንቾም ይህንኑ ትዕዛዝ በመፈጸም አህያው ላይ ተቀመ ጠና ከአውራው መንገድ ሳይወጣ ማደሪያ ቦታ ለማግኘት የሚ ቻል መስሎ በታየው አካሄዱ ጉዞውን ቀጠለ ፤ ይህም መንገድ በዚያን ሰዓት ብዙ መንገደኞች የተመላለሱበት መሆኑን የሚያ ስረዳ ትኩስ ዱካ የታየበት ነበር ። ሆኖም ለዶን ኪሾት የመን

ጋገዎቹ ሕመም ሩታም ሆነ የመቸኮል ፍላጐት ስላልሰጡት በዚህ ምክንያት ጌታ ከኋላ ጋሻ ጃግሬ ከፊት ሆነው በጣም ዝግ ባሰ እርምጃ እያዘገሙ በሚሄዱበት ጊዜ ሳንቾ ይህን የሚያበ ሳጭ እዶጋ ለማስረሻ ለጊዜ ማሳለፊያ ፤ ጌታውን ለማበረታቻ የሚሆን ልዩ ልዩ ወሬዎች እያመጣ ሲያጫውተው ፈለገ ። ከወ ሬዎቹም ውስጥ የመጀመሪያው ከዚህ በሚቀጥለው ምዕራፍ ላይ የሚተረከው ነው ።

ምዕራፍ 19

ዶን ኪሾት ከጋሻ ጃግሬው ጋር በጨለማ ሲጓዝ ካንድ ሬሳ ጋር ተጣናኝቶ ያከናወነው ግጥሚያና እንደዚሁም ስለ ሴሎች ልዩ ልዩ አስደናቂ ሁኔታዎች ሳንቾ ፓንቻ ለጌታው ያደረገው ቁምነገር የሞላበት ንግግር ይተረካል ።

ሳንቾ ፓንቻ እርምጃውን በመቀጠል እንዲህ ሲል ወግ አመጣ ። « የተከበሩት ጌታዬ ሆይ ! እኔ እንደሚመስለኝ በነ ዚህ ቀኖች ውስጥ የደረሱብን አደጋዎች ሁሉ ከክቡርነትዎ የፊ ረሰኛነትን ሕግ አፍርሰው ለሠሩት ኃጢአት የተጣሉ መቀጫ ዎች መሆን አለባቸው እላለሁ ። ምክንያቱም ያስታውሱት እን ደሆነ ባለፈው ጊዜ ሲናገሩ እንደሰማሆት ያንን ማሳንደሪና ወይም ማንትስ እንዳሉት እንጂ በውል አላስታውሰውም የዚ ያን የሳረቡን የራስ ቁር ማርከው እጅዎ ከማግባትዎ በፊት በተ ሠናዳ ገበታ ላይ ቀርበው ዳቦ ላይበሉ ፥ በተነጠፈ አልጋ ላይ ላይተኙ ፤ ከንግሥት ጋር ላይጨዋወቱ ፥ ከዚህም በስተቀር በዚ ያኑ ጊዜ ምንም ቢሆን ከቶ አላደርገውም ያሉትን ሌላውንም ድርጊት ሁሉ ላያደርጉ የማሉትን መሐላ አክብረው ባለመጠ በቅዎ ነው ።

ዶን ኪሾትም መለሰ እዚህ ላይ እውነት አልህ ፥ ሳንቾ ፥ ጸሩ ግን እውነተኛውን ስነግርህ የማልኩት መሐላ ሁሉ ከሃ ላቤ ውስጥ በመውጣቱ በሞራሽ ዘንግቼው ነበር ። ባንተም ላይ የብርድልብሱ ጉኖሽ ሊደርስብህ የቻለው ስለአንድ ጉዳይ መሣ ሌን እያወቅህ እንዳልረሳው በየጊዜው እየጐተጐትህ ሳታስጠ ነቅቀኝ በመቅረትህ መሆኑን ለማረጋገጥ ትችላለህ ። ይሁን እንጂ በፈረሰኛነት ትእዛዛትና ደንቦች ውስጥ በያንዳንዱ አንቀጽ ላይ

የሚያርሰውን የተጣመመ ጉድለት እያቃኑ ለማረም የሚረዳ ዘዴ ስለማይታጣ ይህ ከመዘንጋት የመጣ ጉድለታችን የሚሻሻል በትን መንገድ ለማግኘት እንደምችል ተስፋ አደርጋለሁ ። አለው

ሳንቾም በመገረም እንዲህ ሲል ጠየቀ ፥ «ጌታዬ ሆይ ! ይቅርታዎን ያድርጉልኝና እረ ለመሆኑ እኔን በዚህ መሐላ ውስጥ የሚያገባኝ ነገር ኖሯልን? ምናልባት ደግሞ ስላንዳች ጉዳይ ስምል ሰምተውኝ ይሆንን አለው ።

« ያንተ አለመማል በውነቱ ቁምነገር የለውም » አለ ዶን ኪሾት ምክንያቱም ከጓላዬ እንደጅራት ተጣብቀህ ከኔ ጋር የምትዞር ስለሆንክ በዚህ የተነሳ የመሐላው ተካፋይ መሆን አለብህ ። ስለዚህ ለኔ የመጣው ዳፋ ሁሉ ላንተም የተረፈ ከደ ጉም ሆነ ከክፉው ድርሻህን ከማግኘት በአባሪ ተባባሪነት ተከ ስሰህ ከመቀጣት ለመዳን አትችልም ። የሆነው ሆኖ ለአሁኑ የሚበጀን ክርክሩን መተውና የስህተታችን ማረሚያውን ዘዴ ፈልገን ማግኘት ነው ።

ነገሩ እንዲህ ከሆነማ « አለ ሳንቾ አደራውን ጌታዬ ከዛሬ ጀምረው የማሉትን መሐላ ሁሉ እንደገና መላልሰው ያስታው ሱት ፥ ለወደፊቱም እንዳይረሱት ይጠንቀቁ ፤ ምናልባት መሐ ላው ያልተዘነጋ እንደሆነ እነዚያ የተረገሙት ቄራቆች ዳግመኛ በኔ ላይ ለማላገጥና በትከሻዬ ላይ ለመጨፈር የሚኖራቸው ፍላጐት ይወገድላቸው ይሆናል ፤ በርስዎም ላይ ቢሆን የመተናኮያ ሰበብ ሲያጠብዎ ይተውዎታል አለው ።

እንግዲህ ከብዙው በጥቂቱ ይሆን እየተባባሉ ሲጓዙ በመ ንገዳቸው ላይ ቀኑ ስለጨለመባቸው የሚያድሩበትን ሥፍራ ለማግኘትም ሆነ ለማወቅ የነበራቸው ተስፋ ያመነታ ጀመር ። የባሰውን ደግሞ ሁኔታቸውን ይበልጥ ያከፋው ረሃቡ እየሞረ ሞረ ሊገድላቸው መድረሱ ስለሆነ ምን ለማድረግ እንደሚችሉ ግራ ገብቷቸው ተጨንቀው ነበር ። ምክንያቱም የውዲሳው ቦርሳ ከጠፋ ወዲህ ከስንቅ ጋር ተሰነባብተዋልና ነው ። በዚህም በሚ ገኙበት ችግር ላይ የሚጐድለውን ችግር ለመሙላት ሲል አሳ ረኛው ዕድላቸው ሌላ አደገኛ አጋጣሚ ፈልጐ አቀረበላቸው ።

ይህም የተገኘው አጋጣሚ በዚያን ጊዜ በከበባቸው ጨለማ ውስጥ ሆነው በሩቁ ሲያዩት የአደገኛነቱን ብርቱነት ለማረጋገጥ አን ዳች ማሰብና መጨነቅ ሳያሻ እውነተኛ አስፈሪ አጋጣሚ መስሎ ይታይ ነበር ።

ጊዜው ወደ መንፈቀ ሌሊቱ በተቃረበ ቁጥር ጨለማው እያደር እየደነጐረ ይሄድ ጀመር ። ይህም ሆኖ ይህ የሚጓዙበት መንገድ አውራ ጐዳና በመሆኑ ምክንያት በሳንቾ አስተያየት ከዚህ ከአለበት ነጥብ አንስቶ ግፋ ቢል ካንድ ወይም ከሁለት ምዕራፍ ጉዞ በኋላ ወደ አንድ የመንገድ ዳር ሆቴል ቤት ለመ ድረስ እንደሚቻል ገምቶ ነበርና በመጨረሻ ተስፋቸው እየተጥ ናኑ ጉዞአቸውን ቀጥለው ነበር ። ይሁን እንጂ በዚህ አካኋን በደነጐረው ጨለማ ውስጥ እየተደናበሩ ጋሻ ጃግሬው በረሀብ እን ደጠወለገ ፥ ጌትዬውም መብላት እንዳስከጀለው ሆነው በሚንጠራ ወዙበት ጊዜ በዚያው መንገድ በስተፊታቸው በኩል የብዙ ተወር ዋሪ ከዋክቶች ብርሃን የሚመስሉ እያሌ የችቦ መብራቶች በሚያስደ ነግጥ ሁናቴ እየተንቦገቦገ ወደነሱ ሲመጣ አዩ ። ሳንቾ ይሀን ትር ዒት አሻግሮ በተመለከተ ጊዜ ከመደንገ ጡ የተነሳ እንደሕፃን ልጅ ባብቶ እንደፈዘዘ ቀረ ። ዶን ኪሾትም በወትሮው የፀ ጥታ ስሜቱ ላይ ነበር ለማለት አያስደፍርም ነበር ። ይህም ሆኖ እንደኛው የአህያውን ሉኮ ስቦ ሁለተኛውም የፈረሱን ልጓም ጐትቶ ከቆሙ በኋላ ይህ ወደነሱ የሚመጣው መብራት ምን ለመሆን እንደሚችል ለማወቅ በጥንቃቄ ይመለከቱ ጀመር ። መብራቶቹ ወደእነሱ እየተቃረቡ በመጡ ቁጥር የብርሃናቸው ውጋጋን እያደር እየነገሠ ይታያቸው ነበር ። ሳንቾ ይሀን ቃጠሎ እንዳየ ወዲያውኑ የእንቅጥቅጥ በሽታ እንደለከፈው ሰው ሰው ነቱ ይርድ ጀመር ። ዶን ኪሾትም እንደተቆጣ አንበሳ የአራሱ ጠጕሮች ሲቆሙ ተሰማው ። ቢሆንም ልቡን አደፋፈረና ሳን ቾን እንዲህ አለው ።

ሳንቾ ሆይ ! ይህ የቀረበልን አጋጣሚ ያላንዳች ጥርጥር በጣም ታላቅና በጣምም አደገኛ አጋጣሚ መሆን ስላለበት ድፍረቱ ንና ኃይለኝነቴን ሁሉ አጠቃልዬ እዚህ ላይ አጋፍጬ ማሳየት ይገባኛል ።

«ወይኔ ያልታደልኩት» ሲል አቅማማ ሳንቾ ይህ አጋጣሚ ምናልባት እንደዚያን ሰሞኑ ያሰ የሚከናወን እንደሆነ መቸም በአመጣጡ እንደሚታየው ይሽው የጭራቆች መስሎ ታይቶኛል እና ፤ እርግጫውንና ጡጫውን የምንችልበት ትርፍ ታፋና ጀርባ ማን ያበድረኝ ይሆን ? የኛው እንደሆነ ሰሞኑን ተወቅጦ ስለደቀቀ ለዛሬው እንደማይበቃ እርግጠኛ ነኝ ። ወዮልኝ ይብላኝ አለ ።

«ጭራቆችም ሆኑ ወይም ብራቆች» ሲል መለሰ ዶን ኪሾት እኔ በመጀመሪያው ግጥሚያ ላይ ተመትቼ ካልወደቅሁ በስተ ቀር በሕይወቴ ቆሜ እያለሁ የፀጉርህን አንዲቷን ዘለላ እንኳ እንደማላስነካብህ እመነኝ ። ይህንንም የምልህ ባለፈው ጊዜ አንተ ስትልፈሰፈስ ከኔ ተለይተህ ወደኋላ በመቅረትህ ጭራቆቹ ብቻ ህን አግኝተው ሊጫወቱብህ የቻሉት እኔ የመስኩን አጥር ጥሼ ወይም ዘልዬ ለማለፍና ለእርዳታ ልደርስልህ ባለመቻሌ ነው ። አሁን ግን ሁላችንም የምንገናኝበት ሥፍራ አንዳች የሚያግድ አጥር የሌለበትና ጐራዴዬንም እንደልቤ ወዲያና ወዲህ ለመ ሰንዘር በምችልበት በጠራ ሜዳ ስለሆነ ፤ በፍጹም ቅንጣት ሥጋት ሊኖርህ አይችልም አለው ።

ሳንቾም እንዲህ ሲል ጠየቀ «ባለፈው ጊዜ እንደደረሰብዎ ሁሉ ያበሰኝ በምትሐታቸው ኃይል አፍዝዘው ያደነዝዙዎት እንደሆነ እጅና እግርዎ ሽባ ሆኖ ተጣትረው ሲቀሩ በገላጣ ሜዳ ላይ መገኘትዎና አለመገኘትዎ ለምን ጉዳይ የሚረዳዎ ይመ ስልዎታል ? አለው» ።

ሰማኝ ሳንቾ «አለ ዶን ኪሾት» በማናቸውም ረገድ እንግ ዲህ ተመልሰህ እናትህ ሆድ አትገባምና አይዞህ አትፍራ ልብ ህን ጥቂት ደፈር አድርገው ፥ አሞትህም ቆጣ ይበል ከዚያም በኋላ በግጥሚያው ሰዓት እኔ ምን ያህል ጀግንነት እንዳለኝ ፈተና ውን ታየዋለህ ። ለአደጋም አጣጣል ውድቀት ሌሊት ምቹ መሆኑን ግንንም ጠይቅ አለው ።

«ደግ ነው አለ» ሳንቾ» መቸስ ወዴት እደርሳለሁ በትክክል ለኛነቴ ተግምኜ ግጥሚያውን ለማየት ያህል እንኳ ዓይኔን እን ድገልጥ ከረዳኝ ማየቴ ወዴት ይቀራል ።

ከዚህም በኋላ ሁለቱም ከመንገዱ ጐራ ብለው የእነዚያ የሚንቀሳቀሱት መብራቶች ምስጢር ምን ለመሆን እንደሚችል ለማጣራት እንደገና በጥንቃቄ መመልከት ጀመሩ ። ከጥቂት ቆይታም በኋላ ነጫጭ ካባ የለበሱ ብዙ ሰዎች ታዩዋቸው። ይህም አስደንጋጭ ትርዒት የሳንቾን ነፍስ በሙሉ ስለ አሻከረው አርባ ቁጥር ትኩሳት እንደያዘው ሰው ጥርሶቹ ይንቀጫቀጩ ጀመር ፤ መንቀጫቀጩም እየበረታበት የሄደው የመጪዎቹ ሁኔታ ተገልጦ በውል ከታየ በኋላ ነው ። ይኸውም ሃያ የሚሆኑ ካባ ለባሾች ሁሉም በበቅሎ ተቀምጠው የተቀጣጠለ ችቦ ይዘው የሚመጡ ነበሩ ። ከነሱም በስተጀርባ በጥቁር የከል ጨርቅ የተሸፈነ አንድ ቃሬዛ ነበር ። ይህንንም ቃሬዛ በበቅሎ የተቀመጡ ስድስት ሰዎች እስከ በቅሎዎቻቸው ኩቴ ድረስ የተንዘረፈፈ ጥቁር የሐዘን ጨርቅ የለበሱ ስድስት ሰዎች ግራና ቀኝ አጅበውት ነበር ። የተቀመጡባቸውም ከብቶች በቅሎዎች መሆናቸው የታወቀው በአካሄዳቸው ዝግታና ዳተኛነት ነው ። ካባ ለባሾችም እርስ በእርሳቸው እየተቀባበሉ ዝቅ ባለ አጉረምራሚ ድምጽ ሥርዓተ ፍትሐት እያደረሱ ይንዙ ነበር ።

በዚያ በውድቅቱ ሌሊትና በዚያ ጭው ባለው በበረሃ ቀበሌ የሚታየው ይህ ልዩ የሆነው ትርዒት በጌታውና በተለይም በጋሻጃግሬው ልብ ውስጥ ተቅማጥ የሚያስመጣ ፍርሐት ለማሳደር ያህል በቂነቱ ከመጠኑ በላይ ነበር ።

ምንም እንኳ ዶን ኪሾት በእኳኋኑ ፍርሐት ያደረበት መሆኑን ለመግለጥ ባለመፍቀዱ ጨክኖ ቢግደረደር የሳንቾ ፖንቻ ድፍረት ሁሉ ገና ድሮ እንደ በረዶ ማሙቶ ውሀ ሆኖ ማለቁ ተረጋግጧል ። ዶን ኪሾት ግን ስሜቱ አፍራሻውን ሆኖ በመገኘቱ በዚያን ሰዓት በቅዠት አስተያየቱ እንደሚመለከተው የተጨበጠ እውነት አድርጐ የገመተው ይህ የሚመጣው አጋጣሚ በዚያ ባነበበው የፈረሰኞች ታሪክ መጽሐፍ ላይ ተደረገ ተብለው በሚ ተረክው ዓይነት እና መልክ ሆኖ የሚታይ መሆኑን ነበር ። ይህን ግምት መሠረት በማድረግ በዚያ በቃሬዛው ውስጥ ተኝቶ የሚገኘው ክፉኛ የቆሰለ ወይንም የሞተ ፈረሰኛ መሆኑን አሰበ ። እንዲሁም ደግሞ የዚህን ፈረሰኛ ደም ለመበቀል የቀረበው ግጥ

ሚያ በተለይ ለሱ ብቻ የተወሰነ መሆኑን አመነ ። ስለዚህ ብዙ ሐተታ ሳያበዛ ጦሩን ዘቀዘቀና በኩርቻው ላይ ተመቻችቶ ተቀመጠና በቁርጠኝነትና በቀልጣፋነት መንፈስ ፈረሱን እያራመደ ሄደ ። እነዚያ ካባ ለባሾች በግዴታ ለማለፍ በሚመጡበት መንገድ መካከል ቆሞ ጠበቃቸው ።

ሰዎቹ እየቀረቡ መጥተው አጠገቡ መድረሳቸውን ካየ በኋላ ድምጹን ከፍ አድርጐ እንዲህ ሲል አስጠነቀቃቸው ። የሴሊት ዙዋሪ ፈረሰኞች ሆይ! ሁላችሁም ባላችሁበት ሥፍራ ቁሙ ፥ ማንኛችሁም ብትሆኑ ሳትነቃነቁ እዚያው እንዳላችሁ ማን እንደሆናችሁ ፥ ከወዴትስ እንደምትመጡ ወዴትስ እንደምትሄዱ ፥ በዚያ በቃሬዛው ውስጥ የተሸከማችሁት ማንን እንደሆነ በዝርዝር አስታውቁኝ ። ለኔ እንደሚመስለኝ ግን ሁኔታችሁ የሠላም ወይም የጠብ መሆኑ ስለማይለይ ፥ ምናልባት እናንተ በሌሎች ላይ የግፍ ሥራ ሠርታችሁ በጨለማ ውስጥ ተደብቃችሁ ለማምለጥ የምትሞክሩ ሰዎች እንደሆናችሁ ወይም ደግሞ ሌላ ሰው በእናንተ ላይ የግፍ ሥራ ሠርቶባችሁ በብርሃን መንገድ እንዳትሄዱ ከልክሏችሁ እንደሆነ ከሁለት አንዱ ሳይሆን አይቀርምና ምስጢሩን አብራርታችሁ ልትነግሩኝ ይገባችኋል ። ምክንያቱም የፈረሰኝነት ተግባሬ እንደሚፈቅድልኝ አጥፊዎቹ እናንተ እንደሆናችሁ የሚገባችሁን ቅጣት ለመስጠት ፥ ወይም ደግሞ ሌላ ሰው በድሏችሁ እንደሆነ እሱን ተከታትዬ ልበቀልላችሁ እንድችል በቂ የሆነ ማስረጃ ከናንተ ዘንድ ለማግኘት እፈልጋለሁና በፍቅርና በሰላም ንገሩኝ አላቸው ።

ከካባ ለባሾች መካከል ወደፊት ቀደም ብሎ የቆመው አንደኛው ሰው እንዲህ ሲል መለሰለት ። እኛ በአካሄዳችን መቻኮል እንደሚያዩት ወደሰፈር ለማድረስ በጣም ተጣድፈናል የምናድርበት ሆቴል ሩቅ ስለሆነ ይህን የተጠየቅነውን አስረጂ መልስ ለመስጠት ስንል እዚህ ተግተረን የምናባክነው ትርፍ ጊዜ አናገኝልዎትምና እርስዎም በፍቅርና በሠላም መንገዱን ይልቀቁልን ካለው በኋላ በቅሎይቱን ኮረኮረና ወደፊት ጥሎ ለማለፍ መጣ ።

ዶን ኪሾትም በዚህ ጕምዛዛ በሆነ መልስ በመደፈሩ የንቀት ሁኔታ ስለተሰማው የበቅሎይቱን ልጓም አፈፍ አድርጕ የተናጋሪውን እርምጃ ከዳኘ በኋላ እንዲህ አላቸው ።

« ኋላ አይሆንም ቁሙ ብያለሁ ፣ ትሁታንም ሁኑ ፣ ለጠ የቅኋችሁ ጥያቄ ተገቢውን መልስ ስጡኝ አለበለዚያ ግን ሁላ ችሁንም ለግጥሚያ ጋብዣችኋለሁ ።

ለተንኮሉ ደግሞ በቅሎይቱ ደንባራ ቢጤ ኖራ የልጓሟ መያዝ በጣም ስለአስበረገጋት የፊት እግሯን ሽቅብ አነሳችና ጌታዋን ከኮርቻው ላይ አሽቀንጥራ ወደመሬት ጣለችው ። በዚ ህን ጊዜ በእግሩ ይሄድ የነበረው እንደኛው አሽከር ካባ ለባሹ ባጉል ሁኔታ መውደቁን በተመለከተ ጊዜ በዶን ኪሾት ላይ የስድብ መዓት ያወርድበት ጀመር ።

ዶን ኪሾትም ከቅድሙ አንስቶ በቁጣ ላይ ነበርና ይህ ስድብ ተጨምሮ ቁጣውን ይብስ ስለአጋለው ጦሩን ዘቀዘቀና ሴላ ድጋሚ ማሰጠንቀቂያ ሳይሰጥ እንደኛውን ባለጥቁር ካባ ወግቶ ክፉኛ አቁስሎ እመሬት ላይ ዘረረው ። ቀጥሎም ወደ ሴሎቹ ዞረና መካከላቸው ገብቶ እየጓጮጠ ያተራምሳቸው ጀመር ። በምን ያህል ፍጥነትና በምን ያህል ቅልጥፍና እየዋከበ እንደሚያ ስፈረጥጣቸው ለማየት በእውነቱ እዚያው አቦታ ላይ መገኘት የሚያስፈልግ ነበር ። በተለይም ደግሞ በዚያን ሰዓት ሮንዜና ንቴ እንደነፋስ ሲሮጥ ለተመለከተው ሰው የፍጥነቱ ብዛት በኮ ቴዎቹ ላይ ክንፍ ያበቀለ ይመስል ነበር ።

ካባ ለባሾቹ ሁሉም ጀሌዎችና ወዲህም ግርግር የማይወዱ የገዳም ሰዎች ስለነበሩ እንዳች መለመን ሳያስፈልጋቸው በቶሎ የጦር ሜዳውን ለቀቁለትና እነዚያን በቡሔ ሌሊት የሚጨፍ ሩትን ጕረምሳዎች ይመስል የችቦአቸውን መብራት ከነፋስ ጋር እያውለበለቡ ቀሚሳቸውን ከፍ ከፍ አድርገው በማይገታ ፍጥነት በእርሻው መካከል ተፈተለኩ ። እነዚያ ጥቁር ሰናፍል የለበሱት ደግሞ ተከታትለው በሚሸሹበት ጊዜ እስከተረከዛ ቸው በተንዘረፈፈው መቀነታቸው በመጠቅለላቸውና በመጠ ምጠማቸው የተነሳ እየተወላከፉ እንኳንስ እሮጠው ለማምለጥ

ቀርቶ መላወስ ስለአቃታቸው ሞገደኛው ዶን ኪሾት አንዳች ተከላካይ እጅ ሳያግደው ቅድም እንደተናገረው እጁን በነፃነት ወዲያና ወዲህ እየሰነዘረ ቀሳውሶቶቹን በሶሩ ዛቢያ እየጀለጠ እነሱንም ያለውዱታቸው የጦሩን ሜዳ ለቅቀው እንዲሄዱ አስ ገደዳቸው ። ካባ ለባሾችም ሁሉ ይህን በድንገት የወደቀባቸ ውን አደጋ በተመለከቱ ጊዜ ያንን በቃሬዛው ላይ የሚገኘውን ሬሳ ነጥቆ ለመውሰድ በክፋቱ የለየለት ተንኮለኛ የመጣባቸው መሰላቸው እንጂ በውነቱ ከሰው የጭካኔ መንፈስ የመነጨ ያደጋ አጠጣል ዘዴ መስሎ ስለአልታያቸው በእንቆቅልና በእን ብርክክ እየዳሁ የተወቁበትን አውድማ ለቀውለት ሸሹ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ሳንቾ የአህያውን ጆሮ ግንድ ተገን አድ ርጕ ቆሞ የጌታውን ዲና ጣይነትና ጀግንነት እያደነቀ በመመ ልከት ብቻውን እንዲህ ይል ነበር ።

« ለካንስ ይህ የኔ ጌታ የማንቻው ዶን ኪሾት እርሱ እራሱ እንደሚለው በጉራ ብቻ ሳይሆን እውነትም ደፋርና ጀግና ኖሯል።

ዶን ኪሾት ነጋዴዎቹን አባርሮ ሲመለስ መጀመሪያ ከበ ቅሎይቱ ላይ ተገልብጦ የወደቀው አንደኛው ካባ ለባሽ አንድ እግሩን እርካብ ጠልፎት ሁለተኛው እግሩ በኮርቻው መሃል ተሰንቅሮ ከበቅሎይቱ ጋር እንደወደቀ የያዘውም ችቦ እስከዚያን ሰዓት ድረስ እንደበራ ይታይ ስለነበር ዶን ኪሾት በዚህ መብራት ብርሃን እየተመራ መጥቶ አጠገቡ ደርሶ ሰውዬውን ከአየው በኋላ ባንድ አፍታ ከፊረሱ ላይ ዱብ ብሎ ጀርባው ላይ ተከ መረበትና የአንካሴውን ጫፍ እፊቱ ላይ ደግኖ እንዲህ ሲል ጮኸበት ። ነፍስህን ትመርጥ እንደሆነ ተማረክ ፣ አለበለዚያ ግን ገደልኩህ አለው ።

ወዳቂውም እንዲህ ሲል መለሰለት ፣ ከዚህ ይበልጥ ምር ኮኛ ለመሆን አልችልም ፣ ምን ዓይነት መማረክ ነው የሚጠ ይቁኝ አንዱ ቅልጥሚ ስለተሰበረ ለመነቃነቅ እንኳ አልሆነል ኝም ። ይልቁንስ በእውነት ፈረሰኛ እንደሆኑ ነፍሴን እንዲያተ ርፉልኝ ክቡርነትዎን ተማጥኜዎታለሁ ። በተረፈ ግን እኔ እንድ

ካህን ስለሆንኩ የገደሉኝ እንደሆነ ይቅርታ የማይደረግለት ሠረይ ከባድ ጥፋት መሥራትዎን ይወቁ አለው ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል ጠየቀው ፥ የቤተ ክህነት አገልጋይ ከሆኑ እዚያው ቤተ ክርስቲያን መጸለይዎን ትተው የምን ዲያብሎስ ነው እየነዳ በዚህ ሰዓት እዚህ ስፍራ ያመጣዎት? ያም መለሰ ። የነዳኝማ መጥፎው ዕድሌ ነው አለው ።

«ይጠንቀቁ አለ ዶን ኪሾት ፥ የተዛተብዎ አደጋ ከቅድሙ የባሰ ብርቱ ስለሆነ በመጀመሪያው ጊዜ ላቀረብኳቸው ጥያቄዎች ሁሉ የሚያጠግብ መልስ ካልሰጡኝ በስተቀር ፥ ያልኩትን ማድረጌን» ነው አለው ።

« ማናቸውንም ሁኔታ ባጭር ቃል ስነግርዎ ከቡርነትዎ ለጠየቁት ሁሉ የሚያጠግብ መልስ በቀላሉ ሊያገኙበት ይችላሉ» አለው ። ካህኑ ንግግሩን በመቀጠል «ምንም እንኳ ቅድም በድንጋጤ መንፈሴ ተሸብሮ ካህን ነኝ ብልዎት ካህንነቴን አፍርሼ ደብተራ ከሆንኩ ሰንብቻለሁ ፥ ስሜም ያብተራ አሎንሶ ሎፔዝ ይባላል ፥ ተወላጅነቴም በአልኮቬንዳንስ አውራጃ ነው ። የመጣሁትም ከነዚያ ከነችበአቸው ከሸሹት አስራ አንድ ቀሳውስቶች ጋር ከቦይዛ ከተማ ነው ። የምንሄደውም እዚያ ቃሬዛ ላይ የተጋደመውን አፅም ይዘን ወደ ሲጐቪያ ነው ። ይህ ሟቹ በአገራችን የታወቀ ጀግና ፈረሰኛ ነበር ። በድንገት ቦዬዛ ላይ ሞቶ ለጊዜው እዚያው ተቀብሮ ሲኖር አሁን ደግሞ እንደነገር ኩዎት ሴጐቪያ የተወለደበት አገር ስለሆነ እዚያ አድርሰን ከቤተሰቦቹ መቃብር ጐን ለመቅበር እንደሚያዩን ሆነን ስንነገዝ ይህ አደጋ ወደቀብን አለው ።

«ለመሆኑ ግን ናሯል የገደለው» ሲል ዶን ኪሾት ጠየቀ ።

«ደብተራውም መለሰ» የሞተበት ምክንያት በብጫ ወባ ተቀስፎ ነው ገዳዩ ግን እግዚአብሔር መሆኑ ነው» አለው ።

«አሚሚቱ እንዲህ ከሆነማ» ሲል ዶን ኪሾት ተግባባ ። « መቸም ሌላ ሰው ገድሎት ቢሆን ኖሮ ደሙን ሳልበቀልለት አልቀርም ነበርና ጌታችን የዚህ ሰው ሞት ለመበቀል ስል ማድ

ረግ ከነበረብኝ ድካም አዳነኝ ማለት ነው ። ዳሩ ግን የገደለው እጅሬ ስለሆነ አፈን ዘግቼ ዝም ከማለትና እንጉቴን ከማቀርቀው ሌላ ምንም ለማድረግ አልችልም ። ምክንያቱም እንኳንስ ሌላ ሰው በመገደሉ ልቆጣው ይቅርና እኔንም ቢገድለኝ ኖሮ ከዚህ ይበልጥ መኩራመት ስላሰብኝ ነው ። የሆነው ሆኖ ያካሄዳችሁ ምክንያት ከተገለጠልኝ ወዲህ እጄን በቤተ ክህነት ሰዎች ላይ በማሳረፌ በውነቱ ልቤ በሃዘን ሳይነካ አልቀረም ። ይሁን እንጂ ያለፈው አልፏልና ላሁን ብፁዕነትዎ እንዲያውቁልኝ የምሻው እኔ ዶን ኪሾት የምባለው የማንቻው ፈረሰኛ መሆኔንና ተግባሬና ግዳጄም በዓለም ዙሪያ እየተዘዋወርኩ አጋጣሚዎን መፈለግና ጠማማዎችን ማቅናት ጉዳትን መጠገን መሆኑን ነው ። ደብተራው እንዲህ ሲል መለሰ ፤ ጠማማዎችን ለማቅናት የሚችሉት በእንዴት ያለ አኳኋን እንደሆነ በውነቱ ምስጢሩ ሊገባኝ አልቻለም ። እኔ ቅድም ቀጥ ብዬ የነበርኩትን አሁን ጠማማ እንድሆን አድርገውኛል ። ይህንንም ማለቴ እንዱ እግሬ እንዲሰበር ምክንያት ስለሆኑብኝ ምን ጊዜም ቢሆን ተመልሶ ሊቃና እንደማይችል እርግጠኛ በመሆኔ ነው ። ጉዳትን በመጠገን ረገድ ደግሞ እኔን እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ እንደተጐዳው በምቀርበት አኳኋን ጐድተውኛል ። ስለዚህ አጋጣሚ ፍለጋ ከሚዞሩት ከክቡርነትዎ ጋር መገናኘቴ በኔ ላይ የቱን ያህል የከበደ አደጋ እንደ ጣለብኝ በሁኔታዬ ሊረዱት ይችላሉ አለው ።

ዶን ኪሾትም መለሰ « ወዳጄ ደብተራ አሎንዝ ሎፔዝ ሆይ» አንዴ ይስሙኝና ልንገርዎት ፥ ጉዳዮች የተባሉት ሁሉ ባንድ ዓይነት አቅድ ተመርተው አይፈጸሙም ። የዛሬውን ሁኔታ ወደ እደ ገኛ መልክ የለወጠው ይህ የሴሲት አመጣጣችሁ መሆኑን ይመኑኝ ። በዚህ አኳኋን በጥቁር ካባ ተጠቅልላችሁ የተቀጣጠሉች ችቦ ፥ እያውለበለባችሁ ፤ እንደዚያ እያጉረመረማችሁ ፤ የሀዘን ከል ለብሳችሁ ፥ በሴሲት ስትሄዱ ላያችሁ ሁሉ መጥፎ መንፈስ የሚያሳድርበት ስለሆነ ፤ አምሳያችሁ የልቡን ክፋት ወይም ደግሞ የሌላ ዓለም ልዩ ፍጥረቶች እንጂ የዚህ ዓለም ሰዎች መሆና ናችሁን የሚያምን ከቶ አይገኝም ነበር ። ስለዚህ እኔም ባየኋችሁ ጊዜ ይኸው መንፈስ ያደረብኝ በመሆኔ ምክንያት ተግባሬን ለማንደል ስላልቻልኩ በቀጥታ ላጠቃችሁ ተገደድኩ ። እስካ

ሁንም ድረስ እንደገመትካችሁ ሁሉ እውነተኞቹ የክፋት ምን ጮች መሆናችሁን አረጋግጩ ባውቀውም ኖሮ ያለ ጥርጥር ሳላንኩታችሁ አልቀርም ነበር ።

« መቼም » አለ ደብተራ « ገደቢሱ እጣዬ እዚህ አደጋ ላይ እንድወድቅ እንዴ ፈርዶብኛልና የዛሬውን ቀን በማናቸ ቸውም አካሏን ላመልጠው አልችልም ነበር ። አሁንም ጌታው ዙዋሪ ፈረሰኛ መልካም ፈቃደዎ ይሁንና ከዚህች በቅሎዬ ስር እንድወጣ ይርዱኝ ። አንዱን እግሬን በእርካቡና በኩርቻው መካ ከል አጣብቃ ስለያዘችኝ ብቻዬን ለመላቀቅ አቅቶኛል አለው ።

«እኔ እርስዎን ብሆን ኖሮ» ሲል ዶን ኪሾት በማፌዝ መለሰለት «ይህን እርዳታ ለመጠየቅ እስከ ነገ ጡዋት ድረስ እጠብቅ ነበር ፣ ለመሆኑ ነገሩ ከታወቀ ወዲህ እርዱኝ ለማለት እስከዚህ ሰዓት ድረስ መቆየት ያሻ ኖሩዋልን? ይህን ከተናገረ በኋላ ለእርዳታ ፈጥኖ እንዲደርስ ሳንቾን ጠራው ። ሳንቾ ግን ለጊዜው ጥሪውን ሰምቶ መልስ ለመስጠት ፋታ አላገኘም ነበር ። ምክንያቱም ፣ እነዚያ የተባረኩ ሰዎች የመንገድ ስንቃቸውን በደንብ አሰናድተው ጭነው በስተኋላቸው ያስከተሉትን አጋሰስ አግኝቶ እሱን ከመንገድ አግ ልሎ ቀርቃባውን ፈትቶ አገልግል በመበዝበዝ ሥራ ተወስኖ ስለነበረ ነው ። ስለዚህ ባናውን መሬት ላይ አንጥፎ ከሞኑቱ ውስጥ ጠቃሚ ሆኖ ያገኘውን ሁሉ አራግፎ ባናው ለመያዝ የቻለውን ያህል አንሰቶ በአህያው ላይ ከጫነ በኋላ ጌታው የተጣራበትን ምክንያት ለማወቅ ሄደና ደብተራውን ከበቅሎይቱ ሥር ጐትቶ ለማውጣት እገዘው። ቀጥሎም ደጋግፈው እበቆሎይቱ ላይ ካስቀ መጡት በኋላ ሳንቾ ችቦውን ሲያቀብል ዶን ኪሾት ደግሞ እነ ዚያ ጓደኞቹ የሸሹበትን አቅጣጫ ይዞ እንዲከተላቸው በመም ከር ይህን የወደቀባቸውን አደጋ ከመጣል ለመታገድ ሳይችል ከቀረ ጥፋቱ የሱ አለመሆኑን ገልጦ በማስረዳት በሱ ስም ሆኖ ይቅርታ እንዲጠይቅለት ለመነው ። ሳንቾም በተጨማሪ ለደብተ ራው እንደዚህ ሲል አስረዳ። ምናልባት እነዚያን መኳንንቶች በዚህ ሁኔታ አጉሳቁሎ ያስፈረጠጣቸው ጀግና ሣን መሆኑን ለማወቅ የፈለጉ እንደሆነ ስመ ጥሩው የሚንቻው ዶን ኪሾት መሆኑን እንዲሁም ተደራቢ ስሙ «የአረመመው ፈረሰኛ የሚባል መሆ ኑን እንዲያስታውቁአቸው አለው ።

ደብተራውም ንግግራቸውን ካሰጨረሱ በኋላ እንደተመ ከሩት ጓደኞቻቸው የሸሹበትን ዱካ ተከትለው ሄዱ ። ዶን ኪሾት ግን ይህ ጋሻ ጃግሬው ያወጣለት አዲስ ስም ምስጢሩ ምን እንደሆነ ለማወቅ ስለቸኮለ ከዚህ ቀደም ሳይሆን ልክ ባሁኑ ሰዓት የአረመመው ፈረሰኛ ብሎ የሰየመበት ምክንያት እንዲ ያብራራለት ጠየቀው ። ሳንቾም ምስጢሩን አሁኑ ገልጭ እነ ግርዎታለሁ ሲል መለሰለትና ማስረዳቱን በመቀጠል» እንዲህ ብዬ መሰየሜ በዚህ ባልታደለው የተንኮለኛ አጠገብ ሲበራ በነበረው የችቦ ብርሃን ትይዩ ሰጥቂት ጊዜ ስመለከትዎ ቆይቼ ነበርና ይህን ያህል ጊዜ አብሬዎ ስኖር ምን ጊዜም ያላየሁቦ ትን እጅግ የሚያስቀይም ጨፍጋጋ የትካዘ መልክ በፊትዎ ላይ በማየቴ ነው ።

መልክዎንም ለመለወጥ ምክንያት የሆነው ለኔ እንደሚመስ ለኝ በዚህ ውጊያ ላይ ደካም ስለተሰማዎት ወይም ደግሞ የጥርስዎ መርገፍ እያበሳጨዎት ይሆናል አለው ።

«ምክንያቱም ይህ ሊሆን አይችልም» አለ ዶን ኪሾት ዳሩ ግን የጀብዱ ሞያዬን ታሪክ ለመጻፍ ኃላፊነት የተጣለበት ሊቅ ለጥንቶቹ ዙዋሪ ፈረሰኞች እንደሚወጣላቸው ሁሉ እኔም አንድ ተደራቢ ስም እንዲወጣልኝ አስፈላጊ መሆኑን ስለአመነ ይሆናል ። ለጥንቶቹም ዙዋሪ ፈረሰኞች የወጣላቸውን ስም የግ ስታውሰውን ሰምሳሴ ያህል ልጠቅስልህ እፈቅዳለሁ ። ይኸውም ባለ አብረቅራቂ ሰይፍ ባለ አንድ ቀንድ ፣ ባለ ሴት ወይዘሮ ፣ ባለ አፈ ያፈድ ፣ ባለ ጆቢራ አሞራ ፣ ባለዓዕረ ሞት የሚባሉ ፈረሰ ኞች ሁሉ በየጊዜያቸው በዚህ ተደራቢ ስም እየተጠሩ በመላው ዓለም የታወቁ ሆነው ነበር ። ስለዚህ እኔ እንደማምነው ያ ያል ኩህ ሊቅ አንተ ባለ ትካዘ መልክ የሚል ስም እንድትለወጣ ልኝ ሃሳቡን በእራስህ ውስጥ አግብቶ በምላስህ ላይ አናግሮህ ይሆናል ። እኔም ከአሁኑ ጀምሬ ወደፊት በዚሁ በወጣልኝ ተደ ራቢ ስም ለመጠራት አስቤአለሁ ። እንዲያውም ስመ ጥሩ ሆኖ ከመልኬ ጋር እንዲመሳሰል ጊዜ ሳገኝ በጋሻዬ ስጉድ ላይ የት ካዘ መልክ ሰዕል አስልበታለሁ አለው ።

«የዚህን ዓይነት መልክ ለማሳል ሲሉ ጊዜ ማጥፋትና ገን ዘብ ማባከን በፍጹም የሚያስፈልግ አይደለም «ሲል መለሰ ሳንቾ ክቡርነትዎ ፊትዎን ወደሚመለከትዎ ሰው አዙረው ከታዩ ይህ ብቻ በቂ ነው ፣ በዚያን ጊዜ ማናቸውም ተመልካች ስዕል ማየ ትና ጋሻ መመከት ሳያስፈልገው መልክዎንና ስምዎን በማመሳ ከር ወዲያውኑ በቀጥታ ይህ «የአረመመው ፈረሰኛ » ነው ብሎ እንደሚጠራዎት እርግጠኛ ለመሆን ይችላሉ ። የተናገርኩትም እውነቴን መሆኑን ይመኑኝ ። ምክንያቱም (በመቀለዴ ይቅርታ ያድርጉልኝና) በረሃብ መጠውለግዎና ጥርስዎም መርገፉ መል ክዎም አጨማዶ አስቀያሚ ስለአደረገዎት ቅድም እንደነገር ክዎት ተጨማሪ መግለጫ የሚሆን አስቀያሚ መልክ ማሳል በፍጹም ሊቀር የሚችል ነገር መሆኑን አረጋግጥልዎታለሁ» አለው ።

ዶን ኪሾትም በሳንቾ የቀላጅነት መንፈስም ከልቡ ሳቀ ። ሆኖም ያንን የወጣለትን ተደራቢ ሰም ለመውሰድና እንዲሁም እንዳሰበው ሁሉ የትካዜውን መልክ ስዕል በጋሻው ላይ ለማ ሳል ቁርጥ ሃሣብ አድርጐ ሳንቾን እንዲህ አለው ።

« የምወድህ ሳንቾ ሆይ ! የተቀደሰውን ነገር ያረከሰ እር ኩስ ይሁን እንደተባለው እኔ በዛሬው ቀን የተወገዝሁ መሆ ኔን አሳምሬ አውቄዋለሁ ። ምክንያቱም ምንም እንኳ እነዚያን ሰዎች የነካኋቸው በእጄ ሳይሆን በዚህ በያዝኩት አንካሴ ቢሆን በአጥቂነት መንፈስ ተገፋፍቼ ብፁዓን የሆኑትን የቤተ ክህነት ሰዎች በመንካቴ ተፀጽቻለሁ ። እንደምታውቀኝ በምግባሬ ፍጹም በአልሁበት ነገር የጸናሁ እንደመሆኔ መጠን እጅግ አድርጌ የማ ከናውነውንና የማመለክተበትን የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይና በተ ለይም ካህናትን ለመበደል አላሰብኩም ነበር ። መቼም ልፋቴ ሁሉ እነዚያን አጋንንቶችና የሌላ ዓለም ጀግያኮሳትን ከምድር ላይ ለማጥፋት ስለነበረ አስማተኞቹ አዛውረው ወደምወገዝበት ጥፋት ላይ ጣሉኝ ። ይህም ውግዘት የሚያርስብኝ ቢሆንም ቅሉ በሴዲ ሩዋይዲያዝ ላይ የደረሰውን ሁኔታ ፣ አስታውሰዋለሁ ፣ ይኸውም በብፁዕነታቸው ፊት ቀርቦ የነበረው አምባሳደር የተቀ መጠበትን ወንበር ረግጦ በመሰባበሩ በዚህ ምክንያት መወ

ገዙን ነው ። ይህም ሆኖ በዚያኑ ዕለት ጉበዙ የቪቫሩ ርድ ሬጉ በፈጸመው የወንድነት ሙያ የተከበረና ዋጋ ያለው ፈረሰኛ የሚ ያደርገውን ስመ ጥሩነትን አግኝቷል ።

ይህን አነጋገር ደብተራው ከሰማ በኋላ እንደተባለው ሁሉ አንዳችም መልስ ሳይሰጥ ትቷቸው ሄደ ።

ዶን ኪሾትም በዚያ በቃሬዛው ውስጥ እውነት እንደተ ባለው የሰው አጽም መኖር አለመኖሩን አይቶ ለማረጋገጥ ፈቅዶ ነበር ፣ ሳንቾ ግን ይህን ሃሳቡን በመቃወም እንዲህ አለው ።

«ክቡርነትዎ ይህን የዛሬውን አደገኛ ግጥሚያ ከሌሎች እስካሁን ድረስ ከአየኋቸው ግጥሚያዎች ሁሉ እጅግ በተሻለ አኳኋን ተወጥተውታል ፣ እነዚህ ሰዎች ምንም እንኳ ቢሸ ነፉና ቢበታተኑ እንዲህ አድርጉ ያንኰዳቸው አንድ ሰው ብቻ ውን መሆኑን ሲያመዛዝኑ ጥቃትና እፍረት ተሰምቷቸው በመ በቀልና ድሉን ለማግኘት ሊፈልጉ መመለሳቸውና ቢያገኙም እንደማንተርፋቸው አድርገው ማጥመልመላቸው የማይቀር ነገር ስለሆነ በኔ ይሁንብዎትና ምክሬን ይቀበሉኝ ። አህያይቱ ዝማጁ ሆናለች፡ ዝማጁ የሆነችውም ደስ በሚያሰኝ መሰናዶ ነው ፣ አፋፍ ቅርባችን ነው ። እረሃቡ ወንቷል ፣ ስለዚህ ባሁኑ ሰዓት እንዲህ እንደ አማረብነ እርምጃችንን አስረዝመን ከመሥገስ በስተቀር ሌላ ነገር መመራመር አያስፈልገንም ተረቱም የሚለው «የሞቱት ወደመቃብራቸው ፣ የቆሙት ወደ እንጀራቸው ትዳራቸው» ነውና እዚህ ስንልከሰከስ ተገኝተን አደጋ እንዳይደርስብን መሥጋት ይገ ባናል ፤ ካለ በኋላ መልስ እስኪሰጠው ድረስ ሳይጠብቅ አህያይቱን ወደፊት እየነዳ ጌታው ተከትሎት እንዲመጣ ለመነው ። ጌታውም የሳንቾ አስተያየት ትክክለኛ ስለመሰለው እንደል ማዱ ሳይከራከር ተከተለውና ጉዞአቸውን ጀመሩ ። በሁለቱ ኮረ ብታዎች መካከል ተጠምዘዘው ጥቂት ምዕራፍ መንገድ ከተ ጓዙ በኋላ ሰፋ ያለመስክ የሚገኝበት ሆኖ ምኞት የሚያን ሰው እረባዳ ቦታ ላይ ደርሰው ሠፈር አደረጉ ። ሳንቾም ፈጥኖ አህያውን አራገፈና እነዚያ የሚቹ አጃቢ ቂሶች (በረሀብ መጐዳትን ያልለመዱ ሰዎች በመሆናቸው) በደንብ ሰንቀው

በበቅሎ ጭነው በሰተኋላቸው ካስከተሉት ላይ ዘርፎ የያዘውን ስንቅ ዘርግፎ በመስኩ ላይ ማዕዳቸውን ዘርግተው ተቀመጡና በረሃብ ወጥ እያጣፈጡ አንድ ሰሞን ለቁርስ ለምሳ ለመሸን ገሃ ለእራት የሚበቃውን ሁሉ በአንድነት አጠቃልለው ከሰ ከሱ ። ዳሩ ግን እዚህ ላይ ሌላ ጠንከር ያለ ችግር ደረሰባቸው ። ይኸውም በሳንቾ አስተያየት ከማናቸውም ችግር ይበልጥ የከፋ ሆኖ የታየው የሚጠጣ ወይን ጠጅ ባለማግኘቱና የባሰውን ደግሞ ከንፈራቸውን የሚያርሱበት አንድ ጠብታ ውሀ እንኳ መታ ጣቱ ነው ። በውነቱ ይህ የውሃ ጥም ታላቅ ሥቃይ ፈጥሮባቸው ነበርና ከተቀመጡበት መስክ ላይ የበቀለውን ሣር እርጥበትና ለምለምነት ሳንቾ ተመልክቶ በሚቀጥለው ምዕራፍ ላይ የሚ ተረከውን ተናገረ ።

ምዕራፍ 20

በስመ ጥሩነታቸው ፡ በመላው ዓለም ላይ የነገኑት ዙፋሪ ፈረሰኞች ምን ጊዜም ይህን የመሰለ ብርቱ አጋጣሚ ለማግኘት እድል ሳይኖራቸው ጀግናው የማንቻው ዶን ኪሾት አማኙቱ እጅግ ባነሰ አደጋ ያከናወነው ከቶ ያልተሰማና ያልታዩ የጥሚያ ሁኔታ ይተረካል ።

ሳንቾ ፖንቻ እንዲህ ሲል ሃሳቡን ለጌታው አካፈለ ። «የተከበሩ ጌታዬ ሆይ ! ይህ የምንነካው ሣር እንደዚህ እርጥብና ለምለም ሆኖ ለመብቀል የቻለው በአቅራቢያው የምንጭ ወይም የወንዝ ስሜት ቢያገኝ ስለሆነ ጥቂት ወደፊት እለፍ ብለን ብን ፈልግ አይከፋም ። ዕድላችን አግዞን ወሀ ብናገኝ ይህን የሚ ያስቃየንን ብርቱ የውሀ ጥም በቶሎ ልናስወግደው እንችላለን ። ከረሃቡ ይልቅ ይበልጥ የጉዳን ውሃ ጥሙ ነው አለው »

ይህ ምክር ለዶን ኪሾትም የተስማማ ሆኖ ስለተገኘ ከእራታቸው ያተረፉትን ስንቅ በአህያይቱ ላይ ከጫኑ በኋላ ሳንቾ የአህያውን ሎሀ ሲስብ ዶን ኪሾት ደግሞ የሮንዚናንቴን ልጓም ይዞ መቸም የሴሊቱ ጨለማ አንዳች ነገር እንዲያዩ አልፈቀ ደላቸውም ነበርና በዳበሳ እየተመሩ ተከታትለው በመስኩ ላይ መሄድ ጀመሩ ። ዳሩ ግን ሁለት መቶ እርምጃ የሚሆን እንደ ተንዙ ካንድ ትልቅና ረጅም ከሆነ ቋጥኝ ላይ ቁልቁል የሚወርድ ፏፏቴ የሚመስል ታላቅ የውሀ ጉርምርምታ በኃይል እያስተ ተጋባ ወደ ጆሮአቸው ደረሰ ። ይህንንም ኃይለኛ ጉርምርምታ በሰሙ ጊዜ በደስታ ተጽናንተው ድምጹ የሚመጣበትን አካያ ለማወቅ ሲያዳምጡ እነሆ ሌላ ኃይለኛ ነጐድጓድ ተቀላቅሎ

ስለተሰማቸው በዚህ ምክንያት ቅድም ውሃ ለማግኘት ያደረጉት ደስታና ተስፋ ወዲያውኑ ወደ ፍርሃት ተለወጠባቸው ።»
በተለይም ሳንቾ በተፈጥሮው ፈሪና አሞተ ትንሽ በመሆኑ ይህ እሽባሪ ድምጽ ልቡን አባብቶ በድንጋጤ ሊገድለው ደረሰ ። ይህም አስገምጋሚ ድምጽ ከተራራና ከቋጥኝ ጋር እየተላጋ እንደሚወድቅ ብዙ ናዳ በመንጋጋትና እንዲሁም የብረትና የሰንሰለት ቅጭልጭል የሚመስል ኳኳታ አብሮት እየወረደ ከፏፏቴው ጩኸት ጋር ተገኝቶ የሚያሰማው ድብልቅልቅ ጩኸት የዶን ኪሾትን ልብ ላልያዘ ለሌላ ለማናቸውም ሰው ፍርሃትና ሽብር የሚፈጥርበት መሆኑ የተረጋገጠ ነበር ። ከላይ እንደተባለው ሁሉ ሌሊቱ በጣም የጨለመ በመሆኑና እነሱም ወደ ፈት ተጉዘው ረጣኙም ዛፎች የሞሉበት ጫካ ውስጥ በመግባታቸው ፣ የዛፎችንም ቅጠል ነፋስ እያወዛወዛቸው የለዘበና የቀፈፈ ሹክሹክታ ፣ በማሰማታቸው በዚህ አካኋን የሰፍራው መከበድ የጨለማው መደንገር ፤ የውሃው ማጉረምረም ፣ የቅጠሎቹ መንከሻከሽ ፤ ይህ ሁሉ እንድነት ተደምረው ሲታሰብ በውነቱ የሚያስደነግጥና የሚያስፈራ ነበር ። ይህም ሆኖ ፍርሃታቸውን ለመቀነስ ያህል እንካ ጉርምርምታው አላቋረጠም ፣ነፋሱም ፀጥ አላለም ፤ ሌሊቱ የመንጋት ምልክት አላሳየም ነበር ። በዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ በተጨማሪ ሁለቱ ከርታታዎች የሚገኙበትን ቦታ በፍጹም አያውቁም ነበር ። ዶን ኪሾት ግን በቆራጡ ልቡ ተደፋፍሮ ዘልሎ ሮንዝናንቴ ላይ ወጣና ጋሻውን አንግቦ ፣ እንካሲውን አጓምዶ ወደ ጉርምርምታው አቅጣጫ ለመሔድ ዝግጁ ከሆነ በኋላ ጋሻ ጃግሬው እንዲህ አለው ።

« ወዳጄ ሳንቾ ሆይ ! እኔ እውነትና ትክክለኛነት ከአንተ ጋር ይሁን ፤ በዚህ በብረት ዘመን መወለዴ ያንን የወርቅ ወይም የወርቀ ዘቦ የሚባለውን ዘመን ለማንሳት ነው ። እኔ ታላላቅ የጀብዱ ተግባሮችና መቅሰፍት የሆኑ አደጋዎች የተደገሱለት ሰው ነኝ ። እኔ አውንም መላልሼ እናግረዋለሁ ፤ እነዚያን የክብ ጠረጴዛ ጀግኖችን ፣ አስራ ሁለቱን የፈረንሳይ የኮበዝ አውራዎችን ፣ ዘጠኙን የዓለም ሰመ ጥሩዎችን ከተረሱበት ሥፍራ የማስነሳ ነኝ ። እኔ የነፕላቱርን ፣ የነታብላንቴን ፤ የነአባልቴን ፣ የነቴራንቴን ፣ የነፈቦን ፣ የነቤሊያንጂንና እንዲሁም ደግሞ ባለፉት ዘመናት

የነበሩት እነዚያ ስማቸውን ለማስጠራት ሲሉ ይህን የመሰለ ታላላቅ የጀብዱ ተግባርና የጦርነት ጉዳይ የፈጸሙትን ዘውሪ ፈረሰኞች ከንተከታዮቻቸው እጅግ ከባድና ጠንካራ የሆነ ሞያቸውን ዛሬ በጥላዬ የማጨልመው ነኝ ።

« ስለዚህ ታማኙና ቁምነገራሙ ጋሻ ጃግሬዬ ሆይ ! በል እንግዲህ ቅደምና የዚህን የሌሊት ጨለማ መንገድ ምራኝ ። የጨለማው አስደናቂ ዝምታና የነዚህ ዛፎች ልዝብና ድንቁር ያለው ሹክሹክታ ይህ ዱካውን ተከትለን የምንሄድበት እርዝመቱ ካለቀው ከጨረቃ ተራራ ላይ ፈልሶ የሚመጣ የሚመስለው አስደንጋጭ ድንፋት ፣ ይህ ጀሮአችንን እያቆሰለ የሚያደነቁርና ያለማቋረጥ የሚደወለው የብረት ቅጭልጭል ድምጽ እነዚህ ሁሉ አንድነት ተደምረው ፣ እንዲያውም እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ችለው ሲታሰቡ የዚያኑ የጦርነትን አምላክ የማሪቴን ልቡ በድንጋጤ ፣ በፍርሐትና በሽብር ለመሙላት የሚበቁ ናቸው ።

« ወዮላቸው እነዚያ ያለፉት ጀግኖች ይህን የመሰለ ከባድ ሁኔታና አደገኛ አጋጣሚ ሲያገኛቸው አሸንፈው ለመውጣት የቱን ያህል መጨነቅ እና መጠበብ ፣ ፍርሐትና ድንጋጤ እንደሚደርስባቸው ሳስበው በእጅጉ ያሳዝኑኛል ። ዳሩ ግን እነዚህ የማስደንገጥን ኃይል አከማችተው የያዙትና ድምጻቸውን የሚያሰሙ መሳሪያች ሁሉ በኔ ልብ ውስጥ ድፍረቴን ከማጋጋልና ወኔዬን ከማነቃቃት በስተቀር ከቶ ፍንክች አያደርጉኝም ። እንዲያውም እነዚህን የነጐድጓድ መሳሪያች ከሰማሁበት ጊዜ ጀምሮ የቱን ያህል አደገኛና ቀሰፊ ቢሆኑም አጠገባቸው ደርሼ ለመግጠም ያለኝ ፍላጐት በመገንፈሉ የተነሳ ገና ቅድም ልቤ መግሸቶ ወጥቶ ደረቴ ላይ ደርሷል ። ስለዚህ የሮንዜናንቴን ቅናት በደንብ አጥብቅልኝና እስከ ሶስት ቀን ድረስ እዚሁ ሆነህ ስትጠብቀኝ ቆይ ። እውነትና ትክክለኛነት ካንተ ጋር ይሁን ። ምናልባት ሰውና እንጨት ተሰባሪ በመሆኑ በዚህ በሶስት ቀን ውስጥ ተመልሼ ሳልመጣ በዚያው ቀልጬ የቀረሁ እንደሆነ አንተ በመሞቴ ቁርጠኛ ሆነህ ወደ መንደራችን ለመመለስ ትችላለህ ። እዚያም እንደደረስህ ሳትውልና ሳታድር ወደ ቶቦዞ ተሸግረህ ለእመቤቴ ለወደር የለሽ ዱልቺኒያ ባሪያዎ ፈረሰኛ የማንቻው

ዶን ኪሾት የኔ ነው ተብሎ ለመጠራት የሚያበቃውን እጅግ ከፍ ያለ የጀግንነት ተግባር ሲፈጽም ሞተ ብለህ እንድትለ ረዳት አደራዬን ጥዬብሃለሁ አለው ።»

ሳንቾ ይህን የኑዛዜ ቃል ከጌታው እንደበት በሰማ ጊዜ እንደተቆረጠች በለስ እንባው እየረገፈ ተንሰቅስቆ ያለቅስ ጀመር ። ወዲያውም ቀጠለና እንዲህ ሲል ምክር አቀረበ ።

«ተወዳጁ ጌታዬ ሆይ ! መቼም ከዚህ እጅግ አደገኛ ከሆነው ጥሞሪያ ውስጥ በሕይወት ተርፎ መመለስ በፍጹም ተስፋ የሌለው ነገር ስለሆነ ክቡርነትዎ እስከዚህ ድረስ ጨክነው ለመጋጠም የፈለጉበት ምክንያት ከቶ ሊገባኝ አልቻለም ። እንደሚያዩት ወቅቱ መንፈቀ ሌሊት ነው ። ከሁለታችን በስተቀር ገበናችንን ዓይቶ የሚታዘበን ሰው ባጠገባችን የለም ። ምንም እንኳ ውሀ ሳንጠጣ ሶስት ቀን ያለፈን ብንሆን ያላንዳች መሣደርደር በቀጥታ በሌላ መንገድ አሳብረን ከዚህ አደጋ ለመራቅ እንችላለን ። እንደነገርክዎት ባሁኑ ሰዓት ማንም ሰው ስለማያየን ፈርጣጮች ብሎ ሊሰድበን አይችልም ። ይልቁንም ደግሞ እርስዎ በጣም የሚያውቋቸው የመንደራችን ቄስ አባ ጴጥሮስ ሲሰበኩ የሰማኋቸውን እንደማስታውሰው » አደጋን የሚፈልግ በዚያው ቀልጠ ይቀራል » ብለዋልና እርስዎም ይህን የቄሱን እውነተኛ ስብከት የሚያምኑ ከሆኑ ይህን ከመሰለው በተአምር ካልሆነ በስተቀር ሊዳንበት ከማይቻለው አቅላጭ አደጋ ውስጥ በገዛ እጅዎ ተሰንቅረው በእውነት ሌላ ሊያማርሩ አይገባዎትም ። ባለፈው ጊዜ እንደኔ በብርድ ልብስ ከመራገብ የጠበቅዎትንና እንዲሁም እነዚያን የሙት አጀቢዎችን የመሰሉ ብዙ ጠላቶች ብቻዎን ገጥመው አንዳች ጥቃት ሳያገኝዎት ድል እንዲያደርጉ የረዳዎትንና ቀኑንም የሰጠዎትን አምላክ የቸርነቱን ስፋት አመስግነው አርፈው ቢቀመጡ አይሻልዎትምን ? ዳሩ ግን ይህ ሁሉ ምክሬ ይህን የብረት ልብዎን ለማላሳትና ችኩላዎን ለማስታገሥ የማይቻል ሆኖ ከተገኘ ክቡርነትዎ ከዚህ እንደራቁ ወዲያውኑ ነፍሴን ሊወስዳት ለሚፈልገው ለማናቸውም ፍጥረት ያለክር ክር ለመስጠት የተዘጋጀሁ መሆኔን አውቀው በዚህም ምክን ያት የሚደርስብኝ ጭንቀት የቱን ያህል የከበደ መሆኑን አስ

በው ይዘኑልኝ ። እኔ ሚስቴንና ልጆቼን በትኜ ክቡርነትዎን በጋሻ ጃግሬነት ተከትዬ ለማገልገል ቆርጬ ከአገሬ የወጣሁት ቀድሞ ከነበርኩበት ሁኔታዬ ጥቂት ከፍ ለማለትና እንደሚያልፍልኝም ተስፋ በማድረግ ነው እንጂ የባሰ አደጋ ላይ ለመውደቅ አል ነበረም ። መቼም ብዙ የሚፈልግ ሰው ምንም አያገኝም ተብ ሏልና እኔም በዚሁ መጠን ተስፋዬንም ጭምር ለማጣት በቃሁ። ምክንያቱም ያቺን ተስፋ ያደረጉልኝን የተረገመች ደሴት ለመ ቀበል አጠገቧ የደረስኩ ሲመስለኝ እነሆ ይኸው አፍራሻውን ለአገልግሎቴ ዋጋ አድርገው ሊከፍሉኝ የተሰናዱት ሚናቸውም የሰብአዊ ማኅበር እርዳታ ሊገኝ በማይችልበትና እሪታዬንም ሁሉ ነፋስ በልቶት በሚቀርበት እጅግ ተናጠል በሆነ ዱር ውስጥ ብቻዬን ትተውኝ ክቡርነትዎ ወደ ሞት መሄድዎ ሆነ ። የተከ በሩት ጌታዬ ሆይ ! ስለ እውነኛው ብለው እንዲህ ያለ ክፉ በደል አይበድሉኝ ። ምንአልባት እንኳ ይህን ግጥሚያ ከማድ ረግ በፍጹም ለመታገድ የማይችሉ ሆነው ቢገኙ በዛሬው ሌሊት መሆኑ ቀርቶ ለነገ ጠዋት ያስተላልፉት ። በኔ በእረኛው ሂሳ ብና አገማመት እንኳ ወደ ጐሕ ለመድረስ ከሶስት ሰዓት ይበ ልጥ የሚርቅ አይመስለኝም ። ይህንንም የምለው አጥቢያው ኮከብ በእናታችን አቅጣጫ በግራ ክንድ መስመር ሲታይ መንፈቀ ሌሊት መሆኑን ስለማውቅ ነው » አለ ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል ጠየቀው «ለመሆኑ እንዴት አድርገህ ነው ይህን አጥቢያና ይህን መስመር ፥ ይህን ክንድ ለማወቅ የቻልከው ? ሌሊቱ በጣም የጨለመ በመሆኑ በመላው ሰማይ ላይ እንዲት ኮከብ እንኳ አትታይም» አለው ።

«እርስዎ ያሉት እርግጥ ነው ።» ሲል መለሰ ሳንቾ ። ዳሩ ግን ፍርሃት የሚባለው መቶ ዓይኖች ያሉት ስለሆነ ማናቸውንም ነገር ከመሬት ውስጥ የተቀበረውንም ጭምር ጠልቆ ለማየት ሲችል በጠራው ሰማይ ላይ ደግሞ ይበልጥ እንደሚያይ ጥርጥር የለበትም ። ከዚህም በስተቀር ደግሞ በዓይን ጭፍን ቢገመትም እንኳ ካለሁን አንስቶ እስከ ንጋት ድረስ የሚቀረው ጥቂት ሰዓት መሆኑን በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል» አለው ።

«ለመንጋት የሚቀረውን ያህል ቢቀርም «አለ ዶን ኪሾት» ዛሬም ሆነ ምንጊዜም እንባ እያፈሰሱ መለመንና መለማመጥ፣ መውትወት የዙዋሪ የፈረሰኛነት ግዳጁን ከማከናወን ያስተን ጉለኛል ብሎ በኔ ላይ ተስፋ ማድረግ ከንቱ ነገር ነው። ይል ቁንስ ሳንቾ ለማልበገርበት ጉዳይ ማልቀሱን ተወውና እረጋ በል፣ ሴት ይመስል አትነዝንዝኝ፣ በተለይ የምለምንህ ዝም እንድትለኝ ብቻ ነው። ይህን ምንግዜም ያልታየና አስፈሪ የሆነ ግዮሚያ እንድአከናውን ግዴታውን በልቤ ውስጥ ያሳደረው አውነት እኔን ከአደጋው ለማዳንና ያንተንም ጭንቀት ለማጽ ናናት ያስብበታል። ስለዚህ የሮንዝናንቴን ቅናት አጥብቅል ኝና እዚሁ ቆየኝ። እኔ ቆሚም ሆነ ሞቼ በፍጥነት እመለሳለሁ» አለው።

ሳንቾ ከጌታው የተሰጠው መልስ የመጨረሻ ቁርጥ ቃል መሆኑን በማመን፣ ልቅሶውም ምክሩም ልመናውም ለምንም እንዳልጠቀመው በመረዳት፣ በሌላ የተንኮል ዘዴ ሊያስገድ ደው አሰበ። ይህም ዘዴ የሚያዋጣው ቢሆን ዓለማው እስኪ ነጋ ድረስ ጌታውን ከአጠገቡ እንዳይርቅበት ለማድረግ ነበርና በዚህ ቁርጥ ሐሳብ ውሳኔ ካደረገ በኋላ ወደ ፈረሱ ተጠግቶ ዝቅ ብሎ ቅናቱን የሚያጠብቅ በመምሰል ምንም ሳያስማና ሳይታ ወቅበት በአህያይቱ ሰካ የሮንዝናንቴን ሁለት እግሮች አጥብቆ አሰረው። ዶን ኪሾትም ለመሄድ በሚነክርበት ጊዜ ፈረሱ እየተፈራገጠ ሽቅብ ከመዘለል በስተቀር ሊራመድለት አልቻ ለም ነበር። ሳንቾም ያጠመደው ተንኮል እንደያዘለት አወቀና እንዲህ አለ።

«አዩት የእኔ ጌታ የሰውን ልብ ርህሩህነትና የሰውን ልበ ደንዳናነት ለቅሶዬና ልመናዬ ሰርስዎ አልሰማ ቢል በእውነት ኃይል ተንበርክቆ እነሆ የሮንዝናንቴን እግር ሰነከለው። ከእንግዲህ ወዲያ ከቡርነትዎ ወርደው በእግርዎ ካልሄዱ በስተቀር ፈረሱ ይሄድልኛል ብለው እንስሳውን በኃይል ቢኰረኩሩት ዕድልዎን እንደማታከትና ግድግዳ እንደመኰርኮር የሚቆጠር ስለሆነ በክ ንቱ አይድከሙ» አለው።

ዶን ኪሾትም በዚህ ስውር በሆነ መታገድ ክፉኛ ተበሳ ጭቶ ፈረሱን ከቀድሞው ይበልጥ አከታትሎ ቢኮረኩረው የመ ነቃነቁ ኃይል ይበልጥ እየቀነሰ ይሄድ ጀመር። እግሩ የታሠረ መሆኑን ባለማወቁ የተነሳ ይህ ብርቱ መታገድ የመጣው በሳ ንቾ መሠሪነት ሳይሆን ከፍጡር በላይ በሆነ ሥልጣን ተዳኝቶ መሆኑን ስለአመነ ሴሊቱ እስቲነጋ ድረስ ወይም ደግሞ ሮንዜናንቴ ዛሩ ገለል ብሎለት ለመነቃነቅ እስቲሞክር ድረስ ታግሶ ለመጠ በቅ ከወሰነ በኋላ እንዲህ አለ።

«እንግዲህ ሳንቾ እንደምታየው ሁሉ ሮንዜናንቴ በፍጹም ለመነቃነቅ አልቻለም። ስለዚህ ምንም እንኳ ወደ አደጋው ቦታ ደርሼ ለመጋፈጥ ባለመቻሌ የተነሳ እስቲነጋ ድረስ መጠ በቅ ግዴታ ቢሆንብኝ እስከዚያው ድረስ እዚሁ ተገትሬ በክ ንቴ የማሳልፈው ጊዜ ሁሉ እያንገበገበ እንደሚቆጨኝ ይሰ ማኛል።

«አይዝዎት የኔ ጌታ አይበሳጩ» አለ ሳንቾ። «እኔ እንዳ ይቆጭዎት አድርጌ በዘዴ አጽናናዎታለሁ። መቸም እንደዶንቡ ሌሊቱ ነግቶልዎት ከዚህ ዓይኑን አፍጥጦ ከሚጠብቅዎት ታላቅ አደጋ ጋር ፊት ለፊት እየተያዩ የሚጋጠሙበት ጊዜ ሲደርስ ሕዋሳትዎ ቀደም ብሎ ጥቂት ዕረፍት አድርጐ በርትቶና ተብቶ መገኘት ይገባው ስለነበረ፣ ምንም እንኳ አስተዋዮች ዙዋሪ ፈረ ሰኞች የሚያደርጉትን በመከተል በአውኑ ሰዓት ከፈረስዎ ላይ ወርደው በዚህ በለመለመው ሣር ላይ ጋደም ለማለት ባለመ ፈለግዎ የተነሳ እንደተገተሩ የሚያነጉ ቢሆንም እኔ በበኩሌ ካውኑ ጀምሬ እስከ ነገ ጥዋት ድረስ ልዩ ልዩ ዓይነት ተረቶች እያከታተልሁ በማውራት አጫውትዎታለሁ» አለው።

«እንዴት በል? ከፈረስህ ላይ ወርደህ ተኛነው የምትለኝ?» ሲል ዶን ኪሾት በመገረም ጠየቀው፣ ንግግሩን በመቀጠል እረ ለመሆኑ ስትገምተኝ እነዚያን በተውጤ ውስጥ ተዝናንተው የሚገኙትን ዳተኛ ፈረሰኞች መስዬ ታየሀሀን? ይልቁንስ አንተ ጥንቱንም ለመተኛት የተፈጠርህ ስለሆንክ ተኛ።

ወይም ሌላ የሚያሰኝህ ነገር እንዳል አድርግ ፥ እኔ ግን ለተግባሬ የተገባውን ግዳጅ ከመፈጸም የሚያሰናክለኝ አንዳች ነገር ሊኖር እንደማይችል እወቀው » አለው

ሳንቾም መለሰ «ጌታዬ ሆይ ! አይቆጡ የተናገርኩት ለማ ለት ያህል ነው እንጂ እውነትስ የኔን ሃሳብ ይቀበላሉ ብዬ አይደለም » አለው ።

ከዚህ በኋላ ወደ ዶን ኪሾት ተጠጋና ባንድ እጁ ቀዳማ ውን ፥ በሌላኛው እጁ ደሐራውን ይዞ የጌታውን የግራ ታፋ ተደግፎ ያስደንጋጩን ጉርምርምታ ማስተጋባት እየሰማ አለ መጠን ፈርቶ ነበርና ያንዲት ቅንጣት ፈቀቅታ እንኳ ሳይርቅ ቆመ ። ዶን ኪሾትም ሳንቾ በሰጠው ተስፋ መሠረት አንዳንዴ ተረት እያወራ እንዲያጫውተው ጠየቀው ።

«መልካም ፈቃዴ ነው» አለ ሳንቾ ፥ የዚህ ጉርምርምታ ማደ ንቆር የልቤ ትርታ ምላሴን ካላሠረው በስተቀር አንዳችም ቃል ሳልሳሳት ሁሉንም በትክክል ለመናገር የቻልኩ እንደሆነ ከተረ ቶች መካከል በጣም ምርጥ የሆነውን ለማውራት ቻልኩ ማለት ነው ። እንግዲህ መጀመሪ ስለሆነ ተጠንቅቀው ይስሙኝ ።

«አንድ ጊዜ የነበረው አንድ ጊዜ ነበር ፤ ለሚገባው መል ካም ነገር ይግጠመው ፤ ክፉ ነገርም በሚፈልገው ላይ ይድረ ስበት ፤ ይህን ማለቴ የዱሮ ሰዎች ተረት ሲናገሩ የሚጀምሩበ ትን ፈሊጥ ክቡርነትዎ እንዲያውቁት ብዬ ነው ። ይህም ፈሊጥ ማናቸውም ዓይነት አይደለም፤ ዳሩ ግን ከአባት ነፍጠኞች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ምሳሌ ነው። የጥንቶቹ ሮማውያን እንደሚሉት «ክ ራን ነገር ለሚፈልገው ይሰጠው ፤ ያሉት በውነቱ ባሁኑ ሰዓት ተረትነቱ ከሁኔታችን ጋር እንደ እጅ ሹራብ ልክክ ያለ ስለሆነ ክቡርነትዎ በየትኛውም ቦታ ክፉ ነገር ለመፈለግ ባይሄዱ ደስ ይለኛል ። እንዲያውም ይህን መንገድ ትተን በሌላ መንገድ ብንሄድ እመርጣለሁ ። በዚህ ባሁኑ መንገዳችን ላይ በያንዳንዱ እርምጃ ከፍርሃትና ከድንጋጤ ጋር እየተገናኘን እንድንሄድ የሚያስገ ድደን ሰው የለም» አለው ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል መለሰ «አንተ ያለብህ ተረ ትህን መቀጠል ነው እንጂ ያልተጠየቅኸውን ይህን ሁሉ ሐተታ

ማውራት አልተፈቀደልህም ። የምንሄድበትን መንገድ የመም ረጡ ጉዳይ እኔን የሚመለከት ስለሆነ እኔው አስብበታለሁ » አለው ።

«ይሁን ደግ ነው» በማለት ሳንቾ ምክሩን ተወና እንዲህ ሲል ተረቱን ቀጠለ። እንግዲህ ኢስትራማዱራ በሚባል አገር አንድ ጊዜ አንድ ፍየል አርቢ ይኖር ነበር ። ይህም ማለት ፍየሎችን የሚጠብቅ እረኛ መሆኑን ነው ። የሆነው ሆኖ የኔ ተረት እንደሚለው ሰውየው ፍየል አርቢ ወይም የፍየሎች እረኛ ቢሆንም ባይሆንም ስሙ ሎፔ ሩዌዝ ይባላል ። ይህም ሎፔ ሩዊዝ የሚባለው እረኛ ቶራልቫ የምትባለዋን እረኛ አፍቅሮ ነበር ፥ ይህችም ቶራልቫ የምትባለው እረኛ ያንድ ባለ አሩት ከብት አርቢ ልጅ ነበረች ። ይህ ባለአሩት ከብት አርቢ እዚህ ላይ ዶን ኪሾት አቋረጠው ። አንተ ተረትህን በዚህ ዓይነት ፈሊጥ አንዱን ነገር ሁለት ጊዜ እየደጋገምህ የምት አወራው ከሆንክ በሁለት ቀን እንኳ ልትጨርሰው አትችልም ማለት ነው ። ስለዚህ ሁሉንም አከታትለህ በመናገር እንደብ ልህ ሰው አድርገህ ተርተው ። አለበለዚያ ግን ብትተወው ይሻ ላል » አለው ።

«በኔ አገር» ሲል መለሰ ሳንቾ «ተረቶች ሁሉ በዚህ ዓይ ነት ፈሊጥ ነው የሚተረቱት ። እኔ በሌላ አኳኋን መተረቱን አላውቅበትም ። እንዲሁም ደግሞ ያልተለመደውን አዲስ ፈሊጥ እንድከተል መፈለግዎ የተገባ አይደለም» አለው ።

«አንተ እንደፈለግኸው አድርገህ ተርት ፤ አለ ዶን ኪሾት» «መቸም እድሌ አልሰማም እንድል አልፈቀደልኝምና በል» ቀጥል ።

«እንግዲህ የተወደዱት የነፍሴ ጌታ ሆይ! ይስሙኝና ልን ገርዎት» ሲል ቀጠለ ሳንቾ ቅድም እንዳልኩት ሁሉ ይህ እረኛ እረኛይቱን ቶራልቫን አፍቅሮ ነበር ። ይህችም እረኛ ወፍራም ረጅም ፤ ደንደሮ ፤ ኃይለኛ ፤ ስለሆነች በሁኔታዋ ከሴትነት ይልቅ ወደ ወንድነቱ ታደላ ነበር ። ይህም ሆኖ ጥቂት ሪዘች ነበራት ። ዋ ! ልክ አሁንም ባይኔ ላይ ትታየኛለች » ።

«እንግዲያውማ ታውቃታለህ ማለት ነዋ?» ሲል ጠየቀው ዶን ኪሾት ።

«የለም ማወቅስ አላውቃትም» ሲል መለሰ ሳንቾ «ዳሩ ግን ተረቱን ያወራልኝ ሰው ድርጊቱ ፍጹም እውነተኛ ነው ስላለኝ እኔም ለሌላ ሰው በማወራበት ጊዜ ሁሉንም በዓይኔ እንዳየሁት አድርጌ ለማረጋገጥ እችላለሁ ። ስለዚህ በጊዜ ብዛት መቸም ዲያብሎስ ለክፋት ሥራ የማይተኛና ጅራቱን በየቦታው የሚወትፍ በመሆኑ የእረኛውና የእረኛይቱ ፍቅር ወደ ጠብ እንዲለወጥ አደረገ ። የጠባቸውም ምክንያት አዋላቶች እንደሚሉት እሷ እጅግ የሚያንገፈግፍና ከመጠን ያለፈ ቅናት እንዲያድርበት አድርጋ ስለቀለደችበት ነው ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጠባቸው በጣም እየከረረ ስለሄደ እረኛው በተሰማው የጥላቻ ስሜት ተስፋ ቆረጠ የእሷን ዓይን ለማየት ወደማይችልበት አገር ለመጥፋት ወሰነ ። ቶራልቫ ግን ሎፒዝ አንቅሮ እንደተፋት አወቀችና ከዚህን ቀን በፊት ችላ ትለው የነበረችውን እንደገና የሱ ፍቅር ገነነባት ።

«ሴቶች ሲባሉ በሙሉ ጠባያቸው ይሽው ነው» አለ ዶን ኪሾት «የሚያፈቅራቸውን ይጠሉና የሚጠላቸውን ያፈቅራሉ ጠባያቸው ባካና ስለሆነ አይፈረድባቸውም» በል ቀጥል ሳንቾ ።

ሳንቾም ቀጠለ «በዚህም ምክንያት እረኛው ቁርጥ ሃሳቡን በገቢር ላይ ለማዋል ሲል ፍየሎቹን ሰበሰበና እየነዳ የኤስትራ ማዱራን ሜዳ አቋርጦ ወደ ፖርቱጋል ግዛት ለመግባት ተሰደደ ። ቶራልቫም ይህን ነገር በማወቋ ምርኩዝ ከዘራዋን ይዛ ጫማ ሳታደርግ ሻንጣዋን አዝላ በዚህም ሻንጣ ውስጥ አንድ ስባራ መስታወትና ግማሽ ሚዶ ፣ የጉንጭ ቀለም የያዘ መዳይ ነበረበት ። ዳሩ ግን በውስጡ ያፈቀደው ዕቃ ቢኖርበትም ይህን ሁሉ ዝርዝር ለመተንተን ጊዜ ስለማላገኝ ዋና ዋናውን ብቻ አወራለሁ ። በዚህ አኳኋን እረኛው መንገዱን ሲቀጥል እሷም ዱካውን ይዛ ስትከተለው ከነመንጋዎቹ ጓዲያና ጅረት ደረሰ ። ይህም ጅረት በዚያን ወቅት አለመጠን ሞልቶ ከመውረጁው መልካ ተርፎ ፈረሰኛው ሲያናጥር ይታይ ነበርና በዚያን ጊዜ

በደረሰበት ዳርቻ እሱንና ፍየሎቹን ወዲያ ማዶ ለማሻገር የሚችል ታንኳ ሆነ ጀልባ ጀልበኛም ስላልነበረ በጣም ተበሳጨ ። ምክንያቱም ቶራልቫ ተከታትላው መምጣቷንና ልትደርስበትም ምን ያህል እንዳልቀራት በማወቁና እንዲሁም የደረሰችበት እንደሆነ በልመና በለቅሶ እንደምታስቸግረው በማመኑ ነው ። በዚህ ሥጋት ላይ ሆኖ የጅረቱን ዳር ለዳር ሲቃኝ እነሆ አንድ አሳ አጥማጅ አንዲት ታንኳ ላይ ተቀምጦ ሲቀዝፍ አየው ። ይህችም ታንኳ በጣም ትንሽ በመሆኗ ለአንድ ሰውና ለአንድ ፍየል የሚሆን ቦታ በስተቀር ትርፍ ለመያዝ አትችልም ነበር ። የሆነው ሆኖ የማይቀር ነገር ስለሆነበት ሦስት መቶ ፍየሎችና እሱን ጭምር በተራ እንዲያሻግርለት ከባለታንኳው ጋር ተዋውሎ ተከራየ ። ከዚህ በኋላ ባለታንኳው በታንኳው ውስጥ ገብቶ አንድ ፍየል አሳፍሮ አሻገረ ፤ ከዚያም ተመልሶ ሁለተኛዋን ፍየል አሻገረ ፤ እንደገና ደግሞ ተመለሰና ሶስተኛዋን አሻገረ ፤ እንግዲህ እዚህ ላይ ጌታዬ ከአሁኑ ጀምረው ይጠንቀቁና አሳ አጥማጁ ተራ በተራ የሚያሻግራቸውን ፍየሎች ሁሉ አንድ ባንድ እየቆጠሩ ሂሣቡን አስታውሰው እንዳይዙ ። ይህንንም ማለቴ ከአቆጣጠር ላይ ተሳስተው አንዲት ፍየል ቢያበልጡ ወይም ቢያሳንሱ ተረቱ ተፈጸመ ማለት ነው ። ምክንያቱም በኔ በኩል ቁጥራቸው በትክክል ካልተነገረኝ በስተቀር አንዲት ቃል እንኳ ጨምሬ ለመቀጠል የማልችል በመሆኔ ነው ።

«እነሆ እንግዲህ ምን ብዬ ነበር ፤ ከጅረቱ ወዲያ ማዶ ያለው የፍየሎች መራገፊያ ዳርቻ በጣም አረንቋና ጥቅ የሞላበት ስለሆነ አሳ አጥማጁ ፍየል ባሻገረ ቁጥር ከታንኳው ላይ አውርዶ በጫንቃው ተሸክሞ ከደረቅ ሥፍራ ለማድረስ በጣጡ ውስጥ ሲዳክር ውሎ አድሮ እስኪመሰስ ድረስ ጊዜ እየፈጀበት ይዘገይ ነበር ። ይህም ሆኖ አንድ ፍየል አድርሶ ተመለሰና እንደገና አንድ ፍየል አሻገረ ፤ ቀጥሎም አንድ ደገመ አሁንም አንድ ጨመረ.....»

ዶን ኪሾት በሽቀና እንዲህ ሲል አቋረጠው ፤ «ስማኝ ሳንቾ በዚህ አኳኋን መሄድህንና መመላለስህን ተወውና ፍየሎቹን ሁሉ ጠራርጎ አሻገራቸው ብለህ ንገረኝ ። አለበለዚያ ግን በመሄድና

በመመለስ የምትቀጥል የሆንክ እንደሆነ ተረትህን ለመጨረስ አንድ ዓመት ሙሉ ብትመላለስም ላይበቃህ ነው» አለው ።

«እረ ለመሆኑ እስካሁን ድረስ ምን ያህል ፍየሎች ወዲያ ማዶ እንደተሻገሩ እስተ: ይበሉ የቆጠሩትን ይንገሩኝ?» ሲል ጠየቀ ሳንቾ ።

«እንጃልህ ምን አውቅልሃለሁ» ሲል መለሰለት ዶን ኪሾት ።

«ይህም ሆኖ » አለ ሳንቾ «የተሻገሩትን ፍየሎች ተጠን ቅቀው ይቁጠሩ ብዬ ነግሬዎት ነበር ፤ እንግዲህ አሁን ተረቴ ስለአከተመ በማናቸውም አኳኋን ቢሆን ወደፊት ለመቀጠል አልቻልኩም» ።

«ምን ማለትህ ነው» አለ ዶን ኪሾት «ተራ በተራ የተሻገሩትን ፍየሎች ቁጥር በትክክል ማወቅ ይህን ያህል ለተረትህ መቀጠል እስፈላጊ ነውን? አንድ ፍየል እንኳ ቢሳሳት ተረቴ ላይቀጥል ነውን ?»

«አዎን በርግጥ እንዲሁ ነው» አለ ሳንቾ ምክንያቱም እኔ ምን ያህል ፍየሎች እንደተሻገሩ ይንገሩኝ ብዬ በጠየቅሁዎት ጊዜ እርስዎ ደግሞ እንጃልህ አላውቅም ብለው ሲመልሱልኝ ልክ በዚያኑ ሰዓት ወደፊት የቀረው ተረት ሁሉ ባንድ አፍታ ከት ውስታዬ ውስጥ እልም ብሎ ሲጠፋ ተሰማኝ ። ይህም ተቋርጦ የቀረው ተረት በእውነቱ በጣም አስቂኝና በጣምም ተፈላጊው ክፍል እንደነበረ አረጋግጥልዎታለሁ ።

«ያም ሆነ ይህ» ተረትህ ተፈጸመ ማለት ነዋ ፤ ሲል ዶን ኪሾት ጠየቀው ።

«አዎን እንዳልታደለችው እናቴ ሞት ተፈጽሟል ። አለው ሳንቾ ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል መለሰለት «ይህ እስካሁን ድረስ የዘባረቅኸው ተረት ወይም ታሪክ ምን እንደምትለው እንጃ ልህ በዚህ ዓለም ላይ ምንጊዜም ታስቦ የማይታወቅ በጣም አሪ

ታዊ በመሆኑ በዚህ ዓይነት ፈሊጥ ማውራትን ጀምሮ ወዲያው ደግሞ ከወገቡ ላይ እድርሶ ተቋረጠ ማለት ከቶ ተሰምቶና ታይቶ የማይታወቅ ወደፊትም ሊሰማና ሊታይ የማይችል መሆኑን አረጋግጥልሃለሁ ።

ምንም እንኳ ባንጐልህ ውስጥ ካለው ዕውቀት ከዚህ የተሻለ ፍሬ ነገር ይገኝበታል ብዬ መጠባበቅ ባይገባኝም ቅሉ ይህ መላቢስ የሆነው አተራረትህ ሊያስደንቀኝ አይችልም ። ምክን ያቱም ምናልባት እነዚህ ያለማቋረጥ የሚደውሉት አደንንቋሪ ድምጾች አንጐልህን አቃውሰውት ይሆናልና ነው ።

«ይህም ያሉት ሊሆን ይችላል» ሲል መለሰ ሳንቾ «ዳሩ ግን በተረቴ ጉዳይ ላይ ከእንግዲህ ወዲህ ልናገረው የምችለው አን ዳች ነገር እንደሌለ አውቄዋለሁ ። ምክንያቱም የተሻገሩት ፍየ ሎች ቁጥር በተሳሳተ ጊዜ ልክ እዚያው ነጥብ ላይ ተጐርዶ የሚያልቅ ስለሆነ ነው» አለው ።

«ሳንተ እንደመሰለህና እፈለግኸው ቦታ ላይ ብትጨርሰውም የተረትህ መቋረጥ እኔን አላስቸገረኝም ። ይልቁንስ ያንተን ትቼ እስ ቲሮንዚናንቴ ለመንቀሳቀስ ይችል እንደሆነ ልሞክር» ካለ በኋላ እንደገና ሮንዚናንቴን ኩርኩሮ ለማንቀሳቀስ ሞከረ ፤ ዳሩ ግን ፈረሱ የታሠረው በደንብ ተጠፍሮ ነበርና ኩርኩራው ሲሰ ማው አንድ ጊዜ ሽቅብ ዘለለና ተመልሶ እንደቀድሞው ቆመ ።

ይህም በሚሆንበት ጊዜ ወቅቱ ወደ ንጋቱ ስለተቃረበ የማ ልዳው ቅዝቃዜ ስሜት ይሁን ወይም እራት ላይ ሆድ የሚያ ለስልስ ምግብ በልቶ ይሆን ወይም ደግሞ የተፈጥሮ ፍላጐት አጣድፎት ይሆን (ይበልጥ የሚታመነው ይኸኛው ነውና) ያም ሆነ ይህ ሆዳባሻው ሳንቾ ሴላ ዘመድ ወይም ወዳጅ ስለ ርሱ ተወክሎ ሊፈጽምለት የማይችለው ጉዳይ መጣበት ። መቼም ወደሥራ አካላቱ የገባው ፍርሃት እጅግ የበረታ በመሆኑ ከጌታው ጐን ያንዲት ጣት ማሳረፊያ እርቀት ያህል እንኳ አልተነጠ ለም ነበርና በዚህ ምክንያት ጉዳዩን ለመፈጸም ሲል እስከዚ ያን ሰዓት ድረስ የያዘበትን የቀኝ እጁን ከቀዳማው ላይ አው ርዶ አንዳች ኩሽታ ሳያሰማ በቀስታ እጁን ሰድዶ ሱሪውን የታ ጠቀበትን የጥብጣብ ሽምቀቆ ከሚላላት በስተቀር ከዚህ የተ

ሻለ ሌላ ብልሃት ሊያገኝ አልቻለም ። ሱሪውም ሌላ የሚተዘ ተብ ማሰሪያ የሌለው በመሆኑ ወዲያውኑ ላልቶ ቁልቁል ወረ ደለትና እንደ እግረ ሙቅ እግሩ ላይ አረፈ ። ቀጥሎም የተቻ ለውን ያህል ሸሚዙን ከፍ ከፍ አደረገና ቁጢጥ ለማለት ዝቅ ሲል ሁለት ጥንድ የጦላ ላጥታ ወደ አየር ተኮሰ ። በዚህም ጊዜ ከሥጋት ለመገላገል ያህል የመጀመሪያው ዋናው አዋጅ ነጋሪ በመውጣቱ የተገላገለ ሊመስለው እነሆ ደግሞ ሌላ የባሰ ጣጣ ተከታትሎ ደረሰ ። ይኸውም ዕቃው የሚራገፍበትን መን ገድ ያለ ጓጓታ ለማለፍ አለመቻሉን ስለአወቀው ጥርሱን ነከሰ። ትክሻውንም ገጠመ ፤ የተቻለውን ያህል ትንፋሹን ዋጠ ። ዳሩ ግን ይህን ሁሉ ጥንቃቄና ጭንቀት ቢያደርግም ቅሉ ዕድል አሳገዘውም ነበር ። ምክንያቱም በመጨረሻው ውጤት ከበድ ያለ ድዝታ አምልጠ ወጣ ፤ ይኸው በሰውነቱ ውስጥ ታላቅ ፍርሃት ካሳደረበት የጉርምርምታ ድምጽ ጋር በምኑም የማ ይመሳሰል ነበር ።

ዶን ኪሾት ይህንኑ ድምጽ በሰማ ጊዜ እንዲህ ሲል ጠየ ቀው ፣ «ሳንቾ ይህ የሚተኩሰው የምን ድዝታ ነው?» አለው ።

ያም መለሰ «ጌታዬ ሆይ ! በውነቱ ምን እንደሆነ አላወ ቅሁትም ። ዳሩ ግን አንዳች አዲስ ነገር በእርግጥ መኖር አለ በት ። ከዚህም በስተቀር አጋጣሚና አደጋ መዝነላ በሚጀም ርበት ጊዜ በእንቅርት ላይ ጀሮ ደግፍን ያስከትላል» አለውና እንደገና እድሱን ሞከረ ፤ ፈተና አደረገ ። በዚህም ጊዜ አገፋፉ ላይ ስለቀናው እንደበፊቱ ድዝታ ሳያሰማ በጣም ወጥሮ ያስጨነቀውን ጭንት አራግፎ ነፃ ለመሆን ቻለ ። ዶን ኪሾት ግን በጀሮው ከሰማው ይልቅ ባፍንጫው ያሸተተው ማጠንት ምንነቱን ይበልጥ ስለአሳመነውና ያኛውም አጠባቡ ተለጥፎና ተሰፍቶ የሚገኝ በመሆኑ ከታች ወደ ላይ የሚነሳው የትኩስ ጢስ ብናኝ አንዳች ነገር ሳያግደው በቀጥታው መስመር ወደ አፍንጫው ያርሶ ስለአጠነው በቶሎ አፍንጫውን በጣቱ ያዘና በመነፋነፍ እንዲህ ሲል ጠየቀው።

«ሳንቾ እንደምሰማው አለመጠን የፈራህ ይመስለኛል?» አለው ።

«አዎን መፍራትስ በጣም ፈርቻለሁ ፤ ለመሆኑ እርስዎስ ከቅድሙ ይልቅ አሁን መፍራቴን እንደምን አድርገው ተረዱት» ሲል ጠየቀ ።

«ከቅድሙ ይልቅ አሁን የምታሰማው ሽታ በውነቱ የቢ ርሞኬ አይደለም ? ።

«ላይሆንም ይችላል» ሲል መለሰ ሳንቾ «ዳሩ ግን ጥፋቱ የኔ አይደለም ፤ በዚህ በበረሃ ቀበሌ ውስጥ ጊዜ አለጊዜ አስ ከትለው የሚያንከራትቱኝ እርስዎ በመሆንዎ ጥፋቱ የርስዎ መሆን አለበት » አለው ።

«እባክህን ወዳጄ ወግድልኝ ከዚህ» አለ ዶን ኪሾት ፤ ጣቱን ከአፍንጫው ላይ ሳያነሳ «ከአጠገቤ ሦስት ወይም አራት እር ምጃ ያህል ፈቀቅ ብለህ ጉዳይህን ፈጽም ። ከዛሬ ጀምረህ ወደ ፊት ደንበኛውን ቦታህን ፈልገህ ያዝ ። ለኔም የሚገባኝን የክ በሬታ አሰተያየት አድርግልኝ ። ይህ የአክብሮት መጓደል ካንተ ጋር ዘወትር በጓደኝነት መንፈስ እየተናገርሁ ፊት በመስጠቴ የተ ገኘ ፍሬ ነው» አለው ።

«አሁን» ሲል መለሰ ሳንቾ «እኔ ማድረግ የማይገባኝን ነገር ያደረግሁ እንደመሰለዎት ተረድቼዋለሁ» አለው ።

«አፍህን አሳርፍና ፈቀቅ በል ! አለበለዚያ ወዮልህ አለው ዶን ኪሾት ።

ይህንንና ይህን የመሰለውን ንትርክ እየተነታረኩ ጌታና አሽከር እንደተጋሰሱ ሴሊቱን አዋገዱት ።

ዳሩ ግን ሳንቾ ሌሊቱ ሊነጋ መቃረቡን ተመለከተና በፍጥነት የሮንዘናንቴን እሥር ፈትቶ የራሱንም ሱሪ ታጠቀ ። ሮንዘና ንቴም የእግሮቹ ነፃ መሆን በተሰማው ጊዜ ምንም እንኳ በተ ፈጥሮው ፎሌ ባይሆን እግሩን ለማፍታታት ያህል ጥቂት ፈነ ጫጨ ። ይህም ሲባል ደንገላሳ አይደለም ምክንያቱም እሱን ለማኳሰስ ሳይሆን ደንገላሳ የሚባል ነገር ጨርሶ የማያውቅ በመ ሆኑ ነው ። ዶን ኪሾትም ሮንዘናንቴ መነቃነቁን እየና ይህን

ከፊቱ እያጉረመረመ የሚዝትበትን አደጋ ለመግጠም የሚያ በረተታ ምልክት መሆኑን ተረዳው ።

በዚህን ጊዜ ጀንበር ጮራዋን መፈንጠቅ ስለጀመረች እነሱም በዙሪያቸው የከበባቸውን ነገር በግልጥ ለማየት ቻሉ ። እዚህ ላይ ዶን ኪሾት በጣም የከበደ ጥላ ያላቸው የብር ብራና የሰሰ ዛፎች ሥር የሚገኝ መሆኑን አወቀ ። ዳሩ ግን የፏፏቴው ጉርምርምታ አውንም ፀጥ አለማለቱን ሰማ ። ምክ ንያቱም ምን እንደሆነ ሊገባው አልቻለም ነበር ። ስለዚህም ያላንዳች ዝግያቴ ለሮንዜናንቴ ኩርኩራ አሰማውና ከሳንቾም ጋር እንደገና ተሰነባበተና ካሁን ቀደም እንዳስታወቀው ግፋ ቢል እስከ ሦስት ቀን ድረስ እዚሁ እንዲጠብቀው ነገረው ። ከሦስት ቀንም በኋላ ያልተመለሰ እንደሆነ ግን በዚህ አደገኛ መጋፈጥ ላይ ሕይወቱን እንዲያሳልፍ በተፈጥሮ የተወሰነ መሆ ኑን እንዲያረጋግጥ አሰረዳው ። እንዲሁም በርሱ ስም ሆኖ ለእ መቤት ሆይ ዱልቼኒያ ሊያደርስ የሚገባውን መልዕክት ደጋ ግሞ አሰጠነቀቀው ። ስለውዝፍ ደመወዙም ጉዳይ በፍጹም እን ዳያስብ ተሰፋ ሰጠው ። ምክንያቱም ከአገሩ ከመውጣቱ በፊት ባደረገው ኑዛዜ ላይ በተጻፈው መሠረት በጋሻ ጃግሬነት አገ ልግሎት ላይ በሚቆይበት ጊዜ መጠን ታስቦ የሚደርሰው ድርሻ አንድም ነገር ሳይቀርበት የሚከፈለው መሆኑን የምነት ቃሉን ሰጠው ። ምናልባት ደግሞ እግዚአብሔር በሠፊው ምሕረቱ ከዚህ ከብርቱ አደጋ አትርፎ በሰላምና በሕይወት የመለሰው እንደሆነ ከብዙ ጊዜ አንስቶ ተስፋ የሰጠው ደሴት አውንም ቢሆን ያላንዳች ጥርጥር የራሱ ገንዘብ መሆኑን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ እርግጠኛ እንዲሆን ነገረው ።

ሳንቾም ይህን ልብ የሚቀሰቅስ (የደንቆን) ጌታ ንግግር በሰማ ጊዜ ሃዘን ስለአንሰፈሰፈው እንደገና በለቅሶ እየተንሰቀ ሰቀ እርሱም በበኩሉ በዚህ አደገኛ ግጥሚያ ላይ ለመገኘትና እስከመጨረሻው ወሰን ድረስ ጌታውን ተከትሎ አብሮ ለመ ሞት ቁርጥ ሃሳብ ማድረጉን ገለጠለት ።

ሆኖም የዚህ እውነተኛ ታሪክ ደራሲ ይህን አስተያየት በማ ስተባበል ይህ የሳንቾ ለቅሶና አብሮ የመሞት ቁርጥ ሃሳብ ሊሆን

የቻለው ከመልካም ቤተሰብ ተወልዶ ያደገ በመሆኑ ወይም ደግሞ ከመሠረቱ የሐቀኛ ልጅ በመሆኑ በርህራሄ ስሜት ተገፋፍቶ ነው እንጂ በቀጥታ ከደፍረት መንፈስ የመጣ ቁርጥ ሐሳብ አይ ደለም በማለት ተከራክሯል ። ስለዚህ ይኸው ያልተጣራው የር ህራሄ ስሜቱ የዶን ኪሾትን ልብ ሊያገራው ቢችልም ተግባሩን የሚያስተው አንዳች ማመንታትና የሃሳብ ገመምተኛነት ዝን ባሌ እንዲፈጠርበት ለማድረግ አልቻልም ነበር ። እንዲያውም አፍራሻውን የደፋርነት ወኔውን የተቻለውን ያህል አነቃቅቶ የውሀው ድንፋታና የመውቀሪያው አስተጋቢ ድምጽ የሚመጣ መስሎ በተሰማው አኳያ አመራ ። ሳንቾም እንደወትሮው ልማዱ ያቺን የክፉም ሆነ የደግ እድሉ ተካፋይና የልብ ጥብቅ ጓደ ኛው የሆነችውን አህያውን በሉከዋ እየሳበ በስተኋላው ተከ ትሎ በንዚያ ብርበራ ዛፎች መካከል አቋርጠው ደህና ርቀት መንገድ ከሄዱ በኋላ ረዘም ወዳለ ቋጥኝ የሚዘረጋ መስክ ላይ ደረሱ ። በቋጥኙም አናቃ መካከል ከየመመንጫው ፉካ ውስጥ ከመጠን ያለፈ ይዘታ እየተፋ የሚወጣውን ፏፏቴ አዩ ። ከቋ ጥኙም ግርጌ ካንድ ደልዳላ ሥፍራ ላይ አንድ የወለለቀ አሮጌ ቤት አገኙ ። ይህም ቤት ከቤትነት ይልቅ በውነቱ የጥንት ፍራሽ የሚመስል ነበር ። እዚያም አጠገብ እንደደረሱ የማያባራው ወቃሪ ድምጽ የሚወጣው ከዚያው ከቤቱ ውስጥ መሆኑን ለማ ወቅ ቻሉ ። ሮንዜናንቴም የፏፏቴውን መንቧቸትና የወቃሪውን ድምጽ ማደንቆር በሰማ ጊዜ ፉር እያለ ደንብሮ ቆመ ።

ዶን ኪሾትም ፈረሱን በተቻለው መጠን እያባበለ ቀስ በቀስ እያለ ወደ አሮጌው ቤት ቀረበ ፣ ከዚያም በኋላ ከዚህ እጅግ አስፈሪ ከሆነው አደጋ በድል አድራጊነትና በሕይወት እንዲመለስ የእ መቤቱን የዱልቼንያን ውቃቢ በሙሉ ልቡ ተለማመነና እግረ መንገዱንም ውለታውን እንዳይረሳው ተግጠና በቁርጠኝነት መንፈስ ወደፊት ቀጠለ ። ሳንቾም ከአጠገቡ አልተነጠለም ነበ ርና አልፎ አልፎ የተቻለውን ያህል አንገቱንና አስተያየቱን እያስረዘመ በሮንዜናንቴ እግር መካከል አሸጋግሮ በመመልከት ይህን ያህል ታሳቅ ፍርሃት በሆዱ ውስጥ ለማሳደር የቻለውና አሰጨንቆም የያዘው ድብልቅልቅ ያለ ጩኸት ምናልባት ሊከ ሰትለት ይችል እንደሆነ በማለት ይመራመር ጀመር ። በማምት

አንድ መቶ የሚሆን እርምጃ ሄደው የአንዲት ገብታ አግድ መት ካለፉ በኋላ ለነሱ አስፈሪ ጉርምርምታ ሆኖ የተሰማቸው እና ሌሊቱን በሙሉ ሲያስጨንቃቸው ያደረው የዚህ አደንቋሪ ጩኸት ምክንያት በግልጥ ተከስተላቸው ። ይኸውም (አንባቢ ሆይ ቅር አይበልህና) በውሀ ኃይል የሚንቀሳቀሱ የስድስት ወፍጮ መጅት መፋጨት ስለሆነ እየተከታተለ በሚያስገመግመው ዣርዳፊ ድምፃቸው ያንን ጉርምርምታ ሲፈጥሩ መኪናውን የሚያንቀሳቅሰው ፏፏቴ ደግሞ ከየቋጥኙ ጋር እየተደራገመ ሲወ ርድ በጅውታው ስለሚያስተጋባው መሆኑን ያላንዳች ጥርጣሬ ለማመን ቻሉ ። ዶን ኪሾት ይህን ሁሉ አሸባሪ ጉርምርምታ ለመፍጠር ምክንያት የሆነውን ነገር ባወቀ ጊዜ አለመጠን የማ ፈሩ ብዛት ኩምሽሽ ብሎ ጨፍ አከለ ። ሳንቾም ጠጋ ብሎ ቢመ ለከተው እንደኳሽ ሰው አንገቱን ከደረቱ ላይ ደፍቶ አየው ። ዶን ኪሾትም በበኩሉ ቀና ብሎ ሳንቾን ቢመለከተው በጌታው ሁኔታ ተደንቆ በሳቅ ታፍኖ ኖሮ በተቻለው መጠን ሳቁን ለመ ግታት ሲል ጉንጩን አሳብጦ ከንፈሩን ነክሶ አይኑን እያቁለ ጨለጨ ለመፈንዳት ደርሶ አየው ። ዶን ኪሾት ይህን በማየቱ ምንም እንኳ በሐፍረት የተሸማቀቀ ቢሆን ከመሳቅ ለመታ ገድ ስላልቻለ አስቀድሞ መሳቅ ግዴታ ሆነበት ። ሳንቾም ጌታው በጀማሪነት መንገዱን በከፈተለት ጊዜ እሱም በቋፍ ነበርና እስ ቲንፈራፈር ድረስ ከት ብሎ ሳቀበት ። የመሳቁም ኃይል እን ዳያፈነዳው በመሥጋት በሁለት እጁ አንዴ ወገቡን አንዴ ጉል በቱን መመርከዝ ግዴታ ሆነበት ።። በዚህ አኳኋን አራት ጊዜ ያህል እየሳቀ አባርቶ እንደገና ደግሞ እያስታወሰ በመጀመሪ ያው ዓይነት አሳሳቅ ሲንከተከት ቆየ ። ዶን ኪሾት ይህ የሳንቾ አሳሳቅ የፌዝ መሆኑ ገብቶት ገና ከቅድሙ አንስቶ ተዶርሮ ነበርና ሳንቾ ጌታውን በማሽሚጠጥ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ከሣቁ ጋር እያቀላቀለ ሲናገር በሰማው ጊዜ ነገሩ ወደ መሣረር አዘነበለ ።

ይኸውም ባለፈው ጊዜ በጉራና በፉከራ የተናገረውን ቃል በማስታወስ «ወዳጄ ሳንቾ እኔ በእግዚአብሔር ፈቃድ በዚህ በብ ረት ዘመናችን ውስጥ የተወለድሁት ያንን የወርቁን ዘመን ለማ ስነሳት መሆኑን ማወቅ አለብህ ። የጀግንነት ተግባሮችና ታላ

ላቅ ግጥሚያዎች ፣ አስፈሪ አደጋዎች ሁሉ በተለይ ለኔ የተደ ገሱ ናቸው» እያለ ነበር ።

ይህንንና ሌላውንም ዶን ኪሾት ያንን አስደንጋጭ እና አደንቋሪ ጉርምርምታ በሰማበት በመጀመሪያው ጊዜ በፉከራ መንፈስ የተናገረውን ቃል እየመላለሰ ከሳቁ ጋር እያቀላቀለ በመ ተቸት አፈዘበት ። ዶን ኪሾትም ሳንቾ እንዳሳገጠበት በመገን ዘብ ገና ከቅድሙ አንስቶ ኩርፊያ ላይ ነበርና ።

ወዲያውኑ ባንድ አፍታ ግልፍ ስላለው በቁጣ እንደነደደ ቦሩን እነሳና በዛቢያው ወገን ሁለት ጊዜ ጀለጠው ። በትሩ ያረፈው በጀርባው ላይ መሆኑ ቀርቶ ለጥቂት አናቱን አማኝ ቶት በነበን ኖሮ እስካሁን ድረስ ያገለገለበትን ደመወዙን ለወ ራሾቹ ካልሆነ በስተቀር ለሱ ለመክፈል አይጨነቅም ነበር ። ሳንቾም ከዚህ ከሳቁና ከቀልዱ የለቀመው ፍሬ መራራ መሆኑን ቀምሶ ስለተረዳውና ወዲህም ድንጥ ሰው በመሆኑ ጌትዬው እንደገና የዱላውን መጠን እንዳያበዛበት በመፍራት እንዲህ ሲል በብዙ ትሕትና አነጋገረው ።

« ጌታዬ ሆይ ተዳፍሬ በመሳቁ አጥፍቻለሁና አይቆጡ ፣ ይተውት ተቀናጥቼ ለቀልድ ያህል የተናገርሁ መሆኔን ይመ ኑኝ » አለው ።

«እርግጥ ነው አንተ መቀለድህ ነበር እኔ ግን አልቀለድ ሁም» ሲል ዶን ኪሾት መለሰለትና ንግግሩን በመቀጠል «እኽ አቶ ቀልደኛው ፣ በል እስቲ ልጠይቅህና ንገረኝ? እነዚያ የታ ዩት የወፍጮ መጅዎች መሆናቸው ቀርቶ እውነተኛዎቹ አደ ገኛ አጋጣሚዎች ሆነው ቢገኙ ኖሮ አስፈላጊውን ድፍረት ለማ ሳየት እና ግጥሚያም አድርጌ ተግባሬን በድል አድራጊነት ለማ ከናወን ራቴን የምመልሰው ኑሬአለሁን? ወይስ ደግሞ ፈረሰኛ በመሆኔ ምክንያት ይህ የሚሰማው ድብልቅልቅ የመገርደፊያ ወፍጮ መጅ ወይም የፏፏቴ ጉርምርምታ ድምጽ መሆን አለ መሆኑን እንዳውቅ አገዶድ ኖሮአልን? መቸም በውነቱ እንደማስታ ውሰው በሕይወቴ እርዝማኔ ውስጥ አስከዛሬ ድረስ እንዲህ ያለ ነገር አጋጥሞኝ አይቸም ሰምቸም ስለማላውቅ እንግዳ ነገር እንደ

ሚሆንብኝ ግልጥ ነው ። እንዳንተ ያለ ቀፎ ስቃይ ባላገር ግን ይህን ከመሳሰለው መሣሪያ ጋር አብሮ ተወልዶ አብሮ ያደገ በመሆኑ በቶሎ ሊለየው ስለሚችል አንተም በድምጹ ለይተህ ልታውቀው እንደምትችል አምናለሁ ። ዳሩ ግን የሚሆንልህ ከሆነ በል እስቲ እነዚህ ስድስት የወፍጮ መጅቶ በስድስት ጠርብ ጃሞዛዎች ለውጣቸውና አንድ ባንድ ወይም ሁሉንም አን ነት እየነጋጋህ ገፍትረህ በላዩ ላይ ጣላቸውና ይግጠሙኝ ። በዚያን ጊዜ ሁሉንም ወደ አየር እያንገሁ ሳልፈነቸራቸው የቀ ረሁ እንደሆነ የፈለግኸውንና የመስለህን ያህል እያፈዝህ ብት ስቅብኝ በጭራሽ ቅር አይለኝም ።

«ጌታዬ ሆይ ! መቆጣቱ ይብቃዎት ለዛሬው ጥፋቴ ይቅ ርታ ያድርጉልኝ ። እኔም ተዳፍሬ በመሳቄ ለክቡርነትዎ መስ ጠት የሚገባኝን ያክብሮት ወሰን እንዳለፍኩት አውቄአለሁ ። መቼም ታርቀናልና እባክዎን አንዴ ይፍቀዱልኝና እኔም በፍ ጅታዬ አንድ ነገር ልጠይቅዎት» እግዚአብሔር በምህረቱ ክዚህ አደጋ ሰውሮ እንዳተረፍዎት ሁሉ እንዲሁም ለወደፊቱ ከሌ ሎች ገና ተከታትለው ከሚመጡት አደጋዎች ያትርፍዎትና ይህ የዛሬውአጋጣሚና እሱም ያሳደረብን ታላቅ ፍርሃት ይህ ነንም ስል በተለይ እኔን እጅግ አድርጎ ያስፈራኝን ነው እንጂ እርስዎ እንደሆኑ ፍርሃት የሚባለውን እንኳንስ እሱን እራሱን መኖሪያ ቤቱ የት እንደሆነ ስለማያውቁት ነገሩን ሲመለ ከቱት የሚያስቅና ሊወራም የሚገባው አይመስልዎትምን? ሲል ጠየቀው ።

ዶን ኪሾትም መለሰ ፣ « ይህ የደረሰብን ነገር የሚያስቅ መሆኑን አልክድም ፣ ዳሩ ግን ሊወራ የሚገባው አይደለም ። ምክንያቱም ወሬውን ከሚሰሙት ሰዎች መካከል ሁኔታውን ከትክክለኛው መስመር ሳያዛንፉ በቀጥታ ለማስተላለፍ የሚ ችሉ ሐቀኞች ጥቂቶች ከመሆናቸው የተነሳ አንዳንዶቹ ወሬ ያዳ መቂ እየመሰላቸው የስሙትን ካልሰሙት ጋር እያዳቀሉና እያ ቀጣጠሉ ከውነተኛው ድርጊት አዘልለው ሌላ ትርጓሚና ፍቺ በመስጠት ታሪክ ጸሐፊዎችን ስሜን ወደሚያሰብር ስህተት ላይ እንዲደርሱ ያደርጓቸዋልና ለሰው አውራው ብዬ በፍጹም አልፈ ቅድልህም» አለው ።

ሳንቾም እንዲህ አለ ፣ «ክቡርነትዎ የጦርዎን ዛቢያ ለአ ናቴ አልመው ትከሻዬ ላይ በማሳረፍዎ ከትክክለኛው መስመር ሳይወጡ ስለቀሩ በሐቀኝነትዎ አመሰግንዎታለሁ ፣ እንዲሁም ለእግዚአብሔርና ለእኔም በፍጥነት ዘወር ብዬ አደጋው ማም ሳጥን ለአወቅሁት ምስጋና ይግባንና እንደርስዎ ዒላማ ቢሆን ኖሮ እስካሁን ድረስ ሌላ መኖሪያ ቦታ ለውጬ ነበር ። የሆነው ሆኖ የማያልፍ ነገር የለምና ይህን የዛሬውን ድርጊት « የሚ ያስቅና የማይወራ» ብለን ያስከተልነውን ጠንቅ በትዕግሥት እን ለፈው ። ከዚህም በስተቀር የዱሮ ሽማግሌዎች ሲተርቱ እንደ ሰማሁት « የማይወዱትን ሰው አይቆጡትም » ያሉት በመደ ብደቤ ሆድ እንዳይብሰኝ ያጽናናኛል ። ይህም ሆኖ ጥንት ታላ ላቆቹ ጌቶች በሚቆጡበት ጊዜ አንድ የስድብ ቃል አምልጧ ቸው አሽከሮቻቸውን የተሳደቡ እንደሆነ ቆየት ብለው ሙሉ ልብስ ካሣ ይክሏቸዋል ። ዳሩ ግን በዱላ ከተደባደቡ በኋላ ምን እንደሚከሱ አላውቅም ። ለኔ እንደሚመስለኝ ግን ዘዋሪ ፈረ ሰኞች ጋሻ ጃግሬአቸውን ከደበደቡ በኋላ ካሣውን አንድ ደሴት ወይም በረጋ መሬት ላይ የሚገኝ የተንጣለለ ሠፊ ግዛት ሳይ ሰጡዋቸው እንደማይቀሩ አምናለሁ » አለ ።

«ይህ ሊሆን የሚችል ነው » አለ ዶን ኪሾት ይህን አሁን ያልከውን ካሣ የምታገኝበት ጊዜ ላንተም የሚርቅ አይደለም ። አሁን ግን ለጊዜው ማናቸውንም የደረሰውን ሁኔታ እርሳውና እለፈው ። ግሳጼዬንም በትእግሥት በመቀበልህ አስተዋይ ሰው መሆንክን መዝኘዋለሁ ። አንተም እንደምትገነዘበው ሰው ሆኖ የተፈጠረ ሁሉ ከደም ፍላት የወጣውን ግልፍታ በመጀመ ሪያው ላይ ለመዳኘት ስለማይችል በአፍላው ጊዜ ከፊቴ ተገ ኝተህ በመመታትህ አትዘንብኝ፣ ዳሩ ግን ከዛሬ አንስተህ ወደ ፊት ከኔ ጋር እኩል ከመነጋገር እንድትቆጠብ በተቻለህ መጠን ተመከር ። እኔ ካነበብኳቸው ከብዙዎቹ የፈረሰኛነት ታሪክ መጻሕ ፍት ውስጥ እንዲህ እንዳንተ በሙሉ ስድነት ከጌታው ጋር የሚከ ራከርና ከእፍ የሚናጠቅ ጋሻ ጃግሬ መኖሩን የሚያሰረዳ ምዕራፍ አላገኘሁበትም ። እውነቴን ስነግርህ እስከዚህ ድረስ ባለጌ ለመሆን የበቃኸው ባንተና በኔ ጥፋት ነው ። ያንተ ጥፋት ነው ያል ኩህ የሚገባኝን ያህል በደንብ ስለማታከብረኝ ነው ። የኔ ጥፋት

ነው የምለው ደግሞ ይበልጥ እንድትአከብረኝ አድርጌ ስላላ ስለጠንኩህ ነው ። ስለዚህም ጉዳይ ምናልባት ሊገባህ ይችል እንደሆነ ሁለት ምሳሌዎች ጠቅሼ ላስረዳህ እፈቅዳለሁ ። ባለ ፈው ዘመን ጋላዲኖ የሚባለው የጋውላው አማዲስ ጋሻ ጃግሬ በአገልግሎቱ መልካምነትና በሰው አክባሪነቱ የፊርሜ ደሴት መስፍን ሆኖ ነበር ። ስለርሱም የትሕትና ጠባይ ታሪክ እንደ ሚመሰክርለት ከጌታው ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ዘወትር ባር ኔጣውን አውርዶ በእጁ ይዘ እንደቱርከችና ዓረቦች የመከባበር ፈሊጥ ከደረቱ ጐንበስ ብሎ አንገቱን ደፋ አድርጐ ጌታው የሚ ነግረውን ያዳምጥ እንደነበር ተጽፏል ። ጋስባል የሚባለው የዶን ጋላዎር ጋሻ ጃጋሬ ደግሞ በጣም ዝምተኛ ከመሆኑ የተነሳ ይህ እጅግ አስደናቂ የሆነ ዝምታው እምን ወሰን እንደደረሰ ሃሳብ ለመስጠት ያህል በዚያ በተጻፈው እውነተኛና ሰፊ ታሪክ ውስጥ እሱ ከጌታው ጋር ሲነጋገር የተሰማው አንድ ጊዜ ብቻ መሆ ኑን ስትረዳው ያንተ ለፍላፊነት ባለመቶ ምላስ መሆንክን የሚ መስክር አይደለምን ? ስለዚህ በዚህ በሰጠሁህ ማስረጃ አስገን ዛቢነት እራስህን በራስህ ታገዝበህ ፣ በፈረሰኛና በጋሻ ጃግሬ በጌታና በአሽከር ፣ በገርና በጓባር መካከል የተራራቀ ልዩነት መኖሩን አውቀህ ጠባይህን ለማረም መጣጣር አለብህ ። ሁለ ታችንም ከእንግዲህ ወዲያ ልጓማችንን ስናላላ በበለጠ መከባበ ርና አንጋፋነት መተያየት ይገባናል ። ምክንያቱም ባንተ የም ናደድበት ስበብ ማናቸውም ዓይነት ቢሆን «የሸክላ ድስት ዘወ ትር በሥጋት » እንደሚባለው ነውና ተጠንቀቅ ። ተስፋ ያደረ ግህልህ ወሮታና ችሮታ ጊዜው ሲደርስ እንደምፈጽምልህ እመነኝ ። ምናልባት ጊዜው ርቆ ቢዘገይ እንኳ አስቀድሜ እን ደነገርኩህ ደመወዝህ እንደማይቀርብህ እርግጠኛ ሁን ።

«ክቡርነትዎ የነገሩኝ ሁሉ መልካም ነው» ሲል መለሰ ሳንቾ « ዳሩ ግን ለማወቅ የምፈልገው ምናልባት የተስፋው መፈጸሚያ ጊዜ እንዳሉት ዘግይቶ ደመወዜን በማግኘት ብቻ የምወሰን የሆንኩ እንደሆነ በዱሮው ዘመን የዙዋሪ ፈረሰኛ ጋሻ ጃግሬ በወር ደመወዝተኛነት ወይም ደግሞ እንደቀን ሠራተኛ በቀን አገልግሎት ሂሣብ ምን ያህል ደመወዝ ይከፈለው ኖሯል ?

«እኔ እንደማውቀው» ሲል መለሰ ዶን ኪሾት «የዱሮዎቹ ጋሻ ጃግሬዎች ስለአገልግሎታቸው ዋጋ ወሮታ ይከፈላቸዋል እንጂ የተወሰነ ደመወዝ ተቆርጦላቸው በወር ወይም በቀን የሚ ከፈላቸው አይመስለኝም ። እኔ በኑዛዜው ወረቀት ላይ በደመ ወዝ ስም ድርሻህን ለይቼ በማህተሜ አጽድቄ እቤት የተው ኩበት ምክንያት ምናልባት ካንድ ቀን አንድ ቀን ሊደርስብኝ በሚችለው ድንገተኛ አደጋ የሞትኩ እንደሆነ ያንተ አገልግ ሎት ያለ ዋጋ እንዳይቀር ለመጠንቀቅ ስል ነው ። ይህንንም ጥንቃቄ እንዳደርግ ያሳሰበኝ በዚህ አደገኛ በሆነው ዘመናችን ውስጥ ዙዋሪ ፈረሰኞችን ምን ዓይነት ዕድል ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ደህና አድርጌ ባለማወቄ የተነሳ በዚህ በጥቂት ነገር ነፍሴ በሌላው ዓለም በዕዳ እንድትጠየቅ ስለማልፈቅድ ነው ። ውድ ሳንቾ ! በነዚህ በሁለቱ ዓለሞች ላይ ዙዋሪ ፈረሰኞች ከሚጠየቁበት የበለጠ አደገኛ ግዳጅ እንደማይገኝ ልታውቀው ይገባሃል » አለው ።

«ይህ የተረጋገጠ እውነት ነው » አለ ሳንቾ « የመገርደፊያ ወፍጮ መጀች ጉርምርምታ እንኳ ክቡርነትዎን የመሰለ የጀግና ዙዋሪ ፈረሰኛ ልብ ለማናወጥና ለማመሳቀል ሲችል ዕድሜያ ችሁ ሁሉ ከአደጋ ጋር የተቆራኘ መሆኑን ለማስረዳት ይሽው ብቻ በቂ ነው ። የሆነው ሆኖ ከእንግዲህ ወዲህ የክቡርነትዎን ክብር በሚነካ በማናቸውም ጥፋት ላይ እንደማልወድቅ ፣ በመ ቀለድም ስሜት አንዳች ነገር እንደማልተነፍስ ፣ ብተነፍስም እንኳ አንድ ጌታ ሊከበር በሚገባው መንፈስ ብቻ መሆኑን ። አረጋግጥልዎታለሁ» አለው ።

«በዚህ መንፈስ ከተመራህ » ሲል መለሰ ዶን ኪሾት «ከወ ላጆች ቀጥለው የሚከበሩት ጌቶች ስለሆኑ ከነሱ በምትቀበለው ምርቃንና ቡራኬ ዕድሜህ ረዝሞ በደስታና በተድላ ትኖራለህ» አለው ።

ምስጋና

ከተረጉምኩ በኋላ የእንግሊዝኛውን ሐረግና የአማርኛውን አሰካክ ገጽ በገጽ ያለአንዳች ድካም የተመለከተልኝን ጓድ ታደሰ ወልዴን አመሰግናለሁ ።

ኣ. ተ. ወ. መ.

ከታደሰ ወልዴ

ስለመጽሐፉ ትርጉም የተሰጠ አስተያየት

ልዩ ግንዛቤ በሚል ከላይ የተገለፀው በትክክል ከሰርቫንቲስ መጽሐፍ መቅድም ከሳሙኤል ፑትናም በቀጥታ የተተረጐመ ነው ። ይህንኑ ትርጉም አቶ አስፋው ተፈራ (ተርጓሚው) ምናልባት ታማኝ ሁኜ ተርጉሜ እንደሆነ ወይም የአገር አነጋገር ፈሊጥ ዘልዬ እንደሆነ በማለት በሐምሌ 1975 ካለው የሥነጽሑፍ ሥራ ውስጥ ይህን የዶን ኪሾትን የመጀመሪያ ክፍል መጽሐፍ እንግሊዝኛውንና የአማርኛውን ትርጉም ሰጠኝ ። የትርጉሙን ትክክለኛነት ለመመልከት ማመሳሰሉ ብዙ ጊዜ ከፈጀብኝ በኋላ ተርጓሚውን እኔ ግር ባሉኝ ሐረጐች አተረጓጐም ላይ ተወያየን ። በትርጉሙ አሠራር የተርጓሚው ስሜት ሳይነካ ለማረም በመጋበዜ እጅግ ተደስቻለሁ ።

ይህም አጋጣሚ የዚህን የታላቅ ደራሲ ጽሑፍ አንድ በአንድ አረፍተ ነገሮችን ጭምር እንድመለከት ስለገፋፋኝ ታሪኩ ይበልጥ እንዲገባኝና እንድ መረምረው አድርጐኛል ።

ይህ ጽሑፍ በታወቁት የዓለም ቋንቋዎች የተተረጐመና በሥነ ጽሑፍም ትምህርት ላቅ ብለው የሚገኙ ምሁራን ሳያነቡትና ሳያደንቁት የሰርቫንቲስን አስተሳሰብ ከየዘመናቸው ግንዛቤ ጋር ሳያመዛዝኑ የቀሩ ሊኖሩ አይችሉም ፤ ለዚህ ያልታደሉት የሥነ ጽሑፍን ክምር ሳያስተውሉ ያለፉ ብቻ ናቸው ። በተለይ በእስፔን የታላቅነት ዘመንና አውሮፓም በታላቅነቷ ባረጀችበት ዘመን የሰርቫንቲስ ሥራ በመወለዱ ያንን ዘመን ታላቁ ሰርቫንቲስ ቁልጭ አድርጐ አቅርቦታል ።

ሰርቫንቲስም በአስፔይን እውነተኛ ልጅዋ አድርጋ በየኒቨርስቲዎችዋና በተለይም የቀድሞ ግዛቶችዋ የነበሩት የብዙ የላቲን አሜሪካ የሥነ ጽሑፍ ተቋሞች የሰርቫንቲስን ሥራ በመጀመሪያ ደረጃ ያስቀምጡታል ።

በዚህ ለሞን ሃገራችንን የጐበኘው የታላቁ የሞስኮ ባልቮይ ቴያትር የባሌ ቡድንም የዚህን ታላቅ ጸሐፊ ሥራ የሚገልጽ አንድ የባሌ ውዝዋዜ ማቅረቡ የሰርቫንቲስን ሥራ ተደናቂነትና ተወዳጅነት ያረጋግጥልናል ።

የሰው ልጅ ከቀድሞው ዘመን ሰዎች አለመማሩ ነገም ተነገወዲያም ሥራ ምቾቹ ያልተሠሩ እየመሰለው ጀግሬነት ማብዛቱ የብረት ብስኪሌት መሠራቱን ያላወቀ የእንጨት ብስኪሌት እንደሚሠራው የዋህ ዓይነት ነውና ከዶን ኪሾት ብዙ እንማራለን ።

አቶ አስፋው ተፈራ ዶን ኪሾትን ለአማርኛ አንባቢዎች አቅርቦአል ። በዚህ ሳይገታ ክፍል ሁለትንም ቢነካ እጅህ አንለዋለን ።

ዋጋው

ብር 3.25